የሁሉም አገር ሠርቶ አደሮች ተባበሩ !

ማርክሳዊ ሌኒናዊ
ፖለቲካ ኢኮኖሚ

# የካፒታሊስት ስልተ ምርት

ክፍል 2

በኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ ርዕዮተ ዓለም መምሪያ
ለውይይት ክበባት ተዘጋጅቶ የቀረበ

ጥቅምት [illegible]

ማርክሳዊ ሌኒናዊ
ፖለቲካ ኢኮኖሚ

# የካፒታሊስት ስልተ ምርት

proudly brought to you by
www.biyamhk.wordpress.com

ክፍል

በኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ ርዕዮተዓለም መምሪያ
ለውይይት ክበቦች ተዘጋጅቶ የቀረበ

የካቲት 1974

የሁሉም አገር ሠርቶ አደሮች ተባበሩ !

ማርክሳዊ ሌኒናዊ
ፖለቲካ ኢኮኖሚ

# የካፒታሊስት ስልተ ምርት

proudly brought to you by
www.biyamhk.wordpress.com

ል 2


በኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ ርዕዮተዓለም መምሪያ
ለውይይት ክበቦች ተዘጋጅቶ የቀረበ

የካቲት 1974

ቅጽ 16–22–02/74

# ማ ሳ ሰ ቢ ያ

ይህን ጽሑፍ የአከባቢ የኢሠፓአኮን አካል በማስፈቀድ ለግል ወይም ለወል አገልግሎት በማባዛት የተወሰነ ቅጂ ወይም ግልባጭ ለማግኘት ይቻላል። ይሁንና በከፈልም ሆነ በሙሉ፣ በሆነው መንገድ ወይም ዘዴ አባዝቶ፣ አራብቶ ወይም አሳትሞ ለመሸጥ ወይም ለመለወጥ ፍፁም የተከለከለ ነው።



# ማውጫ

ገጽ


መግቢያ........................................ 1

ምዕራፍ 1፤ የሸቀጥ ልውውጥና እሴት

1. የሸቀጥ ምርት........................ 8
2. ሸቀጥና ባሕርይው........................ 16
3. ተጨባጭና ረቂቅ ሥራ........................ 28
4. ግላዊና ማኅበራዊ ሥራ........................ 31
5. በሸቀጥ ውስጥ ያለው የእሴት መጠን መለኪያ.. 34
6. ቀላል ሥራና ውስብስብ ሥራ........................ 35

ጥያቄዎች........................ 36

ቃላት........................ 37

ምዕራፍ 2፤ ገንዘብና የእሴት ሕግ

1. የልውውጥ ዕድገትና ልዩ ልዩ የእሴት መልኮች........................ 39
2. የገንዘብ ተግባራት........................ 47
3. የወረቀት ገንዘብ........................ 60
4. የእሴት ሕግ፡— የሸቀጥ ምርት የኢኮኖሚ ሕግ........................ 62
5. ሸቀጥ አምላኪነት........................ 67

ጥያቄዎች........................ 71

ቃላት........................ 72

ገጽ

ምዕራፍ 3፤ ካፒታልና ትረፊ እሴት

1. የካፒታል ትርጓሜ................ 73
2. የካፒታል አመጣጥ................ 78
3. የገንዘብ ወደ ካፒታል መለወጥና የሥራ ኃይል ወደ ሸቀጥነት መቀየር........... 82
4. ትረፊ እሴት የመፍጠር ሂደት........... 95
5. የትረፊ እሴት ሕግ፤ የካፒታሊዝም መሠረታዊ የኢኮኖሚ ሕግ................. 103
6. የካፒታል ዓይነቶች................ 104
7. በካፒታሊስቱ ሥርዓት በርካታው የወዝአደሩን የሥራ ኃይል ብዝበዛ የሚያባብሱ ገባቸው ስልቶች................... 107
8. በካፒታሊስት ሥርዓት ሙደብ አሰባሰፍ.... 108
አበጻ..................... 114
ጥያቄዎች................... 119
ቃላት..................... 120

ምዕራፍ 4፤ ምንዳና የወዝአደሩ ትግል

1. ትርጓሜና አመጣጥ................ 121
2. ሥራና የሥራ ኃይል................ 124
3. በካፒታሊስት ሥርዓት የምንዳ ልዩ ገጽታ... 130
4. የምንዳ ዓይነቶች................ 132
5. የነጭ ላብ ምንዳ................ 136
6. የይበመጣ/አፍአዊ/ እና አውነተኛ ምንዳ... 140
ጥያቄዎች................... 147
ቃላት..................... 148

ገጽ

ምዕራፍ 5፡ የካፒታል ክምችትና የወዝአደሩ ጭቆና

1. የካፒታል ርባታ.................... 150
2. የካፒታሊስት ክምችት ሂደትና የሥራ አጡ ሠራዊት.................... 163
3. የካፒታል ክምችት አጠቃላይ ሕግ........ 169
4. የካፒታሊስት ስልተምርት መሠረታዊ ቅራኔዎች.................... 173

ጥያቄዎች.................... 179

ቃላት.................... 180

ምዕራፍ 6፡ የካፒታልና የተረፈ እሴት ልዩ ልዩ መልኮች፤ የማኅበራዊ ካፒታል ርባታና የኢኮኖሚ ቀውሶች

1. የካፒታልና የተረፈ እሴት ልዩ ልዩ መልኮች 181
2. በካፒታሊስት ሥርዓት ውስጥ የማኅበራዊ ምርት ርባታና የኢኮኖሚ ቀውሶች....... 203

ጥያቄዎች.................... 217

ቃላት.................... 219

ምዕራፍ 7፡ ሞኖፖል ካፒታል—የኢምፔሪያሊዝም ኢኮኖሚያዊ መሠረት

1. የኢንዱስትሪ አነባበ.................... 220
2. የሞኖፖል ካፒታሊዝም አመጣጥና አሠራር.... 224

ጥያቄዎች.................... 250

ቃላት.................... 251

ምዕራፍ 8፡ በታሪክ የኢምፔሪያሊዝም ሥፍራ

1. ሦስቱ ጠምራ የኢምፔሪያሊዝም ባሕርያት.... 252
2. በኢኮኖሚ ገጽታው የኢምፔሪያሊዝምአራት መሠረታዊ መለያዎች.................... 253

ገጽ


3. መንግሥታዊ ሞኖፖሊ ካፒታሊዝም.......... 272

4. በዘመነ ኢምፔሪያሊዝም በካፒታሊስት አገሮች ያልተስተካከለ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ዕድገት ሕግና በአንድ አገር ሶሻሊዝም በድል አድራጊነት ሊወጣ ስለመቻሉ............... 278

5. የካፒታሊዝም አጠቃላይ ቀውስ............ 282

ጥያቄዎች...................... 300

ቃላት........................ 302

የሚነበቡ መጻሕፍት.................. 303

# መግቢያ

"ካፒታል" ቅጽ 1 የመጀመሪያው የጀርመንኛ እትም እ.አ.አ በ1867 ሲወጣ ካርል ማርክስ በመጽሐፉ ዓይነተኛ ዓላማ የዘመኑን ሕብረተሰብ ማለትም የካፒታሊስቱን ሕብረተሰብ የሚገዙትን ህግጋት አሰራር ግልጥልጥ አድርጎ ማሣየት እንደሆነ በመጽሐፉ መቅድም ውስጥ አብስሯል:: በሦስት ትልልቅ ቅጾችና በሺ በሚቆጠሩ ገጾች የተንጣለለው "ካፒታል" የማርክስ ዋነኛ ሣይንሣዊ ሥራ የአያሌ ዓመታት /እንዲያውም የዕድሜ ልክ ለማለት ይቻላል/ የጥናትና የምርምር ውጤት ነው::

ኢሠፓአኮ ያልተለወሰና ያልተበረዘ የማሌን ሣይንስ ለኢትዮጵያ ሠርቶ አደር ሕዝብ ለማስታጠቅ ባለበት ታሪካዊ ኃላፊነት ተዘጋጅቶ የቀረበው ይህ ክፍል ሁለት የማሌ ፖለቲካ ኢኮኖሚ ማስተማሪያ ጥራዝ በታላቁ የወዝአደር ፈላስፋና መሪ በካርል ማርክስ ስራ ላይ የተመሠረተ ነው:: በማርክስ ሣይንሣዊ ትንተና ይፋ በሆኑት የካፒታሊስት ስልተምርት ህግጋት ላይ ይመሰረት እንጂ ይህ አጭርና የመጀመሪያ ዝግጅት እንደመሆኑ የቡርዧውን ሥርዓት የሚገዙትን የኢኮኖሚ ህግጋት በሙሉ አጠቃላይና ጠለቅ ባለ ሁኔታ ለማቅረብ አይሞክርም:: የመጀመሪያ ዝግጅት እንደመሆኑ ወደፊት ሊሻሻልና ሊጠናከር የሚችል ነው::

ይሁን እንጂ ይህ የመወያያ ዝግጅት የማሌን የካፒታሊስት ፖለቲካ ኢኮኖሚ አበይት ህግጋት አሰራር አጠርና ቀለል አድርጎ ለማቅረብ ይሞክራል:: እርግጥ የማቅለሉም ሆነ የማሳጠሩ ተግባር ውስን ነው፤ ሊከናወን የሚችለው እስከ ተወሰነ ደረጃ ድረስ እንጂ የምንፈልገውንና የምንመኘውን ያህል ሊሆን አይችልም፤ ለዚህ አያሌ ምክንያቶች ቢኖሩ የሕብረተሰባችን የዕድገትና የግንዛቤ ደረጃ ዝቅተኛነት፤ የቋንቋችን አለመዳበርና እንደዚሁም የልምዳችን እጥረትና ጥበት አጠቃላዮቹ ይሆናሉ::

ካፒታሊዝም ፊውዳሊዝምን ሸር የመጣና በምርት መገልገያዎች የግል ባለቤትነትና በቅጥር ሥራ ብዝበዛ ላይ የተመሠረተ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሥርዓት ነው:: የካፒታሊዝም ዋና መለያ ጠባዮች የምርት መገልገያዎች በግል ባለቤትነት መያዝ ብቻ ባይሆን በኢኮኖሚ ውስጥ የሸቀጥ–ገንዘብ ግንኙነት የበላይነት ማግኘት፣ ማኅበራዊ የሥራ ክፍፍል መዳበር፣ የምርት ማኅበራዊነት ማደግ፣ ሁለንተናዊ በሆነ መንገዱ የሥራ ኃይል ወደ ሸቀጥነት መለወጥና የወዝአደሩ መደብ በካፒታሊስቱ መደብ መበዝበዝ ናቸው:: የካፒታሊስት ምርት ዓላማ የወዝአደሩን የሥራ ኃይል በመበዝበዝ ተረፈ እሴት ማስገኘት ነው::

በብዝበዛ ላይ የተመሠረተው የካፒታሊስቱ አመራረት የካፒታሊስቱ የምርት ግንኙነት አጠቃላይ ገጽታ እየሆነ ሲሄድና በአንፃሩም ቀደሙ ካፒታሊስት የነበረው ላዕላይ መዋቅር ማለትም ፖለቲካ፣ ህግ፣ ርዕዮተዓለምና ሌሎችም ማኅበራዊ ተቋሞች በቡርዧው ላዕላይ መዋቅር ሲተኩ፣ ካፒታሊዝም ስልተ ምርቱንና ላዕላይ መዋቅሩን ያቀናጀ ሥርዓተ ማኅበር ይሆናል::

ካፒታሊዝም በሦስት የዕድገት ደረጃዎችን አልፏል:: እነዚህም ቀላል የካፒታሊስት የሕብረት አሠራር፣ አፈብራኪ እና የፋብሪካ ወይም የማሽን ምርት ደረጃዎች ናቸው:: ቀላል የካፒታሊስት የሕብረት አሠራር የተባለው በአውሮፓ ውስጥ በተለይም በኔዘርላንድስና በእንግሊዝ ከአሥራ ስድስተኛው ምዕተ ዓመት ጀምሮ መከናወን የጀመረ ሲሆን፣ በአንድ ካፒታሊስት ቁጥጥር በተለያዩ ቦታዎች በዛ ያሉ ሰዎች የተለያዩ የምርት ሥራዎችን የሚያከናውኑበት ሂደት ነው:: ይህ ዓይነት የአመራረት ዘይቤ የካፒታሊስት አመራረት ሀ ሁ የጀመረበት ነው:: በዚህ ወቅት ለመጀመሪያዎቹ ካፒታሊስቶች የርካሽ ሥራ ምንጭ ሆኗቸው የነበረው ይህ ሂደት በንብረት ይዞታ ላይ ባስከተለው ለውጥ እየከሰሩ የመጡት ብዛት ያላቸው የዕደ ጥበብ አምራቶችና ገበሬዎች ነበሩ::

የቴክኖሎጂ ዕድገት በአጠቃላይ የምርት ኃይሎች ዕድገት በተለይም በ16ኛው ምዕተ ዓመት አጋማሽ ላይ ቀላል የካፒታሊስት የህብረት ሥራ ወደ አፈብራኪ ደረጃ እንዲሸጋገር ረዳ:: በዚህ ደረጃ ቀደም ሲል በተለያዩ ሥፍራ ተነጣጥለው ሸቀጥ ያመርቱ የነበሩት በአንድ ቦታ ተሰብስበው እንዲያመርቱ ተደረጉ:: በዚህ ሁኔታ የሸቀጥ ምርት እየተስፋፋ ሄደ:: ይሁንና ወደ 18ኛው ምዕተ ዓመት አጋማሽ ላይ በአንዳንድ የአውሮፓ ካፒታሊስት አገሮች የካፒታሊዝም የወደፊት ዕድገት በወቅቱ ከነበረው የካፒታሊዝም የአፈብራኪ የዕድገት ደረጃና ከዚህ ደረጃ ቴክኒካዊ መሠረት ጋር ሊጣጣም አልቻለም:: ስለዚህም የካፒታሊስት የሸቀጥ ምርት ከአፈብራኪ ደረጃ ወደ ፋብሪካ ወይም የማሽን አመራረት ዘይቤ ማደግ አስፈላጊ ሆነ:: ይህም ሽግግር በ18ኛው ምዕተ ዓመት አጋማሽ ላይ በተጀመረው በኢንዱስትሪ አብዮት አማካይነት ተከናወነ::

የፋብሪካ ወይም የማሽን የአመራረት ዘይቤ መከሰት ለካፒታሊዝም ማቴሪያላዊና ቴክኒካዊ መሠረት በመጣል የካፒታሊዝም በልቱምርት የበላይነት እንዲጎናፀፍ አስቻለው:: የማሽን አመራረት የተስፋፋበት ደረጃ ላይ ከመድረሱ በፊት ወደዚህም ደረጃ ለመድረስ ካፒታሊዝም የመጀመሪያ ደረጃ የካፒታል ክምችትን ማከናወን ነበረበት:: የመጀመሪያ ደረጃ የካፒታል ክምችት በይዞታ አነስተኛ አምራቾች በብዛት ከምርት መገልገያ ባለቤትነታቸው የተነጠሉበትና የሥራ ኃይላቸውን ለካፒታሊስቶች ለመሸጥ የተገደዱበት፣ በሌላ በኩል ሀብት በጥቂቶች እጅ የተከማቸበት ሂደት ነው:: በተጨማሪም ቅኝ ግዛቶችን መበዝበዝ ለካፒታሊዝም ዕድገት ተፈላጊውን የካፒታል ክምችት ለማስገኘት አስተዋጽኦ አድርጓል::

በዚህ ሂደት ውስጥ የሥራ ኃይል ወደ ሸቀጥነት መለወጥና ከምርት መገልገያዎች ጋር መቀናጀት አነስተኛ የሸቀጥ ምርት በካፒታሊስት የሸቀጥ ምርት መተካትን አስከተለ:: ካፒታሊዝም በዳበረባቸው ሀገሮች ሁሉ መሠረታዊ የሆኑት

የካፒታሊዝም የዕድገት ሕግጋት ተመሳሳዮች ሲሆኑ፣ በእያንዳንዱ የካፒታሊስት አገር የካፒታሊስት ስልተምርት አጀማመር እንደየአገሩ ታሪካዊና ተጨባጭ ሁኔታ የተለያየ ነው—ማለትም ክላሲካል የሆነው የካፒታሊስት የሕብረት ሥራ፣ አፈተሬክ፣ የፋብሪካ ወይም የማሽን ምርት፡፡ በዚህ ሂደት የተከናወነው በእንግሊዝ አገር ሲሆን፣ በሌሎች የካፒታሊስት አገሮች የካፒታሊዝም ዕድገት የተለያዩ ገጽታዎች ነበሩት፡፡

ካፒታሊዝም በሁለት ወቅቶች የተከፈለ ነው፤ ይኸውም ዝቅተኛው የነፃ ውድድር ወቅት ሲሆን ከፍተኛው ደግሞ የሞኖፖል ካፒታሊዝም /የኢምፔሪያሊዝም/ ወቅት ነው፡፡ የመጀመሪያው ወቅት ከ16ኛው ምዕተ ዓመት እስከ 19ኛው ምዕተ ዓመት መጨረሻ ገደማ የቆየ ሲሆን ሁለተኛውና ከፍተኛው የካፒታሊዝም የዕድገት ደረጃ የሆነው ኢምፔሪያሊዝም ደግሞ ከ19ኛው ምዕተ ዓመት መጨረሻ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ ያለ ነው፡፡ ኢምፔሪያሊዝም ከካፒታሊዝም የነፃ ውድድር ደረጃ ቀስ በቀስ ያደገ ነው፡፡ በነፃ ውድድር ወቅት በካፒታሊስቶች መካከል ያለው ውድድር ሣይነበና ቴክኖሎጂ እንዲያድግ፣ ካፒታል እንዲማከልና እንዲሰበሰብ በማድረጉ፣ ይህ ሂደት ሞኖፖሎች እንዲፈጠሩ አደረገ፡፡ ሞኖፖል ካፒታሊዝም የፋይናንስ ካፒታልና የዚህ ባለቤት የሆነው የፋይናንስ መሣፍንት የበላይነት የበፈነበት ወቅት ነው፡፡

ኢምፔሪያሊዝም አሁን በደረሰበት ደረጃ የመንግሥታዊ ሞኖፖል ካፒታሊዝምን ቅርጽ እየያዘ መጥቷል፡፡ መንግሥታዊ ሞኖፖል ካፒታሊዝም የፋይናንስ መሣፍንት ከቡርዧው መንግሥታዊ ቢሮክራሲ ከፍተኛው ክፍል ጋር በጥብቅ የሚተሳሰርበትና የሚዋሃደበት ሁኔታ የተፈጠረበት ነው፡፡

ካፒታሊዝም ፊውዳሊዝምን በመገርሰስ የዳበረ ሥርዓተ ማኅበር እንደመሆኑ በወቅቱ የተራማጅ ሚና ተጫውቶ ነበር፡፡ ቀደም ካፒታሊስት የኢኮኖሚ ግንኙነቶችን

ሊሆን የሚችለው ደግሞ ሠፊው ሠርቶ አደር ሕዝብ ሲያጠናው፣ ሲያውቀው በደንብ ሲረዳውና ሲገነዘበው፣ ይህንንም በዕለት ተዕለት ተግባሩና ሕይወቱ ሲያረጋግጠው ነው፡፡

ሰፊው ሠርቶ አደር ሕዝብ የማሌን ሣይንስ እንዴት እንደሚያጠና የመጀመሪያው የፖለቲካ ኢኮኖሚ ጥራዝ ተዘጋጅቶ በወጣበት ወቅት በኢሠፓአኮ የተሰጠ የአጠናን መመሪያ ለሠፊው ሕዝብ ተገልጿል፡፡ መመሪያው አጠቃላይ የማሌን የአጠናን ዘዴዎችን ከተጨባጭ ሁኔታዎች ግምገማ ጋር ያዛመደ በለሆነ አያንዳንዱ የውይይት ክበብና አያንዳንዱ ግለሰብ ተግባራዊ እንዲያደርገው ያስፈልጋል፡፡ የማሌን ሳይንስ መልክና ዕቀዱ ባለው መንገድ ለመጨበጥ ጠቃሚነቱ የማያጠያይቅ ነው፡፡ በመሆኑም በመግቢያው ላይ ወደ መጀመሪያ ገደማ እንደተጠቀሰው የዚህ ውይይት ጽሑፍ ዓላማ አበይትና ወቅታዊነት ያላቸውን የካፒታሊስት በልዥምርት የኢኮኖሚ ህግጋት ጠቅለልና ቀለል አድርጎ ለሠርቶ አደሩ ሕዝብ ለማስጨበጥ በለሆነ ሣይንሣዊ በሆነ የአጠናን ዘዴ በመጠቀም ግቡን እንዲመታ ማድረግ ከሁላችንና ከአያንዳንዳችን የሚጠበቅ አብዮታዊ ተግባር ነው፡፡※

ኢሠፓአኮ

# ምዕራፍ 1

## የሸቀጥ ልዉዉጥና እሴት

### 1. የሸቀጥ ምርት፣

ካርል ማርክስ "ካፒታል" በሚባለዉ ዝነኛ መጽሐፉ፣ በመጀመሪያዉ
ምዕራፍ በመጀመሪያዉ አረፍተ ነገር እንዳመለከተዉ የካፒታሊስት ስልተምርት የበ
ፊነባቸዉ ኅብረተሰቦች ሀብት የሚንፀባረቀዉ ወደር በሌለዉ የሸቀጥ ክምችት ነዉ።
ወደፊት በዝርዝር እንደሚገለጸዉም ካፒታሊዝም የምርት ዉጤቶችን ብቻ ሣይሆን የሰ
ዉን የስራ ኃይል ራሱን ወደ ሸቀጥነት በመለወጥ እንደማናቸዉም ዕቃ በገበያ ላይ
እንዲሸጥና እንዲለወጥ የሚያደርግ ሥርዓት ነዉ። ስለዚህ ለካፒታሊስት ሥርዓት
መስፈን መንበዪ የሆኑትን ሁኔታዎችና ምክንያቶች፣ የዕድገቱን ሕግጋትና እንደዚ
ሁም ለሥርዓቱ መክሰም መሠረት የሆኑትን ቅራኔዎች ለመረዳት የሚደረገዉ ትንተና
የዚህ ሥርዓት ማኅበር ዓይነተኛ መገለጫና መለያ በሆነዉ በሸቀጥ ምርት ባ[illegible]ይ
መጀመሩ ተገቢ ነዉ።

ሰዉ በማኅበረሰብ ተሰባስቦ ማምረት ሲጀምር የነበረዉ ኢኮኖሚ
ተፈጥሮአዊ ኢኮኖሚ ይባላል። ይህም ኢኮኖሚ እያንዳንዱ አምራች ክፍል
ለሕልዉናዉ የሚያስፈልጉትን ነገሮች ሁሉ በራሱ የሚያመርትበት፣ የሥራዉም
ዉጤት ለፍጆታዉ ብቻ የሚዉልበትና ልዉዉጥ ያልዳበረበት ኢኮኖሚ ነዉ። በሌላ
አነጋገር ተፈጥሮአዊ ኢኮኖሚ ማለት እያንዳንዱ አምራች ክፍል ለምርቱ ክን
ዉኔ የሚያስፈልጉትን ጥሬ ዕቃዎች ከማሰባሰብ እንስቶ የማምረቻ መሣሪያዎች
ንና ሌሎችም የምርት መገልገያዎችን ሁሉ በራሱ የሚያመርትበት፣ የምርት ዉጤ
ቱም ለዚያዉ አምራች ክፍል ጥቅም ብቻ የሚዉልበት ኢኮኖሚ ነዉ። ማኅበረሰብ

በዚህ ዕድገት ደረጃ ላይ በነበረበት ዘመናቹ የምርት ኃይሎች ዕድገት እጅግ ዝቅተኛ በመሆኑ እያንዳንዱ አምራች ክፍል የሚያመርተው ምርት መጠን ከራሱ ፍጆታ ተርፎ ለገበያና ለልውውጥ የሚውል አልነበረም:: ስለሆነም የምርት ክንዋኔው መሠረታዊ ዓላማ በተቻለ መጠን የአምራቹን ክፍል ፍጆታ /ፍላጎት/ ለማሟላት ብቻ ነበር:: ባጭሩ ተፈጥሮአዊ ኢኮኖሚ ዛሬ እንደምናውቀው ዓይነት ኢኮኖሚ አንዱ አምራች ክፍል ለምሳሌ የቡና አምራቶችን ብንወስድ የምግብ እህሎች፣ የማምረቻ መሣሪያዎች፣ ልብስ፣ ጫማ፣ የቤት ቁሳቁሶች ወዘተ... የመሳሰሉትን ፍላጎቶችን ከሌሎች የተለያዩ አምራች ክፍሎች በገበያ አማካኝነት በመሸጥና በመግዛት የሚያሟላ ሣይሆን ማናቸውም ለሕልውናው የሚያስፈልጉትን ነገሮች ሁሉ በራሱ የሚያመርትና ለራሱ ፍጆታ ብቻ የሚያውልበት ኢኮኖሚ ነው:: በዚህ ዓይነት ለገበያና ለልውውጥ ሣይሆን የራሱን ፍላጎት ብቻ ለማርካት የሚመረት ነገር ምርት ይባላል:: ይህም ወደፊት እንደምናየው ከሸቀጥ ምርት በጣም የተለየ ነው::

ከምርት ኃይሎች ዕድገት ጋር ሰዎች ከራሳቸው ፍላጎት በላይ ማምረት ሲጀምሩ የምርት ልውውጥ ተከሰተ፣ ይህም የምርትና የልውውጥ ተግባር እየተስፋፋ በመሄዱ ቀስ በቀስ ተፈጥሮአዊ ኢኮኖሚ እየተዳከመ የሸቀጥ ምርት ኢኮኖሚ በቦታው እየተተካ ሊመጣ ችሏል:: የሸቀጥ ምርት ማለትም እንደ ተፈጥሮአዊ ኢኮኖሚ የምርቱ ውጤት ለአምራቹ ክፍል ፍጆታ ብቻ ሣይሆን በገበያ አማካኝነት ለሚካሄድ ልውውጥ ማለትም ለሽያጭ ታስቦ የሚመረትበት ኢኮኖሚ ወይም የምርት ተግባር ነው::

የሸቀጥ ምርት በአንድ ኅብረተሰብ ኢኮኖሚ ውስጥ በአንድ ጊዜ በሙሉ ተግባራዊነት ያገኘ ሣይሆን ቀስ በቀስ እየዳበረ የመጣ፣ ረጅም ጊዜ የወሰደ የለውጥ ሂደት ነው:: በኅብረተሰብ ዕድገት ታሪክ ውስጥ የሸቀጥ ምርት መስፈን የሁለት መሠረታዊ ሁኔታዎችን መሟላት የሚጠይቅ ነው:: ከነዚህ ሁኔታዎች ውስጥ

አንደኛው የማኅበራዊ የሥራ ክፍፍል መስፋፋት ነው። የማኅበራዊ የሥራ ክፍፍል መከሰት የማናቸውም የኅብረተሰብ ቀደምት የኢኮኖሚ ተግባር የሆነው የአርሻ ሥራ መሻሻልንና ተረፈ ምርት የሚያስገኝበት ዕድገት ደረጃ ላይ መድረስን ይጠይቃል። አርሻ ተረፈ ምርት ከሚያስገኝበት የዕድገት ደረጃ ላይ ካልደረሰ ከአርሻ ውጪ የሚተዳደሩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ሊኖሩ ስለማይችሉ የሥራ ክፍፍልና ልውውጥም ሊከሰት አይችልም። ስለዚህ የማኅበራዊ የሥራ ክፍፍል መከሰት የኅብረተሰቡ አምራች ክፍሎች በተለያዩ ሥራዎች ወይም ሙያዎች መሠማራትን ያስከትላል።

በዚህ መሠረት በታሪክ ውስጥ የተከሰተው ሁለተኛው ማኅበራዊ የሥራ ክፍፍል ኅብረተሰቡን በግብርናና በዕደ ጥበብ የለየው ነው። ይህም ማኅበራዊ የሥራ ክፍፍል አራሾች በጥራጥሬ፣ በቅባትና በሌሎችም የእህል ዓይነቶች፣ የዕደ ጥበብ ባለሙያዎች ደግሞ በሽማ፣ በሸክላ፣ በእንጨትና በብረት ሥራዎች ማለትም በግብርና ለተሰማራው ክፍል የሚያስፈልጉትን የምርት ማከናወኛዎችና የቤት ቁሳቁሶች በማምረት ተግባሮች እንዲሠማሩ አስችሏል። በእያንዳንዱ የሥራ ዘርፍ የተሰማራው ክፍል የሚያመርተው የምርት ውጤት የራሱን ፍላጎት ብቻ ለማርካት አይደለም። ሊሆንም አይችልም። በግብርና የሚተዳደረው ክፍል የግብርናው ሥራ የሚጠይቀውን እንደሞፈር፣ ቀንበር፣ ወገል፣ ማረሻ ወዘተ... የመሳሰሉትን የማምረቻ መሣሪያዎችና እንዲሁም የተሟላ ሕይወትም ለመኖር የሚያስፈልጉትን እንደ ድስት፣ ወንበር፣ ጠረጴዛ፣ ሸማ ወዘተ... የመሳሰሉትን ቁሳቁሶች ከዕደ ጥበብ ባለሙያው ማግኘት አለበት። በተመሳሳይ መልክ የዕደ ጥበብ ባለሙያውም ለሥራው ክንዋኔ ጥጥ፣ እንጨት ወዘተ...እና ለሕልውናው የሚያስፈልጉትን ነገሮች ለምሳሌ እህል፣ሥጋ...በግብርናው ዘርፍ ከተሰማራው ክፍል ማግኘት ይኖርበታል። በዚህ መልክ በተዋቀረ ኢኮኖሚ ውስጥ እያንዳንዱ አምራች ክፍል ለምርቱ ውጤት መገኘትና ለሕልውናው የሚያስፈልጉትን የፍጆታ እቃዎች ለማሟላት በሌሎች አምራቾች ላይ የሚተማመን ይሆናል። ይህ በተለያዩ የሥራ ዘርፎች በተሰማሩት አምራቾች መካከል ለምርትና ለፍጆታ የሚካሄደው የዕቃዎች ልውውጥ ለሸቀጥ ምርት መስፋፋትና መስፈን መሠረት ሆኗል።

ስለዚህ ለሸቀጥ ምርት ማደግ መሟላት ካለባቸው አስፈላጊ ሁኔታዎች መካከል አንዱ የማኅበራዊ የሥራ ክፍፍል መከሰትና መዳበር ነው።

በኅብረተሰቡ ዕድገት ውስጥ ማኅበራዊ የሥራ ክፍፍል መከሰት ብቻ የሸቀጥ ምርትን ለመጀመርና ለማዳበር አያበቃም። ለሸቀጥ ምርት መጀመርና ማደግ መሟላት ያለበት ሌላው አስፈላጊ ሁኔታ የምርት መገልገያዎች በግል መያዝ ነው። እንዲያውም ለሸቀጥ ምርት መዳበር ዋነኛው ምክንያት የግል ይዞታ መስፋፋት ነው ለማለት ይቻላል። አንዱ ሰው ከፍጆታው በላይ ቢያመርትም ተራፊውን ምርት ሊሸጥ የሚችለው ምርቱን ለማምረት የተገለገለባቸው የምርት መገልገያዎችና የምርት ውጤቶም ባለቤት ቢሆን ብቻ ነው። ይህ ሁኔታ በኢኮኖሚው ሥርዓት ውስጥ ካልተሟላ ገዥም ሊያገኝ አይችልም። ከግ ለሰብ ምሳሌ ቢሻገር ሁኔታውን በሥርዓተ ማኅበሮች የምርት ግንኙነት ባሕር ይም አንጻር ማነባትና ማየት ይቻላል።

እንደሚታወቀው በጥንታዊ የጋርዮሽ ሥርዓተ ማኅበር ውስጥ በግ ርድፍ መልክም ቢሆን የሥራ ክፍፍል ነበር። ሆኖም የአንዱ ቀበሌ ወይም መንደር አባሎች የሚያመርቷቸውን የተለያዩ ምርቶች የሚለዋወጡት በሽያጭ መልክ አልነበረም። የምርት መገልገያዎች የቀበሌው አባሎች የወል ሀብት በመሆናቸው በመካከላቸው የሥራ ክፍፍል ቢኖርም የሥራቸውን ውጤት የሚከፋ ፈሉት በአኩልነት በመሆኑ የሸቀጥ ምርትና የሸቀጥ ልውውጥ ሊከሰት አልቻ ለም። እርግጥ አንዱ ቀበሌ ከሌላው ቀበሌ ጋር የዕቃዎች ልውውጥ ቢያደ ርግ ልውውጡ የይዞታ ለውጥን ያስከትላል። በመሆኑም በቀበሌዎች መካከል የሚደረገው የዕቃዎች ልውውጥ የሸቀጥ ምርትን ባሕርይ የያዘ ነበር። ይህም ቢሆን ኅብረተሰብ በዚህ ዕድገት ደረጃ ላይ በነበረበት ጊዜያት ይህንን ያህል የዳበረ አልነበረም።

ባጭሩ የሸቀጥ ምርት መከሰት መሠረት የማኅበራዊ የሥራ ክፍፍል መዳበርና የምርት መገልገያዎች በግል መያዝ ነው። ባንዱ ሁኔታ መሟላት

ብቻ የሸቀጥ ምርት ሊያድግ ወይንም ሊዳብር አይችልም። ስለሆነም የሸቀጥ ምርትና በሽያጭና በግዥ መልክ የሚካሄደው የዕቃዎች ለውጥ ሲከሰትና እየዳበረም ሊሄድ የሚችለው እነዚህ ሁለት ሁኔታዎች ሲሟሉ ብቻ ነው።

በኅብረተሰብ ዕድገት ታሪክ ውስጥ እቃዎችን በግዥና በሽያጭ መልክ ለማካሄድ ለውጥ የማምረቱ ሂደት የተከሰተው ጥንታዊው የጋርዮሽ ሥርዓተ ማኅበር መፈራረስ ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ ነው። በመሆኑም የሸቀጥ ምርት በባሪያ አሳዳሪውና በፊውዳሉ ስልተ ምርቶችም ውስጥ የነበረና ያለም ክስተት ነው። ስለዚህ የሸቀጥ ምርት ከካፒታሊስት ሥርዓተ ማኅበር መስፈንም በፊት ረጅም ዕድሜና ታሪክ ያለው ክስተት ነው። ይሁን እንጂ በቅድመ ካፒታሊስት ሥርዓተ ማኅበሮች ውስጥ የሚካሄደው የሸቀጥ ምርት በካፒታሊስት ሥርዓተ ማኅበር ውስጥ ካለው የሸቀጥ ምርት በባሕርይው የተለየ ነው።

በቅድመ ካፒታሊስት ሥርዓተ ማኅበሮች ውስጥ የሚካሄደው የሸቀጥ ምርት ተግባር ቀላል ወይም ዝቅተኛ የሸቀጥ ምርት በመባል የሚታወቀው ነው። ይህም ቀላል የሸቀጥ ምርት ቀደም ሲል በገለጽነው በገበሬውና በዕደ ጥበብ ባለሙያው መካከል የሚካሄደውን ዓይነት የምርትና የእቃዎች ለውጥ የሚያመለክት ነው። የቀላል ሸቀጥ ምርት ዓይነተኛ ባሕርይ በዝቅተኛ የግል ይዞታና በራስና በቤተሰብ ጉልበት ላይ የተመሠረተ መሆኑ ነው። ይህንን የምርት ባሕርይ ለመገንዘብ የአንዱ ኢትዮጵያዊ የእደ ጥበብ ባለሙያና የአንዱ ገበሬ የአመራረት ዘይቤ በምሳሌነት ማስተዋል በቂ ይሆናል። ለምሳሌ የእደ ጥበብ ባለሙያው ሸማኔ ወይም ብረት ሠሪ /ቀጥቃጭ የሚባለው/ ነው እንበል። ሸማኔውን ብንወስድ የማምረቻ መሣሪያው ባለቤት ነው። በምርቱ ሂደት ውስጥ መከናወን ያለባቸውን ልዩ ልዩ ተግባሮች የሚያከናውነው በአመዛኙ ራሱ ቢሆን ሚስቱና ልጆቹም ይሳተፋሉ። ምንዳ እየከፈለ ቀጥሮ የሚያሠራው ሠራተኛ አይኖረውም። የሚያመርተው ምርት ውጤት ግን ለገበያ ወይም ለሽያጭ ታስቦ የሚሠራ ነው። የብረት ሠሪውም ሁኔታ ተመሳሳይ ነው። የገበሬውን ሁኔታ ስን

ባለሙያው በአመዛኙ የሚተማመነው በራሱ ጉልበት ቢሆን ቤተሰቡም በማምረት ሂደት ውስጥ ተሳትፎ አላቸው። በሁለቱም ረገድ የምንገነዘበው መሠረታዊ ነገር የምርት መገልገያዎቻቸው ባለቤት ቢሆኑም የምርት ውጤታቸው የራሳቸውና የቤተሰባቸው የሥራ ኃይል ውጤት ብቻ መሆኑን ነው። ስለዚህ በቀላል የሸቀጥ ምርት ሂደት ውስጥ የሰው በሰው መበዝበዝ አይኖርም። እያንዳንዱ አምራች የሥራው ውጤት ባለቤት ነው።

ቀላል የሸቀጥ ምርት በቀድሞ ካፒታሊስት ሥርዓተ ማኅበሮች ብቻ ሳይሆን በካፒታሊዝምና ከዚያም አልፎ ወደ ሶሻሊዝም በሚደረገው የሽግግር ወቅትም ውስጥ ሕልውናው ይቀጥላል። ይህንን ከማናቸውም አገሮች የኢኮኖሚ ዕድገት ሂደት መገንዘብ ይቻላል። በዛሬው የአገራችን ኢኮኖሚም ውስጥ ቢሆን ቀላል የሸቀጥ ምርት ይዞታ ይገኛል። በአገራችን የኢኮኖሚ ሕይወት ውስጥ በሚያስተዳድረው ሕዝብ ብዛትም ሆነ ለአጠቃላይ የሀገሪቱ ኢኮኖሚ በሚያደርገው የምርት አስተዋጽኦ ከፍተኛ ሥፍራ የሚይዘው የአነስተኛ ሸቀጥ ምርት ይዞታ ነው። በዚህ የኢኮኖሚ ይዞታ ውስጥ የሚጠቃለሉት ገበሬዎች፣ ዕደ ጥበብ ባለሙያዎችና አነስተኛ ነጋዴዎች ናቸው።

በዚህ ዓይነት ቀላሉ የሸቀጥ ምርት በሽግግሩ ወቅት የሚኖር ቢሆንም በየትኛውም ሥርዓተ ማኅበር ውስጥ የኅብረተሰብ ዕድገትን የሚመራና የሚወስን ስልተ ምርት አይሆንም። በባሪያ አሳዳሪውና በፊውዳሉ ስልተ ምርቶችም ውስጥ ዋነኛው ክፍል ለገበያ የሚመረተው ባይሆን ለባሪያ አሳዳሪውና ለፊውዳሉ በጉልበትና በዓይነት/በምርት/ ፈሰስ የሚደረገው ምርት ነው። በተመሳሳይ መልክ በካፒታሊስት ሥርዓተ ማኅበርና እንዲሁም ሶሻሊዝምን ለመገንባት በሚኖረው የሽግግር ወቅት ውስጥ ያለውን ኢኮኖሚ ሁኔታም

ብንመለከት ቀላል የሸቀጥ ምርት ክፍል የኢኮኖሚውን ዕድገት የሚመራ ኃይል
አይደለም። አሁንም የአገራችንን ኢኮኖሚ በዓማሊነት ብንጠቅስ ኢኮኖሚው
የተለያዩ ክፍሎችን የያዘና ከፍተኛው የአነበተኛ ሸቀጥ ምርት ይዞቱ ቢሆ
ንም የሀገሪቷን ዕድገት የሚመራውና ወሣኙ ክፍል ግን የሶሻሊስቱ ኢኮኖሚ
ክፍል ነው።

ቀላል የሸቀጥ ምርት ይዞታ በየትኛውም ሥርዓተ ማኅበር ውስጥ
የነኛውን ሥፍራ ማለትም የኅብረተሰብን የኢኮኖሚ ዕድገት የመምራት ኃይል ሊና
ረው የማይችለው ለማደግ የሚያደርገው ትግል የበለጠ የሚያቆረቁዘውና ሕልው
ናውንም የሚያከስመው በመሆኑ ነው። በዚህ መሠረት የፊውዳሉ ሥርዓተ ማኅ
በር መፈራረስ በጀመረበት ወቅት ቀላል የሸቀጥ ምርት ይዞታ ለከፍተኛው
የሸቀጥ ምርት ዕድገት መሠረት ሆኗል። በቀላል የሸቀጥ ምርት ላይ የተመ
ሠረተው የካፒታሊስቱ የሸቀጥ ምርትም የሥርዓተ ማኅበሩ ዕድገት የነኛ አው
ታር በመሆን የመሸጥና የመግዛት መርህ በየትኛውም የኢኮኖሚ ዘርፍ እንዲስ
ፋን ያደርጋል።

ቀላል የሸቀጥ ምርትና የካፒታሊስት የሸቀጥ ምርት በምርት መገ
ልገያዎች የግል ይዞታ ላይ የተመሠረቱ በመሆናቸው ተመሳሳይነት ቢኖራቸውም
በመካከላቸው መሠረታዊ ልዩነት መኖሩንም መገንዘብ ያስፈልጋል። ቀላል የሸ
ቀጥ ምርት ቀደም ሲል እንደተመለከትነው በአምራቹ የግል የሥራ ኃይልና የም
ርት መገልገያዎች የግል ባለቤትነት ላይ የተመሠረተ ነው። የካፒታሊስት
የሸቀጥ ምርት ግን ከዚህ በጣም የተለየ ነው። የካፒታሊስት ሸቀጥ ምርት
በምንዳ በሚቀጠሩ ሠራተኞች ሥራ ኃይል ብዝበዛ ላይ የተመሠረተ ነው።

በቀላልና በካፒታሊስት ሸቀጥ ምርት መካከል ያለው አንዱና መሠረታዊው ልዩነት ይህ ነው። በካፒታሊስት ሸቀጥ ምርት ውስጥ ሠራተኛው ከምርት መገልገያዎች ባለቤትነት ወርቦ ስለሚለቀቀ የምርት መገልገያዎችና የሠራተኛውን ሥራ ለማቀናጀት የሠራተኛውን የሥራ ኃይል በገበያ መሸጥና መግዛት አስፈላጊ ይሆናል። ከዚህ እንደምንገነዘበው በካፒታሊስት ሥርዓት ውስጥ ወደ ሸቀጥነት የሚለወጠው የሠራተኛው የሥራ ውጤት ብቻ ሣይሆን የሥራ ኃይሉም ጭምር ነው። ስለሆነም በካፒታሊስት ሥርዓት ውስጥ የሰው የሥራ ኃይል እንደማንኛውም ሸቀጥ በገበያ ውስጥ የሚሸጥና የሚለወጥ ነው።

በባሪያ አሣዳሪውና በፊውዳሉ ሥርዓተ ማኅበሮች ውስጥ የሸቀጥ ምርት የኢኮኖሚውን ዕድገት እንደማይመራ ቀደም ብሎ ተገልጿል። በካፒታሊስት ሥርዓተ ማኅበር ግን የሸቀጥ ምርት የኢኮኖሚ ዕድገት መሠረት ወይም ሕግ ስለሚሆን ማናቸውም ምርት ወይም የሥራ ውጤት የሸቀጥነት መልክ በመያዝ ለሽያጭ የሚቀርብ ይሆናል። በቀላል የሸቀጥ ምርት ውስጥ የልውውጥ ዓላማ የአምራቾችን መሠረታዊ ፍላጎት ለማርካት ሲሆን፣ የካፒታሊስት የሸቀጥ ምርት ግን ትርፍን ለማካበት ነው። በቀላል የምርት ሸቀጥ ሂደት ውስጥ የሥራ ውጤት የአምራቹ የግል ሀብት ሲሆን በካፒታሊስት ምርት ሂደት ውስጥ የአምራቹ የሥራ ውጤት ለካፒታሊስቱ ጥቅም የሚውል ነው።

ሁለቱ የአመራረት ዘይቤዎች የሚለዩባቸውን ባህርያት ከፍ ብሎ ለመጥቀስ ሞክሯል። ይሁንና ከዚሁም በተጨማሪ የካፒታሊስት ሥርዓትን ባሕርይበሚገባ ለመገንዘብ የሸቀጥ ምርትን ባሕርያት በጥልቀት መመርመሩ አስፈላጊ ነው።

## 2. ሸቀጥና ባሕርይው:

ለግል ፍጆታ ባይሆን የሰዎችን የተለያዩ ፍላጎት ለማርካት ለሽያጭ የሚውልና የሰዎች የሥራ ውጤት የሆነ ምርት ሁሉ ሸቀጥ ይባላል። ለምሳሌ አንዱ የጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ ባለቤት የሆነ ካፒታሊስት ብዙ የተለያዩ ልብሶች እንዲመረት ያደርጋል። ግን የተመረቀውን/የተሠራውን/ ጨርቅ ሁሉ ለራሱ ይጠቀምበታል ማለት አይደለም። ወይም ደግሞ አንዱ የቆዳ ፋብሪካ ያለው ካፒታሊስት በብዙ ሺ የሚቆጠር የከብት ቆዳ ለጫማ፣ ለቀበቶ፣ ለቦርሳ፣ ወዘተ... ሥራ እንዲያገለግል አድርጎ ያዘጋጃል። ግን ይህን ሁሉ ቦርሳ፣ ጫማ፣ ቀበቶ፣ ወዘተ...ለራሱ አይጠቀምበትም። ካፒታሊስቶች በድርጅቶቻቸው ውስጥ የሚመረቱትን ነገሮች ሁሉ ለራሳቸው ፍጆታ አይጠቀሙባቸውም። ስለዚህ በካፒታሊስት ድርጅቶች ውስጥ የሚመረቱ ማናቸውም ዓይነት ምርቶች ሁሉ የሚመረቱት ለሽያጭ፣ ለገበያ ነው።

ለሽያጭ፣ ለገበያ የሚመረት ማንኛውም ሸቀጥ ሲመረት የሰው የሥራ ኃይል እንዲፈስበት ያስፈልጋል። ምንም ዓይነት ምርት/ሸቀጥ/ ያለ ሰው የሥራ ኃይል ሊገኝ አይችልም። የሰው የሥራ ኃይል ከፈሰሰበት ደግሞ ጠቀሜታ ሊኖረው ይገባል። ምክንያቱም ጠቀሜታ ለሌለው ነገር ማንም ሰው የሥራ ኃይሉን በከንቱ አያፈስበትም። ስለዚህ የሚመረተው ሸቀጥ ሁሉ ጠቀሜታ እንዲኖረው ያስፈልጋል። ጠቀሜታ ስንል የአንዱ ሸቀጥ የሰዎችን ፍላጎት የማርካት ባህርይ ማለታችን ነው። የአንዱ ሸቀጥ የሰውን ፍላጎት የማርካት ጠባዩ የጠቀሜታ እሴት ይባላል። ይህ ጠባይ ሸቀጥ ካሉት ሁለት ባህርያት አንዱ ነው። የጠቀሜታ እሴት የሌለው ሸቀጥ ሊመረት አይችልም።

የአንዱ ሸቀጥ የሰውን ፍላጐት የማርካት ጠባይ ወይም ጠቀሜታው እንዴት ነው የሚታየው? ለምሳሌ አንዱን ሰዓት እንውሰድ፣ የሰዓቱ ጠቀሜታ የሚገለጸው ጊዜውን ወይም ሰዓቱን ስንት ሰዓት እንደሆነ ሲያሳየን ነው። የአንዱ የጽሕፈት መኪና ጠቀሜታ የሚታየው ስንጽፍበት በሚሰጠን ግልጋሎት ነው። የአንዱ የብረት ማረሻ ጠቀሜታ የሚታየው እቤት ውስጥ በመቀመጡ ባይሆን አርሻን ስናርስ መሬቱን ሲሰነጥቅልን ነው። አንዱ አዝራር /ቁልፍ/ እንውሰድ፣ ጠቀሜታው የሚታየው ባሉት ቀዳዳዎች ወይም በመልኩ ባይሆን ከትን፣ ሸሚዝን፣ ወይም ሱሪን በመቆለፍ በሚሰጠው ግልጋሎት ነው። በምሳሌ የጠቀስናቸው ሰዓት፣ የጽሕፈት መኪና፣ ማረሻና ቁልፍ የጠቀሜታ እሴት አላቸው ማለት ነው። በዚህ ዓይነት ብዙ ምሳሌዎች ማቅረብ ይቻላል። ከዚህ እንደምንረዳው የአንዱን ነገር የጠቀሜታ እሴት የምንገነዘበው በንገለገልበት ማለትም በፍጆታ ሂደት ውስጥ ነው።

የጠቀሜታ እሴት የሰውን ፍላጐት ለማርካት ከሚውልበት አኳያ በሁለት መሠረታዊ ክፍሎች ይከፈላል፡—

1. የፍጆታ ዕቃዎች፣ እነዚህ ማናቸውንም የሰዎችን ፍላጐት በቀጥታ ለማርካት የሚጠቀሙ ነገሮችን የሚያጠቃልሉ ሲሆን ይህም ለሰው ልጆች ሕልውና በጣም መሠረታዊ የሆኑ ባንዱ ጊዜ ተበልተው የሚያልቁ እንደ ምግብ ሸቀጥ፣ ለጥቂት ጊዜ የሚያገለግሉ እንደ ልብስ፣ ጫማ፣ እንደ ቤት ዕቃ ወንበር፣ ጠረጴዛ፣ ብርጭቆ፣ ማንኪያ፣ ያሉ አሉ። በሰው ዕድሜ ደረጃና ከዚያም ይበልጥ የሚያገለግሉ እንደመጠለያ፣ የሰውን መንፈሳዊ ፍላጐት ማርኪያ የሆኑ መጻሕፍት፣ ጋዜጣ፣ መጽሔት፣ ቴያትር፣ ፊልም፣ ወዘተ... ለደሉትና ለቀንጦት

ወይም የሰውን ውበት ለመጨመር የሚፈለጉ በጥቂት ጊዜ የሚበላሹ ወይም ለረጅም ጊዜ የሚያገለግሉ እንደ ሽቶ፣ ወርቅ፣ እንቁ፣ ቅባት ያሉ ናቸው:: እነዚህ ባጠቃላይ ለራስ ፍጆታ የሚውሉ እንጂ ሌላ አዲስ ነገርን ወይም እቃን ለማስገኘት የሚውሉ አይደሉም::

2. <u>የምርት መገልገያዎች፤</u> እነዚህ ሲለበሱ፣ ሲበሉ፣ ሲጠጡ፣ መጠለያ ሲሆኑ ሊገጥባቸው የማይችሉ ነገሮች ናቸው:: እንዲህ በለ ተብሎም፣ ለሰው ልጅ ግልጋሎት አይሰጡም ማለት አይደለም:: እንዲያውም ግልጋሎታቸው እጅግ ከፍተኛ ነው:: በቀጥታ የሰውን ፍላጎት ለማርካት የምንጠቀምባቸው ባይሆኑ፣ በተዘዋዋሪ መልክ የሰውን ፍላጎት ለማርካት የሚያስፈልጉትን ነገሮች ለማምረት የሚያገለግሉ ናቸው ማለታችን ነው:: ለምሳሌ ማረሻን እንውሰድ:: አናገጥበትም፣ መጠለያ አይሆነንም፣ አይበላም ወይም አይጠጣም:: ስለዚህ በቀጥታ ለፍጆታ የሚውል አይደለም:: ግን መሬቱን በማረስ/በመሰንጠቅ/ እህል ዘርቶ እንዲበቅል መሬቱን አመቺ ለማድረግ ይረዳል:: ከመሬቱ የሚገኘው ሰብል ሌላም ዓይነት ሥራ በሌሎች መሣሪያዎች አማካኝነት ተከሂደበት በኋላ በቀጥታ ለፍጆታ እንዲጠቀሙበት ይሆናል::

አንድ የዘይት መጭመቂያ ሞተርን እንመልከት:: በማረሻው እንደተመለከትነው ሁሉ በቀጥታ ለፍጆታ የምንጠቀምበት አይደለም:: ግን በውስጡ የቅባት እህል ገብቶ ተፈጭቶ፣ ተጨምቆ ዘይት እንዲወጣና ዘይቱ በቀጥታ ለፍጆታ እንዲውል ያደርጋል:: ከዚህ ባሻገርም የምርት መገልገያዎች ሌላ የምርት መገልገያ ያመርታሉ:: ለተለያዩ የወርቃ ወርቀ ፋብሪካ የሚውሉ መሣሪያዎችንና ማሽኖችን፣ የእርሻ መኪናዎችን ወይም የዘይት መጭመቂያዎችን፣ ወዘተ... የሚያወጡ ትልልቅ የሆኑ ማሽኖች አሉ:: ባጠቃላይ ከትንሽ እስከትልቅ የሰዎችን ፍላጎት ለማርካት የሚያስፈልጉትን ነገሮች ለማምረት የምንጠቀምባቸው የማምረቻ መሣሪያዎች፣ ጥሬ ዕቃዎች፣ የማምረቻ ሕንጻዎች፣ ወዘተ... በእዚህ ውስጥ የሚጠቃለሉ ናቸው::

የሰው ልጅ መሠረታዊ ፍላጎቱን ለማርካት የሚጠቀምባቸው ነገሮች በብዛትም በዓይነትም አንድ ጊዜ የተገኙ አይደሉም:: እንደ ኅብረተሰብ ዕድገት አብረው የሚያድጉና የጠቀሜታ እቢታቸውም እየጨመረ የሚሄድ ነው:: መጀመሪያ የሰው ልጅ የሚጠቀምባቸው ነገሮች የተወሰኑ ነበሩ:: ቆመጥ፣ ቢላ አንወት፣ ድቡልቡል ድንጋይና ባልጩት የመጀመሪያዎቹ መገልገያ መሣሪያዎች ነበሩ:: በኋላ በብረት መሣሪያ ተተክተዋል:: እንዲያም ቢል ከተለያዩ ማዕድናት የሚሠሩ መሣሪያዎች ተፈልስፈዋል:: ባጠቃላይ ከቴክኖሎጂ ዕድገት ጋር የሰውን ፍላጎት ለማርካት የሚፈለሰፉትና የሚሠሩት ዕቃዎች እየበዙ ሲሄዱ የጠቀሜታ እቢትም እንዲሁ ዓይነቱ እየበዛ ይሄዳል:: አንድ ዓይነት መሣሪያም/ ነገር/ የተለያዩ ጠቀሜታዎች

ይኖሩታል፡፡ ለምሣሌ፡— የከብት ቆዳን እንውሰድ፡፡ ለመኝታ፣ ለቀበቶ፣ ለቦርሳ፣ ለጫማ፣ ለልብስ፣ እንደገና ፀጉሩ ደግሞ ለተለያዩ ሥራዎች ይውላል፡፡ ቀንዱንም እንውሰድ፣ ለዱላ፣ ለቢላዋና ለጎራዴ እጀታ፣ ለቀንጫ፣ ለማንኪያ ለመሳሰሉት ሥራ ጠቀሜታ አለው፡፡ የነዚህ ነገሮች ጠቀሜታ ባንድ ጊዜ የተከሠተ አይደለም፡፡ ስለዚህ የጠቀሜታ እሴት ከሕብረተሰብ ዕድገትና ፍላጎት ጋር እየዳበረ የሚሄድ ታሪካዊ ሂደት ያለው ነው፡፡ የማንኛውም ነገር የሰውን ፍላጎት የማርካት ባህርይ ከማናቸውም ሥርዓተ ማኅበር ጋር የተያያዘ ባለመሆኑ የጠቀሜታ እሴት በማናቸውም የሕብረተሰብ የዕድገት ደረጃ ላይ የሚኖር ዘላለማዊነት ወይም ዘላቂነት ያለው ፈርጅ ነው፡፡

ጠቀሜታ እሴት ስንል ሁልጊዜ በሰው የሥራ ኃይል ብቻ የሚገኝ ሸቀጥ ወይም ነገር ብቻ እንዳልሆነ መገንዘብ አለብን፡፡ ለምሣሌ አንድ የተፈጥሮ የውሃ ምንጭ የሰው የሥራ ኃይል ሳይፈስበት ሊገኝ ይችላል፡፡ የምንተነፍሰው አየር፣ የምንሞቀው የፀሐይ ብርሃን፣ ከዱር ወፍ ዘራሽ ሆነው የምናገኛቸው ልዩ ልዩ የዱር ፍራፍሬዎች፣ የሰው የሥራ ኃይል አይፈስባቸውም፡፡ ግን የጠቀሜታ እሴት አላቸው፡፡ ስለዚህ የጠቀሜታ እሴት በሁለት መንገድ ይገኛል ማለት ነው፡፡ ይህም ሰዎች አንዱን ሸቀጥ ለማምረት የሥራ ኃይላቸውን በማፍሰስ የሚያስገኙትና በተፈጥሮ የሚገኘው ማለት ነው፡፡

ቀደም ሲል እንደተመለከትነው አንድ ሰው አንዱን ነገር አምርቶ ለራሱ ፍጆታ ከአዋለው የአመረተው ነገር ሸቀጥ አይደለም፡፡ ማናቸውም ምርት ሸቀጥ የሚሆነው ማኅበራዊ ፍላጎትን ለማርካት ሲሸጥና ሲለወጥ ነው፡፡

የሸቀጥ ምርት በሰፈነበት የኢኮኖሚ ሥርዓት ሁሉ አንድ ዓይነት የጠቀሜታ እሴት ከአለው ሸቀጥ ሌላ ዓይነት የጠቀሜታ እሴት ካለው ሸቀጥ ጋር መለዋወጡ ግዴታ ነው፡፡ ልውውጡም የማያቋርጥ ሂደት ነው፡፡ እንዲህ ስንል አንድ ዕቃ የተወሰነ የልውጥ ደረጃ ከሄደ በኋላ ለፍጆታ አይውልም ወይም ደግሞ ልውውጡን አያቋርጥም ማለታችን

አይደለም:: ለምሳሌ፣ አንድ ካኪ ጨቅ ከዋናው አምራች ፋብሪካ ወደ ጅምላ ነጋዴ፣
ከጅምላ ነጋዴ ወደ ቸርቻሪ ነጋዴ፣ ከቸርቻሪ ነጋዴ ወደ ተጠቃሚው ሕዝብ ድርስ
ዝርፍቶ ስለሚለበስ ልውውጡ በለበሰነቱ ያበቃል:: በዚህ ዓይነት ብዙ ነገሮች
መጥቀስ ይቻላል:: እንግዲህ ልውውጥ የማያቋርጥ ሂደት ነው ሆኖም አዲስ ለየተ
ብሬ የሚወጡ የተለያዩ ዕቃዎች በየጊዜው ይሸጣሉ፣ ይለወጣሉ ማለታችን ነው::

አንድ ሸቀጥ ሲሸጥ ወይም ሲለወጥ እንዲሁ በዘፈቀደ አይደለም:: ከሚ
ሸጥበት ወይም ከሚለወጥበት ነገር ጋር ተመጣጣኝነት እንዲኖረው ያስፈልጋል::
ተመጣጣኝነቱ በብዛት፣ በዓይነት፣ ወይም በጥራት ሊሆን ይችላል:: ለምሳሌ ለራሱ
ፍጆታ ባይሆን ለሽያጭ ቢል ካራ አየሠራ የሚሸጥ ወይም የሚለውጥ ሰው እንውሰድ::
ይህ ሰው አንድ ካራ በ5 ኪሎ ስንዴ ይለውጥ፣ ወይም ደግሞ ለ5 ኪሎ ስንዴ ተመ
ጣጣኝ በሚሆን ሁለት ብር ይሸጥ እንበል:: ይህ ነገሮችን በተወሰነ መጠን ተመዛ
ዝነው እንዲለዋወጡ ወይም እንዲሸጡ የሚያደርግ ጠባይ የልውውጥ እሴት ይባላል::
እንግዲህ ሸቀጥ ካሉት ባህርያት ሁለተኛው ይህ ነው::

አላይ እንደጠቀስነው፣ አንድ የጠቀሜታ እሴት ያለውና የሰዎች የሥራ
ኃይል የፈሰሰበት ነገር ሸቀጥ እንዲሆን ከተፈለገ የሰዎችን ማኅበራዊ ፍላጐት
ማርካት ብቻ አይበቃም:: ሊለወጥ ሊሸጥ የሚያስችለው ባህርይ ሊኖረው ይገባል::
ለምሳሌ፣ የፀሐይ ብርሃን የሰዎችን ማኅበራዊ ፍላጐት ያረካል፣ የጠቀሜታ እሴትም
አለው:: ግን አይሸጥም አይለወጥም:: ካልተሸጠ ካልተለወጠ ሸቀጥ አይደለም::
ሸቀጥ ካልሆነም የልውውጥ እሴት የለውም:: እንግዲህ አንድ ነገር እኒህን ባህ
ርያት ያጣመረ እንደሆነ ብቻ ነው ሸቀጥ ሊሆን የሚችለውና የልውውጥ እሴት የሚኖ
ረው:: አንድ ነገር የጠቀሜታ እሴት ስላለው ብቻ የልውውጥ እሴት አይኖረውም:: የ
ሆኖም፣ ማንኛውም ነገር የልውውጥ እሴት እንዲኖረው ከተፈለገ የጠቀሜታ እሴት መ

ሊኖረው ይገባል:: ለማብረጃ ያህል ለላይ የጠቀስነውን አንዱ ጧፋ ኬኬ ለንወስድ:: በአንዱ የጥጥ ፋብሪካ ውስጥ እንዲሸጥ፣ እንዲለወጥ ባጠቃላይ ሸቀጥ እንዲሆን ሆኖ ነው የተሠራተው:: ይህ ጧፍ የልውውጥ እሴት አለው:: ምክንያቱም የተወሰነ ገንዘብ ያወጣል:: ሰዎችም ገንዘብ አውጥተው የሚገዙት ጠቀሜታ ስላለው ነው:: መለበሱ፣ ገበናን ይጋርዳል፣ ከብርድ ይከላከላል፣ ሰዎችን ያስጌጣል፣ ወዘተ... ይህ ግልጋሎቱ የጠቀሜታ እሴት እንዲኖረው ያደርጋል:: ይህን ግልጋሎት ባይሰጥ ወይም ጠቀሜታ ባይኖረው እንዴም ሰው አይገዛውም:: ሰው ካልገዛው፣ ካልወሰደው፣ ካልፈለገው የልውውጥ እሴት የለውም:: ስለዚህ የልውውጥ እሴት እንዲኖር አንዱ ነገር የጠቀሜታ እሴት ሊኖረው ያሻል::

እንግዲህ፣ ከልውውጥ አንፃር በንመለከተው፣ የአንዱ ሸቀጥ የጠቀሜታ እሴት ሁለት ባህርያት አሉት::

1. የበያችን ፍላጎት ለማርካት አንዱ ሸቀጥ ባለው ጠቀሜታ ከየናው አምራች ወደ ሌሎች በያች ይተላለፋል:: በለዚህም፣ የአንዱ ሸቀጥ የጠቀሜታ እሴት በተፈጥሮው ማኅበራዊ ጠባይ አለው::

2. የአንዱ ሸቀጥ የጠቀሜታ እሴት ከአምራቹ ወደ ሌላው ወይም ወደ ተጠቃሚው ሰው ቢተላለፍ በሽያጭ ወይም በልውውጥ አንበልም በግዥ ነው:: ይህን ጠባይ ካልያዘ ሸቀጥም ሊሆን አይችልም ወይም ደግሞ የልውውጥ እሴት አይኖረውም::

እስከዚህ ከደረስን ደግሞ፣ አንዱን ሸቀጥ ከሌላው ሸቀጥ ጋር እንዲለዋወጥ የሚያስችለውን፣ ወይም የሚያመጣጥነውን ኃይል ምሥጢሩ ምን እንደሆነ ለማወቅ እን ሞክር:: ፍሬም የተለያዩና የጠቀሜታ እሴታቸውም አንዱ ያልሆኑ ሸቀጦች እንዴት ነው

የሚመጣጠኑት? ለምንድነው የተለያዩ ሸቀጦች በተወሰነ አኀዛዊ ወይም መጠናዊ ተዛምዶ የሚመጣጠኑት? ለዚህ መመጣጠንና ለመለዋወጡ አመቺ ሁኔታ የፈጠረ፣ የተለያዩ ሸቀጦችን የሚያስማማቸው ወይም የሁሉም የጋራ ጠባይ የሆነ አንድ ነገር ይኖር ይሆናል። ያ ነገር ምን ይሆን? እስቲ ባጠቃላይ በተለያዩ ሸቀጦች ሁሉ በተለያየ ደረጃ የሸቀጥ ጠባይ ሊሆኑ የሚችሉ ነገሮችን እያነሳን እንመልከት።

ዕቃዎች የጠቀሜታ እሴት ወይም የሰውን ፍላጐት የማርካት ባሕርይ አላቸው፣ ዕቃዎች የተወሰነ ፍላጐትን የማሟላትና በተወሰነ መጠን የመቅረብ ባሕርይ አላቸው፣ ዕቃዎች የሰው ሥራ ውጤት ናቸው። እነዚህ ባሕርያት የዕቃዎችን የልውውጥ መጠን ወይም የልውውጥ እሴት ለመወሰን የቱን ያህል እንደሚያስችሉን አንድ በአንድ ለመመልከት እንሞክር።

በዓይነ ኅሊና ግምት ቢታይ ከሁሉም በላይ የዕቃዎች የሰውን ፍላጐት የማርካት ባሕርይ ወይም ጠቀሜታ እሴት የልውውጥ እሴትን የሚወስን ይመስላል። በዚህም የተነሣ በጣም ጠቃሚ የሆኑ ዕቃዎች የልውውጥ እሴት በጣም ከፍ ያለ፣ ይህንን ያህል ጠቀሜታ የሌላቸው ወይም ዝቅተኛ ጠቀሜታ ያላቸው ደግሞ ዝቅተኛ የልውውጥ እሴት የሚኖራቸው ይመስላል። ሆኖም ከተግባር እንደምናየው ለሰው ልጅ ሕልውና በጣም መሠረታዊና ጠቃሚ የሆኑ እንደ ውሃና ምግብ የመሳሰሉት ነገሮች በየትኛውም ኅብረተሰብ ውስጥ በቀላል ዋጋ የሚገኙ ናቸው። በሌላ በኩል ለሰው ልጅ ሕልውና አስፈላጊ ያልሆኑና ይህንን ያህልም ለሰው ጠቀሜታ የማይሰጡ እንደ አልማዝ፣ ወርቅና ሌሎችም የከበሩ የጌጣጌጥ ድንጋዮች በየትኛውም ኅብረተሰብ ውስጥ ከፍተኛ ዋጋ የሚያወጡ ናቸው። የዕቃዎች የልውውጥ እሴት በጠቀሜታ እሴት የሚወሰን ቢሆን ኖሮ ውሃና ዳቦ የአልማዝና የወርቅ ያህል በተወደዱና አልማዝና ወርቅ ደግሞ የውሃና የዳቦ ያህል በረከሱ ነበር። እርግጥ የጠቀሜታ እሴት እያላቸው የልውውጥ እሴት የሌላቸው ነገሮች /ምሳሌ አየር/ ቢኖሩም የጠቀሜታ እሴት የሌላቸው ነገሮች የልውው

አቤት አይኖራቸውም። ሆኖም ከፍ ሲል ከተጠቀሱት ማመዛዘኛዎች መገንዘብ እንደሚቻለው የጠቀሜታ አቤት ለልውውጥ መካሄዱ አንዱ ሁኔታ ቢሆንም የልውውጥ አቤትን የሚወስን አይደለም።

የዕቃዎች የአቅርቦትና የፍላጎት መጠን ሌላው የልውውጥ አቤትን ለመወሰን የሚያስችል ሁኔታ ይመስላል። አቅርቦትና ፍላጎት ከልውውጥ አቤት ወይም አቤት ጋር ያላቸውን ግንኙነት ከመመርመራችን በፊት በቅድሚያ አቅርቦትና ፍላጎት ብንል ምን ማለታችን እንደሆነ እናተኩራ። ለምሳሌ በአንድ መንደር ውስጥ በሣምንት ጫማ ሰሪዎች አሉ እንበል። ስምንቱ ጫማ ሠሪዎች በሣምንትውስጥ 50 ጥንድ ጫማዎች ሠርተው ቢያወጡና ለራሳቸው አንዳንድ ጥንድ ጫማ በማስቀረት የተቀረውን ወደ ገበያ ቢያወጡት ወደ ገበያ የቀረበው የጫማ መጠን ሃያ ሁለት ይሆናል። በዚያ መንደር ገበያው የሚውለው በቅዳሜ ቀን ቢሆን በቅዳሜ ገበያ በዚያ መንደር ውስጥ የቀረበው የጫማ መጠን ወይም የጫማ አቅርቦት ሃያ ሁለት ነው ማለት ነው።

በገበያ ውስጥ ለጫማው ያለውን ፍላጎት ከሚወስኑት ነገሮች መካከል ደግሞ በዚያ መንደር ውስጥ ጫማ ለመግዛት የሚፈልገው የሰው ብዛትና ለመግዛት የሚፈልገውም ሰው የመግዛት ችሎታ ዋነኛዎቹ ናቸው። እንደሚታወቀው የአንድ ዕቃ ፍላጎት በጣም ከፍተኛ ከሆነና በዚያ በተወሰነ ወቀት የዕቃው ምርት ከበፊቱ ካልጨመረ ዋጋው ከፍ ይላ በሌላ በኩል ደግሞ አቅርቦቱ በጣም ከፍተኛ ከሆነ የዕቃው ዋጋ ዝቅ ይላል።

በጥልቀት ሲታይ ግን የዕቃዎች ምርትና ፍላጎት መጠን የልውውጥ አቤትን እንደማይወሰኑ መገንዘብ አያዳግትም። ይህንን ለማረጋገጥ የሚከተሉትን ምሳሌዎች እናጤን። እንበል በአገራችን ውስጥ የስኳርና የጨው ምርት መጠንና እንደዚሁም ኅብረተሰቡ ለነዚህ ዕቃዎች ያለው ፍላጎት መጠን እኩል ነው። ሆኖም የአንድ ኪሎ ስኳር ዋጋ በምንም ዓይነት ከአንድ ኪሎ የጨው ዋጋ ጋር እኩል አይሆኑም። የምርትና የፍላጎት መጠናቸው እኩል ቢሆንም አንድ ኪሎ የስኳር ዋጋ ከአንድ ኪሎ የጨው ዋጋ የበለጠ እንደሚሆን አያጠያይቅም። ሌላ ምሳሌ እንመልከት።

በአገራችን ውስጥ የጤፍና የባቄላን አቅርቦትና ፍላጐት መጠን እኩል ነው ብንል በምንም ዓይነት የአንዱ ኩንታል ጤፍ ዋጋ ከአንዱ ኩንታል ባቄላ ዋጋ ጋር እኩል አይሆንም:: ከረጅም ጊዜ የአገራችን የገበያ ዋጋዎች ማየት እንደሚቻለው የጤፍ ዋጋ ከባቄላ ዋጋ ከፍ ያለ እንደነበርና እንደሚሆንም ግልጽ ነው:: ከነዚህ ሁለት ምሳሌዎች የምንገነዘበው የዕቃዎች ምርትና ፍላጐት መጠን የልውውጥ እሴትን ለመወሰን የማያስችል መሆኑን ነው::

እርግጥ የእቃዎች አቅርቦትና የፍላጐት መጠን በገበያ ዋጋ ላይ ልዩነት እንደሚያስከትል የሚያጠያይቅ አይደለም:: እዚህ ላይ በገበያ ዋጋና በልውውጥ እሴት መካከል ያለውን ልዩነት በአእምሮአችን ማስታወስ አለብን:: በአንድ በተወሰነ ጊዜ የአንድ እቃ ፍላጐት ከእቃው አቅርቦት በላይ በጣም ከፍ ካለ የገበያው ዋጋ ከእቃው የልውውጥ እሴት በላይ ከፍ ሊል ይችላል፣ በሌላበኩል የእቃው የምርት መጠን ከዕቃው ፍላጐት በላይ ከሆነ ደግሞ የገበያው ዋጋ ከእቃው የልውውጥ እሴት ወይም እሴት፣ በታች ዝቅ ሊል ይችላል:: የአንድ ሸቀጥ የገበያ ዋጋ ከሸቀጩ ልውውጥ እሴት ጋር እኩል የሚሆነው የሸቀጩ የአቅርቦትና የፍላጐት መጠን እኩል ቢሆን ብቻ ነው:: በለዚህ የእቃው የአቅርቦትና ፍላጐት መጠን የገበያ ዋጋ ከእቃዎች የልውውጥ እሴት በላይና በታች ምን ያህል እንደሚዋዥቅ የሚያሣይ እንጂ በራሱ የዕቃዎችን እሴት ወይም የልውውጥን እሴት የሚወስን አይደለም::

በካፒታሊስት ኢኮኖሚ ሥርዓት አንድ ሸቀጥ በጥቂቱ ለገበያ ቀርቦ በገበያ ውስጥ ግን ብዙ ፈላጊ ቢኖረው፣ ይወደዳና የሸቀጩ ዋጋ ከእሴቱ በላይ ይወጣና ይሸጣል:: በአንፃሩ ደግሞ ከፍላጐት በላይ ገበያ ውስጥ ከቀረበ ይረክስና

የሽቶው ዋጋ ከእሴቱ በታች ይወርዳል፤ አምራቾችም ያከስራል። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ለሽቶው ያለው ፍላጎትና ሽቶው በገበያ ላይ የቀረበበት መጠን የተጣጣመ እንደሆነ የሽቶው ዋጋና እሴት እኩል ይሆናሉ።

ከነዚህ በተጨማሪ የእቃዎችን መጠንና ክብደት መልክና ቅርጽ፣ የንጥረ ነገር ይዘታቸውንና የተፈጥሮ ባሕሪያቸውንም ማሰብ ይቻላል። ይሁን እንጂ ከተግባር ወይም ከልምድ እንደምንገነዘበው ከጠቀስናቸው ባሕርያት መካከል አንዳቸውም የእቃዎችን የልውውጥ መጠን ወይም እሴት ለመወሰን የሚረዱ አይደሉም። በመጠንና ክብደት ቢሆን አልማዝ፣ ወርቅ ዛሬ የሚገዙበትን ያህል ዋጋ ባላወጡ ነበር። በሌላ በኩል ከፍተኛ ክብደት እያላቸውም በጣም በርካሽ ዋጋ የሚገዙ አያሌ ሸቀጦችን ማሰብ ይቻላል። የእቃዎች የንጥረ ነገር ይዘትም የጠቀሜታ እሴታቸውን እንጂ የልውውጥ እሴታቸውን አይወስንም። መልክና ቅርጽም የእቃዎችን የልውውጥ እሴት ለመወሰን ምንም ያህል እንደማያግዝ መገመት አያዳግትም።

ከፍ ብሎ የተመለከትናቸው ባሕርያት ሁሉ የአንዱን ሸቀጥ የልውውጥ እሴት ለመወሰን የማያስችሉ ከሆኑ የዕቃዎች ልውውጥ እንዴት ሊካሄድ ይችላል? ባጭሩ አንድ ሸቀጥ ከሌላ ሸቀጥ ጋር እንዴት ሊነጻጸርና የልውውጥ መጠን ሊተመንለት ይችላል? ለዚህ ጥያቄ የማያወላውል ሳይንሳዊ መልስ የሰጠው ታላቁ የወዛደር ፈላስፋ ካርል ማርክስ ነው። ካርል ማርክስ ባደረጋቸው ምርምሮች እንዳረጋገጠው ማናቸውም የልውውጥ እሴት ያላቸው ሸቀጦች ሁሉ የጋራ ወይም የወል ባሕርይ የሰው ሥራ ውጤት መሆናቸው ነው። ስለዚህ አንዱ ሸቀጥ ከሌላው ሸቀጥ ጋር ለመዛዘንና የልውውጡም መጠን ሊተመንለት የሚችለው

ለያንዳንዱ ሸቀጥ የተወሰነ የሰው ሥራ ውጤት በመሆኑ ነው:: በስህነም የሸቀጦች የልውውጥ እሴት የሚወሰነው ሸቀጡን ለማምረት በፈሰሰው አስፈላጊ ማኅበራዊ የሥራ ጊዜ ነው::

ይህንን መሠረታዊ እውነታ ከዕለት ተዕለት ሕይወታችን ወይም ከልምዳችን በቀላሉ ማረጋገጥ ይቻላል:: እንደሚታወቀው ለሰው ልጅ ከፍተኛ የጠቀሜታ እሴት ያላቸው ነገር ግን የሰው ስራ ውጤት ባለመሆናቸው ያለምንም ወጪ ወይም ክፍያ የምናገኛቸውና የምንጠቀምባቸው አያሌ ነገሮች አሉ:: አየር፣ የምንጭ ወይም የወንዝ ውሃ ወዘተ...በዚህ አንጻር ሊጠቀሱ የሚችሉ ምሳሌዎች ናቸው:: ያለምንም ክፍያ ከወንዝ የምንቀዳው ውሃ በዘመናዊ መልክ ተዘጋጅቶ በቧንቧ እቤታችን ወይም አካባቢያችን ድረስ ሲቀርብ ዋጋ የምንከፍልበት አገልግሎትን ለማቅረብ የተወሰነ የሰው ሥራ በለፈሰሰበት ብቻ ነው::

የዕቃዎች የልውውጥ እሴት በፈሰሰባቸው የሥራ ኃይል መጠን የሚወሰን መሆኑን የሚያረጋግጠው ሌላው ሁኔታ ከፍተኛ ሥራ የሚጠይቁ ቁሳዊ ሀብቶች ሁሉ ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው መሆኑ ነው:: ደጋግመን ያነሳነውን የአልማዝና ወርቅ ሁኔታ እንደገና ብንመለከት ዋጋቸው ሊወደድ የቻለው እነዚህን ማዕድናት ከመሬት ውስጥ ለማውጣትና ለሰው ጥቅም ሊውሉ በሚችሉበት መልክ ለማዘጋጀት ከፍተኛ የሰው ሥራ የሚጠይቁ በመሆናቸው ነው:: እንዲያውም ካርል ማርክስና ሌሎችም የኢኮኖሚ ሊቃውንት አንዳንድ ጊዜ የአንዳንድ የወርቅና የአልማዝ ማዕድናት የፈሰሰባቸውን የሰው ሥራ ዋጋ እንኳን የማይመልሱበት ጊዜ እንደሚኖር አረጋግጠዋል:: በሌላ በኩል ወርቅና አልማዝ እንደ ድንጋይ የትም ወድቀው የሚገኙ ቢሆኑ ኖሮ ዋጋቸውም የዚያኑ ያህል በረከሰ ነበር::

ለአብዛኛ ዎቻችን ሕይወት በጣም ቀርብ የሆኑትን የጤፍና የገብስ፣ ወይም የበንዴና የባቄላ ዋጋዎች ልዩነትም ብንመለከት የልዩነቱ መሠረት አያንዳንዱን በብል ለማምረት የሚጠይቀው የሰው የሥራ ጊዜ መጠን ልዩነት እንደሆነ መገን ዘብ አያዳግትም።

የልውውጥ እሴት በሰው ሥራ ጊዜ መጠን የሚወሰን መሆኑን የሚ ያረጋግጥልን ለሳው ተወባጭ ማስረጃ የእቃዎች ዋጋ ከቴክኖሎጂ እድገት ጋር እየቀነሰ መምጣቱ ነው። የቴክኖሎጂ ዕድገት ዓላማ አንዱን ምርት ለማምረት የሚወስደውን የሥራ ጊዜ መጠን መቀነስ ነው። በዚህም የተነሣ በአንድ ወቅት በጣም ውድ የሆኑ ሸቀጦች የተሻሻለ ማምረቻ መሣሪያ ሲፈለሰፍ ዋጋቸውም እየ ረከሰ መጥቷል። ይህንን በይበልጥ ለመረዳት አንድ ምሳሌ እንውሰድ። በአ ሁኑ ወቅት የአገራችን ገበሬ በሚጠቀምባቸው የማምረቻ መሣሪያዎች ባለርይ የምርት ውጤት በሄክታር ሲታሰብ በጣም አነስተኛ ነው። አንድ የአገራችን ገበሬ ከአንዱ ሄክታር መሬት በአማካኝ የሚያመርተው ስንዴ 12 ኩንታል፣ ጤፍ ደግሞ ከ5 እስከ 6 ኩንታል እንደማይበልጥ ይገመታል። እንበል የተ ሻሻሉ የማምረቻ መሣሪያዎች፣ ዘርና ዳዴ በመጠቀም በሚቀጥሉት ዓመታት አንድ ገበሬ በሄክታር የሚያመርተው ስንዴ ወደ 40 ኩንታል፣ ጤፍ ደግሞ ወደ 15 ኩንታል ከፍ ቢል በተወሰነ የሥራ ጊዜው የሚያመርተው የምርት መጠን ከፍተኛ በመሆኑ የዛሬው የጤፍና የስንዴ ዋጋ ከግማሽ በታች የማይቀንስበት ምክንያት የለም ወይም አይኖርም። //

ለማጠቃለል ከፍ ቢል ከቀረበው ትንተና መገንዘብ የምንችለው ማርክስ እንዳለውም የልውውጥ እሴት መሠረት የሰው ስራ ነው። በስዚህ ሸቀጦች እርስ በእርሳቸው ለመዛዘኛና በተወሰነ መጠን ሲለዋወጡ የሚችሉ ትም እያንዳንዱን ሸቀጥ ለማምረት በወሰደው አስፈላጊ ማኅበራዊ የሥራ ጊዜ መጠን ነው። ይሽ በአንዱ ሸቀጥ ውስጥ የተጠናቀረ አስፈላጊ ማኅበራዊ

የሥራ ጊዜ ደግሞ የአንዱን ሸቀጥ እሴት የሚወስን ነው::

3. <u>ተጨባጭና ረቂቅ ሥራ</u>፣ ከፍ ብሎ እንደተመለከተው ማናቸውም ሸቀጥ ሁለት ወይም ጥንድ ባሕርያት አሉት:: አንደኛው ባሕርይ ሸቀጥ የጠቀሜታ እሴት ያለው መሆኑ ሲሆን፣ ሁለተኛው ባሕርይው ደግሞ ሸቀጥ የልውውጥ እሴትም ያለው መሆኑ ነው:: ማናቸውም ሸቀጥ የሰው ሥራ ውጤት እንደመሆኑ የሸቀጥ ምርት ጥንድ ባሕርይ የሚወስነው ሸቀጡን ለማምረት ጥቅም ላይ የዋለው የሰው ሥራ ያለው ጥንድ ባሕርያት ነው:: የሰው ሥራ ያሉት ጥንድ ባሕርያት ምንድን ናቸው?

ሥራ ምንጊዜም የተወሰነ ዓላማና ግብ ያለው ማኅበራዊ ተግባር ነው:: ስለዚህ ማናቸውም የሰው ልጅ የሥራ ኃይሉን የሚያፈስባቸው ተግባሮች ሁሉ የተወሰኑ የምርት ተገብሮችንና የምርት መሣሪያዎችን በመጠቀምና የተለያዩ የአሠራር ዘዴዎችን በመቀየስ የተወሰኑ ውጤቶችን ለማስገኘት የሚታቀዱ ናቸው:: የማዕድን ሥራ፣ የባንክ ሥራ፣ ብረት ማቅለጥ፣ ግንበኝነት፣ አናጢነት፣ ወዘተ... የተለያዩ የምርት መገልገያዎችን በመጠቀም፣ የተለያዩ ውጤቶች ለማስገኘት የሚታቀዱ ሥራዎች ናቸው:: በዚህ መልክ ማናቸውም የተወሰነ ግብ ለማስገኘት ጥቅም ላይ የሚውል የሰው የሥራ ኃይል <u>ተጨባጭ ሥራ</u> ይባላል:: አናጢነት አንዱ ተጨባጭ ሥራ ነው፣ ግንበኝነት እንዲሁ ሌላ ተጨባጭ ሥራ ነው:: አካውንታንት፣ ኢኮኖሚስት፣ ልብስ ሰፊ፣ ወዘተ... በማለት ሌሎች አያሌ ምሳሌዎችን ማንሳት ይቻላል:: ስለዚህ ተጨባጭ ሥራ የምንለው አንዱ የተወሰነ የጠቀሜታ እሴት ለማስገኘት የሚውለውን የሰው ሥራ ነው::

በዚህ መሠረት ሥራ የተወሰነ ግብ ያለውና ለኅብረተሰብ ሕልውና አስፈላጊ የሆኑ የጠቀሜታ እሴት ያላቸውን ዕቃዎች ለማምረት የሚውል እንደመሆኑ ምንጊዜም ተጨባጭ ነው። ተጨባጭ ሥራ ኅብረተሰብ በሥራ አማካኝነት መሠረታዊ ፍላጎቶችን ለማሟላት ማምረት ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ የነበረ ታሪካዊ ፈርጅ እንደመሆኑ ከሥርዓተ ማኅበራትና ስልተምርቶች ባሕርያት ጋር ያልተያያዘ፣ ዘላለማዊና የኅብረተሰብ ሕልውና መሠረት ነው።

ተጨባጭ ሥራ ሸቀጦች ያላቸውን አንዱን ባሕርይ ማለትም የጠቀሜታ እሴት ባሕርያቸውን የሚገልጽ ነው። የተለያዩ የሰው ሥራ ውጤት የሆኑ ሸቀጦች በጠቀሜታ እሴትነታቸው እርስ በርሳቸው ሊወዳደሩ እንደማይችሉ ሁሉ የተለያዩ ተጨባጭ ሥራዎችም እርስ በርሳቸው ሊወዳደሩ ወይም ሊመዛዘኑ የሚችሉ አይደሉም። አንድ ጠረጴዛና ማረሻን በምሳሌነት ብንወስድ በዓይነት የተለያዩ የጠቀሜታ እሴት እንደመሆናቸው ሸቀጦችን ለማምረት የሚውለውም የሥራ ዓይነት የተለያየ ነው። ጠረጴዛው የአናጺ፣ ማረሻው ደግሞ የብረት ሠሪ ሥራ ውጤቶች ናቸው። የአንድ አናጺንና የብረት ሠሪን ሥራ ለመመዛዘን እንደማይቻል ሁሉ እነዚህ ሁለት ተጨባጭ ሥራዎች የሚፈጥሯቸውም ሸቀጦች በሚያስገኙት የጠቀሜታ እሴት እርስ በርሳቸው ማመዛዘን አይቻልም።

በሌላ በኩል በሌላው ክፍል በቀረበው ትንተና አንድ ዓይነት የጠቀሜታ እሴት ያላቸው ወይም የአንድ ዓይነት ተጨባጭ ሥራ ውጤት የሆኑ ሸቀጦች እርስ በእርሳቸው እንደማይወዳደሩ ወይም እንደማይለዋወጡ ተገንዝበናል። ኮት በሌላ ተመሳሳይ ኮት፣ ማረሻን በተመሳሳይ ማረሻ የሚለውጥ አይኖርም። ስለዚህ ልውውጥ ምንጊዜም የሚካሄደው የተለያዩ ተጨባጭ ሥራ ውጤቶች በሆኑ ሸቀጦች መካከል ነው። እዚህ ላይ የሚነሳው መሠረታዊ ጥያቄ ተጨባጭ ሥራ ሊመዛዘን ወይም ሊወዳደር የማይችል ከሆነ የተለያዩ ተጨባጭ ሥራ ውጤቶች የሆኑ ሸቀጦች ልውውጥ እንዴት ሊካሄድ ይችላል የሚለው ነው?

ተጨባጭ ሥራ ሊመዘዘን ወይም ሊወዳደር የማይችል ቢሆንም ማናቸውም የተጨባጭ ሥራ ውጤት የሆኑ ሸቀጦች የወል ወይም የጋራ ባሕርይ አላቸው:: ሁሉም በጥቅል የሠው ሥራ ማለትም የሰው ልጅ የአዕምሮ፣ የአካሉና የጡንቻ /ነርቭ/ ኃይል ውጤት መሆናቸው ነው:: በማናቸውም ተጨባጭ ሥራ ሂደት ውስጥ የሚፈሰው ወይም የሚውለው የሰው የሥራ ኃይል በዓይነት ሊለይ ረቂቅ ሥራ ተብሎ ይጠራል:: ዕቃዎች ሁሉ በጥቅሉ የሰው ሥራ ኃይል ውጤት ወይም የረቂቅ ሥራ ውጤት መሆናቸው የዓይነት ተመሳሳይነት ስለሚያስገኝላቸው ከዋጋት አንፃር ሊመዘዘኑና ሊወዳደሩ ይችላሉ:: ስለሆነም የሸቀጦች የልውውጥ እሴት መሠረት ረቂቅ ሥራ ነው::

ይህንን ሃሳብ በይበልጥ ለመገንዘብ በመጠኑም ቢሆን ዝርዝር ያለ መግለጫ ማቅረቡ ጠቃሚ ይሆናል:: ሰዎች ሁሉ በኅብረተሰቡ ውስጥ የተለያዩ ሥፍራና ማናቤናራቸውም የወል ባሕርያቸው ሰው መሆናቸው ነው:: በተመሳሳይ መልክ ሸቀጦች ሁሉ የተለያዩ ተጨባጭ ሥራ ውጤቶች ቢሆኑም፣ የሁሉም መሠረት በጥቅሉ የሰው ሥራ ኃይል ውጤት መሆናቸው ነው:: ሰዎች በተለየ ምክንያት /ትምህርት፣ ሥልጠና፣/ የተለያዩ የሥራ ችሎታ ቢኖራቸውም ማናቸውም ግለሰብ በተፈጥሮ ባሕርዩ ያለው የሥራ ኃይል ቀላል የሥራ ኃይል ነው:: ለርግጥ ይህ ቀላል የሥራ ኃይል በተለያዩ ዕድገት ደረጃ ላይ በሚገኙ ኅብረተሰቦችና በአንድ ኅብረተሰብም ውስጥ ቢሆን በተለያዩ ጊዜያት የተለያዩ ባሕርያት ይኖሩታል:: ሆኖም በአንድ ኅብረተሰብ ውስጥ በአንድ በተወሰነ ጊዜ ለማናቸውም ነገር መመዘዘን እንዲረዳ የቀላል ሥራ ኃይል አማካኝ ግምት ይኖራል:: በአገራችንም አንድ ሙያ የሌለው ሠራተኛ በአማካኝ በቀን ወይም በሰዓት ምን ያህል በይ ሊቆፍር፣ ቁጥቋጦ ሊመነጥር ወይም ሊያርስ ወይም ሊያርም እንደሚችል ከልምድ መገመት ይቻላል:: ማናቸውም ሙያ ያላቸው ሠራተኞች በተወሰነ ወቅት የሚያስገኙት የምርት ውጤት ሊገመት ወይም ሊወዳደር የሚችለው በማዕከላዊ ግምት አንድ ሙያ የሌለው ወይም ቀላል የሥራ ኃይል ያለው ሠራተኛ ሊያመርት ከሚችለው ጋር በማመዛዘን ነው:: ከዚህ በመነሣት ሸቀጦች

የዓይነት ልዩነት ያላቸው ሠራተኞች ሥራ ወይም የተለያዩ ተጨባጭ ሥራዎች ውጤት ቢሆኑም ሸቀጦችን በማምረት ከሚጠይቀው አማካኝ ተባል የሥራ ኃይል ግምት ጋር በማመዛዘን የሸቀጦችን የልውውጥ እሴት መወሰን ይቻላል:: ረቂቅ ሥራ የሸቀጦችን የልውውጥ እሴት ለመወሰን የሚያስችለው በዚህ መልክ ነው:: እርግጥ የተጨባጭ ሥራ ውጤቶች ከጥቅል የሰው ሥራ ጋር የሚመዛዘንበት ዝምድ በምርት ሂደት ውስጥ በማኅበራዊ ልምድ የሚወሰን በመሆኑ አሠራሩ በግልጽ የሚታይ አይደለም:: የዚህ ዓይነት ማወዳደሪያ ዘዴ ባይኖር ኖሮ ኅብረተሰብ አንዱን እቃ ከሌላው ጋር ለማመዛዘንና በዕቃዎች መካከል ልውውጥ እንዲካሄድ የሚያስችል አኅዛዊ ዝምድ ለመመሥረት ባልቻለም ነበር::

በኅብረተሰብ ዕድገት ታሪክ ውስጥ ረቂቅ ሥራ ሕልውና ያገኘው ከሸቀጥ ምርት መስፈን ጋር ነው:: እርግጥ የሸቀጥ ምርት ከመስፈኑም በፊት ዕቃዎች ይመረቱ፣ የሚመረቱትም ዕቃዎች በጥቅል የሰው ሥራ ውጤት ነበሩ:: ሆኖም ከሸቀጥ ምርት መስፈን በፊት ማለት በተፈጥሮአዊ ኢኮኖሚ ውስጥ የምርት መገልገያዎች በወል የተያዙ በመሆናቸው አምራቾች የሥራቸውን ውጤት የሚከፋፈሉት በእኩልነት በመሆኑ የምርታቸውን የልውውጥ እሴት መወሰን አስፈላጊ አልነበረም:: አንዱን የተጨባጭ ሥራ ውጤት ከሌላው ጋር ማወዳደር የተጀመረው ሰዎች የሥራቸውን ውጤት በገበያ አማካኝነት መሸጥና መለወጥ ከጀመሩ ወዲህ ነው:: ስለሆነም ረቂቅ ሥራ ከሸቀጥ ምርት መክሰም ጋር የሚያከትም እንደ ሸቀጥ ምርት ዘላለማዊነት የሌለው ታሪካዊ ክስተት ነው::

## 4. ግላዊና ማኅበራዊ ሥራ

የሸቀጥ ምርት በሰፈነባቸው ኅብረተሰቦች ውስጥ በግልና በማኅበራዊ ሥራ መካከል ቅራኔ ይኖራል:: ይህም ቅራኔ የሰው ሥራ ጥንድ ባህርያት በሆኑት በተጨባጭ ሥራና በረቂቅ ሥራ መካከል የሚከሰት ቅራኔ ነው::

የምርት መገልገያዎች በግል በተያዙባቸው ኅብረተሰቦች ዘንድ የአያንዳንዱ ሸቀጥ አምራች ሥራ ግላዊ የመሆን ባሕርይ አለው:: በለዚህ አያንዳንዱ የሸቀጥ አምራች የሚያመርተው ምርት ማኅበራዊ ጠቀሜታ ያለው ቢሆንም የምርቱ ዓይነትና ብዛት እንዲሁም የምርቱ መጠንና ስርጭት የሚወሰነው ግን በተናጠል በአያንዳንዱ አምራች ግላዊ ግምት ነው:: የምርት አደረጃጀቱ ባሕርይ ግላዊ በመሆኑ በሸቀጥ አምራቾች ዘንድ በተግባር ላይ የዋለው የሰው ሥራ አጠቃቀም ከኅብረተሰቡ አጠቃላይ ፍላጎት አንፃር የሚቀናጅና የሚታቀድ አይደለም::

በዚህ ዓይነት የሸቀጥ ምርት በሰፈነባቸው ኢኮኖሚዎች ውስጥ የምርቱ ዓይነትና መጠን የሚወሰነው በአያንዳንዱ የግል አምራች ቢሆንም በሌላ በኩል በኢኮኖሚ ውስጥ ማኅበራዊ የሥራ ክፍፍል መኖሩ በአሉት የተለያዩ አምራቶች መካከል ግንኙነትና ጥገኝነት እንዲኖር ያስገድዳል:: አንድ የጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካን ምሳሌ አድርገን እንውሰድ:: ፋብሪካው የሚያስፈልጉትን ጥሬ ዕቃዎች ሁሉ በራሱ ሊያመርት አይችልም:: ጥጡን ከገበሬው፣ በምርቱ ሂደት ውስጥ የሚያስፈልጉትን ልዩ ልዩ ንጥረ ነገሮች ከሌሎች አምራቶች ማግኘት አለበት:: ፋብሪካውን ለማንቀሳቀስ የሚያስፈልገውን ኃይል ለማግኘትና እንዲሁም ጥሬ ዕቃዎችንና የምርት ውጤቶቹን ለማጓጓዝ ልዩ ልዩ አገልግሎቶች ከተለያዩ ድርጅቶች ይሻል:: ከዚህ ሁሉ በላይ ደግሞ የምርት ውጤቱን ለሸማቹ ሕዝብ ማቅረብ አለበት:: ከዚህ አንፃር ከሸማቾም ጋር ግንኙነት ይኖረዋል:: ባጭሩ በምርት ሂደት ውስጥ የሚያስፈልጉትን ጥሬ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ለማግኘት እንዲሁም ሸቀጡን ለመሸጥ በብዙ ሌሎች ድርጅቶች ላይ መተማመንና ጥገኛ መሆን ይገደዳል:: እንዲያውም በኢኮኖሚው ውስጥ ማኅበራዊ የሥራ ክፍፍል ይበልጥ እየዳበረ በሄደ ቁጥር እያንዳንዱ አምራች ከሌሎች አምራቶች ጋር የሚኖረው ግንኙነትና ጥገኝነት እየተበፋፋና እየተጠናከረ ይመጣል:: ከዚህ ግንኙነት የምንገነዘበው ዋና ነገር የሸቀጥ

አምራቾች ሥራ ወይም በሥራቸው የተሰማራው የሰው ሥራ በመሠረቱ ማኅበራዊ መሆኑንና የእያንዳንዱ ሥራ አጠቃላይ የኅብረተሰቡ ማኅበራዊ ሥራ አካል መሆኑን ነው:: ስለ ዚህ በሸቀጥ ምርት ኢኮኖሚ ውስጥ የሚከሰተው ዓይነተኛ ቅራኔ የእያንዳንዱ አምራች የግል ጉዳይ የሆነው ሥራ ማኅበራዊ ባህርይም ያለው መሆኑን ነው::

እያንዳንዱ አምራች የሚያከናውናቸው የምርት ተግባሮችና በዚህ ረገድ የሚወስዳቸው እርምጃዎች በግልና በተናጠል የሚወሰኑ መሆናቸው፣ የተግባሩን ማኅ በራዊ ባህርይ ቢሸፍነውም ይህ ባህርይ ገሃድ የሚወጣው እያንዳንዱ አምራች ሸቀ ጦቹን ለመሸጥና ለመለወጥ ገበያ ውስጥ ሲገባ ነው:: በዚህ የልውውጥ ሂደት አም ራቾች የሰው ሥራ ውጤት የሆኑት ሸቀጦቻቸው ማኅበራዊ ባሕርይ እንዳላቸው ይገነ ዘባሉ:: ሸቀጦቹ በኅብረተሰቡ ዘንድ ተፈላጊ ካልሆኑም ሸቀጦችን በማምረት የፈሰሰው ሥራ ፍሬ አልባ ከመሆኑም በላይ እንደአምራቱ አቀሟና የሥራ ደረጃ ድርጅቱ ከገበያ ወርዶ ሊወጣና ሠራተኛውም ሥራ አጥ ሊሆን ይችላሉ::

በአጠቃላይ ማኅበራዊ የሥራ ክፍፍል መዳበር ሥራን ማኅበራዊ ቢያደርገውም የምርት መገልገያዎች በግል መያዝ ደግሞ ግላዊ ባሕርይ ይሰጠዋል:: የሥራ ማኅበራዊ ባህርይ የአጠቃቀሙንም ማኅበራዊነት የሚጠይቅ ነው:: የምርት መገልገያዎች በግል በተያዙበት የሸቀጥ ኢኮኖሚ ውስጥ የሰዉ ሥራ አጠቃቀም በግል መወሰኑ ሥራ ካለው ማኅበራዊ ባሕርይ ጋር መሠረታዊ ቅራኔ ይፈጥራል:: ይህም በመሆኑ የሸቀጥ ምርት በሰፈነ ባቸው ካፒታሊስት አገሮች ውስጥ ምንጊዜም የኅብረተሰቡን ፍላጎት ለማርካት አስቸጋሪ ይሆናል:: አምራቹ የሚያመርተው ለኅብረተሰቡ ጠቃሚና ተፈላጊነት ያላቸውን ሸቀጦች ሳይሆን፣ ከአራቡ ጥቅም አንጻር በማየት በጣም ከፍተኛ ትርፍ የሚያስገኙለትን ሸቀጦች ነው::

ስለሆነም በካፒታሊስት አገሮች ውስጥ ምንጊዜም የምርቱ መጠንም ሆነ ዓይነት ከኅብረተሰቡ ፍላጎት ጋር የሚጣጣም አይሆንም:: በዚህም የተነሣ በማናቸውም ዕድገት ደረጃ ላይ በሚገኙ የምርት መገልገያዎች በግል በተያዙባቸው የሸቀጥ ምርት ኢኮኖሚዎች ውስጥ ምንጊዜም የምርት ቀውስ መፈጠሩና ከሚንደላቀቁት መደቦች በተፃራሪ በድኅነትና በሥራ አጥነት የሚቀረመዱ መደቦችና ክፍሎች መኖራቸው የማይቀር ክስተት ነው::

## 5. <u>በሸቀጥ ውስጥ ያለው የእሴት መጠን መለኪያ</u>::

ቀደም ባሉት ክፍሎች የጠቀሜታ እሴት ያላቸው ሸቀጦች የልውውጥ እሴት የሚወስነው ሸቀጦችን ለማምረት በወጣው ወይም በዋለው ረቂቅ ሥራ መሆኑን ተገንዝበናል:: ከዚህ ቀጥሎ ሊነሳ የሚገባው ጥያቄ የልውውጡ እሴት ወይም የእሴት መጠን እንዴት ይለካል? የሚለው ነው:: ቀጥተኛና አጭሩ መልስ የእሴት መጠን ሸቀጡን ለማምረት በወጣው የሰው ሥራ መጠን ይለካል ማለት ነው::

የአንድ ሸቀጥ እሴት መጠን የሚወሰነው ሸቀጡን ለማምረት በፈጀው የሰው ስራ ጊዜ መጠን ከሆነ፣ ሌላው ሊነሣ የሚችለው ጥያቄ ሠራተኛው ሠነፍና ሙያ የሌለው በመሆኑ ሸቀጡን ለማምረት ረጅም ጊዜ ቢወስድበት ሸቀጡ በጣም ውድ ይሆናል ወይ? የሚለው ነው:: ማንም ሊገምት እንደሚችለው የእያንዳንዱ ሸቀጥ የልውውጥ እሴት መጠን እያንዳንዱ አምራች በወሰደበት የሥራ ጊዜ መጠን የሚለያይ ሊሆን አይችልም:: በማናቸውም ጊዜ በማናቸውም ሕብረተሰብ ውስጥ አንድን የተወሰነ ሥራ ለመሥራ፣ የሚወሰደው የሥራ ጊዜ መጠን ማዕከላዊ ግምት ይኖራል:: ከአገራችን አንዳንድ ምሣሌዎችን ብንወስድ አንድ ገበሬ አንድ የተወሰነ መጠንና የተፈጥሮ ባሕርይ ያለው መሬት ለማረስ የሚወስድበትን የሥራ ጊዜ በአማካኝ መገመት ይቻላል:: በተመሣሣይ መልክ በማናቸውም ኢንዱስትሪ ወይም የሕንፃ መስኮች ውስጥ ልዩ ልዩ ሥራዎችን ለማከናወን

የሚወስደው አማካይ የሥራ ጊዜ ለመተመንና ለመገመት ይቻላል። ለምሳሌ በአንድ አካባቢ ሠላሣ ማጭድ ሰሪዎች ቢኖሩና ተመሳሳይ ማጭዶች ለመሥራት፣ ሃያ ሰባቱ ማጭድ ሰራተኞች አንዳንዱ ማጭድ ለመሥራት እያንዳንዳቸው ሰባት ሰዓት ቢወስድባቸው፣ ሌሎቹ አራቱ ለያንዳንዱ ማጭድ አምስት ሰዓት ቢፈጅባቸውና የተቀሩት ሰባቱ ደግሞ ስድስት ሰዓት ቢፈጅባቸው በዚህ ሁኔታ የአንዱ ማጭድ እሴት የሚወሰነው አብዛኞቹ ማጭድ ሰሪዎች ማጭዱን ለመስራት በፈጀባቸው የሥራ ጊዜ መጠን እንጂ እያንዳንዱ አምራች በወሰደበት የሥራ ጊዜ ሊሆን አይችልም። ስለዚህ በዚህ ምሳሌ መሠረት በአንድ ማጭድ ውስጥ የተጠናቀረው አስፈላጊ ማኅበራዊ የሥራ ጊዜ ስድስት ሰዓት ተኩል ገደማ ይሆናል ማለት ነው። በዚህ ዓይነት አንድ የተወሰነ ሸቀጥ ለማምረት በአማካይ የሚፈጀው የሰው ሥራ ጊዜ መጠን <u>አስፈላጊ ማኅበራዊ የሥራ ጊዜ</u> ይባላል። ይህም <u>አስፈላጊ ማኅበራዊ የሥራ ጊዜ በአንድ ወቅት ሠራተኛው ባለው አማካይ ዕውቀትና ምርታማነት ደረጃ አንድ የተወሰነ ሸቀጥ ለማምረት የሚወስድበት የሥራ ጊዜ ነው</u>። ስለሆነም አስፈላጊ ማኅበራዊ የሥራ ጊዜ ከቴክኖሎጂ ዕድገትና ከሠራተኛው ምርታማነት መሻሻል ጋር እየቀነሰ የሚመጣ ነው።

ቀደም ሲል ወደ አነሳነው ጥያቄ ለመመለስ የአንድ ሸቀጥ የልውውጥ እሴት መጠን የሚወሰነው እያንዳንዱ ግለሰብ አምራች በሚወስድበት የሥራ ጊዜ ሳይሆን ያንን ሸቀጥ ለማምረት <u>በሚወስደው አስፈላጊ ማኅበራዊ የሥራ ጊዜ ይሆናል ማለት ነው።</u>

6. <u>ቀላል ሥራና ውስብስብ ሥራ</u>

ሥራ በቀላልና በውስብስብ መከፈሉ በሸቀጦች ውስጥ በተጠናቀረው እሴት ላይ ተጽዕኖ ይኖረዋል። ቀላል ሥራ የሚባለው በአንድ የተወሰነ የሙያ ዘርፍ ያልሠለጠነ ሰው ሊሰራው የሚችል ልምድ የማይጠይቅ ሥራ ሲሆን፤ ውስብስብ ሥራ የሚባለው ደግሞ በሙያ የሰለጠነንና ልዩ ልምዱን የሚጠይቅ ሥራ ነው። በአንድ በተወሰነ የጊዜ ክልል

ውስጥ ውስብስብ ሥራ ከቀላል ሥራ ይበልጥ ከፍተኛ እሴት ያስገኛል፤ ይህም በሸቀጦች የዋጋ ደረጃ ላይ ይንፀባረቃል። ስለሆነም ውስብስብ ሥራ በቀላል ሥራ ሲመነዘርና ሊዘረዘር ይችላል፤ ቀላልና ውስብስብ ሥራ ከፍ ብለው የተጠቀሱት የተጠቃሏና ረቂቅ፤ የግላዊና ማኅበራዊ የሥራ ባህርያት ገጽታ አላቸው፤ የእነዚህን ቅርጽ ይይዛሉ።

ውስብስብ ሥራ የሙያ ስልጠናን፤ ሰፊና ጥልቅ እውቀትና ከፍተኛ ትምህርትን የሚጠይቅ እንደመሆኑ ይህንን ለመቀበም ወይም ለማግኘት የሚደረገው ወጭ የዚህን ሥራ ኃይል እሴት ከፍ ያደርገዋል። ለምሳሌ ሐኪም፤መሐንዲስ፤ፕሮፌሰር፤ጠበቃ ወዘተ.. ለመሆን ከፍተኛ ትምህርት፤ ሰፊ እውቀት፤ የተሟላ የሙያ ስልጠና ይጠይቃል፤ የሚፈጀው ጊዜ፤ ለዚህም ወጪው ከፍተኛ ነው። ስለሆነም ሐኪሞች፤መሐንዲሶች፤ ፕሮፌሰሮች፤ ወዘተ.. የሚያስገኙት እሴት ከፍተኛ ስለሚሆን በዚሁ አንፃር የሚያገኙትም ክፍያ ከፍተኛ ይሆናል። በአንፃሩ ቀላል ሥራ ለምሳሌ ተሸካሚነት፤ ፈላጭነት፤ ቆፋሪነት፤ ተላላኪነት፤ ዘበኝነት፤ ወዘተ.. ልዩ ሙያ ወይም ትምህርት አይጠይቅም፤ በመሆኑ ለዝግጅት የሚጠይቀው ወጭ መጠነኛ ነው፤ ስለሆነም የዚህ የሥራ ኃይል እሴት አነስተኛ ነው።

እነዚህ የሥራ ዓይነቶች ማለትም ውስብስብ ሥራ እና ቀላል ስራ የሚፈጥሩት የእሴት መጠን ይለያያል ወይም ይበላለጣል፤ ከፍተኛ የሥራ ኃይል እሴት ያለው ውስብስብ ሥራ ከፍተኛ እሴት ሲያስገኝ ዝቅተኛ የሥራ ኃይል እሴት ያለው ቀላል ሥራ ደግሞ የሚፈጥረው እሴት አነስተኛ ይሆናል። ይህም የሚወሰነው በረቂቅና ማኅበራዊ ሥራነታቸው በተጠራቀመባቸው ውጤቶቻቸው ወይም ሸቀጦች አማካይነት በገበያ ላይ ግብታዊ በሆነ መንገድ ሲለዋወጡ ነው። እነዚህ ሸቀጦች ገበያ ላይ ወጥተው ቀጥታ ወይም በገንዘብ አማካይነት ሲለዋወጡ አንዱ የተወሰነ ውስብስብ ሥራ ለምሳሌ ሜካኒካል መሐንዲስነት የሥራ ውጤት አንዱ የተለየ ሙያ ከሌላው ሠራተኛ የሥራ ውጤት ምን ያህል ጊዜ እንደሚበልጥ መገመት ይቻላል።

አብዛኛውን ጊዜ እነዚህ የሥራ ዓይነቶች ባንድ ሸቀጥ ውስጥ ተጣምረው ስለሚገኙ ለይቶ ለማወቅ ያስቸግራል፤ ለምሳሌ አንድ አውቶሞቢል መኪና ብንወስድ ከተራቀቀ የመሐንዲስ ሥራ እንስቶ እስከ ተራ የተሸካሚ ሥራ ደረስ ያሉ የተለየ ሙያ ያላቸውና የሌላቸው ሠራተኞች የሥራ ውጤት ያለበት ነው። በሸቀጡ ውስጥ እነዚህን ሁሉ የሥራ ዓይነቶች ለይቶ ለማወቅ ቢያስቸግርም መኖራቸው አጠራጣሪ አይሆንም። እሴታቸው የሚለካውና በመካከላቸው ያለው ተዛምዶ የሚታወቀው ወይም የሚገለጠው በሚሰጠው ክፍያ ነው።

# ጥያቄዎች

1. ሸቀጥ ማለት ምን ማለት ነው? ታሪካዊ አመጣጡን አስረዳ::

2. የሸቀጥ ሁለት ባሕሪያት ምን ምን እንደሆኑ ከገለጽክ በኋላ እያንዳንዳቸውን አጠር ባለ ሁኔታ አብራራ::

3. በተፈጥሮ ኢኮኖሚና በሸቀጥ ኢኮኖሚ መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው? የኢትዮጵያን ምሣሌ ወስደህ አብራራ::

4. በአነስተኛ የሸቀጥ ምርትና የካፒታሊስት የሸቀጥ ምርት መካከል ያለውን ልዩነት አስረዳ::

5. እሴት ማለት ምን ማለት ነው? የአንድ ሸቀጥ እሴት እንዴት ይወሰናል እን
ዴትስ ይለካል::

6. በተጨባጭ ሥራና በረቂቅ ሥራ መካከል ያለው ልዩነት ምንድነው?

7. አስፈላጊ ማኅበራዊ የሥራ ጊዜ ሲባል ምን ማለት ነው?

8. በዋጋና በእሴት መካከል ስለአለው ግንኙነት አብራራ::

9. በካፒታሊስት የሸቀጥ ምርት ውስጥ በግልና በማኅበራዊ ሥራ መካከል ስለአለው ቅራኔና ስለ ቅራኔው ይዘት አብራራ::

10. በቀላል ሥራና በውስብስብ ሥራ መካከል ስለአለው ልዩነት አብራራ::

# ቃ ላ ት

| | | |
|---|---|---|
| 1. | የሸቀጥ ምርት | Commodity Production |
| 2. | ሸቀጥ | Commodity |
| 3. | ምርት | Product |
| 4. | የተፈጥሯዊ ኢኮኖሚ | Natural Economy |
| 5. | የካፒታሊስት የሸቀጥ ምርት | Capitalist Commodity Production |
| 6. | ማኅበራዊ የሥራ ክፍፍል | Social Division of Labour |
| 7. | እሴት | Value |
| 8. | የጠቀሜታ እሴት | Use Value |
| 9. | የልውውጥ እሴት | Exchange Value |
| 10. | ዋጋ | Price |
| 11. | ቀላል የሸቀጥ ምርት | Simple Commodity Production |
| 12. | የፍጆታ እቃዎች | Comsumer Goods |
| 13. | የምርት መገልገያዎች | Means of Production |
| 14. | አቅርቦት | Supply |
| 15. | ፍላጎት | Demand |
| 16. | ሥራ | Labour |
| 17. | ተጨባጭ ሥራ | Concrete Labour |
| 18. | ረቂቅ ሥራ | Abstract Labour |
| 19. | ግላዊ ሥራ | Private Labour |
| 20. | ማኅበራዊ ሥራ | Social Labour |
| 21. | ማኅበራዊ አስፈላጊ የሥራ ጊዜ | Socially Necessary Labour Time |
| 22. | ቀላል ሥራ | Simple Labour |
| 23. | ውስብስብ ሥራ | Complex Labour |
| 24. | ትርፍ ምርት | Surplus product |
| 25. | የሽግግር ወቅት | Period of transition |
| 26. | ተዛምዶ | Proportion |
| 27. | መሰኪያ | Measurement |
| 28. | ኦፈብራኪ | Manufacture |
| 29. | ቀላል የካፒታሊስት የሕብረት አሠራር | Simple Capitalist Cooperation |
| 30. | ክላሲካል | Classical |
| 31. | ብሔረ መንግሥት | Nation State |

## ም ዕ ራ ፍ 2

# ገንዘብና የእሴት ሕግ

### 1. የልውውጥ እድገትና ልዩ ልዩ የእሴት መልኮች፣

የአንድ ሸቀጥ እሴት በማምረት ሂደት ውስጥ በሰራ ኃይል ይፈጠራል፣ የሸቀጡ እሴት በተጨባጭ በእሴትነት የሚገለጠው ግን በልውውጥ ሂደት ውስጥ ነው። ይኸውም አንዱን ሸቀጥ ለምሳሌ ጨውን በስንዴ፣ ቡናን በጤፍ፣ ስኳርን በሻይ፣ ጫማን በኮት፣ ሰዓትን በልብስ ወዘተ...በምንለውጥበት ጊዜ በእነዚህ ሸቀጦች ውስጥ የተጠራቀመው እሴት ይፋ ይወጣል፣ ይገለጣል።

ሸቀጦች የሰው ስራና የተፈጥሮ ውህድ ቢሆኑም ጠቃሚነታቸውን፣ ተፈላጊነታቸውን የሰው ፍላጐት የማርካት ባሕርያቸውን ወይም ችሎታቸውን ማለትም እሴታቸውን የሚያገኙት በስራ አማካይነት ነው፣ የእሴታቸው መንበሩ የሆነው ነገር ወይም ቁብቁብ የተወሰነ የስራ ጥርቅም በውስጡ ይዞአል፣ እሴቱን የሚያቀዳጀው ይህ በውስጡ የተጠራቀመው ስራ ነው።

አንድ ሸቀጥ እሴት አለው ስንል የሸቀጡን እሴት በአካሉ ላይ ተለጥፎ አናይም፣ ለምሳሌ መጽሐፍ፣ ጠረጴዛ፣ ጫማ፣ ልብስ...እነዚህ ሁሉ የሰው ስራ የፈሰሰባቸው የሰውን ልዩ ልዩ ፍላጐቶች ለማርካት የሚችሉ እንደመሆናቸው እሴት ቢኖራቸውም፣ ይህ እሴታቸው በላያቸው ላይ አይንፀባረቅም ወይም በተጨባጭ የምናየው ነገር አይደለም። ወንበር፣ ጠረጴዛ፣ መጽሐፍ፣ ወረቀት፣ እስክሪብቶ፣ ደብተር፣ ዳቦ፣ ... ተደርድረው በሱቅ ውስጥ እናያለን፣ የእነዚህ እሴት ምን እንደሆነ ግን አናይም። የሸቀጦችን እሴት ለማወቅ የምንችለው በልውውጥ ሂደት ውስጥ ብቻ ይሆናል። በዚህ ጊዜ መቶ

ግራም ዳቦ ምን ያህል ግራም ስኳር፣ አንድ ኩንታል ጨው ስንት ፈረሱላ በርበሬ፣ አንድ የጽሕፈት ጠረጴዛ ስንት ወንበሮች...እንደሚያወጣ ለማ ወቅ እንችላለን።

በዚህ የልውውጥ ሂደት ውስጥ ሸቀጦች ይወዳደራሉ፣ ዓይነታቸውና መጠናቸው ይነጻጸራል፣ በዚህ ሂደት ውስጥ እሴታቸው ይገለጣል፣ ለምሳሌ ባንድ ደብተር 10 እርሳሶች ለመለወጥ ቢቻል የደብተሩ እሴት በእርሳሶች ተገለጠ ወይም ታወቀ ማለት ነው፡ይኸውም ደብተሩ ውስጥ የተ ጠራቀመው ማኅበራዊ ተቀባይነት ያለው የሥራ ጊዜ መጠን በአሥሮቹ እርሳ ሶች ውስጥ ከተጠራቀመው አስፈላጊ ማኅበራዊ የስራ ጊዜ መጠን ጋር ተመ ጣጣኝ ነው ማለት ነው።

የሸቀጦች እሴት የሚታወቀው፣ የሚገለጠውና ይፋ የሚሆነው በል ውውጥ ሂደት ውስጥ ቢሆንም የሚፈጠረው ግን በምርት ሂደት ውስጥ ነው። እነዚህ አምራቾች በጉልበታቸውና በአእምሮአቸው የተፈጥሮን ልዩ ልዩ ክፍ ሎች /አፈር፣ ድንጋይ፣ ማዕድናት፣ እንጨት.../ በመለወጥ የሰውን ፍላጎት ለማርካት የሚችሉ ነገሮች/ዳቦ፣ በርበሬ፣ እንጀራ፣ ስኳር፣ ጨው፣ ልብስ፣ ወንበር፣ አልጋ.../ ይሠራሉ። በሸቀጦች ውስጥ የተጠራቀመው ወይም የተጠናቀረው የስራ ጊዜ የአምራቾች የስራ ጊዜ መሆኑ ነው። ስለሆነም ከሸቀጦች በስተጀርባ አምራቾችን እናገኛለን። እንደዚሁም ሸቀጦችን በመለዋወጥ እሴታቸውን ስንወስን፣ የምናነጻጽረው ልዩ ልዩ አምራቾች ያፈሰሱትን የሥራ ኃይል መጠን ይሆናል፣ ለምሣሌ ዳቦን በስኳር፣ ደብተርን በእርሳስ፣ ጫማን በሰዓት ወዘተ...ስንለውጥ ዳቦ አምራቹ ያፈሰሰውን የሥራ ጊዜ መጠን ከስኳር አምራቹ፣ ጫማ አምራቹን

ከስፋት አምራቹ ከአፈበሰው የሥራ ጊዜ መጠን ጋር እናነፃፃራለን ማለት ነው፡

አቤት በአምራቾች መካከል የሚፈጠር ማኅበራዊ ግንኙነት መሆኑን ከዚህ በላይ ከተደረገው ትንተና ለመረዳት ይቻላል። ይህ በአምራቾች መካከል ያለው ማኅበራዊ ግንኙነት በሸቀጦች መካከል እንዳለ ግንኙነት ሆኖ ነው የሚታየን፣ በትክክል ግን በሸቀጥ አምራቾች መካከል ያለ ግንኙነት ነው።

አሁን ኅብረተሰብ በደረሰበት የዕድገት ደረጃ የሸቀጦች እሴት የሚገለጠው በገንዘብ መልክ ቢሆንም በጥንት ጊዜ ምርትና ልውውጥ ባልተስፋፋበት ኅብረተሰብ በዝቅተኛ የዕድገት ደረጃ ላይ በነበረበት ዘመን የሸቀጦች እሴት የሚገለጸው በተለያየ መልክና መንገድ ነበር።

የሸቀጦች እሴት ይገለጥባቸው የነበሩትን ዋና ዋና መልኮች ከዚህ ቀጥለን ባጭሩ ለመመልከት እንሞክራለን። ኅብረተሰብ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ በነበረበትና የንግድ ልውውጥ ሲጀመር አንድ ሸቀጥ በሌላው በአጋጣሚ ወይም በድንገት ይለወጥ ነበር፣ የልውውጥ ስራ ስነ ስርዓት አልያዘም ነበር። በዚህ ጊዜ ሸቀጥ በሸቀጥ፣ ቁሳቁስ በቁሳቁስ እንደ አሙቸና እንደአጋጣሚ ይለወጥ ነበር፣ ለምሳሌ አንድ ጋቢ ባንድ በሬ፣ አንድ መጥረቢያ በ2 እንስራ እንደሁኔታው ይለወጥ ነበር እንበል። የጋቢው እሴት በበሬ፣ የመጥረቢያው እሴት በእንስራ ተገለጠ ማለት ነው። ይህ በመጀመሪያው የልውውጥ ወቅት የነበረው የአንድ ሸቀጥ የራሱን እሴት በሌላው መገለጥ ሁኔታ የእሴት ጥንተ መልክ በመባል ይታወቃል።

በዚህ ሸቀጦች በቀጥታ ርስ በርሳቸው በሚለዋወጡበት ጊዜ እሴቱ በሌላ ሸቀጥ የሚገለጸው ሸቀጥ በምሳሌያችን ውስጥ ጋቢው ወይም መጥረቢያው የሚኖረው የእሴት መልክ አንጻራዊ ይባላል፤ ከፊት ለፊቱ እሴቱን የሚገልጥ ወይም የእሴቱ መለኪያ የሆነ ሌላ ሸቀጥ መኖሩን የሚያሳይ ወይም የሚያመለክት ነው። ይህ አንጻራዊ የእሴት መልክ በሁለቱ ሸቀጦች መካከል ያለውን የወል ባህርይ ማለትም ማኅበራዊ ስራን ያመለክታል፤ ከዚህም በተጨማሪ በሁለቱ ሸቀጦች መካከል የልውውጡን መጠን ማለት በንት ለስንት እንደሚለዋወጡ ያመለክታል።

የሌላውን እሴት ገላጭ የሆነው ሸቀጥ በምሳሌያችን ውስጥ በሬ ወይም አንበራ <u>አኩያዊ የእሴት መልክ</u> ይባላል፤ የሌላ ሸቀጥ እሴት በመግለጥ የቆመ የሌላው ሸቀጥ እሴት መልክ የሚገለጥበት ማለት ነው። አንዱ ጋቢ በ5 በጎች ይለወጣል ብንል የ5 በጎችን የጠቀሜታ እሴት የሚገልጠው ሸቀጥ የጠቀሜታ እሴት በልውውጡ ውስጥ የሌላውን ሸቀጥ እሴት መልክ በመያዝና በመግለጥ ከጠቀሜታ እሴት ወደ እሴት ይለወጣል። እዚህ በተጠቀሰው ምሳሌያችን ውስጥ የጠቀሜታ እሴት የነበሩት 5 በጎች ከጋቢው ጋር በማወዳደር የአንድ ጋቢ እሴት መግለጫ ሆነው ሲቀርቡ የጠቀሜታ እሴትነታቸውን ትተው የጋቢውን እሴት መልክ ያዙ። አኩያዊው የእሴት መልክ ተጨባጭ ወይም የግል ስራ ወደ ረቂቅ ወይም ማኅበራዊ ሥራ የሚለወጥበት የሸቀጦች ማኅበራዊ ተፈላጊነትና ተቀባይነት የሚረጋገጥበት ዓይነተኛ መንገድ ነው።

በኅብረተሰብ እድገት ታሪክ ውስጥ ማኅበራዊ የሥራ ክፍፍል እየተስፋፋ በመጣ የሸቀጥንም ልውውጥ ይበልጥ የዘወትር ተግባር እያደረገው መጥቶአል። ከብት አርቢዎች ለራሳቸው ከሚፈልጉት በላይ ከብት ማርባትና በነዚሁ በትርፍ ከመረቷቸው ከብቶች ሌላ እነሱ ሊያመርቱ የማይችሉትን ሸቀጥ ከሌሎች ማግኘት ቻሉ። የእርሻ ውጤትን ከገበሬዎች

የዕደ ጥበብ ዉጤትን ከዕደ ጥበብ አምራቶች፣ በግ ሰጥቶ ሰንጂ ወይም ጦር ወይም ሌላ ሸቀጥ መለወጥ ተቻለ:: በዚህ የዕድገት ደረጃ ላይ ያለው የሸቀጥ ልውውጥ በሁለት ሸቀጦች መሀል ብቻ ባይሆን በብዙ ሸቀጦች መካከልም በቀጥታ የሚካሄድ ነበር:: ይህ የልውውጥ ዕድገት ደረጃ የተስፋፋ የእሴት መልክ የታየበት ደረጃ ነበር:: ለምሳሌ አንድ ከብት አርቢ በአንድ በግ ቢፈልግ 10 ቁና ሰንዴ ወይም 20 ክንድ ሸማ ወይም ሁለት መጥረቢያ ወይም 3 መሐለቅ ወርቅ ወዘተ... ሊለውጥ ይችላል እንደማለት ነው::

በዚህ ምሣሌያችን መሠረት ቀደም ሲል እንዳየነው ልውውጡ በሁለት ሸቀጦች ብቻ መሀል ሣይሆን አንድ ሸቀጥ የተለያዩ ሸቀጦችን በተናጠል ሊለውጥ ይችላል ማለት ነው:: ይህ ማለት ደግሞ በምሣሌያችን መሠረት የአንድ በግ እሴት በተለያዩ ሸቀጦች የጠቀሜታ እሴት ይገለጧል ማለት ነው:: በዚህ የዕድገት ደረጃ ላይ የታየው የዚህ ዓይነት የልውውጥ ዘዴ ማኅበራዊ የሥራ ክፍፍልና የሸቀጦች ምርትም ይበልጥ አያደገ ቢሄድ መለወጥ ነበረበት:: የዚህም ዋና ምክንያት የሸቀጥ ምርት እድገት አየጨመረ መሄዱ በሸቀጦች መሀል ያለውን የልውውጥ ሁኔታ አያሰፋው በመሄዱ ነው::

አንድ ጫማ የሚያመርት ሰው መጥረቢያ ይፈልግና ጫማውን ይዞ መጥረቢያ ካለው ሰው ዘንድ ይሄዳል:: ባለ መጥረቢያው ሰው ዘንድ ሲደርስ ባለ መጥረቢያው ጫማ ሣይሆን በግ እንደሚፈልግ ይነግረዋል:: አሁን ባለ ጫማው መጥረቢያ ለማግኘት ሁለት ዘዴ ይኖረዋል:: አንዱም ጫማ ወሰዶ መጥረቢያ የሚሰጠው ሰው መፈለግ አለበት:አለዚያም በጫማው በግ ለውጦ በጉን ለባለ መጥረቢያው ሰጥቶ መጥረቢያውን መውሰድ አለበት::

በዚህ ምሳሌያችን መሠረት ልውውጡ ሶስት ሸቀጦችን ማለትም ጫማ፣ በግና መጥረቢያን ይመለከታል። ከነዚህ ከሶስቱ ሸቀጦች ደግሞ አንደኛው በብዛትና በማንኛውም ጊዜ የሚፈለግ ይሆናል። ለምሳሌ በጉን ጫማ ሰሪውም ሆነ መጥረቢያ ሰሪው ይፈልጉታል። እነሱ ብቻ ሳይሆኑ ሌሎችም ይፈልጉታል። ስለዚህ ባለ ጫማው መጥረቢያ ለማግኘት ቀላል መንገዱ የሚሆንለት ሁሉም የሚፈልገውን በግ በጫማው ለውጦ ያገኘውን በግ በመጥረቢያ መለወጥ ነው። እንዲህ ካልሆነ ጫማ የሚፈልግ ባለ መጥረቢያ እስኪያገኝ ቢንከራተት ሊከርም ነው።

በዚህ ዓይነት በልውውጥ የእድገት ደረጃ የመጀመሪያ ወቅት ላይ የተመለከትነው በሁለት ሸቀጦች መካከል የሚደረገው የቀጥታ ልውውጥ አክትሞ ቀስ በቀስ አንድ ሸቀጥ በሁሉም ዘንድ ተፈላጊ እየሆነ ቢሄድ በዚ ያሉ ሸቀጦችን ሊለውጥ የሚችልበት ደረጃ ላይ ይደርሳል። ይህ የልውውጥ የእድገት ደረጃም አጠቃላይ የእሴት መልክ የታየበት የእድገት ደረጃ ነው።

በዚህ ምሳሌያችንና በዚህ የልውውጥ የእድገት ደረጃ በግ በብዙ ሸቀጦች ሊለወጥ የሚችል ሸቀጥ ሆነ ማለት ነው። በሌላ አነጋገር በግ ሁለንታዊ እኩያ በመባል ይታወቃል። ይህ ሆኖ ግን በዚህ የልውውጥ የእድገት ደረጃ ላይ አሁንም አንድ ሸቀጥ ሁለንታዊ እኩያ መሆኑ ገና ሙሉ በሙሉ አይረጋገጥም። ለምን? ምክንያቱም በግ በማንኛውም ጊዜና በሁሉም ሥፍራ ተፈላጊ ስለማይሆን ነው። በተለያዩ ስፍራዎች የተለያዩ ሸቀጦች ሁለንታዊ እኩያ ሚና ሲጫወቱ ስለሚችሉ ነው። አንደኛው ቦታ በግ ሊሆን ይችላል፤ ሌላ ቦታ ስንዴ። አሁንም በሌላ ቦታ አሞሌ ጨው ወዘተ. . . እያለ በተለያዩ ስፍራዎች የተለያዩ ሸቀጦች የልውውጥ

አማካይ ሊሆኑ ይችላሉ። ይህ ሁኔታ ደግሞ የለውጥን ሁኔታ ሌላ ችግር ወይም ቀራኒ ውስጥ ይከተዋል። ይህ ቀራኒም በአዲስ የለውጥ የእድገት ደረጃ ይፈታል። ይህን ቀጥሎ እንመለከታለን።

ኅብረተሰብ እያደገና እየደረጀ ሲሄድ፣ የምርት ኃይሎች ይበልጥ እየዳበሩ በተለይም በነሐስና ብረት መገኘት ምክንያት የእደ ጥበብና የእርሻ ሥራ ይበልጥ እየተለየና እየሰፋም ሲሄድ ምርት በዓይነትም ሆነ በጥራት እየጨመረ ገበያን እያሰፋው ይሄዳል። ይህም ለውጥ በሁለት ሰዎች ወይም በሁለት መንደሮች ብቻ መወሰኑ ቀርቶ በጣም ብዙ በሆኑ ሰዎች፣ መንደሮችና አገሮች መካከል እንዲካሄድ ያስችላል።

ይህ የእድገት ደረጃ በተራውም በሁሉም ስፍራና አገሮች በሁሉም ሰዎች ዘንድ ተቀባይነት የሚኖረው አንድ የጋራ መገበያያ መገኘትን ያስገድዳል። የሁለንታዊ አቻያ ሚና ከአንዱ ሸቀጥ ጋር በመያዝ የሸቀጦችን ለውጥ በማንኛውም ሥፍራና ጊዜ ሊያገለግል የቻለበት ደረጃ ላይ ሲደርስ አቢት የገንዘብ መልክን ሊይዝ በቃ።

በገንዘብ እድገት ሂደት ውስጥ በመጀመሪያ ወቀት ላይ እያሌ የተለያዩ ብረታ ብረትና ነጠቦች እንደ ገንዘብ አገልግለዋል። በመጨረሻው ግን ውድ በሆኑት የማዕድን ውጤቶች ማለትም በወርቅና በብር ላይ ብቻ ሊቆናጠጥ ችሏል። ይህም ያለ ምክንያት አይደለም። ወርቅና ብር ውድና ብርቅ ናቸው። ለመከፋፈል፣ ለመሸረፍ፣ ጥራታቸውን ሳይለውጡ ብዙ ጊዜ ለመቆየት፣ የሚያስችል ባሕርይ አላቸው። ወርቅና ብርን ለማምረት

የሚወጣባቸው የሥራ ኃይል ከፍተኛ በመሆኑ ከፍተኛ ለቤት አሳቸው:: ወርቅና ብር ለብዙ ዘመናት ሁለቱም እንደ ሁለንታዊ እኩያ ቢያገለግሉ ቆይተው አንድ ሸቀጥ የልውውጥ አማካይ መሆኑ ይበልጥ ተፈላጊ እየሆነ በመጣ ወርቀ ብቻውን ይህን ሚና መጫወት ጀመረ:: ይህ የለቤት የገንዘብ መልክ ይባላል::

ለቤት የገንዘብን መልክ በያዘበት ሁኔታ የማና ቸውም ሸቀጥ ለቤት በአንዱ ሸቀጥ የጠቀሜታ ለቤት ሲገለጥ በመቻሉ ሁሉንታዊ ለኩያ በአንዱ ሸቀጥ ማለትም በወርቀ ለክናወን ተችሏል:: ገንዘብ ብቅ ያለው እንግዲህ ከላይ በዝርዝር እንዳየነው በረጅም ጊዜ የልውውጥ ለዕገት ሂደትና በዚህም ባቢያ በየጊዜው በታየው የለቤት መልክ መለዋወጥ ነው:: በገንዘብ ብቅ ማለትም የተነሳ ሸቀጦች በሁለት ወገን ሲከፈሉ በቀ ተዋል:: በአንደኛው ወገን አያሌ ሸቀጦች ሲገኙ በሌላው ወገን ደግሞ አንድ ሸቀጥ ብቻ ማለትም ገንዘብ/ወርቀ/ ይገኛል:: በዚህም ምክንያት በአንዱ ወገን በብዛት የሚገኙት ሸቀጦች ሁሉ ለቤታቸውን በሌላው ወገን ባለው ሸቀጥ ማለትም ገንዘብ /ወርቀ/ ይገልጧሉ:: በለዚህም ገንዘብ ከሌሎቹ ሸቀጦች ተለይቶ ብቻውን በመቆም ሁለንታናዊ ለኩያ በመሆን ያገለግላል:: ማንኛውም ዓይነት ሸቀጥ በገንዘብ ይለወጣል:: ይህ ልዩ የሆነ የገንዘብ ባሕርይ ሁሉንም የሸቀጥ ባለቤት የሚያረካ ነው:: የሁሉንም በው የተለያየ ፍላጐትም ያረካል:: ሌሎች ሸቀጦች ግን የተወሰነ ፍላጎት ብቻ ነው ሊያረኩ የሚችሉት:: ለምሳሌ በገንዘብ ምግብ፣ የልጆች ደብተርና ጥብቆ፣ ጫማ፣ ልብስ፣ ቤት ወዘተ...መግዛትና የተለያየ ፍላጎትን ማሟላት ቢቻል፤ ምግብ ወይም ልብስ ወይም ሌላ ሸቀጥ የተወሰኑ ፍላጐቶችን ብቻ ነው ሊያሟሉ የሚችሉት::

ለማጠቃለል እንግዲህ ገንዘብ /ወርቀ/ ራሱ ሸቀጥ ነው:: ሸቀጥ በመሆኑ ግን ከሌሎች ሸቀጦች የሚለይበት ባሕርይው የሁሉም ሸቀጦች ለቤት የሚገለጥበት ሁለንታዊ ለኩያ ነው:: ገንዘብ ሸቀጥ እንደመሆኑም ማኅበራዊ ሥራ የፈሰሰበትና በሸቀጥ አምራቾች መሃል ያለውን የምርት ግንኙነትንም የሚገልጽ ነው:: ከገንዘብ መከሰት ጋር የሸቀጦች ለቤት ለመጀመሪያ ጊዜ በቀጋ አማካይነት

ሲገለጽና የሸቀጦች የቀጥታ ልውውጥም ተርታ ሸቀጦች በገንዘብ አማካይነት
እንዲለዋወጡ አስችሏል::

## 2. <u>የገንዘብ ተግባራት</u>

ከፍ ብለን የገንዘብን አመጣጥ ባጭሩ ተመልክተናል:: ገንዘብ በበ
ዎች መሐከል በፍላጐትና በስሜት ወይም በመንግሥት ዉንጋጌ ምክንያት ብቅ
ያለ ነገር ሳይሆን በሸቀጥ ምርት እድገትና በሸቀጦች ልውውጥ መስፋፋት ሂደት
ዉስጥ ብቅ ያለ <u>ማህበራዊ ክስተት ነው</u>::ወርቅ የሌሎችን ሸቀጦች ለቤት መለ
ካት መቻሉ በተፈጥሮ የተቀዳጀው ባህርይው አይደለም:: በሕብረተሰብና በሕብ
ረተሰብ የኢኮኖሚ ግንኙነት እድገት አማካይነት የተሰጠው ተግባር ነው:: በለ
ሆነም ገንዘብ /ወርቅ/ ከሌሎች ሸቀጦች ሁሉ ልዩ ሸቀጥ በመሆን የሌሎች ሸቀ
ጦችን እሴት በመግለጥ ሁለንታዊ አኩያ ሆኖ ብቻውን ሊወጣ ችሏል:: በዚህም
ምክንያት በሸቀጥ ምርት እድገት ሂደት ዉስጥ የገንዘብ መከሰት ሸቀጦችን በሁ
ለት ከምኝ ሊከፍላቸው እንደቻለ ከፍ ብሎ ተመልክቷል:: ባንዱ በኩል ሁለን
ታዊ አኩያ ያለው ሸቀጥ ማለትም ገንዘብ ሲገኝ በሌላ በኩል ደግሞ ሌሎች
ሸቀጦች ሁሉ ይገኛሉ:: በሸቀጦች የዝውውር ሂደት ሸቀጦች በገንዘብ አማካይ
ነት ብቻ እንጂ በሌላ ሸቀጥ ሊለወጡ አይችሉም:: በለሆነም ገንዘብ በአምራ
ቶች መሐከል ያለውን ማኅበራዊ ግንኙነት የሚወክን ሁለንታዊ የጋራ መገበያያ
ለመሆን በቃ:: ገንዘብ በታሪክ የተወሰነ በሸቀጥ አምራቶች መካከል ያለውን
የኢኮኖሚ መተባበር የሚገልጽ ማህበራዊ ግንኙነት ነው:: በተጨማሪም ገንዘብ
በገበያ አማካይነት ሸቀጥ አምራቶች ያፈሰሱትን የሥራ ኃይል መጠንና ጥራት
ግብታዊ በሆነ መንገድ ለማወቅ ያስችላል::

የሸቀጥ ምርት እየጎለበተና እየሰፋ ሲሄድ ገንዘብ የሚያሟላቸውም ተግ
ባሮች እንዲሁ እየሰፉና እያደጉ ሄደዋል:: በዳበረ የሸቀጥ ምርት ዉስጥ

ገንዘብ አምስት ተግባራት አሉት እነዚህም:-

1. የእሴት መለኪያነት
2. የዝውውር አማካይነት
3. የክምችት መሣሪያነት
4. የክፍያ መሣሪያነት
5. ዓለም አቀፍ የክፍያ መሣሪያነት ናቸው::

## 2.1 ገንዘብ እንደ እሴት መለኪያነት

የገንዘብ ዋነኛና መሠረታዊ ተግባር የሸቀጦች እሴት መለኪያ ሆኖ ማገልገሉ ነው:: የአንዱን ሸቀጥ እሴት ሸቀጡን ለማምረት በፈጀው የሥራ ጊዜ አማካይነት በቀጥታ ለመተመን አይቻልም:: ምክንያቱም እያንዳንዱ ሸቀጥ አምራች የሚሠራበት ሁኔታ አንዱ ከሌላው በተለያየና አንዱ ከሌላው በተገለለ መንገዱ በለሆነ አንዱ አምራች የተወሰነ ሸቀጥ ለማምረት የሚያውለውን ሥራ ወይም ጉልበት ለመመጠን አይቻልም:: ታዲያ እንዴት ነው የአንዱ ሸቀጥ እሴት የሚታወቀው? ቀደም ብለን በለዚህ ነገር አንስተን የአንዱ ሸቀጥ እሴት የሚገለጠው በሸቀጦች መሃል በሚደረግ የልውውጥ ሂደት ውስጥ ነው ብለን ነበር:: አንዱ ሸቀጥ በሚመረትበት ወቅት እሴቱን በቀጥታ መተመን ካልተቻለ እንግዲህ በልውውጥ ሂደት ውስጥ በሸቀጦች መሃከል በሚደረግ ልውውጥ በተዘዋዋሪ መን-ገዱ እሴቱ ሊገለጥ ይችላል ማለት ነው:: በልውውጥ እድገት ሂደት ውስጥ ደግሞ አንዱ ሸቀጥ ማለት ገንዘብ ሁለንተናዊ ለኪያ እንደሆነና የሁሉም ሸቀጦች እሴት በገንዘብ ሊገለጥ እንደቻለ ተመልክተናል:: በለዚህ የሸቀጥ እሴት ከገንዘብ ጋር በሚደረግ የልውውጥ ሂደት ውስጥ ይከሰታል ማለት ነው:: ይህም ሁኔታ በገንዘብ ረዳትነት የያንዳንዱ የሸቀጥ አምራች ሥራ ማኅበራዊ በሆነ

መንገዱ እንዲገለጥ ያግዛል::

ገንዘብ/ወርቅ/ የእሴት መለኪያ ለመሆን በቀዳሚያ ራሱ እሴት ያለው ሸቀጥ መሆን ይኖርበታል:: አንድ ሰው የክብደቱን መጠን ራሳቸው ክብደት ባላቸው መለኪያዎች ተጠቅሞ እንደሚለካ ሁሉ የእሴት መለኪያም ራሱ እሴት ያለው መሆን ይገባዋል:: ቀደም ብለን እሴት የገንዘብ መልክን ያገኘው ሁሉም ሸቀጦች በወርቅ አማካይነት መለዋወጥ በጀመሩበት የዕድገት ደረጃ ነው ብለናል:: ወርቅ ደግሞ ራሱ እሴት ያለው ሸቀጥ ነው:: በመሆኑም የሸቀጦች የእሴት ልክ ሸቀጦቹ ከገንዘብ ጋር በመለዋወጣቸው አስቀድሞ በወርቅ አማካይነት ሲተመኑ ወይም ሲታወቁ ይችላሉ:: ስለሆነም የሸቀጦችን እሴት በገንዘብ ለመተመን አንድ ሰው በቀዳሚያ በእጁ ጥሬ ገንዘብ የግድ እንዲኖረው አያስፈልገም:: የአንድ ሸቀጥ ልክ ለመተመን የሸቀጡ ባለቤት በሃሣቡ፣ በአእምሮና በረጅም ጊዜ የልውውጥ ልምዱ የሸቀጡን እሴት በተወሰነ የወርቅ መጠን ይወስናል:: ለምሳሌ 40 ኪሎ ስንዴ 3 ግራም ወርቅ ይሆናል ብሎ ይወስናል:: ይህ ሲሆን የሚችለውም ሁለቱንም ሸቀጦች ለማምረት አስፈላጊ የሆነ ማኅበራዊ ሥራ በሁለቱም ላይ ፈሷልና ነው:: ይህ ሁኔታ በሸቀጦች እሴት መሀከል ተጨባጭ የሆነ ግንኙነትን ይፈጥራል:: የአንድ ሸቀጥ እሴት በገንዘብ ሲተመን የሸቀጡ ዋጋ በመባል ይታወቃል:: ዋጋ የሸቀጦች እሴት በወረቀት፣ በሸርፍራፊ ወርቅ፣ ብር፣ ነሐስ፣ ኒኬል ወዘተ.. ባንኮች የሚገለጥበት ነው:: ስለ ወረቀት ገንዘብ በዝርዝር ወደ ኋላ እንመለከታለን::

የሸቀጦች እሴት በተወሰነ የወርቅ ወይም የገንዘብ መጠን ይገለጻል ወይም ይለካል:: ገንዘብ ይህን ተግባር ከማሟላቱ በፊት ግን ራሱ

በመበጣጠስ በምትኩ የገንዘብ ግንኙነት እንዲስፋፋ፣ ትላልቅና ዘመናዊ ከተሞች
እንዲቆረቆሩ፣ የፊውዳል የግዛት መከፋፈል በማዕከላዊ አስተዳደር እንዲተካና
ብሔረ-መንግሥታት እንዲቋቋሙ፣ ከዚያ ቀደም ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ የምርት
ኃይሎች በከፍተኛ ደረጃ እንዲያድጉ አድርጓል::

ካፒታሊዝም በተለያዩ ወቅቶች የተከፈለ ቢሆንም/ማለትም በነፃ ውድድርና
በሞኖፖል ካፒታሊዝም/ እነዚህ ሁሉ የካፒታሊስቱ ሥርዓተ ማኅበር የዕድገት ደረ
ጃዎች እንጂ ከካፒታሊስት ሥርዓት ውጭ ያሉ ወቅቶች አይደሉም:: በነዚህ በካፒ
ታሊዝም የተለያዩ የዕድገት ወቅቶች የአመራረቱ ሁኔታና ተቋም፣ ተረፈ እሴት የማ
ጋበሱ ዘዴ ቢለያይም፣ የካፒታሊስቱ ሥርዓት መሠረታዊና ዓይነተኛ መገለጫዎች የሀ
ኔት የሸቀጥ ምርት፣ የምርት መገልገያዎች በግል ባለቤትነት ሥር መያዝ፣ የሥራ
ኃይል በካፒታል መበዝበዝ አይቀየሩም::

ካፒታሊዝም በውስጡ መሠረታዊ የሆኑ ቅራኔዎችን ያዘለ ሥርዓት ነው::
የሥርዓቱም መሠረታዊ ቅራኔ ማኅበራዊ በሆነ የአመራረት ዘይቤ የሚመረተውንና
የሠራተኛው መደብ የሥራ ውጤት የሆነውን ሃብት በግል በማጋበስ መካከል የሚነሳ
ቅራኔ ነው:: ይህም ሁኔታ የምርት ሥርዓተ አልበኝነትን፣ ሥራ አጥነትን፣ የኢኮኖ
ኖሚ ቀውስን፣ ብሎም በሥርዓቱ መሠረታዊ መደቦችና ማኅበራዊ ክፍሎች መካከል የማ
ይታረቅ ቅራኔን ያስከትላል:: የካፒታሊዝም መሠረታዊ ቅራኔዎች በየጊዜው እየከረሩ
መምጣታቸው የካፒታሊዝምን መዳከምና ሟች መሆኑን፣ እንዲሁም ታሪካዊ ውስንነቱና
በሶሺያሊዝም የሚተካ መሆኑን ያበስራሉ::

በየካቲት 1966 የፈነዳው የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮት የብሔራዊ ዲሞክ
ራሲያዊ አብዮት ፕሮግራምን በማካሄድ ላይ የሚገኝ እንደመሆኑ የካፒታሊስት የኢ
ኮኖሚ ህጋጋት ወርሰው አልተወገዱም፣ በአነስተኛ የሸቀጥ አምራችነትና በካፒታሊስቱ

በተወሰነ ክብደት ወይም መጠን መለኪት አሰበት፡፡ ቴክኒካዊ መመዘኛ በመሆን
በተወሰነ የገንዘብ ዉሀዳና ክፍልፋዮች ዉስጥ ያለውን የወርቅ መጠን ለመለ
ከት የምንገለገልበት፤ የዋጋ ደረጃ በመባል ይታወቃል፡፡ የዋጋ ደረጃ መለ
ኪያ በሚወሰንበት ጊዜ ያ የተወሰነ የዋጋ ደረጃ በሚወክለው የወርቅ መጠን
ዉስጥ ካለው እሴት ጋር እኩል ነው ማለት አይደለም፡፡

ለምሳሌ በእንግሊዝ አገር የገንዘብ መመዘኛ ዉህዳ ፓዉንድ ስተ
ርሊንግ፤ በአሜሪካ ዶላር፤ በሩስያ ሩብል፤ በፈረንሣይ ፍራንክ፤ በኢት
ዮጵያ ብር ወዘተ... በሚል የተለያየ መጠሪያ ይታወቃል፡፡ እነዚህ የገ
ንዘብ መመዘኛ ዉህዳዎች የተወሰነ የወርቅ ክብደት ልክን የሚያመለክቱ ናቸው፡፡
ለልዉዉጥ አመቺ እንዲሆኑ ለማድረግም በክፍልፋይ ይዘረዘራሉ፡፡ ብር በመቶ
ሣንቲም፤ ዶላር በመቶ ሣንቲም፤ ሩብል በመቶ ኮፔክ ወዘተ... ይከፋፈላሉ፡፡

ገንዘብ እንደ ዋጋ ደረጃ መለኪያ ሲወሰድ እንደ እሴት መለኪያ
ከሚያገለግልበት ሁኔታ ፈጽሞ የተለየ ነው፡፡ ቀደም ብለን እንደተመለከትነው
ገንዘብ የእሴት መለኪያ በሚሆንበት ጊዜ የሸቀጦችን እሴት ነው የሚለካው፡፡
ይህም ማለት አንዱን ሸቀጥ ለማምረት አስፈላጊ የሆነውን ማኅበራዊ የሥራ
ጊዜ መጠን ይገልጧል ማለት ነው፡፡ የዋጋን ደረጃ በሚወሰንበት ጊዜ ግን
የራሱን የገንዘብን /የወርቅን/ መጠንና በክፍልፋዮቹ ዉስጥ የታቀፈውን የወ
ርቅ መጠን ብቻ ለመለካት ያገለግላል፡፡

የሸቀጦች እሴት ገንዘብን/ወርቅን/ ለማምረት በሚወሰደው ማኅበራዊ
የሥራ ጊዜ መጠን ከፍና ዝቅ ሊል ይችላል፡፡ ይህ ሁኔታ ግን በገንዘብ የዋጋ
ደረጃ መለኪያ ላይ አይንፀባረቅም፡፡ የገንዘብ /የወርቅ/እሴት ምንም ያህል
ከፍና ዝቅ ቢልም አንዱ ብር ሁልጊዜ አንዱ ብር ነው ወይም 100 ሣንቲም ነው

ለምሳሌ 40 ኪሎ ስንዴን ለማምረት የሚወስደው ማኅበራዊ አስፈላጊ የሥራ ጊዜ 3 ግራም ወርቅ ለማምረት ከሚወስደው አስፈላጊ ማኅበራዊ የሥራ ጊዜ ጋራ እኩል ነው እንበል:: በአንድ ብር ውስጥ ግማሽ /$\frac{1}{2}$/ ግራም ወርቅ ታቅፏል ብንል፣ 40 ኪሎ ስንዴ ለመግዛት፣<

| | | |
|---|---|---|
| $\frac{1}{2}$ ግራም | ወርቅ | 1 ብር |
| 3 " | " | ? |

3×1×2 = 6 ብር ያስፈልጋል ማለት ነው::

አዳዲስ የማምረት ዘዴንና ቴክኖሎጂን በመጠቀም 3 ግራም ወርቅ ለማምረት የሚፈጀው አስፈላጊ ማኅበራዊ ሥራ ጊዜ 4 ግራም ወርቅ ለማምረት ቢቻል የወርቅ ጠቅላላ ምርት ይጨምራል:: በሌላ በኩል ስንዴን ለማምረት አስፈላጊ የሆነው የሥራ ጊዜ ባለመቀነሱ የስንዴ አቅርቦት ካልተለወጠ ተጨማሪው የወርቅ ምርት/ማለትም ተጨማሪው የመግዛት ኃይል/ በስንዴ ዋጋ ላይ ለውጥ ያስከትላል:: በአንድ ብር ውስጥ ግማሽ ግራም ወርቅ ቢታቀፍ 40 ኪሎ ስንዴ ለመግዛት:-

4×1×2= 8 ብር ያስፈልጋል ማለት ነው::

በዚህ ምሳሌያችን መሠረት የገበያው ዋጋ ከፍ ማለቱን ከማየታችን በስተቀር የገንዘብ መመዘኛ ውህዳዎች ክፍልፋዮች ማለትም አንድ ብር መቶ ሣንቲም መሆኑ ወይም በገንዘብ የዋጋ ደረጃ መለኪያ ላይ ለውጥ አለመታየቱን እንገነዘባለን:: ይሁን እንጂ የወርቅ ዋጋ በመርከሱ ምክንያት በገበያ ላይ የሸቀጦች ዋጋ መናርን ሊያስከትል ችሏል::

መንግሥት በገንዘብ የመመዘኛ ውህዳና በክፍልፋዮቹ ውስጥ የሚታቀፈውን የወርቅ መጠን ሊቀንስ ወይም ሊጨምር ይችላል:: ይሁን እንጂ በወርቁና በሌሎች ሸቀጦች መካከል ያለውን የእሴት መጠን ዝምድ ለመቀያየር አይቻለውም:: ይህ ማለት ግን የሥራን ምርታማነት በመጨመር በተወሰነ ማኅበራዊ ተቀባይነት ባለው የሥራ ጊዜ ውስጥ ተጨማሪ የወርቅ ወይም ሌላ ሸቀጥ ማምረት አይቻልም ማለት አይደለም::

መንግሥት በገንዘብ የመመዘኛ ውህዳ በክፍልፋዩቹ ውስጥ የሚታቀፈውን የወርቅ መጠን ቢቀያይር የገበያውም ሁኔታ በዚሁ መሠረት ይቀያየራል:: የወርቁን መጠን ቢቀንስ በገበያው ውስጥ ያለው ዋጋ ከፍ ይላል::

ለምሳሌ በአንድ ብር ውስጥ የታቀፈው የወርቅ መጠን ግማሽ /$\frac{1}{2}$/ግራም ከመሆን ፋንታ አንድ አራተኛ /$\frac{1}{4}$/ ግራም ቢሆን 40 ኪሎ ስንዴ ለመግዛት በፊት ስድስት ብር የነበረው አሁን:-

$$3\times1\times4 = 12$$ ብር ይሆናል ማለት ነው::/

እንግዲህ በዚህኛውም ሆነ በመጀመሪያው ምሳሌያችን መሠረት ተጨማሪ ብሮች ማስፈለጋቸውን እንጂ በምርታማነትም ሆነ በመንግሥት ውሣኔ ምክንያት የሚፈጠረው የገበያ ውጣ ውረድ በገንዘብ የዋጋ ደረጃ መለኪያ ባይ ምንም ለውጥ እንዳላመጣ ለመረዳት ችለናል::

## 2.2 ገንዘብ እንደ ዝውውር አማካይነት

በገንዘብ አማካይነት/ረዳትነት/ የሚካሄደው የሸቀጦች ለውጥ የሸቀጦች ዝውውር በመባል ይታወቃል:: የሸቀጦች ዝውውር ከገንዘብ ዝውውር ጋር

በጥኑ የተቆራኘ ነው:: አንዱ ሸቀጥ ከሻጩ እጅ ወጥቶ ወደ ገዥው እጅ ሲገባ ገንዘቡም በዚያው ከገዥው እጅ ወጥቶ ወደ ሻጩ እጅ ይገባል:: የገንዘብ የልውውጥ የአማካይነት ተግባርን በሸቀጦች ልውውጥ ለማከናወን የሚ ዳሰስ፣ የሚጨበጥ የሚታይ ገንዘብ መኖር አለበት:: ምን ማለታችን እንደሆነ ቀጥለን እናያለን::

○ የገንዘብ መልክ እየተለዋወጠ መጥቶ ዛሬ ባለበት ሁኔታ ላይ ከመ ገኘቱ በፊት በመጀመሪያ የሸቀጦች ልውውጥ ወቅት ላይ ገንዘብ በወርቅ ወይም በብር ጥፍጥፍ መልክ ጥቅም ላይ ይውል ነበር:: ገዥና ሻጭ ሸቀጥ ለመለዋ ወጥ ሲፈልጉ ይህንን የወርቅ ወይም የብር ጥፍጥፍ መመዘን፣ ወደ ትናንሽ መጠን መቆራረጥና በዚህ መልክም ቲመን ማድረግ አስፈላጊ በለነበር ችግር ማስከተሉ አልቀረም:: ቀስ በቀስ ይህ ለልውውጥም ሆነ ለአያያዝ አስቸጋሪ የነበረው የወርቅ ወይም የብር ጥፍጥፍ በሣንቲም እየተተካ ሄደ:: ሸርፍራፊ፣ አነስተኛ የማዕድናት ዓይነት ሆኖ የተወሰነ ቅርጽ ክብደትና በላዩ ላይ የተወሰነ ቲመን የተፃፈበት ነው፣ ከወርቅ፣ ከብር፣ ከነሐስ፣ ከመዳብ ወዘተ.. የተሠራ የሸቀጥ ልውውጥ አማካይ ሆነ::

በልውውጥ ሂደት ወቅት ሣንቲሞች ከእጅ ወደ እጅ ብዙ ጊዜ በመዘዋ ወር፣ እርስ በርስ በመተሻሸት፣ በመላሳግ፣ ለአየርም ጠባይ በመጋለጥ ማርጀት፣ መዛግና ማለቅም ይደርስባቸዋል:: ከረጅም ዘመናት የገንዘብ ልውውጥ ሂደት በተገኘው ልምድ መሠረት ሣንቲሞች ቢያረጁም አዲስ ሣንቲሞች ካላቸው እሴት እኩል እንደ ልውውጥ አማካይ ጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላሉ:: በመሠረቱ አንዱ ሻጭ ሸቀጡን በገንዘብ ሲለውጥ ባገኘው ገንዘብ እሱም በተራው ሌላ ሸቀጥ ለመ ግዛት እንዲችል ነው:: ስለሆነም ገንዘብ እንደ ልውውጥ አማካይ ጥቅም ላይ ሲውል የግዴታ ተገቢ እሴቱን መያዝ የለበትም:: የገንዘብ የማርጀትና የማለቅ ጠባይ ያስከተለው ይህ ሁኔታም መንግሥታት ቀስ በቀስ የሣንቲሞችን ክብደት መቀነስ፣ ቅርፃቸውንና መጠናቸውን ማሣነስ እንዲችሉ ረዳቸው:: ይህ የመቀነስ ሁኔታ ግን ሣንቲሞች የሚወክሉትን እሴት መጠን አይቀንሰውም:: ምክንያቱም

ባንኮች የሚወክሉትን የእሴት መጠን ሙሉ በሙሉ የያዙ በማስመሰል በሲያቸው ላይ በሚፅፍባቸው የሠን መጠን የሚገለጥ በመሆኑ ነው፡፡ ይህ ሁኔታ ይበልጡኑ ሣንቲሞች ቀስ በቀስ የእሴት ምልክት ወይም የገንዘብ መግለጫዎች ብቻ ወደመሆን ለውጧቸዋል፡፡ እውነተኛ እሴታቸው በምልክትነት ከሚታዩባቸው በጣም ያነሰ ነው፡፡

ገንዘብ እንደ ዝውውር የሚጫወተውን ሚና በናጠና ልንመለከተው የሚገባ አንድ አቢይ ጉዳይ አለ፡፡ ይህም የግል ሀብት በበፈነበት ኅብረተሰብ ውስጥ ለሚታየው ቀውስ አንዱ ምክንያት በለመሆኑ ነው፡፡

የሸቀጦች በሁለት ክምኘ መክፈል ማለትም በገንዘብና በሌሎች ሸቀጦች መከ መከፋፈል የሸቀጥ ምርትን ቀራኒ ቀዜማ ያስከተለ ክስተት ነው፡፡ አንዱ ሸቀጥ በሌላ ሸቀጥ በቀጥታ ይለወጥ በነበረበት ወቅት አያንዳንዱ የልውውጥ አርምጃ ከልውውጡ በኋላ ወዲያውኑ የሚያከትም ነበር፡፡ ይህም ማለት መሸጥና መግዛት አንድ ጊዜ የሚከናወኑና እዚያም ላይ የሚያበቁ በመሆናቸው አንዱ ከሌላው የተለየ አልነበረም፡፡ ልውውጥ እያደገ ሄዶ ገንዘብ የሸቀጥ ዝውውር አማካይ በሆነበት ወቅት ግን ሁኔታው የተለየ ሆኗል፡፡ አሁን ልውውጥ በሸቀጥ አምራቾች መካከል የማያቋርጥ የንግድ ውልና ስምምነት የሚያካሂዱበት መስክ ሆነ፡፡ ይህም በበኩሉ የመሸጥንና የመግዛትን ተግባር ሊለያያቸው በቃ፡፡ አንድ የሸቀጥ አምራች ሸቀጡን ከሸጠው በኋላ ገንዘቡን ለተወሰነ ጊዜ ይዞት ሊቆይ ይችላል፡፡ ምክንያቱም ሸቀጡን የሸጠው በጊዜው የሚፈልገው ነገር ኖሮ ባይሆን ወደፊት የሚፈልገውም ነገር ቢኖር ገንዘብ ካለው በፈለገው ጊዜ ወይም ፍላጎቱ በሚያስገድደው ጊዜ ሊገዛ ስለሚችል ነው፡፡ ብዙ ሸቀጥ አምራቾች ሸቀጣቸውን እየሸጡ ገንዘቡን ሌላ ሸቀጥ ባይገዙ ቢያስቀምጡት ባይሸጡ የሚቀሩ የሸቀጥ ክምችቶች ሊፈጥር ይችላል፡፡ በሌላ በኩል ሸቀጥ ገዢዎች ከሸቀጥ አቅርቦትም በላይ ለግዢ የሚሯሯጡበት ጊዜ ሊፈጠር ይችላል፡፡ ይህ ከመግዛት የመገታትና ሉላ ጊዜ ደግሞ

ለመግዛት የመሸቀጻደም ሁኔታ በሸቀጥ ዝውውር ሂደት ውስጥ የሚኖረውን ቅራኔና የሚያስከትለውን ቀውስ ያመለክታል:: በዚህ ሁኔታ ይበልጥ የሚጎዱትና ከምርት ሂደት ውስጥ የሚገለሉት አነስተኛ ሸቀጥ አምራቾች ይሆናሉ:: እርግጥ ይህ ሁኔታ ሙሉ በሙሉ ግልህ ሆኖ ለመታየት የበዙ ነገሮችን መሟላት ከመጠየቁም በላይ በካፒታሊስት ሥልተ ምርት ውስጥ የሰለተ ተሰለት ክስተት ነው :: የሸቀጥ ዝውውር የሚፈጥረውን የኢኮኖሚ ቀውስ በሌላ በፍራ በዝርዝር እንመለከታለን ::

## 2.3 ገንዘብ እንደ ክምችት መሣሪያነት፣

ገንዘብ ከዝውውር ሂደት ውጭ ቢሆን ወደ ክምችት ይለወጣል፣ ይጠራቀማል:: ገንዘብ በማንኛውም ጊዜ ወደ ማንኛውም ዓይነት ሸቀጥ ሊለወጥ የሚችል በመሆኑ የሀብት ሁለንታዊ እኩያ ጠባይ አለው:: በማንኛውም ዓይነት መጠን ሊቆጥ ይችላል:: አምራቾች ገንዘብን የሚያጠራቅሙት ወይም የሚያከማቹት የምርት መሣሪያዎች ለመግዛት ወይም ለቁጠባ ነው:: የሸቀጥ ምርት እየዳበረ ቢሄድ የገንዘብ ጥቅምና ኃይሉም እየዳበረ መጥቷል:: እነዚህ - ሁኔታዎች ገንዘብን ለማከማቸት፣ ለማጠራቀም፣ ለመቆጠብ መንገዱ ጠረጉ፣ በር ከፈቱ፣ ኋላ ከፍተኛ ስግብግብነትን፣ ገንዘብ መቀበርን፣ መደበቅን፣ ማፈንን አስከትሉ:: ገንዘብን ለማንኛውም ዓይነት ምክንያት ቢሆን የመደበቅ፣ የመቀበር፣ ተግባር ሙሉ በሙሉ ሊከናወን የሚችለዉ ሙሉ እሴትን በያዘ ገንዘብ ማለትም በወርቅ/ወይም በብር/ ሸርፍራፊ ወይም ጥፍጥፍ ወይም ከወርቅ በተሰሩ ቁሳቁሶች፣ ነገሮች/እቃዎች/ ነው:: ሌሎቹ የእሴት ምልክቶች ወይም የገንዘብ መግለጫዎች ማለት ሸርፍራፊዎች የወረቀት ምልክቶች ወይም የገንዘብ መግለጫዎች በመሆናቸው በደበቁ፣ ቢቀበሩ ለተወሰነ ጊዜ ብቻ ነው፣ ተደብቀውና ተቀብረው ለብዙ ጊዜ አያገለግሉም፣ ይሻገታሉ፣ ይበላሻሉ::

የሸቀጥ ምርት ሲቀንስና በዚህም ምክንያት የሸቀጥ ዝውውር ጋብ ቢል በገበያ ላይ ይዘዋወር የነበረው የወርቅ ሽርፍራፊ ይጠፋና ወደ ክምችት ወደ ጥርቅም ይለወጣል። በአንጻሩ ደግሞ የሸቀጥ ምርት ጨምሮ የሸቀጥ ዝውውርም ሞቅ ሞቅ ቢል ወደ ክምችትና ወደ ጥርቅም የተለወጡት ሽርፍራፊዎች ብቅ ብለው መዘዋወር ይጀምራሉ።

የሸቀጥና የገንዘብ ግንኙነት መዳበርና በዚህም ምክንያት የገንዘብ ኃይል አንድ ደረጃ ላይ በደረሰበት ጊዜ ገንዘብን አጠራቅሞና አፍኖ መያዝ ብቻ በራሱ ወባኝ እንደሆነ አድርገው የሚገምቱ ሰዎች ታይተዋል። ገንዘብንም ከዝውውር ውጭ ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት የሚያደርጉም አልታጡም። ይህ ኋላቀር የሆነ የገንዘብ ደባቂዎችና በግብግቦች ገንዘብን ከዝውውር የማሸሽና የመቀበር ተግባር በካፒታሊዝም ሥልተ ምርት ውስጥ ለምብዛም ሥፍራ የለውም። የካፒታሊስት ሥልተ ምርት ኋላ ቀር የሆነውን የገንዘብ መቀበር በዳበረ የካፒታሊስት ክምችት በመተካት ለሸቀጦችና ለገንዘብ ዝውውር አመቺ ሁኔታን በመፍጠር የሸቀጥ ምርትን ለማለዋወጥ ረድቷል። በዚህም ገንዘብን ከኋላ ቀር አጠቃቀም በማላቀቅ ገንዘብ ይበልጡኑ በዝውውር ውስጥ እንዲገኝ አድርጓል። ይሁንና በአሁኑ ጊዜም ቢሆን በካፒታሊስቱ ኢኮኖሚ ውስጥ ቀውስ በሚነሳበት ጊዜ በተለይም ገንዘብ በሚረክስበት ወይም የዕቃ ዋጋ በሚንርበት ወቅት ካፒታሊስቶች በወረቀት ገንዘብ ላይ እምነት ስለሚያጡ ወርቅ ገዝተው ለማካበት ይሯሯጣሉ። በአብዛኞቹ አገሮች ወርቅ የማጠራቀም ሥልጣን ያለው የሀገሩ ማዕከላዊ ባንክ ቢሆንም ካፒታሊስቶች ከዚሁ ውጭ ወርቅ ያባዷዳሉ። ሁኔታው ቢለወጥ ወይም ቢሻሻል ወርቁ እንደገና መዘዋወር ይጀምራል።

## 2.4 ገንዘብ እንደ ክፍያ መሣሪያነት፡

በሸቀጥ ምርት ሂደት ውስጥ በሚከሰቱት ልዩ ልዩ ምክንያቶች ሸቀጦችን የመግዛትና የመሸጥ ተግባር በዱቤ ይከናወናል። በዚህ ጊዜ

ከሻጩ ወደ እቃ ገዥው የሚደረገው የሸቀጡ መተላለፍ ወዲያውኑ ክፍያ አያስከትልም:: ክፍያው ለሌላ አመቺ ጊዜ ይተላለፋል:: የክፍያው ጊዜም ሲደርስ ገዥው ገንዘብ ለሻጩ ቢሰጥ ሸቀጡ አይኖርም:: ምክንያቱም ሸቀጡ ቀደም ብሎ ከሻጩ ወደ ገዥው ተላልፏልና:: ስለሆነም ዱቤው በሚከፈልበት ወቅት ገንዘብ እንደ ዝውውር አማካይ ሳይሆን እንደ ክፍያ መሣሪያነቱ ጥቅም ላይ ዋለ ማለት ነው:: ገንዘብ ከሸቀጥ ልውውጥ ወይም ዝውውር በተጨማሪም እንደ ክፍያ መሣሪያነትም ያገለግላል:: ለምሳሌ ለታክስ ለልዩ ልዩ ኪራዮች ዓይነት ለቤት፣ ለእቃ፣ ወዘተ...ገንዘብ ለክፍያ ብቻ ይጠቀማል::

ገንዘብ እንደ ክፍያ መሣሪያነቱ ጥቅም ላይ መዋሉ በሸቀጥ ምርት ኢኮኖሚ ውስጥ ለሚታየው ቅራኔ ተጨማሪ አስተዋጽኦ ያደርጋል:: በተለያዩ ሥፍራዎች የተለያዩ ሸቀጦችን በሚያመርቱ ሰዎች መካከል ያለው መቆራኘትና አንዱ በአንዱ ላይ የሚኖረው መፈላለግ እየጨመረ ይሄዳል:: ገዥው አሁን ባለእዳ ቢሆን ሻጩ ደግሞ አበዳሪ ወደመሆን ይለወጣሉ:: በዚህ ግንኙነት አማካይነት ብዙ የሸቀጥ ባለቤቶች ሌሎች ሸቀጦችን በዱቤ እየገዙ በመሄዳቸው በላያቸው ላይ የሚከመረውን እዳ በስምምነታቸው መሠረት ቃላቸውን አክብረው በወቅቱ ሊከፍሉ የማይችሉበት ሁኔታ በሚያጋጥም በዱቤ ግንኙነት በተያያዙ የሸቀጥ ባለቤቶች ላይ ኪሣራ ይደርሳል:: ስለሆነም ገንዘብ እንደ ዝውውር አማካይ ቢሆን የነበረው ቅራኔ በዚህም ደረጃ ላይ ማለትም እንደ ክፍያ መሣሪያም ቢያገለግል ይበልጥ ቅራኔውን እንደሚያሰፋ ማየት አያዳግትም::

ገንዘብ እንደ ዝውውርና እንደ መክፈያ መሣሪያነት ተግባር ላይ መዋሉ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ የተመረቱ ሸቀጦችን ለማዘዋወር የሚያስፈልገንን የገንዘብ መጠን ለማወቅ የሚያስችለንን ሕግ በግልፅ ያስረዳናል::

ሸቀጦች በአንድ ጊዜና በአያሌ በፍራያች ይሸጣሉ፤ ይገዛሉም። ይህ ሁኔታ ለበግ ብዙና የተለያዩ ሸቀጦችን ይመለከታል። በአንድ በተወሰነ ወቀት ውስጥ የሚመረተውን ሸቀጥ ለማዘዋወር የሚያስፈልገው የገንዘብ መጠን በመጀመሪያ ለዝውውር በቀረቡት ሸቀጦች ጠቅላላ ዋጋ ላይ ይመሰረታል፤ ወይም እነዚህን ይይዛል፤ ይህ ጠቅላላ ዋጋ ደግሞ በተራው የሸቀጦችን ጠቅላላ ብዛትና የእያንዳንዱንም ሸቀጥ ዋጋ በማጠቃለል ይተነናል። ከዚሁም ጋር በተጨማሪ ገንዘብ ራሱ በዚህ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ በምን ያህል ፍጥነት እንደሚዘዋወር ማወቅም አስፈላጊ ነው። ገንዘብ በፍጥነት በተዘዋወረ መጠን ለዝውውር የሚያስፈልገው የገንዘብ መጠን አነስተኛ ይሆናል። ቀስ ብሎ ከተዘዋወረ ደግሞ የሚያስፈልገው የገንዘብ መጠን ከፍ ይላል።

ገንዘብ እንደ ክፍያ መሣሪያ የሚጫወተው ሚና በካፒታሊስት ሥልተ ምርት ውስጥ ከፍተኛውን የእድገት ደረጃ ለመያዝ በቅቷል። በዚህ ሥልተ ምርት ውስጥ ገንዘብ እንደ ዝዉውር አማካይ የሚጫወተውን ሚና በአብዛኛው በመተው በክፍያ ሚናው ይበልጥ ጥቅም ላይ ይውላል። ክፍያ በልዩ ልዩ ዘዴ ማለትም የብድር ገንዘብ በሚባል የዝውውር መሣሪያ ይካሄዳል። እነዚህ የዝውውር መሣሪያዎች የዱቤ ባለዕዳዎች ግዴታ የሚገልጥባቸውሆነውልዩ ልዩ የልውውጥ ሰነዶችን፤ የቃል ኪዳን ሰነዶች፤ የባንክ ኖት፤ በባንክ ቼክና በድራፍት የሚደረግ የክፍያ የትዕዛዝ ሰነዶችን ወዘተ...ይይዛሉ። ሁሉም ዘዴዎች በሸቀጥ ሻጭና ገዥ መካከል የሚካሄደውን የገንዘብ የክፍያ አማካይነት የሚያፋጥኑና የካፒታሊስት ሥልተ ምርት የሚያካሂደውን የሸቀጦች ልውውጥ ሂደት ዓይነተኛ የሚያደርጉት ናቸው።

## 2.5 ገንዘብ እንደ ዓለም አቀፍ የዝውውር መሣሪያነት፤

የሸቀጥና የገንዘብ ግንኙነት ማደግ፤ በተለያዩ አገሮች መካከል የሚደረግ ንግድ ግንኙነት መስፋፋት ምክንያት የሸቀጦች ዝውውር ብሔራዊ ዳንበርን

ለየጧስ መሄዱ በመጀመሩ የገንዘብን ተግባር በማበሩት እስከሁን በየብሔራዊ ድንበሩ ብቻ ተወስኖ የነበረው ተግባሩ ዓለም አቀፍ ባሕርይ እየያዘ ለመጣ በቅቷል ::

በዓለም አቀፍ ደረጃ በሚደረገው የሸቀጥና የገንዘብ ግንኙነት ገንዘብ የሚያሟላው ዋና ተግባር እንደ ክፍያ መሣሪያ ማገልገል ነው:: የክፍያው ግንኙነትም ቀነኛ ዘዴ በባንኮች አማካይነት በሚደረግ ስምምነት ማለት በልውውጥ ሰነዶች ወይም በሌሎች የብድር ገንዘብ ዓይነቶች ነው:: ሁለት አገሮች የሸቀጥ ልውውጥ ማድረግ ፈልገው ግን ከላይ ባልናቸው ዘዴ ዎች ለመጠቀም ስምምነት ላይ ካልደረሱ በወርቅ ገንዘብ አማካይነት ዝውው ሩን ሊያካሂዱ ይችላሉ:: ይህ ሁኔታ የገንዘብን /ወርቅን/ ሁለንታዊ ሚና ያመለክታል:: ገንዘብ በአገሮች መካከል የሸቀጥ ልውውጥ ለማካሄድ መሣሪያ በመሆኑ ሁለንታዊ ሚና ቢኖረውም በዓለም አቀፍ ንግድ ውስጥ ከሚ ያመለክቱት እሴት ያነሰ እሴት ባላቸው ሸርፍራፊዎች ወይም የወረቀት ገን ዘብ መጠቀም አይችልም::

በዓለም ገበያ ላይ ገንዘብ በሸርፍራፊ መልክ መቅረቡን ይተውና ወርቅ ሁለንታዊ እኩያ ሚና መጫወት ሲጀምር በነበረበት በጥንት መልኩ ማለ ትም በጥፍጥፍ፣ በክፍልፋይ ወይም በሸርፍራፊ ወይም በሌላ ለማጓጓዝ በሚያ መች መልክ /ወርቅ/ ተዘጋጅቶ ይቀርባል:: በዓለም ገበያ ላይ በአገሮች መካከል ወርቅ የመገበያያ መሣሪያ በመሆን ወደ አገር ውስጥ ለማገባ ሸቀጥ፣ ለዓለም አቀፍ እዳ መሸፈኛ፣ ከውጭ አገር ለሚገኝ ብድር ወለድ ለመክፈልና ለሌላም ዓይነት ግዴታን ለመወጣት ይጠቀማል::

ከፍሏት ኢኮኖሚ ውስጥ ተግባራዊ እየሆኑ ናቸው:: የተያያዝነውን የሽግግር ወቅት አገባደን የሶሺሊዝምን መሠረት በማጠናከር ሰው በሰው የማይጠቀምበትንና የማይበዘበዝበትን ፍትህ፣ እኩልነት፣ ነፃነት የሰፈነበት በማኅበራዊ ብልጽግና ላይ የተመሠረተ ሶሺሊስት ሥርዓተ ማህበር እስክንገነባ ድረስ የካፒታል የኢኮኖሚ ህግጋት እየመነመኑ የሚሄዱ ቢሆኑም ወዲያው አይጠፉም::

የካፒታሊስትን የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የሚገዙ ሕግጋት ዕውቀት ለሶሺሊዝም መሠረት ለመጣልና በሚካሄደው የግንባታ ምዕራፍ ውስጥ አስፈላጊ እንደመሆናቸው በሰፊው ሠርቶ አደር ሕዝብ እነዚህን ሕግጋት በመገንዘብ የግንባታውን ችግር ለመቋቋምና ወደ [illegible]ተፋጠነ ሁኔታ ለመገስገስ የሚያስችለው መሆኑ በግልጽ ይታያል:: ከዚህም ባሻገር በወዝአደራዊ ዓለም አቀፋዊነት በንደቀ በር ለምናካሂደውም ትግል የእነዚህ ህግጋት ግንዛቤ ጠቀሜታ እንዳለው ለመረዳት አዳጋች አይሆንም::

ማርክሲዝም ሌኒኒዝም ሣይንስ እንደመሆኑ በሚገባ መጠናትና መወበጥ ያለበት መሆኑ ተደጋግሞ ተነግሯል፣ ይህ እንደዚሁ የሚነገር ሣይሆን መሠረታዊ ጉዳይ በመሆኑ ተግባራዊ መሆን ይኖርበታል፣ ካለንበት እጅግ በጣም ዝቅተኛ የዕድገት ደረጃ፣ ያለፈው አድሃሪ የብዝበዛና የጭቆና ሥርዓት ካወረሰን የድንቁርና፣ የበሽታ፣ የረሃብ በአጠቃላይ ጉስቁል ሕይወት በመላቀቅ በብልጽግና ላይ የተመሠረተ ፍትህ፣ እኩልነት፣ ነፃነት፣ ወንድማማችነት የሰፈነበት ሕብረተሰብ ለመገንባት መመሪያችን ይህ ሣይንስ ነው:: የምንገነባው ሕብረተሰብ ምን እንደሚመስልና እንዴት እንደምንገነባው የስትራቴጂያችንና የታክቲካችን ምንጭ የማሌ ሣይንስ ነው፣ "ማርክሲዝም ሌኒኒዝም የተግባር መመሪያችን ነው!" የምንለው በከንቱ አይደለም::

ማሌ የተግባራችን መመሪያ ነው ስንል የሰፊው ሠርቶ አደር ሕዝብ የተግባር መመሪያ መሆን አለበት ማለታችን ነው፣ ማሌ የሰፊው ሠርቶ አደር የተግባር መመሪያ

በዓለም ገበያ ላይ የሚደረግ ዝውውር በወርቀ ገንዘብ አማካይነት ነው ቢባልም አንዳንድ አገሮች በዓለም ገበያ ውስጥ ባላቸው ሰፊ ዓለም አቀፍ የገበያ ድርሻና የብድር ግንኙነት ሳቢያ በወርቀ ምትክ የሚጠቀሙባቸው ገንዘቦች ወርቀን ተክተው ሊሠሩ ችለዋል:: ይህ ሊሆን የቻለው ለነዚህ ገንዘቦች በማንኛውም ሥፍራና ጊዜ በላያቸው ላይ በተመለከተው መጠን ለዓለም አቀፍ ክፍያ የሚያገለግሉ በመሆናቸው ነው:: ለነዚህ ገንዘቦች ለምሳሌ የአሜሪካን ዶላር፣ የእንግሊዝ ፓውንድ ስተርሊንግ፣ የጀርመን ማርክ፣ የጃፓን ዩን፣ የፈረንሣይ ፍራንክ ወዘተ...ናቸው:: የሶሺያሊስት ኅብረት ሩብልም በሶሻሊስት አገሮች መካከል እንደክፍያ መሣሪያነት ያገለግላል::

የካፒታሊስት አገሮች በዓለም ገበያ የበላይነትን ለማግኘት በመካከላቸው በሚያደርጉት መራኮት ምክንያት ባንዱ ወቀት በከፍተኛ ደረጃ ተፈላጊ የነበረው ጠንካራ ገንዘብ በሌላ ወቀት ተፈላጊነቱ ዝቀ በለሚል ጠንካራ መገበያያ በሆኑት ገንዘቦች መካከል የዋጋ መዋዠቀ በየወቀቱ ይካሄዳል:: በዚህ መሠረት በዓለም ገበያ ውስጥ የገንዘቦች የበላይነት በየጊዜው ይለዋወጣል:: ለምሳሌ ከአንደኛው የዓለም ጦርነት በፊት ጀምሮ የእንግሊዝ ፓውንድ ስተርሊንግ ለረጅም ጊዜ የበላይነቱን ይዞ ከቆየ በኋላ በአሜሪካን ዶላር ተተክቷል:: ይሁን እንጂ በአሁኑ ወቀት የጀርመን ማርክና የጃፓን ዩን የበላይነቱን ለመያዝ ከአሜሪካን ዶላር ጋር ከፍተኛ ፉክክር በማድረግ ላይ ናቸው::

## 3. የወረቀት ገንዘብ

ቀደም ሲል በልዩ ልዩ ቨርፍራፊያች ሲወከል የነበረው ገንዘብ /ወርቀ/ የካፒታሊስት ሥልተ ምርት እየዳበረ ሲሄድ የወረቀት ገንዘብ ጥቀም ላይ እየዋለ መጥቷል:: በልዩ ልዩ ቨርፍራፊያች ላይ የታተሙ ወይም

የተጻፈው የዋጋ መጠን ሸርፍራፊዎች ከእጅ ወደ እጅ በመዘዋወር ቢያረጁና የማለቅ ሁኔታ ቢደርስባቸው የሚወክሉት የወርቅ መጠን ግን አልተነካም:: ወርቅ ከዝውውር እየወጣ ለግል ጌጥ ሥራና ለመባበሉት እንዲያገለግል በመደረጉ በዝውውር አማካይነት ማገልገል ያለበትን የወርቅ መጠን በመቀነስ የሸቀጦችን ዝውውር አናጋው:: ወርቅን የሚወክል በራሱ የጠቀሜታ እሴት ባይኖረው ለልውውጥ ብቻ የሚያገለግል ነገር አስፈላጊ ሆነ:: እነዚህ ሁኔታዎች የወረቀት ገንዘብን ክስተት አስከተሉ:: ባንኮችም ሆኑ ወረቀት በምልክትነት እስኪገለገሉ ድረስ ከእጅ ወደ እጅ መዘዋወራቸው ቀላልና አመቺም ስለሆነ ተፈላጊነታቸው እየጎላ ሊመጣ ችሏል:: ለመሆኑ የወረቀት ገንዘብ ምንድነው?

ባሁኑ ጊዜ የወረቀት ገንዘብ ሙሉ እሴት ያለው የወርቅ ገንዘብ የሚኖረውን የዝውውርና የክፍያ ተግባር ለማሟላት የሚያስችል የእሴት ምልክት የሆነና በሕግ አስገዳጅነት በዝውውርና በክፍያ ተግባር ላይ የሚውል በመንግሥት የሚታተም ልዩ ሰነድ ነው:: የወረቀት ገንዘብ በራሱ እሴት የለውም:: ይህም በመሆኑ የሸቀጦችን እሴት ለመለካት አይችልም:: የሸቀጡ እሴት ወረቀቱ በሚወክለው ወርቅ የሚለካ ነው::

ምንም ያህል የወረቀት ገንዘብ ሥርጭት ላይ ቢውልም፤ በሥርጭት ላይ የዋለው ይህ የወረቀት ገንዘብ ብዛት ሊወክል የሚችለው በተወሰነ ጊዜ ውስጥ የተመረተውን ሸቀጥ ለማዘዋወር የሚያስፈልገውን የወርቅ እሴት መጠን ብቻ ነው:: በአንድ ወቅት የሚሠራጨው የወረቀት ገንዘብ ሸቀጦችን ለማዘዋወር ከሚያስፈልገው የወርቅ እሴት መጠን ጋር ተስተካክሎ ከተሠራጨ የወረቀት ገንዘቡ የመግዛት ኃይል ዝውውሩና ክፍያው ከወርቅ የመግዛት ኃይል ጋር ይመጣጠናል ማለት ነው:: ወርቅ ግን በቀጥታ ከዝውውርና ከክፍያ መስክ ወጥቶ በየአገሩ ብሔራዊ ማዕከላዊ ባንክ ውስጥ ይቀመጣል:: ወርቅ የሌላቸው አገሮች ተመጣጣኝ ሀብት ሊኖራቸው ይገባል::

ኢምፔሪያሊስት መንግሥታት በተለያዩ ምክንያቶች በሚያጋጥሙዋቸው ቀውሶች ለምሳሌ በጦርነት ጊዜ፣ በኢኮኖሚ ቀውስ ጊዜና በሌሎችም ድንገተኛ ምክንያቶች የተመረተውን የምርት መጠን ያልተመጣጠነ የወረቀት ገንዘብ በብዛት ሊያትሙ ይችላሉ፤ ያትማሉም። ይህ ሁኔታ ሲያጋጥም የወረቀት ገንዘብ የመግዛት ኃይል በመቀነስ የሸቀጦችን ዋጋ ያንረዋል። በማዕከላዊ ባንክ ከሚገኘው የወርቅ አቤት መጠን በላይ የወረቀት ገንዘብ ታትሞ እንዲሠራጭ ሲደረግ የገንዘብ የመግዛት ኃይል ሲዳከም ወይም ሲቀነስ በዚህ ባሕያ የሚደርሰው የኢኮኖሚ ቀውስ የዋጋ ንረት ይባላል።

በካፒታሊስት አገሮች በየጊዜው የሚመደበው እጅግ ከፍተኛ የጦር መሣሪያ በጀት ለኅብረተሰቡ ፍጆታ አስፈላጊ ዕቃዎች ለማምረት አማይረዳ በመሆኑ ለዋጋ ንረት ዋነኛው ምክንያት ነው። የዚህም ንረት ሸክም የሚወድቀው ዝቅተኛ ገቢ ባለው በሠራተኛው ሕዝብ ላይ ነው። ምክንያቱም በዚህ ወቅት የሚከሰተው ከፍተኛ የሆነ የዋጋ መናር በተለይም በምግብ፣ በመጠለያና በሌሎችም ለሠራተኛው ሕይወት እጅግ አስፈላጊ በሆኑ ሸቀጦች ላይ ስለሚደርስ ነው። በተለይም በሞኖፖል ካፒታሊዝም ደረጃ ካፒታሊስቶች የዋጋ ንረትን እንደዋነኛው የትርፍ ማካበቻና የሠራተኛውን የሥራ ኃይል እንደ መበዝበዣ የሚጠቀሙበት ሥልት ነው። ሞኖፖል ካፒታሊስቶች የገንዘብና የምርት መጠን ተመጣጣኝ በሆነበትም ወቅት በው ሠራሽ የሸቀጥ እጥረት በመፍጠር የዋጋ ንረት እንዲደርስ ስለሚያደርጉ የሠራተኛው ሕዝብ ኑሮ ከዕለት ዕለት እያሽቆለቆለ ሲሄድ የካፒታሊስቶች ሀብት እየደለበ ይሄዳል።

## 4. የአቤት ሕግ :- የሸቀጥ ምርት የኢኮኖሚ ሕግ፤

በካፒታሊስት የሸቀጥ ምርት በቡርዧዎች መካከል ከፍተኛ ፉክክር ይካሄዳል። አንዱ ሌላውን አስወግዶ ገበያውን ለብቻው ለመያዝ ይጥራል፤

ይፍወረወራል። ማኅበራዊ ምርት የሚመራው በፕላን ባይሆን ግብታዊ በሆነው በካፒታሊስት ገበያ ጠቋሚነት በመሆኑ አያንዳንዱ ካፒታሊስት በመሰለውና ከፍተኛ ትርፍ ያስገኝልኛል ብሎ በገመተው መንገድ ያመርታል። በለዚህ በገበያ ላይ የሚቀርበው የሸቀጥ ዓይነትና መጠን ከኅብረተሰቡ ፍላጐትና አቅም ጋር ብዙውን ጊዜ የሚጣጣም አይሆንም። ይህ የሚያሳየው የማምረቻ መሣሪያዎች በግል ባለቤትነት በተያዙበት ሁኔታ ሥር የሚካሄደው የሸቀጥ ምርት የሚገዛበት ዓይነተኛ ሕግ "ውድድርና ሥርዓተ አልባ የሆነ አመራረት" መሆኑን ነው።

የአሴት ሕግ ከሸቀጥ ልውውጥ ጋር የተጀመረ አንደመሆኑ መጠን የሸቀጥ ምርት ባለበት ስርዓተ ማኅበር ሁሉ የሚኖር ነው። የምርት መገልገያዎች በግል ባለቤትነት በተያዙበት ሁኔታ ሁሉ፣ የአሴት ሕግ ግብታዊ በሆነ መንገድ በመሥራት በሸቀጥ አምራቾች መካከል የገቢ ልዩነት አየሰፋ አንዲሄድና ብሎም በካፒታሊስት ሥርዓት የሥራ ኃይል በካፒታል አንዲበዘበዝ ያደርጋል።

የአሴት ሕግ በዝውውር ሂደት ውስጥ ሸቀጦች የሚለዋወጡበትን መጠን /ለምሳሌ አንድ ጋቢ በሁለት ማጭድ ቢለወጥ ልውውጡ አንድ ለሁለት መሆኑ ነው ማለት ነው/ የሚወስን አንደመሆኑ ልውውጥን ብቻ የሚገዛ ሕግ ሊመስል ይችላል። በመሠረቱ የአሴት ሕግ የሸቀጥ ልውውጥ ሕግ ቢሆንም፣ ለልውውጥ መነሻው ማምረት አስከሆነ ድረስ፣ በአመራረቱም ዘይቤ ላይ ከፍተኛ ተጽአኖ ይኖረዋል።

የአሴት ሕግ የሸቀጥ ምርት የኢኮኖሚ ሕግ ቢሆን፣ ሸቀጦች ቢለዋወጡ፣ ልውውጡ የሚካሄደው በሚለዋወጡት ሸቀጦች ውስጥ በተጠናቀረው

ማኅበራዊ ተቀባይነት ባለው የሥራ ጊዜ መጠን መሆኑን የሚቆጣጠር ሕግ ነው። የዚህን ሕግ ውስጣዊ ባህርይ ጠለቅ ብለን ብንመለከት ይዘቱ ወይም ፍሬ ነገሩ እንደሚከተለው ሆኖ እናገኘዋለን።

1:- የእሴት ሕግ የሥራ ኃይልና የምርት መገልገያ በልዩ ልዩ ኢኮኖሚ ዘርፎች መካከል መሠራጨቱን በመቆጣጠር ረገድ ከፍተኛ ተጽእኖ በለሚያደርግ፣ ግብታዊ በሆነ መንገድ የሸቀጥ ምርትን ይቆጣጠራል።

በገበያ ውስጥ በሚታየው የአቅርቦትና የፍላጎት መዋዠቅ አቅርቦት ከፍላጎት በላይና በታች በመሆን የሸቀጦችን ዋጋ አንዳንዴ ከእሴታቸው በላይ አንዳንዴ ደግሞ በታች እንዲሆን ያደርጋል። በገበያ ላይ የሚቀርብ አንዱ ሸቀጥ ከሚፈለገው በላይ ከሆነ ዋጋው ከእሴቱ በታች ይሆናል። ከሚፈለገው በታች ከሆነ ደግሞ ዋጋው ከእሴቱ በላይ ይሆናል። በገበያው ላይ የሚታየውን ይህን ውጣ ውረድ በግብታዊነት የሚመራው የእሴት ሕግ በምርት መገልገያና በሥራ ኃይል አሠረጫጨት ረገድ ግብታዊ የሆነ መስተካከል እንዲኖር ያደርጋል።

ለምሳሌ በገበያ ውስጥ ያለው የመኪና መግዛት ፍላጎት እያሽቆለቆለ ቢሄድና በዚህም ምክንያት ዋጋው ቢቀንስ፣ በአንጻሩ ደግሞ የሞተር ብስክሌት መግዛት ፍላጎት ቢጨምርና በዚህም ምክንያት ዋጋው ከፍ ቢል የመኪና ምርት እየቀነሰ የሞተር ብስክሌት ምርት እየጨመረ ይሄዳል። የማኅበራዊ ሥራም ሥርጭት/ሠራተኞች/ እንዲሁ ወደ ሞተር ብስክሌት ፋብሪካ

ይጨፈል። በዚህም የተነሣ ብዙ ሞቱር ብስክሌቶች በለማምረቱ አቀርቦቱ ከፍላጎት በላይ ይወጧል። ስለሆነም የሞቱር ብስክሌት መግዛት ፍላጎት ቀንቦ የመኪና መግዛት ፍላጎት ሊወምር ይችላል። በገበያ ውስጥ ያለው መኪና መጠን ትንሽ በመሆኑ ዋጋው ይወምራል። ፍላጎቱን ለማሟላት ባባል ደግሞ ብዙ አዳዲስ መኪናዎች መሥራት ያስፈልጋል። በገበያ ውስጥ ያለው ቀጥሩ ብዙ የሆነ ሞቱር ብስክሌት ደግሞ ከፍላጎት ጋር ስለማይጣጣም ዋጋው ይቀንባል። ሌላ ማምረትም እየቀዘቀዘ ይሄዳል። ሠራተኞችም እንዲሁ ካንዱ ወዳንዱ ይንከራተታሉ። ሠራተኛው የሥራ ቀስትና በለሌለውም በማንኛውም ገዜ ይባረራል። እንግዲህ ቀውሱና ቀራነው ዙሪያ ክቡ በመሆን ይህን ለመ በጠስ የሚቻለው በዕቀዱ በሚመራው በሶሻሊስት ሥርዓት ብቻ ነው።

2፡— የአቢት ሕግ በሸቀጥ ምርት ሊኾኖሚ ውስጥ የምርት ኃይ ሉችን እድገት ይመራል ።

ደጋገመን እንዳልነው የአንዱ ሸቀጥ እቢት ሸቀጡን ለማምረት በወሰደው ማኅበራዊ አስፈላጊ ሥራ ገዜ መጠን ይወሰናል። በአንዱ በተ ወሰነ ወቀት ውስጥ አንዱን ሸቀጥ ለማምረት የሚያስፈልገው ማኅበራዊ አስ ፈላጊ የሥራ ገዜ በሠራተኛው ምርታማነት ዕድገት ሊቀንስ ይችላል። በፋ ብሪካዎቻቸው ውስጥ አዲስ ቴክኖሎጂ የሚያስገቡ ካፒታሊስቶች ወይም ሸቀጥ አምራቶች በአነስተኛ ወጭና ገዜ ብዙ ሊያመርቱ ይችላሉ። ይህ ቢሆን የሚያጋጥመውን ሁኔታ እንመልከት።

አንዱ ሬዲዮ የሚሠራ ፋብሪካ ከፍተኛ ምርምር አካሂዶ አዲስ የሬዲዮ ማምረት ቴክኖሎጂ ያገኛል እንበል። ሠራተኞቹን በማሠልጠን

የቴክኒክ አውቀታቸውን በማዳበር የተሻለ የሬዲዮ ምርት ያመርታል። ይህ ፋብሪካ ከሌሎች ተመሳሳይ ሬዲዮ ከሚያመርቱ ፋብሪካዎች የተሻሻለውን ዘዴ ቀድሞ በማግኘቱ ሌሎቹ አንዱን ሬዲዮ ለማምረት ከሚያወጡት ማኅበራዊ አስፈላጊ የሥራ ጊዜ ባነሰ ዋጋ ያመርታል። በገበያ ላይ ቢያቀርበው የሬዲዮ አሴት የሚወሰነው ግን ቀድሞ በነበረው ማኅበራዊ አስፈላጊ የሥራ ጊዜ በገበያው ዋጋ ስለሆነ ይህ አዲስ ቴክኖሎጂና አዲስ ዘዴ ያገኘው ካፒታሊስቱ ከሌሎቹ የላቀ ብዙ ትርፍ ያገኛል። ከሌሎቹ ሀብታም እየሆነ ይሄዳል። ይህ ሁኔታ ሌሎቹም ካፒታሊስቶች ለቴክኖሎጂ ምርምርና ለአዲዲስ የተሻሻለ ፈጠራና ለምርታማነት የሚያደርጉትን ውድድር ያፋጥነዋል። በዚህ ዓይነት የአሴት ሕግ ለምርት ኃይሎች መዳበር ወይም አድገት በር ይከፍታል። ይህ ሁኔታ ግን የራሱ ቅራኔ እንዳለውም ማየት ያስፈልጋል።

የአሴት ሕግ ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው ለምርት ኃይሎች መዳበር አመቺ ሁኔታ የሚፈጥር ቢሆንም የቴክኖሎጂ ግኝት የእያንዳንዱ ካፒታሊስት የግል ሀብት መሆኑ በኢኮኖሚው ውስጥ ብዙ ቀውስ ያስከትላል። የምርምር ውጤትን በመደበቅ፣ የሥራ ኃይልን በማባከን፣ በተለያዩ የኢኮኖሚ ዘርፎች መካከል ሊኖር የሚገባውን ሚዛናዊ ግንኙነት በማሰናከል የኢኮኖሚ ቀውስ እንዲነሳና በካፒታሊስቱ ስርዓት ውስጥ ያለው ቅራኔ እየተስፋፋና እየናረ እንዲሄድ ያደርጋል።

3:- የአሴት ሕግ አነስተኛ የሸቀጥ ምርት ወደ ካፒታሊስት የሸቀጥ ምርት እንዲሸጋገር ያደርጋል።

የዋጋ እንደ ሁኔታው ከአሴት በላይም ሆነ በታች መዋዠቅ የሚያስከትለው የምርት መገልገያና የሥራ ኃይል አሠረጫወት ቀጥ ማጣት፣ በሸቀጥ

አምራቾች መሀል የገቢ ብሎም የሀብት መበላለጥንና ፉክክርን ያፋፍማል።
ይህ ፉክክር ገሚሶቹን ሸቀጥ አምራቾች እያዳከመ በማደኽየት ወደ ወዝአደርነት ሲለውጣቸው ሌሎቹን ደግሞ በሀብት በማደለብ ካፒታሊስቶች ያደርጋቸዋል።

ስለሆነም የእሴት ሕግ በሸቀጥ አምራቾች መካከል ልዩነትን በመፍጠር ጥቂቶች እየደለቡ እንዲሄዱ በመርዳት ብዙሃን ግን በድህነትና በጭቆና ቀንበር ሥር እንዲወድቁ በማድረግ የካፒታሊስት የኢኮኖሚ ግንኙነትን ማለትም ከማምረቻ መሣሪያዎች ባለቤትነት የተገለሉና የሥራ ኃይላቸውን ብቻ እንደ ሸቀጥ ገበያ አውጥተው የሚሸጡ ብዙሀን ሠርቶ አደሮችንና በነሱም ትይዩና ፊት ለፊት ደግሞ ጥቂት በማምረቻ መሣሪያዎች ባለቤትነት ብቻ መሳውን ሠርቶ አደር የሚበዘብዙ ካፒታሊስቶችን፣ ቡርዧዎችን ይፈጥራል፡ ፡

## 5. ሸቀጥ አምላኪነት፣

የሸቀጥ ልውውጥን እድገት ሳናጠና ልናልፈው የማንችል አንድ ቁም ነገር አለ። ይኸውም፣ ሸቀጦች ለሰዎች መለከታዊ መስለው የመታየታቸውን ልዩ ባሕሪ ነው። ሸቀጥ ላይ ላዩን ሲታይ እጅግ በጣም አነስተኛ ግምት የሚሰጠውና ለመረዳትም የቀለለ ይመስላል። ሁኔታው ግን ይህ እንዳልሆነ ከፍ ብለን ለማየት ሞክረናል።

በግል ሀብት ላይ በተመሠረተ የሸቀጥ አመራረት ተግባር ውስጥ የሥራ ኃይል ከሚኖረው ማኅበራዊ ፀባይ የተነሳ ሸቀጦች ወይም ቁሳዊ ምርቶች




የሸቀጥ እምላኪነትን ሁኔታ ለማሳየት የ20ኛው ምዕተ ዓመት ታሪክ ከሚለው መጽሐፍ የተወሰደ

Proudly brought to you by

www.binyamhk.wordpress.com



በቀጥታ ለግለሰብ ጠቀሜታ ወይም ግልጋሎት የሚመረቱ ሣይሆኑ ለገበያ፣ ለሽያጭና ለልውውጥ የሚመረቱ ናቸው። ይህም ማለት በካፒታሊዝም የእነዚህ ቁሳዊ ምርቶች መሠረታዊ ዓላማ ፡ለግረ መንገዱን ካልሆነ በስተቀር በተቀዳሚ የኅብረተሰቡን አጠቃላይ ፍላጐት ማሟላትና ማርካት ባይሆን ለካፒታሊስቱ ትርፍ ማካበቻ ዓይነተኛ መሣሪያ መሆን ነው።

የግል ሀብት አምራቾችን የሚበታትንና የሚነጣጥል በመሆኑ በዚህ ሁኔታ ውስጥ በሰዎች መካከል ሊኖር የሚችለው ኢኮኖሚያዊ ግንኙነት በሸቀጦች ልውውጥ አማካይነት ወይም በእቃዎች የእንቅስቃሴ ሂደት ምክንያት ሊፈጠር የሚችል ግንኙነት ዓይነት ብቻ ነው። ይህ የእቃዎች የእንቅስቃሴ ሂደት ወይም የሸቀጦች ልውውጥ በንቃት ላይ ተመሥርቶ የሚከናወን ባይሆን በዘፈቀደ ወይም በግብታዊነት የሚፈጸም በመሆኑ ሸቀጦችን የሚያመርቱም ሰዎች ሕልውና እንዲሁ በዚሁ የሸቀጦች ግብታዊ የልውውጥ እንቅስቃሴ ማለትም በሸቀጦች የገበያ ሁኔታ ላይ የሚመሠረት ይሆናል። በመሆኑም የሸቀጥ አምራቾች ሕይወት ሙሉ በሙሉ በሸቀጦች የዋጋ ውጣ ውረድና በገበያ ሁኔታ ላይ የሚመሠረትና በዚያም የሚመራ ይሆናል። የሸቀጡ መሸጥ ወይም አለመሸጥ፣በአንድ ሸቀጥ ላይ የሚገኘው ገቢ ሸቀጡን ለማምረት የሚወጣውን ወጭ መሸፈኑ ወይም ያለመሸፈኑ በሻጩ ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ ይኖረዋል። ገዥውም ቢሆን በአንድ በኩል ሸቀጦች አምረው ተሠርተው በሱቁ ውስጥ ተደርድረው ገዥ እየጠበቁ መሆናቸውን ቢገነዘብም የአብዛኞቹ የሸቀጦቹ ዋጋ ከሱ የመግዛት ችሎታ በላይ በሚሆንበት ጊዜ ከፍተኛ የሸቀጥ ጉጉትና ባለማግኘቱም ንዴት ይሰማዋል። ይህ ፍላጐት እየቆየ ሲሄድ ወደ አምልኮት ይቀየራል።

እንደ ሰው ራሱ ለፈጠረው፣ እራሱ ለቀረጸውና በአእምሮው ውስጥ ለሳለው ጣኦት እንደሚሰግድ፣ እንደሚያገለግልና እንደሚንበረከክ ሁሉ ሸቀጥ

አምራቾችም ከመልበው ሸቀጥ ገዥዎች እንደመሆናቸው ሊያገኙዋቸው ለማይችሉት ሸቀጦች ይንበረከካሉ፣ ያጎበድዳሉ:: የአምራቾች ሕልውና በገበያ ኃይል ላይ መቆሙ ሸቀጥና ገንዘብ በሰዎች ላይ ያላቸውን "መለኮታዊ" ተጽአና የሚያመለክት ነው::

ይህ የሸቀጥ አምላኪነት ባህሪ በነዚህ ዕቃዎች የጠቀሜታ እሴት ወይም ሸቀጦች በተፈጥሮ በታደሉት ሌላ ስውር ኃይል ምክንያት የተፈጠረ አይደለም:: ሸቀጦች ሰዎችን የመቆጣጠራቸው ሁኔታ ወይም ይህ በካፒታሊስት ኢኮኖሚ ውስጥ ያለ የሸቀጦች ባህሪ ለገበያ ብቻ ሲባል ከሚመረቱ ሸቀጦች ውስጥ የሚመነጭ ውስጣዊ ባህሪያቸው ነው:: በልዩ ልዩ ቦታ ወይም በተናጠል በሚሠሩ ሸቀጥ አምራቾች መካከል ያለው ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ግንኙነት በምርት ውጤቶቻቸው ወይም ደግሞ በሸቀጦቻቸው መካከል በሚደረገው ልውውጥ አማካኝነት ብቻ ይገለጻል:: ይህ በሸቀጦች መካከል የሚደረገው ልውውጥ ቁሳዊ መልክን ይወስዳል:: ካርል ማርክስ ይህን ቁሳዊ ባህሪ የተጎናፀፈውንና በዚህ ምክንያትም በሰዎች አአምሮ ውስጥ በሸቀጦች የመለኮታዊ ኃይል ፀባይና ወይም ባህሪ የሚንፀባረቀውን የምርት ግንኙነት "የሸቀጥ አምላኪነት" ሲል ሰይሞታል::

የሥራ ማኅበራዊነት እየበለጸገ፣ አምራቾች በገበያ ላይ ያላቸው ጥገኝነት እየጎለበተና እያደገ ሲሄድ በሸቀጦች የማምለክ ዝንባሌም እንዲሁ እያደገና እየጎለበተ ይሄዳል:: በዳበረ የካፒታሊስት ሥልተ ምርት ውስጥ የሰው ልጅ እራሱ በሚያመርታቸው ሸቀጦችና በዙሪያው በሚገኙት ሌሎች ነገሮች ሥር በባርነት ከማጎብደዱና ባምላኪነት ከማቀርቀሩም ሌላ የሸቀጦች ወይም የገንዘብ ጥገኛ ይሆናል:: ይህም በየዕለቱ በሚታየው በወርቅና በገንዘብ ገደብ የለሽ ሥልጣንና ኃይል አማካኝነት ይገለጻል:: ለገንዘብ

የመገዛት ወይም ለሱ የመታመን፣ ወርቅንና ገንዘብን እንደ "ፈጣሪ" ወይም እንደሌላ ሀያል ጣኦት የሚመስል ባህሪ የካፒታሊስቱን ዓለም የሸቀጥ አምላኪነት ያመለክታል።

የሸቀጥ አምላኪነት ሚስጥር በማርክሲዝም–ሌኒኒዝም የፖለቲካ ኢኮኖሚ ሳይንስ ገሀድ ሊወጣ ችሏል።

የቡርዧው ፖለቲካ ኢኮኖሚ የሸቀጥ አምልኮን ዓይነተኛ ባህሪ በትክክል የማይገልጽ ብቻ ሳይሆን በተቃራኒው በተቻለ መጠንና በተገኘው መንገድ ሁሉ ይህንን አምልኮ ለማጠናከር የሚጥር፤ የገንዘብንና ገንዘብ በሰዎች ላይ ያለውን ኃይል እንደ ወርቅ/ገንዘብ/ ዓይነተኛና ልዩ ባህሪ አድርጎ የሚስልና "ገንዘብ ካለ በሰማይ መንገድ አለ" እንዲሉ ሰዎች ለዚህ ኃይል የሚኖራቸውን ተገዥነት አጉልቶ የሚያሳይ ነው።

## ጥ ያ ቄ ዎ ች

1. የሸቀጥ ልውውጥ ማለት ምንድነው? ተጨባጭ ምሳሌ በመስጠት አብራራ።
2. የአንድ ሸቀጥ እሴት በሌላ ሸቀጥ ይገለጣል ሲባል ምን ማለታችን ነው? በምሳሌ አስረዳ።
3. እንጻራዊ እሴት ማለት ምንድነው? አኩያዊስ? ሚናቸውን በምሳሌ አስረዳ።
4. በልውውጥ ዕድገት ሂደት ውስጥ በየደረጃው የታዩትን የእሴት መልኮች ግለጽ። የልውውጥ ዕድገት አንቀሳቃሽ ኃይልስ ምንድነው?
5. ገንዘብ ምንድነው? ገንዘብ እራሱ እሴት ያለው ሸቀጥ ነው ቢባል ምን ማለት ነው?
6. የገንዘብን ተግባራት በዝርዝር አስረዳ።
7. በመደብ በተከፋፈለ ኅብረተሰብ ውስጥ የገንዘብ ተግባራት ለኢኮኖሚ ቀውስ ምክንያት የሚሆኑት እንዴት ነው?
8. የወረቀት ገንዘብ ከወርቅ ገንዘብ እንዴት ይለያል?
9. የዋጋ ንረት ቢባል ምን ማለት ነው? የዋጋ ንረት ሠራተኛውን እንዴት ይጎዳል?
10. የሸቀጥ ምርትን የእሴት ሕግ አብራራ።
11. የሸቀጥ ምርት የኢኮኖሚ ሕግ ውስጣዊ ባህርያትን በዝርዝር አስረዳ።
12. ሸቀጥ አምላኪነት ማለት ምንድነው? ሠራተኛውን እንዴት ባለ መንገድ ከትግሉ ያዘናጋዋል?

# ቃ ላ ት

| | | |
|---|---|---|
| 1. | የእሴት መልክ | Form of Value |
| 2. | የእሴት ጥንት መልክ | Elementary Form of Value |
| 3. | የተስፋፋ የእሴት መልክ | Extended Form of Value |
| 4. | ጠቅላላ የእሴት መልክ | General Form of Value |
| 5. | ሁለንታዊ የእሴት መልክ | Universal Form of Value |
| 6. | ሽርፍራፊ | Coins |
| 7. | ገንዘብ | Money |
| 8. | አኩያዊ የእሴት መልክ | Equivalent Form of Value |
| 9. | አንጻራዊ የእሴት መልክ | Relative Form of Value |
| 10. | የልውውጥ አማካይ | Medium of Exchange |
| 11. | የዝውውር አማካይ | Medium of Circulation |
| 12. | የወረቀት ገንዘብ | Paper Money(Bank Note) |
| 13. | የዋጋ ንረት | Inflation(Price) |
| 14. | የገንዘብ መቀበር | Hoarding(Money) |
| 15. | የክፍያ መሣሪያ | Means of Payment |
| 16. | ውህዳ | Unit |
| 17. | ዱቤ | Credit |
| 18. | የቃል ኪዳን ሰነድ | Promissory Note |
| 19. | የልውውጥ ሰነድ | Bill of Exchange |
| 20. | የእሴት ሕግ | Law of Value |
| 21. | ሸቀጥ አምላኪነት | Commodity Fetishism |
| 22. | የእሴት መለኪያ | Measure of Value |
| 23. | የእሴት የገንዘብ መልክ | Money form of Value |
| 24. | የገንዘብ ተግባራት | Functions of Money |
| 25. | የመግዛት ኃይል | Purchasing Power |
| 26. | የዋጋ ደረጃ | Standard of Price |
| 27. | የክምችት መሣሪያ | Means of accumulation |
| 28. | ጥፍጥፍ | |

# ም ዕ ራ ፍ 3

# ካፒታልና ተረፈ እሴት

## 1. የካፒታል ትርጉም፣

ካፒታል ምንድነው? ለብዙ ሰዎች ይህ ጥያቄ አስፈላጊ ሳይመስ ላቸው ይችላል፣ ካፒታል ገንዘብ ነው፣ ስለዚህ ግልጽ የሆነን ነገር ለምን እንጠይቃለን፣ ለምን እንተረጉማለን ይሉ ይሆናል። ይሁንና ነገሩ እንደ ዚህ ቀላልና ግልጽም አለመሆኑን ከሚከተለው ለማየትና ለመገንዘብ ይቻላል።

ካፒታል በኅብረተሰብ ዕድገት ታሪክ ባንድ በተወሰነ ወቅትና ደረጃ የተከሰተ የራሱ ሕግጋት ያሉት ማኅበራዊ የምርት ግንኙነት ነው። ይህ ማኅበራዊ የምርት ግንኙነት በቡርዧ መደብና በወዝአደር መደብ መካ ከል የተፈጠረ በምርት መገልገያዎች የግል ባለቤትነት ላይ የተመሠረተ ነው። የምርት መገልገያዎች/መሬት፣ ማሽን፣ ጥሬ ዕቃ፣ ኃይል ወዘተ..../ ባለቤት የሆነው ቡርዧ ከሥራ ኃይሉ በስተቀር ምንም ነገር የሌለውን ወዝአደር የሰራ ፍሬ የሚበዘብዝበት ግንኙነት ነው። በቀድም ይህን የምርት ግንኙነት አይነተኛ የሚያደርገው የተበዝባዥ መደቦች መኖር ብቻ ሳይሆን የሥራ ኃይላቸውን እንደማንኛውም ሸቀጥ በገበያ አማካኝነት እንዲ ሸጡና እንዲለውጡ የሚገደዱበት ሥርዓት መሆኑ ነው።

ቡርዧው ወዝአደሩን የሚበዘብዘው ከምርት መገልገያዎች ጋር በማቀናጀት ሸቀጥ በማምረትና ተረፈ እሴት በማስፈጠር ነው። በዚህ

ሂደት ወዝአደሩ ጡንቻውንና አዕምሮውን በማንቀሳቀስና በማሠራት በሞተሮች፣ በማሽኖችና በሌሎች ነገሮች ወይም ቁሳቁሶች አማካይነት የምርት ተገብሮችን /ጥሬ ዕቃዎችን/ ወደ ሸቀጥነት ይለውጧቸዋል፣ የጠቀሜታ እሴት ይፈጥራል፣ ትርፍ እሴትም በዚሁ ሂደት ውስጥ ይፈጠራል።

ካፒታል የቡርዧ የምርት ግንኙነት ነው በኋላ ይህ ግንኙነት በምርት መገልገያዎች የግል ባለቤትነት ላይ የተመሠረተ መሆኑን ከዚህ በላይ ጠቆም አድርገን ነበር፣ ይሄንን ሃሣብ ጠለቅ አድርገን በንመለከተው ካፒታሊስቱ ወዝአደሩን ትርፍ እሴት በማስፈጠር ሊበዘብዘው የሚችለው የምርት መገልገያዎች ባለቤትነቱ በሚያስገኝለት ኃይል እንደሆነ እንገነዘባለን። የእነዚህ መሣሪያዎች ባለቤት ባይሆን ኖሮ የወዝአደሩን የሥራ ኃይል ለመግዛትና ከምርት መገልገያዎች ጋር በማቀናጀት ሸቀጥ በማስመረት ትርፍ እሴት ለማስፈጠር አይችልም ነበር። ወዝአደሩም ተበዝባዥ ሊሆን የበቃው ከምርት መገልገያዎች ባለቤትነት የተገለለ ወይም የተላቀቀና ለመኖር የሥራ ኃይሉን ከመሸጥ በስተቀር አማራጭ የሌለው በመሆኑ ነው።

ታላቁ ፈላስፋና የወዝአደር መሪ ካርል ማርክስ ካፒታልን ሲገልጽ "ካፒታል ቁሳዊ ነገር ሳይሆን ይልቁኑ ባንድ በተወሰነ የኅብረተሰብ ታሪክ ወቅት የሚከሰት የተወሰነ ማኅበራዊ የምርት ግንኙነት ነው፣ ይህ ግንኙነት የተለየ ማኅበራዊ ባሕርይ በሚሰጠው ቁሳዊ መልክ ይገለጻል" ብሏል።*

ከፍ ብሎ ከተመለከተውና ከማርክስ መግለጫ እንደምንረዳው ካፒታል የቡርዧ የምርት ግንኙነት ቢሆን ቁሳዊ ገጽታዎች አሉት፣ ለነዚህ ቁሳዊ ገጽታዎች

---

*ማርክስና ኢንግልስ፣በብበብ ሥራዎች፣ቅጽ 25፣ ክፍል 2፣ ገጽ 380—81 በትልቁ ሶቪዬት ኢንሳይክሎፔዲያ ቅጽ 11፣ ገጽ 98 እንደተጠቀሰው።

የቀጥር በሩና የምርት መገልገያዎች መሆናቸውን እንገነዘባለን። እነዚህ ባንድነት ተጣምረው ቢንቀሳቀሱ ሸቀጥ ይመረታል፣ ወዝአደሩ ተረፈ እሴት ይፈጥራል። ከፒታሊስቱ ወዝአደሩ አከሉንና አለምርውን በማንቀሳቀስ የፈ ጠረውን ተረፈ እሴት ይመዘብራል፣ ለፍጆታው የሚያስፈልገውን ካነሳ በኋላ የቀረውን/አብዛኛውን/ ወደ ካፒታል ይለውጠዋል/ ተጨማሪ የምርት መገልገ ያዎችን ይገዛል፣ ወዝአደር ይቀጥራል።/

ካፒታል የሚያድገውና የሚዳብረው ተረፈ እሴትን በማከበትና በማጠራቀም ነው። የካፒታልን ታሪክ ስንመለከት የተረፈ እሴት ጥርቀም ወይም የተከበተ ወይም የተጠራቀመ ተረፈ እሴት ሆኖ እናገኘዋለን። ለዚ ህም ነው ማርክስ የካፒታልን ምንነትና ልዩ ባህሪይ ደህና አድርጎ ከመረ መረና ካጤነ በኋላ ካፒታል እሴትን የሚወልድ እሴት ነው ያለው። ይህ ተረፈ እሴትን በማጠራቀም ካፒታልን ማሳደግ ወይም ማዳለብ በቡርዧው ስርዓት ውስጥ ሁልጊዜ የሚከናወን በግልጽ የሚታይ ሁኔታ ነው። ለምሳሌ አንድ ኩባንያ/ካፒታሊስት/ ለምርት መገልገያዎችና ለሥራ ኃይል/ወዝአደር/ ሃብት ሚሊዮን ብር አውጥቶ አንድ ሚሊዮን ብር ቢያተርፍ፣ ከዚህ ትርፍ ውስጥ ሃምሳ ሺ ያህል ለራሱና ለቤተሰቡ ፍጆታ አስቀርቶ ዘጠኝ መቶ ሃምሳ ሺውን ካፒታል ያደርገዋል።

አዲስ ማሽኖችን፣ አዲስ ሕንፃዎችን፣ ተጨማሪ የምርት ተገባሮችና ተጨማሪ የሥራ ኃይልን ይገዛበታል፣ እነዚህን በፊት ከነበረው ጋር በማደረ ግና ከወዝአደሩ የሥራ ኃይል ጋር በማቀናጀት አዲስና ተጨማሪ ተረፈ እሴት እንዲፈጠር ያደርጋል። ይህ ሂደት ያለማቋረጥ በለሚቀጥል ተረፈ እሴት ወደ ካፒታል እየተለወጠ ካፒታል እየደለበ ይሄዳል።

ይህ የካፒታል የሚሉ ፖለቲካ ኢኮኖሚ ገንዘብ በተለምዶ ካፒታል ነው ብለው ከሚወስደው፣ ወይም የቡርዧ የኢኮኖሚ ሊቃውንት ለካፒታል ከሚሰጡት ትርጉም ጋር አይገጥምም፣ የተለየ ነው። የቡርዧ የኢኮኖሚ ሊቃውንት የማምረቻ መሣሪያዎችን፣ ጥሬ ዕቃን፣ መሬትን፣ ሕንፃን በእጁ ወይም በባንክ ያለ ገንዘብን ወዘተ....ለየብቻቸው ካፒታል ብለው ሊጠሩ እንደሚችሉ አድርገው ያቀርቧቸዋል። ይህ የቡርዧ ኢኮኖሚ ሊቃውንት የካፒታል ትርጉምና ገንዛቤ የወዝአደሩን መበዝበዝ ለመሸፈን ሆን ብሎ የተቀናጀ ነው። ነገሩን በጥሞና ከተመለከትነው ምርትን ለማምረት አስፈላጊ የሆኑና ከላይ የተጠቀሱት ነገሮች በተናጠል ካፒታል ሊባሉ አይችሉም።

ለምሳሌ ገንዘብን እንውሰድ። ቀደም ሲል ባለፈው ምዕራፍ እንደተጠቀሰው፣ ገንዘብ የሸቀጥ ምርትና ልውውጥ የዕድገት ውጤት ነው። ኅብረተሰብ በተለያዩ የዕድገት ደረጃው ውስጥ የተለያዩ የከበሩ ማዕድናትን በኋላም ወርቅን እንደ ጋራ መገበያያ በማድረግ ሲገለገል ቆይቷል። ገንዘብ በተለያዩ መልክና ቅርጽ እንደ ጋራ መገበያያ ሆኖ ማገልገል የጀመረው የስርዓተ ማኅበር ዕድገት የካፒታሊስት ስርዓተ ማኅበር ደረጃ ላይ ከመድረሱ በፊት/በባሪያውና በፊውዳሉ ስርዓቶች/ እንደነበረ በታሪክ የተረጋገጠ ነው። በቀደሙ ካፒታሊስት ሥርዓተ ማኅበሮች ውስጥ የገንዘብ ዓይነተኛ ሚና እንደልውውጥ አማካይነት ማገልገል እንደመሆኑ ካፒታል አልነበረም። ወደፊት በዝርዝር እንደሚብራራው ገንዘብ የካፒታልን መልክ የያዘው ተጨማሪ ተረፈ እሴትን ለመፍጠር የሥራ ኃይልና የምርት መገልገያዎችን ለመግዛ ማገልገል በጀመረበት በካፒታሊስት ሥርዓተ ማኅበር ብቻ ነው። በአጭሩ ገንዘብ ካፒታል የሚሆነው የብዝበዛ መሣሪያ ሲሆን ነው።

የምርት መገልገያዎችንም ብንወስድ ሁኔታው ከገንዘብ የተለየ አይደለም። በማናቸውም ስርዓተ ማኅበር ቢሆን ዓይነቱ ይለያይ እንጂ


የማምረት ተግባር እስከ ተከናወነ ድረስ የማምረቻ መሣሪያም የግዴታ ይኖራል፡፡ የማምረቻ መሣሪያዎችና የምርት ተገብሮች ወዘተ...በቀደም ካፒታሊስት ስልተ ምርቶች ነበሩ፡፡ በኮሚኒስት ሥርዓተ ማኅበርም ውስጥ ይኖራሉ፡፡ ስለዚህ የምርት መገልገያዎች ለብቻቸው ካፒታል ሊሆኑ አይችሉም፡፡ ካፒታል የሚሆኑት ከቀጥር ሥራ ጋር በመቆራኘት ተረፈ እሴት ለመፍጠርና አምራችን ኃይል ለመበዝበዝ በሚውሉበት በካፒታሊስት ሥርዓተ ማኅበር ብቻ ነው፡፡

ካፒታል ለገንዘብ፣ ለማምረቻ መሣሪያዎች፣ ለአክስዮን ቦንድ ወይም ድርሻ በተናጠል የተሰጠ ስም ባይሆን እነዚህ የተጠቀሱት ነገሮች በሙሉ በአንድ በተወሰነ ማኅበራዊና ታሪካዊ ሁኔታ ከቀጥር ሥራ ጋር ተጠቃለው ቢገኙ የሚሰጣቸው ስም ነው፡፡ ለምሳሌ አንዱ ሰው ለኑሮው በጣም አስፈላጊ የሆኑትን ምግብ ልብስና የመሳሰሉትን ቢገዛ የገዛበት ገንዘብ ተራ የጋራ መገበያያ እንጂ ካፒታል አይባልም፡፡ በያዘው ገንዘብ የፍጆታ ዕቃ ብቻ ባይሆን የምርት መገልገያ መሣሪያዎች ቢገዛም እንኳ፣ ከነዚህ የማምረቻ መሣሪያዎች ጋር የተቆራኘው ሥራ የሌላ የተቀጠረ ሰው ሥራ ባይሆን የራሱ ሥራ እስከሆነ ድረስ የማምረቻ መሣሪያውን ለመግዛት ያወጣው ገንዘብ ካፒታል አይባልም፡፡ የማምረቻ መሳሪያውም በተናጠል ካፒ ታል አይደለም፡፡

ካፒታል ሊከሰት የሚችለው ገንዘብና የማምረቻ መሣሪያዎች ከቀጥር ሥራ ጋር ተዋህደው፣ ቀጥር ሥራን በመበዝበዝ ትርፍ ሲያስገኙ የቻሉ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡ የካፒታል ዝባዩ ገጽታዎች ያለ ቀጥር የሥራ



የካፒታልን አመጣጥ ለማሳየት "ታዳጊ አገሮች ከማርክሳዊ ፖለቲካ ኢኮኖሚ አንፃር" ከሚለው የዩሪ ፖፖቭ መጽሐፍ የተወሰደ


Proudly brought to you by
www.binyamhk.wordpress.com

ኃይል ካፒታል ሊባሉ አይችሉም። በሌላ አነጋገር ያለ ወዝአደሩ የሥራ ኃይል ብዝበዛ ካፒታል የሚባል ነገር ሊኖር አይችልም። ማርክስ እንዳለው፣ "ካፒታል የቅጥር ሰራን መኖር እንደሚጠይቅ ሁሉ፣ ቅጥር ሥራም የካፒታልን መኖር ይጠይቃል።" ካፒታልና ቅጥር ሥራ የአንድ ዓይነት ግንኙነት ሁለት ገጽታዎች ናቸው። ቅጥር ሥራ ደግሞ በሥርዓተ ማኅበራት የዕድገት ታሪክ ሁለንተናዊ በሆነ መንገድ ሊሰፍን የቻለው በካፒታሊስት ስርዓተ ማኅበር ውስጥ ብቻ ነው።

## 2. <u>የካፒታል አመጣጥ፣</u>


የቡርዧ የኢኮኖሚ ምሁራን ልክ በተፈጥሮ ቀንና ሌሊት እንደሚኖር፣ በኅብረተሰብ ውስጥ ሀብታምና ድሀ ከጥንት ጀምሮ የነበረ፣ ትጉሆችና ገንዘብ ቆጣቢዎች ቀስ በቀስ ሀብት ሲያጠራቅሙ ሰነፎች ግን በስንፍናቸውና በአባካኝነታቸው ድሀ ሆነው ቀሩ ይላሉ። ይሁንና ይህ የቡርዧ የኢኮኖሚ ምሁራን አባባል ትክክል አይደለም። በካፒታሊስት ሥርዓት ውስጥ ሀብታምና ድሀ ሊኖሩ የቻሉት ሰነፎችና ትጉሆች በመኖራቸው አይደለም። ሀብታምነት የትጋትና የሠራተኛነት፣ ድሀነት የስንፍና ውጤት አይደለም። ምክንያቶቹ ሌሎችና ፍጹም የተለዩ ናቸው። እነሱንም ከዚህ በታች ባጭሩ እንዳበባ ቸቀለን።

ለካፒታሊዝም ማደግ ሁለት መሠረታዊ ነገሮች መሟላት ነበረባቸው። <u>አንደኛው፣</u> የምርት መገልገያዎችና ገንዘብ ቀስ በቀስ በጥቂቶች እጅ መከማቸትና <u>ሁለተኛው፣</u> በዚህም ምክንያት የምርት መገልገያዎች ባለቤትነታቸውን ያጡ፣ ቀደም ሲል ባለቤትነት የነበራቸው አብዛኛዎቹ ሰዎች ለመኖር የግድ የሥራ ኃይላቸውን ለመሸጥ መገደዳቸው ነበር። ይህ እንዴት ሊሆን እንደቻለ ከዚህ ቀጥሎ እናያለን።

የካፒታል መጻበርና ካፒታሊዝም በተለይ በአውሮፓ ውስጥ በ16ኛው ምዕተ ዓመት ሊስፋን የቻለው ከመቀጸበት አልነበረም። ከ15ኛው ምዕተ ዓመት ጀምሮ የምርት መገልገያዎችን በጥቂቶች እጅ የማሰባሰብና፣ በንግድ ካፒታል አማካይነት ገንዘብን በከፍተኛ ደረጃ የማካበቱ ሂደት ሲካሄድ የቆየ ነገር ነበር። ከዚህም በተወማሪና በዚህም ምክንያት በአውሮፓ የሳይንስና የቴክኖሎጂ ማደግ ከእምቶቹ ማደግ ጋር ቀጥታ ግንኙነት ነበረው።

ለምሳሌ በ15ኛው ምዕተ ዓመት በአውሮፓ አህጉር ውስጥ ማተሚያ ቤት ተቋቋመ። በመቋቋሙም ዕውቀትን ከሥፍራ ሥፍራ በሰፊው በማስተላለፍ ከ16ኛው ምዕተ ዓመት ጀምሮ 18ኛው ምዕተ ዓመት ድረስ፣ ቀደም ካሉት ዘመናት ይልቅ፣ ለቴክኖሎጂ በከፍተኛ ፍጥነትና ጥልቀት መጻበር ምክንያት ሆኗል። የጠመንጃ ባሩድ የተሠራው በዚሁ በ15ኛው ምዕተ ዓመት በቻይና ቢሆንም፣ አውሮፓውያን ዕውቀቱን በመቀበም ጠመንጃን በብዛት ሠርተው አውጥተው የመጀመሪያ ደረጃ የካፒታል ክምችት አንዱ አካል የሆነውን የቀኝ ግዛት ማስፋፋት ሊያከናውኑበት ችለዋል። የአቀጣጫ ማመልከቻ /ኮምፓስ/ መፈልሰፍም መርከበኞች አቅጣጫቸውን ባይበቁ ወደ ሩቅ ሥፍራእንዲጓዙ ረድቶአ ጀዋል። ይህም ለካፒታሊዝም ዕድገት አመቺ ሁኔታ ለፈጠረው ንግድ በዓለም አቀፍ ደረጃ እንዲስፋፋ ረድቶአል።

የንግድ ካፒታል ዘመን /ሜርካንቲሊዝም/ እየተባለ በሚታወቀው ከ15ኛው እስከ 18ኛው ምዕተ ዓመት ድረስ ንግድ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተስፋፍቶ ነበር። በተለይ ከ17ኛው ጀምሮ እስከ 18ኛው ምዕተ ዓመት አጋማሽ ድረስ በአውሮፓ ውስጥ ካፒታሊዝም ሥር እየሰደደ የሄደባቸው አገሮች /ሆላንድ፣ እንግሊዝ፣ ፈረንሳይ፣/ ከሌላው ክፍለ ዓለም ጋር ባልተመጣጠነ ንግድ ባቢያ ከፍተኛ ትርፍ ያካብቱ ነበር።




London School of Economics

ካፒታል ታክስን በተለያየ መልክ በማስፋፋት እንዴት የካፒታል ክምችት ሊፈጥር እንደቻለ ለማሳየት የ20ኛው ምዕት ዓመት ታሪክ ከሚለው የተወሰደ



Proudly brought to you by
www.binyamuk.wordpress.com

በአንዱ በኩል በቀጥተኛ ቅኝ አገዛዝ አማካይነት ካፒታሊዝም ያላደገባቸውን አገሮች በተዛባ ንግድ አማካይነት መበዝበዝ፤ በሌላ በኩል ደግሞ በዚሁ በዝበዛ አማካይነት ሊቀላጠፍ የቻለውን የቴክኖሎጂ ዕድገት በማፋጠንና ምርትን በከፍተኛ ደረጃ በማካሄድ አነስተኛ አምራቾች በብዛት እንዲከስሩ ተደርጓል:: ለምሳሌ ያህል በእንግሊዝ አገር በ17ኛው ምዕተ ዓመት መባቻ ላይ "አበከፌ ሕጐች" ተብለው የሚታወቁ ሕጎችን በማውጣት፣ በጊዜው ታዳጊ የነበረው የእንግሊዝ የቡርዧው መደብ በመንግሥት ኃይል በመጠቀም ገበሬዎችን ከገጠር በኃይል በማፈናቀል መሬታቸውን ለከበርቴ አራሾች በሽያጭ በማደላደል በብዛት ከገጠር ወደ ከተማ እንዲጎርፉና፣ ለካፒታሊዝም መስፋፋት አስፈላጊ የሆነውን ርካሽ የሥራ ኃይላቸውን ለሽያጭ እንዲያቀርቡ አስገድደአቸው ነበር:: በአጠቃላይ የካፒታሊዝም ዓይነተኛ ገጽታ የሆኑትን ትላልቅ የማምረቻ ተቋሞችን ለማቋቋም አስፈላጊ የነበረውን የካፒታል ክምችት ካፒታሊዝም ያጠራቀመው እንደሚከተለው ነበር:—

ሀ. በአገር ውስጥ የሚገኙ አነስተኛ አምራቾችን በማቆርቆዝና በነበረው በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ለመጠቀም በሚያስችለው የገንዘብ ኃይል አማካይነት ከነበራቸው የማምረቻ መሣሪያዎች ባለቤትነት በማላቀቅ፣

ለ. ከማምረቻ መሣሪያ ባለቤትነት የተላቀቀው በረው ገበሬና የዕደ ጥበብ አምራች ርካሽ የሥራ ኃይል አቦቃቂ በሆነ መንገድ በከፍተኛ ደረጃ በመበዝበዝ፣

ሐ. በዚሁ ሂደት ውስጥ የቡርዧው መደብ በፖለቲካ ስልጣኑ በመጠቀም ከተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ከፍተኛ ግብር በመሰብሰብ ካፒታሉን ለማዳበር ሊጠቀምበት ቻለ፣



በካፒታሊዝም የቅኝ አገዛዝ ሥርዓት ለከፍተኛ ትርፍ ርካሽ ጉልበት ሲመለመል (ከመስከረም መጽሔት ቅጽ 1 ፣ ቁጥር 4)


Proudly brought to you by
www.binyamuk.wordpress.com

መ. ሰፊ የቅኝ ግዛቶችን ይዞ በዘበዘ፤

የኢንዱስትሪ አብዮት የተጀመረባት እንግሊዝ ለፋብሪካዎቿ አስፈላጊ የሆኑትን ጥሬ ዕቃዎችና ርካሽ የሥራ ኃይል ለማግኘት በሁሉም ክፍለ ዓለማት መረቧን ዘርግታ ነበር :: እንደውም በዘመኑ የእንግሊዝ የቡርዧ መደብ በቅኝ ግዛቱ ሥር ስለነበሩ አገሮች ብዛት ሲናገር "በብሪታኒያ መንግሥት ግዛት ውስጥ ፀሐይ አትጠልቅም" የሚል አባባል ነበረው:: ይህም አባባል የእንግሊዝ የቡርዧ መደብ የመጀመሪያ ደረጃ የካፒታል ክምችቱን ከሌሎች የአውሮፓ አገሮች ቀድም ብሎ በፊት ባለው መንገድ ለማከናወን የቻለው በሥሩ በነበረው ሰፊ ያለ የቅኝ ግዛት መሆኑን በግልጽ ያሳያል::

ሠ. የባሪያን የሥራ ኃይል አሰቃቂ በሆነ ሁኔታ በዘበዘ፤

ከንግድ ካፒታል/ሜርካንቲሊዝም/ ዘመን ጋር የተያያዘው ቅኝ ግዛት የማስፋፋቱ ትግል በሌላ መልኩ ቅኝ ግዛቶች በተለይም ከአፍሪካ አህጉር በዛ ያለ ለመሥራት የሚችለውን የኅብረተሰብ ክፍል ወደ ሌሎች ክፍለ ዓለማት በተለይም ወደ ሰሜን አሜሪካ በማጋዝ በዚያ አገር ደቡባዊ ክፍል አሰቃቂ በሆነ መንገድ የሥራ ኃይሉን በመበዝበዝ ለታዳጊ ኢንዱስትሪዎች ጥሬ ዕቃ እንዲያቀርብ መደረጉ ነበር :: ይህም የባሪያ ንግድ እየተባለ የሚታወቀውን ለመጀመሪያ ደረጃ የካፒታል ክምችት አስተዋጽኦ ያደረገ ነው::

ካፒታሊዝም እንግዲህ በዚህ ዓይነት ሁኔታ ሊያድግና ሊያንሰራራ ቻለ ::

## 3. የገንዘብ ወደካፒታል መለወጥና የሥራ ኃይል ወደሸቀጥነት መቀየር

### 3.1 ተረፈ እሴት ከዝውውር አይመነጭም

ገንዘብ ወደ ካፒታል ሊለወጥ የቻለበትን ሂደት ከመዘርዘራችን በፊት በመጀመሪያ ደረጃ በካፒታሊስት ሥርዓት የአመራረቱ ዘይቤ ዋነኛ ዓላማ ፍላጎትን ማርካት ሣይሆን ተረፈ እሴትን ማግኘት መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። ገንዘብ ወደካፒታል የሚለወጥበት ሂደት የተለያዩ ደረጃዎችን ያቀፈ ቢሆን፣ ባጭሩ ይህን ሂደት በሚከተለው ቀመር ማመልከት ይቻላል፣

ገንዘብ → ሸቀጥ → ገንዘብ ወይም ገ → ሸ → ገ

እዚህ ላይ ማስተዋል የሚገባን ነገር በቀደመ ካፒታሊዝም የነበረውን የሸቀጥ ዝውውር ቀመር ስንመለከት ዓላማው ሸቀጥ ሸጦ ሌላ ሸቀጥ ለመግዛት ቢሆን፣ ካፒታል የሚገለጽበትን ቀመር ስንመረምር ግን ዓላማው ሸቀጥን ገዝቶ መልሶ ለመሸጥ መሆኑን እንገነዘባለን።

እዚህ ላይ ጥያቄ ለማንሳት ይቻላል። በቀደመ ካፒታሊዝም የነበረውን የልውውጥ ሁኔታ ስንመለከት በመጀመሪያየነበረው ልውጡ ሸቀጥን በሸቀጥ /ሸ—ሸ/ የሚለውጥ ነበር። በመጀመሪያውና በመጨረሻው ላይ የተመለከቱትሸቀጦች የሰውን የተለያየ ፍላጐት የሚያረኩ በመሆናቸው ልውውጡ ሸቀጥ በሸቀጥ ነበር። ይህ በመጀመሪያ ላይ የነበረ ቢሆን በልውውጥ ዕድገት ውስጥ ገንዘብ ከተከሰተ በኋላ ግን ምርትን ወደ ገንዘብ ከዚያ ወደሌላ ዓይነት ምርት መለየወጥ ተጀመረ። ለምሳሌ አንድ ገበሬ ምርቱ ባበላሸበት፣ ወይም ለቡም ሆነ ለቤተሰቡ ልብስ

ለመግዛት ቢያስብ፣ ወይም ሳምባ ሊገዛ ቢፈልግ ያመረተውን እህል ገበያ በማውጣት ሸጦ ባገኘው ገንዘብ ለማምረትም ሆነ ለፍጆታ የሚያገለግለውን ዕቃ ገዝቶ ይመጣል። ይህን ሁኔታ በቀመር መልክ ብናስቀምጠው /ሸ—ገ—ሸ/ ይሆናል።

ገበሬው አንዱ ዓይነት ሸቀጥ /በምሳሌው እንደተመለከተው እህል/ ሸጦ ሌላ ሸቀጥ/ በምሳሌ እንደተመለከተው ምፈር፣ ልብስ፣ ሳምባ ሊሆን ይችላል፣ ከነዚህ መካከል አንደኛውን/ ገዝቶ መመለሱ በልየው የገዛው ሸቀጥ የቤን የተወሰነ ፍላጐቱን የሚያረካለት ከመሆኑም በላይ የሚለየወጡት ሸቀጦች እሴት ተመጣጣኝ ነው። በፖለቲካዊ ኢኮኖሚ አጠራሩ በልየው የተገኘው ወይም የተገዛው ሸቀጥ ሊገዛ የሚችለው የተለየ የጠቀሜታ እሴት ስላለው ነው:: ማለትም ቀደም ሲል የተጠቀሰውን ምሳሌ በማሰብ፣ ገበሬው ለመብላት ካለው ፍላጐት በተጨማሪ ሌሎች ፍላጐቶችን ለማርካት የሚያበረ ልጉትን ነገሮች በሸቀጦች ልውውጥ /በገበያ/ አማካይነት ያገኛቸዋል። ስለዚህ የልውውጡ ዓላማ ትርፍ ለማግኘት ሣይሆን ፍላጐትን ለማርካት ብቻ ነው።

የካፒታል መገለጫ ዘዴ በተመለከተው ቀመር ላይ እንቅስቃሴው፣ አርግጥ ያለማቋረጥ የሚካሄድ ቢሆንም፣ በመሠረቱ ከገንዘብ ይጀመርና እንደ ገና ወደገንዘብ ይመለሳል። ቀደም ሲል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል እንደተገለው፣ ጥያቄው ሊነሳ የሚችለው እዚህ ላይ ነው። አንዱ ዓይነት ፍላጐትን የሚያረካ ሸቀጥ/ወይም የጠቀሜታ እሴት ያለውን ሸቀጥ/ ሌላ ዓይነት ፍላጐትን በሚያረካ ሸቀጥ መለወጡ ግልጽ የሆነና የማያከራክር ነው።

በካፒታሊስት ሸቀጥ ምርት ውስጥ የሚታየው እንቅስቃሴ ሸቀጥን በማምረት በልውውጥ አማካኝነት የአምራቹን መሠረታዊ ፍላጐት ለማርካት

ሳይሆን የተመረተውን ሸቀጥ ወደ ገንዘብ ለመለወጥ ነው። ይሁን እንጂ በካፒታሊስት ሸቀጥ ምርት ውስጥ በልውውጡ መጀመሪያ ተይዞ የነበረው ገንዘብና በልውውጡ መወረሻና በልውውጡም አማካይነት የተገኘው ገንዘብ በዓይነት አንድ ይሁን እንጂ፣ በመጠን የተለያየ ነው። በለዚህ የምርትና የልውውጥም ጥቅም በመወረሻ የተገኘው ገንዘብ ከመጀመሪያው በመጠን የሚበልጥ ሆኖ መገኘቱ ነው። ይህ ሁኔታ በሚከተለው ቀመር ማለትም በ/ገ—ሸ—ገ/ ይገለፃል።

በፖለቲካ ኢኮኖሚ ጥናት ውስጥ ወሣኙ የሆነው ጥያቄ የሚነሳው እዚህ ላይ ነው። ከልውውጡ በኋላ በመወረሻ ላይ የሚገኘው ገንዘብ በመጠን ልውውጡ ከመከናወኑ በፊት ከነበረው ገንዘብ በልጦ የሚገኝ ከሆነ ትርፉ ወይም በኋላ እንደሚገለጸው ተረፈ እሴት የሚባለው ነገር የሚመነጨው ከሽያጭና ከግዢ፣ ከልውውጥ ወይም ከገበያ ነው ማለት ነውን? ወይም በተለምዶ አነጋገር፣ ትርፍ የሚገኘው አንድ ሸቀጥ በርካሽ ዋጋ ገዝቶ በውድ ዋጋ በመሸጥ ነው?

በአንዳንድ የቡርዧው የኢኮኖሚ ሊቃውንት አመለካከት የትርፍ ምንጭ በገበያ ውስጥ አንዱን ሸቀጥ በርካሽ ገዝቶ መልሶ በውድ መበሸጥ ወይም በሸቀጦች የዝውውር ሂደት ውስጥ የሚገኝና በዚህም አማካይነት የሚገለጽ ነው ቢሉ፣ የማርክሳዊ የፖለቲካ ኢኮኖሚ አቋም ግን ከዚህ በጣም የተለየ ነው።

እንደዚህ ከሆነ ታዲያ በካፒታሊዝም ሥርዓት ከመነሻው ገንዘብ በልጦ የሚገኘውና በተለምዶ አጠራሩ በአጠቃላይ ትርፍ ተብሎ የሚጠራው ምንጩ ምንድነው? ወይንም ደግሞ በሌላ አነጋገር ተረፈ እሴት ከምን ይመነጫል?

ባለፉት ምዕራፎች በዝርዝር እንደተመለከትነው የዕቃዎች ልውውጥ የሚካሄደው በእሴታቸው ላይ በመመሥረት እንደመሆኑ ካፒታሊስቱ አንዱን ሸቀጥ ለማምረት የሚያስፈልጉትን ነገሮች ማለት የሥራ ኃይል፣ ጥሬ ዕቃና የማምረቻ መሣሪያዎች የሚገዛው በእሴታቸው ነው። በተመሳሳይ መልክ የሚያመርታቸውንም ሸቀጦች ሊሸጥና ሊለውጥ የሚችለው በእሴታቸው ወይም ሸቀጦችን ለማምረት በወሰደበት አስፈላጊ ማኅበራዊ የሥራ ጊዜ መጠን ነው። ስለዚህ ምንም እንኳን እሴት የሚገለጸው በልውውጥ ሂደት ውስጥ ቢሆንም የማናቸውም ሸቀጥ እሴት የሚመነጨው በምርት ሂደት ውስጥ ያንን ሸቀጥ ለማምረት በፈበበው አስፈላጊ ማኅበራዊ የሥራ ጊዜ መጠን እንደመሆኑ በልውውጥ አማካይነት ተጨማሪ እሴት ሊፈጠር አይችልም። በሌላ አነጋገር ልውውጥ በዕቃ መልክ ያለን እሴት በገንዘብ መልክ የሚቀይርበት ሂደት እንደመሆኑ በዚህ ሂደት ውስጥ የእሴቱ መልክ እንጂ መጠኑ ሊለወጥ አይችልም። ባጭሩ ልውውጥ እኩሌታ እሴት ባላቸው ሸቀጦች መካከል የሚካሄድ እንደመሆኑ ትርፍ እሴት ወይም አጠቃላይ ትርፍ ቡርዧዎች እንደሚሉት አንዱን ሸቀጥ በርካሽ ዋጋ ከመግዛትና በውድ ከመሸጥ ወይም በገበያ ውስጥ ከሚታየው የዋጋ፣ ውጣ ውረድ የሚመነጭ አይደለም።

እርግጥ በሸቀጦች የአቅርቦትና የፍላጎት መጠን አለመጣጣም የተነሣ በገበያ ውስጥ የሸቀጦች ዋጋ ከእሴታቸውም በላይ ሆነ በታች ከፍና ዝቅ ሊል ይችላል። ይህ የዋጋዎች ከእሴታቸው በላይና በታች መዋዠቅ አንዱ ካፒታሊስት ከሌላው ካፒታሊስት ኪሣራ የሚከብርበትን ሁኔታ የሚያባይ እንጂ የኢቤቅ ጭማሪን የሚያመለክት አይደለም። ይህንን በይበልጥ ለመገንዘብ የሚከተለውን ምሳሌ እንመልከት።

ለምሳሌ ያህል በአንድ ወቅት በአንድ ኅብረተሰብ ውስጥ የተመረቱ ብር ቶካናች 100 ናቸው እንበል። የአንዱ ብር ቶካን እሴት በዋጋ ቢገለጥ

10 ሣንቲም ነው ብንል፣ የመቶው ዋጋ 10 ብር ይሆናል። እነዚህ ብር ቁጥሮች በልውውጥ ውስጥ ቢገቡ ማለትም ቢሸጡና ቢገዙ 50ዎቹ በስምንት ሣንቲም፣ 50ዎቹ በአሥራ ሁለት ሣንቲም ሂሣብ በሰዎች እጅ ቢለዋወጡ ግማሹ ሻጭ ቢያተርፍ ግማሹ ገዥ ይከስራል፣ ግማሹ ገዢ ቢያተርፍ ግማሹ ሻጭ ይከስራል እንጂ በአጠቃላይ ግን እሴታቸው ያው ማለትም 10 ብር ነው። አንዳንድ ሰዎች ቢያተርፉና አንዳንዶቹ ቢከስሩም በአጠቃላይ ኅብረተሰቡ ግን ያተረፈው ወይም ያከሰረው ነገር የለም።

በኅብረተሰብም ውስጥ ቢሆን ለሽያጭ በሚቀርቡ ሸቀጦች ብዛት ሣቢያ፣ ከገዢውና ከሻጩ ብዛት አንፃር ቢታይ ሁኔታው የተወሳሰበ መሆኑ ባይካድም፣ በይዘት ግን ፍሬ ነገሩ ቀደም ቢል በተጠቀሰው ተራና ቀላል ምሳሌ ሊገለጽ ይችላል። በካፒታሊስት ኢኮኖሚ ውስጥ /በማናቸውም ምርት ዓይነት ማኅበር ውስጥ/ <u>በአንድ በተወሰነ የጊዜ ክልል</u> ውስጥ የሚኖረው የምርት መጠንና እሴቱም የተወሰነ ነው። ምርቱን በመከፋፈሉ ረገድ ሁኔታው በተናጠል ቢታይ፣ አንዱ ካፒታሊስት በሌላው ኪሣራ ብዙ ሊያተርፍ፣ ወይም ሁኔታው የተገላቢጦሽ ከሆነ ሊከስር ይችላል። የኅብረተሰቡ ሀብት ግን ያው ነው። በክፍፍልና በዋጋ ውጣ ውረድ የምርት መጠኑም ሆነ እሴቱ ከፍ ወይም ዝቅ አይልም። ኪሣራውም ሆነ ትርፉ በጊዜው ባለው የምርት ውጤት ላይ የሚካናወንና ለርስ በርሱ የሚጣፉ በመሆኑ በልውውጡ ሂደት አማካይነት ኅብረተሰቡ በአጠቃላይ ትርፍ ምርት ወይም ሀብት አላገኘም። በመሆኑም አጠቃላይ ከሆነው የኅብረተሰብ ሁኔታ ስንነሳ ከልውውጡ ሂደት ማለትም በቀናሽ ገዝቶ በውድ በመሸጥ ትርፍ ወይም ተጨማሪ ሀብት አይገኝም።

'ካፒታሊስቶች በተናጠል ቢወሰዱ በገበያ አማካይነት አንዱ ባንዱ ኪሣራ ሊከብር ቢችልም፣ የአንዱ መክበር በሌላው መክሰር ቢለጫፉ፣

የካፒታሊስቱ መደብ አጠቃላይ ዉርሻ አይቀየርም፡፡ አንዱ ሻጭ በሌላው ገዥ ላይ በማትረፍ ቢከብርም፣ ሻጩም ደግሞ ሎልቦ ገዢ በመሆኑ ከዚህም አንፃር ቢታይ በርካሽ ገዝቶ በዉዱ የመሸጡ ሁኔታ አርስ በርሱ የሚጣፋ በመሆኑ የካፒታሊስቱ መደብ በአጠቃላይ የሚከብረው በዚህ ዓይነት መንገድ አይደለም፡፡

ማርክስ እንዳለው፣ "ከማናቸውም አገር የካፒታሊስቱ መደብ በዚህ ዓይነት ሁኔታ /አንዱ ለሌላው ሸቀጥን ከዋጋው በላይ አስወድዶ በመሸጥ/ ካለው ሀብት በላይ ሊወመር አይችልም፣"

/ካፒታል ቅጽ 1፣ ገጽ 160/

ተረፈ እሴት ከልውውጥ ሂደት የማይመነጭ ቢሆንም ልውውጥ ከሌለ ሊከሰት እንደማይችል መገንዘብም ያስፈልጋል፡፡ ካፒታሊስቱ ገንዘቡን ወደካፒታል ሊለውጥና ሊያዳብረውም ሊሄድ የሚችለው በገንዘቡ የሥራ ኃይልና ጥሬ ዕቃ በመግዛት ሊሸጡና ሊለወጡ የሚችሉ ሸቀጦችን በማምረት ብቻ ነው፡፡ በዚህ ዓይነት ተጨማሪ እሴት በመፍጠር በገበያ አማካኝነት እሴቱን ወደገንዘብ ካልቀየረ በስተቀር ገንዘብ መያዝ ብቻ ካፒታል አይፈጥርለትም፡፡ በለዚህ ማርክስ እንዳለው ተረፈ እሴት በልውውጥ ሂደት ውስጥ ሊመነጭ የማይችለውን ያህል ካልልውውጥም ሊከሰት አይችልም፡፡ በሌላ በኩል ቀደም ቢል እንደተመለከትነው ልውውጥ የሚካሄደው በእሴት ሕግ በመገዛት የእሴት እኩሌታ ባላቸው ሸቀጦች መካከል ነው፡፡ ካፒታሊስቱ ተረፈ እሴት የሚያገኘው በዚህ የእሴት ሕግ በመገዛት ነው፡፡ ተረፈ እሴት የሚመነጨው በምርት ሂደት ውስጥ ሆኖ ያለልውውጥ ሊከሰት አለመቻሉና ልውውጡም በእኩሌታ እሴት ላይ የተመሠረተ መሆኑ የተረፈ እሴት ሕግ የእሴትን ሕግ የሚቃረን ያስመስለዋል፡፡

የተረፈ እሴት ሕግ የእሴትን ሕግ የማይቃረን ከመሆኑም በላይ በእሴት ሕግ ላይ የተገነባ መሆኑን በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ሳይንሳዊ በሆነ መልክ የገለጸውና ያረጋገጠው ታላቁ የወዛደሩ ምሁር ካርል ማርክስ ነው።

የሸቀጦች ልውውጥ፣ በአጠቃላይ ሲታይ፣ በእኩያዊ/ ተመጣጣኝ/ የእሴት ልውውጥ ላይ የተገነባ ከሆነ፣ ተረፈ እሴትም በልውውጡ ሂደት ሊገኝ ካልቻለ፣ ማርክስ እንዳለው ቡርዧው ገንዘቡን ወደ ካፒታል ለመለወጥ የግዴታ በምርት እንቅስቃሴው ውስጥ ከራሱ እሴት በላይ ተረፈ እሴት ለማስገኘት የሚችል ልዩ ሸቀጥ በገበያ ውስጥ ማግኘት ይኖርበታል። ይህም ሸቀጥ የወዝአደሩ <u>የሥራ ኃይል</u> ነው። ወደፊት በዝርዝር እንደምናየው ማናቸውንም ሸቀጥ ለማምረት አስፈላጊ ከሆኑት ነገሮች ማለትም ከማምረቻ መሣሪያዎች፣ ጥሬ ዕቃና የሥራ ኃይል መካከል፣ በምርት ሂደት ውስጥ የተቀሩት ሁሉ እሴታቸውን አዲስ ወደሚመረተው ሸቀጥ በማስተላለፍ ቢወስኑ፣ የሥራ ኃይል ግን ከእሴቱ በላይ ተጨማሪ እሴት ይፈጥራል። ይህ የሥራ ኃይል ተባለው ምርትን ለማምረት አስፈላጊ ከሆኑት ነገሮች ሁሉ እንዴት ብቸኛ የእሴት አስገኚ ወይም ፈጣሪ ሊሆን ቻለ? የሥራ ኃይል የተባለው ሸቀጥ ስለአሉት ጠባዮች ከዘረዘርን በኋላ እንዴት የእሴት ምንጭ ሊሆን እንደቻለ ለማስረዳት እንሞክራለን።

## 3.2 <u>የሥራ ኃይል ሸቀጥ ስለመሆኑና ስለሚኖሩት ጠባዮች</u>

በካፒታሊስት ሥርዓት የወዝአደሩ የሥራ ኃይል እራሱ ሸቀጥ ነው፣ ስለሆነም ማናቸውም ሌላ ሸቀጥ ያሉት ጠባዮች በሙሉ ይኖሩታል። ከዚህ በተጨማሪ ግን ወደፊት እንደምናየው ማናቸውም ሌላ ሸቀጥ የሌለውና የሥራ ኃይል ብቻውን ያለውም ጠባይ አለው።

የሥራ ኃይል በው በምርት ሂደት ውስጥ ለሥራ ያለው አካላዊና አዕምሮአዊ ችሎታ ነው። ይህ ለመሥራት ያለ ችሎታ ጥንትም የነበረና ወደፊትም የሚኖር ነው። ሸቀጥ ሊሆን የሚችለው ግን በካፒታሊስት ሥርዓት ብቻ ነው። የሥራ ኃይል ሸቀጥ ሊሆን የሚችለው ሁለት ነገሮች ቢሟሉ ነው።

1ኛ/ ወዝአደሩ ከማምረቻ መሣሪያ ባለቤትነቱ የተላቀቀና ለመኖር የሥራ ኃይሉን ለመሸጥ ቢገደድና፣

2ኛ/ ወዝአደሩ በግለሰብ ደረጃ የሥራ ኃይሉን ለፈለገው ቀጣሪ ለመሸጥ ወይም ላለመሸጥ "መብትና" "ነፃነት" ያለው ቢሆን ነው።

የነዚህ ሁለት ሁኔታዎች በአገር አቀፍ ደረጃ በአብዛኛው መሟላት የካፒታሊስት ሥርዓተ ማኅበር መንበሩን ያበስራል። እነዚህ የሥራ ኃይልን ሸቀጥ የሚያደርጉ ሁኔታዎች መሟላት ከተፈጥሮ ጋር የመጡ ወይም የተፈጥሮ ሕግ ውጤቶች ሣይሆኑ፣ የፊውዳሉ ሥርዓተ ማኅበር መፈራረስ፣ የኢኮኖሚያዊ ይዞታ ለውጦችና በአጠቃላይ የኅብረተሰብ የታሪክ ዕድገት ውጤቶች ናቸው።

በአነስተኛ የሸቀጥ ምርት ወቅት አምራቹ ይሸጥ የነበረው የሥራ ኃይሉን ሣይሆን የሥራ ኃይሉን ያፈሰሰበትን ሌላ ሸቀጥ ነበር። ምክንያቱም የማምረቻ መሣሪያ ባለቤትነቱን ወርሶ አላጣም ነበርና።

ከኢንዱስትሪ አብዮት በኋላ፣ ከዚያም በፊት ለብዙ ጊዜ ቀስበቀስ ሲከናወን በነበረው የመጀመሪያ ደረጃ የካፒታሊስት ክምችት ሂደት አማካይነት፣ አነስተኛ የሸቀጥ ምርት ደረጃ በደረጃ በካፒታሊስት

የሸቀጥ ምርት እየተተካ ሲመጣ፣ አነስተኛ ሸቀጥ አምራቾች በጊዜው በነበረው ዘመናዊ ቴክኖሎጂ እየተተኩ ቀደምሲል ከነበራቸው የማምረቻ መሣሪያ ባለቤትነታቸው ተገለሉ:: ቀደም ሲል የማምረቻ መሣሪያ ባለቤትነት በነበራቸው ጊዜ የሥራ ኃይላቸውን በባለቤትነታቸው ሥር ካለው የማምረቻ መሣሪያ ጋር በማቀናጀት ሸቀጥ አምርተው በመሸጥ የሚፈልጉትን ሸቀጥ ለመግዛት ይችሉ ነበር::

አነስተኛ ሸቀጥ አምራቾች ከቴክኖሎጂ ዕድገትና ከካፒታሊዝም መስፋፋት ጋር ቀስ በቀስ አብዛኞቹ የማምረቻ መሣሪያ ባለቤትነታቸውን ሲያጡ በቀራቸው የሥራ ኃይል ብቻ ሸቀጥ ሊያመርቱ አልቻሉም:: ሸቀጥ ለማምረት የሥራ ኃይላቸውን የማምረቻ መሣሪያ ባለቤትነት ላለው አዲስ የካፒታሊስት መደብ ለመሸጥ ተገደዱ::

በአነስተኛ የሸቀጥ ምርት ወቅት አነስተኛ ሸቀጥ አምራቾች የሚሸጡት የሥራ ኃይላቸውን ሳይሆን የሥራ ኃይላቸውን ከምርት መገልገያዎቻቸው ጋር በማቀናጀት የፈጠሩትን ሌላ ዓይነት ሸቀጥ /መጥረቢያ፣ እህል፣ ወርቅ፣ ጫማ፣ ወዘተ.../ ነበር:: በካፒታሊስት የሸቀጥ ምርት ወቅት ግን ከማምረቻ መሣሪያ ባለቤትነት የተገለለው ወዝአደር እንደአነስተኛ ሸቀጥ አምራች የተለያዩ ሸቀጣ ሸቀጦችን ሳይሆን ሊሸጥ የሚችለው ማናቸውም ሸቀጥ ለማምረት አስፈላጊ የሆነውን የሥራ ኃይሉን ነው::

የሥራ ኃይል ሸቀጥ እስከሆነም ድረስ ማናቸውም ሸቀጥ የሚኖረው ጠባይ ይኖረዋል:: የሚኖሩትም ጠባዮች የጠቀሜታ እሴትና የልውውጥ እሴት በመባል ይታወቃሉ::

ማናቸውም ሌላ ሸቀጥ የሌለውና የሥራ ኃይል የሚባለው ሸቀጥ ብቻ ያለው ባሕርይ የሥራ ኃይሉን የሚሸጠው ወዝአደር በምርት ሂደት

ውስጥ ከራሱ የሥራ ኃይል እሴት በላይ ተጨማሪ ተረፈ እሴት የመፍጠር ችሎታው ነው። ይህም የሥራ ኃይል የጠቀሜታ እሴት ይባላል። ለምሳሌ የተወሰነ ሥራ ለመሥራት ወዝአደር ከበደ የሥራ ኃይሉን በማፍሰስ የተወሰነ ጊዜ ይሠራል። ያፈሰሰውን የመሥራት ኃይሉን ለመተካትና እንደገና ለመሥራት እንዲችል በአካባቢው ባለው የኑሮ ሁኔታ መሠረት በዝቅተኛ ደረጃ አካላዊ፣ ባሕላዊና ማኅበራዊ ፍላጎቶቹን ማርካት ይኖርበታል። እነዚህ ፍላጎቶች ሊረኩ የሚችሉት ደግሞ ወዝአደር ከበደ በሚያገኘው ምንዳ ሊገዛቸው ቢችል ነው። ባንዱ በተወሰነ አገር ውስጥ ባለ ዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ አንፃር /ወዝአደሩ ተበዝባዥ በመሆኑ ከካፒታሊስቱ ጋር ቢነፃፀር የግዴታ ዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ በለሚኖረው/ ወዝአደሩ ለሱና ለቤተሰቡ መሠረታዊ ፍላጎቶቹን ለማርካት የሚችሉ ሸቀጦችን ለማግኘት ይችል ዘንዱ የሥራ ኃይሉን የሚያፈሰበት አስፈላጊ የሥራ ጊዜ የወዝአደሩን የሥራ ኃይል የልውውጥ እሴት ያስገኛል።

ለመሆኑ የሥራ ኃይል እሴት እንዴት ይወሰናል?

የሥራ ኃይል እሴት የሚወሰነው ወዝአደሩ ባያቋርጥ ለመሥራት ይችል ዘንዱ ለሱና ለቤተሰቡ ለኑሮ የሚያስፈልጉ ነገሮችን ለማግኘት ባለው አቅም፣ ወይም ደግሞ በሌላ አነጋገር፣ ለኑሮ አስፈላጊና መሠረታዊ በሆኑ ሸቀጦች እሴት ነው። ካፒታሊስቱ የወዝአደሩን የሥራ ኃይል የሚገዛበት ጊዜ በመሠረቱ ለሥራ ኃይሉ እሴቱን መክፈል ይኖርበታል።

የወዝአደሩ የሥራ ኃይል እንዳይገታና የምርት እንቅስቃሴ እንዳይቆም፣ ወዝአደሩ ለመኖር የሚያስፈልጉ ነገሮችን ለመግዛት የሚችልበትን ምንዳ ካፒታሊስቱ መስጠት ይኖርበታል። ካፒታሊስቱ ለወዝአደሩ የሚከፍለው ምንዳ ወዝአደሩን ብቻ ሳይሆን ቤተሰቡንም ለመደገፍ ማለትም ልጆች ወልዶ

ለማሳደግ በማስቻል ለካፒታሊስቱ ዝነታቱ የሠራተኛ ፍላጎት መርካቱን የሚያረጋግጥ መሆን አለበት። ይህ እስካልሆነ ድረስ የምርት እንቅስቃሴ አይኖርም፤ የኅብረተሰቡም መሠረታዊ ሕልውና ይናጋል።

## 3.3 የሥራ ኃይል የእሴት ፈጣሪ ስለመሆኑ

እዚህ ላይ ማስታወስ የሚገባን ሌላ ነገር አለ፤ ይኸውም በሥራ ኃይልና በሥራ መካከል ልዩነት እንዳለ ነው። በቀላል የሸቀጥ ምርት ወቅት የራሣቸው አነስተኛ የምርት ማከናወኛ ባለቤትነት የነበራቸው አምራቾች የሚሸጡት የሥራ ኃይላቸውን ሣይሆን የሥራ ኃይል የፈሰሰባቸውን ሸቀጦች ነው ብለናል። በካፒታሊስት የሸቀጥ ምርት ወቅት ግን ወዝአደሮች ከማምረቻ መሣሪያ ባለቤትነታቸው የተገለሉ በመሆናቸው የሥራ ኃይላቸው ከማምረቻ መሣሪያ ጋር እስካልተቀላቀለ ድረስ ሸቀጥ ሊመረት አይችልም። ወዝአደሮች የሥራ ኃይላቸውን ከማምረቻ መሣሪያዎች ጋር ለማቀላቀል የሚችሉት ደግሞ የሥራ ኃይላቸውን የማምረቻ መሣሪያ ባለቤትነት ላለው የቡርዧ መደብ ሲሸጡ ብቻ ነው።

በሥራና በሥራ ኃይል መካከል ያለውንልዩነት የቡርዧ የፖለቲካ ኢኮኖሚስቶች በትክክል ሊገነዘቡት አልቻሉም። በሥራና በሥራ ኃይል መካከል ያለውን ልዩነት ለመጀመሪያ ጊዜ ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ የተገነዘበው ማርክስ ነበር፤ ይህ ግንዛቤው በካፒታሊስት ሥርዓት ውስጥ የትርፍ ሁሉ ምንጭ ምንድን ነው? ለሚለው ጥያቄ ሣይንሣዊ መልስ ሊሰጥ እንዲችል አድርጎታል።

ካፒታሊዝም እያቆጠቆጠ መጥቶ፤ አነስተኛ ሸቀጥ አምራች የነበረው ወደ ወዝአደርነት ተለውጦ፤ በገበያ ላይ የሚቀርበው ነገር እንደቀደሞው የሥራ ኃይል የፈሰሰበት ሸቀጥ ብቻ ሣይሆን፤ እራሱ የወዝአደሩ የሥራ

ኃይልም እንደሌሎች ሸቀጦች ሁሉ ለሽያጭና ለግዥ በቀረበበት ወቅት፣ ወደፊት እንደሚገለጸው በዚህ የሥራ ኃይል የተለየ ባሕርይ ምክንያት ትርፍ የሚሉት ታሪካዊ ፈርጁ በቋሚነት መከሰት ይጀምራል።

ካርል ማርክስ በሩ ባለ ታሪካዊ ገንዛቤውና ሣይንሳዊ በሆነ የኢኮኖሚ ጥናቱ የካፒታሊስት የሸቀጥ ምርት ማቆጥቆጥ በጀመረበት ጊዜ በምርት ሂደት ውስጥ አዲስ ክስተት መታየቱን ተገነዘበ። ይኸውም ቀደም ሲል የዝቅተኛ የሸቀጥ ምርት ተስፋፍቶባቸው በነበሩት በባሪያው አባዳሪና በፊውዳሉ ሥርዓቶች ውስጥ የነበረውን የሸቀጥ የልውውጥ አይማስ በካፒታሊስት ሥርዓት ውስጥ መስፋፋት ብቻ ሣይሆን በታሪክ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ የተለወጠ ጠባይ ይዞ መምጣቱን ነው።

የዝቅተኛ የሸቀጥ ምርት ተስፋፍቶባቸው በነበሩት ቀደመ ካፒታሊስት ሥርዓት ማኅበሮች ውስጥ በገበያ ላይ የሚለዋወጡት ሸቀጦች የሥራ ኃይል የፈሰሰባቸው ተጨባጭ የሆኑ ሸቀጦች ነበሩ። በካፒታሊስት ሥርዓት ውስጥ በገበያ ላይ ከሌሎች ሸቀጦች ጋር፣ አዲስ ሸቀጥ፣ ሌሎች ሸቀጦች ሁሉ ከያዙት ጠባይ በተጨማሪ ልዩ ጠባይ ያለው የሥራ ኃይል የሚባል፣ ተጨባጭ ያልሆነና ለመሥራት ዝግጁ የሆነ ኃይል በሸቀጥነት ይከሰታል።

የካፒታሊስት የሸቀጥ ምርት እየተስፋፋ በመጣበት ጊዜ፣ ማርክስ እንዳስገነዘበው፣ ምንዳ እየተበጠው ተቀጥሮ የሚሠራ ማንኛውም ሠራተኛ የሚሸጠው በተመረተ ሸቀጥ ውስጥ የተጠናቀረውን ሥራውን ሣይሆን ከማምረቻ መሣሪያ ጋር በመቀናጀት ሊያመርት የሚያስችለውን የሥራ ኃይሉን ነው። ይህ ለማምረት የሚያስችል ኃይል ሸቀጥ ሆኖ መቅረብ የቡርዧ ፖለቲካ ኢኮኖሚስቶች ያልተገነዘቡት ከካፒታሊስት የሸቀጥ ምርት ማቆጥቆጥ ጋር በአዲስነት የተከሰተ ነው።

በግልጽ ለማየት እንደሚቻለው ሠራተኛው ለመሥራት የሚያበቅለውን የሥራ ኃይሉን ለካፒታሊስቱ የመሸጡ፣ አነስተኛ ሸቀጥ አምራቹ በሥራው ያመረተውን ሸቀጥ በገበያ ላይ መሸጡ በዓይነት የተለያዩ ናቸው። በካፒታሊስት የሸቀጥ ምርት ወቅት አብዛኛው ሠርቶአደር ሥራዉን ሊሸጥ አይችልም። ምክንያቱም የማምረቻ መሣሪያ ባለቤትነት የለውም፤ ከሌለው ደግሞ በሥራ ኃይሉ ብቻ የምርት ሥራ ሊሠራ በለማይችል፣ የሚሸጠው ሸቀጥ ሊኖረው አይችልም። እዚህ ላይ ማስታወስ የሚገባው ሥራ በሚባልበት ጊዜ ወደፊትም በዝርዝር እንደሚገለጸው በአንድ በተወሰነ ዓይነት ሸቀጥ ውስጥ የተጠናቀረ፣ ያለቀ ድርጊት መሆኑን ነው፤ በአንፃሩ ደግሞ የሥራ ኃይል በሚባልበት ጊዜ ለመሥራት የተዘጋጀ፣ የሁኔታዎችን መሟላት የሚጠባበቅ፣ ያልተፈጸመ ድርጊት መሆኑን ነው።

በካፒታሊስት ሥርዓት ውስጥ በምንዳ ተቀጥሮ የሚሠራው ሠራተኛ /ወዝአደር/ ለካፒታሊስቱ የሚሸጠው ሥራዉን አይደለም፣ ለመሥራት በቀዳሚያ በካፒታሊስቱ ቁጥጥር ሥር ከሆነው የማምረቻ መሣሪያ ጋር የሥራ ኃይሉን ማቀናጀት ይኖርበታል፣ የሚሸጠው ለመሥራት የሚያስችለውን የሥራ ኃይሉን ነው። ካፒታሊስቱ ደግሞ የወዝአደሩ የሥራ ኃይል በይዞታው ካለው የማምረቻ መሣሪያ ጋር እንዲቀናጅ ካደረገ በኋላ የወዝአደሩ ሥራ የተጠናቀረበትንና የተመረተውን ሸቀጥ ይሸጣል።

ይህ ከካፒታሊዝም ጋር የተከሰተው የሥራ ኃይል የተባለው አዲስ ሸቀጥ ደግሞ ቀደም ሲልም እንደተገለጸው ከሌሎች ሸቀጦች ሁሉ የተለየና የራሱ የሆነ ጠባይ አለው። ይኸውም ይህ የሥራ ኃይል የተባለ ሸቀጥ እንደማናቸውም የተወሰነ ሸቀጥ ለማምረት ግልጋሎት ላይ የሚውል ሸቀጥ፣ በምርት ሂደት ውስጥ በውስጡ ተጠናቅሮ የነበረውን እሴት አዲስ ወደ ማምረቱ ሸቀጥ በማስተላለፍ አዲሱ ሸቀጥ በሚሸጥበት ጊዜ እሴቱን

በአዲስ መልክ ከመተካቱም በላይ፣ በዚሁ ሙሰባይ ወቅት ውስጥ ተጨማሪ እሴት የመፍጠር ችሎታ አለው።

እንደሚታወቀው በሸቀጥ ልውውጥ ሕግ ማናቸውም ሸቀጥ ለሸያጭ በሚቀርብበት ጊዜ በልውውጡ የሚከፈለው ገንዘብም ሆነ ሌላ ክፍያ በውስጡ የተጠናቀረው እሴት መሠረት ነው። ይህ የሥራ ኃይል የተባለው ግን በምርት ሂደት ውስጥ ከራሱ እሴት በላይ ተጨማሪ እሴት የመፍጠር ችሎታ አለው። ካፒታሊስቱ ደግሞ ለወዝአደሩ የሚከፍለው ምንዳ የሥራ ኃይሉን እሴት ነው እንጂ፣ የሥራ ኃይል በተጨማሪ ለፈጠረው እሴት አይደለም። በመሆኑም ይህ ሁኔታ በጥልቀት ሲገመገም የአንዱ ሸቀጥ የገበያ ዋጋና ያንን ሸቀጥ ለማምረት የዋለው የሥራ ኃይል በሚከፈለው ምንዳ መካከል ልዩነት እንደሚኖርና፣ በአጠቃላይ ትርፍ ለሚባለው ፈርጅ መከሰት ቀዳሚ ሁኔታ መሆኑን እንገነዘባለን። በካፒታሊዝም ሥርዓት የወዝአደሩ የሥራ ኃይል መበዝበዝ መሠረት ይህን ሲመስል፣ ብዝበዛው በተጨባጭ እንዴትና በምን መልክ እንደሚከሰት ከዚህ ቀጥሎ እንመለከታለን።

## 4. ተረፈ እሴትን የመፍጠር ሂደት

የሥራ እንቅስቃሴን ከማኅበራዊ መልኩ ገንጥለን በምንመለከትበት ጊዜ በሰውና በተፈጥሮ መካከል ያለ ግንኙነት ብቻ መስሎ ሊታይ ይችላል። ተፈጥሮ በለገሠችው ፀጋ አማካይነት ሰው በማያቋርጥ ሁኔታ ለሱ የሚጠቅሙትን ነገሮች መሥራቱ ወይም በፖለቲካ ኢኮኖሚ አነጋገር የጠቀሜታ እሴት ያላቸውን ሸቀጦች ማምረቱ የሕይወት ግዴታ መሆኑም፣ ይህን ቀደም ሲል የተጠቀስነውን አባባል የሚያጠናክር ይመስላል።

ይሁንና፣ የሥራ እንቅስቃሴ ወይም የማምረት ሂደት በሰውና በተፈጥሮ መካከል ግንኙነት ላይ በመሠረትም፣ ይህ ግንኙነት የሚከሰተው፣ ሊከሰትም የሚችለው በተወሰነ ማኅበራዊ መልኩ ነው። በእያንዳንዱ ታሪካዊ ወቅትና በተለያዩ ሥርዓት ማኅበሮች የሥራ እንቅስቃሴ የተለየና የራሱ የሆኑ ጠባዮች አሉት።

ለምባሌ በባሪያው አባዳሪ ሥርዓት 1ኛ/ የሠራተኛው /የባሪያው/ የሥራ ኃይል ብቻ ሣይሆን እራሱ ሠራተኛውም በሕግ በባሪያ አባዳሪው ሙሉ ቁጥጥር ሥር ነው፤ 2ኛ የሠራተኛው /የባሪያው/ የሥራ ውጤት በባሪያ አሰዳሪው ይወሰዳል። ይሁን እንጂ ባሪያው አገልግሎት ሊሰጥ የሚችለው ሕይወቱን ለማቆየትና ምርታማነቱንም ለማዳበር የሚያስችለው ምግብ ሲያገኝ በመሆኑ በዚህ መጠን ከመረተው ምርት በጣም አነስተኛ ድርሻ አለው ማለት ይቻላል።

በፊውዳሉ ሥርዓት፤ 1ኛ/ የሠራተኛው /የገባሩ/ የሥራ ጊዜ በፊውዳሉ ሕግ በተደነገገው የኮንትራት ግንኙነት መሠረት እንበል ሦስት ቀን የባላባቱን መሬት አርሶ እንደሆነ ሦስት ቀን ደግሞ የራሱን ማሣ ያርሳል። /ይህ የጊዜ መጠን እንደየአገሩና እንደየሁኔታው ይለያያል።/ በመሆኑም በፊውዳሉና በገባሩ መካከል በአስፈላጊና በትርፍ የሥራ ጊዜ በኩል ያለው ክፍፍል ግልጽ ነው። 2ኛ/ ገባሩ ከባሪያው ጋር ሲነፃፀር ከፊውዳሉ ጋር ባለው ኮንትራታዊ ግንኙነት ምክንያት አንፃራዊ ነፃነት ያለው በመሆኑም፤ በዚህ ሥርዓት የገባሩ የሥራ ውጤት በፊውዳሉ ይወሰዳል፡፡በትርፍ የሥራ ጊዜው የሚያስገኘው ሙሉ በሙሉ በፊውዳሉ ሲወሰድ፤ ለራሱ ከሚያመርተውም ምርት መካከል ፊውዳሉ በተለያየ ግብር ብዙ ይወስድበታል። በዚህም ስለተምርት ገባሩ በከፊልም ቢሆን የምርት መገልገያዎች ባለቤትነት ስለ አለው ከምርቱም መጠነኛ ድርሻ ያለው መሆኑ በግልጽ የሚታይ ነው።

በካፒታሊስቱ፤ሥርዓት ውስጥ ደግሞ 1ኛ/ ሠራተኛው /ወዝአደሩ/ የሥራ ኃይሉን ለተወሰነ ካፒታሊስት ብቻ ሣይሆን ለፈለገው ካፒታሊስት የመሸጥ መብት ወይም ነፃነት" በሳለው የቡርዧ ኢኮኖሚስቶች ይህን ወዝአደሩ ሙሉ ነፃነት እንዳለው አስመስለው ያቀርቡታል። እንደዚህ ዓይነቱ ነፃነት ራበን የማስበዝበዝ ነፃነት እንጂ ሌላ ትርጉም የሚሰጠው ወይም ሌላ ጥቅም የሚያስገኝ አይደለም። 2ኛ/ በዚህም በካፒታሊስት ሥርዓት ምንዳውን በመክፈል የሠራተኛውን/የወዝአደሩን/ ሙሉ የሥራ ውጤት ማለትም ትርፉን ካፒታሊስቱ ይወስዳል። በሌላ በኩል ደግሞ ወዝአደሩ ምንዳ ስለሚከፈለው ሙሉ የሥራ ዋጋውን ያገኝ ይመስላል። ግን የሥራው ፍሬ የሆነውን ተረፈ እሴት

ቡርዧው በሚወበዉበት የሥራ ኃይሉን ሙሉ ውጤት አያገኝም። ስለዚህም ጩብጭባ. ዜል። የወዝአደሩ ሥራ ማግኘትና ራሱን የማበዝበዝ "ምብት" የመበበና የተወበነ ስለሆነ በሥራ አጥነት የሚሠቃየው ሠራዊት ለጅግ በጣም ብዙ ነው።

እንግዲህ ከባሪያው አገዛዝ ሥርዓት ጀምሮ እስከካፒታሊስቱ ሥርዓት ድረስ በወቷችና በተወቷች መደቦች መካከል ያለውን ግንኙነት በንመረምር፣ አንደኛ ግን ኙነቱ በቀርጽ አይተለያዩ በጣም በይዘት ግን የብዝበዛ ግንኙነት መሆኑ ግልጽ ነው። ሁለተኛ ባሪያውና ገባሩ መበዝበዛቸውበግልጽ የሚታይ ቢሆን የወዝአደሩ ግን ግልጽ ሆኖ አይቀርብም፣ ሙሉ የሥራ ፍሬውን ያገኝ ይመስላል።

በካፒታሊስት ሥርዓት የአመራረት ዘይቤው ጣምራ ጠባዬች አሉት። የካፒ ታሊስት የምርት ሂደት በአንዱ በኩል የጠቀሜታ እሴት የሚፈጠርበት ቢሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ ተወጣሪ እሴት ወይም ትረፈ እሴት የሚፈጠርበት ነው። እንዲያውም የካፒታሊስት ምርት ዋና ዓላማ የጠቀሜታ እሴት ማስገኘት ሳይሆን ትረፈ እሴት ማስገኘት እንደሆነ በሌላ ሥፍራ ተጠቅሷል። ይሁንና ትረፈ እሴት ከመገኘቱ በፊት የሰውን ፍላጎት የሚያረኩ ሸቀጦች መመረት ስለአለባቸው ትረፈ እሴት የማስገኘቱ ሂደት የግዴታ የጠቀሜታ እሴትን ማስገኘት ይኖርበታል። ይህ አባባል ትንሽ ጥን ቃቄን ይጠይቃል። ምክንያቱም የጠቀሜታ እሴት ያለው ነገር ሁሉ የግዴታ የልውውጥ እሴት ወይም በአጠቃላይ እሴት ይኖረዋል ለማለት አይቻልም። ቀደም ሲል እንደተጠቀ ሰው ለምሳሌ አየር ለሰው ልጅ ከፍተኛ ጠቀሜታ ይሰጣል፣ በመሆኑም የጠቀሜታ እሴት አለው። ይሁንና የሥራ ኃይል ፈሰሰበት ያልተገኘ በመሆኑ የጠቀሜታ እሴት ቢኖረውም የል ውውጥ እሴት የለውም። በመሆኑም የጠቀሜታ እሴት ያለው ሸቀጥ ሁሉ ሁልጊዜም የልውውጥ እሴት ይኖረዋል ለማለት አይቻልም።

ማርክስ የካፒታሊስት ምርትን ተቀዳሚ ዓላማ በማስመልከት "የካፒታሊስቱ ፍላጎት የጠቀሜታ እሴትን ማስገኘት ሣይሆን፣ ...እሴትንም ጭምር ለማስገኘት ይፈልጋል....እሴትንም ብቻ ሣይሆን ትረፈ እሴትንም ጭምር ለማስገኘት ይጥራል፣" ብሏል።

ተረፈ እሴት ወዝአደሩ የሥራ ኃይሉን በመሸጥ በምርት እንቅስቃሴ ውስጥ የራሱን የሥራ ኃይል ለመተካት ከሚያበቃለው በላይ በማምረት የሚያስገኘው እሴት ነው። በዚህ አጋጣሚ ተረፈ እሴት ማለት ከመነሻው እሴት በላይ በምርት ሂደት ውስጥ የሚገኘው ተጨማሪ እሴት መሆኑን መጠቆም ያስፈልጋል።

የመቀሚያ እሴትና እሴት ወይም ተረፈ እሴት ከመሰባሰብ በሆነ ሂደት ሊፈጠሩ የሚችሉበትን በአንክሮ ለማጤን እንድንችል ከዚህ በታች የሰፈረውን ምሳሌ እንመልከት።

አሮን ወርቃ ወርቀ ፋብሪካ 100 ወዝአደሮችን በመቀጠር በቀን አራት ሰዓት በሣምንት ለስድስት ቀን ያሠራቸዋል እንበል። ይህ የቀን የሥራ ጊዜ መጠን በአብዛኛው ለወዝአደሩ ሕይወት አስፈላጊ የሆኑትን መሠረታዊ ነገሮች ሊያስገኝ የሚችል ነው። ምሳሌያችንን ዝርዝር እናድርገውና ለምርት መገልገያዎች ማለትም፦

| | |
|---|---|
| ለጥጥ | 10,200 ብር |
| ለቀለም፣ ለልዩ ልዩ ኬሚካሎችና ለኃይል | 10,000 ብር |
| ለዕልቀት | 5,000 ብር |
| ለምንዳ | 2,400 ብር |
| | 27,600 ብር |

አወጣና 600 ጧቃ ካኪ አመረተ። አሮን እነዚህን ስድስት መቶ ጧቃዎች እንዱን ጧቃ በ46 ብር ሂሣብ ቢሸጥ በሃያ ሰባት ሺ ስድስት መቶ ብር ይሸጠዋል። በዚህ ዓይነት ምንም ትርፍ አያገኝም፣ ወጪውን ብቻ ነው የሸፈነው። እንደዚህ ዓይነቱ ያለትርፍ መሥራት በካፒታሊስቱ በሊዝምርት ውስጥ ዘወትር የሚደርስ ወይም የተለመደ አይደለም። በተቃራኒው የካፒታሊስቶች ዓይነተኛ ዓላማ ዘወትርና ሁልጊዜ ከፍተኛ ትርፍ ለማጋበስና ትልቅ ሀብታም ለመሆን ነው። ስለሆነም አሮን ወርቃ ወርቀ ፋብሪካም በአጋጣሚ አልፎ አልፎ ገቢው ወጪውን ብቻ ሊሸፍን በሚችልበት ሁኔታ ማለትም ከዚህ በላይ እንደተመለከተው ያመረተ እንደሆነ ነው እንጂ አብዛኛውን ጊዜ በትርፍ ነው የሚሠራው።

ምሳሌውን እንደገና እንመልከትና እጥፍ አድርገን ማለትም በሁለት አባዝተን እንመልከተው። ወዝአደሮች ቁጥራቸው እንደበፊቱ ማለትም 100 ይሆናሉ፤ በሳምንት 6 ቀን ይሠራሉ፤ ግን በቀን የሚሠሩት የሥራ ሰዓት እንደበፊቱ አራት ሣይሆን 8 ሰዓት ይሆናል፤ ይህ ደግሞ በአብዛኛው የወዝአደሮች የሥራ ጊዜ ነው። ሌሎችም የምርት መገልገያዎች መጠን ሁለት ጊዜ ከፍ ብሏል፤

| | |
|---|---|
| ለጥጥ | 20,400 ብር |
| ለቀለም ከሚካሎች ነዳጅ | 20,000 ብር |
| ለእልቀት | 10,000 ብር |
| ለወዝአደሮች ምንዳ | 2,400 ብር |
| | 52,800 ብር |

እውጥቶ 1200 ጣቃ ካኪ በማምረት ሁሉንም 1200 × 46=በ55,200 ብር ሸጠው እንበል። አሁን በወጪውና በገቢው መካከል ያለው ልዩነት 2,400 ብር ነው፤ ይህ ትርፉ ነው ማለት ነው። ይህ እንደዚህ የሚተረፉ ነገር ደግሞ ዕለት በዕለት ሕይወታችን ውስጥ አዘውትሮ ሊያጋጥመን የሚችል እንጂ ብዙ ነው ሊባል የሚችል አይሆንም፤ ይህንን ያህል ቀርቶ ከዚህ ያነሰ ወጪ የሚያደርግ ካፒታሊስት ከዚህ የበለጠ እንጂ ከዚህ ያነሰ የሚያተርፍበት ሁኔታ ብዙ ጊዜ አያጋጥምም።

አሁን ወደ ምሳሌያችን እንመለስና ይህ አሮጌ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ ያገኘው ትርፍ ከየት መነጨ? በማለት እንጠይቅ። የምርት መገልገያዎች በሁለት ተባዝተዋል፤ እሴታቸው /በገንዘብ መልክ የተገለጠው/ ከፍ ብሏል። የምርቱም መጠን እንደዚሁ ከፍ በማለት ከ600 ወደ 1200 ጣቃ አድጓል። ሌላው መጠኑን የጨመረው የሥራው ሰዓት ነው፤ ይህም ከአራት ወደ ስምንት ሰዓት ከፍ ብሏል። እነዚህ ሁሉ ሲያድጉና መጠናቸውን ሲጨምሩ የወዝአደሮቹ ቁጥርም ሆነ ምንዳ ግን አልተለወጠም፤ ያው በፊት እንደነበረው ቀርቷል። ወዝአደሮቹ ለሕይወታቸው አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች ለማግኘት በፊትም አሁንም በቀን አራት ሰዓት ይሠራሉ። በፊት በዚሁ በአራት ሰዓት ሥራ ሲገላገሉ አሁን ግን በቀን የሚሠሩት ስምንት ሰዓት በመሆኑ በቀን ውስጥ

አራት ሰዓት ያለምንም ክፍያ በነፃ ይሠራሉ ማለት ነው። በዚህም በትርፍ ጊዜ ለአሮጌ ወርቃ ወርቅ ፋብሪካ 2,400 ብር ዋጋ ያለው ተረፈ እሴት ፈጥረዋል ማለት ነው። ካፒታሊስቱ 52,800 ብር ቀጥተኛ ወጪ ያወጣበት ሸቀጥ ዋጋ /ማለትም እሴቱ/ ወደ 55,200 ብር ከፍ ሊል የቻለውም ወዛደሩ ያልተከፈለበት፣ በካፒታሊስቱ ወጪ ውስጥ የማይታየው ከራሱ እሴት በላይ የፈጠረው ተጨማሪ እሴት በመኖሩ ነው። ትርፍ ወይም በፖለቲካ ኢኮኖሚ ተረፈ እሴት ከየት ይመጣል? ለተባለው መሠረታዊ ጥያቄ መልሱን ለማግኘት ችለናል፣ ከዚህ በላይ በተጠቀሰው ምሳሌ ተረፈ እሴትን የሚፈጥረው ወዛደሩ መሆኑን ለማሳየት ተችሏል።

እንግዲህ በምሳሌው መሠረት ካፒታሊስቱ በምርት ሂደት ውስጥ አስፈላጊ ለሆኑት ለጥጡ፣ ለቀለሙ፣ ለኬሚካሉ፣ ለነዳጅ ወዘተ... እንዲሁም ለመሣሪያው አለቃ መተኪያ ያወጣውን ወጪ፣ የተመረተውን ጣቃ በገበያ ላይ ሸጦ ሙሉ በሙሉ የመለሰው ሲሆን፣ ለወዛደሩ ከከፈለው ምንዳ በላይ በአጥፍ ገቢ ያስገኘ የወዛደሩ የሥራ ኃይል ብቻ ነው። በለሆነም የወዛደሩ የሥራ ኃይል በምርት ሂደት ውስጥ ተረፈ እሴትን ይፈጥራል ማለት ነው።

በመሆኑም ከዚህ ምሳሌ ለመረዳት እንደሚቻለው የተረፈ እሴት ምንጭ ያልተከፈለው፣ የተበዘበዘው የወዛደሩ የሥራ ኃይል ነው ማለት ነው። ይህንን በበለጠ ለመረዳት በካፒታሊስት የምርት ተቋሞች ውስጥ የቀን የሥራ ሰዓት እንዴት እንደሚከፈል መመልከቱ የካፒታሊስቱን የብዝበዛ ዘዴ ይበልጥ ግልጽ ያደርገዋል።

የሥራ ጊዜ ሁለት ላይ የተከፈለ ነው። አንደኛው የሥራ ጊዜ አስፈላጊ የሥራ ጊዜ ቢባል፣ ሁለተኛው ደግሞ ትርፍ የሥራ ጊዜ ይባላል።

አስፈላጊ የሥራ ጊዜ የሚባለው ወዛደሩ ያፈሰሰውን የሥራ ኃይሉን ለመተካት የሚያስፈልገውን ነገር በሙሉ ለማግኘት መሥራት ያለበት ጊዜ ነው።

ትርፍ የሥራ ጊዜ የሚባለው ወዝአደሩ በምርት ሂደት ውስጥ ያፈሰሰውንና መተካት ያለበትን የሥራ ኃይሉን ከተካ በኋላ ትርፍ ምርት ለማምረት የሚሠራበት የሥራ ጊዜ ነው።

ይህን ሁኔታ ቀለል ባለ መንገዱ ለማስተዋል እንዲቻል ለምሳሌ ባንዱ የሥራ ቀን ውስጥ ከበደ የተባለው ወዝአደር የሚሠራው ለስምንት ሰዓት ቢሆን አራቱ ሰዓት አስፈላጊው የሥራ ጊዜ ቢሆንና የቀረው አራት ሰዓት ደግሞ ትርፍ የሥራ ጊዜ ቢሆን የከበደ የሥራ ኃይል ብዝበዛ መጣኔ 100% ይሆናል። በሌላም እንደሚከተለው ይሆናል።


4 ሰዓት / አስፈላጊ የሥራ ጊዜ

4 ሰዓት / ትርፍ የሥራ ጊዜ

የብዝበዛው መጣኔ % $= \frac{4}{4} \times 100 = 100\%$

በዚህ ምሳሌ አማካይነት ወዝአደር ከበደ በቀን ውስጥ ካለው የስምንት ሰዓት የሥራ ጊዜ ውስጥ አራቱን ሰዓት የሥራ ኃይሉን እሴት ለመተካት ጉልበቱን ያፈሰሰበት ጊዜና በምንዳ መልክ የተከፈለው የሥራ ጊዜ ቢሆን፤ በተረፉት አራት ሰዓቶች ውስጥ ከበደ በሥራ ላይ ባዋለው የሥራ ኃይል ክፍያ የማያገኝበት፤ በአንፃሩም ለካፒታሊስቱ ተረፈ እሴት ለማስገኘት የሚሠራበት ትርፍ የሥራ ጊዜ ነው። የሥራ ኃይሉን ለመተካት በሚሰጠው ምንዳ ወዝአደር ከበደ ለሱም ሆነ ለቤተሰቡ ለኑሮ የሚያስፈልገውን ነገር ለመግዛት ይገለገልበታል። እዚህ ላይ ሌላ ሊጠቀስ የሚገባው ነገር በአንዱ ቀን የሥራ ጊዜ ውስጥ በአስፈላጊና በትርፍ የሥራ ጊዜ መካከል ያለውን መጣኔ የሚወስነው በዚያ በተወሰነ አገር ውስጥ በወቅቱ የምርት ኃይሎች የደረሱበት የዕድገት ደረጃና በወቅቱ በዚያው አገር ውስጥ ያለው አጠቃላይ የኑሮ ደረጃ በማመዛዘን ነው።

በካፒታሊስት ሥርዓት ውስጥ ትርፍ ምርት በካፒታሊስቱ የሚወሰደውን የተረፈ እሴት መልክ ይይዛል። በሌላ አነጋገር ትርፍ ምርትና ትርፍ የሥራ ጊዜ



ብዝበዛ ባለበት ሥርዓተ ማህበር (በካፒታሊዝም) ውስጥ ወዝአደሩ የሥራ ውጤቱን በሙሉ እንደማይወስድና እንደዬት ተረፈ እሴት እንደሚያስገኝ የሚያሳይ (ታዳጊ አገሮች ከማርክሳዊ ፖለቲካ ኢኮኖሚ አንፃር፣ በዩሪ ፖፖቭ)

proudly brought to you by

www.binyamhk.wordpress.com



በቀደሙ ካፒታሊዝም ሥርዓተ ማኅበሮችና በሶሻሊዝምም ውስጥ ያሉ ቢሆኑም፣ ትርፍ የሥራ ጊዜ ተረፈ እሴትን የሚያስገኘው የወዝአደሩ የሥራ ኃይል እንደማናቸውም ሸቀጣ ሸቀጥ በሆነበት በካፒታሊስት ሥርዓት ውስጥ ብቻ ነው። ቀደም ሲል በተጠቀሰው ምሳሌ የካፒታሊስት ብዝበዛ የተሸፋፈነና የተደበቀ የሚመስለው ካፒታሊስቱ ለወዝአደሩ /በምሳሌው ላይ እንደተጠቀሰው ለከበደ/ የሚሰጠው ክፍያ ወዝአደሩ ስምንት ሰዓት በሙሉ ከሠራ በኋላ በመሆኑ ክፍያው ለስምንት ሰዓት በሙሉ የተከፈለ ስለሚመስል ነው። በተጠቀሰው ምሳሌ ግን ወዝአደር ከበደ የተከፈለው የሥራ ኃይሉን ሳፈበበበት ስምንት የሥራ ሰዓት በሙሉ ሳይሆን ለአራቱ ሰዓት ብቻ ነው።

ማርክስ በካፒታሊስት ሥርዓት ውስጥና በቀደሙ ካፒታሊስት የመደብ ሥርዓቶች ውስጥ ያለውን የሠራተኛውን መደብ ብዝበዛ በማነፃፀር "ምንዳ፣ ዋጋና ትርፍ"* በተሰኘው ጽሑፉ ውስጥ፣

> "፣በባሪያ አሳዳሪ ሥርዓት/ ለባሪያው /የሥራ ኃይሉን ለመተካት ለሠራበት አስፈላጊ የሥራ ጊዜ የተከፈለው ቢሆን፣ ይህ የተከፈለው የሥራ ኃይል ያልተከፈለ መስሉ ሊታየን ይችላል። ምክንያቱም በባሪያውና በባሪያ አሳዳሪው መካከል የግዥና የሽያጭ ስምምነት የለም። ባሪያው ጉልበቱን የሚያፈስበት መላው የሥራ ጊዜ ያልተከፈለ ይመስላል። እንደ እውነቱ ከሆነ ግን ባሪያው ለመኖር እስከቻለ ድረስ ለአስፈላጊ የሥራ ጊዜው ክፍያ አግኝቷል ማለት ነው። ...በሌላ በኩል ደግሞ የገባሩን/የገበሬ ጪሰኛውን/ እንመልከት፣ ገበሬ ሦስቱን ቀን በራሱ ወይም በጪሰኝነት በሚያርሰው ማሣ ላይ የሥራ ኃይሉን ቢያፈስ፣ በሌሎች ሦስት ቀናት ደግሞ በባላባቱ ማሣ ላይ በነፃ በመሥራት ግዴታውን ይወጣል። በዚህ ሁኔታ ትርፍና /ያልተከፈለ/ አስፈላጊ/የተከፈለ/ የሥራ ጊዜ በደንቡ ቁልጭ ብሎ ይታያል። .../በካፒታሊስቱ/ የምንዳ ሥርዓት ወቅት ደግሞ በአንፃሩ የተከፈለ መስሉ ይከስታል። ወዝአደሩ የሚከፈለው ለአስፈላጊው የሥራ ጊዜ ብቻ ቢሆን፣ /በካፒታሊስቱ ሥርዓት ውስጥ/ ትርፍና አስፈላጊ የሥራ ጊዜ እርስ በርስ የተወባበጡና በግልጽ ያልተነጣጠሉ በመሆናቸው ነፃ በሆኑ ሻጭና ገዥ መካከል በሚደረግ የገበያ ኮንትራታዊ ስምምነት የተሸፈነ በመሆኑ ለአጠቃላዩ ጊዜ የፈሰሰው የሥራ ኃይል የተከፈለው ይመስላል፣**" በማለት አስቀምጧል።

*Karl Marx, Wages, Price & Profit, P. 51.

የካፒታሊስት ብዝበዛ ከባሪያ አሳዳሪውና ከፊውዳሉ ብዝበዛ የሚለየው በሌላ በምንም ነገር ሳይሆን በሥራ ኃይል ሽያጭና ግዥ አማካይነት፣ በልውውጥ ግንኙነት ካባ በመሸፈኑ ብቻ ነው። ቀደም ሲል እንደ ተጠቀሰው፣ በካፒታሊስት ሥርዓት ትርፍ የሥራ ኃይል የሚመዘበረው በትርፍ እሴት መልክ ነው። በመሆኑም ትርፍ እሴት ሁለንታዊ በሆነ ሁኔታ በካፒታሊዝም ውስጥ ብቻ የሚገኝ ታሪካዊ ፈርጅ ነው።

## 5. የትርፍ እሴት ሕግ፣ የካፒታሊዝም መሠረታዊ የኢኮኖሚ ሕግ

የትርፍ እሴት ሕግ በካፒታሊዝም ውስጥ መሠረታዊ የኢኮኖሚ ሕግ ነው። ማርክስ በካፒታሊስት ሥርዓት ውስጥ በለአለው ዋነኛ የኢኮኖሚ ሕግ ቢያወሳ "የትርፍ እሴት ምርት የካፒታሊስት ስልተምርት ፍፁም የሆነ ሕግ ነው" ብሏል። የካፒታሊስት ምርት ዓላማ የተፈጠረ ትርፍ እሴትን ካፒታሊስቱ እንዲያከማች ማድረግ ነው።

የአንዱ ስልተምርት መሠረታዊ የኢኮኖሚ ሕግ የሥርዓቱን መሠረታዊ የአመራረት ዓላማ የሚያሳይ ነው። በካፒታሊስት ሥርዓት ውስጥ የአመራረቱ መሠረታዊ ዓላማትርፍ እሴትን መፍጠር ነው። የትርፍ እሴት ሕግ በካፒታሊስቱና በወዝአደሩ መካከል ያለውን በብዝበዛ ላይ የተመሠረተ ግንኙነት የሚገልጽ ከመሆኑም በላይ፣ ሌሎች በካፒታሊዝም ውስጥ ያሉ የኢኮኖሚ ግንኙነቶችና በሥርዓቱ ውስጥ ያሉ ቅራኔዎችን ይወስናል።

የትርፍ እሴት ሕግ በእሴት የሥራ ንድፈ ሃሣብ ላይ የተመሠረተ ሕግ ቢሆን፣ በካፒታልና በሥራ ኃይል መካከል ያለው ግንኙነት ላይ ላዩን ሲታይ፣ ካፒታል ለሥራ ኃይል ተገቢ/ሙሉ/ የሆነ ክፍያ የሚያደርግ ይመስላል። ነገር ግን ሁኔታው በጥልቀት ሲታይካፒታል የወዝአደሩን የሥራ ኃይል እንደሚበዘብዝ የሚያስረዳ የኢኮኖሚ ሕግ ነው።

ይህን የተረፈ እሴት ንድፈ ሃሣብ ይዘትና የካፒታሊስቱን የብዝበዛ ዘዴ ሣይንሣዊ በሆነ መንገድ ለመጀመሪያ ጊዜ በማስተዋወቁና በማብራራቱ ማርክስ ለኢኮኖሚ ሣይንስ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክቷል። በሌላም በኩል ማርክስ የመሰለውን ዓለም የቡርዧው መደብና የአፈቀላጤዎቹን የከረረ ጥላቻ ያተረፈው በአብዛኛው በዚሁ በተረፈ እሴት ንድፈ ሃሣብ ነው ቢባልም ማጋነን አይሆንም።

## 6. <u>የካፒታል ዓይነቶች</u>

በማርክሳዊ የፖለቲካ ኢኮኖሚ ትንታኔ ካፒታል በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላል። እነሱም:-

1. ቋሚ ካፒታል
2. ተለዋዋጭ ካፒታል ናቸው።

<u>ቋሚ ካፒታል:</u>- የሚባለው የምርት ማከናወኛ መሣሪያዎችን ማለትም ማሽኖችን፣ ሕንፃዎችን ጥሬ ዕቃና የመሳሰሉትን የሚያጠቃልል ሲሆን፣ በአንድ የምርት ክንዋኔ ወቅት የመጠን ለውጥ የማያሳይ ነው። በሥራ ኃይል አማካይነት እሴቱን ወደአዲስ የተመረተው ሸቀጥ የሚያስተላልፍ እንጂ ተጨማሪ እሴት አይፈጥርም።

<u>ተለዋዋጭ ካፒታል:</u>- የሚባለው የሥራ ኃይልን ለመግዛት የወጣው ምንዳ ሲሆን፣ በአንድ የምርት ክንዋኔ ወቅት የወዝአደሩ የሥራ ኃይል በሚያስገኘው ተረፈ እሴት መሠረት የመጠን ለውጥ የሚያሳይ ነው። ይኸውም አዲስ እሴት ይፈጥራል ማለት ነው፥

ለምባሌ አንዱ ፓፓቢኖበ የሚባል ካፒታሊስት ባለው የአረቄ ፋብሪካ ውስጥ አረቄ ለመሥራት፣ የተለያዩ ማሽኖች ለአረቄ ሥራ የሚያገለግሉ ጥሬ ዕቃዎችና በፋብሪካው ውስጥ የሚሠሩ ወዝአደሮች ሊኖሩት ይገባል ወይም ይኖሩታል እንበል።

እንግዲህ በእዚህ ምባሌ አማካይነት አረቄው አንድ ጊዜ ተሠርቶ እስ ከሚወጣበት ጊዜ ድረስ ባለው አንድ የምርት ሂደት ውስጥ ለመሣሪያው አልቆት ተተምኖ በወጭ መልክ የሚቀመጠው፣ ለጥሬ ዕቃ ግዥ የሚጣጣው አንድ ላይ ተደምሮ ጸሚ ካፒታል ሲባል በፋብሪካው ውስጥ ላሉ ወዝአደሮች በዚያ በተወሰነ የምርት ወቅት ለሠሩበት ጊዜ የሚከፈላቸው ምንዳ ለብቻው ተለዋዋጭ ካፒታል ይባላል።

ቀደም ሲል ካፒታል ቁሳዊ ነገር ሣይሆን ማኅበራዊ ግንኙነት ነው ተብሎ ነበር። አሁን ደግሞ ካፒታልን በሁለት ዓይነት በመክፈልና ቁሳዊ ገጽታ ይዞ እንዲቀርብ ለማድረግ ያስፈለገው ቀደም ሲል በለካፒታል የተጠቀሰውን ለመቃረን ሳይሆን፣ ካፒታልን በቋሚና በተለዋዋጭ መክፈሉ ከትንተና አንፃር የወዝ አደሩን የሥራ ኃይል የብዝበዛ ይዘትና መጠን በተወሰነ ሊቀመን የሚችልበትን መንገድ ለማሳየት ነው።

ካፒታል በነዚህ በሁለት ዓይነቶች መከፈሉን ለመጀመሪያ ጊዜ ያስታወቀው ማርክስ ከመሆኑም በላይ፣ ይህ ዓይነት የካፒታል አከፋፈል፣ ትረፊ እሴት በአጠቃላይ ካፒታል ሣይሆን በተለዋዋጭ ካፒታል ብቻ የሚፈጠር መሆኑን በግልጽ ያመለክታል። በመሆኑም ከላይ እንደተጠቀሰው በካፒታሊስቱ መደብና በወዝአደሩ መደብ መካከል ያለውን በብዝበዛ ላይ የተመሠረተ ግንኙነት በግልጽ ያሳያል።

የቡርዧ ኢኮኖሚስቶች ግን የትርፍ ምንጭ የወዝአደሩ የተበዘበዘ የሥራ ጊዜ መሆኑን ለመሸፈን ካፒታልን በማይንቀሳቀስና በተዘዋዋሪ ይከፍሉታል።

በማይንቀሳቀስ ካፒታል ሥር ትላልቅ ማሽኖችንና የማምረቻ መሣሪያዎችን፣ ሕንፃዎችን ወዘተ... ሲያስቀምጡ፣ በተዘዋዋሪ ካፒታል ሥር ጥሬ ዕቃን፣ምንዳንና የመሳሰሉትን ያጠቃልላሉ። የዚህ ዓይነት የካፒታል አከፋፈል የተለያዩ የካፒታል ክፍሎች ያላቸውን የተለያየ ጠባይ /ማለትም በአንድ የምርት ሂደት ውስጥ እሴታቸውን አዲስ ወደሚመረተው ሸቀጥ የሚያስተላልፉትንና እሴታቸውን ቀስ በቀስ የሚያስተላልፉትን የካፒታል ክፍሎች በመለያየት የካፒታልን የገልብጥ ፍጥነት/ ለማሳየት ቢረዳም በካፒታልና በሥራ ኃይል መካከል ያለውን በብዝበዛ ላይ የተመረኮዘ ግንኙነት ይሸፍናል ወይም ያደበስብሳል። ትርፍንም መጀመሪያ በሥራ ላይ ከዋለው የገንዘብ መጠን ጋር በማነፃፀር የሥራ ኃይል ብቻ ሳይሆን ጥሬ ዕቃዎችና የማምረቻ መሣሪያዎች ጭምር ትርፍን የፈጠሩ ያስመስላል። የማርክሳዊ የፖለቲካ ኢኮኖሚ ትንታኔ ግን በምርት ሂደት ውስጥ የጥሬ ዕቃዎች በአዲስ ወደሚመረተው ሸቀጥ እሴታቸውን የሚያስተላልፉ መሆናቸውን፣ የማምረቻ መሣሪያዎች እልቀት ካፒታሊስቱ የተመረተውን ሸቀጥ በሚሸጥበት ጊዜ ሙሉ በሙሉ የሚተካው መሆኑን ስለሚገነዘቡ፣ የትርፍ ብሎም የትርፍ እሴቱ ምንጭ የተበዘበዘ የወዝአደሩ የሥራ ኃይል ብቻ መሆኑን ቁልጭ አድርጎ ያስቀምጣል።

የትርፍ እሴቱን መጠን ወይም የወዝአደሩ የሥራ ኃይል የተበዘበዘበትን መጠን ለማስላት የምንጠቀመው ካፒታሊስቱ ለጥሬ ዕቃ፣ለእልቀትና ለምንዳ ያወጣውን ወጪ በአጠቃላይ በመውሰድ ሳይሆን ለምንዳ ብቻ ያወጣውን ወጪ ከትርፍ እሴቱ ጋር በማገናዘብ ነው። የትርፍ እሴትን እክብ ለማስላት የሚያስችለው ቀመር በዚህ ምዕራፍ መወረሻ ላይ ተመልክቷል። በመሆኑም ካፒታሉን በሁለት የመክፈሉ ሁኔታ በካፒታሊስት ሥርዓት ውስጥ የወዝአደሩን የብዝበዛ ይዘት በጉልህ ለማሳየት የሚረዳ ከመሆኑም በላይ፣ ስለካፒታሊስት የብዝበዛ ስልት የሚኖረው ትክክለኛ ግንዛቤ የካፒታሊስቱን ሥርዓት በሚገባና ያለርኅራኄ ለመዋጋት ያገለግላል።

## 7. በካፒታሊስቱ ሥርዓት በርዝሙ የወዝአደሩን የሥራ ኃይል ብዝበዛ የሚያሳድጉባቸው ስልቶች

ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው የካፒታሊስት ምርት ዓይነተኛ ዓላማ ትርፍን ማጋበስ ነው። ከካፒታሊስት ሥርዓት መባቻ ጀምሮ የካፒታሊስቱ መደብ የወዝአደሩን የሥራ ኃይል ለመበዝበዝ የሚጠቀምባቸውን ስልቶች እንደየጊዜው ሁኔታ እየለዋወጣቸው መጥቷል። በካፒታሊዝም ዝቅተኛ የዕድገት ደረጃ ላይና የወዝአደሩ መደብ ሙያ ማኅበር የንቃተሕሊና ደረጃ ወቀሳ በነበረበት ወቅት፣ የመደብ ጥቅሙን ከካፒታሊስቱ መደብ ጥቃት ሊከላከል የሚችልበት መሣሪያ አልነበረውም። በመሆኑም ካፒታሊስቱ ወዝአደሩ የሚሠራበትን ሰዓት በየጊዜው እስከአመቺው ድረስ በማራዘም ወዝአደሩን እስከከፋ በሆነ ሁኔታ ይበዘብዝ ነበር። በዚያን ወቅት ካፒታሊስቱ ወዝአደሩን እንዲሁም ሕፃናትንና ለመውለድ የተቃረቡ ሴቶችን ሣይቀር እጅግ አስቸጋሪ በሆነ የሥራ ሁኔታ በቀን እስከ 18 ሰዓት ያሠራ እንደነበር በታሪክ የተመዘገበ ነው። የወዝአደሩ መደብ የሙያ ማኅበር የንቃተሕሊና ደረጃ በዳበረበትና ለመደብ ጥቅሙም መከበር በሚገባ መታገል በጀመረበት ጊዜ ካፒታሊስቱ ወዝአደሩ የሚሠራበትን የሥራ ሰዓት እንደፈለገው ለማራዘም አልቻለም። እ.ኤ.አ. ከ1820 ጀምሮ እስከ 1890 ድረስ ባሉት ዓመታት በተለያዩ ካፒታሊስት አገሮች ማለትም በአሜሪካ፣ በእንግሊዝ፣ በጀርመን፣ በአውስትራሊያ ወዘተ... ያሉ ወዝአደሮች በተናጠል ያደረጉት ትግል የቀን የሥራ ሰዓትን መጀመሪያ ወደ 15 ከዚያም ወደ 12 እና ወደ 10 ሰዓት ዝቅ ብሎ በሕግ እንዲደነገግ ለማድረግ አስችሉ ነበር። በኋላም በተለይ ከሁለተኛው ኢንተርናሽናል መቋቋምና ከወዝአደሩ መደብ ትግል ሥር መስደድ ጋር የቀን የሥራ ሰዓት ወደ በምንት ሰዓት ሊደርስ ችሏል። የሜይ/ዴይ ታሪክም ከዚህ የሥራ ሰዓት ቅነሣ ትግል ጋር የተያያዘ መሆኑ የሚታወቅ ነው።

ካፒታሊስቶች የቀኑን የሥራ ሰዓት ማራዘም ባለመቻላቸው፣ በሕግ የተወሰ ~~ነው~~ የሥራ ሰዓት እንዳለ ሆኖ በዚያ ውስጥ በተሻለ የሥራ አደረጃጀት ዘይቤና

በቴክኖሎጂም ዕድገት በመጠቀም ከተወሰነው ሰዓት ውስጥ አስፈላጊውን የሥራ ጊዜ በመቀነስና ትርፉን የሥራ ጊዜ በማስፋት የሚያካብቱትን የትርፍ እሴት መጠን ለመጨመር ችለዋል። የሠራተኛውን የቀን የሥራ ሰዓት በማራዘም የሚገኘው ትርፍ እሴት ፍፁም ትርፍ እሴት ሲባል፣ የቀኑ የሥራ ሰዓት መጠን ባይጨምር አስፈላጊ የሆነውን የሥራ ጊዜ በመቀነስ የሚገኘው ትርፍ እሴት ደግሞ አንጻራዊ ትርፍ እሴት ይባላል። ከዚሁ ጋር የተያያዘና የአንጻራዊ ትርፍ እሴት የተለየ ገጽታ የሆነ ተጨማሪ ትርፍ እሴት የሚባልም አለ። የእነዚህም ሦስት ዓይነት ካፒታሊስቱ ብዝበዛውን የሚያሳድጉባቸው መንገዶች ዝርዝር ማብራሪያና የሚሰጡበት ቁጥር በዚህ ምዕራፍ መጨረሻ ላይ ይገኛል።

## 8. በካፒታሊስት ሥርዓት የመደብ አሰላለፍ

በካፒታሊስት ሥርዓት ውስጥ ሁለት መሠረታዊ መደቦች ይገኛሉ።እነሱም የቡርዧውና የወዝአደሩ መደቦች ናቸው። የቡርዧው መደብ የምርት መገልገያዎችን በግል ሀብትነት በመያዙ ብቻ የወዝአደሩን መደብ በተለይ የሠርቶአደሮችን የሥራ ፍሬ በአጠቃላይ የሚበዘብዝ መደብ ነው። በሌላ በኩል የወዝአደሩ መደብ ከምርት መገልገያዎች ባለቤትነት የተገለለ በመሆኑ ለመኖር የግዴታ የሥራ ኃይሉን በመሸጥ ለቡርዧው መደብ ትርፍ እሴት የሚያስገኝና በዚህም ሂደት ውስጥ የሚበዘበዝ መደብ ነው። በካፒታሊስት ሥርዓት አምራች የሆነው የወዝአደር መደብ በቡርዧው ሕግ ነፃ ነው ቢባልም የምርት መገልገያ መሣሪያዎች ባለቤትነት የሌለውና የሥራ ኃይሉን በመሸጥ የሚኖር በመሆኑ ማርክስና ኤንግልስ እንዳሉት የካፒታሊስት ብዝበዛ በምንዳ ባርነት ላይ የተገነባ ነው። በአጠቃላይ በቡርዧው ኅብረተሰብ ውስጥ ምንዳ፣ ትርፍና ኪራይን የሚያጠቃልለውን ብሔራዊ ገቢ በመጀመሪያ ደረጃ የሚከፋፈሉት የካፒታሊስቱና የወዝአደሩ መደቦች እንደመሆናቸው እነዚህ መደቦች በካፒታሊስት ሥርዓት ውስጥ መሠረታዊ መደቦች በመባል ይታወቃሉ። የራሳቸው የምርት መገልገያ ያላቸው በራሣቸው ሥራ የሚተዳደሩ አነስተኛ አምራቾች በእነዚህ ጠርዝ ላይ ይገኛሉ።/ስለእነዚህ መደቦች በምዕራፍ 6 ውስጥ ተጨማሪ ማብራሪያ ይገኛል።/

የቡርዧው መደብ የረጂም የታሪክ ዕድገት ሂደት ውጤት ነው። የቡርዧውም ኅብረ ተሰብ በፊውዳሉ ኅብረ ተሰብ መቃብር ላይ የሰመለመ እንደመሆኑ የመደብ ቅራኔዎችን ወደአዲስና ልዩ ደረጃ አሸጋግሯቸዋል። በእርግጥ በወቅቱ ቡርዧው በታሪክ አብዩታዊ ሚና ተጫውቷል። ቡርዧው ሥልጣኑን በእጁ ካስገባ በኋላ የተበታተኑ ከተሞችን፣ አስተዳደሮችን፣ የምርት መገልገያዎችን፣ በአጠቃላይ የግል ሀብትን አንድ ላይ በመሰብሰብ አጠናክሯታል። በግለሰብ ካፒታሊስቶችም መካከል ነፃ ውድድሩ መስፋፋት ጀመረ። ነፃ ውድድርም በሳይንስና ቴክኖሎጂ ዕድገት ውስጥ ቁልቀ ሚና ተጫውቷል። ስራ መደረክም ከፍቷል። "ነፃ ውድድር" ይባል እንጂ ታዲያ ውድድሩ የሚያባየው በካፒታሊስቶች መሐከል ያለውን ቅራኔና ትግል ነው። በኋላቀር አገሮች ላይ በመዝመት በቅኝ አገዛዝ ቀንበር ሥር እያንበረከኩ ለፋብሪካዎቻቸው የጥሬ ሀብት ምንጭ ለማግኘት በአፍሪካ፣ በላቲን አሜሪካና በእስያ ሲሯሯጡ በመሐከላቸው ያለውን ቅራኔ አፋፍመውታል። በትግሉም ሂደት ውስጥ አንዳንዶቹ እየተረገጡ ዘቅጠዋል። ሌሎች ደግሞ እየፋፉና እየዳበሩ ወደሞኖፖሊ ደረጃ ደርሰዋል። በሞኖፖሊስቶች መሐከልም ቅራኔውና ትግሉ ቀጥሎ ከዛሬው ደረጃ ላይ ደርሰናል። ምንም እንኳ ሞኖፖሊስቶች በመሐከላቸው ያለውን ቅራኔና ትግል "ለመግታትና ለመቆጣጠር" ቢሞክሩም ቅራኔውና ትግሉ ዘወትር እየጋነ ነው። በዚህም ቅራኔና ትግል አማካይነት አንዱ ጠንካራ ሞኖፖሊ ሌላውን ደካማ ሞኖፖሊ ይውጣል።

በካፒታሊስት ሥርዓት ውስጥ የቡርዧው መደብ አካል የሆነ የመሬት ከበርቴ አለ። ካፒታሊዝም በገጠሩ በሚስፋፋበት ሂደት ውስጥ፣ የመሬት ከበርቴው መሬትን ለካፒታሊስት አራሹ ያከራያል። ካፒታሊስት አራሹ ደግሞ በዘመናዊ የእርሻ መሣሪያዎች በመጠቀምና የእርሻ ወዝአደሮችን ሥራ በመበዝበዝ ከሚያገኘው ትርፍ /የልዩነት ኪራይ/ ቀንቦ ለመሬት ከበርቴው ኪራይ/ፍፁም ኪራይ/ ይከፍላል። ለካፒታሊስቱም ትርፍ ሆነ ለመሬት ከበርቴው ኪራይ ምንጩ ዞሮ ዞሮ የእርሻ ወዝአደሮች የተበዘበዘ የሥራ ኃይል ነው።

በካፒታሊስት ሥርዓት ከመሠረታዊ መደቦች ውጭ በሩ ያለ መሠረታዊ ያል ሆነ መደብ አለ። ሊቡም የንዑስ ከበርቴው መደብ ነው። በዚህ መደብ ውስጥ የሚጠቃለሉት የኅብረተሰብ ክፍሎች ካፒታሊዝም እንደደረሰበት ዕድገት ደረጃ የሚወሰን ነው። በካፒታሊስት ሥርዓት ይህ መደብ በሩ ያለ ከመሆኑም በላይ፣ በፖለቲካ ትግል ውስጥ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል። አነስተኛም ይሁን ለንሿ የተወሰነ የንብረትና የምርት መገልገያዎች ባለቤት በመሆኑ ከቡርዧው ጋር ሲያቀራርበው፣ በምርት እንቅስቃሴ ውስጥ የራሱን የሥራ ኃይል የሚጠቀም ከመሆኑም በላይ በቡርዧው መደብ በተለያየ መንገድ የሚጨቆንና የሚበዘበዝ በመሆኑ ደግሞ ከወዝአደሩ ጋር የሚያቀራርበው ሁኔታ አለ።

የካፒታሊዝም ዕድገት የንዑስ ከበርቴውን መደብ ኢኮኖሚያዊ ተቋም እያናጋው ይሄዳል። አብዛኛው የንዑስ ከበርቴ መደብ አባላት እየከሰሩ ወደወዝአደርነትና ከፊል ወዝአደርነት ይለወጣሉ፤ ወይም ደግሞ በተለያየ መንገድ የካፒታሊስቱ ጥገኛ ይሆናሉ። በጣም ጥቂቶቹ ደግሞ ካፒታሊስት ይሆናሉ።

የካፒታል የመበባበብና የመከማቸት ሂደት አነስተኛ አምራቾችን የማፈለሱ ሁኔታ ቋሚ የሆነ ነገር ቢሆንም፣ ይህ ሂደት አነስተኛ አምራቾችን ጨርሶ ያጠፋል ማለት አይደለም። በሞኖፖል ካፒታል ደረጃም ቢሆን አነስተኛ አምራቾች ጨርሰው አይጠፉም። ሞኖፖል ካፒታል በከፍተኛ ደረጃ በተስፋፋባቸው የካፒታሊስት አገሮች አነስተኛ ቡና ቤቶች፣ ምግብ ቤቶች፣ ጊጧጊጥ ሠራተኞች አልፍ አልፍ አነስተኛ ገበሬዎችና የመሳሰሉት መኖራቸው ለዚህ ምስክር ነው።

ከተጠቀሱት መደቦች ውጭ በካፒታሊስት ኅብረተሰብ ልዩ ልዩ ማኅበራዊ ቡድኖች /ንጥፍጧፎች/ ይገኛሉ። የልዩ ልዩማኅበራዊ አገልግሎቶች፣ መንግሥታዊና ሕጋዊ ተቋሞች፣ የትምህርትና የምርምር ተቋሞች ወዘተ... ሁሉ ያለቢሮ ሠራተኞች ሊንቀሳቀሱ አይችሉም። ዛሬ በካፒታሊስት አገሮች የቢሮ ሠራተኞች ቁጥር በብዛት እየጨመረ ነው።

በቡርዧው ኅብረተሰብ ውስጥ በያዙት ቦታ የቢሮ ሠራተኞች በሁለት ዋና ዋና ጫፎች ሊመደቡ ይችላሉ። እነሱም በሕዝባዊ አገልግሎቶችና በሞኖፖሊ ድርጅቶች ውስጥ የሚሠሩ ናቸው። በነዚህ ውስጥ ቁልፍ ቦታዎችን የያዙና በቁንጮ ላይ የሚገኙ ሰፊውን ሕዝብ ለማስበዝበዝ የቡርዧው የቀኞና መሣሪያ በመሆናቸው ከቡርዧው ተለይተው ሊታዩ አይችሉም። ሆኖም ይህ ሰፊውን የቢሮ ሠራተኛ አይወክልም። አብዛኛው የቢሮ ሠራተኛ የሠርቶአደሩ ሕዝብ አካል ነው። የኑሮ ደረጃውም ከሠርቶአደሩ መደብ የተለየ አይደለም። እንዲያውም የሥራ አጥነት ዕጤልበላያቸው ያንዣብባል። ስለሆነም ዝቅተኛውና መለስተኛው የቢሮ ሠራተኛ የሠርቶአደሩ መደብ አጋር ነው። ከዚሁ ጋር በተያያዘ መንገዱ የካፒታሊዝም መሣሪያና ጥቅም አስከባሪ የሆነ ሌላም ማኅበራዊ ክፍል አለ። ይህም በካፒታሊዝም ሥርዓተ ማኅበር ውስጥ የሚገኘው የወታደራዊ፣ የፖሊስና የፀጥታ ተቋሞችን ወዘተ... የሚያጠቃልል ነው።

የካፒታሊዝም ዕድገት የተለያዩ ማኅበራዊ ክፍሎች እንዲመሠረቱ ረድቷል። ምሁርም አንዱ ማኅበራዊ ክፍል ነው። ምሁር በአዕምሮ ሥራ ላይ ያተኮሩ ቡድኖችን ያጠቃልላል። በካፒታሊስት ኅብረተሰብ በማኅበራዊ የሥራ አደረጃጀት በቁጥሩና በባሕል አቤት ምርት ውስጥ ምሁር ልዩና እጅግ ጠቃሚ ሚና ይጫወታል። ምሁር በእነዚህ እንቅስቃሴዎች ውስጥ የሚሳተፈው ለካፒታሊስት የምርት ሕጋጋትና ከገዥው መደብ ጥቅም አንፃር ነው። በካፒታሊስት ሥርዓት አጠቃላይ አቀራረብ ምሁሩ የቡርዧው አገልጋይና መሣሪያ ነው ለማለት ይቻላል። በዚህም የተነሣ ወዝአደሩ በምሁሩ ላይ እምነት ያጣል። ሆኖም ታዲያ ከካፒታሊስት ኅብረተሰብ መሠረታዊ መደቦች አንፃር ቢታይ ምሁር አንድ ወጥና አንድ አቋም ያለው አይደለም። ጥቂቶቹ የቴክኒክ ማኔጀሮች፣ የድርጅቶች ግምባር ቀደም ኢንጂነሮች፣ የሞኖፖሊዎች አማካሪዎች የምሁሩ ቁንጮ ናቸው። በልዩ ልዩ የቁጥና የባሕል ምርት መስክ ውስጥ የአመራር ቦታውን ይዘዋል። ይህ ክፍል ከቡርዧው ጋር በቀጥታና በጥብቅ የተሳሰረ በመሆኑ ሰፊውን ሕዝብ በመበዝበዙ ድርጊት ውስጥ ይሳተፋል። የካፒታሊዝምም ታማኝ አገልጋይ ነው። ይህ የምሁር ክፍል በማኅበራዊ ባሕርዩ፣ በማኅበራዊ ኑሮ ውስጥ በያዘው ሥፍራ ወዘተ...

ቢገመገም ከቡርዧው መደብ በጥቅም የተሣሠረና የተቆራኘ ነው። የቡርዧውን መንግሥትና ርዕዮተዓለሙን የሚመሩ፣ ካፒታሊስታዊ ኢኮኖሚውን የሚቆጣጠሩና የሚያስተዳድሩ ሰዎችም የሚመለመሉት ከዚሁ የምሁር ክፍል ውስጥ ነው።

የአብዛኛው ምሁር ዕድል ግን ከሰፊው ሠራተኛ ሕዝብ ዕድል ጋር የተያያዘ ነው። ከጉልበት ሥራ ነፃ ይሁን እንጂ ቡርዧው ምሁሩን ቢቀጥረው ከሥራ ኃይል ለቤት ክፍያ አንፃር ነው። ይህም ማለት የምሁሩ የሥራ ዋጋ አከፋፈል እንደወዝአደሩ መደብ ነው። እንደወዝአደሩ መደብ ሁሉ ከሞኖፖሊያች በኩል ብዝበዛ ይደርስበታል። ስለሆነም ካፒታሊዝምን አንድ ዓይነት ቀውስ ቢገጥመው የአብዛኛው ምሁራን ለውነተኛ ገቢ እንደወዝአደሩ ያሽቆለቁላል። ከእርሱም ጥቂቶቹ ሥራ በማጣት የሥራ አጥነትን ቁጥር ያደልባሉ። ካፒታሊዝም እየዳበረ ሄዶ በኢምፔሪያሊዝም ደረጃ ላይ ቢደርስ የዚህ ምሁር ክፍል አብዛኛው ወደወዝአደሩ መደብ በመጠጋት ወዝአደሩ ለነፃነት በሚያደርገው ትግል ውስጥ ይሳተፋል። አጋርም ይሆናል። ይህን የምሁራን ክፍል በይበልጥ አሸንፎ በጐኑ ለማሰለፍ የወዝአደሩ ድርጅት ጠቀኛና ጠንካራ መሆን ይኖርበታል።

በካፒታሊስት ሥርዓት ውስጥ በመሠረታዊና መሠረታዊ ባልሆኑ መደቦች ውጭ የሚገኙ፣ ራሳቸውን ችለው መደብ ለመባል የማይበቁትና በአጠቃላይ አጠራር ማኅበራዊ ክፍል በመባል የሚታወቁት በቀጥታ በምርት እንቅስቃሴ ውስጥ የማይሳተፉና ብሔራዊ ሀብት የማይፈጥሩ ናቸው። ሆኖም ግን በኅብረተሰብ የዕድገት ሂደትና ከጊዜ ወደጊዜ እየተስፋፋ በመጣው የማኅበራዊ የሥራ ክፍፍል አስገዳጅነት በካፒታሊስቱም ሆነ በሶሺያሊስቱ ሥርዓት የእነዚህ ክፍሎች ሙያ/ማለትም የቢሮና የአገልግሎት ሠራተኞች፣ የምሁራን፣ የወታደር ወዘተ.../ አስፈላጊ ነው። በመሆኑም ወዝአደሩ ገበሬውና የዕደ ጥበብ ሠራተኛው በምርት ሂደት ውስጥ በመሰማራት ከሚፈጥሩት ብሔራዊ ሀብት መካከል የመጀመሪያው ድርሻ መሠረታዊ ለሆኑት መደቦችና ከንዑስ ከበርቴው መደብ ውስጥ አምራች ለሆኑት ክፍሎች በቅድሚያ ከተዳረሰ በኋላ፣ ለእነዚህ ማኅበራዊ ክፍሎች በመንግሥት አማካይነት ይከፈላቸዋል።

በካፒታሊስት ኅብረተሰብ ውስጥ ከመደቦችና ከማኅበራዊ ክፍሎች ውጭ የሚገኙና በዘኔ በመባል የሚጠሩም አሉ። ከምርት መስክ የተገለሉ ለማኞች፣ ማጅራት መቺዎች፣ ሌቦች፣ ደላላዎች፣ ሸርሙጦች፣ ወዘተ... ይገኙበታል። በዘኔ የሚባለው ክፍል ይህ ቢሆን በዘኔ ማለትም ከነበረበት መደብ የተፈናቀለ የኅብረተሰብ ዝቃጭ ማለት ነው። ከፊውዳሊዝም ይልቅ በካፒታሊዝም ውስጥ የበዘኔው ቁጥር እጅግ ብዙ ነው።

## ም ዕ ራ ፮

1. ### የተረፈ እሴት መጣኔ ቀመር

ካፒታሊስቱ ወዝአደሩን የሚበዘብዝበትን ዘዴና የብዝበዛውን ይዘት ከተገነዘብን ዘንድ፣ የብዝበዛውን መጠን ለመለካት የሚያስችል ቀመር ማወቅ ያስፈልጋል። ለምሳሌ በአንድ የተወሰነ የምርት ወቀት የወጣው አጠቃላይ ካፒታል /ካ/ 500 ብር ቢሆን፣ ከዚህ ውስጥ 410 የፀሚ ካፒታል/ፀ.ካ/ ድርሻ፣ 90 ደግሞ የተለዋዋጭ ካፒታል/ተ.ካ/ ድርሻ ነው እንበል። የምርቱ ወቀት ሲጠናቀቅ አዲስ ሸቀጥ ይመረታል። የዚህ አዲስ ሸቀጥ እሴት 410 ፀ.ካ + 90 ተ.ካ + 90 ተረፈ እሴት /ተ.እ/ ቢሆን፣ 410 ከዱሮው የማምረቻ መሣሪያና ጥሬ ዕቃና የመነጨሉት በምርት ሂደት ውስጥ ወደአዲሱ ሸቀጥ ያስተላለፉት እሴት ቢሆን፣ 90 ተ.ካ በምርት ሂደት ውስጥ የዋለው የሥራ ኃይል እሴት ቢሆን፣ 90 ተ.እ ደግሞ በምርት ሂደት ውስጥ የዋለው የሥራ ኃይል ያስገኘው ተረፈ እሴት ነው። በዚሁ ሂደት ውስጥ ወዝአደሮች ያፈሰሱትና ወደአዲሱ ሸቀጥ ያስተላለፉትን እሴት ከመተካታቸውም በላይ ተጨማሪ ተረፈ እሴት ፈጥረዋል። ይህን ተጨማሪ ተረፈ እሴት በፈጠሩበት ጊዜ የሥራ ኃይላቸው የተበዘበዘበትን መጠን ለመለካት፣ የተፈጠረው ተረፈ እሴት /ተ.እ./ ለምርት ከወጣው አጠቃላይ ካፒታል /ካ/ ጋር ሳይሆን፣ ተረፈ እሴትን ከፈጠረው ተለዋዋጭ ካፒታል ጋር መመዘን አለበት። ይህ ግንኙነት በአብዛኛው የሚገለጸው በመቶኛ ነው። ከላይ የተጠቀሰውን ምሳሌ በመውሰድ የብዝበዛውን መጠን ወይም ደግሞ የተረፈ እሴትን መጣኔ/ተ.እ/ ለመለካት ተከፈልግ:—

$$ተረፈ\ እሴት\ መጣኔ = \frac{ተረፈ\ እሴት}{ተለዋዋጭ\ ካፒታል} \times 100$$

$$ተ.እ\ መጣኔ = \frac{90}{90} \times 100 = 100\ ይሆናል\ ማለት\ ነው።$$

$$ተ.እ\ መጣኔ = 100\%$$

በሌላ በኩል ደግሞ ይህንኑ የተረፈ እሴት መጠኑ እስፈላጊ የሥራ ጊዜን በትርፍ የሥራ ጊዜ አካፍሎ በመቶ በማባዛት ለማገኘት ይቻላል:: ለምሳሌ ባንዱ የሥራ ቀን ወዝአደሩ ለ8 ሰዓት ይሠራል እንበል:: ወዝአደሩ በመጀመሪያዎቹ 4 የሥራ ሰዓቶች በምርት ላይ ያዋለውንና ያለቀውን እሴቱን ቢተካና ለሚቀጥሉት አራት ሰዓቶች ደግሞ ተረፈ እሴት ቢፈጥር፣ የተረፈ እሴት መጠኑ $\frac{4}{4}$ × 100% ይሆናል ማለት ነው::

ይህም ማለት ወዝአደሩ የሥራ ኃይሉን እሴት ያህል ይበዘበዛል፣ ወይም ደግሞ የተበዘበዘው መጠን ከሥራ ኃይሉ እሴት ጋር ሲነፃፀር 100%ያህላል ማለት ነው::

2. <u>የተረፈ እሴት እክብ</u>

የተረፈ እሴት መጠኑ የወዝአደሩ የሥራ ኃይል የሚበዘበዝበትን ደረጃ የሚገልጽ ሲሆን፣ ብዝበዛው በተወባጭ /በገንዘብም ሆነ በመባባይ ዋና ባለው መለኪያ/ ምን ያህል እንደሆነ ሊጠቁም አይችልም:: ወዝአደሩ በተወባጭ በምን ያህል እንደ ተበዘበዘ የሚያስረዳን የተረፈ እሴት እክብን ለመለካትና ለመተመን ስንችል ነው:: የተረፈ እሴት እክብን ለማስላት የምንጠቀምበት ቀመር፣

$$\text{ተረፈ እሴት እክብ} = \frac{\text{ተ.እ/1/}}{\text{ተ/ካ/1/}} \times \text{ተ.ካ}$$

ተረፈ እሴት እክብ/ተ.እ.እ/ = በአንዱ የምርት ተቋም ውስጥ በአሉት ወዝአደሮች የተፈጠረውን ተረፈ እሴት አጠቃላዩ መጠን የሚያመለክት ነው::

ተረፈ እሴት/1/ = አንዱ ወዝአደር በተወሰነ ጊዜ የሚፈጥረው የተረፈ እሴት መጠን ነው::

ተለዋዋጭ ካፒታል/1/ = አንዱ ካፒታሊስት በተወሰነ ጊዜ ለአንዱ ወዝ አደር የሚከፍለው ምንዳ ነው።

ተለዋዋጭ ካፒታል ፡፡ በአንዱ በተወሰነ ጊዜ ለተወሰኑ ወዝአደሮች ካፒታሊስቱ የሚያወጣው ጠቅላላ የምንዳ መጠን ነው።

በዚህ መሠረት ለምሳሌ በአንድ ፋብሪካ ውስጥ 60 ወዝአደሮች በቀን 2 ብር ለእያንዳንዳቸው ቢከፈል በጠቅላላ የተከፈላቸው 120 ብር ይሆናል። ያስገኙት ትርፍ እሴት መጠን 120 ብር የሚያወጣ ቢሆን፣ እያንዳንዱ ወዝአደር የፈጠረው ትርፍ እሴት 2 ብር የሚያወጣ መሆኑ ነው።

በለዚህ፣

የትርፍ እሴት አክብ ፡፡ $\frac{2}{2} \times 120$

$= \underline{\underline{120}}$

3. <u>ፍፁም ትርፍ እሴት</u>

ፍፁም ትርፍ እሴት የሠራተኛውን የቀን የሥራ ሰዓት በማራዘም የሚፈጠር ትርፍ እሴት ነው። ለምሳሌ ሠራተኛው በቀን 8 ሰዓት ቢሠራና አራቱ አስፈላጊ የሥራ ጊዜ ቀሪው አራቱ ደግሞ ትርፍ የሥራ ጊዜ ነው እንበል። በዚህ ሁኔታ የትርፍ እሴቱ መጣኔ $\frac{4}{4} \times 100 = 100\%$ ይሆናል። ነገር ግን ካፒታሊስቱ የቀኑን የሥራ ሰዓት ወደ አሥር ከፍ ቢያደርግ አስፈላጊ የሥራ ጊዜው ባይለወጥ የሠራተኛው ትርፍ የሥራ ጊዜ ወደ ስድስት ከፍ ይላል፤ የትርፍ እሴት መጣኔ ወደ 150% /$\frac{6}{4} \times 100 = 150$/ ከፍ ይላል። ይህ በተለይ በመጀመሪያው የካፒታሊዝም የዕድገት ደረጃ ላይ ካፒታሊስቱ ብዝበዛውን የሚጨምርበት መንገድ ነበር። ፍፁም ትርፍ እሴት በቀጥታ በሠራተኛው የሥራ ሰዓት መራዘም ብቻ ሣይሆን ድብቅ የሆነ የሥራ ሰዓት መራዘም በሆነው የሥራ እምቅታ መጨመርም ሊፈጥር ይችላል።

<u>አንፃራዊ ተረፈ እሴት</u>

አንፃራዊ ተረፈ እሴት የሠራተኛው የቀን የሥራ ሰዓት እንዳለ ሆኖ አስፈላጊ የሥራ ጊዜን በመቀነስ የሚፈጠር ተረፈ እሴት ነው። ካፒታሊስቱ የተሻሻሉ የማምረቻ መሣሪያዎችን በሥራ ላይ በማዋልና የሠራተኛውን ምርታማነት በማሳደግ አስፈላጊ የሥራ ጊዜን እንዲቀንስ ለማድረግ ይችላል። ለምሳሌ የቀኑ የሥራ ሰዓት ስምንት ሰዓት ሆኖ በመጀመሪያ አራቱ ሰዓት አስፈላጊ የሥራ ጊዜ፣ ቀሪው አራት ሰዓት ደግሞ ትርፍ የሥራ ጊዜ ነበር እንበል። የፍጆታ ዕቃዎችና እነርሱን ለማምረት የሚያገለግሉ የምርት መገልገያዎች በሚመረቱባቸው የኢኮኖሚ መስኮች የሥራ ምርታማነትና በአጠቃላይም ቴክኖሎጂ በማደጉ ምክንያት አስፈላጊ የሥራ ጊዜ ከአራት ወደ ሦስት ሰዓት ቢቀነስ፣ ቀሪው አምስት ሰዓት ሠራተኛው የሚበዘበዝበት ትርፍ የሥራ ጊዜ ይሆናል። በዚህ መሠረት የብዝበዛው መጣኔ 167% /$\frac{5}{3}$ × 100 = 167 በመቶ/ከፍ ይላል።

5. <u>ተጨማሪ ተረፈ እሴት</u>

ተጨማሪ ተረፈ እሴት የተወሰኑ ካፒታሊስቶች ብቻ የሚያገኙት የሚችሉ የአን
ፃራዊ ተረፈ እሴት ዓይነት ነው። በተለይ በነፃ ውድድር ካፒታሊዝም ዘመን
እያንዳንዱ ካፒታሊስት ከፍተኛ ትርፍ ለማጋበስ ባለው ፍላጎት አዳዲስ መሣሪያዎ
ችን በማስገባት ድርጅቱን ይበልጥ ዘመናዊና ምርታማ ለማድረግ ይሽቀዳደማል። በዚ
ህም መንገድ አንዳንድ ካፒታሊስቶች ከሌሎች ካፒታሊስቶች ቀድመው አዳዲስ መሣሪያ
ዎችንና የአሠራር ዘዴዎችን በምርት ተግባር ላይ በማዋል የሥራን ምርታማነት ያሳ
ድጋሉ። እነዚህ ካፒታሊስቶች የሚያስመርቱት የእያንዳንዱ ዕቃ እሴትም ሌሎች ካፒ
ታሊስቶች ከሚያስመርቷቸው ተመሳሳይ ዕቃዎች እሴት ዝቅ ያለ ይሆናል። የሸቀጦች
ዋጋም የሚወሰነው ባለው አማካይ የአመራረት ሁኔታ እንደመሆኑ፣ እነዚህ ከሌሎች
ቀድም በማለት አዲስ ቴክኖሎጂ ያስተዋወቁት ካፒታሊስቶች ሸቀጦችን በማኅበራዊ
እሴታቸው ይሸጧቸዋል። ሸቀጦች በተሸጡበት እሴትና በቴክኖሎጂ በተጠና ቀረው እነ
በተኛ እሴት መካከል ያለው ልዩነት <u>ተጨማሪ ተረፈ እሴት</u> ይባላል። ተጨማሪ

ትርፍ እሴት አንዳንዱ ካፒታሊስቶች ለአጭር ጊዜ ብቻ የሚያገኙት የትርፍ እሴት ዓይነት ነው፡፡ የተሻሻለው የማምረት ቴክኒክ በሌሎች ካፒታሊስቶች ታውቆ በሥራ ላይ ሲውል፣ ተጨማሪው ትርፍ እሴት ያከትማል፡፡ ለተጨማሪ ትርፍ እሴት የሚደረገው እሽቅድምድም ግን ያለማቋረጥ ይካሄዳል፡፡ ይህ እሽቅድምድም የቴክኖሎጂ ግብታዊ ዕድገትን ያስገኘ ቢሆንም፣ በካፒታሊስቶች መካከል ያለውን ቅራኔ እያባባሰ የብዙዎቹን መደቀቅና የጥቂቶቹን መበልጸግ አስከትሏል፡፡ በተጨማሪም የተሻሻሉ የማምረቻ መሣሪያዎችንና የአመራረት ዘዴዎችን ለመጀመሪያ ጊዜ በሥራ ላይ ያዋሉ ካፒታሊስቶች ተጨማሪ ትርፍ እሴት የማግኛ ጊዜያቸውን ለማራዘም በምስጢር የመያዝ አዝማሚያ ያላቸው መሆኑ ለቴክኖሎጂ ዕድገትና መስፋፋት እንቅፋት መሆኑ ግልጽ ነው፡፡



## ጥ ያ ቄ ዎ ች

1. ወዝአደሩ የሥራ ኃይሉን ለመሸጥ የሚገደድበት ምክንያት ምንድነው? በምሳሌ አስረዳ ።

2. የሥራ ኃይል እሴት እንዴት ይወሰናል? አብራራ ።

3. በሥራና በሥራ ኃይል መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው? በተወሰነ ምሳሌ ግለጽ ።

4. ካፒታል ማለት ምን ማለት ነው? ዘርዝር አድርገህ አስረዳ ።

5. የካፒታሊዝም መሠረታዊ የኢኮኖሚ ሕግ ምንድነው? በተወሰነ ምሳሌ አብራራ ።

6. ቋሚ ካፒታል ማለት ምን ማለት ነው? ልዩ ልዩ ክፍሎቹን ዘርዝር ።

7. ካፒታሊስቱ የወዝአደሩን የሥራ ኃይል በዝበዛ የሚያካብትባቸው ስልቶች ምን ምን ናቸው? በምሳሌ አስረዳ ።

8. በካፒታሊስት ሥርዓት ውስጥ ያሉት መሠረታዊ መደቦች የትኞቹ ናቸው? በትርፍ እሴት ምርት ውስጥ የሚጫወቱትን ሚና አብራራ ።

9. ትርፍ እሴት እንዴት ይፈጠራል? ማነው የሚፈጥረው? በተወሰነ ምሳሌ አስረዳ ።

10. ገንዘብ እንዴት ወደካፒታል ይለወጣል? በምሳሌ አብራራ ።

11. በትርፍ እሴት ፈጠራ ውስጥ ዝውውር ምን ሚና አለው? በምሳሌ ግለጽ ።

# ዶ ባ ት

| | | |
|---|---|---|
| 1. | ቅጥር ሥራ | *Wage Labour* |
| 2. | ሜርካንቲሊዝም | *Mercantilism* |
| 3. | አሠከፊ ሕጎች | *The Bloody Laws* |
| 4. | ቀመር | *Formula* |
| 5. | ተመጣጣኝ የእሴት ልውውጥ | *Exchange on the basis of equal value* |
| 6. | መጣኔ | *Rate* |
| 7. | ትርፍ | *Profit* |
| 8. | የገበያ ዋጋ | *Market Price* |
| 9. | ቋሚ ካፒታል | *Constant Capital* |
| 10. | ተለዋዋጭ ካፒታል | *Variable Capital* |
| 11. | የማይንቀሳቀስ ካፒታል | *Fixed Capital* |
| 12. | ተዘዋዋሪ ካፒታል | *Circulating Capital* |
| 13. | ዕልቀት | *Depreciation* |
| 14. | የካፒታል መገለባበጥ | *Turnover of Capital* |
| 15. | የተረፈ እሴት እክብ | *Mass of Surplus Value* |
| 16. | የተረፈ እሴት መጣኔ | *Rate of Surplus Value* |
| 17. | የብዝበዛ ደረጃ | *Degree of Exploitation* |
| 18. | ፍፁም ተረፈ እሴት | *Absolute Surplus Value* |
| 19. | አንፃራዊ ተረፈ እሴት | *Relative Surplus Value* |
| 20. | ተጨማሪ ተረፈ እሴት | *Extra Surplus Value* |
| 21. | የሥራ እምቀታ | *Intensity of Labour* |
| 22. | ነፃ ውድድር | *Free Competition* |
| 23. | ምሁር | *Intellectual* |
| 24. | ማኅበራዊ ክፍል | *Social Group* |
| 25. | ንዑስ ከበርቴ | *Petty-Bourgeois* |
| 26. | ቦዘኔ | *Lumpen* |
| 27. | ንጥፍጣፍ | *Stratum* |
| 28. | አስፈላጊ የሥራ ጊዜ | *Necessary Labour Time* |
| 29. | ትርፍ የሥራ ጊዜ | *Surplus Labour Time* |

.../121

## ም ዕ ራ ፍ 4

# ምንዳና የወዝአደሩ ትግል

## 1. ትርጉምና አመጣጥ፤

ምንዳ የሚለው ቃል በአማርኛ ለሙያተኛ/ለቀን ሠራተኛ/ የሚከፈል ወይም የሚሰጥ የሥራ ኃይል ዋጋ ወይም ክፍያ ሲሆን፣ ዌጅስ ከሚለው የእንግሊዝኛ ቃል ጋር ይቀራረባል ወይም ተመሳሳይነት አለው:: ከአጠቃላይ ዕድገታችንና ከቋንቋችን አለመስፋፋት ወይም ውሱንነት የተነሳ ምንዳ የሚለው ቃል በስፋትና በጥራት ባይታወቅም ዌጅስ የሚለውን የእንግሊዝኛ ቃል እንዲተካ ወይም የዚህን ቃል ፍቺ በሙሉ እንዲሸፍን ተደርጎ ተወስዷል:: ስለዚህም ዌጅስ ለሚለው ቃል ትርጉም ምንዳ በሚለው እንጠቀማለን::

በካፒታሊስት ስልተ ምርት ምንዳ ለወዝአደሩ የሥራ ኃይል የሚከፈል ዋጋ ነው:: ምንዳና ወዝአደር የካፒታሊስት ስልተ ምርት ፈርጆች /አጠቃላይ ሃሳብ መግለጫዎች/ እንደመሆናቸው ጽንሰ ሃሳባቸው — ይዘታቸው — ከዚህ ሥርዓት ጋር የተቆራኘ ነው:: በሌሎች ስልተ ምርቶች እነዚህ ቃላት ወይም አይኖሩም ወይም ትርጉማቸውና ይዘታቸው የተለየና ሌላ ይሆናል:: ለምሳሌ በሶሻሊስት ኅብረተሰብ ወዝአደር የሚለው በሠራተኛ ሲተካ ምንዳ ግን ከብዝበዛ ነጻ የሆነ የሥራ ክፍያ ወይም ዋጋ ይሆናል፤ ክፍያውም "ከእያንዳንዱ እንደችሎታው ለእያንዳንዱ እንደሥራው" በሚለው የሶሻሊስት መርሆ ይከናወናል::

የምንዳ አመጣጥ ከካፒታሊስት ስልተ ምርት አመጣጥ ጋር የተያያዘ ነው፤ ጽንሰ ሃሳቡም በቡርዧውና በወዝአደሩ መካከል በሸቀጥ ማምረትና

በማከፋፈል አካባቢ የሚፈጠረውን ግንኙነት ያጠቃልላል። ቡርዧው የወዝአደሩን የሥራ ኃይል እየገዛ ማለትም ምንዳ እየከፈለ እንደሚበዘብዝ ያመለክታል። ወዝአደሩ እያመረተ ሀብትን በዚያም ተረፈ እሴትን እየፈጠረ ካፒታሊስቱ ግን የምርት መገልገያዎችና የምርቱም ባለቤት በመሆኑ የዉጤቱን ፍሬ ይመዘብረዋል።

ካርል ማርክስ የወዝአደሩን አስከፊ የብዝበዛ ሁኔታ በአጭሩ ቁልጭና ግልፅ ባለ መንገድ ሲያስቀምጠው "የምንዳ ባርነት" ይለዋል። በካፒታሊስት ስልተ ምርት ከሥራ ኃይሉ በስተቀር መናሪያ ወይም መተዳደሪያ የሌለው ወዝአደር የሕይወት ማቆያ ወይም መሰንበቻ በሆነችው ምንዳ-ኑሮውን ይገፋል፤ ሕይወቱ ከእጅ ወደ አፍ ብቻ እንጂ ሌላ ፍቺ የለውም። ካፒታሊስቱ ወይም ቡርዧው የሕይወት ማሰንበቻ እንጂ የሕይወት ምንነትና ትርጉም ሊታወቅበት በማይችል የመነመነች ምንዳ አማካይነት ወዝአደሩን እንደባሪያ ሰጥ ለጥ አድርጎ ይገዛዋል፤ ይበዘብዘዋል። በወዝአደሩና በቡርዧው መካከል ያለው ግንኙነት በጌታና በባሪያ መካከል ካለው ግንኙነት የተሻለ ወይም የተለየ አይደለም፤ በማለት ነው ታላቁ የወዝአደር ምሁርና መሪ ካርል ማርክስ "የምንዳ ባርነት" በማለት ሁኔታውን ያጠቃለለው።

ወደ ቃሉ ትርጉም ለመመለስ ምንዳ ደመወዝ ከሚለው ቃል ጋር ይቀራረባል፤ ሁለቱም ቃላት ለሠራተኛ የሚደረግን ክፍያ ያመለክታሉ። አንድ ሠራተኛ የተወሰነ ሥራ ይሰራል፤ ለተወሰነ ጊዜ አገልግሎት ይሰጣል፤ ለምሳሌ እንበል አንድ የወርቃ ወርቀ ወይም የብ/ታ ብረት ፋብሪካ ሠራተኛ አንድ

ሜትር ካኪ፣ 1 ኪሎ ምስማር ያመርታል፣ ሌላው በፀሐፊነት፣ በሂሣብ ያዥነት፣ በሹፌርነት ተቀጥሮ አገልግሎት ይሰጣል። በቀጥታ ለሚያመርቱት የወርቻ ወርቀ፣ የብረታ ብረት ሠራተኞች ለምርቱ ተግባር አስፈላጊውን አገልግሎት ለሚሰጡት፣ ፀሐፊ፣ ሂሣብ ሠራተኛ፣ ሹፌር — ለምርት ሥራቸው፣ ለአገልግሎታቸው በቋሚነ ጊዜ ገንዘብ ይከፍላቸዋል። ይሁንና የክፍያው ጊዜ ይለያያል። ወዝአደሩ ማለትም በምርት ላይ የተሰማራው የፋብሪካው ሠራተኛ የክፍያው መጠኑ /ሬት/ በሰዓት፣ በቀን በሚያስገኘው የምርት መጠን ይወሰናል፤ ለምሳሌ በሰዓት 1 ብር፣ 2 ብር፣ 3 ብር፣ ... በቀን 5 ብር፣ 6 ብር፣... ወይም በቀን፣ በሣምንት፣ ወዘተ በተወሰነው ብዛት መጠን ይሆናል። ይህ በሰዓት ወይ በቀን የተወሰነው ክፍያ አብዛኛውን ጊዜ በሣምንት በአሥራ አምስት ቀን ተጠራቅሞና ተደምሮ ይከፈላል። በአብዛኛው በአገልግሎት ዘርፍ የተሰማሩት የሥራቸው ባሕርይ በቀን፣ በሰዓት ወይም በምርት መጠን ሊወሰን የማይችል ሠራተኞች ክፍያ ደሞዝ ይባላል። ይህም በወር የሚታሰብ ነው።

የወዝአደሩ ምንዳ መጠኑና ክፍያ በሰዓት ወይም በቀንና በሣምንት ወይም በሁለት ሣምንት የተደረገው ያለ ምክንያት አይደለም። አንደኛ ወዝአደሩ በማያመርትበት ጊዜ ባለመከፈሉና በቀላሉ ለማባረር እንዲያመች ነው፣ ወዝአደሩ በማይሠራበት ሰዓት በዕረፍት ጊዜው ለምሳሌ ከሥራ ሰዓት ውጭ ማታ በበዓላት ቀን በሕመም ጊዜ ወዘተ... አይከፈለውም።

የካፒታሊስት የማምረት ሂደት በግላዊ ጥቅም፣ በትርፍ ማጋበስ ላይ የተመሠረተ በለሆነ ገቢው ቀዝቀዝ ትርፉ ቀነሰ በሚያደርግበት ጊዜ የሰዓቱን ወይም የቀኑን ሂሣብ በጥቶ ቶሎ ለማባረር ቡርዧው ለወዝአደሩ ያመቻቸዋል። በሌላ በኩል ደግሞ አንዳንዱ ወዝአደር በየሰዓቱ በየቀኑ

ያመረተውን ለመቆጣጠርና ለይቶ በማወቅ ውጤታቸው ደከም ያለ የመሰለውን ለማስጠንቀቅና እንዲሻሻሉ ለማድረግ ወይም ዝቅዝቅተኛ ምርት ደከም ያሉትን ለማስወጣት የትርፉ መጠን ከፍ የሚልበትን ዘዴ ለመፈለግ በዚህ ዘዴ ይገለገላል። የዚህ የምንዳ መጠን በሰዓት ወይም በቀን የመክፈልና የመወሰን የመጨረሻ ውጤት ባንድ በኩል የወዝአደሩን ጭቆናና ብዝበዛ ማባባስ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ የቡርዧውን ትርፍ ከፍ ለማድረግ ነው።

እንደዚህ ዓይነቱ የመበዝበዣና የመጨቆኛ ዘዴ ካፒታሊዝምን በመተካት በሚመጣው ስርቶ አደሩ ሕዝብ ጥቅም ላይ በተገነባው የሶሺሊስት ኅብረተሰብ አይኖርም። ሠራተኛው የሚከፈለው በሥራው መጠን ቢሆን የጋርዮሽና የሶሺሊስት መንግሥት ዓላማና ግብም የሰፊውን ስርቶ አደር ሕዝብ መሠረታዊ ፍላጎት ለማሟላት የከፍተኛውን ኅብረተሰብ ማለትም የኮምዩኒዝም ቁሳዊና ቴክኒካዊ መሠረት መገንባት በመሆኑ የካፒታሊዝም ዓይነተኛ ገጽታ የሆነው ብዝበዛና ጭቆና ሊኖር አይችልም።

2. <u>ሥራና የሥራ ኃይል፤</u>

ከዚህ በላይ ስለምንዳ ስናወሳ የሥራ ኃይል ዋጋ መሆኑን ጠቅሰናል፤ ስለሥራ ኃይል ስንናገር ደግሞ ከሥራ ጋር ማያያዝ አስፈላጊ ይሆናል። ሥራና የሥራ ኃይል የተወሳሰቡና የተያያዙ ቢሆኑም አንድና ተወራራሽ አይደሉም። ስለሆነም በሁለቱ ጽንሰ ሃሣቦች መካከል ያለውን ግንኙነት በአጭሩም ቢሆን ገልጦ ማሳየት ያስፈልጋል።

ከካርል ማርክስ በፊት የነበሩት የቡርዧ ክላሲካል የኢኮኖሚ ሊቃውንት የሥራንና የሥራ ኃይልን ምንነት ልዩነትና ግንኙነት አላብራሩትም ነበር፣ ሥራ የእሴት ፈጣሪ መሆኑን ቢያረጋግጡም የሥራ ኃይልንና ሥራን ግን ለይተው ጽንሰ ሃሣባቸውን ለመግለጽ አልበቁም ነበር ። በእነዚህ የፖለቲካ ኢኮኖሚ ሊቃውንት አስተሳሰብ ሥራና የሥራ ኃይል አንድና ተመሳሳይ ወይም ያው ናቸው ። በአንጻሩ የሥራን ትክክለኛ ትርጉም የገለጸውና የሥራ ኃይል የሚለውንም ፈርጅ ያብራራው ታላቁ ወዝአደራዊ ምሁር ካርል ማርክስ ነው ።

ከሁሉ በፊት ሥራ ምንድነው? በማለ ፖለቲካ ኢኮኖሚ ሥራ ተፈጥሮንና የሥራ ኃይልን በማዋሀድ የእሴት መፍጠሪያ ሂደት ነው ። በምሳሌ እናብራራ፡— እንጨት ከዛፍ ተቆርጦ፣ ተጠርቦ፣ ተልጎ፣ እንደገና ተቆራርጦ፣ ተገጣጥሞ፣ በርጩማ፣ ወንበር፣ ጠረጴዛ፣ አልጋ፣ ኮመዲኖ...ሌሎችም ቁሳቁስ ይሆናል፣ በዚህ ሂደት ውስጥ የተፈጥሮ ክፍል ወይም አካል የሆነው እንጨት በልዩ ልዩ ደረጃ አልፎ በመጨረሻ ወንበር ጠረጴዛና ሌላም ሌላም ነገር ሆኖአል፣ ይሄንን የተፈጥሮ ክፍል ማለትም እንጨትን ወደ ወንበርነትና ጠረጴዛነት ወደ መሳሰሉት የለወጠው የሰው የሥራ ኃይል ነው ። ሥራም የምንለው እንጨትና/ተፈጥሮ/ የሰው የሥራ ኃይል በተግባራዊ እንቅስቃሴው /እንጨት መቁረጥ፣ መጥረብ፣ መላግ፣ መገጣጠም.../ ባንድነት ተዋህደው በመጨረሻ ላይ እሴት/ ወንበር፣ በርጩማ፣ ጠረጴዛ፣ ኮመዲኖ፣ ወዘተ.../ ያስገኙበት ሂደት ነው ።

ሥራ እሴት የሚፈጠርበት ሂደት/የእሴት ፈጣሪ/ ቢሆን ሥራ ራሱ ግን እሴትነት የለውም፣ ወይም ሥራ እሴት አይደለም ። በሌላ አባባል ሥራ እሴትን ይፈጥራል እንጂ ራሱ እሴት አይደለም፣ እሴት እሴትን ሊፈጥር አይችልም፣ ይህ ትርጉም የለሽ ወይም ፍቺ የሌለው ነገር ይሆናል ። የቡርዧ የኢኮኖሚ ሊቃውንት ግን ሥራን እንደ እሴት አድርገው ይቆጥራሉ፣ ይህ ግን ትልቅ ስህተትና መወናበድ ነው ።

ሥራ ተፈጥሮና የሥራ ኃይል ባንድነት ተዋህደው አቢትን የሚፈጥሩበት ሂደት ቢሆን የሥራ ኃይል ግን የሰው የመሥራት ችሎታ ነው። ለምሳሌ እንጨትን መቁረጥ አፈርን መቆፈር ጠረጴዛን መሥራት ብረትን መቀጥቀጥና መጥረቢያ ማቀፅ... መሥራት መኪና መገጣጠም አንዱን ነገር አስቦ መሥራት ወይም መፍጠር ለነዚህና የመሳሰሉት ሁሉ የጉልበት ወይም የአእምሮ ኃይል ወይም ችሎታ የሚጠይቁ ናቸው። በጉልበት ሆነ በአእምሮ ማለትም አስቦ ወይም በሀሣብ ኃይል አንዱን ነገር የመሥራትን፣ የመፍጠርን ወይም የመለዋወጥን ችሎታ የሥራ ኃይል እንለዋለን። ይህ የመሥራት ወይም አንዱን ነገር የማከናወንና የመለወጥ ችሎታ ከሂደቱ ማለትም ከሥራ የተለየ ቢሆንም ከዚህ ጋር የተያያዘና የተወሳሰበ ሆኖ እናገኘዋለን።

ታላቁ ካርል ማርክስ የሥራንና የሥራ ኃይልን ጽንሰ ሃሳቦች ካብራራ በኋላ በቡርዧ ሥርዓት ወዝአደሩ የሥራ ኃይሉን እንደ ሸቀጥ ለካፒታሊስቱ እየሸጠ የሚኖር መሆኑን በሰፊ ትንተናው አሳይቷል። በመሠረቱ በካፒታሊስት ሥልተ ምርት ወዝአደሩ ከሥራ ኃይሉ ማለትም ከመሥራት ችሎታው በስተቀር ምንም ዓይነት ሀብት፣ ንብረት፣ ጥሪት የለውም። የምርት ማከናወኛውንና የማምረቻ መሣሪያውን፣ ቋሚ ሀብቱንና ንብረቱን በመግፈፍና በመንጠቅ ገበሬ፣ ጪሰኛው፣ ቀጥቃጩ፣ ሸማኔው፣ ፋቂው፣ አንጥረኛው፣ ሸክላ ሠሪው... ወደ ወዝአደርነት የተለወጠው በካፒታሊዝም አመጣጥ ሂደት ውስጥ ነው፣ ይህ ሂደት የመጀመሪያ ደረጃ "የካፒታል ክምችት" በሚለው ርዕስ ሥር በአንደኛው የማሌ ፖለቲካ ኢኮኖሚ ማስተማሪያ ውስጥ ተብራርቷል። ከዚህ በፊት ባለው ምዕራፍ ፫ ውስጥም ተወስቷል።

ከሥራ ኃይሉ በስተቀር መኖሪያና መተዳደሪያ አልባ የሆነው ወዝአደር ሸቀጡን ማለትም የመሥራት ችሎታውን ለቡርዧው የሚሸጠው በምንዳ

እንደሆነ ከላይ ተመልክቷል። ወዝአደሩ የሥራ ኃይሉን ለካፒታሊስቱ ይሸጥና /ተቀጥሮ በመሥራት/ ለዚህ ዋጋ ምንዳ ይሰጠዋል፣ ይህ ምንዳ የሚተመነውና የሚሰጠው በአብዛኛው በተለይም ባሁኑ ጊዜ በገንዘብ ቢሆንም ቀደም ብሎ ካፒታሊዝም በማደግ ላይ በነበረበት ወቅት በዕቃ ሸቀጥ በዓይነት መልክም ይከፈል ነበር።

የካፒታሊስት ሥልተ ምርት ዓይነተኛ ባህርይ ወዝአደሩ የሚፈጥረውን ተረፈ እሴት መበዝበዝና ሁልጊዜ ትርፍ ማሳደግ እንደመሆኑ የምንዳ መጠን ወይም ልክ የሚወሰነው ከሥርዓቱ ሕልውናና ዓላማ አኳያ ይሆናል። የካፒታሊስት ሥርዓት ዓላማ ወዝአደሩን ተረፈ እሴት እያስፈጠረ መበዝበዝ ነው፣ የዚህ ሥርዓት ሕልውና ግን የወዝአደሩን መኖር ይጠይቃል፣ በሌላ አባባል ያለ ወዝአደር፣ ያለ ተረፈ እሴት፣ ያለ ትርፍ፣ ካፒታሊዝም ሊኖር አይችልም። የወዝአደሩ ምንዳ በሚወሰንበት ጊዜ እነዚህ መሠረታዊ ነገሮች መታየት ይኖርባቸዋል።

ቀደም ማርክስ የቡርዧ ፖለቲካ ኢኮኖሚ ሊቃውንት የምንዳ መጠን የሥራ ኃይል ዋጋ እንዴት እንደሚወሰን ለማወቅና ለማሳወቅ ተደጋጋሚ ሙከራ አድርገው ነበር፣ ግን አልተሳካላቸውም። በሳይንሳዊ ትንተናው የምንዳን መጠን የአወሳሰን መሠረታዊ ሃሣቦች በትክክል የገለጸውና ያብራራው ማርክስ ነው። ማርክስ የወዝአደሩን የሥራ ኃይል ሸቀጥነት ካስረዳ በኋላ የዚህ ሸቀጥ እሴት እንደማናቸውም ሸቀጥ እሴት ለማምረት ወይም ለማፍራት አስፈላጊ በሆነው ማኅበራዊ የሥራ ጊዜ እንደሚወሰን ባደረገው ትንተና አስረድቷል።

የሥራ ኃይል እሴት የሚወሰነው የወዝአደሩን የመሥራት ችሎታ /የሥራ ኃይል/ ለመፍጠር ወይም ለማስገኘት አስፈላጊ በሆነው ማኅበራዊ የሥራ ጊዜ ነው ሲባል በትክክል ምን ማለት ነው? ይህ መብራራት ያለበት ዐቢይ ነጥብ ነው:: ከሁሉ በፊት ማኅበራዊ አስፈላጊ የሥራ ጊዜ የሸቀጦች /ማናቸውም ሸቀጥ/ እሴት መሠረታዊመለኪያና መወሰኛ ሲሆን የበሊቱ መሠረት ለያንዳንዱ ሸቀጥ ወይም ዕቃ ወይም ቁሳቁስ ለምሳሌ ይህን /እዚህ፣ እዚያ ያለውን/ ወንበር፣ ጠረጴዛ፣ መጽሐፍ ብስክሌት ወዘተ... ለማምረት በፈጀው ተጨባጭ የሥራ ጊዜ ሳይሆን በአጠቃላይ አንድ ዓይነት ሸቀጥን ለምሳሌ በአንድ ኅብረተሰብ ውስጥ በአንድ በተወሰነ ጊዜ በአጠቃላይ ወንበርን ወይም ጠረጴዛን ወይም መጻሕፍትን፣ ወይም መኪናን ወዘተ... ለማምረት የፈጀውን የሥራ ጊዜ አማካይ በመውሰድ ነው:: የወዝአደሩን የሥራ ኃይል እሴት ለመተመንም እንደዚሁ በአንድ ዓይነት የሥራ መስክ ለምሳሌ በወርቃ ወርቅ፣ በጫማ፣ በስኳር፣ በቤት ዕቃ ፋብሪካዎች፣ የተሰማራውን የወዝአደር የሥራ ኃይል ለማፍራት የፈጀውን ማኅበራዊ የሥራ ጊዜ አማካይ መሠረት በማድረግ ይሆናል::

በማናቸውም ወቅትና ጊዜ የወዝአደሩ የሥራ ኃይል እሴት የሚተመነው ከላይ በተመለከተው አኳኋን ሲሆን በአብዛኛው የዚህ ሸቀጥ እሴትና ዋጋው ተመሳሳይ ወይም እኩል ናቸው፣ የሌሎች ሸቀጦች ዋጋዎች ግን አብዛኛውን ጊዜ የፍላጎትንና የአቅርቦትን እንቅስቃሴ በመከተል ከእሴታቸው ከፍ ወይም ዝቅ ይላሉ:: የሥራ ኃይል እሴት ወይም ዋጋ ስንል ምንጻ ማለታችን በሰሆነ የዚህ መጠን ወይም ልክ ከላይ እንደተመለከተው የሥራ ኃይሉን ለማፍራት ወይም ለማግኘትና ለማምረት በሚችልበት ሁኔታ ለማቆየት ወይም ለማኖር የሚያስፈልጉትን ነገሮች ለማምረት በሚወስደው አስፈላጊ ማኅበራዊ የሥራ ጊዜ ይሆናል:: ይህንን ነጥብ ትንሽ ዘርዘር አድርጎ በምሳሌ ማብራራት ያስፈልጋል::

የሥራ ኃይልን ለማፍራት ወይም ለማምረት አስፈላጊ ማኅበራዊ የሥራ ጊዜ ዝርዝር ቢደረግና ቢብራራ የሚከተሉትን ፍሬ ሃሳቦች ይይዛል። ወዝአደሩ ጡንቻውን አንቀሳቅሶ፣ አጥፎና ዘርግቶ አንዱ ነገር ለመሥራት ለምሳሌ እንጨት ለመቁረጥ፣ ድንጋይ ለመፍለጥ ወዘተ...እንደዚሁም አንጎሉን አንቀሳቅሶ፣ አስቦ፣ አውጥቶ፣ አውርዶ፣ ልዩ ልዩ ስራዎችን ——ለምሳሌ ግንብ፣ መዝጊያ፣ ጠረጴዛ ——ለመሥራት ከሁሉ በፊት መሠረታዊ ፍላጎቶችን ማለትም ምግብ፣ ልብስ፣ መጠለያ ማግኘት ያስፈልገዋል። የእነዚህም መጠን ዓይነት ጥራት እንደኅብረተሰቡ የዕድገት ደረጃ እንደሥራው ባህርይ ይወሰናል እንጂ በማናቸውም ኅብረተሰብ በማናቸውም አገር ለማናቸውም ሥራ አንድ ወይም እኩል አይሆንም። ለዚህም ነው ዛሬ የወዝአደሩ ምንዳ ከአገር አገር፣ ከሥራ ሥራ የሚለያየው።

ወዝአደሩ ብቻውን አይኖርም፣ ቤተሰብ አለው፣ ቤተሰቡ ከእርሱ ተነጥሎ አይታይም፣ እርሱ በልቶ፣ ጠጥቶ፣ ለብሶ፣ መጠለያ አግኝቶ ሚስቱና ልጆቹ እንደዚሁ ባዶአቸውን ሊቀሩ አይችሉም፣ የተገኘውን ነገር ከእርሱ ጋር መካፈል የግዴታ ነው፣ በሌላ በኩል ደግሞ የካፒታሊስቱ ሥርዓት ሕልውና ከወዝአደር ጋር የተያያዘ ያለ ወዝአደር ሊኖር የማይችል እንደሆነ ከዚህ በላይ ተመልክቷል። የወዝአደር ምንጭ ገበሬው፣ ንዑስ ከበርቴው፣ በተለይም ራሱ ወዝአደሩ ስለሆነና በመሠረቱም የእያንዳንዱ ወዝአደር ልጅ ከወዝአደርነት ሌላ የተሻለ እድል በለማይኖረው ለዚህ ሙያ ወይም ተግባር መዘጋጀት ይኖርበታል። ስለሆነም ወዝአደሩ ልጆቹን ለወዝአደርነት የሚያበቃ ትምህርት እንዲያገኙ ያደርጋል። ይህም እንደየአገሩ የዕድገት ደረጃና እንደሥራው ባህርይ ይሆናል።

የምንዳ መጠንና ልክ ማለትም የወዝአደሩ የሥራ ኃይል ዋጋ የሚወሰነው ከላይ እንደተመለከተው፣ 1. ወዝአደሩን በሕይወት ለማቆየትና ምርታማ

ለማድረግ፣ 2. ቤተሰቡን ለማኖርና ልጆቹን ለወዝአደርነት ለማዘጋጀት በሚያስችሉ አስፈላጊ ነገሮች ዋጋ መጠን ይሆናል። በመሠረቱ ይህ ሁሉ ተጠቃለሉ የመወረሻው ወይም ዝቅተኛው አስፈላጊ የምንዳው መጠን መለኪያ ይሆናል።

በካፒታሊስት ሥርዓት በመሠረቱ የወዝአደሩ ምንዳ የሚጠመነው ከላይ በጠለከተው መንገድ ቢሆን ተደጋግሞ እንደተባለው ይህ ከኅብረ ተሰብ ኅብረ ተሰብ፣ ከአገር አገር፣ ከሥራ ሥራ ይለያያል። ለምሳሌ የካፒታሊዝምን የዕድገት ጎዳና በሚከተሉት አገሮች ማለትም ኋላቀር ካፒታሊስት አገሮችና በዳበሩት ካፒታሊስት አገሮች የወዝአደሩ ምንዳ በጣም የተለያየ ነው፣ እንደ አሜሪካ፣ እንግሊዝ፣ ጀርመን...ባሉት የዳበሩ ካፒታሊስት አገሮች የወዝአደሩ ምንዳ መጠን ታዳጊ ወይም ኋላቀር ካፒታሊስት አገሮች ከሆኑት እንደ ግብጽ፣ ኬንያ፣ ሱዳን፣ ...ከመባበሉት እጅግ በጣም የላቀ ነው።/

## 3. በካፒታሊስት ሥርዓት የምንዳ ልዩ ገጽታ

በካፒታሊስት ሥርዓት ምንዳ በትክክለኛው ገጽታው አይታይም፣ ካርል ማርክስ ምንዳ የተዘቀዘቀ መልክ እንዳለው አሳይቷል። ለምንድነው ምንዳ የተጠመመ ወይም ትክክለኛ ያልሆነ ገጽታ ይዞ የሚታየው?

ምንዳ የወዝአደሩ ሙሉ የሥራ ኃይል እሴት ወይም ዋጋ ማለትም የሥራ ፍሬው ክፍያ መስሎ ይታያል፣ ግን ይህ ትክክል አይደለም፣ ወዝአደሩ ለምሳሌ በቀን አሥር ሰዓት ይሠራ እንደሆነ ከዚህ ውስጥ ቢያንስ ግማሹን ማለትም 5 ሰዓት ለራሱ ማኖሪያ አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች ማግኛ ሲያመርት፣ በግማሹ ማለትም በቀረው 5 ሰዓት ደግሞ ለካፒታሊስቱ ትርፍ እሴት ይፈጥራል። /ይህ ነጥብ ባለፈው ምዕራፍ ዝርዝር ተደርጎ የተብራራ መሆኑ ይታወሳል/። ይሁንና ምንዳ የወዝአደሩ ሙሉ የሥራ ውጤት ዋጋ መስሎ ይቀርባል ወይም ይታያል፣ ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል?

አንደኛ ወዝአደሩና ካፒታሊስቱ በገበያ ላይ ይገናኛሉ፤ ወዝአደሩ የሥራ ኃይሉን /የመሥራት ችሎታውን/ ይዞ ይቀርባል። ካፒታሊስቱም ገንዘቡን ይዞ ይመጣል። አብዛኛውን ጊዜ ከብዙ የሥራ ኃይል ሻጮች መካከል አማርጦና አጫርቶ የተወሰነ ወዝአደርን የሥራ ኃይል ይገዛል። ይህ በነጻ ገበያ ውስጥ የሚከናወነው የሽያጭና የግዥ ሁኔታም ወዝአደሩ ሙሉ የጉልበቱን ዋጋ ያገኘና ምንዳንም ሙሉ የሥራ ውጤት ዋጋ ያስመስለዋል። ግን ከላይ እንደተመለከተው ይህ ትክክል ወይም እውነት አይደለም፤ በካፒታሊስት ሥርዓት ከቶ ሊሆን አይችልም።

ሁለተኛ ካፒታሊስቱ ወዝአደሩን ከቀጠረውና ለተወሰነ ጊዜም በሆን የሥራ ኃይሉን ከወሰደ በኋላ ክፍያውን ማለትም ምንዳውን ይከፍላል። ይህ ሁኔታ ማለትም ወዝአደሩ የሥራ ፍሬውን ባይበዘበዝ በሙሉ ያገኘ ያስመስለዋል።

ሦስተኛ ምንዳ ከሥራ ጊዜ ጋር ከፍና ዝቅ ይላል፤ ካፒታሊስቱ የሥራውን ጊዜ ከተወሰነው በላይ ቢያራዝም ክፍያውንም በመጠኑ ያክልበታል። ለምሳሌ መደበኛው የሥራ ሰዓት ስምንት ሰዓት እንደሆነ ወዝአደሩን ከዚህ በላይ እንበል አስር ሰዓት ቢያሰራው ለተጨመረው 2 ሰዓት ምንዳውን ትንሽ ከፍ ያደርጋል። በዚህም ምክንያት ምንዳ ሙሉ የሥራ ውጤት ዋጋ መስሎ ይታያል።

በእነዚህ ሦስት ምክንያቶች በካፒታሊስት ሥርዓት ውስጥ ምንዳ የተዛባና የተጭበረበረ ገጽታ ይዞ ይታያል። ካፒታሊስቱ ለሥራ ኃይል ሙሉ ዋጋ የሚከፍል መስሎ ይታይ እንጂ የወዝአደሩን ትርፍ የሥራ ጊዜ ራሱ ለሚወስደው ትርፍ እሴት ማፍሪያ እንደሚጠቀምበትና የወዝአደሩን የሥራ ፍሬ እንደሚበዘብዝ የማያጠያይቅ ነው። ወዝአደሩ ጉልበቱን፣ ነርቡን፣ አእምሮውን አንቀሳቅሶና አድክሞ የፈጠረውን ሀብት በመበዝበዝ ነው የቡርዧው መደብና የካፒታሊስት ሥርዓት ሕልውና የሚረጋገጠው።

## ፬. የምንዳ ዓይነቶች

አንድ ካፒታሊስት የወዝአደሩን የሥራ ኃይል በሚገዛበትና በሚበዘብዝበት ጊዜ በልዩ ልዩ ዘዴዎች ይጠቀማል። በአቀጣጠሩ ላይ የወዝአደሩን የሥራ ኃይል በሚገዛበት ወቅት ሆን ብሎ ገበያውን በማዛነፍ ሁልጊዜ የሥራ ኃይል ፍላጎትና አቅርቦት እንዳይመጣጠኑ፣ ፍላጎት ከአቅርቦት እንዲያንስ በማድረግ የሥራ ኃይልን አስበፈላኒ የሥራ ጊዜ ዝቅ በማድረግ ምንዳውንም ዝቅ ያደርገዋል።

### ፬.፩ የጊዜ ምንዳ

ለወዝአደሩ የሚከፈለው ክፍያ ምርት ላመረተበት፣ አንድ ነገር ላከናወነበት ጊዜ ብቻ ይሆናል። የክፍያው መጠኑ በሰዓት ወይም በቀን ይወሰናል። ክፍያው ወዝአደሩ ለሠራው /የሥራ ኃይሉን ላቃጠለው/ ጊዜ ብቻ ይሆናል። ለምሳሌ ወዝአደሩ በቀን ስምንት ሰዓት በመሥራት አራት ብር ቢያገኝ የሰዓት መጠኑ ወይም ክፍያው ሃምሣ ሣንቲም ይሆናል ማለት ነው።

ካፒታሊስቱ ወዝአደሩን በጊዜ ምንዳ በሚያሠራበት ጊዜ ልዩ ልዩ ዘዴዎችን በማቀናበርና በማቀናጀት ተረፈ እሴቱን ከፍ ቢያደርግ የወዝአደሩን የሰዓት የምንዳ መጠኑ አንጻራዊ በሆነ መንገድ ዝቅ ያደርገዋል። ለምሳሌ የቀኑን የምንዳ መጠኑ ባይለውጥ ወይም ባይጨምር የሰዓቱን መጠኑ ዝቅ ሊያደርገው የሚችልበት መንገድ አለው። አንደኛው የሥራ ሰዓቱን /የቀኑን/ ያራዝመዋል፣ ለምሳሌ ስምንት ሰዓት የነበረውን የሥራ ሰዓት ወደ አሥር ወይም ወደሌላ ከፍ ያለ ቁጥር ይለውጠዋል። የቀኑ ምንዳው መጠኑ ግን አራት ብር እንደሆነ ይቆያል።

ሁለተኛ ይህንን ዓይነት ውጤት የሥራ ሰዓቱን ሳይለውጥ ወይም ሳይጨምር በሥራ አምቀታ ማለትም ወዝአደሩን በኃይል በማሠራት ሊያገኝ ይችላል። በስምንት ሰዓት የአሥር ሰዓት ሥራ እንዲያከናውን በማድረግ ወይም በሌላ አባባል የሰዓቱና የክፍያው መጠኑ ሳይለውጥ ውጤቱ ከፍ እንዲል ለማድረግ ይችላል። ይሰውም በስምንት ሰዓት የአሥር ሰዓት የሥራ ውጤት ያገኛል ማለት ነው። በዚህ በሌት የአንድ ሰዓት የሥራ ዋጋ ወይም የሰዓቱ መጠኑ ከሃምሣ ሣንቲም ወደ አርባ ሣንቲም ዝቅ ይላል።


በሌላ በኩል ደግሞ ካፒታሊስቱ የቀኑን ክፍያ በመጠኑ ከፍ በማድረግና የሥራ ሰዓቱን በማሳደግ የሰዓቱን መጠኑ ወይም የሥራ ኃይል ዋጋ ዝቅ ለማድረግ ይችላል። ለምሳሌ የቀኑን የሥራ ሰዓት ከስምንት ወደ አሥር ከፍ አደረገው። ክፍያውንም ከአራት ወደ አራት ብር ተኩል አሳደገው እንበል። በዚህ መንገድ ወይም ዘዴ የሰዓቱን መጠኑ ወደ አርባ አምስት ሣንቲም ዝቅ ያደርገዋል። ካፒታሊስቱ በእነዚህና በመሳሰሉት ቀንብሮች የወዝአደሩን የሥራ ኃይል ዋጋ ማለትም ምንዳውን ዝቅ ያደርጋል። በአንፃሩ የሚበዘብዘውን ትረፈ እሴት ያሳድጋል። በዛሬው ጊዜ በዋናዎቹ የካፒታሊስት አገሮች በቀጥታ የሥራ ጊዜን ማራዘም አስቸጋሪ በሆነም የጊዜ ምንዳ ልዩ ልዩ ቀንብሮች በተግባር ላይ ይውላሉ። በካፒታሊስት አገሮች የጊዜ ምንዳ በቀን ሳይሆን በሰዓት ይወሰናል። የዚህም ምክንያት ካፒታሊስቱ በፈለግ ወዝአደሩን በቀን ውስጥ ከሚያሠራው በተወሰነው መጠኑ የበለጠ ብዙ ሰዓት ለማሠራትና ለመበዝበዝ ያስችለዋል። እንደዚሁም በቂ ሥራ በማይኖርበትም ጊዜ በቀን ውስጥ አነስተኛ ሰዓት በማሠራት ክፍያውን ይቀንሳል። ይህ የአሠራር ሁኔታ ለወዝአደሩና ለቤተሰቡ ችግር ቢፈጥር፣ ለካፒታሊስቱ ግን ትረፈ እሴትን ለማካበት ይጠቀማል። በካፒታሊስቱ ዓለም ዛሬ በተፈጠረው ከባድ የኢኮኖሚ ቀውስ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ወዝአደሮች በሣምንት የተወሰኑ ሰዓቶች ብቻ ||ለሚሠሩ እንደክፈል ሥራ አጥ የሚቆጠሩ ናቸው። ካፒታሊስቶች ትርፋቸው ከሚቀንስ ወዝአደሩ ሥራ



ወዝአደሩ አንድን የተወሰነ ሥራ በተወሰነ ሰዓት በቁርጥ ተዋውሎ በሚሠራበት ወቅት ምን ያህል እንደሚደክምና ክፍያው ከሥራው ጋር እጅግ ከፍተኛ ልዩነት እንዳለው የሚያሳይ (ታዳጊ አገሮች ከማርክሳዊ ፖለቲካ ኢኮኖሚ አንፃር ፣ በዩሪ ፖፖቭ)

proudly brought to you by

www.binyamhk.wordpress.com



በማጣት ቢንገላታና ቢቸገር ስለማይመርጡ በሥራ ማነስ ወይም መጥፋት ቅጥሩ ለአደጋ የበዛ ወዝአደር ለየተሠቃየ ነው። በዛሬው ጊዜ በዳበሩት ካፒታሊስት አገሮች የሥራ አጡ ቁጥር ከሃያ አንድ ሚሊዮን በላይ ቢሆን በቀን ውስጥ አንድ ወይም ሁለት ሰዓት እንደዘሁም በሣምንት ጥቂት ሰዓቶች ብቻ በመሥራት በችግር አዘቅት ውስጥ የሚፈራገጡ ቁጥራቸው ከእነዚህ ለአደጋ በጣም የላቀ ነው።

## 4.2 የቁርጥ ሥራ ምንዳ

ወዝአደሩ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ የተወሰነ ውጤት እንዲያስገኝ ይደረጋል፤ ለምሳሌ ባንድ ቀን ሁለት ጫማዎች እንዲሰፋ፣ ወይም አሥር ካልሲዎች እንዲያመርት ወይም ሃያ የመኪና ቡሎኖች እንዲሠራ ከካፒታሊስቱ ጋር ይዋዋላል። ይዋዋላል በኋላ ወደ ማይሆን መኖር ግዴታ በለሆነበትና ለመኖርም የሥራ ኃይሉን መሸጥ በላለበት ብቻ ነው እንጂ በሀብትና በመብት በእርግጥ እኩል ሆነው አይደለም። ይህ ዓይነቱ የሥራ ዋጋ ስሌትና አተማመን የቁርጥ ሥራ ምንዳ ይባላል። ካፒታሊስቱ በተወሰነ ጊዜ /በሰዓት፣ ቀን.../ አንድ በቁጥር የተወሰነ የሥራ ውጤት /በሰዓት 2 ካልሲዎች፣ በቀን ሁለት ጫማዎች.../ ወዝአደሩ ሠርቶ እንዲያቀርብ ያደርገዋል። በዚህ መሠረት ምንዳውን ይተምናል፣ ይከፍላል።

በመሠረቱ የቁርጥ ሥራ ምንዳና የጊዜ ምንዳ የተያያዙና የተወሳሰቡ ናቸው። የቁርጥ ሥራ ምንዳ ውጤት ላይ ቢያተኩርም የጊዜ ጉዳይም አለበት፤ ከጊዜ አንፃርም ይታያል፤ ይሄንን ያህል ውጤት በዚህ ጊዜ ውስጥ ተሰሉ ነው የሚወሰነው። በሌላ በኩል ደግሞ ካፒታሊስቱ በጊዜ ምንዳ ወዝአደሩን በራሱ ከሚንቀሳቀስ ማሽን ጋር በማቀናጀት የተወሰነ ውጤት እንዲያመጣ ወይም እንዲያስገኝ ያደርገዋል። ካፒታሊስቱ ወዝአደሩ በሰዓት ወይም

በቀን ውስጥ መሥራት ወይም ማምረት ያለበትን የሸቀጥ መጠንና ዓይነት ለመወሰን አንድ በሙያው የላቀ ጠንካራ ወዝአደር የሚያመርተውን አስልቶ ካረጋገጠ በኋላ በዚህ ወዝአደር የሥራ ውጤት መጠን ወይም ልክ አዲስ የሚቀጠረውን ወዝአደር እንዲያመርት ያደርገዋል። በዚህ መጠን ካላመረተ ደካማ ነህ አትችልም... በማለት ክፍያውን ዝቅ ያደርገበታል።

በሌላ በኩል ደግሞ ሥራው ጥራት የለውም፤ እንደዚህ ዓይነት ጉድለት አለበት ወዘተ... በማለት ካፒታሊስቱ በወዝአደሩ ላይ ከባድ ተጽእኖ ያደርጋል። የክፍያው መጠን ቢለወጥ ወዝአደሩ ተወንቶና ተጠቦ ከሚገባው በላይ ጊዜ አጥፍቶ ወይም የሥራ ኃይሉን አቃጥሎ ከፍተኛ ጥራት ያለው ሸቀጥ እንዲያመርት ያስገድደዋል። በዚህም ዘዴ ወዝአደሩ ከፍተኛ የኢኮኖሚ አንቀብቃቢ በሚታይበት ወቅት ብዙ ጊዜ እንዲሠራ በማድረግ ወዝአደሩን ቢያጎብጠውና ቢያስቸግረው ራሱ ግን የትርፍ መጠኑን ሁልጊዜ ከፍ ለማድረግ ይጥራል።

ካፒታሊስቱ የቁርጥ ምንዳንና የጊዜ ምንዳን በልዩ ልዩ መንገድና ዘዴ በማቀናበርና በማቀናጀት ከወዝአደሩ የሚበዘብዘውን ትርፍ እሴት ለማባደግና ለማዳበር ይጠቀሙባቸዋል። እነዚህን ከዘመናዊ ቴክኖሎጂ ውጤቶች ጋር በማቀናጀት በልዩ ልዩ መንገድና ዘዴ የወዝአደሩን የሥራ ኃይል ይመዘብራል። ዛሬ በየናያቱ ካፒታሊስት አገሮች ውስጥ ወዝአደሩን በዚህ ዘመናዊ ዘዴ የመበዝበዙና የመመዝበሩ ሥራ በሰፊው እየተካሄደ ነው።

የቁርጥ ሥራ ምንዳና የጊዜ ምንዳ ወደሶሻሊዝም በሚደረገው የሽግግር ወቅቶችና በሶሻሊዝም ውስጥ ይሠራባቸዋል፤ በእነዚህ ሁኔታዎች የሰው በሰው መበዝበዝና መመዝበር ስለማይኖር ሠራተኛው የሚያስገኘው ከፍተኛ ምርት የአዲሱን ኅብረተሰብ ግንባታ ለማራመድ ይውላል። የሶሻሊዝም መሠረት ሲጣልና የግንባታው ተግባር ሲከናወን ብቅ ብቅ

ከሚሉት ችግሮች ውስጥ ከሠራተኛው ንቃተሕሊና ከፍ አለማለት የተነሣ ምርታማነት በሚፈለገው መጠን አለማደግ እንደሆነ የሶሻሊስት አገሮች ልምዱ ያሳያል። እነዚህን ችግሮች ለመቋቋምና ለማስወገድ ማለትም ምርታማነትን ከፍ ለማድረግ በቁርጥ ሥራ መጠቀም የግዴታ ነው። ይህ እንግዲህ የሚደረገው ለብዝበዛ ሳይሆን የሶሻሊዝምን ቁሳዊ መሠረት ለማጠናከርና ለማሳደግ የኅብረተሰቡንምፍላጎት ለማሟላት ነው።

5. <u>የነጭ ላብ ምንዳ</u>

የወዝ አደሩን የሥራ ኃይል በመበዝበዝና በመመዝበር ላይ የተመሠረተው ካፒታሊስት በሊቀምርት ባለፈባቸው የዕድገት ምዕራፎች ወዝአደሩ የበለጠ የሚበዘበዝበትን መንገዱና ዘዴ እየለየወጠና እየፈጠረ መጥቷል። ካፒታሊስቱ በቃኝ ጠገብኩ ማለትን በለማያውቅ ጥዋት፣ ማታ፣ ዘወትር ወዝአደሩን የበለጠ መጭመቅና የበለጠ ትርፈ እሴት ማግኘትን፣ ሀብቱን ማዳበርን ማደለብን ነው የሚያስበው፣ የወዝአደሩ ወዝ ተመጦ ነጭ ላብ እስኪወጣው ድረስ ሊያስበዘብዙት የሚችሉ የአዳዲስ ማሽኖች በየጊዜው መሥራት አልጠገብ ባይ ቢተፋ ያደርጋል፣ እንደሚባለው የበርሃውን ትርፍ ማጋበስና ሀብት ማደለብ ፍላጎት በየጊዜው እንደአጠናከረት ነው። በሳይንስና ቴክኖሎጂ ውጤቶች በመጠቀም ወዝ አደሩ ነጭ ላብ እስኪወጣው ድረስ ከሚበዘብዝባቸው ዘዴዎች ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፦

1. <u>ቴለሪዝም፣</u> ይህ ሣይንሣዊ የአሠራር /አመራረት/ ዘዴ እፍ ደብሊዩ ቴለር ከተባለው ታዋቂ አሜሪካዊ መሐንዲስ ስምና ሥራ ጋር የተያያዘ ነው። ቴለሪዝም ወይም የቴለር ዘዴ የመነሻው የብርቱና ፈጣን ወዝ አደሮችን የሥራ እንቅስቃሴና ጊዜ በማጥናትና በመተንተን አስፈላጊ ያልሆኑትን እንቅስቃሴዎች በማስወገዱና ሥራን ከማፋጠን ነው።


ጠንካራና ፈጣን የሆኑ ወዝአደሮች በተወሰነ ጊዜ ውስጥ የሚያመርቱት ምርት መጠን ወይም የሚያከናውኑት የሥራ ድርሻ እንደመለኪያ ይወሰድና

መደበኛው የክፍያ መጠኑ ይወሰናል። ወዝአደሮቹ በዚህ መጠን እንዲያመርቱ ወይም ሥራ እንዲያከናውኑ ይደረጋሉ። በመለኪያው ወይም በመመዘኛው መጠን ወይም ልክ ያላመረቱት ወይም ያላከናወኑት የክፍያቸው መጠኑ ዝቅ እንዲል ይደረጋል።

ካፒታሊስቱ የክፍያውን መጠን ሳይለውጥ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ መመረት ያለበትን ምርት ከፍ በማድረግ ወዝአደሩን እንደፈለገው ይበዘብዘዋል።


ሌኒን ስለ ቴለሪዝም የሥራን ምርታማነት ለማሳደግና ለሶሻሊስት ግንባታ ጠቃሚነት ብዙ ጊዜ ደጋግሞ ተናግሯል። "ከቴለር ሲስተም /ቀንዴት/ ሳይንሳዊና ተራማጅ የሆነውን ክፍል እንድንጠቀምበት ያስፈልጋል፤" በማለት ሌኒን በትክክል አስቀምጦታል። ቴለሪዝም ሳይንሳዊነት ያለው የሥራ አደረጃጀትና የምርታማነት ማዳበሪያ እንደመሆኑ፤ በካፒታሊስት ሥርዓት የወዝአደሩ ዓይነተኛ መበዝበዣ ሲሆን በሶሻሊስት ስልተ ምርት ግን የሠርቶአደሩ ሕዝብ ፍላጎት ማርኪያና የግንባታ መሣሪያ ነው።

2. <u>ፎርዲዝም</u>፤ በካፒታሊስት ሥርዓት ሌላው ወዝአደሩ ነጭ ላቡ እስኪወጣ ድረስ የሚበዘበዝበት በዓለም ከታወቁት ትልቁ ካፒታሊስት ከሄንሪ ፎርድ ስም ጋር የተያያዘ የምርት ሥራ አከናወን ዘዴ ነው። ፎርድ በመኪና ፋብሪካው ውስጥ የሚሠሩትን ወዝአደሮች በተራና በመስመር አስገብቶ ልዩ ልዩ የመኪና ክፍሎችን ተሸክሞ ከፊታቸው የሚያልፍ "ኮንቬየር ቤልት" /ተሸካሚ ቀበቶ/ እያንዳንዱ ወዝአደር የተወሰነ እንቅስቃሴ በማድረግ አንድ ዕቃ አንስቶ ከዋናው ላይ እየገጠመ መኪናው በጥቂት ጊዜ ውስጥ ተገጣጥሞ ያልቃል። በሜካኒካዊ ኃይል የሚንቀሳቀሰውን ተሸካሚ





ኮንቬየር ቤልት (ተሽከርካሪ ቀበቶ) ሥራን እንዴት እንደሚሠራና እንደሚያፋጥን የሚያሳይ - (ብዝበዛ ባለበት ሥርዓት ማህበር ንቢው ለካፒታሊስቱ ስለሆነ አደገኛ ቢሆንም በሶሻሊስት ሥርዓት ግን ምርታማነትን ለማሳደግ ጥሩ ዘዴ ነው)።



ቀበቶ በማፋጠን ወዝአደሮች በፍጥነት እንዲንቀባቀሱና የሥራ ድርሻቸውን በቶሎ እንዲያከናውኑ ያደርጋል። የባይንበንና የቴክኖሎጂን ውጤት ከሰው ጋር በማቀናጀት በሥራ ለሥቀታ ከፍተኛ የሥራ ምርታማነትን የሚያስገኘው ፎርዲዝም ወዝአደሩን የሚያደነዝዝና በአጭር ጊዜ ውስጥ ከጥቅም ውጭ የሚያደርግ ነው። የተንቀባቃሹ ተሽከሚ ቀበቶ ፍጥነት እንደተፈለገ ከፍ ሊል የሚችል ቢሆን፣ ሥራውም አዕምሮን የማያሠራና አሰልቺ በመሆኑ ወዝአደሩን የሚያደነዝዝና የሚያፈዝ ነው። ከዚህም የተነሣ በወዝአደሩ ላይ ሰመም ተኝነት ይበዛል።

ይህ የአመራረት ዘዴ ዛሬ በካፒታሊስት አገሮች የወዝአደሩ ዓይነተኛ መበዝበዣ ነው። ወዝአደሩ በዚህ መንገድ ብዙ አምርቶ ትንሽ ስለሚከፈለውና ለጤናውም እንክብካቤ ስለማይደረግለት፣ ቶሎ ከጥቅም ውጭ ይሆናል። ብዝበዛና ምዝበራ በጠፋበት የምርታማነት ዓላማና ግብ የኅብረተሰቡን መሠረታዊ ፍላጎት ማሟላት ቀዳሚያ በተሰጠው በሶሺሊስት ሥርዓት ይህ ዘዴ ጉጂነቱና ኢብብአዊነቱ ተወግዶ ከፍተኛ ግልጋሎት ሊሰጥ ይችላል። ዛሬ በሶሺሊስት አገሮች አገልግሎት ላይ የሚውለው በጥንቃቄ ሠርቶአደሩን ሰዝብ በሚጠቅም በት መንገድ ነው።

3. "<u>የትርፍ ክፍያ</u>" ካፒታሊስቱ ወዝአደሩን የማትነጥፍ ጥገት አድርጎ ብዝበዛውን በማጠናከር ለመቀጠል ልዩ ልዩ ዘዴዎችን ይጠቀማል ብለናል። ከላይ ከተጠቀሱት ሌላ ቡርዧው ወዝአደሩን የሚደልልበትና ወጥመዱ ውስጥ አስገብቶ የሚበዘብዝበት ሌላው ዘዴ "የትርፍ ክፍያ" የሚባለው ነው። የወዝአደሩን ምንዳ ዝቅ አድርጎ ይወስንና ምርቱ ካደገና ትርፉ ከፍ ካለ ይሄንን ያህል ታገኛለህ፣ የትርፍ

ተካፋይ ትሆናለህ ወዘተ... በማለት ወዝአደሩ በኃይል እንዲሠራና የትርፉ መጠኑ ከፍ እንዲል ያደርጋል። በመሠረቱ ወዝአደሩ ይመስለዋል እንጂ ምንም ዓይነት የትርፍ ድርሻ አያገኝም። "የትርፍ ክፍያ" ብሎ የሚሰጠው ከምንዳው ላይ ያስቀረበትን ነው። ካፒታሊስቶች በዚህ ዘዴያቸው ወዝአደሩ የትርፍ ተካፋይና ካፒታሊስት እንደሆነ አድርገው ያቀባጥሩታል። ሁላችንም አንድ ነን፤ ሁላችንም የትርፍ ተካፋይ ነን፤ ሁላችንም ካፒታሊስት ነን፤ እያሉ ያምታቱታል። ከዚህ፡ በመነሳትና በማለፍም "ሕዝባዊ ካፒታሊዝም ወይም የሕዝብ ካፒታሊዝም" የሚባለውን ማወናበጃ ፕሮፓጋንዳ ይለፍፋሉ፤ በዚህም ወዝአደሩን ከመደብ ትግሉ ያዘናጉታል፤ ይከፋፍሉታል።

4. <u>ጉርሻ ወይም መደለያ /ቦነስ/፤</u> ወዝአደሩ ዓመቱን ሙሉ በዝቅተኛ ምንዳ ሲበዘበዝ ይከርምና በዓመቱ መጨረሻ ላይ ሂሣብ ተዘግቶ ትርፉ በሚገለጥበት ጊዜ ደህና ሠርታችሁ ከፍተኛ ትርፍ ስለተገኘ ይሄንን ያህል ለጉርሻ ተወስኖላችኋል፤ ይባላል። ወይም ተዘውን ጊዜ ይሄንን ያህል ትርፍ የተገኘ እንደሆነ ይሄንን ያህል ጉርሻ ይሰጣችኋል ተብሎ በምምነት ይደረጋል። ያንን ትርፍ ለማስገኘትና ያቺን ጉርሻ ለማግኘት ወዝአደሩ ከፍተኛ ጥረት ያደርጋል። ይህም እንደ "ትርፍ ክፍያ" ወዝአደሩን በትንሽ ጥቅም በመደለል ለከባድ ምዝበራና ብዝበዛ የሚዳርግ የካፒታሊስቶች ልዩ ዘዴ ነው።

በአንፃሩ በሶሻሊስት ሥርዓት በተለይም በመጀመሪያ ወቅት የወዝአደሩን ምርታማነት ለማሳደግና የኅብረተሰቡን ፍላጎት ለማርካት ሠራተኛውን ለማበረታታት ይህ ከላይ የተመለከተው ዘዴ ይሠራበታል። በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ሠራተኛው እንዲያመርት ከተሰጠው በላይ ያመረተና ከፍተኛ ውጤት ያስገኘ እንደሆነ የተወሰነ ገንዘብ ወይም ሌላ ጥቅም እንዲያገኝ ይደረጋል። በተጨማሪም ልዩ ልዩ ሽልማትና የሞራል ማበረታቻዎች ይሰጣሉ። የዚህ ሁሉ ዓላማ የሥራን ምርታማነትና ምርትን ለማሳደግ የሠርቶ አደሩ ሕዝብ ኑሮ ለማሻሻል እንጂ ካፒታሊስቶች እንደሚያደርጉት ለብዝበዛና ለግል ጥቅም አይደለም።

ካፒታሊስቶች ለነዚህን በመሳበሉ ልዩ ልዩ ዘዴዎች የወዝአደሩን ትግል ለማክሳሸትና የብዝበዛ ቀግምታቸውን ለማስፋት ይጥራሉ። ዞሮ ዞሮ የካፒታሊስቱ ሥርዓት ያለ ወዝአደር ሊንቀሳቀስ በለማይችል ነው እንጂ በቡርዧው አለመግብ ባይ ነትና በሚጠቀምባቸው ልዩ ልዩ ዘዴዎች ወዝአደሩ ሥጋና ደሙ አልቆ አጥንቱ ብቻ ቀርቶ ከእነቁራሹ ሊጠፋ ይችል ነበር ። ግን የሥርዓቱን ሕልውና ለመጠበቅ ተረፈ እሴትን ለማግኘት የግድ ለመሥራት የሚችል ወዝአደር ያስፈልጋል። የካፒታሊስቱ ሥርዓት ለራሱ ሲል ወዝአደሩ ተረፈ እሴትን ለማፍራት መኖር የሚችልበትን ሁኔታ መፍጠር አለበት። በሌላ አባባል ለወዝአደሩ ሕይወት ማለትም ለካፒታሊስቱ ለማምረት እንዲችል አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች ለማሟላት የሚያስችል ምንዳ መክፈል ግዴታው ነው።

## 6. የይስሙላ /አፍአዊ/ እና እውነተኛ ምንዳ

በቡርዧ ሥርዓት ወዝአደሩ የሥራ ኃይሉን ለካፒታሊስቱ በመሸጥ በሰዓት ወይም በቀን የሚተመንና በሣምንት ወይም በሁለት ሣምንት የሚከፈል ምንዳ ይቀበላል፣ በዚህ ምንዳ ራሱንና ቤተሰቡን ያኖራል፣ ያስተዳድራል ብለናል። ቡርዧው የወዝአደሩን የሥራ ኃይል በሚገዛበት ጊዜ አማርጦና አጣርቶ በለሚገዛ በአጠቃላይ የምንዳውን መጠንና ልክ ዝቅና የሚበዘብዘውን ተረፈ እሴት ከፍ በማድረግ ነው። በቃኝንና ጠገብኩን የማያውቀው ቡርዧ ወዝአደሩን የሚበዘብዘው በዚህ ብቻ አይደለም፣ ከዚህም ባሻገር በልዩ ልዩ ዘዴዎች በመጠቀም የወዝአደሩን ምንዳ ያዳክማል።

በዛሬው ወቀት ካፒታሊስቱ የወዝአደሩን ምንዳ የሚከፍለው በአብዛኛው በገንዘብ መልክ ወይም ቀርጽ ቢሆንም አልፎ አልፎ በዓይነት ማለትም በዕቃ በቁሳቁስ /ምግብ፣ ልብስ፣ መኖሪያ/ ይከፍላል። ይህ ምንዳን በዓይነት መክፈል ቀደም ብሎ ማለትም የቡርዧው ሥርዓት በዝቀተኛ የዕድገት ደረጃ ላይ በነበረበት ጊዜ ይበልጥ ይሠራበት ነበር ። በዚያን ጊዜ ካፒታሊስቱ ቀለቡን፣ ልብሱንና መኖሪያን በመቻል ወይም በመስጠት ብቻ ወዝአደሩን ይበዘብዘው እንደነበረ ታሪክ

ይመክራል። ይኸውም በዓይነት የሚከፈለው ምግቡ ሆነ ሌላው ነገር መናኛ /አብዛኛውን ጊዜ ትራፊ/ ስለሆነ ግምቱ እጅግ በጣም ዝቅተኛ ነበር።

ካፒታሊስቱ ምንዳን በዓይነት በሚከፍልበት ጊዜ ብዙ የማጭበርበር ሥራ ይሠራል፤ በአብዛኛው ወዝአደሩ ደካማና ችግረኛ ስለሆነ በዚህ ሁኔታው በመጠቀም አንዳንድ ጊዜ ምንዳውን በዓይነት ከእርሱ እንዲወስዱ ያስገድደዋል፤ እነዚህን በዓይነት የሚከፍሏቸውን ዕቃዎች ዋጋ ከፍ አድርጎ ይተምናቸዋል።

የይስሙላ ወይም አፋዊ ምንዳ ማለት ሠራተኛው የሚከፈለው ገንዘብ ከመግዛት አቅሙ ማለትም ሊገዛቸው ከሚችለው አስፈላጊ ዕቃዎች ወይም ሸቀጦች ዋጋ ጋር ሳይነፃፀር በጥሬ ገንዘብ የሚከፈል ምንዳ ነው። የዚህ ዓይነቱ ምንዳ ዓይነተኛ ድክመት ከኑሮ ውድነት ጋር ያልተያያዘ መሆኑ ነው። ለወዝአደሩና ለቤተሰቡ አስፈላጊ የሆኑት ሸቀጦች ዋጋ በየጊዜው ይንራል፤ ለዚህም ዋነኛውና ብቸኛው ተጠያቂ የካፒታሊስቱ ሥርዓት ነው። ምንዳው ከተተመነና ከተወሰነ በኋላ ለወዝአደሩና ለቤተሰቡ አስፈላጊ የሆኑት ሸቀጦች ዋጋ ያለማቋረጥ ያሻቅባል፤ ወዝአደሩ ታግሎ ጭማሪ ቢያገኝም ወዲያውኑ ካፒታሊስቱ የእነዚህን ለሕይወት አስፈላጊ የሆኑ ሸቀጦች ዋጋ በማሳደግ ተገዶ የሰጠውን መልሶ ይቀማል። በገንዘብ የሚተመንና የሚከፈል ምንዳ የይስሙላ የሚባልበት ዋናው ምክንያት ለወዝአደሩ እና ለቤተሰቡ ሕይወት አስፈላጊ የሆኑት ሸቀጦች በካፒታሊስቱ ስግብግብነትና ካፒታሊስቶቹ እርስ በርሳቸው በሚያደርጉት ፉክክር የሸቀጦች ዋጋ በየጊዜው እየናረ ስለሚሄዱ የወዝአደሩ ምንዳ የመግዛት ኃይል እሚያሽቆለቁል በመሆኑ ነው።

በካፒታሊስት ሥርዓት የወዝአደሩ ምንዳ በኑሮ ዋጋ ያለማቋረጥ መናር የሚበረበርና ደካማ ቢሆንም፤ በዚህ አንፃር ወዝአደሩ በሚያገኘው ምንዳ ራሱንና ቤተሰቡን ለማኖር የሚያስችለውን ትክክለኛ ምንዳ መገመት ይቻላል። እውነተኛ ወይም ትክክለኛ ምንዳ የሚባለው ወዝአደሩ የሚከፈለው ምንዳ ከዓመት ወደ ዓመት እየናረ ከሚሄደው የኑሮ ውድነት ጋር በማዛመድ የሚደረስበት የምንዳው እውነተኛ የመግዛት ኃይል ነው። ይኸውም የሚተመነው ለወዝአደሩና ለቤተሰቡ አስፈላጊ ዕቃዎች

/ምግብ፣ ልብስ፣ መኖሪያ፣ ጤና፣ ትምህርት.../ የወቅቱን ዋጋ በመውሰድና መሠረት በማድረግ ነው።

ወዝአደሩ የሚከፈለው ምንዳ ራሱንና ቤተሰቡን ለማኖር እንዲያስችለው ትግል ያደርጋል፣ ካፒታሊስቱ እስከተቻለውና ሁኔታዎች እስካላስገደዱት ድረስ የወዝ አደሩን ጥያቄዎች ሳለመቀበልና ጀሮ ዳባ ልበስ ለማለት ይሞክራል። ነገሩ የሞት የሽረት፣ የመኖር ያለመኖር ስለሆነ ወዝአደሩ መታገሉን አያቋርጥም፣ በሕብረትና በማኅበር ሆኖ የሚያካሂደው ትግል በመጠኑም ቢሆን ውጤት ስለሚያስገኝለት የይስሙላ ምንዳ እንዲሻሻል ይደረጋል። በሌላ በኩል ደግሞ ወዝአደር ከሌለ ቡርዧው ራሱና ሥርዓቱም ሊኖሩ ስለማይችሉ ቡርዧው በይስሙላ ምንዳና በኑሮ ዋጋ መካከል ያለው ልዩነት በጣም እንዳይሰፋና ወዝአደሩ ለመኖርና ለማምረትከማይችልበት ደረጃ ላይ እንዳይደርስ እንዲጠነቀቅ ይገደዳል። ይህን የሚያደርገው ወዝአደሩ ከጠፋ ወይም ለማምረት ካልቻለ ቡርዧው ሕልውና እንደማይኖረው ስለሚገነዘብ እንጂ ለወዝአደሩ በማሰብና በመራራት አይደለም። በይስሙላ ምንዳና በኑሮ ዋጋ በቡርዧና በወዝአደር መካከል ያለው ቅራኔ በቦሻሊስት አብዮት እስከሚፈታ ድረስ ፍትጊያውና ግብ ግቡ ይቀጥላል።

ኅብረተሰብ ወደ ሶሻሊዝም ሲሸጋገር የይስሙላ ምንዳና ትክክለኛ ወይም እውነተኛ ምንዳ አንድ ይሆናሉ። ዛሬ በዳበረት ወይም ወደፊት በተራመዱት ሶሻሊስት አገሮች ለሠራተኛው የሚከፈለው የሠራተኛውን መሠረታዊ ፍላጎቶች የሚያሟላው እውነተኛ ምንዳ ነው። እርግጥ አብዮት በሚካሄድበት በሽግግር ወቀት ሠራተኛውና ወዝአደሩ በአጠቃላይ ከቀድሞው የተሻለ ምንዳ የሚያገኝ ቢሆንም የእሱንና ቤተሰቡን ፍላጎት በሚገባ የሚያሟላ አይሆንም። አብዛኛውን ጊዜ እነዚህ አገሮች ዝቅተኛ ከሆነ የዕድገት ደረጃ የሚነሱ በለሆነ የሠራተኛውን ፍላጎት ለማሟላት አይችሉም። ለአዲሱ ኅብረተሰብ ግንባታ ለምርት ኃይሎች ዕድገት የሚያደርጉት ጥረት በሠራተኛው ምንዳ ላይ ተጽእኖ ያደርጋል። ከአድኅሮትና ከኢምፔሪያሊዝም የሚሰነዘርባቸውን ጥቃት ለመቋቋም የሚያደርጉት ዝግጅት፣ ለመከላከያና ፀጥታ አስከባሪ ኃይላቸው

የሚያወጡት ወጪ የሠራተኛውን ፍላጎት ለማሟላት የሚያደርጉትን ጥረት ያደናቅፉዋል፣ አቋማቸውን ይቀንሰዋል። አገራችንና አብዮታችን ለዚህ ጥሩ ምሳሌና ማስረጃ ይሆናሉ።

በካፒታሊስት ስልተምርት በአጠቃላይ የወዝአደሩ ምንዳ እያዘቀዘቀ እንደሚሄድ ታላቁ ወዝአደራዊ ፈላስፋና መሪ ካርል ማርክስ ባደረገው ሰፊና ጥልቅ ሳይንሳዊ ትንተና አረጋግጦአል። እርግጥ ይህ አጠቃላይ አዝማሚያው እንጂ በአንዳንዱ አገሮች በልዩ ልዩ የሥራ መስኮች ለተወሰኑ ጊዜያት የወዝአደሩ ምንዳ የመሻሻል ወይም የማደግ ሁኔታዎች ሊኖሩና ሊታዩ ይችላሉ።

በግላዊነትና ስግብግብነት ላይ የተመሠረተውን የቡርዧ ሥርዓት የብዝበዛ ቀንበር አሽቀንጥሮ ለመጣል ወዝአደሩ የይበሏው ምንዳ ወደ አስፈላጊ ዕቃዎች ዋጋ እንዲጠጋ በሚያደርገው ያላሰለሰ ትግል አንዳንድ ውጤቶችን ማግኘቱ የማይቀር ነው። ወዝአደሩ በረጅም ጊዜ ትግሉና ከአብዮታዊ ምሁራን ባገኘውና በሚያገኘው የመደብ ንቃተሕሊና የቡርዧውን አፈቀላጤዎችና ከፋፋዮች እየመታና እያስወገደ ሕብረቱንና ማኅበሩን በማጠናከር ትግሉን ያፋፍማል። በሥራ መስክና ዓይነት በአገር አቀፍና በዓለም አቀፍ ተደራጅቶ በወዝአደራዊ ዓለም አቀፋዊነት የካፒታሊስቱን የጭቆናና የብዝበዛ ቀንበር አነኳኩቶ ነፃ የሆነ ኅብረተሰብ ለመገንባት ውስብስብና መራራ ትግል እያካሄደ ነው።

ምንም እንኳን ወዝአደሩ ራሱንና ኅብረተሰቡን ከብዝበዛና ከጭቆና ነፃ የሚያወጣውና እኩልነት፣ ፍትሕ፣ ነፃነት፣ ብልጽግና የሰፈነበት አዲስ ሶሻሊስት ኅብረተሰብ ለመገንባት የሚችለው የቡርዧውን ሥርዓት ማለትም የመጨቆኛና የመበዝበዣ አውታሮቹን በማንኳኰትና በዚህ ላይ የራሱን የበላይ ገዢነት በመመሥረት ቢሆንም፣ ዛሬም ለምንዳ ጭማሪ ለኑሮው መሻሻል የሚያካሂደው የኢኮኖሚ ትግል በቀላሉ የሚታይ አይደለም። በመሠረቱም ወዝአደሩ በመጀመሪያ ላይ በሙያ ድርጅቱ አማካይነት

በኢኮኖሚ ጥያቄዎች ላይ ያተኩራል፣ ግን ቀስ በቀስ ቡርዧው ምንም እንኳን ተገዶ ምንዳውን ለጊዜው ቢያሻሽልለት ከላይ ከፍ ብሎ እንደ ተመለከተው የዕቃዎችን ዋጋ በማናር ቡርዧው ጭማሪውን ዋጋ ቢስ ማድረጉን ሲገነዘብ የፖለቲካ ትግል ላይ በማተኮር ሥርዓቱን ለመገርሰስና ለመጣል ግብ ግቡን ያፋፍማል።

ዛሬ ካፒታሊዝም ወደ ኢምፔሪያሊዝም የዕድገት ደረጃ በደረሰባቸው አገሮች ምንዳው አዘቅዝቆ እንዳይወርድበት ወዝአደሩ የሚያካሂደው ትግል ሥር እየሰደደና እየተጠናከረ በመምጣት ላይ መሆኑን ቀጥለን የምንጠቀሳቸው አሐዞች ያሳያሉ፡፡* በካፒታሊስቱ ዓለም አ.አ.አ. ከ1919 እስከ 1939 ማለትም በሃያ ዓመታት ውስጥ አራት ሚሊዮን ሰዎች በሥራ ማቆም እንቅስቃሴ ተሳትፈው ነበር፣ ከ1946–1960 ይህ አጧዝ ማለትም ሥራ ያቆሙት ወዝአደሮች ቁጥር 150 ሚሊዮን ደርሶአል። ከ1961 — 1971 ማለትም በአሥር ዓመት አሐዙ 315 ሚሊዮን፣ በ1970ዎቹ አጋማሽ ማለትም እስከ 1975 314 ሚሊዮን ወዝአደሮች በሥራ ማቆም እንቅስቃሴ ተሳትፈዋል። በ1978 በዳበሩት ካፒታሊስት አገሮች 50 ሚሊዮን ሰዎች ተካፋይ የሆኑባቸው 30,000 የሥራ ማቆም እንቅስቃሴዎች ተደርገዋል። በአሜሪካ ብቻ በ1979 39** ሚሊዮን የሥራ ቀን የወሰደ እንቅስቃሴ ተካሂዷል። እነዚህ ሰናሙና ያህል የተጠቀሱ ናቸው እንጂ ወዝአደሩ ለእውነተኛ ምንዳ በየአገሩ የሚያካሂደው ትግልና ግብ ግብ ከዚህ እጅግ የሰፋና ጥልቀትም ያለው ነው። ባሁኑ ወቅትም እዚህ ከተመለከተው ልቆ በመስፋፋት ላይ ይገኛል።

ታላቁ ካርል ማርክስ ጥልቀትና በፋትባለው ሳይንሳዊ ጥናትና ምርምር ይፋ ያወጣውን ይህን የወዝአደሩ የሥራ ኃይሉን መበዝበዝ ሐቅ የማይዋጥላቸው የቡርዧ ኢኮኖሚስቶች በመሠረቱ በይዘት አንድ የሆኑ ግን በአቀራረባቸው የተለያዩ ተውገር ጋሪ ንድፈ ሃሣቦችን ይዘው ይቀርባሉ። ሁሉም የማርክሲዝምን የሥራና የሥራ ኃይል እንደዚሁም የምንዳ ንድፈ ሃሣብ ትንታኔ የሚቃወሙ የወዝአደሩን የትግል እንቅስቃሴ ባለማየት

*Kozlov - Political Economy- Capitalism pp. 259-260.

**39 ሚሊዮን የሥራ ቀን ማለት /በሊቱ/ በሥራ ማቆም አድማ የተሳተፉት ሰዎች ብዛት ባደሙበት ቀን/ሰዓት/ ብዛት ተባዝቶ የሚገኝ ነው።

ዓይነቶችን የዘጉ ናቸው። እንደ ቶጋራ ባራኖ ቫቦኪ ያሉት "ማኅበራዊ" የምንዳ ንዑፈ ሃሣብ በሚለው አጠቃላይ አበ ዘጋበብ የወዝአደሩ የሥራ ኃይል ሸቀጥ አይደለም፤ እሴት ወይም ዋጋ የለውም፤ ምንዳ የአጠቃላይ ማኅበራዊ ምርት አንዱ ክፍል ነው፤ መጠኑና ልኩ የሚወሰነው በማኅበራዊ የሥራ ምርታማነትና በወዝአደሩ መደብ ማኅበራዊ ኃይል ነው፤ በማለት የካፒታሊስቱን ሥርዓት ብዝበዛና ምዝበራ ሽፋፍኖና አድበስብሶ ለማለፍ ይሞክራሉ።

የቶኚ ክንፉ በሻል ዱሞክራት ፓርቲ በትራቼ አመለካከትም ከዚህ አይለይም። በቦሻሊስት ስም የሚያወናብደው በትራቼ ምርታማነት ሲያድግ የኅብረተሰቡ ልዩ ልዩ ክፍሎች ተገቢ ድርሻቸውን ያገኛሉ በማለት ያወናብዳል፤ ጠቁ ግን የካፒታሊስቱ መደብ ከፍተኛ ብዝበዛ ከማካሄዱም በላይ የሥራ ምርታማነት ባደገ መጠን የሥራ ኃይል እሴት ዝቅ እያለ መሄዱ ነው፤ የዚህም ተጠቃሚ ቡርዧው ነው።

ሌላው የቡርዧ ሊቃውንት የሚያባዝኑት "የተደነገገ ምንዳ" በሚል አጠቃላይ ንዑፈ ሃሣብ አማካይነት በተጋባው በጂ ኤም ኬይንስ የተቀነባበረው አበ ዘጋበብ ነው። በዚህ አበ ዘጋበብ ምንዳን በመወሰን መንግሥትና የወዝአደሩ ማኅበራት ወሣኝ የሆነ ሚና ይጫወታሉ። ሥራ አጥነትን ለመቀነስ የሚቻለው ምንዳን እንዳይንቀሳቀስ "እንቅዝቀዝ" ለወዝአደሩ አስፈላጊ የሆኑትን ሸቀጦች ዋጋ በማናር በእውነተኛ ምንዳና በይስሙላ ምንዳ መካከል ልዩነቱን ማስፋት ነው። እንደዚህ ዓይነቱን እርምጃ መውሰዱ የመንግሥት ግዴታ ነው የሚል ነው። ይህ የቡርዧን ሥርዓት ከውድቀት ለመጠበቅ የተስነዘረ ሃሣብ መናፖሉች በቡርዧው መንግሥት ደጋፊነት ወዝአደሩንና ሠርቶአደሩን እንደልባቸው እንዲበዘብዙት ይጋብዛል።

ይሁንና እነዚህና የእነዚህ ተቀጥላ የሆኑት የቡርዧ አፈቀላጤ ምሁራን የሚቀምሯቸው አብይንበዊ ንዑፈ ሃሣቦች የካፒታሊስቱ ሥርዓት የኢኮኖሚ ቀውስ እየተባባሰ መሄዱና በአንፃሩ ደግሞ የወዝአደሩን ትግል ከመቀጠልና ወደፊት ከመግፋት ሊያግዱት አልቻሉም፤ አይችሉምም። ምንዳን "ኪማብረድ ወይም በማቀዝቀዝ"ና በአንፃሩ

ደግሞ የዕቃዎችን ዋጋ በማናር በልዩ ልዩ ዘዴዎች ወዝአደሩን ለመከፋፈልና ለማዳከም በርሃዉና አፈቀላጤዎቹ ከፍ ያለ ጥረት ቢያደርጉም ወዝአደሩ ትግሉን በማፋፋም ባንዳንድ ሥፍራዎች አልፎ አልፎ ለተወሰነ ጊዜም ቢሆን የኑሮ ሁኔታውን ለያሻሽለ የብዝበዛውን ሥርዓት ለየገዘገዘ መሆኑን ከዚህ በላይ ለማመልከት ሞክሯል።



## ጥ ያ ቄ ዎ ች

1. ምንዳ ማለት ምንድነው? ታሪካዊ አመጣጡን አስረዳ።
2. ምንዳ እንዴት ይወሰናል? ማነው የሚወስነው?
3. በምንዳና በሥራ ኃይል መካከል ያለው ግንኙነት ምንድነው?
4. የቁርጥ ሥራ ምንዳ ከጊዜ ምንዳ በምን ይለያል?
5. ቴለሪዝም ምንድነው? ፎርዲዝምስ? በመካከላቸው ያለው ልዩነትና ተመሳሳይነት ምንድነው?
6. እነዚህ የአሠራር ዘዴዎች በካፒታሊዝምና በሶሻሊዝም እንዴት ያገለግላሉ?
7. የይበልጣ ምንዳ ምንድነው? ለምንድነው የይበልጣ የተባለው?
8. እውነተኛ ምንዳ ምንድነው? ዘርዘር አድርገህ በተጨባጭ ምሳሌ አስረዳ።
9. እንዴትና መቼ ነው እውነተኛ ምንዳ ተግባራዊ የሚሆነው?
10. የወቅቱን የወዝአደሩን ትግል ሁኔታ በዝርዝር አብራራ።

## ቃ ላ ት

| | | |
|---|---|---|
| 1. | ምንዳ | Wages |
| 2. | የምንዳ ባርነት | Wage Slavery |
| 3. | የጊዜ ምንዳ | Time Wages |
| 4. | የቁርጥ ሥራ ምንዳ | Piece Wages |
| 5. | የነጭ ላብ ምንዳ | Sweating system |
| 6. | ኮንቬየር ቤልት | Conveyor belt |
| 7. | ደሞዝ | Salary |
| 8. | ቴይለሪዝም | Taylorism |
| 9. | ፎርዲዝም | Fordism |
| 10. | የትርፍ ክፍያ | Profit Sharing |
| 11. | ጉርሻ | Bonus |
| 12. | የይስሙላ ምንዳ | Nominal Wages |
| 13. | እውነተኛ ምንዳ | Real Wages |
| 14. | ማኅበራዊ የምንዳ ንድፈ ሃሳብ | Social theory of Wages |
| 15. | የተደነገገ ምንዳ | Regulated Wages |
| 16. | ምንዳን ማቀዝቀዝ | Wage Freeze |

# የካፒታል ክምችትና የወዝአደሩ ኑሮ ቁዛ

የካፒታል ክምችትና የወዝአደሩ ኑሮ ቁዛ

ወዝአደሩ በሥራ ሂደት ጡንቻውን በመወጠርና በማኮማተር አዕምሮውን በማበነጠቅ፣ ነርቩን በማንደድ፣ የሥራ ኃይሉን ከተፈጥሮ ልዩ ልዩ ክፍሎች ጋር በማዋሃድ ተረፈ እሴትን ይፈጥራል። ካፒታሊስቱ በነፃ /ለቀ/ ገበያ አማርጦና አጣርቶ፣ የገዛውን የወዝአደሩን የሥራ ኃይል ዘወትርና ሁልጊዜም ከፍተኛ ተረፈ እሴት እንዲፈጥርለት ይጥራል። ተረፈ እሴትን በማካበትና በማጠራቀም ካፒታሊስቱ ካፒታሉን ያሳድጋል። በዚሁ አንፃር የወዝአደሩ ኑሮ ይቆረቁዛል፣ ወደታችም ያሽቆለቁላል።

በሌላ ሥፍራ በሰፊ ብሎ እንደተብራራው ካፒታል ከሁሉ በፊት በኅብረተሰብ ዕድገት ታሪክ ውስጥ የተከሰተ ማለትም በቡርዧውና በወዝአደሩ መካከል ያለው ወይም የተፈጠረው ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ግንኙነት ነው። የዚህ ግንኙነት ቁሳዊ መሠረቶችና ገጽታዎች፣ ገንዘብ፣ ሸቀጥ፣ የምርት መገልገያዎች የሥራ ኃይል... ናቸው፤ እነዚህ ባንድነት ካፒታል ይሆናሉ። ካፒታሊስቱ እነዚህን ባንድነት አቀናጅቶ በማንቀሳቀስ ተረፈ እሴትን ያገኛል፤ በሌላ ሥፍራ በሚገባ እንደተብራራው በካፒታል ቁሳዊ መሠረቶች ይህንን ተረፈ እሴት የሚፈጥረው የወዝአደሩ የሥራ ኃይል ብቻ ነው።

በአጠቃላይ ሲታይ ካፒታል በቁሳዊ ገጽታው ከሁሉ በፊት የወዝአደሩ የሥራ ውጤት ወይም ፍሬ ሲሆን፣ የተረፈ እሴት ጥርቅም ወይም ክምችት ነው። የካፒታል ክምችት የሚከናወነው ተረፈ እሴትን ወደ ካፒታል በመለወጥ ማለትም በምርት /በልውውጥና በክፍፍል/ ሂደት ውስጥ በማስገባትና በማንቀሳቀስ ይሆናል። ካፒታል የሚከማቸው ወይም የሚያድገውና የሚራባው የወዝአደሩ የሥራ ፍሬ የሆነውን ተረፈ እሴትን ወደ ካፒታል በመለወጥ ነው።


በግላዊነት መንፈስ የተመረዘው አልጠግብ ባይና በቃኝን የማያውቀው ቡርዧ የካፒታል ክምችቱን ሂደት ባያንቀሳቅስና ባንድ በኩል የሀብት ተራራ ቢገነባ በሌላ በኩል ከዚህ ከሀብት ተራራ ፊት ለፊት ወዝአደሩ በድኅነት ማጥ ውስጥ እያዘቀጠ ይሄዳል፤ የሥራ አጡ ሠራዊትም ከምር ከዕለት ወደ ዕለት እያደገ ይመጣል:: የሰው ልጅ ከዚህ ከካፒታሊዝም አስከፊ ድርጊቶች ሊላቀቅ የሚችለውና የዚህ ሥርዓት መሠረታዊ ቅራኔ የሚፈታው ብዝበዛንና ጭቆናን አስወግዶ ፍትሕ፣ ብልጽግና፣ እኩልነትና ነፃነት የሰፈነበት ኅብረተሰብ በሚገነባው በሶሻሊስት አብዮት ይሆናል::

## 1. <u>የካፒታል ርባታ</u>

በማናቸውም ሥርዓተ ማኅበር ሰዎች ለመኖር ማምረት፣ የተመረተውንም መከፋፈልና ለፍላጎታቸው ማዋል ይኖርባቸዋል:: እርግጥ ከዚህ በፊት ሌላ ሥፍራ እንደተገለጸው እንዴት እንደሚያመርቱና እንደሚከፋፈሉ እንደየስልተ ምርቱ የተለያየ ቢሆንም ማምረቱና መከፋፈሉ ግን ባንድ አፍታ እንኳን ማቋረጥ የሌለበት ተግባር ነው:: በዚህ የማያሰልስ ሂደት ውስጥ ለኅብረተሰቡ ፍላጎት ማሟያ የሆነው ሀብት ራሱን በራሱ ይተካል፣ ይራባል፣ ይበዛል::

በካፒታሊስት ሥርዓት ይህ ከላይ የተጠቀሰው የሀብት መተካትና መራባት የራሱ የሆነ ልዩ መልክ ይይዛል:: ለኅብረተሰቡ ሕይወት አስፈላጊ የሆኑት ቁሳቁሶች /ሀብት/ ደግመው ደጋግመው በየጊዜው ይመረታሉ፣ በየወቅቱ የተመረተው ይከፋፈላል፣ ለፍጆታ፣ ለጠቀሜታ ይውላል:: ይህ የኅብረተሰብ ሕልውና መሠረት ነውና ዘወትር የሚንቀሳቀስና የሚቀጥል ሂደት ነው::

የቡርዧ ሥርዓት ሐሳዊ ከወዝአደር መኖርና ከሥራ ኃይል ጋር የተያያዘ ስለሆነ ይህንም መተካትና ዝግጁ ሆኖ መገኘት ይኖርበታል:: መራባት ወይም መተካት ከሚኖርባቸው መሠረታዊ ነገሮች ወይም ክፍሎች ውስጥ የሥራ ኃይል አንዱና




ወዝአደሩ በጨቋኞችና በበዝባዦች የሚደርስበት ግልምጫ (የ20ኛው ምዕተ ዓመት ታሪክ ከሚለው መጽሐፍ)

Proudly brought to you by
www.binyamhk.wordpress.com

ቀንኛውም ነው። ለኅብረተሰቡም ሆነ ለሥርዓቱ የሥራ ኃይል መሠረታዊና ወሣኝ በሰ ሆነ በየጊዜውና በየወቅቱ የነበረው ለየተተኪ መራባትና መባዛትም ይገባዋል።

የርባታው ወይም የመተካቱ ሂደት የሥርዓቱን ማለትም የግንኙነቱንም መቀደስ ይጠይቃል። የካፒታሊስቱ ሥርዓት በማያቋርጠው የማምረትና የማከፋፈል እንቅስቃሴው ውስጥ የተመሠረተበትን የምርት ግንኙነትም እንዳለ ያቆየዋል፤ ወዝአደሩ ያመርታል፣ ሀብት ይፈጥራል፣ ካፒታሊስቱ ይበዘብዛል፣ ይመዘብራል፤ ሥርዓቱ እስካለ ድረስ ይህ ግንኙነት ይቀጥላል።

ርባታ ቀላልና የተስፋፋ ተብሎ በሁለት ላይ ሊከፈል ይችላል። ቀላል ርባታ ራሱን በራሱ በመተካት ወይም ራሱን በራሱ በማደስ የሚወሰን ነው። የተስ ፋፋ ርባታ ከዚህ አልፎ የሚሄድና ሀብት ማባበትን ወይም ማከማቸትን የሚወምር ሂደት ነው። ቀላል ርባታ የቅድመ ካፒታሊስት ስልተምርቶች ዓይነተኛ ባሕርይ ቢሆን አብዛ ኛዉን ጊዜ የእነዚህ ስልተምርቶች ኅብረተሰብ የሚያመርተውን ለፍጆታው ብያውል፤ አንዳንድ ጊዜ የነበረውን ሀብት እንኳን ለመተካት ባይችል ይቀርና የኅብረተሰቡ ዕድገት ይቀጧል፤ ወደፊት ከመሄዱ ፋንታ ባለበት ይረገጣል ወይም ወደኋላ ይሄዳል፤ ይህ በታሪክ የተከሰተ ጉዳይ ነው። አልፎ አልፎ እንደ ጦርነትወይም ከባድ የተፈጥሮ አደጋ ያሉት ሁኔታዎች ለዚህ የኅብረተሰብ ወደኋላ መሄድ ምክንያት ሊሆኑ ቢችሉም የምርት ኃይሎችና የምርት ግንኙነቶች ለመጣጣምና አብሮ ለመሄድ ባልቻሉበት፤ በመካከላቸው ያለው ቅራኔ በከረረበት ወቅት ይህ ሁኔታ ይከሰታል። በዚህ ጊዜ ረሃብ፤ በሽታ ጉስቁልና ኅብረተሰቡን በተለይም ሰፊውን ሕዝብ ይመታ ዋል። ይህም ሁኔታ አብዛኛውን ጊዜ ለሕዝባዊ አመጽ ማለትም ለአብዮት ይፋፋና አጋጣሚ መንስዔ ይሆናል። በ1966 ዓ.ም. የፈነዳው አብዮታችን እነዚህን ሁኔታዎች የሚያንፀባርቅ መሆኑ ግልጽ ነው።

ርባታን በሚመለከት የካፒታሊስት ሥርዓት ማኅበር ዓይነተኛ ባሕርይ የተስፋፋ ርባታ ነው ብለናል፤ በመሠረቱ በአጠቃላይ ካፒታሊዝም የምርት

ኃይሎች ከፍተኛ ዕድገት ያስገኙበትና ምርትም የዳበረበት ከሶሻሊዝም በቀር ከሌሎቹ ስልተ ምርቶች እጅግ በጣም የላቀ ነው። ይሁንና በካፒታሊስት ስልተ ምርትም በየጊዜው ጦርነቶች እየተነሱ የኅብረተሰቡን ዕድገት ባለበት አቅጣጫ ወደኋላ እንደሚመልሱት ባለፉት ሁለት ዐበይት የዓለም ጦርነቶች ታይተዋል። ከዚህም ሌላ በምርት ኃይሎችና በምርት ግንኙነቶች መካከል ያለው ቅራኔ እየተካረረና እየከረረ ሲሄድ የኅብረተሰብ ሀብት ይቀረጃል። የተስፋፋ ርባታ የካፒታሊስት ስልተ ምርት ባሕሪይ ብቻ ሣይሆን የሶሻሊስትና የኮሚኒስትም ኅብረተሰብ ዋነኛ ባሕርይ ይሆናል። የካፒታሊስት ስልተ ምርት የተስፋፋ ርባታ የተመሠረተው በወዝአደሩ የሥራ ኃይል ብዝበዛ ላይ ሲሆን የሶሻሊስትና የኮሚኒስት ኅብረተሰብ የተስፋፋና የዳበረ ርባታ ግን ከፍተኛ ሶሻሊስታዊ ንቃተሕሊና፣ እኩልነት፣ ነፃነትና ብልጽግና ላይ የተመሠረተ ይሆናል።

## 1.1 ቀላል የካፒታል ርባታ

የካፒታልን የክምችት ሂደት ደህና አድርጎ ለመገንዘብ በመጀመሪያ ላይ ቀላል ርባታን ተንትኖ ማየቱ ጠቃሚ ነው። ካርል ማርክስም የካፒታልን ምንነትና ዕድገት ደህና አድርጎ ለማጥናት የተጠቀመው በዚህ ዘዴ ነው። ከላይ ከፍ ብሎ እንደተመለከተው ቀላል ርባታ የካፒታል ባሕርይ አይደለም፣ እዚህ ይህንን የምንመለከተው ውስብስቡን የክምችት ሂደት ገባ ብለን ለመረዳት እንዲያስችለን በማለት ብቻ ነው። ቀላል ርባታ ካፒታል ራሱን በራሱ የሚተካበት ወይም የሚያድስበት እንጂ ከዚያ አልፎ ይዞታውን ለማሳደግ ወይም ለማዳበር ክምችት የሚያደርግበት አይደለም። የሚመረተው ቁሳዊ ሀብት ወይም ሸቀጥ በነበረው ሁኔታ ይቀጥላል። የሥራ ኃይልም አይጨምርም፣ እንደበፊቱ ይቆያል። ካፒታሊስቱ የሚያገኘውን ትርፍ እሴት ለራሱና ለቤተሰቡ ያውለዋል። በካፒታሊስቱና በወዝአደሩ መካከል ያለው የበዝባዥና ተበዝባዥ ግንኙነትም እንዳለ ይቀጥላል።

ቀላል ርባታ የሚባለው ይህ የሀብት ማምረትን ተግባር በነበረው ወይም ባለው ሁኔታ ሳይጨምሩ ወይም ሳያባዙት መቀጠልን ሲሆን፣ ነገሩን በምሳሌ ማስረዳቱ ጠቃሚ ይመስላል። ቦከር የሚባለው ካፒታሊስት ሃምሣ ሺህ ብር ግምት ያለው ካፒታል አለው እንበል። ከዚህ ውስጥ አምስት ሺ ብር ለተለዋዋጭ ካፒታል ወይም የወዝአደሩን የሥራ ኃይል ለመግዣ ማለትም ለምንዳ ይመደባል፣ የቀረውን ለማምረቻ መሣሪያዎች ለሥራ ተገብሮች /ጥሬ ዕቃ፣ ኃይል፣ ሕንፃ.../ ወዘተ... ያውላል። ወዝአደሩ ቢያንስ ቢያንስ ከሥራ ጊዜው ግማሹን ለካፒታሊስቱ ተረፈ እሴት በማምረት የሚያጠፋ በመሆኑ ቦከርም አምስት ሺ ብር ገቢ ይኖረዋል። እነዚህ ሁለቱና /የሥራ ኃይል መግዣው ምንዳና ለቦከርና ቤተሰቡ የሚውለው ተረፈ እሴት/ የሥራ ተገብሮች በየጊዜው የሚተኩ፣ የሚታደሱ ሲሆን የማምረቻ መሣሪያዎችም ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ስለሚያልቁ አስፈላጊው የአልቀት ቅናሽ ወጥቶ የመተካት ዝግጅት ይደረጋል። በዚህ ዓይነት መንገድ ምንም ሳይጎድል፣ ሳይጨመርና ሳይቀንስ ርባታው እንዳለ ይቀጥላል።

በሌላ በኩል ቦከር በተረፈ እሴት መልክ በየጊዜው የሚወስደውን አምስት ሺ ብር ይጠቀምበታል ማለትም ለኑሮው ያውለዋል። ይህ ቦከር የሚወስደው ገንዘብ ከአሥር ዓመት በኋላ ሃምሣ ሺ ስለሚደርስ ካፒታሉ ተመለሰ ወይም ሙሉ በሙሉ ተተካ ማለት ነው። በሌላ በኩል ይህ ሂደት ካፒታል የተረፈ እሴት ክምችት ወይም የተጠራቀመ ተረፈ እሴት መሆኑን በግልጽ ያሳየናል። በቀላል ርባታ ሂደት ውስጥ ወዝአደሩ የሚፈጥረው ተረፈ እሴት ተጠራቅሞ በመጨረሻ ላይ ካፒታል ይሆናል፣ ከዚህም ካፒታል የተጠራቀመ ተረፈ እሴት መሆኑን እንገነዘባለን። በሌላ በኩል የወዝአደሩ የሥራ ኃይል በየጊዜው ዝግጁ ሆኖ መገኘት ስለሚኖርበት ይታደሳል ማለት ነው። ከጊዜ ጊዜ፣ ከዓመት ዓመት ካፒታሊስቱ የምርት መገልገያዎች

ባለቤት ቢሆን ወዝአደሩ ደግሞ የሥራ ኃይሉን አየሸጠ የሚኖር ነው፤ ስለሆነም የካፒታሊስቱ የምርት ግንኙነትም ይቀጥላል ይታደባል ማለት ነው።

## 1.2 የተበፋፋ የካፒታል ርባታ

በመሠረቱ የካፒታል ርባታ የተበፋፋ እንጂ ቀላል አይደለም። ከዚህ በላይ ቀላል ርባታ ያልነው ነገሩን ግልጽ በሆነ መንገድ ለማየትና ለመረዳት እንዲያመቸን በማለት እንጂ የካፒታል ርባታ በተጨባጭና በእውቀ እንደዚህ ቀላል ሆኖ አይደለም። ይሁንና ይህ የሚሆነው በመጀመሪያ ደረጃ ካፒታል ራሱን በመተካትና በማደስ ስለሆነ ለተበፋፋ ርባታ መነሻውና መሠረቱ ቀላል ርባታ ይሆናል። የተበፋፋ ርባታ በኋል ካፒታል ያድጋል፤ ይበዛል ይዳብራልለማለት ነው።

እንዱ ካፒታሊስት ወይም ቡርዧ የዘወትር ጥረቱና ምኞቱ ካፒታሉን ለማባደግ ለማባዛት ነው፤ ይሄንን ያህል ሀብት ካገኘው ይበቃኛል፤ እዚህ ላይ አቆማለሁ፤ ወዘተ... ማለት አያውቅም፤ ጥዋት ማታ ቀንና ሌሊት የሚያባበው፣ የሚያሰላስለው፣ የሚጠበበውና የሚወነቀው ካፒታሉን ለማሳደግ ነው። በዛሬው ጊዜ የአሜሪካ ታላላቅ ካፒታሊስቶች ለምባሌ እንደ ነፍርዴ፣ እንደ ሮክፌለር፣ወዘተ... ያሉት በብዙ ቢሊዮን ዶላር የሚገመት ሀብት ታቅፈው በቃን ጠገብን አይሉም፤ እንዲያውም የሀብት ማከበት ጥማታቸው የበለጠ እያደገ የሚሄድ ይመስላል። የዚህ ስግብግብነትና አልጠግብ ባይነት ምንጭና መንስኤ በግል ሀብት አምልኮት ላይ የተመሠረተው የካፒታሊስት ሥርዓት ነው፤ በዚህ ሥርዓት ገንዘብ ወይም ሀብት ትልቁ ፋይዳ ሆኖ በመቆጠሩ ሬጫው ሀብትን ለማጋበስ ሆኖ ይታያል።

ወደፍሬ ሃሣቡ በነመሰበ የቡርዧው ፍላጎትና ምኞት ዘወትር የካፒታሉን መጠን ማሳደግ ነው፤ የሃብትና የእሴት ፈጣሪ ወዝአደሩ ስለሆነ ቡርዧው የወዝአደሩን የሥራ ኃይል ዝቅ አድርጎ በመግዛት ከፍተኛ ተረፈ እሴት ለማግኘት ይጥራል። ቡርዧው ተረፈ እሴቱን ለማሳደግና ለማዳበር በልዩ ልዩ ዘዴዎች እንደሚጠቀምና እነዚህ ዘዴዎች ምን እንደሆኑ በሌላ ምዕራፍ ተብራርቷል።

ይሄንን ወዝአደሩን በመበዝበዝ የሚያጋብሰውን ተረፈ እሴት ካፒታሊስቱ ወደካፒታሉ ይጨምራል፣ ካፒታሉን ያሳድግበታል። አንድ ሚሊዮን ብር ካፒታል ኖሮት ባንድ የተወሰነ ወቅት ለምሳሌ ባንድ ዓመት ሁለት መቶ ሺህ ብር ተረፈ እሴት ቢያገኝ ከዚህ ውስጥ ለኑሮ የሚበቃውን እንበል ሃምሣ ሺ ብር አስቀርቶ የቀረውን ማለትም አንድ መቶ ሃምሣ ሺ ብር ወደካፒታሉ ይጨምራል። በሁለተኛው ዓመት መጀመሪያ ላይ ካፒታሉ አንድ ሚሊዮን አንድ መቶ ሃምሣ ሺ ብር ይሆናል ማለት ነው። በየዓመቱ እንደዚሁ ካፒታሉን ማሳደጉን ይቀጥላል፣ ከላይ እንደተመለከተው እዚህ ደርሺአለሁ እንግዲህስ በቃኝ አይልም። ተረፈ እሴቱ በነበረው ካፒታል ላይ በየጊዜውና በየዓመቱ እየጨመረ ይሄዳል፣ ተረፈ እሴቱ ካፒታል እየሆነ ቢሄድ ራሱም የሌላ ተረፈ እሴት ምንጭ ይሆናል።

የተስፋፋ የካፒታል ርባታ መሠረቱና መነሻው ቀላል ርባታ ወይም የካፒታል ራሱን መተካት ወይም ማደስ እንደሆነ ተመልክቷል። የተስፋፋ ርባታ የሠበተ ዐበይት ነገሮችን በቀዳሚያ መገኘት ወይም መሟላት ይጠይቃል። አንደኛ ተጨማሪ የምርት መገልገያዎች /የማምረቻ መሣሪያዎች፣ ኅንፃ፣ ኃይል፣ ጥሬ ዕቃ ወይም ሸቀጥ.../በገበያ ውስጥ እንዲገኙ ያስፈልጋል። ሁለተኛ፣ ለወዝአደሩ ሕይወት አስፈላጊ የሆኑ ተጨማሪ ነገሮችን /ምግብ፣ ልብስ፣ ቤት/ በበቂ መጠን ማግኘት መቻልን ይጠይቃል።

ሦስተኛ ተጨማሪ የሥራ ኃይል በገበያ ውስጥ መኖር መቻል አለበት። እነዚህ ሦስት አስፈላጊ ነገሮች ሊገኙ ካልቻሉ የተስፋፋ ርባታ ሊከናወን አይችልም። በሌላ አባባል የካፒታሊስት ስልተምርት እነዚህን የጠቀስናቸውን ነገሮች ተሟልተው እንዲገኙ ማድረግ ለሕልውና ወሣኝ ነው።

የተስፋፋ ርባታ ከቀላል ርባታ የሚለይበትንና ሂደቱም እንዴት እንደሆነ አጠቃላይ በሆነ መንገድ ለመገንዘብ አንድ አጭር ምሳሌ እንውሰድ። አበከር የጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ 10 ሚሊዮን ብር ካፒታል አለው እንበል፤ ከዚህ ውስጥ 1 ሚሊዮን ለሥራ ኃይል /ለምንዳ/ መግዣ የቀረውን 9 ሚሊዮን ብር ለምርት መገልገያዎች ያውላል እንበል። ወዝአደሩ ከሥራ ጊዜው ግማሹን ለራሱ አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች ለመግዛ ማለትም ለምንዳው ሲያመርት የቀረውን ግማሹን ደግሞ ለአበከር ትርፍ እሴትን በለሚፈጥር በዓመቱ መጨረሻ 1 ሚሊዮን ብር የሚያወጣ ትርፍ እሴት ያስገኛል። ከፍ ብሎ እንደተመለከተው ይህ በቀላል ርባታ ለኩባንያው ባለቤትና ቤተሰብ ፍጆታ ይውላል። በተስፋፋ ርባታ ግን በተገኘው ትርፍ እሴት አልቀቱን ሸፍኖ አብዛኛውን ለተጨማሪ የምርት መገልገያዎችና ለተጨማሪ ለወዝአደር መቅጠሪያ ይመድባል፤ እንበል ለኩባንያው ባለቤትና ቤተሰብ 50 ሺ ብር ለተጨማሪ ወይም አዲስ የምርት መገልገያዎች ስድስት መቶ ሺ ብር፤ ለአልቀት መሸፈኛ 100,000 ብር ይደለደላል። በሁለተኛው ዓመት የኩባንያው ካፒታል፤ 1. ተለዋዋጭ ካፒታል /የወዝአደሩ ምንዳ/ አንድ ሚሊዮን ሁለት መቶ ሃምሣ ሺ ብር፤ 2. የምርት መገልገያዎች ዘጠኝ ሚሊዮን ስድስት መቶ ሺ ብር ይሆናል። በጠቅላላው ካፒታሉ 10,850,000 ብር ይሆናል። የተስፋፋው ርባታ እንደዚህ እያለ እያደገ ይቀጥላል። በቀላል ርባታ ቢሆን ኖሮ በሁለተኛው ዓመት ካፒታሉ አልቀትን ብቻ በመሸፈን 10 ሚሊዮን ብር ብቻ ነበር የሚሆነው።

የተስፋፋ ካፒታል ርባታን ስንተነትንና ስናጤን ምንድነው የምናገኘው? ከመጀመሪያው አንስቶ ወደ ካፒታል የተለወጠው ትረፍ እሴት ያልተከፈለበት የወዝአደሩ የሥራ ፍሬ እንደሆነ እንገነዘባለን። የተስፋፋ ካፒታል ርባታን አስመልክቶ ካርል ማርክስ "ከርግጥ የሚሆነው ካፒታሊስቱ እየደጋገመ የሌሎችን የተወሰነ ሥራ ውጤት ክፍል ያለ ክፍያ የግሉ በማድረግ በከፍተኛ ህያው ሥራ ይለውጠዋል" በማለት አስቀምጦታል። ካፒታሊስቱ በተጠራቀመውና በተከማቸው ወደካፒታል በተለወጠው ትረፍ እሴት ተጨማሪ /የበለጠ/ ወዝአደር/ሕያው የሥራ ኃይል/ በመቅጠር ተጨማሪና ከፍተኛ ትረፍ እሴት ያገኛል፤ ይህ ተጨማሪ ትረፍ እሴት ወደካፒታል በመለወጥ እንደገና የበለጠ ከፍተኛ ትረፍ እሴትን ይወልዳል። ይህ የትረፍ እሴት/ያልተከፈለበት ሥራ/ ወደ ካፒታል መለወጥና አዲስ የሥራ ኃይልን እየገዛ ከፍተኛ ትረፍ እሴትየማግኘት ሂደት በካፒታሊስት ሥርዓት ውስጥ የማያቆምና የማያቋርጥ ነው። የካፒታሊዝም ዓይነተኛ ባሕርይም ይህ የማያቋርጥ የወዝአደሩ ትረፍ እሴት መፍጠርና ካፒታሊስቱ ይሄንን ትረፍ እሴት የግሉ በማድረግ ወዝአደሩን መበዝበዝ ነው። ስለሆነም የተስፋፋ የካፒታል ርባታ ወይም የካፒታል ክምችት በከፍተኛ ደረጃ የካፒታል መራባትና የካፒታሊስት ግንኙነት መቀጠል ነው።

## 1.3 የካፒታል ክምችትን የሚያፋጥኑ ሁኔታዎች

ካፒታሊስቱ ወዝአደሩ የሥራ ጊዜውን ግማሽ ትረፍ እሴት እንዲፈጥርለት በማድረግና ይሄንን በማከበትና ካፒታሉን በማሳደግ ብቻ አይወሰንም፤ ወዝአደሩ 8 ሰዓት ይሠራ እንደሆነ በ4 ሰዓት የሚፈጥረውን ትረፍ እሴት የግል ሀብቱ በማድረግ በቃኝ ብሎ አይገታም። በልዩ ልዩ ዘዴ ካፒታሊስቱ የትረፍ እሴቱን መጠኑና አቅሙን ከፍ ለማድረግና ካፒታሉን ለማዳበር ሌት ተቀን ይጥራል።

1.3.1 <u>የሥራ ሰዓት ማራዘም</u>

ከዚህ በፊትም በሌላ ሥፍራ እንደ ተመለከተው ካፒታሊስቱ የወዝአደሩን ምንዳ ባይጨምር የሥራ ሰዓቱን በማራዘም ለምሳሌ በቀን 8 ሰዓት የነበረውን ወደ 10 ሰዓት ወይም በቀን 10 ሰዓት የነበረውን ወደ 12 ሰዓት ከፍ በማድረግ ተረፈ እሴቱን ሊያሳድግ ይችላል። ቀደም ብሎ ወዝአደሩ ለራሱ መኖሪያ ማለትም የሥራ ኃይሉን ለማፍራትና ለቤተሰቡ ማኖሪያ 4 ሰዓት፣ ለካፒታሊስቱ ተረፈ እሴት 4 ሰዓት ይሠራ እንደሆነ አሁን ለራሱና ለቤተሰቡ ማኖሪያ አስፈላጊ የሆነው የሥራ ሰዓት ማለት 4 ሰዓት እንዳለ ሆኖ፣ ለካፒታሊስቱ ተረፈ እሴት መፍጠሪያ 4 ሰዓት የነበረውን 2 ሰዓት ታክሎበት 6 ሰዓት ይሆናል። ይሁንና ዛሬ ወዝአደሩ በመራራና ውስብስብ ትግሉ በማኅበር በመደራጀት የማይናቁ ድሎችን በተለይም የሥራ ሰዓት ወደ 8 እና በአንዳንድ መስኮች ከዚያም በታች ባሰወረደበት ወቅት በአብዛኛው ካፒታሊስቱ በዚህ ግርድፍዘዴ አይጠቀምም፣ የሥራ ሰዓትን እንደፈለገ በማራዘም ወዝአደሩን በዚህ ዓይነት መንገድ ይበዘብዝ የነበረው ቀደም ብሎ ካፒታሊዝም በማንሰራራት ላይ በነበረበት ባለፉት ሁለት ምዕተ ዓመታት ነበር። ባሁኑ ጊዜ ባንዳንድ ኋላቀር ወይም ታዳጊ ካፒታሊስት አገሮች ወይም ፋሺዝም የመንግሥት ሥልጣን በያዘባቸው የዓለም ክፍሎች ካልሆነ በስተቀር ካፒታሊስቱ በዚህ ዓይነት ግርድፍ ዘዴ አይጠቀምም።

1.3.2 <u>ማኅበራዊ የሥራ ምርታማነትን ማሳደግ</u>

በማኅበራዊ አመራረት የሥራ ምርታማነት በልዩ ልዩ መንገድ ያድጋል፣ በሳይንስና በቴክኖሎጂ በሥራ እንቅስቃሴና ሂደት

በሚደረጉት ፈጠራዎች በሚገኙት ልዩ ልዩ ዘዴዎች ማኅበራዊ የሥራ ምርታማነት ያድጋል፤ ይዳብራል። ይህ በአጠቃላይ የሸቀጦችን እሴት ዝቅ ሲያደርግ የካፒታሊስቱን ትርፍ እሴት ግን ከፍ ያደርጋል። በዚህም መሠረት ለወዝአደሩ ሕይወት አስፈላጊ የሆኑት ሸቀጦች እሴት ዝቅ ስለሚል ካፒታሊስቱ በዚያው በቀድሞ ተለዋዋጭ ካፒታል /ለሥራ ኃይል መግዣ በሚያውለው/ ቁጥሩ ከፍ ያለ ወዝአደር ለማንቀሳቀስና ለማሰማራት ስለሚችል በዚህም በኩል ትርፍ እሴቱን ያሳድጋል። ይሁን እንጂ ዛሬ የወዝአደሩ የመደብ ትግልና ድርጅታዊ ጥንካሬ በደረሰበት ዕድገት ደረጃ ምንዳውን ለኑሮው አስፈላጊ ከሆኑ አስፈላጊ ዕቃዎች እሴት ጋር በማያያዝ መቀነስ አስቸጋሪ ስለሚሆን የምርታማነት መዳበር ውጤት አስፈላጊ የሥራ ጊዜን በመቀነስ ከትርፍ እሴት መፍጠሪያ የሚውለውን ጊዜ መጨመር ነው። እንደዚሁም ከሥራ ምርታማነት መጨመር የተነሣ ለካፒታሊስቱና ለቤተሰቡ ፍጆታ የሚውሉት ሸቀጦችም እሴት ዝቅ ስለሚል በቀድሞው ወጪው በርካታና ጥራት ያላቸው የፍጆታ ሸቀጦችን ለማግኘት ወይም ለዚህ የሚያወጣውን ለመቀነስና ወደካፒታሉ ለመጨመር ይችላል። በእነዚህና በመሳሰሉት መንገዶችና ዘዴዎችም የትርፍ እሴቱን መጠን በማሳደግ በመጨረሻም ካፒታሉን ያዳብራል።

ካፒታሊስቱ የሀብት ክምችቱን ለማሳደግ ከሚጠቀምባቸው ልዩ ልዩ ዘዴዎች ውስጥ የማምረቻ መሣሪያዎችን ለመተካት ተብሎ በየጊዜው የሚቆጠበው ገንዘብ ይገኝበታል። ለምሳሌ የአበክር የማምረቻ መሣሪያዎች ዋጋ ስምንት ሚሊዮን ብር ቢሆንና እነዚህም በስምንት ዓመት ውስጥ ሙሉ በሙሉ መተካት ቢኖርባቸው በዓመት በዓመት አንድ ሚሊዮን ብር ለመሣሪያዎቹ መተኪያ ባንክ ያስቀምጣል። የማምረቻ መሣሪያዎቹ ትንሽ ጥገና እየተደረገላቸው

ለበከ ስምንት ዓመት መዉረጃ ድረስ የሚያገለግሉ ቢሆኑ በየዓመቱ የሚቀመጠዉን ገንዘብ ሌሎች አዳዲስ መሣሪያዎች በመግዛትና በሥራ ላይ በማዋል ካፒታሉን ያባዙታል። በዳበረት ካፒታሊስት አገሮች የቋሚ ካፒታል ማለትም የማምረቻ መሣሪያዎች ድርሻ በጣም ከፍተኛ ስለሆነ በዚህ መንገድ የሚከናወነዉ የካፒታል ክምችት እንደዚሁ በቀላሉ የሚገመት አይደለም።

በአጠቃላይ የካፒታል ክምችት የሚከናወነዉ በልዩ ልዩ መንገድ ነዉ፣ በቃኝ ጠገብኩኝን የማያዉቀዉ ቡርዧ ሁል ጊዜና ዘወትር ተረፈ እሴቱን ብሎም ካፒታሉን የሚያባዛበትን ዘዴ ቢያዉጠነጥን ነዉ የሚኖረዉ። ይህ ደግሞ ዞር ዞር የወዝ አደረን የሥራ ኃይል ከመበዝበዝ የሚመጣ እንጂ ከሌላ ሥፍራ በተአምር የሚገኝ አይደለም።

1.4 <u>የካፒታል ዉስጣዊ ጥንቅር</u>

ካፒታል የሚያድገዉና የሚዳብረዉ ዉስብስብ በሆነ ሂደት ነዉ። ከፍ ብሎ እንደተመለከተዉ ቡርዧዉ በልዩ ልዩ ዘዴ የወዝአደሩን የሥራ ኃይል እየበዘበዘ ተረፈ እሴቱን ያባዛል፣ ካፒታሉን ያዳብራል። ተረፈ እሴት ወደካፒታል እየተለወጠ ካፒታል እየዳበረና እያደገ ቢሄድ የዉስጣዊ ክፍሎቹ ሚዛን ክብደትና ኃይል ይቀየራል ወይም ይለወጣል፣ ይህም ሁኔታ በካፒታል ዕድገት ላይ ተጽእና ይኖረዋል።

የካፒታልን ዉስጣዊ ጥንቅር የሚወስነት ባንድ በኩል በምርት መገልገያዎችና /የማምረቻ መሣሪያዎች፣ ሕንፃዎች፣ ጥሬ ዕቃዎች፣ ኃይል/ እነዚህን በሚያንቀሳቅሰዉና በሚመራዉ የሥራ ኃይል /ወዝአደር/ መጠን መካከል ያለዉ ግንኙነት ቢሆን የዚህ ግንኙነት ሌላ መልክ ደግሞ

በተለዋዋጭና በቋሚ ካፒታል መካከል ያለው ዝምድ ነው። በምርት መገልገያዎችና በሥራ ኃይል መካከል ያለው ግንኙነት ቴክኒካዊ /ተግባራዊ/ የካፒታል ጥንቅር ሲሆን በተለዋዋጭና በቋሚ ካፒታል መካከል ያለው ግንኙነት ግን እሴታዊ ግንኙነት ነው። ይህንን ጽንሰ ሃሳብ በይበልጥ ለመገንዘብ አንድ ምሳሌ እንውሰድ። አሯን የወርቃ ወርቀ ፋብሪካ አ.ኢ.አ. በ1960 ሲቋቋም ካፒታሉ 15 ሚሊዮን ብር ነበር እንበል። ከዚህ ካፒታል ውስጥ 10 ሚሊዮን ቋሚ ካፒታል ሲሆን፡ 5 ሚሊዮኑ ተለዋዋጭ ካፒታል ሲሆን፡ ፋብሪካው ሲቋቋም በቋሚና በተለዋዋጭ ካፒታል መካከል የነበረው ጥምርታ/ሬሺዮ/ 2:1 ነው። ፋብሪካው በሚቀጥሉት 10 ዓመታት ውስጥ በየዓመቱ ከሚያገኘው ትርፍ እሴት ውስጥ የተሻሻሉ የማምረቻ መሣሪያዎች በመግዛቱ አ.ኢ.አ. በ1970 የፋብሪካው ካፒታል 18 ሚሊዮን ደረሰ እንበል፤ አዳዲሶቹ የማምረቻ መሣሪያዎች የሚፈጥሩት ተጨማሪ የሥራ ዕድል ባንፃራዊ መልክ ሲታይ ከቀድሞዎቹ አነስ ያለ ስለሚሆን በ10ኛው ዓመት ላይ የፋብሪካው ተለዋዋጭ ካፒታል 6 ሚሊዮን ብር ነው ብንል የቋሚና የተለዋዋጭ ካፒታል ጥምርታ 3:1 መሆኑ ነው። ለንግዲህ ከዚህ ምሳሌ የምንገነዘበው ሁለቱም ማለትም ቋሚና ተለዋዋጭ ካፒታል ቢጨምሩም የዕድገታቸው መጠን የተለያየ ነው።

የካፒታል ክምችቱ እያደገ በመሄዱ ውስጣዊ ጥንቅሩ ተለውጧል፤ የተለዋዋጭ ካፒታል ድርሻ ከፍ እያለ ቢሄድም ዕድገቱ ከቋሚ ካፒታል አንፃር ሲወዳደር አነስተኛ ነው። በሳይንስና በቴክኖሎጂ አማካይነት አዳዲስ የማምረቻ መሣሪያዎች እየተፈጠሩ ብዙ ሰው የሚሠራውን ተግባር ጥቂት ሰዎች እንዲያንቀሳቅሱት በመደረጉ የመሣሪያዎቹ ዋጋ ከፍ ከፍ እያለ የሰው ዋጋ በአንፃሩ ዝቅ እያለ ይመጣል። ይህ በአንዱ ፋብሪካ ምሳሌነት የተገነዘብነው ክስተት በዘሬው ወቅት በዳበሩት ካፒታሊስት አገሮች በጉልህ እየታየ ነው። የካፒታል ውስጣዊ ጥንቅር እየተለወጠ መምጣት የሚያስከትለው ውጤት ወይም ተጽእኖ ምንድነው? ቀደም ካሉት.

ምዕራፎች እንደተገነዘብነው የተረፈ እሴት ምንጭ ተለዋዋጭ ካፒታል ነው። ስለዚህ በካፒታል እድገት ሂደት ውስጥ የተለዋዋጭ ካፒታል አንፃራዊ ድርሻ እየቀነሰ መምጣት የትርፍ እድገትንም መጣኔ አንፃራዊነት እየቀነሰ እንዲሄድ ያደርገዋል። ይህ ማለት ግን የትርፍ እክብ መጠን በፍፁምነት ሲታይ እየቀነሰ ይመጣል ማለት አይደለም። የመጣኔ ዕድገት መቀነስ የመጠን እድገት መቀነስ እንዳለመሆኑ የትርፍ እክብ መጠን እየጨመረ ይሄዳል። ይህ የካፒታል ውስጣዊ ጥንቅር የሚያስከትለው ለውጥ በሚቀጥለው ምዕራፍ በዝርዝር ይብራራል።

## 1.5 የካፒታል መሰባሰብና መማከል

የካፒታል እድገት ሌላው ገጽታና ከጥንቅሩ ለውጥ ጋር በቅርብ የተያያዘው የመሰባሰቡ ሂደት ነው። የካፒታል መሰባሰብ ሲባል ግለሰብ ቡርዧዎች በልዩ ልዩ ዘዴ ወዝአደሩን በመበዝበዝ ከፍተኛ ተረፈ እሴት በማጋበስና ወደ ካፒታል በመለወጥ የሀብት ይዞታቸውን የማሳደግና የማጠናከር ሂደት ነው። በሌላ አባባል የካፒታል ክምችት ማለት ይሆናል። ቡርዧው ጠገብኩ ማለት ስለማያውቅ የዘወትር ሕልሙና ፍላጎቱ ከፍተኛ ትርፍ ማጋበስና ካፒታሉን ማሳደግ ነው። በአጠቃላይ ይህ ሂደት ማኅበራዊ ካፒታልን ማለትም የኅብረተሰቡን የሀብት መጠን ከፍ ቢያደርግም ጠቀሜታው ግን አፍኝ ለማይሞሉት ካፒታሊስቶች ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ ካፒታል እየዳበረና እየደለበ ሲሄድ የሥርዓቱ መሠረት በሆነው የፉክክርና የርስ በርስ መወራረስ ሕግ አብዛኞቹ ካፒታሊስቶች በየመንገዱ እየተዋጡ ጥቂቶች አብጠውና ተልቀው ይወጣሉ። በብዙዎቹ ካፒታሊስቶች መቃብር ላይ የጥቂት ሞኖፖሊች አምባ ገነንነት ይዘረጋል። ካፒታል ይህንን ያህል መጠኑ ባይጨምርም በጥቂቶች እጅ ውስጥ ይጠቃለላል። በዘመነ ኢምፔሪያሊዝም ይህ የካፒታል መጠቃለል ወይም

መማከል ዋናው ገጽታ ከመሆኑም በላይ ባለፉት ሠላሣ፣ አርባ ዓመታት ውስጥ የመማከሉ ሂደት እየተፋጠነ ነው። ለምሳሌ በአሜሪካ ኢንዱስትሪ ክፍለ ኢኮኖሚ አ.አ.አ.* ከ1945 እስከ 1954፣ 2929፣ ከ1955 እስከ 1964፣ 7731፣ ከ1965 እስከ 1969 8152 ኩባንያዎች/ካፒታሊስቶች/ ተውጠዋል ወይም ተጠቃለዋል። ካፒታል እጅግ በተፋጠነ መንገድ እየተማከለ ወይም እየተጠቃለለ ማለትም በጥቂት ሞኖፖሊስቶች እጅ ውስጥ እየገባ በመሄድ ላይ መሆኑን ከእነዚህ አጭር ምሳሌዎች ለመገንዘብ ይቻላል።

የካፒታልን መማከል ከሚያግዙና ከሚያፋጥኑ ሁኔታዎች ውስጥ ጦርነት የኢኮኖሚ ቀውስ/የገበያ ጥበት/፣ የቴክኖሎጂ ዕድገትና የመሳሰሉት ይገኙባቸዋል። እነዚህ ሁኔታዎች ደካማዎቹ ወይም ትንሾቹ ካፒታሊስቶች እንዲደኸዩ፣ እንዲከስሩና ከፉክክሩና ከሩጫው ውስጥ እንዲወጡ ሲያደርጉ ጠንካራዎቹና ትልልቆቹ ግን እነዚያን የወደቁትን እየዋጡ ፉክክሩን እንዲቀጥሉ ያግዛሉ። በትልልቆቹ ሞኖፖሊስቶች መካከል አልፎ አልፎ በስምምነት ገበያዎችን መከፋፈል ቢኖርም ፉክክሩና ትንንቅ እንደዚሁም መዋዋጡ የሚቀጥል ነው። ለምሳሌ አ.አ.አ.* በ1974 በምዕራብ ጀርመን ቲሰንና ራይንቦታል የተባሉት ሁለቱ አበይት የብረት ሞኖፖሎች በአንድነት ተቀላቀለዋል። እንደዚሁም በፈረንሣይ ፔጆና ሲትሮይን የተባሉት ትላልቅ የመኪና ፋብሪካ ኩባንያዎች በመዋዋጥ አንድ ሆነዋል። ይህ የካፒታል መማከል ሂደት ከካፒታሊስት ሥርዓት ከፉክክርና ከአመራረት ግላዊነትና ሥርዓቱ አልበኝነት የሚመነጭ በለሆነ ሥርዓቱ እስካለ ድረስ የሚቀጥል ነው።

## 2. የካፒታሊስት ክምችት ሂደትና የሥራ አጡ ሠራዊት

የግል ሀብት ሥርዓቱ አልበኝ አመራረትና ነፃ ፉክክር የካፒታል ክምችትና ምክለት/መማከል/ ውጤት ቁጥሩ ዕለት በዕለት እያሻቀበ የሚገሰግስ የሥራ አጥ


*Koslov - Political Economy - Capitalism, pp. 169-170

ሠራዊት ነው። ካፒታሊስቱ የሠከአደረን የሥራ ኃይል ኑቅ አዉርጎ በመግዛት ለመበዝበዝ የሚችለው የዚህ ሸቀጥ ማለትም የሥራ ኃይል አቅርቦት ከፍላጎት ልቆና በልጦ ለመገኘት በመቻሉ ነው። የካፒታሊዝም ዓይነተኛ ባሕርይ የኅብረተሰቡን አብዛኛው ክፍል በተለይም አምራቾችን ከማምረቻ መሣሪያቸው ለይቶ በማላቀቅ የሥራ ኃይላቸውን ለጥቂት በርዧዎች እየቸረቸሩ እንዲኖሩ ማድረግ መሆኑ ከዚህ በላይ በሌላ ምዕራፍ ተገልጿል።


የሥራ ኃይል አቅርቦት ከፍላጎት ከፍ ብሎ መገኘት ከካፒታሊስት ሥርዓት ሕልውና ጋር የተያያዘ ቢሆንም ካፒታል እየደለበና እየተማከለ የምርት ኃይሎች በሳይንስና በቴክኖሎጂ አማካይነት እየዳበሩ፣ የካፒታል ውስጣዊ ጥንቅር እየተለወጠ፣ የምርት መገልገያዎች ከፍተኛ ሚና እየያዙ፣ ሕያው ማለትም የሥራ ኃይል ድርሻ እየተቀነሰ በመምጣቱ ሁኔታው የበለጠ እየተባባሰ ነው። በዛሬው ጊዜ በዳበሩት ካፒታሊስት አገሮች የሥራ አጡ ሠራዊት ከማናቸውም ጊዜ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሶ ይገኛል። ለናሙና ያህል አንዳንድ አሃዞችን ብንጠቅስ አ.ኤ.አ. በ1982 በዳበሩ ካፒታሊስት አገሮች የመሥራት ችሎታቸው የተሟላ ሆኖ በሥራ አጥነት የተመዘገቡትን ሰዎች ቁጥር* ብንወስድ በዩናይትድ ስቴትስ ከ11 ሚሊዮን በላይ፣ በፈረንሣይ ከ3 ሚሊዮን በላይ፣ በእንግሊዝ ከ3.2 ሚሊዮን በላይ፣ በምዕራብ ጀርመን 2 ሚሊዮን ወዘተ... መሆኑን እንገነዘባለን። እነዚህ አሃዞች የዛሬውን ሁኔታ የሚገልጹ ቢሆኑ፣ ሁኔታው በሚቀጥሉት ዓመታትም እየተባባሰ እንደሚሄድ ከነዚሁ አገሮች የሚወጡት የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ሁኔታዎች መግለጫዎችና ጥናቶች ያበረዳሉ። ኦ.ኢ.ሲ.ዲ. /የአውሮፓ አገሮች የኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ድርጅት/ እንደገመተው በአሜሪካና በምዕራብ አውሮፓ በ1983 የሥራ አጡ ቁጥር ከ23 ሚሊዮን በላይ እንደ ሚደርስ አረጋግጧል። አ.ኤ.አ. ከ1970ዎቹ መባቻ ገደማ ጀምሮ ሥር እየሰደደና እያዘቀጠ በመሄድ ላይ የሚገኘው የካፒታሊስቱ የኢኮኖሚ ቀውስ ይህንን ሁኔታ የበለጠ እያባባሰው እንደሚቀጥል ይገመታል።

---

* መስከረም መጽሔት ቅጽ 1፣ ቁጥር 4




ሥራ አጥነትን ለማሳየት የ20ኛው ምዕተ ዓመት ታሪክ ከሚባለው መጽሐፍ የተወሰደ


proudly brought to you by
www.binyamhk.wordpress.com

ወደ አጠቃላይ ሁኔታዎች ከመለስን የካፒታሊስት ሥርዓት ያቀፈውን እንዷራዊ ትርፍ ሕዝብ ማለትም ሥራ አጥ ሁኔታ እንመለከታለን። የሥራ አጡ ሠራዊት በሦስት ላይ ተከፍሎ ሊታይ ይችላል። በመጀመሪያ ተንሳፋፊ/ፍሎቲንግ/ የሥራ አጥ ሠራዊት የሚባለው በልዩ ልዩ ምክንያት ከሥራ ዓለም አንዴ እየተባረረ አንዴ ደግሞ እየተቀጠረ የሚኖር አስተማማኝና ቋሚ የሆነ ሥራ የሌለው/[redacted] ክፍል ነው። ሌላው ደግሞ ስውር ወይም ከፊል ሥራ አጥ የሚባለው ሲሆን በአብዛኛው ለበጫ ያህል ትንሽ ሥራ ይኖረው እንደሆነ እንጂ ሙሉ ጊዜውንና በሙሉ አቅሙ የሚሠራ ክፍል አይደለም። በሦስተኛ ደረጃ ደግሞ ሃአዘቀጠው ወይም ምንም ዓይነት ሥራ የሌለው በምጽዋት ወይም በልመና የሚኖረው ሠራዊት ነው። እንዚህን በከተማና በገጠር እንፀር እንተነትናቸዋል።

## 2.1 <u>በከተማ</u>

ኢንዱስትሪዎችና ከተሞች የተያያዙ ናቸው፤ በተለይም በካፒታሊስት አገሮች በአብዛኛው ከተሞች የኢንዱስትሪዎች ማዕከል ናቸው።አብዛኛው የሥራ አጥ ሠራዊትም የሚከማቸውና የሚያድገው በከተሞች አካባቢ ነው።

ከላይ ከተጠቀሱት የሥራ አጥ ሠራዊት ክፍሎች ተንሳፋፊው እና ዝቃጩ በአብዛኛው የሚገኙት በከተሞች ውስጥና አካባቢ ነው። አብዛኛዎቹ ኢንዱስትሪዎች የንግድ ድርጅቶችና ሌሎችም አገልግሎት ሰጪዎች የተመሠረቱትና ሥራቸውን የሚያንቀሳቅሱት በከተሞች ክልል ውስጥ ስለሆነ እነዚህ ሥራ አጦች የሚኮለኮሉት በከተሞች ውስጥ ነው። ከዛሬ ነገ የሥራ ቦታ ይገኛል፤ የሥራ ኃይላችንን የሚገዛን ቡርዧ እናገኛለን፤ በማለት እዚያው አካባቢ እየተርመሰመሱ ገማሾቹ በሞትና በሕይወት መካከል የምታኖር "አበል" እየተባለላቸው፤ ገማሾቹ በልመናና በምጽዋት የሥቃይ ኑሮአቸውን ይገፋሉ።

ተንሰፋፊው የሥራ አጥ ሠራዊት እንደኢከኖሚው እንቅስቃሴ ሁኔታ እልፎ እልፎ የሥራ ኃይሉን ለመሸጥ ዕድል ያገኛል። የቡርዧው ገበያ በሚደራበትና ትርፍ በሚያጋብትበት በአጠቃላይ የኢኮኖሚው እንቅስቃሴ በሚፋፋምበት ወቅት ቡርዧው የበለጠ ትርፍ ለማጋበስ ሲል ከወትሮው የበለጠ የሥራ ኃይል ይፈልጋል። በአንፃሩ ገበያው ሲቀዛቀዝ ትርፍ ሲቀንስና የኢኮኖሚውእንቅስቃሴ ዝግ በሚልበት ጊዜ ደግሞ ቡርዧው የምንዳውን ወጪ ዝቅ ያደርገዋል፣ የወዝአደሩን ቁጥር ይቀንሳል፣ የተንሳፋፊው ሠራዊት መጠንና ቁጥር እንደገና ወደላይ ማሻቀብ ይጀምራል።

የተንሳፋፊው የሥራ አጥ ሠራዊት ሕልውና ከቡርዧው ሥርዓት ጋር የተያያዘ ከዚህ የሚመነጭ ነው፡፡ ቁጥሩና መጠኑ ከጊዜ ወደጊዜ እያደገ ካፒታሊስቱ ለማጧረትና የሥራ ኃይልን ዝቅ አድርጌ ለመግዛት የግድ ይህ ሠራዊት እንዲኖር ያስፈልገዋል። ሆኖም በሳይንስና ቴክኖሎጂ ዕድገት የማምረቻ መሣሪያዎች በየጊዜው ሰለሚሻሻሉና በካፒታሊስቶች መካከል በሚካሄደው የማያቋርጥ ፉክክርና ርስ በርስ መፋጀት እንደዚሁም በገበያ እያጠረና እየጠበበ መሄድ የዚህ ሠራዊት ቁጥር እየጨመረና እያደገ ይሄዳል። ከእነዚህም ሌላ ያለማቋረጥ ከትምህርት ዓለም ወደ ሥራ በሚመጡትና ከገጠር ወደከተማ በሚፈልሱት ቁጥሬ ቸው ያብጧል፡፡ የቡርዧ መንግሥታት የዚህ ሠራዊት እየጨመረና እያደገ መሄድ ለሥርዓቱ ሕልውና በለሚያሠጋ "ማኅበራዊ ዋስትና፣ የሥራ አጥ አበል" በሚሉ መደለያዎች ከሚያጋብሱት ከፍተኛ ትርፍ ትንሽ ፍርፋሪ በመወርወር፣ ጊዜያዊና ጥቃቅን ሥራዎችን በመፍጠር የሥራ አጥ ሠራዊቱ እንዳያምጽና በሥርዓቱ ላይ ክንዱን እንዳያነሣ ሙከራ ያደርጋሉ። ይሁንና እነዚህና የመሳሰሉት የቡርዧ መንግሥታት የማስታገሻና የመደለያ ዘዴዎች ለችግሩ ዘላቂ መፍትሔ ለመስጠት የማይችሉ የመሆናቸውን ያህል ሁኔታው ከመባባስና ችግሩም ሥር ከመስደዱ አላቆመም፣ ሊያቆመውም አይችልም።

ከታች በኩል የዚህ /የተንቧፈፈው/፤ ጠርዝ የሆነው ዝቅተኛው የሥራ አጥ ሠራተኛ ክፍል በአብዛኛው በከተሞች ውስጥና አካባቢ የሚገኝ ነው። ከእነዚህ ውስጥ አብዛኞቹ በሥርዓቱ ተስፋ የቆረጡ፤ የሥራ ኃይላቸውን ሸጠው ለመኖር ያላቸው ዕድል የመነመነ፤ በምጽዋትና በልመና የሚኖሩ ናቸው። ሕይወት ሥቃይ የሆነባቸው፤ የኑሮን ጣዕም ያጡ፤ ሕሊናቸውና አእምሯቸው የታወከና የተቃወሰ፤ የቡርዧው ሥርዓት ጠባሳዎች ናቸው። የካፒታሊስቱ ሥርዓት እነዚህን ፍሬዎቹን በማመፅ ተነስተው አደጋ ላይ እንዳይጥሉት በልዩ ልዩ ዘዴዎች በመጠቀም በቁጥጥሩ ሥር ለማዋል ጥረት ያደርጋል፤ በኘሮፓጋንዳው ኃይል ሲያፈዛቸው ሲያደነዝዛቸው የማያቋርጥ ጥረት ያደርጋል፤ ከንቃተ ሕሊናቸው ዝቅተኝነት የተነሣ በትንሽ ፍርፋሪ በመደለልና በማወናበድ በወዝአደሩ ላይ በማሰለፍ በመሣሪያነት ሲገለገልባቸው ይኖራል፤ ይህ የቡርዧው መሰሪነት አልፎ አልፎ አንዳንድ ውጤቶችን ቢያስገኝም፤ ለችግሩ መፍትሔ ሊሆን በለማይችል ፈርሽነቱ የማያጠያይቅ ነው። የሥርዓቱ ቅራኔዎች እየተፋፋሙና እየከረሩ ሲሄዱ፤ ችግሩ የበለጠ ሥር እየሰደደና እየተባባሰ ሲመጣ ወዝአደሩና ሌሎችም ጭቁን የኅብረተሰብ ክፍሎች በሥርዓቱ ላይመነሳታቸው ሳማ-ይቀር ነው።

## 2.2 በገጠር

የካፒታሊዝም ጠቅላይ ሠፈር ከተማ ቢሆንም በገጠርም ቢሆን አውታሮቹን መዘርጋቱ የማይቀር ነው፤ ጥሬ ሀብትና ያልሠለጠነው /በጫያ አንፃር/ የሰው ኃይል የሚፈልቅለት ከገጠር ወይም ከዳር አገር እንደሆነ የታወቀ ነው። ምንም እንኳን ካፒታሊዝም ዓይነተኛ የሀብቱ መሠረት አድርጉ የያዘው ኢንዱስትሪንና ንግዱን ቢሆንም፤ እርሻ ወይም ግብርና ከቁጥጥሩ ውጭ ነው ለማለት አይቻልም፤ እንዲያውም ከአነባቡም ቢሆን በአብዛኛው የመጀመሪያውን የጥሪት ክምችት ያገኘው ከግብርና ስለሆነና አሁንም ከዳበረ በኋላ ከዚህ መስክ ከፍተኛ ትርፍ የሚያጋብስ በመሆኑ ካፒታሊዝም በገጠር ተንሰራፍቶ ይገኛል። ዛሬ በዳበረት

ካፒታሊስት አገሮች ለምሳሌ እንደ አሜሪካ፣ እንግሊዝ፣ ምዕራብ ጀርመን... ባሉት የእርሻ ወይም የገጠር ካፒታል በጣም በተጠናከረ ሁኔታ ላይ ይገኛል።

ምንም እንኳን በካፒታሊስት አገሮች በገጠር የሚኖረውና በግብርና ተግባር ላይ የተሰማራው ሕዝብ ቁጥር ከጠቅላላው ውስጥ አነስተኛው ክፍል ቢሆንም፣ በካፒታሊዝም ጠበ ስውር ወይም ድብቅ የሥራ አጥ ሠራዊት ሕልውና አግኝቶአል። ከፍ ብሎ እንደ ተመለከተው ሥራ አጥነት ከካፒታሊዝም ባሕርይ የሚመነጭ እንደመሆኑ በገጠርም ለካፒታሊስቶች የሥራ ኃይላቸውን እየሸጡ ከሚኖሩ ከፊል ወዝአደሮች አልፎ አልፎ በካፒታሊስቶች በፋፊ እርሻ ላይ የሚሠሩ ግን አብዛኛውን ጊዜ በጥቃቅን ይዞታቸው ላይ በጓሮ አትክልት የሚኖሩ አሉ። ጠገባቸውን የማያውቀው ካፒታሊስት እነዚህን የገጠር አነስተኛ አምራቾች እያደቀቀና እያጻከመ ቢያቆረቁዛቸውና ይዞታውን ቢያስፋና ቢያበፋፋ አብዛኛው የገጠር ሕዝብ ቀስ በቀስ ወደ ከፊል ወዝአደርነት እየተለወጠ ይመጣል።

የእርሻ መሣሪያዎች ቀስ በቀስ በሣይንስና በቴክኖሎጂ አማካይነት እየተሻሻሉ ሲመጡ በካፒታሊስቶች እርሻዎች ላይ የሥራ ኃይላቸውን እየሸጡ በከፊል ወዝአደርነት የሚኖሩት ገበሬዎች የሥራ ዕድል ይመነምናል። ልክ በንግዱና በኢንዱስትሪው መስክ እንደሚደረገው ሁሉ በእርሻ ካፒታሊስቶችም መካከል ፉክክርና እርስ በርስ መባላት፣ ሳለመውደቅና በአሸናፊነት ለመውጣትና በሀብት ማጋበሱ ተግባር ለመቀጠል በዘመናዊ መሣሪያዎች መጠቀም የግድ ይሆናል። በዚህም በኩል ውጤቱ ተመሳሳይ ነው፣ የሥራ አጡ ሠራዊት ቁጥር የሸቀብ ዕድገቱን ይቀጥላል። እነዚህ የገጠር ሥራ አጦች አብዛኞቹ ከላይ እንደ ተመለከተው ለጓሮ አትክልት የሚያገለግሉ ጥቃቅን ይዞታዎች በላቸው የራሳቸው ሥራ ያላቸው ይመስላሉ

እንጂ በአጠቃላይ በከተማዎች ውስጥ ካሉት ሥራ አጦች ምንም አይሸሉም። የነዚህ ስውር ወይም ድብቅ ሥራ አጦች ቁጥር በመዝገብ በለማይሰፍርና በትክክል በለማይታወቅ ነው እንጂ በጣም ከፍተኛ ነው።

3. <u>የካፒታል ክምችት አጠቃላይ ሕግ</u>

ይህ የካፒታል ክምችት አጠቃላይ ሕግ የካፒታል ዕድገትና መዳበር ባንዱ ጫፍ የሀብትና የብልጽግና ተራራ ቢገነባ በሌላው ጫፍ ደግሞ የድኅነትና የሥቃይ አዘቅት እንደሚፈጥርና በዚህ ተፃራሪ ቅራኔ ካፒታሊዝም ወደግብአተ መሬቱ እንደሚሄድ የሚያሳይ ነው። ቡርዧው ጠገብኩ ማለትን በለማያውቅ ሽቀጥ እያመረተ ወዝአደሩ የሚፈጥረውን ተረፈ እሴት እያካበተ /ወደካፒታል እየለወጠ/ ሀብት ያከማቻል። በካፒታሊስቶች መካከል በሚካሄደው የማያቋርጥ ፉክክርና ትንንቅ ካፒታል ከጊዜ ወደጊዜ ይበልጥ እየተማከለ ይመጣና፣ ጥቂት ሞኖፖሊስቶች አብዛኛውን የኅብረተሰብ ሀብት በቁጥጥራቸው ውስጥ ያገቡታል። በዚህ ሂደት ውስጥ የቀረውና አብዛኛው የኅብረተሰብ ክፍል ወዝአደር ሲሆን፣ ባንዱ በኩል ብዝበዛውና ምዝበራው ሲጠፍ በሌላ በኩል ደግሞ የሥራ አጡ ሠራዊት ከዕለት ወደ ዕለት እየናረ ይሄዳል። በአጠቃላይ ባንዱ ጫፍ ማለትም በካፒታሊስቶች ሠፈር ሀብት፣ ብልጽግና፣ ምቾት፣ ድሎት ሲተርፍና ሲትረፈረፍ፣ በሌላው ጫፍ ማለት በወዝአደሩና በሠርቶአደሩ ሠፈር ሥቃይ፣ ድኅነት፣ ጉስቁልና፣ ሥራ አጥነት፣ ረሃብና ችግር ድን ኳናቸውን ይዘረጋሉ። ቀስ በቀስ ግን ያለጥርጥር ካፒታሊዝም ሊወጣ ከማይችልበት የቅራኔ አዘቅት ውስጥ ይዘፈቃል።

በልዩ ልዩ አጋጣሚና ጊዜያዊ ምክንያቶች ለየት ያለ መልክና አቀጣጫ ቢይዝም የዚህ ሕግ አንዳንድ ገጽታዎች ዛሬ በዳበሩት ካፒታሊስት አገሮች ውስጥ እያንፀባረቁ ነው። ጥቂቶቹን በስም ለመጥቀስ ያህል እነሮክፌለርን፣ እነፎርድን፣ እነ ሞርጋንን፣ እነ ክሮኘን፣ እነ ቶምሶንን፣ እነ ፔጅን የመሳሰሉ ሞኖፖሊስቶች አብዛኛውን ማኅበራዊ ሀብትበእጃቸው ውስጥ ሲያስገቡና በድሎት ዓለም ውስጥ ሲቀኙ የኅብረተሰቡ ትልቁ ክፍል ደግሞ ግማሹ በወዝአደርነት በእነዚህ ሲበዘበዝ ግማሹ ደግሞ ሥራ አጥ ሆኖ በፍርፋሪ ሕይወትን ይገፋል። ካርል ማርክስ ከመቶ

ዓመታት በፊት በጥልቀ ማይነማዊ ጥናትና ምርምር ለውን ያደረገው ይህ አጠቃላይ የካፒታል ክምችት ሕግ ከሁለት አንፃር መታየት ይኖርበታል።

### 3.1 አንፃራዊ የኑሮ ሁኔታ መቀርቀዝ፣

ስለ አንፃራዊ የኑሮ ሁኔታ መቀርቀዝ ስናወሳ ስለ ወዝአደሩ የኑሮ ሁኔታ መናገራችን ነው። ካፒታሊስቱ በሀብት እየደለበ ሲሄድ ወዝአደሩ ግን እየደኸየ ወደታች ማዝቀዘቀ ከቡርዧው የኑሮ ሁኔታ አንፃር የሚታይ ሲሆን በመሠረቱ ለተወሰነ ጊዜ ወይም ለአንድ የተለየ የወዝአደር ክፍል በመጠኑም ቢሆን ኑሮው ከራሱ ጋር/ቀድሞ ከነበረው/ ሲነፃፀር ሊሻሻል ይችላል፤ ወይም የተሻሻለ ሊመስል ይችላል። በአጠቃላይ የወዝአደሩ አንፃራዊ ድኅነት በማናቸውም ካፒታሊስት አገሮች ሊታይ የሚችል ነው።

ባንድ ካፒታሊስት የምርት ውጤት ውስጥ የምርት መገልገያዎች /ማምረቻ መሣሪያዎች የሥራ ተገብሮችና ሌሎች አስፈላጊዎች/ ድርሻ አለ፤ እንደዚሁም የሥራ ኀይል /ተለዋዋጭ ካፒታል/ድርሻም ይኖራል፤ ወደካፒታሊስቱ ኪስ የሚገባ ትረፊ እሴት አለ። ከእነዚህ ውስጥ የምርት መገልገያዎች ድርሻ ያለቀውን/አልቀት/ መተካት ሲሆን፤ የሥራ ኀይልና ትረፊ እሴት አዲስ የተፈጠሩ ወይም ገቢ መሆናቸው ነው። ይህ በኅብረተ ሰቡም ደረጃ የሚታይ ነው። ከፍ ብሎ በሌላ ሥፍራ እንደታየው የወዝአደሩ ምንዳ የሆነው ተለዋዋጭ ካፒታል በባይንበና ቴክኖሎጂ አማካይነት የማምረቻ መሣሪያዎች በመሻሻላቸው ቢቀንስ ወደ ካፒታሊስቱ ኪስ የሚገባው ትረፊ እሴት ግን ከፍ ከፍ እያለ ነው የሚሄደው። ከብሔራዊው ገቢ ውስጥ የወዝአደሩ ድርሻ ከቡርዧው ድርሻ አንፃር ሲገመገም ከጊዜ ወደ ጊዜ እያሽቆለቆለ በመሄድ ላይ ይገኛል። ለምሳሌ በታላቋ ብሪታኒያ እ.ኤ.አ. ከ1891* እስከ 1963 የወዝአደሩ ድርሻ ከ42.7 በመቶ ወደ 26

..../171

* Kozlov በላይ የተጠቀሰው መጽሐፍ፣ ገጽ 179

በመቶ ዝቅ ቢል፣ በአሜሪካ ደግሞ ከ1909 እስከ 1965 /እ.ኤ.አ./ ከ39.3 በመቶ ወደ 24.4 በመቶ አሽቆለቆለ። አሁንም በአሜሪካ ኮርፖሬሽኖች የተጣራ ትርፍ እ.ኤ.አ. ከ1960 እስከ 1968 በ91 በመቶ ቢያድግ፣ የኢንዱስትሪ ወዝአደሮች ምንዳ ግን በዚሁ ጊዜ በ11 በመቶ ብቻ ከፍ ብሏል።*

የወዝአደሩ አንፃራዊ ድኅነት ከብሔራዊው ሀብት ውስጥ ባለው ድርሻ ዝቅተኛነትም ይንፀባረቃል። ለምሳሌ በአሜሪካ ከሕዝቡ ውስጥ 3 በመቶ የሚሆኑት ጥቂት ካፒታሊስቶች ከብሔራዊው ሀብት 57 በመቶ የሚሆነውን በባለቤትነት ይዘውታል። በታላቋ ብሪታኒያ እንደዚሁ ከሕዝቡ ከ3 በመቶ የማይበልጡት ሀብታሞች ከአገሪቱ ጠቅላላ ሀብት ውስጥ 61 በመቶ የሚሆነው ባለቤት ናቸው። ይህንን የመሰለ ሁኔታ በሌሎችም ካፒታሊስት አገሮች ውስጥ የሚገኝ ነው። ከጊዜ ወደ ጊዜ ልዩነቱ እየሰፋ የካፒታሊስቶቹ ድርሻ እያደገ ለወዝአደሩ የሚከፈለው ወደታች እያሽቆለቆለ መሄዱ በግልጽ የሚታይ ነው።**

ይህ ሁኔታ ማለትም የወዝአደሩ አንፃራዊ ድኅነት በዛሬው ጊዜ በካፒታሊስቱ ዓለም ጎልቶ የሚታየውና አጠቃላይ ገጽታው ቢሆን፣ ቀስ በቀስ ግን እየተባባሰ የሚሄድ ነው። የቡርዧ መንግሥታትና መኖፖሎች እስከ ተወሰነና የትርፋቸው መጠን እስካልቀነሰ ድረስ ወዝአደሩ ወደ ፍፁም ድኅነት አዘቅት ውስጥ ተጠቃልሉ እንዳይወድቁና አንሰራፍተው የተቀመጡበትን ሥርዓት እንዳይገለባብጡ አንዳንድ ነገሮችን ለማድረግና ትንሽ ፍርፋሪ ለመወርወር ተገድደዋል።

## 3.2 የኑሮ ሁኔታ ፍፁም መቆርቆዝ

በካፒታል የክምችት ሕግ ባንድ ጫፍ የኅብረተሰቡ ሀብት ተከምሮ እፍኝ የማይሞሉት ቡርዧዎች ዓለማቸውን ሲቀጩ በሌላው ጫፍ ደግሞ የኅብረተሰቡ ከፍተኛ ቁጥር የምድር ፍዳውን ያያል። ከፍ ብሎ እንደተመለከተው

*Kozlov ከላይ የተጠቀሰው መጽሐፍ ገጽ 179

ይህ ሁኔታ ዛሬ የካፒታሊስቱ ዓለም ዓይነተኛ ገጽታ ነው በይባልም አንዳንድ ሁኔታዎች በመታየት ላይ መሆናቸው ግልጽ ነው። የማኅበራዊው ሀብት በጥቂቶች እጅ መከማቸትና የብዙኃኑን በሥቃይ አዘቅት ውስጥ መወርወር ለውነታ እየሆነ በሄደ ቁጥር የወዝአደሩ ድኅነት ከአንፃራዊ ወደ ፍፁምነት ማለፉ የማይቀር ነው። ዛሬ በአብዛኛው የወዝአደሩና የብዙኃኑ ሠርቶአደር ድኅነት ከዚህ በላይ ባለው ክፍል እንደ ተመለከተው አንፃራዊ ቢሆንም ፍፁማዊ ድኅነት የለም ማለት አይደለም።

ፍፁም ወይም ፍፁማዊ የወዝአደሩ ድኅነት በኋላ እንደሁኔታው የሚታይ መሆኑን መገንዘብ ያሻል፤ ይህ ዛሬ የካፒታሊስቱ ዓለም ዓይነተኛ ገጽታ አይደለም፤ ይሁንና አልፎ አልፎ እንደያንዳንዱ ካፒታሊስት አገር ልዩና ተጨባጭ ሁኔታ ሊኖር የሚችል ነው። ባንዳንድ አገሮች በእነዚህም ውስጥ ባንዳንድ ሥፍራዎች ወይም የሥራ መስኮች ሊኖር ይችላል። አንዳንድ የሥራ ሁኔታ እጅግ በጣም ከባድና ለጤና አደገኛ ሊሆን ይችላል፤ በዚህ መስክ ተሰማርተው የሚሠሩ ወዝአደሮች ጤና ቢስ ይሆናሉ፤ አካለ ጎደሎ ሊሆኑ ይችላሉ፤ ሕይወታቸው ባጭሩ ሊቀጭ ይችላል። ይህ ሁሉ መታየት ይኖርበታል።

በካፒታሊስት ሥርዓት ውስጥ የሥራ አጡ ሠራዊት ቁጥሩ የማይገመትና ከጊዜ ወደ ጊዜም እያደገ የሚሄድ መሆኑን ከፍ ብለን አይተናል። አብዛኛውን ጊዜያቸውን ያለ ሥራ የሚያባልፉት በፍፁም ድኅነት ደረጃ አይገኙም ማለት አይቻልም። አንዱ በሞን ሰየሠሩ ሌላውን ጊዜ ሥራ በመፈለግ የሚኖሩት፤ በቀን በርከት ያለ ሰዓት ሠርተው ራባቸውንና ቤተሰባቸውን ማስተዳደር ቢችሉ በቀን ወይም በሣምንት ጥቂት ሰዓቶች በመሥራት በሕይወትና በሞት ወይም ከሙታን በላይ ከሕያዋን በታች ሆነው የሚኖሩት በፍፁም ድኅነት አዘቅት ውስጥ የሚማስኑ ናቸው። በአጠቃላይ የካፒታሊስት ሥርዓት ዕድገት የሚተፋቸው በሙሉም ሆነ በከፊል ሥራ አጥ የሆኑ አካለ ስንኩላን፣ አረጋዊያንና በጡረታ ላይ የሚገኙ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው የኅብረተሰብ አካሎች በፍፁም ድኅነት ውስጥ የሚወድቁ ናቸው።

ባንዳንድ ኢምፔሪያሊስት አገሮች ለምሳሌ በአሜሪካ፣ በካናዳ፣ በስዊድን፣ በስዊዘርላንድና በመሳሰሉት በጦርነቱ ወቅት በተገኘው መልካም አጋጣሚ ንግዳቸውን በማስፋፋትና ከፍተኛ ትርፍ በማጋበስ ለወዝአደሩ ትንሽ ፍርፋሪ ለመጣል ችለው ነበር። ከጦርነቱም በኋላ የቀኝ ግዛቶችንና የታዳጊ አገሮችን የተፈጥሮ ሀብትና የሰው የሥራ ኃይል እየዘረፉና እየበዘበዙ ከሚያጋብሱት ከፍተኛ ትርፍ ለወዝአደሩ ትንሽ ፍርፋሪ ጣል በማድረጋቸው በአጠቃላይ በቀንደኛ የካፒታሊስት አገሮች የወዝአደሩ የኑሮ ሁኔታ ትንሽ የተሻሻለ ወይም የተጠበቀውን ያህል አቆልቍሎ ባይወርድ ቀርቷል። በእነዚህና በመሳሰሉት ጊዜያዊና አጋጣሚ ሁኔታዎች የወዝአደሩ ፍፁምና አንፃራዊ ድኅነት የተጠበቀውን ያህል ባይስፋፋም ከላይ እንደተመለከተው የተከሰተባቸው ብዙ አካባቢዎችና ገጽታዎች አሉ።

## 4. የካፒታሊስት ስልተምርት መሠረታዊ ቅራኔዎች

የካፒታሊስት ስልተ ምርት ከማናቸውም ቀድም ብለው ከተከሰቱት የመደብ ስልተምርቶች በው በተፈጥሮ ላይ የበላይነትን የበለጠ ያረጋገጠበት፣ የምርት ኃይሎች ከፍተኛ የዕድገት ደረጃ ላይ የደረሱበት፣ የሥራ ክፍፍልና የምርት ማኅበራዊነት እጅግ በጣም የላቀበት ነው። በዚህ ስልተምርት ባንድ በኩል ማኅበራዊ ምርት በጣም የዳበረና ብልጽግና የሰፈነ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ጥቂቶች የኅብረተሰቡን ሀብት በግል ተቆራምተው በምቾት ዓለም ውስጥ ሲኖሩ ብዙኃኑ የድካማቸውን ፍሬ ተነጥቀው የሥቃይና የችግር ፍዳ ያያሉ። ካፒታሊዝም የኅብረተሰቡ በሁለት ተፃራሪ መደቦች መከፈል በጉልህ የታየበትና በበዝባዦችና በተበዝባዦች መካከል የመደብ ትግሉ ከማናቸውም ጊዜ የበለጠ የተፋፋመበት ሥርዓት ነው። ምንም እንኳን የቡርዧ ሊቃውንት ካፒታሊዝምን እንደ ዘላለማዊና ከሰው ተፈጥሮ እንደሚመነጭ አድርገው በማቅረብ ለማሳመን ቢፈልጉም ይህ ስልተምርት ከርሱ በፊት እንደነበሩት እንደ ባሪያ አሳዳሪውና እንደ ፊውዳሊዝም መደምሰሱና በመቃብሩ ላይ ከብዝበዛና ከጭቆና ነፃ የሆነ ኅብረተሰብ መገንባቱ የማይቀር ባይንባዊ ሐቅ ነው። ዛሬ የዳበረ ሶሻሊዝም በመገንባት ላይ ያሉት እያሉ ታዳጊ አገሮች የዕድገት አቅጣጫቸውን ሶሻሊዝም

ማድረጋቸው በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ወዝአደሮችና ተራማጅ የኅብረተሰብ ክፍሎች ከፍተኛ መስዋዕትነት እየከፈሉ ለሶሻሊዝም የሚያደርጉት ትግል ይህንን ሐቅ የሚያረጋግጥ ነው።

## ፬.፩ ማኅበራዊ ምርትና የግል ሀብት

የካፒታሊስት በል ተምርት ዓይነተኛ ገጽታ በሳይንስና ቴክኖሎጂ አማካይነት የምርት ኃይሎች ከፍተኛ እድገት ማድረጋቸው፣ የሥራ ክፍፍል ከፍተኛ ደረጃ ላይ መድረሱ፣ በሺ፣ በአሥር ሺ፣ በመቶ ሺ የሚቆጠሩ ወዝአደሮች ባንድ ፋብሪካ ወይም የሥራ ድርጅት ውስጥ ተሰባስበው ለአንድ ወይም ለጥቂት ካፒታሊስቶች የሥራ ኃይላቸውን መሸጣቸው፣ የማምረቻና የማከፋፈያ መሣሪያዎች በጥቂት ቡርዧዎች እጅ ውስጥ መከማቸታቸው ወዘተ. ነው። በሌላ አባባል ባንድ በኩል የምርት ማኅበራዊነት ወደ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ሲደርስ በሌላ በኩል ደግሞ አብዛኛው ሕዝብ ሀብት አልባ እየሆነ በችግር ማጥ ውስጥ እየወደቀ አፍኝ የማይሞሉ ካፒታሊስቶች የኅብረተሰቡን ሀብት በግል ባለቤትነት ይዘው ዓለማቸውን ይቀጩበታል።

ካፒታሊዝም በታሪክ መድረክ ላይ ብቅ ለማለት የቻለው ብዙኃኑን የተበታተኑ አነስተኛ አምራቾች ከምርት መገልገያ ባለቤትነት በማስለቀቅና ቁጥራቸው አነስተኛ በሆነ የኅብረተሰብ ክፍሎች ቁጥጥር ሥር በማዋል እንደሆነ የታወቀ ነው። በዚህ ሂደት ውስጥ ባንድ በኩል ሁልጊዜ ቁጥራቸው እየቀነሰ የሚሄደው ጥቂቶች የኅብረተሰቡ አባላት የምርት መገልገያዎች ባለቤት በመሆናቸው የምርቱም ባለቤት ሲሆኑ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ቁጥራቸው ሁልጊዜ እያደገ የሚሄደው የኅብረተሰቡ አብዛኛው ክፍሎች ምንም ዓይነት የራሳቸው የማምረቻ መሣሪያ የሌላቸው ለጥቂቶች የምርት መገልገያ ባለቤቶች የሥራ ኃይላቸውን እየሸጡ እንዲኖሩ ተገደዱ። ዛሬ በቀንደኞቹ ካፒታሊስት አገሮች ውስጥ የሚታየው የጥቂት ሞኖፖሊስቶች የምርት መገልገያዎችን በቁጥጥራቸው ሥር ማዋልና የምርቱም

ባለቤት መሆን በአንፃሩ ደግሞ የብዙኃን ወደ ወዝአደርነት መለወጥ የዚሁ ከላይ የተጠቀሰዉ ሂደት ዉጤት ነው:: የበለጡ የምርት መገልገያዎችን በቁጥጥር ሥር በማዋል ከፍተኛ ሀብት ለማጋበስ በሞኖፖሊስቶች መካከል የሚደረገዉ ትንንቅ አሁንም ቢሆን እየተጧጧፈ ነው:: በዚህ ትንንቅ ዉስጥ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ከፍተኛ ሚና እየተጫወቱ ነው፣ ከዚህም የተነሣ ዛሬ እንደፎርድ፣ ጄኔራል ሞተርስ፣ አይ.ቢ.ኤም. ወዘተ... የመሳሰሉት ትልልቆቹ ሞኖፖሊስቶች ትርፋቸውን ለማሳደግ ለሳይንሳዊ ጥናትና ምርምር የሚያወጡት ገንዘብ እጅግ በጣም ከፍተኛ እንደሆነ ይገመታል::

ይህ የምርት መገልገያዎች በጥቂቶች መያዝ ምርት ወይም የማምረት ተግባር እንዲሰባሰብና የበለጠ ማኅበራዊ መልክ እንዲይዝ አድርጎታል:: በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ወዝአደሮች በትልልቀ የማምረቻ ድርጅቶች ዉስጥ ተሰብስበዉ በተንቀሳቃሽ ቀበቶች/ከንቬየር ቤልት/ አካባቢ አንዱ ወዝአደር አንድ ወይም አነስተኛ እንቅስቃሴ በማድረግ አንድ ነገር በማንባትና በማስቀመጥ /በመግጠም/ አንድ ተግባር ያከናዉናል:: ለምሳሌ ቀደም ባለዉ ጊዜ አንድ ጠረጴዛ፣አንድ ወንበር፣ አንድ ቁም ሣጥን ወዘተ... ባንድ ሰዉ፣ በሁለት ሰዎች ይሠራ ነበር:: በካፒታሊስት ሥርዓት የሥራ ክፍፍል እየሰፋና እያደገ በመምጣቱ ይህ በጥቂት ወዝአደሮች ይከናወን የነበረዉ ሥራ በብዙ ወዝአደሮች እንዲሠራ ስለተደረገ ምርቱ የብዙኃን የሥራ ዉጤት መሆኑ የማያጠያይቅ ነው:: በዚህ በኩል ከማናቸውም ጊዜ የበለጠ ጎልቶ የሚታየዉ የምርት ማኅበራዊነት ከከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሰ መሆኑ ነው::

ባጭሩ ካፒታሊዝም በዳበረባቸዉ አገሮች ሁለት ነገሮች ወይም ሁኔታዎች ጎልተው ይታያሉ፣ ባንድ በኩል የምርት ማኅበራዊ መሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ የምርት መገልገያዎችና የምርት በጥቂቶች በግል ባለቤትነት መያዝ ነው:: እነዚህ ሁለት ሁኔታዎች ፊት ለፊት የሚታዩና የሚጋጩ ናቸው::

የካፒታሊስት ስልተምርት እያደገ ሲመጣ በግልጽ የሚታየውና ሥርዓቱንም ወጥሮ የሚይዘው ይህ በምርት ማኅበራዊነትና በግል ባለቤትነት መካከል የሚከሰተው ቅራኔ ነው። ይህ ቅራኔ የቡርዧውን ሥርዓት ወደ መቃብሩ ከሚወስዱት መሠረታዊ ቅራኔዎች መካከል አንደኛው ነው። ቅራኔው መሠረታዊና ተፃራሪ በመሆኑ የሚፈታውም በትግልና በኃይል ማለትም በአመጽ ይሆናል። በዚህ አንፃር ዛሬ በግንባር ቀደም ካፒታሊስት አገሮች የሚገኘው ሁኔታ ይህ በምርት ማኅበራዊነትና በግል ባለቤትነት መካከል ያለው ቅራኔ ወደ ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሰ መሆኑን የሚያሳይ ሲሆን፣ ቅራኔው እንዳይፈነዳና ሥርዓቱን ወደ መቃብሩ እንዳያወርደው ሞኖፖሊስቶቹ ባላቸው ኃይልና ዘዴ ሁሉ በመጠቀም ጥቂት ለማቆየት እየተፍጨረጨሩ ነው። በተለይም ከታዳጊ አገሮች የሚያጋብሱት ከፍተኛ ትርፍ ለወዝአደሩ ፍርፋሪ በመጣልና በሌሎች ልዩ ልዩ ዘዴዎች የወዝአደሩን ትግል በማኮላሸት ሁኔታውን ለመቋቋም ከፍተኛ መፍጨርጨር እያደረጉ ነው። ጥረታቸው ቅራኔው እንዳይፈነዳ ትንሽ የማዘግየት ጉዳይ እንጂ ሌላ ውጤት ሊኖረው እንደማይችል በሳይንሳዊ ኮምዩኒዝም ንድፈ ሃሣብና በተግባርም የተረጋገጠ ነው።

## 4.2 ወዝአደርና ቡርዧ

ኅብረተሰብ በመደብ ከተከፋፈለባቸው ስልተምርቶች ውስጥ አንዱና ከፍተኛ የሆነው የካፒታሊስት ሥርዓት በውስጡ ሁለት መሠረታዊና ተፃራሪ መደቦችን አቅፎአል። የቡርዧው መደብ ከኅብረተሰቡ ውስጥ ጥቂቶቹን የያዘ ሲሆን፣ በአንፃሩ የወዝአደሩ መደብ የኅብረተሰብን አብዛኛውን ክፍል የሚያጠቃልል የብዙኃን መደብ ነው። የወዝአደሩ መደብ የሥራ ኃይሉን ለቡርዧው መደብ እየሸጠ የሚኖር ሲሆን፣ የቡርዧው መደብ የምርት መገልገያዎችና የምርት ባለቤት ነው። የቡርዧው መደብ ወዝአደሩ በሥራ ኃይሉ የሚፈጥረውን ተረፈ እሴት እየነጠቀ ሀብቱን እያደለበ በደቦታ

ዓለም ውስጥ ቢኖር የወዝአደሩ መደብ ግን ለመሥራት የሚያስችለውን ምንዳ ሳያገኝ በስቃይ ዓለም ውስጥ ይኖራል። የቡርዧው ሥርዓት መሠረት በሆነው በፋብሪካና በሀብት ማጋበስ የምርት መገልገያዎችና በአጠቃላይም የኅብረተሰቡ ሀብት በጥቂት ካፒታሊስቶች እጅ እየተከማቸ ስለሚሄድ የቡርዧው መደብ አባላት ቁጥር ከጊዜ ወደጊዜ እያነሰ ሲሄድ፣ የወዝአደሩ መደብ ደግሞ እየደኸየና እየወደቀ ከፋብሪካ ውጭ በሚሆኑት የቀድሞ አነስተኛ አምራች ካፒታሊስቶችና ከገበሬና ከትምህርት ቤት በሚመጡት ሠራተኞች ቁጥሩ ከዕለት ወደ ዕለት እየጨመረና እየበዛ ይሄዳል።

የማምረቻ መሣሪያዎች በአጠቃላይም የምርት ኃይሎች አመጣጥና ዕድገት ከሥራ እንቅስቃሴ ጋር የተያያዙ ናቸው፣ ምንጫቸውም ሥራ ነው። ስለሆነም እነዚህን በካፒታሊስት ሥርዓት የሚያባድጋቸውና የሚያዳብራቸው ወዝአደሩ ቢሆን በግል ይዞ የሚጠቀምባቸው ግን ቡርዧው ይሆናል። በመሠረቱ ወዝአደሩ ተንቀሳቃሽና ታዳጊ የሆኑትን የምርት ኃይሎች ሲወክል ቡርዧው ደግሞ የጐታችነት ሚና የሚጫወቱትን የምርት ግንኙነቶች ይወክላል። ስለሆነም በምርት ኃይሎችና በምርት ግንኙነቶች መካከል የሚከሰተው ቅራኔ በካፒታሊስት ስልተምርት በወዝአደሩና በቡርዧው መካከል በሚካሄደው ትግል ውስጥ ይንፀባረቃል። የምርት ኃይሎች የምርት ግንኙነቶችን በኀበለት በመበጣጠስ ወደአዲስና ከፍተኛ የኅብረተሰብ ዕድገት ማለትም ወደ ሶሻሊዝም ለመሸጋገር የሚቻለው ወዝአደሩ በቡርዧው መደብ ላይ በሚያካሂደው ውስብስብና ረጂም ትግል ድልን ሲጎናፀፍ ነው። ወዝአደሩ የቡርዧውን ሥርዓት ሲገረስስ የምርት ኃይሎች ታስረውበት የነበረውን የቡርዧ የምርት ግንኙነት በጣጥሰው አዲስና ተራማጅ የሆነ ብዝበዛንና ጭቆናን የሚያስወግድ አዲስ የሶሻሊስት የምርት ግንኙነት ይፈጥራል። ወዝአደሩ ይህንን ተልዕኮውን ሊወጣ የሚችለው በአዝማቹና ግንባር ቀደሙ በማሌ ፓርቲው እየተመራ ነው።

በወዝአደሩና በቡርዧው መካከል ያለው መሠረታዊና ተፃራሪ ቅራኔ በሌላ መልኩ ከዚህ በላይ ከፍ ብሎ የተመለከትነው በሥርተ ማኅበራዊነትና በግል ባለቤትነት መካከል ያለው ቅራኔ ነፀብራቅ ነው። በመሆኑም ወዝአደሩ የቡርዧውን ሥርዓት ሲደመስስና በሶሻሊዝም ሥርዓት ሲተካ የግል ባለቤትነትንም አብሮ በለሚደመስስ የምርት መገልገያዎችና ምርትም በአጠቃላይ የኅብረተሰቡ ይሆናሉ። በዚህም ከፍተኛው የዕድገት ደረጃ በሆነው በኮምዩኒዝም ሳይንስና ቴክኖሎጂ በቡርዧው የጣለባቸውን ገደብ በማስወገዱ ይበልጥ የምርት ኃይሎችም የተፋጠነ ዕድገት በማድረግ ምርት በመጠንና በዓይነት የሁሉንም ፍላጎት ለማርካት ከሚችልበት ሁኔታ ላይ ይደርሳል። ከዚህ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ለመድረስ ግን ከላይ እንደተመለከተው ረጂም መራራና ውስብስብ ትግል መካሄድ ይኖርበታል፤ ወዝአደሩ በዚህ የትግል ሂደት ውስጥ በንቃተ ሕሊናው ማደግና መዳበር በሙያና በፖለቲካ ማኅበር መደራጀት ይጠበቅበታል። በሳይንሳዊው ርዕዮተዓለም እየታጠቀ በረጂሙ ትግል የቡርዧውን ሥርዓት ገርስሶ ሶሻሊዝም ብሎም ኮምዩኒዝምን ይገነባል። //



## ጥ ያ ቄ ዎ ች

1. በቀላልና የተስፋፉ ርባታዎች መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት አብራርተህ ግለጽ ::

2. ቡርዧው ተረፈ እሴቱን ከየት ያገኛል? ተረፈ እሴቱን የሚያሳድግ ባቸውን ልዩ ልዩ ዘዴዎች ዘርዘር አድርገህ ተጨባጭ ምሳሌ በመስጠት አብራራ ::

3. ካፒታል እንዴት እንደሚከማችና እንደሚማከል በምሳሌ አስረዳ ::

4. የካፒታል ውስጣዊ ጥንቅር ምንድነው? ልዩ ልዩ ገጽታዎቹንና አሠራሩን አስረዳ ::

5. የሥራ አጡ ሠራዊት መንስኤ ምንድነው? ለምንድነው እያደገ የሚሄደው?

6. የካፒታሊስት የክምችት ሕግ ምንድነው? አብራራ ::

7. አንፃራዊ የኑሮ ቁር ቆዛን በተጨባጭ ምሳሌ አስረዳ ::

8. ፍፁም የኑሮ ቁር ቆዛ በምን በምን ሁኔታ ለየታየ ነው?

9. የካፒታሊስት ሥርዓት መሠረታዊና ዚራሪ ቅራኔዎች እንዴት እንደሚፈቱ አብራራ ::

## ቃ ላ ት

| | | |
|---|---|---|
| 1. | ክምችት | Accumulation |
| 2. | ቀላል ርባታ | Simple Reproduction |
| 3. | የተስፋፋ ርባታ | Extended Reproduction |
| 4. | የካፒታል ውስጣዊ ጥንቅር | Organic Composition of Capital |
| 5. | የካፒታል ቴክኒካዊ ጥንቅር | Technical Composition of Capital |
| 6. | የካፒታል እሴታዊ ጥንቅር | Value Composition of Capital |
| 7. | የካፒታል መሰባሰብ | Concentration of Capital |
| 8. | የካፒታል ምክለት | Centralization of Capital |
| 9. | ማኅበራዊ የሥራ ምርታማነት | Social Productivity of Labour |
| 10. | የኢንዱስትሪ የሥራ አጥ ሠራዊት | Industrial Reserve Army |
| 11. | ተንሳፋፊ የሥራ አጥ ሠራዊት | Floating Surplus Population |
| 12. | ስውር የሥራ አጥ ሠራዊት | Lattent Surplus Population |
| 13. | ዝቃጭ የሥራ አጥ ሠራዊት | Stagnant Surplus Population |
| 14. | የካፒታል ክምችት አጠቃላይ ሕግ | The General Law of Capitalist Accumulation |
| 15. | አንጻራዊ የኑሮ ሁኔታ መቆርቆዝ | Relative Impoverishment |
| 16. | ፍጹም የኑሮ ሁኔታ መቆርቆዝ | Absolute Impoverishment |
| 17. | ማኅበራዊ ምርት | Social Production |
| 18. | ጥምርታ | Ratio |
| 19. | ሀብት | Wealth |
| 20. | ገቢ | Income |
| 21. | ብሔራዊ ሀብት | National Wealth |
| 22. | ብሔራዊ ገቢ | National Income |

## ምዕራፍ 6

# የካፒታልና የተረፈ እሴት ልዩ ልዩ መልኮች፣ የማኅበራዊ ካፒታል ርባታና የኢኮኖሚ ቀውሶች

## 1. የካፒታልና የተረፈ እሴት ልዩ ልዩ መልኮች

በካፒታሊስቱ ሥርዓት ውስጥ ወዝአደሩ የፈጠረውን ተረፈ እሴት በመካከላቸው የሚከፋፈሉ የቡርዧው መደብ ዋና ዋና ክፍሎች የሚከተሉት ናቸው። የሥርዓቱ መሠረታዊ በዝባዥ መደብ ካፒታሊስቱ እንደሆነ የታወቀ ነው። የካፒታሊስት መደብ በሦስት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላል። እነዚህም 1ኛ/ የኢንዱስትሪ ካፒታሊስት ክፍል፣ የኢንዱስትሪ ካፒታሊስት ተግባር ወዝአደሩ ተረፈ እሴት እንዲፈጥር ማድረግ ነው። 2ኛ/ የንግድ ካፒታሊስት ክፍል፣ የንግድ ካፒታሊስት ተግባር የተመረተውን ሸቀጥ ወደ ገንዘብ መለወጥ ነው። 3ኛ/ የብድር ካፒታሊስት ክፍል፣ የብድር ካፒታሊስት ተግባር ደግሞ ካፒታል በገንዘብ መልክ እንዲከማችና ገንዘብ የሚያስፈልጋቸው የኢንዱስትሪና የንግድ ካፒታሊስቶች ብድር እንዲያገኙ ማድረግ ነው። 4ኛ/ የሰፋፊ መሬት ባለቤቶች፣ ባለትላልቅ መሬቶች ከምርት መገልገያዎች አንዱ ዋና የሆነውን መሬትን በግል ባለቤትነት የያዙ በመሆናቸው በካፒታሊስቱ ኅብረተሰብ መሬትን በማከራየትና በልዩ ልዩ የኢኮኖሚ ዘርፎች በመሳተፍ ወዝአደሩ ከሚፈጥረው ተረፈ እሴት /በተለይም ከእርሻው ክፍል ካሉ ወዝአደሮች/ ይካፈላሉ። ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት አንድ ሌላ የካፒታሊስት ክፍል ለመጥቀስ ይቻላል። ይህም የእርሻ ካፒታሊስት ነው። ነገር ግን የእርሻ ካፒታሊስት ከኢንዱስትሪ ካፒታሊስቱ ጋር የጠበቀ ተመሳሳይነት ያለው በመሆኑ እሱን እንደ አንድ ልዩ የካፒታሊስት ክፍል መቁጠር አስፈላጊ አይሆንም። እነዚህ ልዩ ልዩ የካፒታሊስት ክፍሎች ወዝአደሩ የፈጠረውን ተረፈ እሴት በመካከላቸው ይከፋፈላሉ።

ስለዚህ በካፒታሊስት ሥርዓት ውስጥ ወዝአደሩ የሚፈጥረውን እሴት በመካከላቸው የሚከፋፈሉ ዋና ዋና የበዝባዥ ክፍሎች የኢንዱስትሪ ካፒታሊስቶች፣ የንግድ ካፒታሊስቶች፣ የብድር ካፒታሊስቶችና የሰፋፊ መሬት ባለቤቶች ናቸው። የኢንዱስትሪ ካፒታሊስቶች የኢንዱስትሪ ትርፍ፣ የንግድ ካፒታሊስቶች የንግድ ትርፍ፣ እንዲሁም የብድር ካፒታሊስቶች የብድር ወለድ ያገኛሉ። ባለ ሰፋፊ የመሬት ባለቤቶች ደግሞ የመሬት ክራይ ያገኛሉ።

የካፒታሊስቶች በልዩ ልዩ ክፍሎች ማለት በኢንዱስትሪ ካፒታሊስቶች፣ በንግድ ካፒታሊስቶችና በብድር ካፒታሊስቶች መከፋፈልና በካፒታሊስት ሥርዓት ውስጥ የባለ ትላልቅ መሬት ባለቤቶች መኖር በመካከላቸው ከፍተኛ ውድድር እንዲካሄድ ያደርጋል። በእነዚህ የበዝባዥ ወገን ልዩ ልዩ ክፍሎች መካከል የዚህ ዓይነቱ ውድድር የሚካሄውም እያንዳንዱ የበዝባዥ ክፍል ወዝአደሩ ከፈጠረው ተረፈ እሴት የሚያገኘውን ድርሻ ለማሳደግ የሚጥር በመሆኑ ነው። ይህም ፉክክር በበዝባዥ ወገኖች መካከል ቅራኔ አሚያስከትል ቢሆንም፣ ቅራኔው ግን ተፃራሪ አይደለም።

## 1.1. የኢንዱስትሪ ካፒታልና የኢንዱስትሪ አማካይ ትርፍ

ተረፈ እሴት የሚፈጠረው በኢንዱስትሪ መስክ ቢሆን ፈጣሪውም ወዝአደሩ መሆኑን በሌላ ሥፍራ ተመልክተናል። ኢንዱስትሪ የቁሳዊ ሀብት ማምረት ተግባር ቢሆን በካፒታሊስት ስልተምርት ፋብሪካን፣ ኮንስትራክሽንን /ሕንፀት፣ ግንበት.../ ማዕድንን፣ እርሻን /ሰፋፊ ዘመናዊ እርሻ/ ወዘተ... ያጠቃልላል። በእነዚህ የኢንዱስትሪ ልዩ ልዩ መስኮች የምርት መገልገያዎች /የማምረቻ መሣሪያዎች፣ የምርት ተገብሮች፣ ኃይል.../ ከወዝአደሩ የሥራ ኃይል ጋር ተቀናጅተው የተለያዩ የሰው ፍላጎቶችን የሚያሟሉ ልዩ ልዩ ሸቀጦች ይመረታሉ።

በአጠቃላይ ተረፈ እሴት የሚፈጠረው በዚህ በኢንዱስትሪ ዘርፍ ቢሆን፣ ከላይ የተጠቀሱ ልዩ ልዩ የካፒታሊስት ክፍሎች በመካከላቸው ይከፋፈሉታል። የኢንዱስትሪ ካፒታሊስቱ ለመሬት ካፒታሊስቱ የመሬት ኪራይ፣ ለተዛዋር ካፒታሊስቱ ወለድ፣ ይከፍልና የራሱን ትርፍ አንስቶ ለንግድ ካፒታሊስቱ ድርሻውን ያስተላልፍለታል። የንግድ ካፒታሊስቱም እንደ ኢንዱስትሪ ካፒታሊስቱ የመሬት ኪራይና ወለድ ከከፈለ በኋላ ትርፉን ይወስዳል። ይሁን እንጂ ይህንን በልዩ ልዩ የካፒታሊስት ክፍሎች መካከል የሚከናወነውን የተረፈ እሴት ክፍፍል ከንዋኔ በዝርዝር ከማየታችን በፊት የተረፈ እሴትንና የትርፍን መጠኖች የለውጥ አዝማሚያ እንመልከት።

<u>የትርፍ መጣኝ፣</u> የተረፈ እሴት ብቸኛ ምንጩ ወዝአደሩ እንደመሆኑ በአንድ የምርት ሂደት ውስጥ የሚፈጠረው የተረፈ እሴት መጠን የሚታሰበው ከሚከፈል ምንዳ ጋር በማነፃፀር ነው። ሆኖም ምንምእንኳ የተረፈ እሴት ብቸኛ ምንጩ ወዝአደሩ ቢሆንም፣ ካፒታሊስቱ ትርፉን የሚያሰበው በአጠቃላይ ካወጣው ወጪ ጋር በማነፃፀር ነው። ለምሳሌ ካፒታሊስቱ በአንድ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ለቋሚ ካፒታል 1000 ብር፣ እንዲሁም ለተለዋዋጭ ካፒታል/ለሠራተኞች ምንዳ/ 125 ብር አወጣ እንበል፣ ካፒታሊስቱ ከማምረቻ ድርጅቱ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ያገኘው ትርፍ 250 ብር ቢሆን፣ ካፒታሊስቱ ይህንን ትርፉን የሚያሰበው በአጠቃላይ ለቋሚ ካፒታልና ለምንዳ ካወጣው ወጭ ማለት ከ1125 ብር ጋር በማነፃፀር ይሆናል ማለት ነው። ካፒታሊስቱ ያገኘውን ትርፍ ለቋሚ ካፒታልና ለምንዳ ክፍያ በአጠቃላይ ካወጣው ወጭ ጋር ከመቶ አኳ በማነፃፀር የሚገኘው መጠን የትርፍ መጣኝ ይባላል። ከዚህ በላይ በተጠቀሰው ምሳሌ መሠረት ካፒታሊስቱ ለማምረቻ ድርጅቱ በአጠቃላይ 1125 ብር ቢያወጣና ያገኘው ትርፍ 250 ብር ቢሆን፣ የትርፍ መጣኙ $= \frac{250}{1125} \times 100 = 22.2\%$ ይሆናል ማለት ነው። የትርፍ መጣኝ አንድ ካፒታሊስት የማምረቻ ድርጅቱን ትርፋማነት ለመለካት የሚገለገልበት ነው።

ካፒታሊስቱ የትርፉን መጠኑ በዚህ ዓይነት መንገድ የሚያሰላው በአንድ በኩል የወዝአደሩን የተረፈ እሴት ፈጣሪነት ለመካድ ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ ትርፉን ዝቅ አድርጎ ለማሳየት ነው። ይሁንና የተረፈ እሴት ፈጣሪ ወዝአደሩ መሆኑን በሌላ ሥፍራ የተመለከትን በመሆኑ እዚህ ላይ አንመለስበትም። ሆኖም በዚህ ምሳሌ ትክክለኛው የትርፍ መጠኑ 22.2% ሳይሆን $\frac{250}{125} \times 100 = 200\%$ ይሆናል። ይህ ነው የተደበቀውን መጠኑ የሚያመለክተው።

የትርፍን መጠኑ የሚወስኑ ሁኔታዎች በርካታ ሲሆኑ ዋና ዋናዎቹን ከዚህ በታች እንመለከታቸዋለን። ከእነዚህ የትርፍን መጠን ከሚወስኑት ዋና ነገሮች ውስጥ አንደኛውና ዋነኛው የተረፈ እሴት መጠኑ ነው። የተረፈ እሴት መጠኑ ምን እንደሆነና እንዴትስ እንደሚሰላ ቀደም ብሎ የተብራራ በመሆኑ በትርፍ መጠኑ ላይ የሚያደርገውን ተጽእኖ በምሳሌ እናስረዳለን። ለምሳሌ አንድ ካፒታሊስት ባንድ በተወሰነ ወቅት /6 ወር፣ አንድ ዓመት.../ ለተለዋዋጭ ካፒታል/ምንዳ/ 1250 ብር ቢያወጣና ወዝአደሮቹን 1250 ብር ተረፈ እሴት ቢያስፈጥራቸው የተረፈ እሴት መጠኑ $\frac{1250}{1250} \times 100 = 100\%$ ይሆናል። አሁን ቀደም ሲል በጠቀስነው ምሳሌ መሠረት የትርፉን መጠን ብናሰላ $\frac{125}{1125} \times 100 = 11.1$ በመቶ ይሆናል።

በተመሳሳይ መልክ ወዛደሮቹ የፈጠሩት ተረፈ እሴት መጠኑ 300% ቢሆን በካፒታሊስቱ ስሌት መሠረት የትርፉ መጠኑ $\frac{375}{1125} \times 100 = 33.3$ በመቶ ይሆናል። በአጠቃላይ ከዚህ ምሳሌ የምንገነዘበው ካፒታሊስቱ የተረፈ እሴትን መፈጠር ለመሰወር የሚጥር ቢሆንም የተረፈ እሴቱ መጠኑ ከፍተኛ ቢሆን፣ በካፒታሊስቱም ስሌት መሠረት የትርፉ መጠኑ ከፍተኛ እንደሚሆንና የተረፈ እሴቱ መጠኑ ዝቅተኛ ቢሆን፣ ደግሞ የትርፉም መጠኑ በአንፃሩ ዝቅ ያለ እንደሚሆን ነው።

የትርፍ መጠኑን የሚወስነው ሁለተኛው ነገር ውስጣዊ የካፒታል ጥንቅር ነው። ስለሆነ ውስጣዊ የካፒታል ጥንቅር ማለት ምን ማለት ነው? ይህ ነጥብ ቀደም ሲል የተጠቀሰ ቢሆንም ነገሩን የበለጠ ለመረዳት የሚከተለውን ምሳሌ እን መልከት። ሁለት ተመሳሳይ ምርት የሚያመርቱ ካፒታሊስቶችን በምሳሌነት እንውሰድ። አንደኛው ካፒታሊስት በዘመናዊ መሣሪያዎች የተደራጀ የወርቃ ወርቀ ፋብሪካ አቋቋመ። ሁለተኛው ካፒታሊስት ያንኑ ዓይነት ምርት የሚያመርት በአመዛኙ በሠራተኛ ኃይል በመተማመን የወርቃ ወረቀ ፋብሪካ አቋቋመ። በመጀመሪያው ፋብሪካ የተቀጠሩት ሠራተኞች ሃምሣ ሰዎች ብቻ ሲሆን፣ ሁለተኛው ፋብሪካ ግን 100 ሠራተኞች ቀጠረ። የመጀመሪያው ፋብሪካ ባለቤት የሆነው ካፒታሊስት ባንድ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ለቋሚ ካፒታል 900,000 ብር፣ እንዲሁም ለተለዋዋጭ ካፒታል/ለሠራተኞች ምንዳ ክፍያ/ 200,000 አወጣ እንበል። በዚያው ጊዜ ውስጥ ሁለተኛው የወርቃ ወርቀ ፋብሪካ ያቋቋመው ካፒታሊስት ለቋሚ ካፒታል 600,000 ብር፣ ለተለዋዋጭ ካፒታል 400,000 ብር አወጣ እንበል። በዚህ አኳኋን የመጀመሪያውን ፋብሪካ ያቋቋመው ካፒታሊስት ሁለተኛውን ፋብሪካ ካቋቋመው ካፒታሊስት ጋር ሲነፃፀር ለቋሚ ካፒታል ያወጣው ወጪ ከፍ ያለና ለተለዋዋጭ ካፒታል ያወጣው ወጪ ዝቅ ያለ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል። ውስጣዊ የካፒታል ጥንቅር የምንለውም ለቋሚ ካፒታል፣ ማለት ለማምረቻ መሣሪያዎች ለጥሬ ዕቃና ለመሳሰሉት የዋለውንና ለተለዋዋጭ ካፒታል፣ ማለት ለሥራ ኃይል መግዣ/ለምንዳ የዋለውን ለማመዛዘን የምንገለገልበት ጽንሰሃሣብ ነው። ብዙ ሠራተኞች በሚቀጥሩና፣ ለማሽኖች፣ ለጥሬ ዕቃና ለመሳሰሉት የሚወጣው ወጪ አነስተኛ በሆነበት የማምረቻ ድርጅቶች ውስጣዊ የካፒታል ጥንቅር ዝቅተኛ ነው። በአንፃሩ ደግሞ አብዛኛው የማምረቻ ተግባር እጅግ በዳበሩ መሣሪያዎች የሚንቀሳቀስና እጅግ ውድ የሆኑ ጥሬ ዕቃዎች የሚያስፈልጉት ሲሆን፣ እንዲሁም ለቋሚ ካፒታል ከሚወጣው ወጪ ጋር ሲነፃፀር ለሥራ ኃይል መግዣ /ለምንዳ/ የሚወጣው ወጪ አነስተኛ ቢሆን፣ የማምረቻ ድርጅቶች ውስጣዊ ጥንቅር ከፍተኛ ይሆናል።

ከዚህ በላይ በተሰጠው ምሳሌ መሠረት የአንደኛው ፋብሪካ ውስጣዊ የካፒታል ጥንቅር፣ ለቋሚ ካፒታል የወጣውን 900,000 ብር ለተለዋዋጭ ካፒታል በወጣው

200,000 ብር በማካፈል የሚገኘው ቁጥር 4.5 ነው። ይህም ማለት በዚህ ፋብሪካ ውስጥ ለሚፈጠረው ለያንዳንዱ ሥራ 4.5 የሆነ ካፒታል ያስፈልጋል ማለት ነው። በለሆነም 4.5:1 የሁለተኛው ፋብሪካ ውስጣዊ የካፒታል ጥንቅር ደግሞ ለቋሚ ካፒታል የወጣው 600,000 ብር ተለዋዋጭ ካፒታል በወጣው 400,000 ብር ሲካፈል የሚገኘው ቁጥር 1.5 ነው። ስለዚህ በምሳሌያችን መሠረት የመጀመሪያው ፋብሪካ ውስጣዊ የካፒታል ጥንቅር ከሁለተኛው ፋብሪካ ውስጣዊ የካፒታል ጥንቅር ከፍ ያለ ነው። የዚህ ውስጣዊ ካፒታል ጥንቅር ልዩነት በትርፍ መጣኔ ላይ የሚያስከትለው ውጤት ምንድነው?

በአንድ የካፒታሊስት የማምረቻ ድርጅት ውስጥ የሚገኘው ውስጣዊ የካፒታል ጥንቅር ከፍተኛ ቢሆን፣ ከካፒታሉ ውስጥ ለተለዋዋጭ ካፒታል፣ ወይንም ለሥራ ኃይል መግዣ የዋለው ክፍል አነስተኛ ነው ማለት ነው። ስለዚህ ተረፈ እሴትን የሚፈጥረው ወዝአደሩ በመሆኑ የሚገኘው የትርፍ መጣኔ አነስተኛ ይሆናል ማለት ነው። በአንፃሩ ደግሞ ውስጣዊ የካፒታል ጥንቅር አነስተኛ ከሆነ ለተለዋዋጭ ካፒታል የወጣው የካፒታል መጠን ከፍተኛ ነው ማለት ነው። ስለዚህም የሚገኘው የትርፍ መጣኔ ከፍተኛ ይሆናል። በአጠቃላይ ውስጣዊ የካፒታል ጥንቅር አነስተኛ ቢሆን የትርፍ መጣኔ ከፍተኛ ይሆናል። ለዚህ ምክንያቱ የተረፈ እሴት፣ ብሎም የትርፍ ብቸኛ ምንጩ የወዝአደሩ የሥራ ኃይል መሆኑ ነው።

በአንድ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ካፒታል የሚገለበጥበት ፍጥነት/ዙር ኦቨር/ ሌላው የትርፍ መጣኔን የሚወስነው ሁኔታ ነው። ለምሳሌ አንድ የማምረቻ ድርጅት በአንድ ዓመት ውስጥ የአንድ መቶ ብር ካፒታል አንድ ጊዜ ቢያገላብጥ ወይንም አንድ ጊዜ በማምረት ተግባር ላይ ቢያውል የሚያገኘው ተረፈ እሴት 20 ብር ነው እንበል። ይኸው ካፒታሊስት ያንኑ መቶ ብር በዓመት ሁለት ጊዜ ቢያገላብጠው ወይንም ሁለት ጊዜ በሥራ ላይ ቢያውልና በእያንዳንዱ ጊዜ መጠኑ 20 ብር የሆነ ተረፈ እሴት እንዲፈጠርለት ቢያደርግ በዓመቱ ውስጥ የሚያገኘው የተረፈ እሴት 40 ብር ይሆናል

ማለት ነው። ስለሆነም የካፒታል መገላበጥ ፍጥነት ከፍ ሲል /ቶሎ ቶሎ ሲገላበጥ/ ተረፈ እሴት በዚያው መጠን ያድጋል ወይንም ከፍ ይላል። በአንፃሩ የማገላበጡ ፍጥነት ዝግ ያለ ሲሆን ተረፈ እሴቱ አነስተኛ ወይም ዝቅተኛ ይሆናል።

<u>የትርፍ መጣኔ መስተካከል፣</u> አንድ የካፒታሊስት ማምረቻ ድርጅት የሚያገኘውን የትርፍ መጣኔ ሊወስኑ የሚችሉትን ልዩ ልዩ ነገሮች ከዚህ በላይ ተመለከትን። በአንዱ የማምረቻ ድርጅት ውስጥ ሊገኝ የሚችለው የትርፍ መጣኔ በሌላ የማምረቻ ድርጅት ውስጥ ሊገኝ ከሚችለው የትርፍ መጣኔ የመለያየት አዝማሚያ እንዲኖረው የሚያደርገው የእነዚሁ ከዚህ በላይ የዘረዘሩት ነገሮች ጥንቅር ነው። ሆኖም አንድ ዓይነት ሸቀጥ በሚያመርቱ ድርጅቶች መካከልም ሆነ ልዩ ልዩ ሸቀጣ ሸቀጦችን በሚያመርቱ ድርጅቶች መካከል የሚታይ የትርፍ መጣኔ ልዩነት፣ በተለይ ነፃ "ውድድር" በሰፈነበት የካፒታሊስት ሥርዓት ውስጥ፣ ለረጅም ጊዜ ሊኖር አይችልም። የዚህም ምክንያት ካፒታሊስቶች ትርፍን ለማሳደግ አርስ በርሳቸው የሚያደርጉት ውድድር ነው።

ይህ በካፒታሊስት ሥርዓት ውስጥ አማካይ የትርፍ መጣኔ እንዲሰፍን የሚያደርገው በካፒታሊስቶች መካከል የሚካሄደው ውድድር ሁለት ዓይነት ነው። አንደኛው ተመሳሳይ ሸቀጥ በሚያመርቱ ካፒታሊስቶች መካከል የሚካሄደው ትንቅንቅ ነው። አንድ ዓይነት ሸቀጥ በሚያመርቱ ካፒታሊስቶች መካከል ከፊሉ ከሌሎቹ ጋር ሲነፃፀሩ በአነስተኛ ወጪ ሊያመርቱ ይችላሉ። ይህም የሚሆንበት ምክንያት መጠናቸው እያንዳንዱን ሸቀጥ በአነስተኛ ወጪ ለማምረት የሚያስችለው ሲሆን፣ ወይንም የተሻሻለ የማምረቻ መሣሪያ በምርት ተግባር ላይ ቢያውሉ ወይንም የሥራ አደረጃጀታቸው የተሻሻለ ሲሆን ነው። እነዚህ ጥቂት ካፒታሊስቶች በአነስተኛ ወጪ ሊያመርቱ ቢችሉም የሸቀጡ ዋጋ በገበያ ውስጥ የሚወሰነው ያንን ሸቀጥ በሚያመርቱ ካፒታሊስቶች አማካይ የማምረት ሁኔታ ነው። በለዚህ በአነስተኛ ወጪ የሚያመርቱት ካፒታሊስቶች ለተወሰነ ጊዜ ተጨማሪ ትርፍ ሊያገኙ ይችሉ፣ ሆኖም "ነፃ ውድድር" ባለበት ሁኔታ ይህ ለብዙ ጊዜ ሊቀጥል አይችልም።

ሌሎች ካፒታሊስቶችም ከጊዜ በኋላ የተሻሻሉትን የማምረቻ መሣሪያዎችን በሥራ ላይ ወይም በምርት ተግባር ላይ ያውላሉ፤ አደረጃጀታቸውን ያሻሽላሉ። በዚህ አኳኋን ሌሎቹ ካፒታሊስቶች ሸቀጡን ለማምረት የሚያወጡት ወጪ እንዲቀንስ ያደርጋሉ። የሸቀጡ የገበያ ዋጋ የሚወሰነው ሸቀጡን በሚያመርቱ ካፒታሊስቶች አማካይ የማምረት ሁኔታ በመሆኑ የሸቀጡ የገበያ ዋጋ ዝቅ ይልና አንዳንድ ካፒታሊስቶች ተጨማሪ ትርፍ ማግኘታቸው ለጊዜው ያከትማል። በዚህ አኳኋን ተመሳሳይ ሸቀጥ በሚያመርቱ ካፒታሊስቶች መካከል የነበረው የትርፍ መጠኑ ልዩነት ጠፍቶ አማካይ የትርፍ መጠኑ ለተወሰነ ጊዜ ይሰፍናል። ይሁንና ውድድሩ የማያቋርጥ ስለሆነ እንደገና አንዳንዶቹ ወይም ጥቂቶቹ ከፍ ብለው በተጠቀሱት ምክንያቶች ተጨማሪ ትርፍ ማግኘት ይጀምራሉ። እንደገና ውድድሩ ይፋፋማል፤ እንደገናም አማካይ ትርፍ ይመሠረታል፤ በዚህ አኳኋን ሂደቱ ይደጋገማል።

በካፒታሊስቱ ሥርዓት ውስጥ አማካይ የትርፍ መጠኑ እንዲሰፍን የሚያደርገው ሁለተኛው ምክንያት ልዩ ልዩ ሸቀጦችን በሚያመርቱ ካፒታሊስቶች መካከል የትርፍ መጠኑ የተለያየ ከሆነ ትርፋቸው አነስተኛ የሆነው ካፒታሊስቶች ካፒታላቸውን በማዛወር ከፍተኛ ትርፍ የሚያስገኘውን ሸቀጥ ማምረት ስለሚጀምሩ ነው። ከፍተኛ ትርፍ ያስገኝ የነበረው ሸቀጥ አሁን በብዛት በመመረቱ የገበያ አቅርቦቱ በመጨመሩ የሚያወጣው ዋጋ ዝቅ ይላል። ፊት አነስተኛ የትርፍ መጠኑ የሚያስገኙት ሸቀጦች ደግሞ አሁን በአነስተኛ መጠን የሚመረቱና የገበያ ፍላጎታቸው ከፍ የሚል ስለሆነ ዋጋቸው ከፍ ይላል። በዚህ አኳኋን ልዩ ልዩ ሸቀጦችን በሚያመርቱ ካፒታሊስቶች መካከል ይታይ የነበረው የትርፍ መጠኑ ልዩነት ይወገድና በልዩ ልዩ የኢኮኖሚ መስኮች ለተወሰነ ጊዜ አማካይ የትርፍ መጠኑ ይሰፍናል። ይህ ሁኔታ ጊዜያዊ እንጂ ዘላቂ ስላልሆነ ሂደቱ እንደገና ይጀምርና ተጨማሪ ትርፍ ማሳደዱ፤ ከዚህ ደግሞ እንደገና አማካይ ትርፍ፤ እንደገና ተጨማሪ ትርፍ እያለ ይቀጥላል።

ሆኖም ካፒታሊዝም ወደ ኢምፔሪያሊዝም ደረጃ በተሸጋገረበት ወቅት በኢኮኖሚው በአጠቃላይ አንድ አማካይ የሆነ የትርፍ መጠኑ እንዲሰፍን ማድረግ አስቸጋሪ ይሆናል።

ምክንያቱም ሞኖፖሊዎች የኢኮኖሚ ጥንካሬያቸውን በመጠቀም የገበያ ዋጋዎችን በመቆጣጠር በካፒታሊስቶች መካከል "ነፃ ውድድር" እንዳይኖር ስለሚያደርጉ ነው። ሞኖፖሊስቶች የሚያመርቷቸው ሸቀጦች ከሌሎቹ ጋር ሲነፃፀሩ ከፍተኛ ትርፍ የሚያስገኙትን እነዚህን ሸቀጦች ወደ ማምረት አዛውረው ከሞኖፖሊስቶች ጋር ለመወዳደርና ከፍተኛ ትርፍ ለመካፈል መለስተኛዎቹና አነስተኛዎቹ ካፒታሊስቶች የኢኮኖሚ አቅም ያንሳቸዋል። ስለዚህ በሞኖፖል ካፒታሊዝም ውስጥ ሊኖር የሚችለው አማካይ የትርፍ መጣኔ በሁለት ልዩ ልዩ ደረጃዎች ነው። አንዱ ከፍተኛ የሆነ አማካይ የትርፍ መጣኔ ለሞኖፖሊስቶች ሲኖር፤ ሌላ የትርፍ መጣኔ በዝቅተኛ ደረጃ ሞኖፖሊስቶች ባልተሰማሩባቸውና ቁጥራቸው በርካታ የሆነና ትንንሽ አምራቾች በሚያካሂዷቸው የኢኮኖሚ መስኮች ይኖራል::

<u>የትርፍ መጣኔ እየቀነሰ የመሄድ አዝማሚያ ማሳየት፤</u> በካፒታሊስቱ ሥርዓት ውስጥ አማካይ የትርፍ መጣኔ እየቀነሰ የመሄድ አዝማሚያ ያሳያል፤ ለዚህ ብዙ ምክንያቶች አሉ:: አንደኛው ምክንያት ቴክኖሎጂ እየዳበረ ቢሄድ የማምረቻ ድርጅቶች ውስጣዊ የካፒታል ጥንቅር እያደገ መምጣቱ ነው:: ቴክኖሎጂ እየዳበረ ቢሄድ እንደ ማምረቻ መሣሪያዎችና ጥሬ ዕቃ ለመባበሉት የሚወጣው ከፍተኛ ዕድገትን እያሳየ፤ ለተለዋዋጭ ካፒታል ማለትም ለሠራተኞች ምንዳ የሚደረግ ወጪ ለቋሚ ካፒታል ከሚደረግ ወጪ ጋር ሲነፃፀር በአነስተኛ መጠን እያደገ ይሄዳል:: የተረፈ እሴትና ከዚያም ተያይዞ የትርፍ ምንጩ ካፒታሊስቱ የሚገዛው የሥራ ኃይል በመሆኑ ለተለዋዋጭ ካፒታል የሚውለው ወጪ ለቋሚ ካፒታል ከሚውለው ጋር ሲነፃፀር አነስተኛ እስከሆነ ድረስ የትርፍ መጣኔ የመቀነስ አዝማሚያ ያሳያል፤ በዚህ መሠረት ባለፈው አንድ ምዕተ ዓመት አጠቃላይ የትርፍ መጣኔ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ መምጣቱን በተጨባጭ ማረጋገጥ ይቻላል:: ለምሳሌ በእንግሊዝ አገር በ19ኛው ምዕተ ዓመት ከ20 – 22%ይደርስ የነበረው አማካይ የትርፍ መጣኔ ዛሬ በአማካይ ወደ 10 – 14% ዝቅ ብሎ ይገኛል:: የሌሎችንም ካፒታሊስት አገሮች የትርፍ መጣኔ ሁኔታ ብንመረምር ይህንኑ አዝማሚያ የሚያረጋግጥ ሆኖ እናገኘዋለን::

ሆኖም አማካይ የትርፍ መጣኔ የማሽቆልቆል አዝማሚያን ያሳያል ማለት ፍፁማዊ የሆነው ጠቅላላ የትርፍ መጣኔ/የትርፍ እክብ/ ያሽቆለቁላል ማለት አለመሆኑን መገንዘብ ተገቢ ነው:: ምክንያቱም ጠቅላላ የትርፍ መጠን የሚወሰነው በትርፍ መጣኔ ብቻ ሣይሆን

ካፒታሊስቱ ለምርት ተግባር በሚያውለው ካፒታል መጠንም ጭምር በመሆኑ ነው።
ካፒታሊዝም እየተስፋፋ ቢሄድ ካፒታሊስቶች ለማምረት ተግባር የሚያውሉት ካፒ
ታል እያደገ ይሄዳል። ምንም እንኳ ቋሚ ካፒታል በሚያድግበት መጠን ባይሆ
ንም ተለዋዋጭ ካፒታልም የተወሰነ ዕድገት ያሳያል። ስለዚህ የትርፍ መጣኔ
እየቀነሰ ቢሄድ ፍጹማዊ የትርፍ መጠን እያደገ ሊሄድ ይችላል። ለምሳሌ
አንድ ካፒታሊስት የመቶ ብር ካፒታል በሥራ ላይ አውሎ ትርፉ ከመቶ እጅ
ሰላሣ ቢሆን፣ ወይንም የትርፍ መጣኔ 30% ቢሆን የሚያገኘው ፍጹማዊ የት
ርፍ መጠን ወይም አክብ ሰላሣ ብር ይሆናል። በሚቀጥለው ዓመት ካፒታሊስቱ
በሥራ ላይ ያዋለው ካፒታል ወደ ሁለት መቶ ብር ከፍ ቢል ያገኘው የትርፍ
አክብ ከ30 ብር ወደ 40 ብር ከፍ አለ። በዚህ መልክ ከካፒታሉ እድገት
አንጻር የትርፉ አክብ ዕድገት ቢያሳይም የትርፉ መጣኔ ግን ከ30% ወደ
20% መቀነሱን መገንዘብ ይቻላል።

በተጨማሪም አማካይ የትርፍ መጣኔ የመቀነስ አዝማሚያ ያለው መሆኑን
በመገንዘብ ካፒታሊስቶቹ ይህንኑ አዝማሚያ ለመቋቋም ከሚጠቀሙባቸው ዋና ዋና
ዘዴዎች መካከል አንዳንዶቹ የሚከተሉት ናቸው። ኢምፔሪያሊስት አገሮች ካፒ
ታላቸውን ወደ ውጪ በመላክ የኋላ ቀር አገሮችን የሥራ ኃይልና ጥሬ ሸቀጥ
በመበዝበዝ ሸቀጦችን በገፍ በመላክ በውጭ ንግድና በሌሎች የኢኮኖሚ ግንኙነ
ቶች አማካይነት የሚያጋብሱት ከፍተኛ ትርፍ ካፒታሊስቶች የሚያገኙት አጠቃላይ
ትርፍ መጠን እንዲያድግ የሚያደርጉበት ዋነኛ ዘዴ ነው። በሌላ በኩል ሞኖፖሊ
ስቶች በሸቀጦች ዋጋ ላይ ባላቸው የወሳኝነት ሚና በቁጥጥራቸው ሥር ባሉ የኢ
ኮኖሚ መስኮች የትርፍን መጣኔ የመቀነስ አዝማሚያ ለመቀነስ ያስችላቸዋል።
በዚ፡ መሠረት የሥራ ኃይል ዋጋ ከኑሮ ውድነት ጋር እንዳያድግ ማድረግ፣ የሥራ
ኃይል ምርታማነት የማምረቻ መሣሪያዎችን/የቋሚ ካፒታል/ ወጪን ለመቀነስ በሚያ
በገኘው ትርፍ በመጠቀምና እንዲሁም የቴክኖሎጂ ዕድገት በዓለም ገበያ ውስጥ
ልዩ ትርፍ ማግኘት የትርፍ መጣኔን የመቀነስ አዝማሚያ ለመቋቋም ከሚጠቀሙባቸው
ዘዴዎች ጥቂቶቹ ናቸው። ሆኖም ካፒታሊስቶች ይህን አዝማሚያ ለመቋቋምና ትርፋቸውን

ሽፍ ለማድረግ በሚያደርጉት ጥረት የወዝአደሩን ብዝበዛ በማባባሳቸው በወዝ አደሩና በቡርዧው መካከል ያለው ቅራኔ እየተካረረ ይሄዳል። በካፒታሊስቱ ሥርዓት ውስጥ የሚታየውን የትርፍ መጣኔ የመቀነስ አዝማሚያ ለመቋቋም ካፒ ታሊስቶች በሚያደርጉት መሯሯጥ ምክንያት በሥርዓቱ ውስጥ የሚገኙ ቅራኔዎች መካረርም የሚያመለክተው የካፒታሊስት ስልተ ምርት ዘለዓለማዊነት የሌለውና በአንድ ወቅት የሚከስም መሆኑን ነው።

## 1.2/ <u>የንግድ ካፒታልና የንግድ አማካይ ትርፍ፡</u>

የንግድ ካፒታል በቀደመ ካፒታሊስት የኢኮኖሚ ሥርዓቶች ውስጥ ዝቅተኛ ደረጃ የነበረና ለካፒታሊስቱ ሥልተ ምርት እድገት አስተዋጽኦ ያደረገ ነው። ሆኖም የካፒታሊስቱ ሥርዓት ዓይነተኛ ገጽታ የንግድ ካፒታል ሣይሆን የኢንዱ ስትሪ ካፒታል ነው።

ተረፈ እሴት የሚፈጠረው በማምረት ሂደት ውስጥ በተሰማሩ ወዝአደሮች በመሆኑ ተረፈ እሴትን በመጀመሪያ ደረጃ የሚወስደው የማምረቻ ድርጅቱ ባለቤት የሆነው የኢንዱስትሪ ካፒታሊስቱ ነው። እንደ ንግድ ካፒታሊስቱ ያሉ ሌሎች በካፒታሊስቱ ሥርዓት ውስጥ የሚገኙ የበዝባዥ መደብ ክፍሎች ድርሻቸውን ከተ ፈጠረው ተረፈ እሴት የሚወስዱት ከኢንዱስትሪ ካፒታሊስቱ ነው።

የንግድ ካፒታሊስቱ ተግባር የኢንዱስትሪ ካፒታሊስቱ ያመረተውን ሸቀጥ መሸጥ ነው። ባለኢንዱስትሪው የተመረተውን ሸቀጥ ራሱ ለመሸጥ ቢሞክር ለሽያጭ ተግባር ተጨማሪ ካፒታል ማዋል ይኖርበታል። ሱቆች ማቋቋምና ማካሄድ፣ ሸቀጡን ለማስተዋወቂያና ለሌሎችም ተግባራት ወጪ ማውጣት ይኖርበታል። ስለዚህ የሽያጩንም ተግባር እራሱ ካካሄደው አንድ የተወሰነ የካፒታል መጠን ያለው ካፒታሊስት

የሚያመርተውን ሸቀጥ መጠን መቀነስ ይኖርበታል፣ ወይም ያመረተውን ሸቀጥ በሚሸጥበት ወቀት ሸቀጡን የማምረቱን ተግባር ማቋረጥ ይኖርበታል። ይህ ደግሞ የሚያገኘውን ትርፍ እንዲቀንስ ሲያደርግ ይችላል። ስለዚህ ባለ ኢንዱስትሪ ካፒታሊስቱ የሽያጩን ተግባር ለንግድ ካፒታሊስቱ በማስተላለፍ በካፒታሊስቱ ልዩ ልዩ ክፍሎች መካከል የሥራ ክፍፍል ተደርጎ የማምረቱና የማከፋፈሉ ተግባር ይከናወናል። ይሄም ለትርፍ ማደግ አስተዋጽኦ ያደርጋል።

ባለኢንዱስትሪ ካፒታሊስቶች ያመረቱትን ሸቀጥ ለንግድ ካፒታሊስቶች የሚሸጡበት ዋጋ ለሸማቶች ከሚሸጡበት ዋጋ ዝቅ ያለ ነው። የንግድ ካፒታሊስቶች ሸቀጡን በሸጡ ጊዜ ሽያጩን ለማካሄድ ላወጡት ካፒታል አማካይ ትርፍ ያገኛሉ። የንግድ ካፒታሊስቱ የሚያገኘው የንግድ ትርፍ መጣኔ በኢኮኖሚው ውስጥ ከሚገኘው አማካይ የትርፍ መጣኔ በታች አይሆንም፣ ይህ የሆነ እንደሆነ ነጋዴው ካፒታሉን ከንግዱ መስክ አውጥቶ ሸቀጦችን ወደ ማምረቱ መስክ ስለሚያዛውረው አማካይ ትርፉ እንደገና ስለሚሰፍን የኢንዱስትሪ ካፒታሊስቱም የንግድ ካፒታሊስቱም የሚያገኙት የትርፍ መጣኔ አማካይ ይሆናል። ይህ ማለት የኢንዱስትሪ ካፒታሊስቶችና የንግድ ካፒታሊስቶች የሚያገኙት ጠቅላላ የትርፍ መጠን እኩል ነው ማለት ግን አይደለም። በአብዛኛው ባለኢንዱስትሪ ካፒታሊስቱ ከንግድ ካፒታሊስቱ ይልቅ መጠኑ ከፍተኛ የሆነ ካፒታል በሥራ ላይ ስለሚያውል የሚያገኘውም ትርፍ መጠን በዚያው ልክ ከፍተኛ ይሆናል። ይሁንና ሁለቱም በሥራ ላይ በሚያውሉት የካፒታል መጠን፣ ባለኢንዱስትሪ ካፒታሊስቱና የንግድ ካፒታሊስቱ ተመጣጣኝ ትርፍ ያገኛሉ ማለት ነው። የሚሰፍነው የትርፍ መጣኔ ግን በአጠቃላይ አማካይ ይሆናል።

የባለ ኢንዱስትሪ ካፒታሊስቱ ትርፍም ሆነ የንግድ ካፒታሊስቱ ትርፍ ምንጩ በምርት ሂደት ውስጥ የሚፈጠረው ትረፊ እሴት በመሆኑ በማምረቻ ድርጅቶች

ውስጥ የሚደረግ የሠራተኛ ብዝበዛ መባባስ የሚጠቀመው የኢንዱስትሪ ካፒታሊስቶችን ብቻ ሣይሆን የንግዱ ካፒታሊስቶችንም ጭምር ነው፡፡ የባለኢንዱስትሪው ካፒታሊስትና የንግዱ ካፒታሊስት የመደብ አንድነት ያላቸው እንደመሆኑ የሕልውናቸው መሠረት የወዛደሩ የሥራ ኃይል ብዝበዛ ነው፡፡

በንግዱ መስክ ትርፍ እሴት አይፈጠርም፤ ይሁንና፣ ሸቀጦች በማምረቻ ድርጅቶች ውስጥ በሚመረቱበትና ለሸማቾች በሚቀርቡበት መካከል ባለው ጊዜ ውስጥ ባንዳንዱ መስክ አንዳንድ ከማምረት ተግባር ጋር ግንኙነት ያላቸው ሥራዎች ይከናወናሉ፡፡ በማምረቻ ድርጅቶች ውስጥ የተመረቱትን ሸቀጦች እንደ ማሸግ፣ በመጋዘን ውስጥ እንደማኖርና ከተመረቱበት ቦታ ሸማቾች ወደሚገኙበት ቦታ እንደማጓጓዝ ያሉ ተግባራት ሸቀጦችን ከማምረት ጋር በቀጥታ የተያያዙ ተግባራት ናቸው፡፡ አንድ ሸቀጥ በጥቅም ላይ ለመዋል የሚችለው ለሸማቹ ወይንም በሸቀጡ ለሚገለገለው ሰው ለመቀረብ ሲችል በመሆኑ እነዚህና የመሳሰሉት ተግባራት ከማምረት ጋር የተወሳሰቡ ናቸው፡፡ ስለዚህም ለማሸግ በመጋዘን ውስጥ ለማኖር፣ ለማጓጓዝና ለመሳሰሉት ተግባራት የዋለ ሥራ በማምረቻ ድርጅቶች ውስጥ በተመረቱት ሸቀጦች ትርፍ እሴት ላይ ተጨማሪ እሴት እንዲታከልባቸው ያደርጋል፡፡ ይሁንና ተጨማሪ የጠቀሜታ እሴት ግን አይፈጥርም፡፡

ሆኖም በካፒታሊስቱ ሥርዓት አንድ ሸቀጥ ከተመረተበት ድርጅት ወጥቶ ለሸማቹ እስከቀረበበት ጊዜ የሚወጣው ወጪ ከፍተኛና ያለማቋረጥ ዕድገትን የሚያሳይ ነው፡፡ የዚህ ዓይነቱ ወጪም በአብዛኛው ምርታማ ሣይሆን በሸማቾች ውስጥ አስፈላጊ ያልሆነ ፍላጎት ለመፍጠር በማለት እንደሚወጣ ለምሳሌ ሸቀጡን ለማስተዋወቂያ እንደሚደረግ ወጪ ያለ ከሸቀጡ ግዢ ጋር በቀጥታ የተያያዘ ወጪ ነው፡፡ ምርታማ ያልሆነ ወጪ የሸቀጡ የገበያ ዋጋ እንዲያድግ ስለሚያደርግ
የመግዛት ችሎታ ዝቅ ያደርገዋል፡፡
የኅብረተሰቡን

የካፒታሊስት ንግድ ልዩ ቅርጾች አሉት። ሁለቱ ዋና ዋና ቅርጾች የአገር ውስጥ ንግድና የውጭ ንግድ ናቸው። የአገር ውስጥ ንግድ እንደገና በሁለት ይከፈላል። የጅምላና የችርቻሮ። የጅምላ ንግድ የሚካሄደው በባለኢንዱስትሪ ካፒታሊስቱና በንግድ ካፒታሊስቱ መካከል ነው። ሸቀጦችን ለሸማቾች በቀጥታ የመሸጡ ተግባር ደግሞ የችርቻሮ ንግድ ይባላል። ካፒታሊስቶች በውጭ ንግድ አማካይነት ሸቀጦችን ለውጭ ገበያዎች አቅርበው በመሸጥ ትርፋቸውን ያባዙጋሉ። ለኢምፔሪያሊስት አገሮች ካፒታሊስቶች በተለይ ከፍተኛ ትርፍ የሚያስገኝላቸው ከኋላ ቀር አገሮች ጋር ያላቸው የንግድ ግንኙነት ነው። ምክንያቱም እነዚህ ካፒታሊስቶች የፋብሪካዎች ውጤቶች የሆኑ ሸቀጦችን ለኋላ ቀር አገሮች ሕዝቦች በውድ ዋጋ ስለሚሸጡና በአንጻሩ ደግሞ እነዚሁ ሕዝቦች የሚያመርቷቸውን ጥሬ እቃዎች በርካሽ ዋጋ ስለሚገዙ ነው።

የንግድ ካፒታል ሲነሳ በንግዱ ዘርፍ ተቀጥረው የሚሠሩ ሠራተኞች ሁኔታም መጠቀስ ይገባዋል። እንደሚታወቀው በሽያጭ ተግባር የተሰማሩ ቀጥር ሠራተኞች አዲስ እሴትን አይፈጥሩም። በለዚህ የሚሠሩት ሥራ ትረፍ እሴትን አይፈጥርም። ሆኖም የንግድ ካፒታሊስት አይበዘብዛቸውም ማለት አይደለም። ሸቀጡን በመሸጥ ተግባር የተሰማሩ ሠራተኞች የአንድ ቀን የሥራ ጊዜ ለሁለት ይከፈላል፦ አስፈላጊ የሥራ ጊዜና ትርፍ የሥራ ጊዜ። በአስፈላጊ የሥራ ጊዜ የሚሸጡት ምንዳቸውን ያስገኛል። በትርፍ የሥራ ጊዜ የሚሸጡት ደግሞ የነጋዴውን ትርፍ ያስገኛል። ስለዚህ በለሙ የካፒታሊስት አገሮች ውስጥ ያሉ ነጋዴዎች ከሚበዘብዟቸው መካከል፣ በማምረት ተግባር የተሰማሩ ወዝአደሮችን፣ በሽያጭ ተግባር የተሰማሩ ሠራተኞችን፣ የሸቀጦችን ዋጋ በማናር ሸማቾችንና በአጠቃላይ የኋላ ቀር አገሮች ሕዝቦችን መጥቀስ ይቻላል።

## 1.3 የብድር ካፒታልና ወለድ፣

ገንዘብን በወለድ ማበደር በባሪያ አሣዳሪውና በፊውዳሉ ሥርዓቶች ማኅበሮችም ውስጥ ነበረ። የሸቀጥ ልውውጥ ባቆጠቆጠበት በማንኛውም ኅብረተሰብ

ውስጥ ባለገንዘቦች ገንዘብ በለሳቸው ላይ ኃይል ባኖራቸው ቆይ ቷል፡፡ የብድር ገንዘብ በመጀመሪያ ደረጃ ይዞት የነበረው ቅርጽ የአራጣ ብድር ቅርጽ ነው፡፡ አራጣ አበዳሪዎች ከፍተኛ ወለድ በማስከፈል በፊውን ሕዝብ በዝብዘዋል፡፡ ኢን ዱስትሪና ንግዱ እየተስፋፋ ቢሄድ ግን ባንኮች አራጣ አበዳሪዎችን እየተኳቸው ሊሄዱ ችለዋል፡፡

በአገራችንም ቢሆን አራጣ አበዳሪዎች በፊውን ሕዝብ ለረጅም ዘመናት በከፍተኛ ወለድ አማካኝነት ሲበዘብዙት ቆይተዋል፡ አሁንም የእነዚህ ርዝራዥ ችና ቀሪቶች በየሥርቻውና በየጓራንጉሩ እየተሸሎከሎኩ ብዝበዛቸውን በመቀጠል ላይ መሆናቸው የታወቀ ቢሆንም ከባንኮች አገልግሎት መስፋፋት ጋር እየከሰሙ መሄዳቸው አማይቀር ነው፡፡/

በካፒታሊስት ሥርዓት ማኅበር ባለገንዘብ ካፒታሊስቶች ለጊዜው በሥራ የማያውሉትን ገንዘብ ለኢንዱስትሪ ካፒታሊስቶችና ለንግድ ካፒታሊስቶች በማበደር ትርፍ ያገኙበታል፡፡ የብድር ካፒታል ዋና ምንጭ የሚሆኑትም የኢንዱስትሪ ካፒታል ስቶችና የንግድ ካፒታሊስቶች ናቸው፡፡ አንዳንድ ካፒታሊስቶች ለጊዜው ሥራ ላይ የማያውሉት ገንዘብ ይኖራቸዋል፡፡ ለምሳሌ አንድ የኢንዱስትሪ ካፒታሊስት ያመረ ተውን ሸቀጥ ለንግድ ካፒታሊስቱ የሚሸጠው በየወሩ ቢሆንና ለማምረት ተግባር የሚያውለውን ጥሬ እቃ ግን የሚገዛው በስድስት ወራት አንድ ጊዜ ቢሆን ለአም ስት ወራት ያህል ለጊዜው በሥራ ላይ ያልዋለ ገንዘብ ሊያጠራቅም ይችላል፡፡ ሌሎች ካፒታሊስቶች ደግሞ በአንድ በተወሰነ ወቅት ብድር ሊያስፈልጋቸው ይች ላል፡፡ ለምሳሌ ያመረቱትን ሸቀጥ ሸጠው ባያበቁ ጥሬ እቃዎችን መግዛት ይኖ ርባቸዋል፡፡ ወይንም አዲስ ማምረቻ መሣሪያ ለመግዛት ይሹ ይሆናል፡፡ በዚህ ዓይነት በአንዱ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ አንዳንዶቹ ካፒታሊስቶች ለጊዜው በሥራ

ላይ የሚያውሉት ገንዘብ ሲኖራቸው ሌሎች ካፒታሊስቶች ደግሞ ገንዘብ ለመበደር ይፈልጋሉ። ለጊዜው የማይገለገልበት ገንዘብ ያለው ካፒታሊስት እንደማንኛውም ካፒታሊስት ገንዘቡ ትርፍ እንዲያስገኝለት የሚጥር በመሆኑ ገንዘቡን በባንክ ያስቀምጣል። ባንኮች ከተለያዩ ካፒታሊስቶች በዚህ ዓይነት የሰበሰቡትን ገንዘብ ብድር ለሚፈልጉ ካፒታሊስቶች ለተወሰነ ጊዜ በወለድ ያበድራሉ። ስለዚህ የብድር ካፒታል የምንለው ወለድ እንዲያስገኝ ለተወሰነ ጊዜ ለብድር የተሰጠ የገንዘብ ካፒታል ነው።

ካፒታሊስቱ የተበደረውን ገንዘብ በምርት ተግባር ወይንም በንግድ መስክ በማዋል ሠራተኞችን ይበዘብዛል። ያገኘውንም ትርፍ ከብድር ካፒታሊስቱ ጋር በመካፈል ለብድር ካፒታሊስቱ ወለድ ይከፍላል። ስለዚህ የብድር ካፒታሊስቱ ከማንኛውም የካፒታሊስት ክፍል ይልቅ ከምርት ተግባር የተራራቀ ነው። የብድር ካፒታሊስት ጥገኝነት/ደም መጣጭነት/ ከማንኛውም የካፒታሊስት ክፍል የባሰ ነው የሚባለውም ለዚሁ ነው።

በካፒታሊስቱ ሥርዓት ውስጥ፣ ባንኮች ለጊዜው በሥራ ላይ ያልዋለ ገንዘብ ከካፒታሊስቶች በመሰብሰብ ገንዘብ ለሚፈልጉ ለሌሎች ካፒታሊስቶችና ለቡርዧው መንግሥት በማበደር የፋናንስ ማዕከልነትን ሚና ይጫወታሉ። ባንኮች በካፒታሊስቱ ሥርዓት ሥራቸውን የሚያካሂዱት ለትርፍ ነው። የትርፋቸውም ዋና ምንጭ ገንዘብ አበድረው በሚያስከፍሉት ወለድ እና ሰዎች በባንኩ ውስጥ ገንዘብ ሲያስቀምጡ በሚከፈላቸው ወለድ መካከል ያለው ልዩነት ነው። በካፒታሊስቱ ሥርዓት ባንኮች በተጨማሪም በፋብሪካዎችና በንግድ ድርጅቶች ውስጥ ገንዘባቸውን በቀጥታ በሥራ ላይ በማዋል ባለ አክሲዮን ወይም ባለ ድርሻ በመሆን ትርፍ ያገኛሉ።

በብዙ ካፒታል አማካይነት የካፒታል ባለቤትነትና የካፒታል በሥራ ላይ ማዋል እንዲለያዩ መደረጉ የአክስዮን ማኅበር ኩባንያዎች እንዲቋቋሙ ረድቷል። በካፒታሊስቱ ሥርዓት ውስጥ የምርት መጠን እያደገ ቢሄድ እያንዳንዱ ካፒታሊስት ያለው የካፒታል መጠን ሥራን ለማንቀሳቀስ በቂ ሆኖ ሊያገኘው አልቻለም። ስለዚህ በኢንዱስትሪ፣ በመገናኛ፣ በባንክና በሌሎችም መስኮች የአክስዮን ማኅበር ኩባንያ ዎችን ማቋቋም ተጀመረ። አክሲዮን ማኅበር የሚባለው ካፒታሊስቶች በማኅበሩ ውስጥ በሥራ ላይ ባዋሉት ካፒታል መጠን የማኅበሩን ባለቤትነትና ትርፍ በመካከላቸው የሚ ከፋፈሉበት ዘዴ ነው። እያንዳንዱ የማኅበሩ አባል የተወሰኑ የአክሲዮን ቁጥሮች ባለቤት ነው። አክሲዮን ማለት አንድ ሰው የተወሰነ ገንዘብ በአንድ ድርጅት ውስጥ በሥራ ላይ እንዲውል ያደረገ መሆኑን የሚያረጋግጥበት ሰነድ ነው። የአክሲዮን ባለ ቤት የሆነ አንድ ሰው ኩባንያው ከሚያገኘው ትርፍ የመካፈል መብት አለው። ምንም እንኳ የባለ አክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ በኩባንያው እንቅስቃሴ ላይ ሥልጣን አለው ቢባልም፣ እያንዳንዱ ባለአክሲዮን በአጠቃላይ ስብሰባው ላይ የሚኖረው ድምጽ መጠን የሚወሰነው ባሉት አክሲዮኖች ቁጥር ነው። ስለዚህ የአክሲዮን ማኅበር ኩባንያዎች በጥቂት ትላልቅ ባለአክሲዮኖች ቁጥጥር ሥር ይውላሉ። በአክሲዮን ማኅበር ኩባንያ ዎችም አማካኝነት ትላልቅ ካፒታሊስቶች ትንንሽና መካከለኛ ካፒታሊስቶችን፣ እንዲ ሁም ገንዘብ ለማጠራቀም የሚችሉ የፋብሪካና የቢሮ ሠራተኞችን ገንዘብ ለጥቅማቸው ማዳበሪያ ይገለገሉበታል።

የአክሲዮን ማኅበር ኩባንያዎች መስፋፋት ካፒታሊስቶች በወለድ ላይ ያላ ቸውን ጥገኝነት በበለጠ ቢያጠናክረው የማምረቻ ድርጅቶች አስተዳደር ደግሞ ደመወ ዝተኞች በሆኑ ማኔጀሮችና ዲሬክተሮች በበለጠ እንዲካሄድ ሊያደርግ ችሏል። በዚህ አኳኋን የካፒታሊስት ባለቤትነት ጥገኝነት በበለጠ ግልጽ እየሆነ ሊመጣ ችሏል።

1.4. በካፒታሊስት ሥርዓት ውስጥ የመሬት ኪራይ፡፡

በካፒታሊስቱ ሥርዓት ውስጥ የወዝአደሩን የስራ ኃይል በመበዝበዝ ከሚገኘ ላቀቀት ካፒታሊስቶች መካከል አንዱ ክፍል ትላልቅ ባለመሬቶች ናቸው። በካፒታሊስቱ ሥርዓት ውስጥ በእርሻው መስክ ያሉ የምርት ግንኙነቶች በፊውዳሊስቱ ሥርዓት ውስጥ ከሚገኙት የተለዩ ናቸው። በፊውዳሉ ሥርዓት ውስጥ የሚገኙት መሠረታዊ የሆኑት የምርት ግንኙነቶች በፊውዳል ባለመሬቶችና በገባሮች መካከል ያሉት የምርት ግንኙነቶች ናቸው።

በካፒታሊስቱ ሥርዓት ውስጥ ባለመሬቱ ራሱ በአብዛኛው በእርሻ ተግባር አይሰማራም። በእርሻ ተግባር ላይ ገንዘቡን ለማዋል ለፈለገ ካፒታሊስት መሬቱን ያከራየዋል። ካፒታሊስቱ የእርሻ ሠራተኞችን ቀጥሮ በማሠራት ተረፈ እሴት እንዲፈጠር ያደርጋል። በዚህ አኳኋን የተፈጠረውን ተረፈ እሴት ካፒታሊስቱ ለሁለት ይከፍለዋል። አንደኛውን ክፍል ትርፉ በማድረግ ለራሱ ያስቀረዋል። ሌላውን ክፍል በመሬት ኪራይ ስም ለባለመሬቱ ያስተላልፋል። ካፒታሊስቱ ባለመሬትም ከሆነ የመሬት ኪራይ መክፈል ስለሚቀርለት የተፈጠረው ተረፈ እሴት በአጠቃላይ ለራሱ ይገባለታል።

በካፒታሊስቱ ሥርዓት ባለመሬቶች የሚያገኙት የመሬት ኪራይ ሁለት ዓይነት ነው። እነዚህም የልዩነት ኪራይ እና ፍጹማዊ ኪራይ ይባላሉ። የልዩነት ኪራይ ለማግኘት የሚያስችሉ ምክንያቶች ሦስት ናቸው። እነዚህም የተለያዩ ማሣዎች በአፈር ለምነት መበላለጥ፣ ማሣዎች ከመገበያያ ቦታዎች ያላቸው ርቀት መለያየት እና ካፒታሊስቶች የማሣዎችን ምርታማነት ለማሳደግ የሚያደርጓቸው ወጪዎች ናቸው። እነዚህን ምክንያቶች ከዚህ በታች ለማብራራት ይሞከራል።

የተለያዩ ማሣያች በአፈር ለምነት መበላለጥ የልዩነት ኪራይ ለማስገኘት
የሚችለው እንደሚከተለው ነው:: በኢንዱስትሪ መስክ የሸቀጥ ዋጋ የሚወሰነው ልዩ
ልዩ ካፒታሊስቶች ያንን ሰቀጥ በሚያመርቱበት አማካይ ሁኔታ መሆኑ ይታወቃል::
በአርሻ መስክ ግን ይህ አይሠራም:: ምክንያቱም የአርሻ ምርት የገበያ ዋጋ የሚ
ወስነው ጠፍነት ከሁሉም ማሣያች የበለጠ የሚያጠቃቸው ሆነው ለአርሻ ተግባር በዋሉ
ማሣያች ውስጥ ባለ የማምረት ሁኔታ በመሆኑ ነው:: ይህንንም እንደሚከተለው ለማብ
ራራት ይሞከራል:: በአርሻ ተግባር ዋነኛውን ሚና የሚጫወተው መሬት ነው:: መሬት
ከሌሎች የምርት መገልገያዎች የሚለይበት ዋና ምክንያት በሥራ የማይፈጠር፣ መጠኑ
የተወሰነና አስፈላጊ ቢሆን መጠኑን ለማባደግ የማይቻል መሆኑ፣ በማንኛውም አገር
ውስጥ ያለው ለም፣ ለም ከጠፍና ጠፍ መሬት መጠን የተወሰነ በመሆኑ ነው:: ለም
የሆኑት ማሣያች መጠን የተወሰነ በመሆኑ በእነርሱ ላይ የሚመረተው ምርት ብቻ
ለአርሻ ምርት ያለውን ፍላጎት ሙሉ ለሙሉ ሊያረካ አይችልም:: በለዚህ ካፒታሊ
ስቶች በለምነታቸው ዝቀተኛ ደረጃ የያዙትን ማሣያች በምርት ሥራ ላይ ለማዋል
ይገደዳሉ:: ነገር ግን ካፒታሊስቶች እነዚህን ማሣያች በምርት ሥራ ላይ ለማዋል
ፈቃደኛ የሚሆኑት ወጪአቸውን ሸፍነው አማካይ ትርፍ ሊያስገኝላቸው በሚችል ዋጋ
ምርታቸውን ለመሸጥ ቢችሉ ነው:: አማካይ ትርፍ ካላገኙበት ካፒታላቸውን ወደሌላ
የሥራ መስክ ለማዛወር ይገደዳሉ:: ይህ ቢሆን ግን የአርባ ምርት ውጤት እጥረት
ስለሚፈጥርና የአርሻ ምርት የገበያ ዋጋ ከፍ በለሚል ጠፍነት የሚያጠቃቸውን ማሣ
ያች በሥራ ላይ ማዋል አማካይ ትርፍ ሊያስገኝ በለሚችል ካፒታሊስቶች ገንዘባቸውን
እነዚሁኑ ማሣያች ለልማት ለማዋል እንደገና ፈቃደኛ ይሆናሉ:: ለም አፈር ያላ
ቸው ማሣያች ምርታማነት የለምነት ደረጃ ዝቀተኛ ከሆ~~ኑ~~ ማሣያች ምርታማነት ጋር
ሲነፃፀር ከፍተኛ በመሆኑና በማንኛውም ዓይነት ማሣ ላይ የተመረተ አንድ የአርሻ
ምርት ዓይነት የገበያ ዋጋው በለማይለያይ ጠፍነት የሚያጠቃቸውን ማሣያች በምርት
ተግባር ላይ ያዋሉ ካፒታሊስቶች አማካይ ትርፍ ካገኙ ለም ማሣያችን በምርት ተግ
ባር ላይ ያዋሉ ካፒታሊስቶች የሚያገኙት ትርፍ መጠን ከአማካይ ትርፍ መብለጥ
ይኖርበታል:: ሆኖም ይህ በአፈሩ ለምነት ምክንያት የሚገኘው ተጨማሪ ትርፍ

ለካፒታሊስቱ የሚቀር ባይሆን በልዩነት ኪራይ መልክ ለባለመሬቱ የሚገባ ነው። የዚህም ምክንያት ባለመሬቶች በለም መሬቶች ላይ የሞኖፖል ባለቤትነት ያላቸው በመሆናቸው ነው።

የልዩነት ኪራይ የማግኛ ሁለተኛው መንገድ ማሣዎች ከገበያ ቦታዎች ያላቸው ርቀት መለያየት ነው። ለም አፈር ያላቸው ማሣዎች ላይ የሚመረተው ምርት መጠን የኅብረተሰቡን ፍላጎት ሙሉ በሙሉ ለማርካት ባለመቻሉ የለምነታቸው ደረጃ ዝቅተኛ የሆኑ ማሣዎች እንደሚታረሱ ሁሉ፣ በገበያ አቀራቢያ የሚገኙ ማሣዎች ምርት በቂ ባለመሆኑ ከገበያ ቦታዎች ርቀት ያላቸው ማሣዎችም ለምርት ይውላሉ። ማሣዎች ከመገበያያ ቦታ በራቁ መጠን ምርቱን ለመሸጥ የሚያስፈልገው የመጓጓዣ ወጪ ይቀጥላል። ለምሳሌ ጤፍ በአዲስ አበባ አካባቢና በጎጃምና በሌሎች ልዩ ልዩ ቦታዎች ይመረታል። ከነዚህ በልዩ ልዩ ርቀት ላይ ከሚገኙ ቦታዎች ጤፉን ወደ አዲስ አበባ አምጥቶ ለመሸጥ የሚያስፈልገው የመጓጓዣ ወጪ እንደቦታው ርቀት ይለያያል። ከመገበያያ ቦታ አጪግ ርቆ የሚገኘውንና በምርት ተግባር ላይ የቀለውን ማሳ የሚያካሂደው ካፒታሊስት ወጪውን ሸፍኖ አማካይ ትርፍ ማግኘት ይኖርበታል። ለዚህ ካፒታሊስት አማካይ ትርፍ ለማስገኘት የሚችል የገበያ ዋጋ ደግሞ በገበያው አቅራቢያ የሚገኝን ማሣ ለሚያካሂዱ ካፒታሊስት ተጨማሪ ትርፍ ማስገኘት ይኖርበታል። ምክንያቱም በገበያው አቅራቢያ የሚገኘውን ማሣ የሚያካሂደው ካፒታሊስት ምርቱን ወደገበያው ለማጓጓዝ የሚያወጣው ወጪ አነስተኛ ስለሚሆን ነው። አሁንም ባለመሬቶች በገበያ አካባቢ በሚገኙ የእርሻ መሬቶች ላይ የሞኖፖል ባለቤትነት ያላቸው በመሆናቸው ይህን ተጨማሪ ትርፍ በልዩነት ኪራይ ስም እንዲከፈላቸው ያደርጋሉ።

ሦስተኛውና የመጨረሻው የልዩነት ኪራይ የማግኛ መንገድ ካፒታሊስቶች የተከራዩዋቸውን ማሣዎች ምርታማነት ለማሳደግ ከሚያደርጉት ወጪ ጋር የተያያዘ

ነው። ካፒታሊስቶች ማሣዎቹን ከባለመሬቶች ላይ ከተከራዩ በኋላ ትርፋቸውን ለማሳደግ ባላቸው ፍላጎት ምክንያት ተጨማሪ ወጪ አውጥተው የማሣዎቻቸውን ምርታማነት ለማሳደግ እርምጃ ይወስዳሉ። አዳዲስ የአሠራር ዘዴዎችን በሥራ ላይ ያውላሉ። በዘመናዊ የእርሻ መሣሪያዎች፣ በማዳበሪያ፣ በመስኖ ውሃ ይጠቀማሉ። እነዚህንና እነዚህን የመሳሰሉትን ተግባራት ለማከናወን ተጨማሪ ወጪ የሚያስወጡ በተለይ ለም አፈር ያላቸውን ማሣዎች የተከራዩ ካፒታሊስቶች ተጨማሪ ትርፍ ሊያገኙ ይችላሉ። ሆኖም ካፒታሊስቶቹ ይህን ተጨማሪ ትርፍ የራሳቸው ለማድረግ የሚችሉት ለተወሰነ ጊዜ ብቻ ነው። ይህም የሚሆንበት ምክንያት ባለመሬቱ መሬቱን ለካፒታሊስቱ ሲያከራይ ውል የሚቀጥለው ለተወሰነ ጊዜ፣ ለምሳሌ ለአምስት ዓመት፣ በመሆኑ ነው። ካፒታሊስቱ በዚህ በውሉ ዘመን ውስጥ የሚያገኘውን ተጨማሪ ትርፍ የራሱ ለማድረግ ይችላል። የውሉ ዘመን አልቆ አዲስ ውል መፈራረም ሲያስፈልግ ግን የመሬቱ ምርታማነትና የካፒታሊስቱ ገቢ የጨመረ መሆኑን በመገንዘብ ባለመሬቱ ከካፒታሊስቱ የሚጠይቀውን የኪራይ ክፍያ መጠን ከፍ ያደርጋል። በዚሁ አኳኋን ካፒታሊስቱ ያገኘው የነበረው ተጨማሪ ትርፍ ወደልዩነት ኪራይ ይለወጣል።

ፍጹማዊ ኪራይ፣ ስለ ልዩነት ኪራይ በተናገርንበት ጊዜ በለምነቱ እጅግ ዝቅተኛ የሆነውን ማሣ በምርት ተግባር ላይ የሚያውለው ካፒታሊስት ከወጪው በተጨማሪ አማካይ ትርፍ ማግኘት አለበት ብለን ነበር። እርግጥ ካፒታሊስቱ ካፒታሉን በለምነቱ እጅግ ዝቅተኛ በሆነው ማሣ ላይ የማጥል ፍላጎት እንደሌለው ሁሉ የማንኛውም ማሣ ባለንብረት የሆነ ባለመሬት ኪራይ ካልተከፈለው መሬቱን ካፒታሊስቱ በሥራ ላይ እንዲያውለው አይፈቅድለትም። ስለዚህ የእርሻ ምርቱ የገበያ ዋጋ፣ በለምነቱ እጅግ ዝቅተኛ የሆነው ማሣ በምርት ተግባር ላይ የሚያውለውን ካፒታሊስቱ ወጪውን እንዲሸፍን፣ አማካይ ትርፍ እንዲያገኝና ለባለመሬቱ ኪራይ የሚከፍለው ተጨማሪ ትርፍ ለማግኘት ማስቻል አለበት። ይህ በለምነቱ እጅግ ዝቅተኛ ለሆነው ማሣና ለሌሎችም ማሣዎች የሚከፈል መደበኛ የሆነ የመሬት ኪራይ ፍጹማዊ ኪራይ ይባላል።

በካፒታሊስቱ ሥርዓት ለፍጹማዊ ኪራይ መኖር ምክንያት የመሬት በሞኖፖል ባለቤትነት መያዝ ነው። ይህ የመሬት በሞኖፖል መያዝ ካፒታሊስቶች ካፒታላቸውን ከኢንዱስትሪ ወደ እርሻ የማዛወር ችሎታቸውን ይገታዋል። በዚህም ምክንያት ውስጧዊ የካፒታል ጥንቅር ከኢንዱስትሪ ይልቅ በእርሻ ዝቅተኛ ይሆናል። ይህም ማለት ካፒታሊስቱ አንድን የተወሰነ የካፒታል መጠን በኢንዱስትሪ መስክ በሥራ ላይ ከሚያውለው በእርሻ ላይ ቢያውለው የበለጠ ተረፈ እሴት ሊፈጠርለት ይችላል ማለት ነው። ካፒታል ከኢንዱስትሪ ወደእርሻ ለመዛወር የሞኖፖል እክል ባያጋጥመው ኖሮ በእርሻው መስክ የሚፈጠረው ተጨማሪ ተረፈ እሴት በኢንዱስትሪና በእርሻ መስኮች መካከል ይከፋፈል ነበር። ነገር ግን ይህ እንዳይሆን የመሬት በሞኖፖል ባለቤትነት መያዝ ያግደዋል። ባለመሬቱ ይህን ተጨማሪ ተረፈ እሴት በፍጹማዊ ኪራይ መልክ መሬቱን ከተከራየው ካፒታሊስት ይወስዳል። የልዩነት ኪራይ ኅብረተሰቡ ከመሬት ለምነት የሚገኘ ጥቅም ተከፋይ እንዳይሆን ቢያደርግ ፍጹማዊ ኪራይ የእርሻ ምርትን ዋጋ ውድነት ያስከትላል።

በካፒታሊስቱ ሥርዓት ውስጥ የመሬት ኪራይ ኅብረተሰቡ ለባለመሬቶች የሚያደርገው የግዳጅ ክፍያ ነው። ካፒታሊዝም እየዳበረ በሄደ ቁጥር የዚህ ክፍያ መጠን እያደገ ይሄዳል። ይሁንና ባለመሬቱ ለካፒታሊስት ምርት ፈጽሞ አስፈላጊ አይደለም። የሚያገኘው ገቢም ሙሉ በሙሉ የተቀባቢነት ጠባይ ያለው ነው።/

አብዮታችን ከመፈንዳቱ ቀደም ብሎ በነበሩት ጥቂት ዓመታት ውስጥ ከባለመሬቶች ሰፋፊ እርሻዎችን በመከራየት ዘመናዊ እርሻ የሚያካሂዱ ካፒታሊስቶች በማቆጥቆጥ ላይ ነበሩ። ባለመሬቶች ጢሰኞቻቸውን በማስነሳት ለነዚሁ ካፒታሊስቶች መሬት አከራይተዋል። የተባረሩት ጢሰኞችም በከፊል ወደ ከተማ በመፍለስ በከንቱ ሥራ ፍለጋ ሲንገላወዱ በከፊል ደግሞ ለዘመናት ሲያለሙት የቆዩትን መሬት በመልቀቅ ጠፍነት ወደሚያጠቃው መሬት መዛወር

ገዱ ሆኖባቸዋል። የኃይለሥላሴ መንግሥት ረበቷቸው የነበረው ዘላኖች ለዘመናት ከብት ያግጡበት የነበረውን መሬት "የመንግሥት መሬት" በሚል ባቢያ ሌላ መተዳደሪያ ባይፈጥርላቸው ለውጭና ለውስጥ ካፒታሊስቶች በማከራየት የሕልውናቸውን መሠረት አናግቶት ነበር። የምንዳ ወለል ያልተወሰነ ስለነበር በሰፋፊ እርሻዎች ተቀጥረው ይሠሩ የነበሩ ሠራተኞች ለሕልውናቸው የሚበቃ ምንዳ እንኳ አያገኙም ነበር። በአንጻሩ ሠራተኛው የፈጠረውን ተረፈ እሴት በመካከላቸው ይከፋፈሉ የነበሩት የእርሻ ካፒታሊስቶችና ትላልቅ ባለመሬቶች የተንደላቀቀ ኑሮ ሲኖሩ ችለዋል። በአብዮታችን መሬት የሕዝብ ሀብት ከሆነ ወዲህ ይህ ሁኔታ ተለውጧል፤ መሬትን በሞኖፖል በግል በመያዝ ልዩ ልዩ የኪራይ ዓይነቶች መበዝበዝ አክትሟል።

## 2. <u>በካፒታሊስት ሥርዓት ውስጥ የማኅበራዊ ምርት ርባታና የኢኮኖሚ ቀውሶች</u>

### 2.1 <u>የማኅበራዊ ምርት ርባታ ሂደት</u>፤

በማንኛውም ኅብረተሰብ የካፒታሊስቱን ኅብረተሰብ ጨምሮ፣ በየዓመቱ ልዩ ልዩ ቁሳዊ ምርቶች በተለያየ መጠን ይመረታሉ። ለምሳሌ በአገራችን በኢትዮጵያ ውስጥ በየዓመቱ እንጀራ፣ ዳቦ፣ ሥጋ፣ ቢራ፣ ቡና፣ ሸሚዝ፣ ጫማ፣ ቤት፣ ማረሻና ሌሎችም በርካታ የምርት ዓይነቶች በተለያየ መጠን ይመረታሉ። እነዚህ የምርት ዓይነቶች በምርት ሂደት ውስጥ በልዩ ልዩ ደረጃ አልፈው የተጠቃሚውን ፍላጎት የሚያረኩ ናቸው። ለምሳሌ እንጀራ ተጋግሮ የሰውን ፍላጎት በቀጥታ ለማርካት ከመቻሉ በፊት ሞፈርና ቀንበር ተሠርቶ፣ መሬት በበሬ ታርሶ፣ ጤፍ ተዘርቶ፣ ታርሞ፣ ታጭዶ፣ ተወቅቶ፣ ጎተራ ገብቶ፣ ከዚያ ወደ ሸማቹ ወይም በላተኛው ደርሶ፣ ተፈጭቶ፣ ተቦክቶ፣ ተጋግሮ፣ ለሰው ፍላጎት ማርኪያ ይውላል። እንደ እንጀራና ጠላ ያሉት የምርት ዓይነቶች ከተመረቱ በኋላ ባጭር ጊዜ ውስጥ ሙሉ በሙሉ ጥቅም ላይ በመዋል የሚጠቀምባቸውን ግለሰብ ፍላጎት በቀጥታ የሚያረኩ ናቸው። ሌሎች እንደ

ጫማና ልብስ ያሉት የምርት ዓይነቶች ደግሞ ረዘም ላለ ጊዜ አገልግሎት ሊሰጡ ይችላሉ። አሁንም ሌሎች እንደ መኖሪያ ቤት ያሉት ከተሰሩ በኋላ ለብዙ ዓመታት ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ ናቸው። የሰዎችን ፍላጎት በቀጥታ ሊያረኩ ከሚችሉ የምርት ዓይነቶች ሌላ ፍላጎትን በተዘዋዋሪ ሊያረኩ የሚችሉ የምርት ዓይነቶች ይመረታሉ። ለምሳሌ ሞፈር፣ ቀንበርና ማረሻ የሚመረቱት የሰዎችን ፍላጎት በቀጥታ ሣይሆን በተዘዋዋሪ ሊያሟሉ በለሚችሉ ነው። እነዚህን የእርሻ መሣሪያዎች በሥራ ላይ በማዋል እንደጤፍ ያሉ የእርሻ ምርቶች ይመረታሉ። ከተመረተው ጤፍ እንጀራ ተሠርቶ እንጀራው የሰዎችን ፍላጎት በቀጥታ ቢያረካ፣ የእርሻ መሣሪያዎቹ ጤፉን ለማምረት አስፈላጊ በመሆናቸው በተዘዋዋሪ መንገድ የሰዎችን ፍላጎት ያረካሉ።

በአንድ ኅብረተሰብ ውስጥ ልዩ ልዩ ምርቶች ያለማቋረጥ ለፍጆታ የሚውሉ ስለሆነ የማምረት ሂደት ያለማቋረጥ ከዓመት ወደ ዓመት መካሄድ አለበት። የማምረት ሂደት ያለማቋረጥ ካልተካሄደ የኅብረተሰቡ ሕልውና ሊቀጥል አይችልም። ስለዚህ የማንኛውም ኅብረተሰብ የሕልውናው መሠረት ቁሳዊ ሀብትን ያለማቋረጥ ማምረት ነው።

ይህ በኅብረተሰብ ወይንም በአገር ደረጃ ያለማቋረጥ የሚካሄደው የማምረት ሂደት ማኅበራዊ ርባታ ይባላል። በማንኛውም ኅብረተሰብ ውስጥ የኢኮኖሚ ርባታ ሂደት የሚያጠቃልለው የጠቅላላ ማኅበራዊ ምርትን፣ የሥራ ኃይልን እና የሥርዓቱን የምርት ግንኙነቶች መተካት ወይም መታደስ መሆኑ ቀደም ብሎ ተመልክቷል። በካፒታሊስቱ ሥርዓት ውስጥ የማኅበራዊ ምርት ርባታ የካፒታሊስቱ የምርት ግንኙነቶችም ርባታ ነው የሚባለው፣ ካፒታሊስቶች ምርትን የሚያካሂዱት ሠራተኞችን በመበዝበዝ የሚያገኙትን ትርፍ እሴት ለማሳደግ የማያቋርጥ ፍላጎት ስላላቸው በመሆኑ ነው።

በካፒታሊስቱ ሥርዓት ውስጥ የኅብረተሰብ ምርት የሚካሄደው በአንድነት ተጠቃሎ ሣይሆን በግለሰብ የካፒታሊስት ድርጅቶች መካከል ተከፋፍሎ ነው። እያንዳንዱ የማምረቻ ድርጅት በአንድ ካፒታሊስት ወይንም ቁጥራቸው በተወሰነ ካፒታሊስቶች በግል በመያዝ ከሌሎች አምራች ድርጅቶች የተለየ ሆኖ ይሠራል። ነገር ግን በእያንዳንዱ የማምረቻ ድርጅት የሚካሄደው ርባታ በሌሎች የማምረቻ ድርጅቶች ከሚካሄደው ርባታ ጋር የተያያዘ ነው። ለምሳሌ በአንድ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ ውስጥ የሚካሄደው ርባታ ለፋብሪካው የሚያገለግሉ መሣሪያዎች በሚያመርቱ ድርጅቶች፣ ጥጥ አምራች በሆኑ እርሻዎች፣ በጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካው ውስጥ ተቀጥረው ለሚሠሩ ሠራተኞች የፍጆታ ዕቃዎች በሚያመርቱ ድርጅቶችና በመባሰሉትም ድርጅቶች ውስጥ ከሚካሄዱ ርባታ ጋር የተባበረ ነው።

ማኅበራዊ ካፒታል የምንለውም በአንድ የካፒታሊስት ኅብረተሰብ ውስጥ የሚገኙትን እነዚህን እርስ በርሳቸው የተባበሩና የግል ካፒታሊስቶች ወይንም የተወሰነ ቁጥር ያላቸው ካፒታሊስቶች በባለቤትነት የያዙትን ካፒታል በጥቅል ነው።

የማኅበራዊ ካፒታል ርባታ እንዴት እንደሚካሄድ ለመረዳት ይቻል ዘንድ በቅድሚያ በለጠቅላላ የማኅበራዊ ምርት ማወቅ ያስፈልጋል። ጠቅላላ የማኅበራዊ ምርት የምንለው በአንድ ኅብረተሰብ ውይንም አገር ውስጥ በአንድ በተወሰነ የጊዜ ክልል፣ ብዙውን ጊዜ በአንድ ዓመት? ውስጥ የሚመረቱትን ቁሳዊ ምርቶች ማለት የምርት መገልገያዎችና የፍጆታ እቃዎች፣ በአጠቃላይ ነው። ጠቅላላ ማኅበራዊ ምርት በእሴት አንፃር ሲታይ እንደ እያንዳንዱ ሸቀጥ በሦስት ይከፈላል። እነዚህም በተወሰነው የጊዜ ክልል፣ ማለት በዓመት ውስጥ እሴታቸው አዲስ ወደተመረቱት ሸቀጦች ተለውጠው፣ እንደማምረቻ መሣሪያዎችና ጥሬ ዕቃዎች ያሉ የቋሚ ካፒታል ክፍሎች፣ ለሠራተኞች ምንዳ ክፍያ የዋለውን ተለዋዋጭ ካፒታል የሚተካው የእሴት መጠንና ትርፍ እሴት ናቸው።

እነዚህ ሦስት ጠቅላላ የማኅበራዊ ምርት ክፍሎች እያንዳንዳቸው በርባታ ሂደት ውስጥ የሚጫወቱት የተለያየ ሚና አላቸው። እሴታቸው አዲስ ወደ ተመረቱት ሸቀጦች የዞረው የቋሚ ካፒታል ክፍሎች ተተክተው ለመጪው ዓመት በምርት ተግባር ላይ በመዋል ምርት ያለማቋረጥ እንዲመረት ያስችላሉ። ተለዋዋጭ ካፒታል በምንዳ መልክ የሥራ ኃይልን ርባታ እንዲቀጥል ያስችላል። ትርፍ እሴት ለካፒታል ክምችትና ለካፒታሊስቱ ፍጆታ ይውላል። ቀላል ካፒታሊስታዊ ርባታ የሚካሄድ ከሆነ ትርፍ እሴቱ ሙሉ ለሙሉ ለካፒታሊስቱ ፍጆታ ይውላል። ይህም ማለት ጠቅላላ ማኅበራዊ ምርት መጠን ከዓመት ወደ ዓመት ለውጥ አያሳይም ማለት ነው። በካፒታሊስት ሥርዓት ሊኖር የሚችለው የተስፋፋ ርባታ ሲካሄድ ግን ካፒታሊስቱ የሚያገኘውን ትርፍ እሴት በከፊል ለፍጆታው ሲያውለው በከፊሉ ደግሞ ተጨማሪ የምርት መገልገያዎች ለመግዛትና ተጨማሪ ሠራተኞች ለመቅጠሪያ ያውለዋል። የተስፋፋ ርባታ በሚካሄድበት ኅብረተሰብ ውስጥ አጠቃላይ የማኅበራዊ ምርት ከዓመት ወደ ዓመት ዕድገትን ያሳያል።

አጠቃላይ የማኅበራዊ ምርትን ከእሴት አንፃር ብቻ ሳይሆን ከቁሳዊ ቅርጹ አንፃርም ማየት አስፈላጊ ነው። ቀደም ሲል እንደ ተገለጸው በአንድ ኅብረተሰብ ውስጥ የሚመረቱ ምርቶች በሁለት ይከፈላሉ። አንደኛው ክፍል እንደ እንጀራ፣ ልብስ፣ መኖሪያ ቤት ያሉ የሰዎችን ፍላጎት በቀጥታ ሊያረኩ የሚችሉ ናቸው። ሁለተኛው ክፍል እንደማምረቻ መሣሪያዎችና የኢንዱስትሪ ሕንፃዎች ያሉ የሰዎችን ፍላጎት በቀጥታ ለማርካት የሚችሉ የምርት ዓይነቶችን ለማምረት የሚያገለግሉ የምርት ዓይነቶች ናቸው። በሌላ አነጋገር እነዚህ የምርት መገልገያ የምንላቸው ናቸው። በዚህ አኳኋን አጠቃላይ የማኅበራዊ ምርት በሁለት ክፍሎች ይከፈላል። ክፍል አንድ የሚባለው የሚያጠቃልለው የምርት መገልገያዎችን ምርት ነው። ክፍል ሁለት ደግሞ የሰዎችን ፍላጎት በቀጥታ የማርካት ችሎታ ያላቸውን ለፍጆታ የሚሆኑ የምርት ዓይነቶችን ምርት ይይዛል። አንድ ኅብረተሰብ ከማምረት ችሎታው ምን ያህሉን ወደፊት ምርትን ለማምረት ለሚያገለግሉ የምርት መገልገያዎች፣ ምን ያህሉን የኅብረተሰቡን ፍላጎት በቀጥታ ለማርካት ለሚችሉ የምርት ዓይነቶች

ለማዋል የሚያደርገው ውሣኔ ፣ እርባታ ሂደት ውስጥ ከፍተኛ ሚና አለው።

## 2.2፡ የአጠቃላይ ማኅበራዊ ምርት በጥቅም ላይ መዋል/ተግባራዊነት/፡

ካፒታሊስቱ የምርት መገልገያዎችን ገዝቶ ወዝአደሮችን ቀጥሮ ምርት እንዲመረት ያደርጋል። ከዚህ በኋላ የተመረተው ምርት መሸጥ ይኖርበታል። ያመረተውን ሸቀጥ ሸጦ ወደ ገንዘብ ሳለውጠው ካልቻለ ካፒታሊስቱ የማምረቱን ተግባር እንዲቀጥል ለማድረግ ፍላጎትም አይኖረውም፣ ችሎታም ያንሰዋል።

በካፒታሊስቱ ሥርዓት ውስጥ የሚመረተው አጠቃላይ ማኅበራዊ ምርት ገዥ አግኝቶ በጥቅም ላይ እንዲውል መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች አሉ። እነዚህም ሁኔታዎች በመጀመሪያ ቀላል እርባታ በሚካሄድበት ኅብረተሰብ ውስጥ ምን ምን እንደሆኑ እንገንዘብ። ቀላል እርባታ በካፒታሊስቱ ሥርዓት ውስጥ በአብዛኛው ሊኖር የማይችል ቢሆንም በስርቡ ማወቅ የተስፋፋ እርባታን በበለጠ ለማወቅ ይረዳል። በማንኛውም ኅብረተሰብ ውስጥ የማምረቻ ድርጅቶች የምርት መገልገያዎች የሚያመርቱና የፍጆታ እቃዎች የሚያመርቱ ተብለው በሁለት እንደሚከፈሉ ከላይ ጠቅሰናል። ቀደም ቢል እንደ ተብራራው በካፒታሊስቱ ሥርዓት ውስጥ ያሉት መሠረታዊ መደቦች የካፒታሊስቱ መደብና የሠራተኛው መደብ ብቻ ናቸው እንበል። እንዲሁም ኅብረተሰቡ በውጪ ንግድ አይሳተፍም እንበል። ቀላል እርባታ ይካሄድበታል ብለን በወሰድነው ኅብረተሰብ ውስጥ አጠቃላይ የማኅበራዊ ምርት ሙሉ በሙሉ ገዥ አግኝቶ በጥቅም ላይ ለመዋል እንዲችል ሁለት ዋና ዋና ነገሮች መሟላት አለባቸው። አንደኛው መሟላት ያለበት ጉዳይ በተወሰነው የጊዜ ገደብ፣ ማለት በአንድ ዓመት፣ ውስጥ የምርት መገልገያዎችን የሚያመርቱ የማምረቻ ድርጅቶች በአጠቃላይ ያመረቷቸው ሸቀጦች መጠን፣ የምርት መገልገያዎችንና የፍጆታ ዕቃዎችን የሚያመርቱ የማምረቻ ድርጅቶች

በአጠቃላይ በዚያው የጊዜ ገደብ ውስጥ ከሚፈጁት የምርት መገልገያዎች መጠን ጋር እኩል መሆን ያለበት መሆኑ ነው። ለምሳሌ ልዩ ልዩ የምርት መገልገያዎችን የሚያመርቱ የማምረቻ ድርጅቶች በአጠቃላይ ዋጋቸው መቶ ሚሊዮን ብር የሆነ የምርት መገልገያዎች አመረቱ እንበል። በምርት ተግባር ላይ በመዋላቸው እሴታቸው በዚያኑ ዓመት አዲስ ወደተመረቱት ምርቶች የተላለፈው የምርት መገልገያዎች ዋጋም እንደዚሁ መቶ ሚሊዮን ብር ይሆናል ማለት ነው። በዚህ አኳኋን የተመረቱ የምርት መገልገያዎች በሙሉ ገዥ ያገኛሉ። ከዓመት ወደ ዓመት ለውጥ ባያሳይ የሚመረተው የምርት መገልገያዎች መጠን በጠቃላይ ማኅበራዊ ምርት መጠን ለውጥ ባያሳይ ከዓመት ወደ ዓመት እንዲካሄዱ ያስችላል። ሁለተኛው መሟላት ያለበት ነገር ደግሞ በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ የፍጆታ ዕቃዎችን የሚያመርቱ የማምረቻ ድርጅቶች የሚያመርቷቸው ሸቀጦች አጠቃላይ መጠን ከእሴት አንጻር ቢታይ የወዝአደሮች ምንዳና የካፒታሊስቶች ተረፈ እሴት በአንድነት ቢጠቃለል ካለው መጠን ጋር እኩል መሆን ይኖርበታል። ይህም በዚያው ዓመት ውስጥ የተመረቱ የፍጆታ እቃዎች በሙሉ ገዥ ማግኘታቸውን ለማረጋገጥ ያስችላል። ስለሆነም በክፍል አንድና በክፍል ሁለት የተመረቱት ሸቀጦች ያለቀሪ ተከፋፈሉ ወይም ተሸጡ ማለት ነው።

የተስፋፋ እርባታ በሚካሄድበት የካፒታሊስት ኅብረተሰብ ውስጥ የአጠቃላይ ማኅበራዊ ምርት መጠን ከዓመት ወደ ዓመት ይጨምራል እንዲ ባለበት አይቀርም። ምርትን ለማሳደግ ደግሞ የማምረቻ ድርጅቶች መስፋፋት አለባቸው፤ ወይንም አዲስ የማምረቻ ድርጅቶች መቋቋም ያስፈልጋቸዋል። ያም ሆነ ይህ የማምረቻ ድርጅቶች ፊት የነበሩትን የምርት መገልገያዎች መተካት ብቻ ሳይሆን አዲስ የምርት መገልገያዎችን ማምረት ይኖርባቸዋል። እነዚህን አዲስ የምርት መገልገያዎች በዚህ ዓመት ለምርት ተግባር ለማዋል ከተፈለገም ቀደም ብሎ በነበረው ዓመት ውስጥ መመረት ይኖርባቸዋል። በዚህ ምክንያት የምርት መገልገያዎችን የሚያመርቱ የማምረቻ ድርጅቶች የሚያመርቷቸው ሸቀጦች አጠቃላይ መጠን በቀላል እርባታ ከሚያስፈልገው

መጠን ከፍ ያለ መሆን ይኖርበታል። የተበላሸ ርባታ በሚካሄድበት የካፒታሊስት ኅብረተሰብ ውስጥ አጠቃላይ ማኅበራዊ ምርት ሙሉ በሙሉ ገዥ አግኝቶ በጥቅም ላይ ለማዋል የሚያስችሉ ሁኔታዎች የተወሳሰቡ ናቸው። እንደኛውን ለመጥቀስ ያህል የምርት መገልገያዎችን የሚያመርቱ የምርት ዘርፎች በአጠቃላይ አዲስ የሚፈጥሩት እሴት መጠን፣ ማለት የተለዋዋጭ ካፒታላቸውና የትርፍ እሴታቸው መጠን በአንድነት፣ የፍጆታ ዕቃዎችን የሚያመርቱ ዘርፎች በአጠቃላይ በአንድ ዓመት ውስጥ ከሚፈጁት የቋሚ ካፒታል መጠን በልጦ መገኘት አለበት። ይህ ሲሆን ብቻ ነው በክፍል አንድም ሆነ በክፍል ሁለት ምርትን ከዓመት ወደ ዓመት ለማሳደግ የሚያስፈልጉት ተጨማሪ የምርት መገልገያዎች ሊገኙ የሚችሉት።

በካፒታሊስቱ ሥርዓት ውስጥ አጠቃላይ ማኅበራዊ ምርት ሙሉ በሙሉ ገዥ አግኝቶ በጥቅም ላይ ለመዋል ለቀላል ርባታና ለተበላሸ ርባታ የሚያስችሉትን ሁኔታዎች ለማብራራት ከዚህ በላይ ሙከራ ተደርጓል። ነገር ግን እነዚህ ሁኔታዎች በካፒታሊስቱ ሥርዓት ውስጥ ሁልጊዜ ተግባራዊ ይሆናሉ ማለት አይደለም። እንዲያውም ሁኔታዎችን ተግባራዊ የማድረግ ችግርና ከዚህም ችግር ጋር የተያያዙ ኢኮኖሚያዊ ቀውሶች በካፒታሊስቱ ሥርዓት ውስጥ በየጊዜው የሚደርሱ መሆናቸው የታወቀ ነው።/

## 2.3 ብሔራዊ ገቢ፣

ጠቀላላ ማኅበራዊ ምርት ማለት በአንድ ኅብረተሰብ ወይም አገር ውስጥ በአንድ በተወሰነ ጊዜ፣ ለምሳሌ አንድ ዓመት፣ ውስጥ የሚመረተ ጠቀላላ ቁሳዊ በአንድ በተወሰነ ጊዜ ... ከዚህ በላይ ተገንዝበናል። ከዚህ ከጠቀላላ ማኅበራዊ ምርት፣ ሀብት መሆኑን ከዚህ በላይ ተገንዝበናል። ከዚህ ከጠቀላላ ማኅበራዊ ምርት፣ በምርት ሂደት ውስጥ ከምርት መገልገያዎች አዲስ ወደ ተመረቱት ሸቀጦች የተላለፈውን እሴት መቀነስ በሥራ ላይ የቀለውን ቋሚ ካፒታል ለማደስ ስለሚያስችል

ተገቢ ነው:: ቀሪው የጠቅላላ ማኅበራዊ ምርት ክፍል፣ ማለትም ተለዋዋጭ ካፒታልና ተረፈ እሴት፣ በተወሰነው የጊዜ ገደብ፣ ለምሳሌ አንድ ዓመት ውስጥ የተፈጠረው አዲስ እሴት ነው:: ይህም የጠቅላላ ማኅበራዊ ምርት በገንዘብ ሲተመን ብሔራዊ ገቢ ይባላል::

በቁሳዊ ቅርጹ ብሔራዊ ገቢ የፍጆታ ዕቃዎችንና የምርት መገልገያዎችን ያጠቃልላል:: ብሔራዊ ገቢ የሚፈጠረው ቁሳዊ ነገሮችን በማምረት ተግባር በቀጥታ በተሰማሩ ወዝአደሮች፣ አርሶ አደሮች፣ ዕደ ጥበብ አምራቶች ነው::

ቁሳዊ ምርት በማያስገኙ መስኮች ብሔራዊ ገቢ አይፈጠርም:: ቁሳዊ ምርት የማይፈጥሩ መስኮች የምንላቸው መንግሥታዊ አስተዳደርን፣ ውትድርናን፣ የባንክ አገልግሎትን፣ የማምረት ሂደት የማይቀጥልባቸውን የንግድ እንቅስቃሴዎች፣ ትምህርትን፣ ጤናንና የመሳሰሉትን ነው:: በእነዚህ መስኮች ውስጥ ቁሳዊ ነገሮች በቀጥታ የሚመረቱ ባለመሆናቸው ኢምርታዊ መስኮች እንላቸዋለን:: እነዚህን አምራች ያልሆኑ መስኮች ለማካሄድ የሚያስፈልገው ወጪ የሚነሳው አምራች ከሆኑ መስኮች ከሚፈጠረው ከብሔራዊ ገቢ ነው:: አምራች ያልሆኑ መስኮች ከማያስገኙ አገልግሎቶች ውስጥ ለማንኛውም ኅብረተሰብ ሕልውና አስፈላጊ የሆኑ አሉ:: ሆኖም አጠቃቀማቸው በአጠቃላይ መደባዊ ይዘት አለው:: ለምሳሌ በካፒታሊስት ሥርዓት ውስጥ የገዥው መደብ ትምህርትን ጥቅሙን ለማስከበሪያና ለማዳበሪያ ቢገለገልበት በሶሻሊስት ሥርዓት ግን ትምህርት የሚታቀደው የሰፊውን ሕዝብ ጥቅም እንዲያዳብርና እንዲንከባከብ ነው:: እንዲሁም የካፒታሊስት አገሮች መንግሥታት የሚያደራጇቸውን የጦር ኃይሎች በአገር አቀፍና በዓለም አቀፍ ደረጃ የዘረጉትን የብዝበዛ መረብ ዕድሜ ለማስረዘምና ለማስፋፋት ዓላማቸው ሲያውሏቸው የሶሻሊስት አገሮች ግን ከኢምፔሪያሊዝምና ከሌሎች አድሀሪ ኃይሎች ሊቃጣ የሚችልን ወረራ ለመቋቋም የሚያስችላቸው የጦር ኃይሎችን ያደራጃሉ::

ሆኖም ብሔራዊ ገቢ የሚፈጠረው አምራች በሆኑ መስኮች በመሆኑ ሊያድግ የሚችለው አምራች በሆኑ የኢኮኖሚ መስኮች የተሰማሩ ሠራተኞች ቁጥር ሲጨምርና ምርታማነታቸው ሲያድግ፤ በአንጻሩ ደግሞ አምራች ባልሆኑ መስኮች የተሰማሩ ሠራተኞች ቁጥር ሲቀንስና እነዚሁ ሠራተኞች አምራች ወደሆኑ መስኮች እንዲዛወሩ ሲደረግ ነው። ስለዚህ የብሔራዊ ኢኮኖሚን ለማዳበር አምራች የሆኑትን የኢኮኖሚ መስኮች ማዳበር ያስፈልጋል። ካፒታሊዝም ሲዳብር ሲሄድ የብሔራዊ ገቢን ዕድገት የመግታት አዝማሚያ ያላቸው ብዙ ነገሮች ይፈጠራሉ። በመንግሥታዊ አስተዳደር፤ በጦር ሠራዊትና በፖሊስ ሠራዊት ውስጥ የሚቀጠሩ ሰዎች ቁጥር ከፍተኛ ዕድገትን ያሳያል፤ ለካፒታሊስቶች አገልግሎት ሰጪ በሆኑ መስኮች ብዙ ሰዎች ይሠማራሉ፤ በተጨማሪም ሥራ አጥነት ይስፋፋል። ይህ ሁኔታ የካፒታሊስት ሥርዓት ቀራኔ ላለው ገጽታ እንደመሆኑ በመጨረሻ ላይ በዚህ ስልተ ምርት መደምሰስና በሶሻሊስት ብሎም በኮሙኒስት ሥርዓት ግንባታ ይፈታል።

## 2.3.1 የብሔራዊ ገቢ የመጀመሪያ ክፍፍልና ዳግም ክፍፍል፤

በካፒታሊስቱ ሥርዓት ውስጥ የብሔራዊ ገቢ ክፍፍል መደበኛ ይዘት ያለውና ለበዝባዦች በሚጠቅም መንገድ የሚከናወን ነው። በቀዳሚያ የመጀመሪያ ክፍፍልና ዳግም ክፍፍል በተባሉት መካከል ያለውን ልዩነት ግልጽ ማድረግ ያስፈልጋል። ብሔራዊ ገቢ በመጀመሪያ የሚከፋፈለው በሁለቱ ዋና የካፒታሊስት ሥርዓት መደቦች መካከል ነው። እነዚህም ካፒታሊስቶችና ወዝአደሮች ናቸው። ወዝአደሮች ምንዳ ቢያገኙ ልዩልዩ ካፒታሊስት ክፍሎች ተረፈ እሴትን በመካከላቸው ይከፋፈላሉ። አነስተኛ የግል አምራቾች /የገበሬዎችና የዕደ ጥበብ አምራቾች/ ራሳቸውን በራሳቸው የሚችሉ - ስለሆነ በመጀመሪያው ክፍፍል ውስጥ ድርሻቸውን ይወስዳሉ።

ዳግም ክፍፍል የሚካሄደው ብሔራዊ ገቢ ከላይ የተጠቀሱት መደቦችና ክፍሎች ከብሔራዊው ገቢ ድርሻቸውን ካነሡ ወይም ከወሰዱ በኋላ ነው። በዳግም ክፍፍል አማካኝነት ገቢ የሚያገኙት አምራች ባልሆኑ መስኮች የተሰማሩ አሠሪዎችና ሠራተኞች ናቸው። አምራች ባልሆኑ መስኮች ብሔራዊ ገቢ እንደማይፈጠር ተመልክተናል። ካፒታሊስቶች አምራች ባልሆኑ መስኮች ካፒታላቸውን በሥራ ላይ ቢያውሉት ትርፍ ማግኘታቸው አማይቀር ነው። የእነዚህ ክፍያዎችና ገቢዎች ምንጭ ግን አምራቹ በሆኑ መስኮች የሚፈጠረው ብሔራዊ ገቢ ነው። እንደ ትምህርት ቤት፣ ሆስፒታል ያሉ አምራቹ ያልሆኑ ድርጅቶች በመጀመሪያ ብሔራዊ ገቢውን በመካከላቸው ለተከፋፈሉት ለካፒታሊስቱ፣ ለትላልቅ ባለመሬቶች ለአነስተኛ የግል አምራቾችና ለወዝአደሩ መደቦች አባላት አገልግሎት በሚያበረክቱበት መጠንና ወቅት ክፍያ ያገኛሉ። ይህም ክፍያ አምራች ባልሆኑ መስኮች የተሰማሩ ድርጅቶችን ለማካሄድ በእነዚሁ ድርጅቶች ውስጥ ለሚሠሩ ሠራተኞች ደመወዝ ለመክፈልና በድርጅቶቹ ውስጥ ካፒታላቸውን በሥራ ላይ ላዋሉ ካፒታሊስቶች ትርፍ ለመክፈል ያስችላል። በበጀት አማካኝነትም የቡርዧው መንግሥት የወዝአደሩን ገቢ በከፊል በቀረጥ መልክ በመሰብሰብ በተለይ የገዥ መደብ አባላትን ጥቅም ለማዳበርና ለማስከበር በሚረዳ መልክ አምራች ባልሆኑ የሥራ መስኮች ወጪ ለመሸፈኛ ይጠቀምበታል።

### 2.3.2 <u>የብሔራዊ ገቢ አጠቃቀም፣</u>

ብሔራዊ ገቢ በመጀመሪያና በዳግመኛ ከተከፋፈለ በኋላ በጥቅም ላይ መዋል አለበት። ሆኖም፡ እንደ ክፍፍል ሁሉ፣ ብሔራዊ ገቢን በጥቅም ላይ ማዋል የመደብዊነት ጠባይ አለው። ከብሔራዊ ገቢ ውስጥ ለሠራተኞች ፍጆታ የሚውለው በአብዛኛው መሠረታዊ ፍላጎታቸውን ለማርካት የሚያስችላቸው አይደለም። ቁጥራቸው ከጠቅላላው ሕዝብ ከመቶ ለ፹ ዘጠና ያህል የሚሆነው አምራች ያልሆነና አምራች በሆኑ መስኮች የተሰማራት በኢምፔሪያሊስት አገሮች ውስጥ የሚገኙት

ሠራተኞች ከብሔራዊ ገቢ ለፍጆታቸው የሚያውሉት ገማሹን እንኳ አያህልም። /አንዳንድ አገሮችን ባለፈው ምዕራፍ ውስጥ ይመልከቱ/ ዛሬ በካፒታሊስቱ ዓለም የሚኖሩ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ወዝአደሮች የሚኖሩባቸው ቤቶች በመጥፎና በአሣዛኝ ሁኔታ ላይ የሚገኙ፣ ልጆቻቸው ጥሩ ትምህርት እንዲያገኙ ለማድረግ አቅም የማያገኙባቸውና መሠረታዊ ፍላጎታቸውን በሌሎች ልዩ ልዩ አንጻር ለማሟላት የሚቸገሩ ናቸው።

በአንጻሩ በዝባዥ መደቦች የብሔራዊ ገቢውን ትልቅ ክፍል የራሳቸው ያደርጋሉ። ካፒታሊስቶች ከገቢያቸው ከፊሉን ለቅንጦትና ለሌላም ፍጆታ ያውሉታል። ሌላውን ክፍል የምርት መገልገያዎችን ገዝተው ምርትን ለማዳበርና ትርፍን ለማባደግ ይጠቀሙበታል። የማምረቻው ዓላማ የኅብረተሰቡን ፍላጎት ማርካት ሳይሆን ትርፍ ማካበት በመሆኑ የሕዝቡን መሠረታዊ ፍላጎቶች ለማርካት የማያስችሉ የምርት ዓይነቶች ትኩረት አይሰጣቸውም። በአንጻሩ ደግሞ በካፒታሊስቱ ሥርዓት ውስጥ ሸቀጣ ሸቀጦችን ለማስተዋወቂያ፣ ለጦር መሣሪያና ለመሳሰሉት ኢምርታዊ ለሆኑ ጉዳዮች ከፍተኛ ወጪ ሲወጣ ይታያል።

## 2.4 የካፒታሊስቱ ሥርዓት የኢኮኖሚ ቀውሶች፣

በካፒታሊስቱ ሥርዓት ውስጥ ሊታረቁ የማይችሉ ቅራኔዎችና በየጊዜው የሚፈጠሩ የኢኮኖሚ ቀውሶች ይገኛሉ። የሌሎቹ ቅራኔዎችና የኢኮኖሚ ቀውሶች መሠረት የሆነም አንድ ቅራኔ አለ። ይኸውም መሠረታዊ ቅራኔ የማምረት ተግባር ማኅበራዊ በመሆኑና ካፒታሊስቱ የሚመረተውን ምርት የግሉ የሚያደርገው በመሆኑ ላይ ያለው ቅራኔ ነው።

ካፒታሊዝም እየዳበረ ቢሄድና የምርት ኃይሎች እያደጉ ቢሄዱ የማምረት ተግባር የበለጠ ማኅበራዊ እየሆነ ይሄዳል። ትላልቅ የማምረቻ ድርጅቶችና

የኢንዱስትሪ ማዕከሎች መፈጠር የኅብረተሰቡ የምርት ኃይሎች በጥቂቶች እጅ እንዲከማቹ ያደርጋሉ። ማኅበራዊ የሥራ ክፍፍል እየዳበረ መሄዱ በአምራቶች መካከል ያሉትን ግንኙነቶች ያስፋፋል። የበለጠ የተስፋፋና የበለጠ የተጠናከረ ጥገኝነት በአምራች ድርጅቶች መካከል እንዲኖርም ያደርጋል። በመጨረሻም የተበጣጠሱ የኢኮኖሚ ክፍሎች ወደ አንዱ ማኅበራዊ የማምረት ሂደት ይጠቃለላሉ። ካፒታሊዝም እየዳበረ ሲሄድ ምርት ይበልጡን የሚመረተው ለገበያ ይሆናል። በአንጻሩ ደግሞ የግልን ፍላጎት በቀጥታ ለማርካት የሚመረት ምርት እየጠፋ ይሄዳል። የአገር ውስጥና የውጭ ንግድ እያደገ በመሄዱም የዓለም ገበያን ይፈጥራል፣ ይጠናከራል። ሆኖም የካፒታሊስቱ ሥርዓት እስከአለ ድረስ የግል ካፒታሊስቶች ምርትን የራሳቸው ንብረት ማድረጋቸውን ይቀጥላሉ። ከካፒታሊስት ሥርዓት የሚፈጠረው ቅራኔ መሠረቱ ይህ ነው።


ይህ በካፒታሊስቱ ሥርዓት ውስጥ የሚገኘ መሠረታዊ የሆነ ቅራኔ የሚያስከትላቸውን ሌሎች ዋና ዋና ቅራኔዎችና የኢኮኖሚ ቀውሶች ከዚህ በታች እንመለከታለን። በእያንዳንዱ የመምረቻ ድርጅት የምርት አደረጃጀትና በአጠቃላይ በኅብረተሰቡ ውስጥ ባለው ሥርዓት አልባ የሆነ የማምረት ተግባር መካከል ያለው ቅራኔ ከእነዚህ ዋና ዋና ቅራኔዎች መካከል አንዱ ነው። ካፒታሊስቱ እያንዳንዱን የማምረቻ ድርጅት የሚያደራጀውና የሚያካሂደው ባንድ ለተወሰነ ዓላማ፣ ማለት ለትርፍ ነው። በዚሁ መሠረት ካፒታሊስቱ በአንድ የማምረቻ ድርጅት ውስጥ ያሉ ክፍሎችን እስከተወሰነ ደረጃ ድረስ አስተባብሮ ያካሂዳቸዋል። በካፒታሊስቱ ኅብረተሰብ ደረጃ ግን ምንም ዓይነት በዕቅድ የሚመራ የምርት አደረጃጀት የለም፣ ሊኖርም አይችልም። በዚህ ምክንያት የኢኮኖሚው እንቅስቃሴ በአጠቃላይ ሥርዓት አልባ ይሆንና የሚመረተው ሸቀጥ ዓይነትና መጠን ከኅብረተሰቡ ፍላጎት ጋር የማይጣጣም ይሆናል። በአንዳንዱ የኢኮኖሚ ክፍሎች፣ ተጠቃሚዎች ከሚፈልጉት በላይ ይመረታል። በሌሎች የኢኮኖሚ ክፍሎች ደግሞ ተጠቃሚዎች የሚፈልጉትን ያህል አይመረትም። ይህም አለመጣጣም በተለይ




በካፒታሊዝም ውስጥ የሚፈጠረው የኢኮኖሚ ቀውስ በወዝአደሩ ጫንቃ ላይ ያርፋል ። (የ20ኛው ምዕተ ዓመት ታሪክ ከሚባለው መጽሐፍ)

proudly brought to you by

www.binyamhk.wordpress.com



በሚባባሰበት ጊዜ የሚመረቱት ሸቀጦች በወቅቱ ተሸጠው የማምረት ተግባር በተፈለገው ደረጃ እንዳይቀጥል እንቅፋት በመሆን የኢኮኖሚ ቀውስ ያስከትላል::

በካፒታሊስቱ ሥርዓት ውስጥ የሚገኝ አንዱ ሌላ ዋና ቅራኔ በምርትና በፍጆታ መካከል ያለው ነው:: የካፒታሊስቱ ፍላጎት ትርፍን ማሳደግ ነው:: ይህንን ዓላማ ተግባራዊ ለማድረግ ቴክኖሎጂን ያሻሽላል፣ አዳዲስና ዘመናዊ የማምረቻ መሣሪያዎችን በሥራ ላይ ያውላል፣ ተጨማሪ ሠራተኞችን ይቀጥራል፣ ምርትን ያባዛጋል:: ነገር ግን የካፒታሊስቱ ፍላጎት ትርፍን ለማሳደግ በመሆኑ የወዝአደሩ ምንዳ እንዳያድግ፣ ብዝበዛውም እንዲባባስ ያደርጋል:: የብዝበዛው መባባስና የሠራተኞች መደኸየት የኅብረተሰቡን የመግዛት ኃይል ይቀንሰዋል:: ካፒታሊስቱም ምርቱን ለመሸጥ የበለጠ ችግር እያጋጠመው ይሄዳል:: ይህም "በለጠ ምርት" የተባለውን የኢኮኖሚ ቀውስ ያስከትላል:: በካፒታሊስቱ ሥርዓት "በለጠ ምርት" ሊኖር ይችላል ቢባል ግን ኅብረተሰቡ ፍላጎቶቹን ለማርካት የሚያስፈልጉትን ነገሮች በብዛት አግኝቷል ማለት አይደለም:: "በለጠ ምርት" አለ ቢባል ከሰፊው ሕዝብ የመግዛት ችሎታ መጠን በላይ ተመርቷል ማለት ነው:: እንዲያውም "በለጠ ምርት" በሚያስከትለው የኢኮኖሚ ቀውስ ምክንያት ሥራ አጥነት ተስፋፍቶ ሠራተኛው የዕለት ጉርሱን የሚያጣበት የካፒታሊስት ሥርዓት አይነተኛው ባሕሪ ነው::

በኢኮኖሚ ቀውስ ምክንያት ትንንሽና መካከለኛ የማምረቻ ድርጅቶች እየተዳከሙ፣ እየተዘጉ ይሄዳሉ:: በአንጻሩ ደግሞ ጥቂት ካፒታሊስቶች እየተጠናከሩ፣ የኅብረተሰቡን ኢኮኖሚ ይበልጥ በቁጥጥራቸው ሥር እያደረጉ ይመጣሉ:: በኢኮኖሚ ቀውሶች ምክንያት የማምረቻ መሣሪያዎች ከሥራ ውጪ ይሆናሉ፣ ምርት ከኅብረተሰቡ የማምረት ችሎታ እጅግ ባነሰ መጠን ይመረታል:: ሥራ አጥነት ይስፋፋል፣ የሰፊው ሕዝብ የኑሮ ደረጃ ያሽቆለቁላል:: የካፒታሊስቱን ሥርዓት

መሠረታዊ ቅራኔዎች ለመፍታት፣ በየጊዜው የሚፈጠሩት የኢኮኖሚ ቀውሶች እንዳይፈጠሩ ለማድረግና የኅብረተሰቡን የምርት ኃይሎች ያለገደብ በማዳበር የሕዝቡን ፍላጎት በአስተማማኝ ለማርካት የሚቻለው በዕቅድ የሚመራ የሶሻሊስትን ሥርዓት በመመሥረት ብቻ ነው።



## ጥ ያ ቄ ዎች

1\. በካፒታሊስት ኅብረተሰብ ውስጥ ሠራተኛው የፈጠረውን ትረፊ እሴት በመካከላቸው የሚከፋፈሉ የበዝባዥ መደብ ክፍሎች የትኞቹ ናቸው? ክፍፍሉ እንዴት እንደሆነ ዘርዝር አድርገህ አብራራ::

2\. እነዚህ የካፒታሊስቱ ሥርዓት የበዝባዥ መደቦች ክፍሎች ሠራተኛው ከፈጠረው ትረፊ እሴት የሚያገኙት ድርሻ ምን ምን ይባላል? ዘርዝር አድርገህ በምሳሌ አብራራ::

3\. የካፒታሊስቱ ብቸኛ የትርፍ ምንጭ ምንድነው? በምሳሌ አብራራ::

4\. የትርፍ መጣኔ ማለት ምን ማለት ነው? የትርፍ መጣኔን ከሚወስኑ ነገሮች መካከል ዋና ዋናዎችን ዘርዝር::

5\. ልዩ ልዩ ካፒታሊስቶች የሚያገኙት የትርፍ መጣኔ የመስተካከል አዝማሚያን እንዴት እንደሚያሳይ አብራራ::

6\. የትርፍ መጣኔ እየቀነሰ የመሄዱ አዝማሚያን እንዴት እንደሚያሳይ አብራራ:: ይህንኑ አዝማሚያ ለመቋቋም ካፒታሊስቶች ከሚጠቀሙባቸው ዘዴዎች መካከል ዋና ዋናዎችን ግለጽ::

7\. የንግድ ካፒታሊስት ትርፍ ምንጩ በማምረቻ ድርጅቶች ውስጥ የሚገኙ ወዝአደሮች ስለመሆናቸው አብራራ::

8\. በካፒታሊስቱ ሥርዓት ውስጥ የባንክ ዋና ተግባር ምንድነው? ዘርዝር አድርገህ አስረዳ::

9. የልዩነት ክራይ ከምን ከምን ይመነጫል? ፍጹማዊ ክራይስ? አብራራ።

10. ማኅበራዊ ርባታ ማለት ምን ማለት ነው? በምሳሌ አብራራ።

11. ጠቅላላ ማኅበራዊ ምርትስ? ዘርዝር አድርገህ ግለጽ።

12. ቀላል ካፒታሊስታዊ ርባታ ምንድነው? ቀላል ካፒታሊስታዊ ርባታ እንዲካሄድ መሟላት ያለባቸው ነገሮች ምን ምን ናቸው?

13. የተስፋፋ ካፒታሊስታዊ ርባታ ምንድነው? የተስፋፋ ካፒታሊስታዊ ርባታ እንዲካሄድ ምን ምን ነገሮች መሟላት አለባቸው?

14. ብሔራዊ ገቢ ማለት ምን ማለት ነው? ዘርዝር አድርገህ አብራራ።

15. ምርታዊ የሆኑ የኢኮኖሚ መስኮች የትኞቹ ናቸው?

16. ኢምርታዊ የሆኑትስ? በምሳሌ አብራራ።

17. በብሔራዊ ገቢ የመጀመሪያ ክፍፍልና በብሔራዊ ገቢ ዳግም ክፍፍል መካከል ያለውን ልዩነት አስረዳ።

18. በካፒታሊስት ሥርዓት በምርት ሂደት ውስጥ የሚከሰቱ ዋና ዋና ቀራኔዎች ባሕሪና የሚያስከትሉትን ተጽእኖ አብራራ።

19. የካፒታሊስት ሥርዓት የኢኮኖሚ ቀውሶች ከሚያስከትሏቸው ችግሮች ለመላቀቅ የሚቻለው ምን ጊዜና እንዴት ነው?

# ቃላት

| | | |
|---|---|---|
| 1. | የትርፍ መጣኔ | Rate of Profit |
| 2. | የተረፈ እሴት መጣኔ | Rate of Surplus Value |
| 3. | ካፒታል የሚገለባበጥበት ፍጥነት | Speed of Capital turnover |
| 4. | ተጨማሪ ትርፍ | Additional Profit |
| 5. | የልዩነት ኪራይ | Differential Rent |
| 6. | ፍፁማዊ ኪራይ | Absolute Rent |
| 7. | የማኅበራዊ ምርት ርባታ | Reproduction of Social Product |
| 8. | የኢኮኖሚ ቀውስ | Economic Crisis |
| 9. | የማኅበራዊ ርባታ | Social Reproduction |
| 10. | ጠቅላላ ማኅበራዊ ምርት | Gross Social Product |
| 11. | ክፍል አንድና ክፍል ሁለት | Department I and Department II |
| 12. | ለማኅበራዊ ምርት ገበያ የማግኘት ሁኔታ | Problem of Realisation |
| 13. | ብሔራዊ ገቢ | National Income |
| 14. | ምርታዊ | Productive |
| 15. | ኢ—ምርታዊ/ምርታዊ ያልሆነ/ | Non-Productive |
| 16. | የመጀመሪያ ክፍፍልና ዳግም ክፍፍል | Primary Distribution and Secondary Distribution |
| 17. | የኢንዱስትሪ ካፒታል | Industrial Capital |
| 18. | የንግድ ካፒታል | Commercial Capital |
| 19. | የብድር ካፒታል | Loan Capital |
| 20. | ባለሰፋፊ የመሬት ባለቤቶች | Big Land Owners |
| 21. | በለጠ ምርት | Over Production |
| 22. | የምንዳ ወለል | Minimum Wage |

## ምዕራፍ 7

## ሞኖፖል ካፒታሊዝም — የኢምፔሪያሊዝም ኢኮኖሚያዊ መሠረት

በ19ኛው ክፍለ ዘመን ከቅኝ ግዛት መስፋፋት ጋር የካፒታሊዝም ባሕርይ መለወጥ ጀመረ፣ ከንግድ ጣቢያዎች፣ ከወደቦችና ከንዳንድ የከበሩ ማዕድናትና ሥፍራዎች ይዞታና ቁጥጥር በማለፍ በሩቅ አገሮችን ወደ ውስጥ ገብቶ መያዝና የተፈጥሮ ሀብትንና የሰው ጉልበትን መበዝበዝና መመዝበር ዓይነተኛ ዓላማቸው ሆነ። ካፒታሊዝም ሥር የሰደደባቸው አገሮች ዓለምን በመቀራመት ብዝበዛቸውን አስፋፉት። እ.ኤ.አ. ከ1860 እስከ 1914 በሃምሣ ዓመታት ውስጥ የካፒታሊስት ስልተ ምርት ዓይነተኛ ባሕርይ የነበረው ነፃ ፉክክር እየደበዘዘና እየተዳከመ ሄደ ከዚህ በአሸናፊነት የወጡ ታላላቅ ካፒታሊስቶች ሞኖፖሊን መሠረቱ። ሞኖፖል የኢኮኖሚው መዋቅርና አደረጃጀት ዋነኛ ገጽታ እየሆነ መጣ። ከሞኖፖል ካፒታሊዝም ጋርና በዚህ ላይ በመመሥረት ዘመነ ኢምፔሪያሊዝም ተዘረጋ። በአብዛኛው እ.ኤ.አ. እስከ 1960ዎቹ ድረስ በቀጥታ ቅኝ ግዛት ብዝበዛ ላይ የተገነባው ኢምፔሪያሊዝም ከነዚህ ዓመታት በኋላ አብዛኛዎቹ አገሮች የፖለቲካ ነፃነታቸውን በመቀዳጀታቸው መልኩን በመለወጥ ወደ አዲስ አዙር ቅኝ ገዢነት ተሸጋገረ።

### 1. የኢንዱስትሪ ካፒታል አነሳስ

ለኢንዱስትሪ መስፋፋት ምክንያት የሆኑት ሁለት የኢንዱስትሪ አብዮቶች ተካሂደዋል። የመጀመሪያው "የኢንዱስትሪ አብዮት" እ.ኤ.አ. በ1760 ገደማ በእንግሊዝ አገር ተካሄደ። የኢንዱስትሪ አብዮቶች ማለት አዲስ ወይም ነባር የቴክኖሎጂ ግኝቶችን አቀናጅቶ ወደ ምርት ማምረቻ መሣሪያነት ማለትም ወደ ማሽን መለወጥ ማለት ነው። በእንግሊዝ አገር በዚያ ወቅት በእንፋሎት ኃይል የሚንቀሳቀሱ ሞተሮች መሥራት ተጀመረ። እነዚህ ሞተሮች ለባቡር ትራንስፖርት፣ ለወርቃ ወርቅና ሌሎችም ፋብሪካዎች፣ ለማዕድን ቁፋሮ፣ ለመርከብ ትራንስፖርት ወዘተ... አገልግሎት ላይ ዋሉ።

እንግሊዝ እነዚህን ምርቶች በመጠቀም የጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካዎች አቋቋመች፤ የባቡር መስመሮች ዘረጋች። ከዚህም ጋር የወዛደሮች ቁጥር እየበረከተ ሄደ። በገጠሮችም ካፒታሊዝም እየተስፋፋ ሲመጣ ገበሬዎች እየተገደዱ እንዲለቁና እንዲበደዱ ወዝአደሮችም እንዲሆኑ አደረጋቸው። ወትሮ የገበሬዎች መንደሮች የነበሩ ወና እየሆኑ ሲሄዱ የኢንዱስትሪና የወደብ ከተሞች አበቡ፣ ተስፋፉ፣ ተሻሻሉ በተሠሩ መርከቦች ከባዱ ጭነት ባጭር ጊዜ ውስጥ ካንዱ አገር ወደ ሌላው ማንቀሳቀስ ከመቼውም ይልቅ ቀላል ሆነ። ከዚህ የመጀመሪያው የኢንዱስትሪ አብዮት ጀምሮ የኢንዱስትሪ ካፒታል የበላይነቱን በመያዝ የቡርዧው ሥርዓት ዓይነተኛ ገጽታ መሆን ጀመረ። ይሁንና የኢንዱስትሪ ካፒታል የበላይነቱን ቢይዝም ንግዱን አስፋፋው፣ እንዲያውም የኢንዱስትሪ መስፋፋት የገበያ ፍለጋን በማፋፋሙ ለቅኝ ግዛት ሽሚያ አዲስ ግፊት ተፈጠረ።

እርግጥ ከኢንዱስትሪ ካፒታሊዝም በፊት አንዳንድ የአውሮፓ አገሮች ለምሳሌ ፖርቱጊዞች፣ ሆላንዶችና እንግሊዞች፣ ፈረንሣዮች ወዘተ...በአፍሪካ፣ በእስያና በላቲን አሜሪካ ውስጥ "የቅኝ ግዛት" ነበራቸው። ነገር ግን እነዚህን በአመዛኙ የቅኝ ግዛቶች ልንላቸው አንችልም፤ ይበልጡኑ የንግድ ጣቢያዎች ነበሩ ለማለት ይቻላል።

ከአውሮፓ ውጭ የሚገኙትን ሸቀጦች በተለይም ቅመማ ቅመሞችን የሐር ጨርቆችን ዝባዱን፣ ባሮችን የአውሮፓ ነጋዴዎች እየገዙ ወደ አህጉራቸው እየወሰዱ ይሸጡ ነበር። በብዙ አውሮፓ አገሮች ታላላቅ የንግድ ኩባንያዎች ተከፈቱ። ለምሳሌ ከታወቁት ውስጥ "የእንግሊዝ የምሥራቅ ሕንድ ኩባንያ፣ የሆላንድ የምሥራቅ ሕንድ ኩባንያዎች" ወዘተ...ነበሩ። እነዚህ ኩባንያዎች ሸቀጥ እየገዙ የሚያከማቹባቸው፣ ሸቀጥም የሚያከፋፍሉባቸው የራሳቸው የንግድ ወኪሎች ወይም "ፋክቶሪስ" በያሉበት ይልኩ ነበር። ወኪሎቹ ታላላቅ መጋዘኖችና መኖሪያ ቤቶች ያሉባቸው የንግድ ጣቢያዎች ወይም "ፋክቶሪስ" አቋቋሙ። ሸቀጥ ለመሰብሰብና ለማከፋፈል እንዲያመች ፋክቶሪዎች የሚቆረቆሩት በባሕር ጠረፎች ላይ ነበር። አውሮፓውያን ከፋክቶሪዎች ባያልፍ ንግዳቸውን

ያካሂዱ ነበር እንጂ ወደ ሀገር ውስጥ ገብተው ሕዝቡን አያስገብሩም ነበር። ይህን ወቅት "የፋክቶሪ ዘመን" እንለው እንደሆነ እንጂ የቅኝ ግዛት ዘመን ልንለው አንችልም።

ፋክቶሪዎች እያደጉ ሄደው የወደብ ከተሞች ሆኑ። እስቲ ለምሳሌ የአፍሪካን ካርታ እንመልከት። ምዕራብ አፍሪካን ከሴኔጋል ጀምረን እስከ ናሚቢያ ድረስ ብንቃኝ ታላላቅ ከተሞች የተቆረቆሩት በባሕር ጠረፍ ላይ ብቻ ሆነው እናገኛቸዋለን። ምሥራቅ አፍሪቃንም ብንቃኝ ከጥቂቶቹ በስተቀር ብዙዎቹ ከተሞች የሚገኙት በባሕር ጠረፍ ላይ ነው። እነዚህ ከተሞች በንግድ ካፒታሊዝም ወቅት የአውሮፓ ነጋዴዎች የንግድ ጣቢያዎች ወይም ፋክቶሪዎች ነበሩ። የአውሮፓ ነጋዴዎች በደረሱባቸው አገሮችና አሕጉሮችም ሁኔታው ከአፍሪካ ጋር ተመሳሳይ ነው።

የኢንዱስትሪ ካፒታሊዝም ከመጣ በኋላ ግን ሁኔታው ተለወጠ። የኢንዱስትሪ ጥሬ ዕቃዎችን በሚያስተማምንና በማያቋርጥ አኳኋን ለማግኘት የሚያመቸው የጥሬ ዕቃ አምራች አገሮችን በሙሉ ቁጥጥር ሥር ማዋል ስለነበር ይህንኑ ተግባራዊ ለማድረግ ኰሎኒያሊዝም ወይም የቅኝ አገዛዝ ማስፋፋት ሂደት ተጀመረ። በኢንዱስትሪ ልማት ተቀዳሚውን ቦታ የያዘችው እንግሊዝ በቅኝ ግዛት ዝርጋታውም የበላይነትን ተቀዳጀች።

በፈረንሣይና በእንግሊዝ መካከል እ.ኤ.አ. ከ1756–1763 በተካሄደው <u>የሰባት</u> ዓመት ጦርነት ፈረንሣይ ድል ስለተመታች አብዛኛውን ግዛቷን ለእንግሊዝ እንድትለቅ ተገደደች። በተለይም እንግሊዝ ሰፊውን የፈረንሣይ ካናዳን ልትይዝ በመቻሏ በአሜሪካ ነፃ መውጣት ምክንያት ሄደባት ከነበረው ግዛት ያላነሰ አዲስ ቅኝ ግዛት አገኘች። ከዚህ በኋላ እስከ 19ኛው ምዕተ ዓመት መጨረሻ ድረስ ባለው ወቅት ውስጥ እንግሊዝ በአፍሪካ፣ በእስያ፣ በአውስትራሊያ፣ የቅኝ ግዛቷን አስፋፍታ "ፀሐይ የማትጠልቅበት ግዛት" ዘረጋች። ለእንግሊዝ ኢምፓየርም መዘርጋት ምክንያት ከሆኑት ዋና ዋና ምክንያቶች አንዱ በአሥራ ዘጠነኛው ምዕተ ዓመት ውስጥ የፈረንሣይ የቡርዧ አብዮት አስፋፊና ተወዳዳሪዋን ቀዳማዊ ናፖሊዮንን በማሸነፏ ነበር፣ ናፖሊዮን ከተሸነፈ በኋላ እንግሊዝ ያለ አንዳች ሥጋት የዓለምን የባሕር መንገዶች ሁሉ በቁጥጥሯ ሥር አውላ ግዛቷንና ንግዷን በመላው ዓለም ልታስፋፋ ቻለች። የእንግሊዝ መላ ዓለማዊ የበላይነት

እስከ 1970ዎቹ ድረስ ባይደፈርና ሳይበገር ሰፍና ቆይቶ ነበር፤ ከዚያ በኋላ ግን አንዳንድ አገሮች በተለይም ጀርመንና አሜሪካ ያዳዲስ ቴክኖሎጂ ጥበቦች ባለቤት በመሆን ተገዳድረው የእንግሊዝን የበላይነት መፈለም ጀመሩ :: ይህ ወቅት ሁለተኛው የኢንዱስትሪ አብዮት የተከናወነበት ወቅት ነበር ::

ከፍ ብለን እንደተመለከትነው የኢንዱስትሪ አብዮት ማለት የሳይንስና ቴክኖሎጂ ዕድገት ይፋ ያደረጋቸውን ልዩ ልዩ ግኝቶችን አቀናጅቶ መካኒካዊ የምርት መሣሪያዎችን በመፍጠር የኢንዱስትሪን ምርት ማስፋፋት ነው:: የኢንዱስትሪ አብዮት ከማለት ይልቅ ምናልባት ሜካናይዜሽን /የቴክኒክ አብዮት/ ማለት የበለጠ ትክክል ሊሆን ይችላል:: ወደ ዋናው አርዕስታችን እንመለስና ሁለተኛው የኢንዱስትሪ አብዮት ተከሰተ ብለናል:: ይህን አብዮት ከመጀመሪያ አብዮት ሙሉ በሙሉ ልዩ የሚያደርገው የውስጠ ነደድ ሞተር መፈልሰም ነው:: ይህ ሞተር በተዘጋ ጋን ውስጥ በኤሌክትሪክ ኃይል ቤንዚን /ወይም ናፍታ/ እና አየርን በተመጠነ ጅረት ተቃጥሎ በማንደድና በማቃጠል ከባድ ሥራ የሚያከናውን ኃይል ያመርታል:: በሁለት ረድፍ ከተበቡ አራት/በድብትም በምንትም ሊሆኑ ይችላሉ/ መክፈቻዎች የሚወጣው ለምቀ ሙቀ አየር ወደ ኃይል ይለወጥና አንድ አካል ያንቀሳቅሳል:: በመጀመሪያው ኢንዱስትሪ አብዮቶች ወቅት የነበረው የእንፋሎት እንቅስቃሴ ኃይል ሲባቱን የሚያገኘው ለብቻው ከውጭው ካለ ምድጃ ነበር :: የውስጠ ነደድ ሞተር መፈልሰም አነስተኛ መጠን ያላቸው ብዙ ሥፍራ የማይዙ የተለያዩ ሞተሮች ለመሥራት አስቻለ :: በዚህም መሠረት ልዩ ልዩ መኪናዎች፣ አውቶሞቢሎች፣ ትራክተሮች፣ ታንከር ከሪዎች፣ አውሮፕላኖች ናፍታ ጠጪ የባቡርና የመርከብ ሞተሮችና የኃይል ማመንጫዎች ሞተሮች ሊሠሩ ችለዋል:: ከውስጠ ነደድ ሞተር ሌላ በውሃ ወይም በእንፋሎት ዘዋሪነት ኤሌክትሪክ የማመንጨት ዘዴም ተገኘ:: በዚህ ወቅት የተገኙት የሳይንስና የቴክኖሎጂ ግኝቶች ብዙ ሰዎች የሚደክሙበትን ሥራ በቀላሉና ባጭር ጊዜ ውስጥ ለመሥራት የሚያስችሉ ልዩ ልዩ መካኒካዊ መሣሪያዎችን ለመሥራት አስችለዋል:: ኤሌክትሪክ ተገኝቶ ሥራ ላይ ዋለ :: የዲዚል ተሠራ፤ በራዲዮ ሞገድ፣ በአየር፣ በቴሌግራፍ መገናኘት ተቻለ :: ሌሎችም አያሌ ነገሮች ተገኝተዋል:: ሁለተኛው የኢንዱስትሪ አብዮት እነዚህን ያቀፈ ነበር ::

ሳይንስና ቴክኖሎጂ ከፍተኛ እርምጃ ባሳየበት በዚህ በ19ኛው ምዕተ ዓመት መገባደጃ ላይ፣ በካፒታሊዝም ዕድገት ውስጥ ሞኖፖል ካፒታሊዝም የተባለው ምዕራፍ ተከሰተ::

## 2. የሞኖፖል ካፒታሊዝም አመጣጥና አሠራር


ሞኖፖል ካፒታሊዝም የኢምፔሪያሊዝም ዋነኛ የኤኮኖሚ ገጽታ ነው:: ሞኖፖል ካፒታሊዝም በሚሰፍንበት ወቀት ውድድር መልኩን ይለውጣል፣ ወይም ይቀንሳል፣ ታላላቅ አምራችና አከፋፋይ ድርጅቶች ተወዳዳሪዎቻቸውን አሸንፈው ወይም ውጠው ገበያውን በብቸኝነት ይይዛሉ:: ሞኖፖል የሚለው ቃል ከግሪክ የተወሰደ ሲሆን ተወዳዳሪ የሌለበት ብቸኛ ንግድ ማለት ነው:: ስለሆነም ሞኖፖል ገበያን በመያዝ ዋጋ መቆጣጠርን፣ በፈለጉት መግዛትና መሸጥን ያቀፈ ነው::

እ ሞኖፖል ካፒታሊዝም የካፒታሊዝም የመጨረሻ የዕድገት ደረጃ የኢምፔሪያሊዝም መሠረት መሆኑን ሌኒን ይናገራል፣ ሌኒን የኢምፔሪያሊዝምን ዋና ዋና ባሕርዮች በአምስት ላይ በመከፋፈልና በመተንተን ገልጿቸዋል፣ እነዚህም የሚከተሉት ናቸው::

1. የምርት መሰባሰብ
2. የባንክ ካፒታልና የኢንዱስትሪ ካፒታል ውኅደት
3. የካፒታል ልከት/ መላክ/
4. የሞኖፖል ድርጅቶች የገበያ ክልሎች መከፋፈል
5. የታላላቅ ካፒታሊስት አገሮች ዓለምን መቀራመት

### 2.1 የምርት መሰባሰብ፣

በ1880ዎቹ የተነሣው ሁለተኛው የኢንዱስትሪ አብዮት ከበፊቱ እጅግ የላቀ መሆኑን ተረድተናል:: በዘመኑና ከዚያ በፊትም የተከሰቱትን የሳይንስንና




የሞኖፖል ካፒታሊዝም አመጣጥ (የ20ኛው ምዕተ ዓመት ታሪክ)


proudly brought to you by
www.binyamhk.wordpress.com

የቴክኖሎጂ ግኝቶች አቀናጅቶ ለምርት መገልገያነት ያዋለ ነበር፡፡ ኢንዱስትሪ በበለጠ እንዲያድግ መሠረት የሆኑ አዳዲስ የኃይል ምንጮችና መሣሪያዎች ለምሳሌ፣ የኤሌክትሪክ ኃይል፣ ነዳጅ ዘይት፣ የዲዘል ሞተር፣ ቴሌግራፍ፣ ወዘተ... በስፋት በአገልግሎት ዋሉ።

በዚህ ወቅት በካፒታሊዝም ስልተምርት ውስጥ የምርት መሰባሰብ የተባለ መሠረታዊ ለውጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ታየ፡፡ የምርት መሰባሰብ ማለት በካፒታሊዝም ሥርዓት ውስጥ ወዝአደሮችንና የማምረቻ መሣሪያዎችን ባንድ ፋብሪካ ውስጥ የሚያሰባስብ ሁኔታ ነው፡፡ የምርት መሰባሰብ ራሱ የምርት ኃይሎች እድገት ውጤት ነው፡፡ የሥራ ክፍፍል አንድ መልክ እንደመሆኑ መጠን አመራረት እድገት እያገኘ ለመሄዱ ጠቋሚ ነው፡፡

ቀደም ብሎ ወዛደሮች ባንድነት ሆነው በእጅ ሥራ ብቻ የሚያመርቷቸው ሸቀጦች አሁን በጥቂት ወዛደሮች ረዳትነት በፋብሪካዎች ይመረቱ ጀመር፡፡ የፋብሪካዎቹም መጠን እያደገ ቢሄድ የወዛደሮችም ቁጥር በረከተ፡፡ ትንንሽ ኢንዱስትሪዎች እየተዋጡ ወይም እየከሠሩ ለታላላቅ ኢንዱስትሪዎች መንገድ ለቀቁ፡፡ ወትሮ ከአሥር የማይበልጡ ወዛደሮችን የሚያሠሩ ፋብሪካዎች እየተ የላቁ ወይም የታላላቆቹ ጥገኛ በመሆን ከሃምሣና ከመቶ በላይ ወዛደሮችን የሚያሠሩ ፋብሪካዎች ሆኑ፡፡ ባጭሩ ባሁኑ ዘመን የምናውቃቸው ፋብሪካዎች ዓይነት በዚያን ወቅት ተጀመረ።

በመሠረቱ የሞኖፖል ኃይል ማለት የብቸኛነት ወይም የተቀናቃኝ አልባነት ኃይል ማለት ነው፡፡ አንድ የሞኖፖል ድርጅት ብቸኛ አምራችና አከፋፋይ ለመሆን ይጥራል፡፡ የገበያውን ግማሽ በብቸኛነት ሊይዝ ይችላል፡፡ ከመቶ 60 ወይም 80 ሊይዝ ይችላል። ነገር ግን የአገሪቱና የዓለምን ገበያ መቶ በመቶ የያዙ የሞኖፖል ድርጅቶች ብዙ ቶም ተብሎ ቶም አያውቅም፡፡

ለምሳሌ በአሜሪካን አገር በአሁኑ ወቅት 450,000 የሚሆኑ የኢንዱስትሪ ድርጅቶች መኖራቸው ይታወቃል:: ከነዚሁ ውስጥ 500 ድርጅቶች ካገሩ ጠቅላላ የኢንዱስትሪ ውጤት ሁለት ሦስተኛውን ያመርታሉ:: እንደገና ከነዚህ ውስጥ 100 ድርጅቶች ካገሩ ጠቅላላ የኢንዱስትሪ ውጤት አንድ ሦስተኛውን ያመርታሉ:: እነዚህ ታላላቅ አምራቾችና አከፋፋይ ድርጅቶች ምንም ያህል ጥረት ቢያደርጉ ብቻቸውን ያገሩን የኢንዱስትሪ ምርት ማጠቃለል ያዳግታቸዋል።

ይህን ሐቅ በመገንዘብ የሞኖፖል ድርጅቶች በመካከላቸው ስምምነት ይፈጥራሉ:: በሚያመርቱት ሸቀጥ መጠን ላይ ሊስማሙ ይችላሉ። ወይም በዋጋ ተመን ላይ ሊስማሙ ይችላሉ። በእንዲህ ያለው ስምምነት ልዩ ልዩ ስም ያላቸው የሞኖፖል ድርጅቶች ይፈጥራሉ። ከነዚህም ዋና ዋናዎቹ፣ ካርቴል፣ ሲንዲኬት፣ ትረስትና ግሩፕ ናቸው።

ሦስት የመድኃኒት አምራች ድርጅቶችን ለምሳሌ እንውሰድ። ሦስቱም አንድ ዓይነት መድኃኒት ወይም መድኃኒቶች ያመርታሉ እንበል። ውድድራቸውን የቀጠሉ እንደሆነ ከንቱ መፍጨርጨርና ንብረት ማባከን መሆኑን ስለሚረዱት በመተጋገዝና በመተባበር እጅ ለእጅ ተያይዞ ለመሥራት ቃል ኪዳን /አለያንስ/ ይፈጥራሉ ወይም ይፈራረማሉ። አንዱ ወገን የተከለለለትን የገበያ ፍጆታ ለመሸፈን የሚበቃ ምርት እንዲያመርት ይፈቀድለታል። በሠራተኛ አቀጣጠርም ረገድ አንድ ዓይነት መመሪያ ይኖራቸዋል። አንዱ ድርጅት ያወጣውን አዲስ ዓይነት የአሠራር ዘዴ ወይም ግኝት ሌላው እንዲጠቀምበት ወይም ፈብርኮ እንዲሸጥ ፈቃድ/ፓቴንት/ ይሰጠዋል።እንዲህ ዓይነቱ የሞኖፖል ስምምነት ካርቴል ይባላል።

ሲንዲኬት የተባለውን የሞኖፖል ድርጅቶችም ለማብራራት ሌላ ምሳሌ እንውሰድ:: አምስት የወርቃ ወርቅ አምራች ሞኖፖል ድርጅቶች አሉ እንበል።

አምቦ ውሃ ድርጅቶች በጥራት እኩል የሆነ ብዙ ሺህ ጣቃ አቡጀዲ፣ ካኪ፣ መርዱፍ፣ ደበላ ወዘተ... ያመርታሉ:: አንዱ አራቱንም ሞኖፖሎች አሸንፎ ብቻውን ለመንገስ የማይችልበት ደረጃ ላይ ይደርሳል:: የሁሉም ኃይል ተመጣጣኝ ይሆናል:: በየጊዜው ለየብሩ በሚሄደው የወርቃ ወርቀ ገበያ ላይ ከመሸከት ይልቅ መስማማት የሚያዋጣ መሆኑን በለሚረዱት ኅብረት ይፈጥራሉ:: በኅብረቱ መሠረት እያንዳንዱ ድርጅት ያመረተውን መጠን /በዚህ ላይ መብት አለውና/ በጋራ ለተቋቋመ ሳንዱ ማዕከላዊ አከፋፋይ ያስረክባል:: አከፋፋዩም የተረከበለትን ሁሉ ባንድ ዋጋ ይሸጣል:: ድርሻቸውን እንደምርታቸው መጠን ያከፋፍላል:: ጥሬ ዕቃንም በሚመለከት ረገድ እንዲሁ አንድ ማዕከላዊ የገዢ ድርጅት ገዝቶ ለአባል ድርጅቶች እንደፍጆታቸውመጠን ያከፋፍላቸዋል:: እንዲህ ዓይነቱ የሞኖፖል ኅብረት ሲንዲኬት ይባላል::

የካርቴል ወይም የሲንዲኬት አባል የሆኑ የሞኖፖል ድርጅቶች እንኳን በመጠኑ ነፃነት አላቸው:: የመጀመሪያው ድርጅት አባሎች የምርትና የሺያጭ መብት አላቸው:: ከዚህም ባሻገር በቃል ኪዳንም ሆነ በሕብረቱ በምምነት መሠረት ሕልውናቸውን ጠብቀው ለመኖር መብት አላቸው:: ትረስት የተባለው የሞኖፖል ድርጅት አባሎች ግን የምርትም የሺያጭም መብት የላቸውም:: የሞኖፖል ድርጅት ባለቤቶች የግል ባለቤትነት መብታቸውን በሙሉ ለትረስት ድርጅቱ አስረክበው ባለአክሲዮኖች ይሆናሉ:: አባል ድርጅቶች በለተቀሃዱ ትራስቱ የብዙኃን የጋራ ንብረት ይሆናል::

በመጨረሻም ገሩኘ የተባለው የሞኖፖል ድርጅት አለ:: የገሩኘ አባል የሆኑ ድርጅቶች ለበሙ ነፃነት አላቸው:: በማቸውንና የምርትና የሺያጭ መብታቸውን ጠብቀው እንዲቆዩ የኅብረት በምምነቱ ይፈቅዱላቸዋል:: ቀረብ ብለን በንመለከተው ግን ሁኔታው የተለየ ነው:: የገሩኘ አባሎች ከላይ ሆኖ የሚቆጣጠራቸው መሪያ የሚገባቸው አንድ አበተባባሪ ድርጅት አለ:: ይህ ድርጅት

በእንግሊዝኛ ሆልዲንግ ይባላል። ይኸውም ያዥ የሚይዝ ተቆጣጣሪ... ማለት ይሆናል። ሆልዲንጉን የሚመሩት በያንዳንዱ አባል ድርጅቶች ውስጥ ከፍተኛ አክሲዮን ያላቸው ግለሰቦች ናቸው። ለነዚህ ግለሰቦች ባንድነት ሆነው ስለግሩፕ የምርት ዘርፍ ማደግና ማነስ፣ ምን ዓይነት ያመራረትና የማከፋፈል ፖሊሲ ሊከተል እንደሚገባው ይወስናሉ። ሆልዲንጉን ከበላይ ሆኖ የሚያዘው ሌላ ኃይል ወይም አካል ያለ መሆኑን ወደፊት እንመለከታለን።

የግሩፕ አባል ሞኖፖል ድርጅቶች ባንድ የምርት ቀጠና ላይ ብቻ የተሰማሩ አይደሉም። አንዱ በመርከብ ግንባታ፣ ሌላው በውጭ ንግድ፣ ሌላው በውስጥ ንግድ፣ ሌላው በመድን፣ ሌላው በሰበነክ ኢንዱስትሪ የተሰማራ ሊሆን ይችላል። በአገራችን ከነበሩትና አሁንም ቢሆን ወርሰው ካላከሉት ከዚህ ዓይነት ሞኖፖሎች ለምሳሌ ሚቸል ኮትስ የተባለውን የእንግሊዝ ኩባንያ መጥቀስ ይቻላል። ይህ የግሩፕ ሞኖፖል ድርጅት ግልገል ልዩ ልዩ ሸቀጦችን ያስመጣል፣ ይልካል፣ ልዩ ልዩ የውክልና ሥራ ይሠራል፣ ጥጥ ተከፋይና ዳማጭም ነበር። ሌሎችም የተለያዩ ተግባራትን ያከናውናል፣ ሚቸል ኮትስ ባንድ ስም የሚጠሩ ልዩ ልዩ የሞኖፖል ድርጅቶችን ያቀፈ ግሩፕ ነው።

ከዚህ በላይ የዘረዘርናቸው የሞኖፖል ድርጅቶች ባሁኑ ወቅት ሁሉም በልዩ ልዩ የካፒታሊስት የማምረት፣ የማከፋፈል፣ የማጓጓዝ ወዘተ... ተግባር ተሰማርተው ይገኛሉ። ትረስት፣ ሲንዲከትና ካርቴል የተባሉት ሞኖፖሎች በዚህ መጠሪያቸው አምብዛም በይፋ አይታወቁትም፣ አይጠሩበትም። ባሁኑ ወቅት የበለጠ ስማቸው የሚጠራውና ታዋቂነት ያላቸው ልዩ ልዩ ዕቃዎችን የሚያመርቱ ሞኖፖል ድርጅቶች በእንግሊዝኛ ኮንግሎመረትስ የሚባሉት ግሩፕ ሞኖፖሎች ናቸው።

## 2.2 የባንክና የኢንዱስትሪ ካፒታል ውኅደት

የሞኖፖል ኩባንያዎች በየጊዜው እያደጉ የሚሄዱት አዲስ ካፒታል በሥራ ላይ በለሚያውሉ ነው፤ በማለት እንቶቢያቸውን ለመጠቆም ሞክረን ነበር። እርግጥ የምርት መሰባሰብን እያሳደጉ ሄደው በአገርና በዓለም ደረጃ ገዥ ቦታ እንዲያገኙ የሚያስችላቸው አዲስ ካፒታል ነው። ይህን ካፒታል የሚያገኙት ከባንኮች ነው። ለሞኖፖል ካፒታል ወይም ለኢምፔሪያሊዝም መከሰት ባንኮች ወሣኝና ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል።

በመሠረቱ የባንኮች ተግባር ደንበኞቻቸው ረዘም ላለ ጊዜ ለነሱ ዘንድ የሚያስቀምጡትን ገንዘብ በንግድ ወይም በኢንዱስትሪ ላይ ለሚያውሉት የማምረቻና የማከፋፈያ ድርጅቶች በወለድ ማበደር ነው። በዚህ ዓይነት የተቀመጠውን ገንዘብ እንዲንቀሳቀስና ለነርሱም ሆነ ለደንበኞቻቸው ትርፍ እንዲያመጣ ያደርጋሉ። የባንክ ተግባር እያደገ ሲሄድ በካፒታሊዝም የነፃ ፉክክር ሕግ አንዳንድ ባንኮች እድገ ተጓብተውና ተስፋፍተው እነሱም በበኩላቸው በገንዘብ ካፒታል ላይ የሞኖፖል ኃይል አያገኙ ሄዱ። ታላላቅና ጠንካራ ባንኮች ደካሞችን እያጠቃለሉ በመያዝ የባንኮች ቁጥር እያነሰ ካፒታላቸው እያደገ፣ ካፒታል እየተማከለና እየተጠቃለለ ሄደ። ለምሳሌ በሃያኛው መቶ ዓመት መጀመሪያ ላይ ከ115 ባንኮች መካከል ዘጠኙ 50% በመቶውን ወይም ከተቀመጠው አሥራ አንድ ቢሊዮን ብር የአደራ ገንዘብ ውስጥ አምስት ቢሊዮን አንድ መቶ ሚሊዮን ብር የተቀመጠው በነዚሁ ታላላቅ ባንኮች ነበር። በአሜሪካም ሁኔታው ተመሳሳይ ነበር። ሁለት ታላላቅ ባንኮች ማለትም የሮክፌለር ባንክና /ቼዝ ማንሀታን/ ሞርጋንትረስት ብቻቸውን የአሥራ አንድ ቢሊዮን ብር አስቀማጭ ባለአደራዎች ነበሩ። በእንግሊዝ አራት ባንኮች /ማለትም ሎይድዝ፣ ስታንዳርድ፣ ናሽናል—ዌስት ሚኒስተር ሚድላንድ፣/ የአገሪቱን አብዛኛውን የገንዘብ ከቁጥጥራቸው ሥር አድርገዋል።
ካፒታል በይበልጥ

የባንክ ሞኖፖሎች ለኢንዱስትሪ ሞኖፖሎች በብዛት የገንዘብ ካፒታል እያበደሩና በማኔጅመንት እየደገፉ የምርትን መሰባሰብ ሂደት አፋጠኑ። በመሆኑም የኢንዱስትሪ ሞኖፖሎችና የባንክ ሞኖፖሎች ዝምድና እየጠበቀ ሄደ፣ "ፋይናንስ ካፒታል" የሚባለውን ክስተት አስከተለ።

የባንኮችና የኢንዱስትሪ ሞኖፖሎች መወሃሃድ የካፒታሊስት አገሮች ዓይነተኛ ገጽታ ነው። ለምሳሌ በጀርመን ፌዴራል ሪፐብሊክ፣ ዶይቼ ባንክ ከሲሜንስ ጋር፣ ድሬዝድነር ባንክ ከክሩፕ ጋር፣ ኮሜርዝ ባንክ ከጉልዩ ሆፍማንስና ጕርሴንግ ጋር የተወሃሃዱ ናቸው።

በፈረንሣይም አገር የሮዝቬልዴ የባንክ ሞኖፖሎች ከብዙ የኢንዱስትሪ ድርጅቶች ጋር ተወሃህደዋል። ብዙውን ጊዜ ኢንዱስትሪያሊስቶች የባንክ ጥገኛ ይሆናሉ፣ የባንኮች የበላይ ኃላፊዎች ወይም ባለቤቶች ኢንዱስትሪያሊስቶችን በቁጥጥራቸው ሥር ያውላሉ። አንዳንድ ትላልቅ የኢንዱስትሪ ሞኖፖሎችም በበኩላቸው የራሣቸውን ባንኮች ሊቋቋሙ ይችላሉ። በዚህ የሞኖፖሎች ውህደት ውስጥ ወሣኝ ሥልጣን ያላቸውን ሰዎች ሌኒን "የፋይናንስ መሣፍንት"/ፋይናንሺል ኦሊጋርክስ/ ይላቸዋል። ለምሳሌ ሮክፌለርና ሮዝ ቬልዴን የመሳሰሉ የባንክ ባለቤቶች ከመሆናቸውም ሌላ በኢንዱስትሪ ላይ የፈላጭ ቆራጭነት ሥልጣን አላቸው። "የጠር መሣሪያ ካልሠራችሁ ገንዘብ አናበድርም፣ ከአንድ ኮምዩኒስት አገር ጋር ከነገዳችሁ ገንዘብ አናበድርም" ሊሉ ይችላሉ፤ ብዙ ጊዜም ይላሉ።

የሞኖፖል ካፒታሊዝም ብሎም የኢምፔሪያሊዝም መሠረተ ፋይናንስ ካፒታል ነው። ኢምፔሪያሊዝም የፋይናንስ ካፒታልን የኢኮኖሚ ኃይል በመጠቀም እያሌ ታዳጊ አገሮችን በቁጥጥሩ ሥር አውሏል፣ ተራማጅ መንግሥታትን በመገልበጥ በምትካቸው

አሻንጉሊት መንግሥታት እንዲቋቋሙ አድርጓል፤ ከመንግሥታቱ በስተጀርባ ሆነው ቅኝ ግዛትንና የለዘበ አዙር ቅኝ ግዛትን ሥራ የሚያቀናብሩ "የፋይናንስ መሣፍንት" ናቸው።

ባሥራ ዘጠነኛው ምዕተ ዓመት መጨረሻና በሃያኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ ላይ ባንኮች ዋናዎቹ የገንዘብ አበዳሪዎች በለጣበሩ በኢንዱስትሪ ላይ የነበራቸው የበላይነት የማይካድ ነበር። ስለሆነም የባንኮችን የፈላጭ ቆራጭነት ኃይል ማርክስ ባንክክራሲ ወይም የባንኮች የበላይነት ኃይል የሚል መጠሪያ ሰጥቶት ነበር። በሌኒንም ዘመን ቢሆን የባንኮች የበላይነት ፍልሚያ የሌለበት ብቸኛ ኃይል ነበር።

ባሁኑ ወቅት ግን በተለይም ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወዲህ ሁኔታው በመጠኑም ቢሆን ተለውጧል። እንደቀድሞው የገንዘብ ካፒታል ምንጮች ባንኮች ብቻ መሆናቸው ቀርቷል፤ በታላላቅ ካፒታሊስት አገሮች የሚገኙ ወዛደሮችና ሠርቶ አደሮች ቁነትና የሌለውን ኑሮአቸውን ለመቋቋም ከወር ገቢያቸው እየቀነሱ ከጡረታ ባሻገር ለሕክምና፤ ለተሽከርካሪዎች አደጋ ዋስትና፤ ለቤት መግዣ፤ ለልጆቻቸው ማስተማሪያና ለመሳሰሉ የኑሮ ግዴታዎች ገንዘብ ያስቀምጣሉ። ይህ ሁሉ ገንዘብ በባንክ ብቻ አይቀመጥም። ከባንክ ሌላ የመድን ድርጅቶች፤ የቤት ሥራ ቁጠባ ሂሣብ ድርጅቶች፤ የፖስታ ቤት የቁጠባ ሂሣብ ድርጅቶች፤ የጡረታ ሂሣብ አስቀማጭ ድርጅቶችን የመሳሰሉ ልዩ ልዩ የገንዘብ ተቋሞች ተፈጥረዋል። እነዚህ ተቋሞች ደንበኞቻቸው ለረጂም ጊዜ የሚያስቀምጡትን ገንዘብ እያሰባሰቡ በሞኖፖል ድርጅቶች ውስጥ በማዋል የባንኮችን ሥራ በከፊል እያከናወኑ ነው። ታላላቅ ባንኮችም የየራሳቸውን የመድን ድርጅቶች እያቋቋሙ ወይም ከታላላቅ የመድን ድርጅቶች ጋር እየተባበሩ በዚያው አኳያ በሚገኘው ንግድ ውስጥ እየተሰማሩ ነው። እንዲያውም በአሁኑ ዘመን የፋይናንስ ካፒታል ምንጭ የባንክና የመድን ድርጅቶች ቅንጅት ነው ለማለት ይቻላል።

የሞኖፖል ድርጅቶችም ባሕርይ ለወጥ ያለ መምጣት ለባንኮች የበላይ ገዢነት ወይም ለባንክክራሲ በመጠኑም መቀነስ ምክንያት ሆኗል። ዘመናዊያቹ የሞኖፖል ድርጅቶች ከባንኮች ወይም ከሌሎች የገንዘብ ተቋሞች ከመበደር ባሻገር በቀጥታ ከግለሰቦች ገንዘብ የሚያገኙበትን ዘዴ ፈጥረዋል። አክሲዮን ወይም የብድር ሰነድ በቀጥታ ለሕዝብ በመሸጥ ከፍተኛ መጠን ያለው ገንዘብ ለመሰብሰብ ይችላሉ።

ነገሩን በምሳሌ እናስረዳ፤ አንድ ድርጅት አዲስ የኢንቀብታቢ ዘርፍ ለመጀመር ወይም ይዞታውን ለማጠናከር በተጨማሪ 50,000,000 ብር ያስፈልገዋል እንበል። ይህን ገንዘብ ለማግኘት እያንዳንዳቸው የአሥር ብር ዋጋ ያላቸው አምስት ሚሊዮን አክሲዮኖች በገበያ ላይ ያወጣል። እያንዳንዱ ዋጋ እንደየሁኔታው በዓመት ሃምሣ ሣንቲም ወይም አንድ ብር ለአክሲዮን ገዢዎች ትርፍ ሊያመጣ ይችላል። ገንዘብ ያለውና ያተርፈኛል ብሎ ያጠራቀመ ግለሰብ ወይም ድርጅት የቻለውን ያህል አክሲዮን ይገዛና የሞኖፖል ድርጅቱ "ባለንብረት" ይሆናል ማለት ነው። ባለ አክሲዮኖቹ ነዋሪነታቸው በውጭ አገር የሆነ ባዕድ ዜጎችም ሊሆኑ ይችላሉ። በዚህ ዓይነት መንገድ በቀላሉ ከፍተኛ ገንዘብ ለማግኘት ተቻለ ማለት ነው።

ካፒታላቸውን በቀጥታ ከሕዝቡ የሚያገኙ የአክሲዮን ማኅበሮች/አ.ማ/ በሌኒንም ጊዜ ነበሩ፤ ግን በብዛት አልተስፋፉም ነበር። እነዚህ የአክሲዮን ማኅበሮች በተለይ በእንግሊዝ አገር በዚያም ጊዜ ቢሆን በስፋት እየታወቁ በመሄድ ላይ ነበሩ። የእንግሊዝ የአክሲዮን ማኅበሮች ከዛሬዎቹ ጋር እጅግ ተመሳሳይ የሆኑበት ዋጋቸው ዝቅ ያለ ብዙ አክሲዮኖች በማውጣቱ ነበር። ለምሳሌ ትልልቅ የሞኖፖል ድርጅቶች ያንዳንዱ ፓውንድ አክሲዮን ይሸጡ ነበር። የእንግሊዝ ሕግ እንዲህ ያለውን ያሠራር ዘዴ ቢፈቅድ ጀርመን ግን ባለመፍቀዱ ዚምንስ የተባለ አንድ ባለ ኢንዱስትሪ ከበርቴ "የእንግሊዝን ኢምፔሪያሊዝም የገነባው እኮ የአንድ ፓውንድ አክሲዮን ነው" ቢል ቅሬታን ለጀርመን ፓርላማንት መግለጹን ሌኒን ይናገራል።

አዳዲስ የገንዘብ አበዳሪ ተቋሞች ብቅ ብቅ ማለት የባንኮችን ፍፁም የበላይነት ቀነስ አደረገው እንጂ አላስወገደውም። ከፍ ብለን ለመጠቆም እንደ ሞከርነው ባንኮችም ራሳቸው ከመድን ድርጅቶችና ከሌሎች የገንዘብ ተቋሞች ጋር እየተካበሩ፤ ከሌሎች ባንኮች ጋር ትብብር እየፈጠሩ የፋይናንስ ካፒታልን እያጠናከሩ ነው። የኢምፔሪያሊዝምን አስከፊ ባሕርይ የሚያስፋፉና የሚያባብሱ የፋይናንስ ካፒታል መሣፍንት ናቸው። የፋይናንስ መሣፍንት ቁጥር እጅግ ጥቂት ነው፤ ነገር ግን ኃይላቸው ዓለም አቀፍ ነው። በአሜሪካ የከፍተኛዎቹ የፋይናንስ መሣፍንት ቁጥር ሃያ፤ በእንግሊዝና በፈረንሣይ አሥር፤ በጃፓን ደግሞ ስድስት ወይም ሰባት ይሆናል። ምንም እንኳን ቁጥራቸው ቢያንስ መላውን የካፒታሊስት ዓለምና በተለምዶ ሦስተኛው ዓለም የሚባለውን የሚያንቀሳቅሱም የሚያተራምሱም እነሱው ናቸው። የፋይናንስ መሣፍንት በአልጠገብ ባይነታቸውና በዕብሪታቸው በዓለም ሰላም ላይ ከፍተኛ አደጋ እያስከተሉና እየጋበዙ ነው። የሰውን ዘር ሕልውና ከጥያቄ ላይ በመጣል ላይ ናቸው።

## 2.3 የካፒታል ልኮት

ካፒታሊዝም ሞኖፖሊ ደረጃ ከደረሰ በኋላ ዓለም አቀፋዊ ሆነ። በቀጥታና በተዘዋዋሪ መንገድ ኋላ ቀርና ታዳጊ አገሮችን በፖለቲካና በኢኮኖሚ የግንኙነት ክሮቹ ጠልፎ በሥርዓቱ ውስጥ አስገባቸው፤ የካፒታሊስቶችንና የሞኖፖሎችን ጥቅም በመጠበቅና በማስፋፋት ላይ በተመሠረተው የሥራ ክፍፍል ውስጥ ሁሉንም አወቃቀለ። የሞኖፖል ድርጅቶች ለጥሬ ዕቃ ፍላጎታቸውም ሆነ ለገበያ ከአገሮቻቸው ውጭ እየወጡ በመላው ዓለም መስፋፋት ጀመሩ። የሞኖፖል ካፒታል የተስፋፋባቸው አገሮች ሁሉ የቀኝ ግዛት ሽሚያ ውስጥ ገቡ። በቀኝ ግዛትነት ወዳልተያዙትም አገሮች እየገቡ የኢኮኖሚ ጥቅም ክልሎችን በመመሥረት የጥሬ ዕቃ ምንጮችንና ገበያም ያዙ። ከነዚህ አገሮች በሚያገኙት ጥሬ ዕቃዎች የኢንዱስትሪ ውጤቶችን እያመረቱ ለጥሬ ዕቃ አቅራቢያዎቹ አገሮች በከፍተኛ ዋጋ

ይሸጡላቸዋል። በዚህ ዓይነት የኢንዱስትሪ ዕቃ አምራቶች ለየበለጸጉ የጥሬ ዕቃ አምራች አገሮች ለየቀረቀሩ ይሄዳሉ። በሌላ አነጋገር የኢንዱስትሪ ዕቃ አምራች አገሮች የጥሬ ዕቃ አምራች አገሮችን ይበዘብዛሉ። ይህ ብዝበዛ ልዩ ልዩ መልክ የያዘ ቢሆንም አንደኛውን በንግድ ወይም በልውውጥ መስክ የሚደረገውን በአጭሩ በምሳሌ እንመልከት። ኢ.ኢ.አ. በ1964 አንድ ፊያት 127 መኪና ለመግዛት አሥር ኩንታል ቡና ማምረት ያስፈልግ ነበር። ስለዚህ የተባለው መኪና ዋጋ ከ10 ኩንታል ቡና ዋጋ ጋር እኩል ነበር ሊንበል። ከአሥር ዓመት በኋላ ግን ያችኑ መኪና ለመግዛት 30 ኩንታል ቡና ማምረት አስፈለገ። 10 ኩንታል ቡና ታወጣ የነበረችው መኪና ከ10 ዓመት በኋላ ዋጋው 30 ኩንታል ቡና ደረሰ። እንግዲህ እንደኢትዮጵያ ያሉ ቡና አምራች አገሮች ከምርታቸው የሚያገኙት ገቢ በዚህ ምሳሌ እንደተጠቀሰው ሦስት እጥፍ ዝቅ ቢል እንደ ኢጣልያ ያሉት መኪና አምራች አገሮች ገቢያቸው በዚያው መጠን ከፍ ይላል። ይህ ምሳሌ ቢሆንም ሐቁ ወይም እውነቱ ከዚህ ብዙ አይራራቅም። መጠኑ ከፍና ዝቅ ቢልም ለቀጨ ወይም ሐቁ ግን ካፒታሊስት በተለይም ኢምፔሪያሊስት አገሮች በዚህ የሸቀጦች ልውውጥ ኋላ ቀር ወይም ታዳጊ አገሮችን ከሚበዘብዙበት ዘዴዎች አንዱ ይህ የተዛባ የንግድ ግንኙነት ነው።

ሌላው ካፒታሊስት አገሮች ኋላ ቀር ወይም ታዳጊ አገሮችን የሚበዘብዙት ካፒታላቸውን ወደ እነዚህ አገሮች በመላክና ጥሬ ሀብታቸውንና የሰው ኃይላቸውን በርካሽ ዋጋ ገዝተው በማቀናጀትና ውጤቱን በከፍተኛ ዋጋ በመሸጥ ነው። በዚህ መሠረት የካፒታሊስት አገሮች ባንኮችና ሌሎች ድርጅቶች በብዛት ካፒታል ወደ ታዳጊ አገሮች ይልካሉ። ወደነዚህ አገሮች የሚላከው ካፒታል እጅግ በጣም ከፍተኛ ትርፍ በሚያመጣላቸው ያለ ምንም ሥራ ቁጭ ብለው ይህንን ትርፍ ለሚበሉ የሚኖሩ በቀላሉ የሚገመቱ አይደሉም። ሌኒን ተቀባቢዎች የሚላቸው ክፍሎች እነዚህን ነው። አገራቸውም ራሱ ከነሱ ላይ ቀረጥ እየተቀበለ ነመናር

ተቀባቢ ይሆናል። በዚህ ካፒታልን በመላክ የሚመጣውን የተበዘበዘ ሀብት እየበሉ የሚኖሩ ካፒታሊስቶች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ መሆኑን ከብዙ አቅጣጫ ለማየት ይቻላል።

የካፒታል ልከትን በተጨባጭ ለመረዳት እንዲቻል ባሁኑ ወቅት ታላላቅ የካፒታሊስት አገሮች ማለትም አሜሪካ፣ እንግሊዝ፣ ጀርመን፣ ፈረንሣይና ጃፓን በተለይ በአፍሪካና በእስያ የሚያደርጉትን የካፒታል ምደባ ተግባር እንመልከት። በተለይ በአፍሪካ ላይ ትኩረት የምናደርገው ለምንኖርበት አህጉር በመሆኑና በቀጥታ ስለሚመለከተን ነው።


አፍሪካ የንግዱ ሸቀጥና የጥሬ ዕቃዎች ምንጭ በመሆን ከጥንት ጀምሮ በአውሮፓ በትበዘበዝ ቆይታለች። የአፍሪካን አብዛኛውን ክፍል በቅኝ ግዛትነት በመያዝ ለረጅም ጊዜ ሲበዘብዙ የቆዩት በተለይ እንግሊዝና ፈረንሣይ ነበሩ። ከ1960ዎቹ ጀምሮ አብዛኞቹ የአፍሪካ አገሮች ነፃ ቢወጡም በኢኮኖሚ በኩል አሁንም በኢምፔሪያሊዝም የእጅ አዙር ቅኝ ተገዥነት ቀንበር ሥር ናቸው። ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት በኋላ አሜሪካን የጀርመን ፌዴራል ሪፐብሊክና ጃፓን የተጠናከሩ የኢምፔሪያሊስት አገሮች በመሆናቸው በአፍሪካ ላይ እጅ አዙር አገዛዝን ለማበረን በሚደረገው ጥረት እንዳቅማቸው ተካፋይ ሆነዋል። ባሁኑ ወቅት እምብርት ቀንደኛ ኢምፔሪያሊስት አገሮች በአፍሪካ የሞኖፖል ካፒታሊዝም ትግል እያካሄዱ ነው። እ.ኤ.አ. 1968 በአፍሪካ የነበረው የውጭ ካፒታል በዶላር የአሜሪካ 1477 ሚሊዮን፣ የእንግሊዝ 1408 ሚሊዮን፣ የፈረንሣይ 1295 ሚሊዮን ነበር። በ1960 ግን በየተራው 586.2 ሚሊዮን፣ 959.2 ሚሊዮን፣ 614.1 ሚሊዮን ነበር። በአሥር ዓመት ጊዜ ውስጥ የእንግሊዝ ካፒታል በአንድ ተኩል፣ የፈረንሣይ በእጥፍ የአሜሪካ ደግሞ በሦስት እጥፍ አድጓል። የአሜሪካ ሞኖፖሊዎች እስከ 1968 መጨረሻ ድረስ

ወደ አፍሪካ የሄዱት ካፒታል አሜሪካ በመላው ዓለም ከላከው ጠቅላላ ካፒታል አራት በመቶ ነበር ። እ.ኤ.አ. በ1960ዎቹ ከዚያ በፊትም የብሪታኒያና የፈረንሳይ ተጽእኖ ጠንካራ ስለነበር፣ የአሜሪካ ሞኖፖሎች የፈለጉትን ያህል ዶላር ለመመደብ ባይችሉ ቀርተዋል፤ ባሁኑ ወቅት ግን አፍሪካ ለሁሉም ክፍት ስለሆነ የአሜሪካን ሞኖፖል ካፒታል ድርሻ ከፍ ከፍ እያለ በመሄድ ላይ ይገኛል።

ከካናዳ፣ ከአውሮፓና ከላቲን አሜሪካ ጋር ሲመዛዘን የአሜሪካ ሞኖፖሎች ከአፍሪካ የሚያገኙት ትርፍ ጥቂት ነው የሚለው ወሬ መሠረት የለውም። ለምሳሌ እ.ኤ.አ. ከ1957 እስከ 1968 ባለው ጊዜ ውስጥ የአሜሪካን ሞኖፖሎች ከያንዳንዱ 100 ዶላር መዋዕለ ንዋያቸው ከካናዳ 6–8 ዶላር፣ ከምዕራብ አውሮፓ 6–14 ዶላር፣ ከአፍሪካ 26–31 ዶላር ትርፍ አግኝተዋል።

የአሜሪካን ሞኖፖሎች በይበልጥ ያተኮሩባቸው የአፍሪካ አገሮች ደቡብ አፍሪካ፣ ናይጄሪያ፣ ኬንያ፣ አይቮሪኮስት፣ ዛየር ወዘተ...ናቸው። ናይጄሪያ ነዳጅ ዘይት አምራች አገር በመሆኗ በርካታ የአሜሪካን ሞኖፖሎች በዚሁ መስክ ተካፋይ ሆነዋል። ቼይስ ማንሀተን ባንክ በተባለው የሮክፌለር ባንክ ጥገኛ ሆኖ የሚሠራው "አርክተርስ ኢንቨስትመንት ኢንዱ ዲቨሎፕመንት" የተባለው ድርጅት ከብዙ የናይጄሪያ የወርቃ ወርቅ ኢንዱስትሪዎች ጋር በፈናንስ ካፒታል በመቆላለፍ የሀገሪቱን የወርቃ ወርቅ ገበያ በከፊል በቁጥጥሩ ሥር አውሏል። እንዲሁም ከታላላቆቹ የትምባሆ ሞኖፖል ድርጅቶች አንዱ በመሆን "ፊሊፕሞሪስ" የተባለው የአሜሪካን ኩባንያ የትንባሆን ገበያ በመጠኑም ቢሆን ይዟል። "የፔፕሲኮላ" ድርጅትም በተወዳዳሪዎቹ ላይ የበላይነት በማግኘት የናይጄሪያን የለስላሳ መጠጦች ገበያ በቁጥጥሩ አውሏል።


በኬንያ ውስጥ ካለው የውጭ ካፒታል አርባ በመቶ የአሜሪካን ሞኖፖሎች ነው። "ኤሶ" እና "ካልቴክስ" የተባሉት ሁለቱ የአሜሪካን የነዳጅ ዘይት



ሞኖፖሊዎች ወደአፍሪካ በሚልኩት ካፒታል ለብዝበዛና ጭቆናው እጅግ መባባስ ያደረጉት አስተዋፅዖ
(ታዳጊ አገሮች ከማርክሳዊ ፖለቲካ ኢኮኖሚ አንፃር፣ በዩሪ ፖፖቭ)

proudly brought to you by

www.binyamhk.wordpress.com



ሞኖፖሎች ባንድነት ሆነው ለስከ ተወሰነ ጊዜ ድረስ በብቸኛነት ደረጃ ለኬንያ የነዳጅ ዘይት አቅራቢያች ሆነው ነበር:: ባሁኑ ወቅት ግን የሞኖፖል ኃይል ያላቸው "ሮያልዳች" እና "ሼል" የተባሉ የእንግሊዝና የሆላንድ የጋራ ድርጅቶች ናቸው:: ሌላው ትልቁ የአሜሪካን ሞኖፖል ድርጅት "ካሊፎርኒያ ፓኪንግ ኮርፖሬሽን" የተባለው ሲሆን በቆርቆሮ የታሸጉ የፍራ ፍሬ ምግቦችን በሰፊው እያዘጋጀ ያከፋፍላል፣ ወደ ውጭም ይልካል፣ የአሜሪካን ሞኖፖል ድርጅቶች የሚያስፈልጋቸውን የገንዘብ ካፒታል እያገኙ የአፍሪካን ንግድ በብቸኛነት እንዲይዙ የሚረዱዋቸው፣ በአህጉሩ በልዩ ልዩ ቦታ ቅርንጫፍ ያላቸው "ቼይስ ማንሀተን ባንክ"፣ "ፈርስት ናሽናል ሲቲ ባንክ፣" "ባንክ ኦፍ አሜሪካ" የተባሉ ታላላቅ ባንኮች ናቸው::

በእንግሊዝና በአሜሪካን ሞኖፖል ድርጅቶች ውስጥ ባለው መራራ ውድድር ባንኮች ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል:: ምንም እንኳን ከፍተኛ ካፒታል እያስገቡ ይዞታቸውን ለማስፋፋት ቢሞክሩም አፍሪካን በመበዝበዝ የበለጠ ልምድ ያላቸው የእንግሊዝ ባንኮች ናቸው:: ለምሳሌ ከ19ኛ ገዛት ዘመን ጀምሮ በአፍሪካ የሚገኙት የእንግሊዝ ባንኮች በትብብር በአፍሪካ ልዩ ባንኮች አቋቁመዋል:: "ሎይድስ ባንክ"፣ ናሽናል ዌስት ሚኒስተር ባንክ፣ በታንዳርድ ባንክ፣ በሕብረት ባንክ ኦፍ ዌስት አፍሪካን አቋቁመው በሱ አካባቢነት መላውን ምዕራብ አፍሪካ በቁጥጥራቸው ሥር አድርገው ነበር፣ በምሥራቅ አፍሪካ ደግሞ ባርክሌይስ፣ በታንዳርድ ባንክ ኦፍ ባውዝ አፍሪካ፣ ናሽናል እቨርቢስ ኤንድ ግሪንድ ሌይስ የተባሉት ባንኮች በሰፊ መረብ ዘርግተዋል:: /በነገራችን ላይ ከአብዮቱ ፍንዳታ በፊት አሁን ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ጋር የተቀሃደው "አዲስ አበባ ባንክ" በከፊል የናሽናል እቨርቢዝ ኤንድ ግሪንድሌይስ ባንክ ካፒታል ነበረበት::/

ምንም እንኳን መጠኑ የአሜሪካንና የእንግሊዝን ባያክልም የፈረንሣይ ሞኖፖል በተፈጠነ እርምጃ በአፍሪካ ውስጥ እየተስፋፋና እየተጠናከረ ነው::

ፈረንሣይ በአፍሪካ ካሉ ከቀድሞ ግዛቶቿ ጋር በኢኮኖሚ፣ በባሕልና በወታደራዊ ስምምነቶች በጥብቅ በለ ቆባበረች ሞኖፖል ካፒታሏን በተባሉ ለማስገባት ትችላለች። ከነዚህ አገሮች ጋር ባላት የተቀራረበ ግንኙነት ምክንያት ሌሎች ተወዳዳሪዎች እንዳይገቡበት ትጥራለች። ነገር ግን በአውሮፓ የጋራ ገበያ አማካይነት ሌሎች የአውሮፓና የአሜሪካም ካፒታል በፈረንሣይኛ ተናጋሪ አገሮች ውስጥ በብዛት እየገቡ ናቸው። እንዲያውም ፈረንሣይ በነዚህ አገሮች ላይ ያላትን አገባብ በመጠቀም በአሜሪካን ሞኖፖሎች ላይ በር የዘጋች እንደሆነ ካፒታሏን ወደ አሜሪካን እንዳታስገባ አርምጃ የማወሰድባት መሆኑን ከቀሽንግተን ማስጠንቀቂያ ስለ ቆበጧት ባትወድ ለቀቅ ማድረግ ተገደደች።

የፈረንሣይ ሞኖፖሎች በይበልጥ ያተኮሩበት የኢኮኖሚ መስክ ነዳጅ ዘይትና ማዕድን ነው። በመሆኑም እ.ኤ.አ. በ1969 ለነዳጅ ዘይት 2041 ሚሊዮን፣ ለማዕድን 130 ሚሊዮን ዶላር መድቦ ዋል። አንድ የፈረንሣይ የነዳጅ ዘይት ሞኖፖል በጋቦን የነዳጅ ምርት ላይ የተቆጣጣሪነት መብት አለው። ከዚህም ሌላ በአይቮሪኮስትና በሌሎችም የፈረንሣይኛ ቋንቋ ተናጋሪ አገሮች ያለው ጥቅም ከፍተኛ ነው። የጋቦን የብረትና የማንጋኒዝ ማዕድናት፣ የጊኒ ኮናክሪ ቦክሳይት ማዕድን፣ የማዕከላዊ አፍሪካ ዩራኒየም ማዕድናት፣ የሞሪታኒያ የብረት ማዕድን በብቸኛነት ወይም በብዛት በፈረንሣይ ሞኖፖል ካፒታል ቁጥጥር ሥር ነው። የፈረንሣይ ሞኖፖሎች በጋቦን የብረት ማዕድን ላይ ያላቸውን ብቸኛ ባለቤትነት በመጋፋት <u>ቤተልሔም በቷል እና ዩናይትድ በቴተስ በቷል</u> የተባሉ ሁለት የአሜሪካ የብረት ሞኖፖሎች ገብተው ከፍተኛ ውድድር በማድረግ ላይ ናቸው። በሞሪታኒያም የፌዴራል ጀርመን ሪፐብሊክ ሞኖፖሎች እየገቡ አገር መትከል ጀምረዋል። ፈረንሣይ ከቤልጅግ ጋር በመተባበር በዛኢር የማዕድን ኢንዱስትሪ ውስጥ ከፍ ያለ መቀዐለ ንዋይ መድባለች። <u>ኡኒዩን ሚኒየር</u> እና <u>ኮምፓኝዛራል</u> የተባሉት ሁለቱ የቤልጅግና የፈረንሣይ ሞኖፖሎች የዛኢርን የመዳብ ማዕድን ሀብት በብቸኛነት ይዘዋል። x

በአፍሪካ የአሜሪካና የአውሮፓ ሞኖፖል ካፒታል ዋና መናኸሪያ ደቡብ አፍሪካ ነው። ይህ አገር በማዕድን ሀብት በዓለም ውስጥ ልዩ ከታወቁት አገሮች አንዷ በመሆኗ ለአሜሪካ፣ ለፌዴራል ጀርመን ሪፐብሊክ፣ ለእንግሊዝ፣ ለፈረንሣይ ወዘተ... ሞኖፖሊች የማትነጥፍ ጥገት ሆናላቸዋለች። እ.ኤ.አ. እስከ 1978 የሁለቱ አዲስ የልዩ አዘር ቀኝ ገዢዎች ማለትም የአሜሪካና የጀርመን ፌዴራል ሪፐብሊክ ሞኖፖሊች ባንዴነት 20 ቢሊዮን ዶላር /15 አሜሪካ፣ 5 ጀርመን/ በደቡብ አፍሪካ የጦር መሣሪያ ፋብሪካዎችና ማዕድኖች ገንዘብ መድበዋል። ከጥንት ጀምሮ በደቡብ አፍሪካ ውስጥ ሥር ሰዶ የሚገኘው የእንግሊዝ ሞኖፖሊችም በሁሉም ወቅት ከአሜሪካ ያላነሰ መዋዕለ ንዋይ እንዳላቸው ይገመታል።

ጃፓን በኢኮኖሚዋ በኩል ከአሜሪካ ቀጥላ ሁለተኛዋ የካፒታሊስት አገር ናት። በዓለም ደረጃ ደግሞ ከአሜሪካና ከሶቪዬት ሕብረት ቀጥሎ ሦስተኛውን ቦታ ይዛ የምትገኝ ናት። በኢኮኖሚዋ ልዩ የደረጀች በመላው ዓለምም ከፍተኛ ሞኖፖል ካፒታል መረብ የዘረጋች መሆኗ ቢታወቅም በኢምፔሪያሊዝም ርዕስ ላይ ብዙ ጸሐፊዎችን ያበረከቱ ታላላቅ ሊቃውንት በፍፁም ችላ ብለውታል። በኤሌክትሮኒክስና የኤሌክትሪክ ዕቃዎች፣ በካሜራና የፎቶግራፍ ዕቃዎች፣ በመርከብ ግንባታ፣ በአቶሞቢል ሥራ ወዘተ... ጃፓን በዓለም አንደኛውን ቦታ ይዛ ትገኛለች። ለምሳሌ በ1980 መጨረሻ ጃፓን 12 ሚሊዮን ተሽከርካሪዎች በማምረት በዚህ የኢኮኖሚ ዘርፍ ሁለተኛውን ቦታ የያዘችው አሜሪካ 8 ሚሊዮን ብቻ ነበር ያመረተችው። በለዚህ ሞኖፖል ካፒታሏ እያበፋፋ በዓለም ላይ የልዩ አዘር ቀኝ አገዛዝን ከሚዘረጉት የኢምፔሪያሊስት አገሮች ውስጥ ጃፓን ቀደምት ቦታ ያላት አገር በመሆኗ በዚህ አጠቃላይ ዳሰሳ ውስጥ አስገብተናታል።

ጃፓን በአፍሪካ እምብዛም ድምጿ አይሰማም። በዚህ ክፍለ ዓለም ውስጥ ያሉት የሞኖፖል ካፒታል ይዞታዎች ከፍ ብለን ከተመለከትናቸው የኢምፔሪያሊስት

አገሮቱ ጥቅም ጋር ሲመዛዘኑ በጣም አነስተኛ ናቸው። የጃፓን ሞኖፖል ካፒታል በይበልጥ የገባው በሰሜን አሜሪካ፣ በላቲን አሜሪካ፣ በአውሮፓና በደቡብ ምሥራቅ እስያ ነው። በመጨረሻ የተጠቀሰውን ክፍል በይበልጥ በኢኮኖሚ ቁጥጥሯ ሥር በመያዝ ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በፊት የነበራትን የኢኮኖሚ የበላይነት እንደገና አስመልሳለች። እንደሚታወቀው የደቡባዊ ምሥራቅ እስያ " ያጠቃልዬ የምሥራቅ እስያ የጋራ ከበባ በሚል ድርጅት ውስጥ አሜሪካ በበላይነት ትመራው ነበር። ወደ ቀደመው ሥልጣኗ እንድትመለስ የረዱዋት ከጦርነቱ ወዲህ በሥራ ላይ ያዋለቻቸው ሁለት ፕሮግራሞች ነበሩ። እነዚህም 1/ በጦርነቱ ወቅት ላጠቃቻቸው አገሮች የጦር ካሣ መክፈልና፣ 2/ የኢኮኖሚክ እርዳታ የተባሉት ነበሩ። በጦር ካሣና በብድር ስም ጃፓን ለእስያ ደቡባዊ ምሥራቅ አገሮች በጠቅላላው 1,890,000 የአሜሪካ ዶላር ወጭ አድርጋለች። በ1970 መጨረሻ የጃፓን መንግሥት ባወጣው በስታቲስቲክስ መሠረት ለእነዚሁ አገሮቱ "በዕርዳታ ስም" 1,963,700 ዶላር ሰጥታለች። የጃፓን የጦር ካሣ፣ ብድር ወይም እርዳታ በቀጥታ የሞኖፖል ድርጅቶቿ መረባቸውን ለመዘርጋት ያወጡት መዋዕለ ንዋይ ነው። ይህንንም ሐቅ ባጭሩ ለማብራራት የቀድሞ የማሌዥያ ጠቅላይ ሚኒስትር ቱንኩ አብዱል ራህማን እንዲህ ብሏል። "ጃፓን በአንድ እጇ ብድር በጥታ በሌላው እጇ ግን የሰጠችውን ሁለት እጥፍ አድርጋ በረቂቅ ዘዴ ትወስዳለች።"

የጃፓን የሞኖፖል ካፒታል ተጠናክሮ በወራሪነት በደቡባዊ እስያና በሌሎችም ክፍለ ዓለሞች ውስጥ በብዛት ከመሰማራቱ በፊት በከፍተኛ ደረጃ የምርት መሰባሰብ ተደርጎ ነበር። በዚሁ መሠረት በልዩ ልዩ የኢኮኖሚ ዘርፎች ተበታትነው የነበሩ ኢንዱስትሪዎች ተሰባስበው ሞኖፖል እንዲፈጥሩ በተለይ በመንግሥት በኩል ግፊት ተደርጎ ስለነበር ታላላቅ ሞኖፖሎች ተፈጠሩ። በተለይም የብረት አቅላጭ፣ የአውቶሞቢል፣ የኮምፒዩተር፣ የኤሌክትሪክ ኢንዱስትሪዎችና ባንኮች ቁጥራቸው

ለያቢነቱ ካፒታላቸውን ከፍ በማድረግ ዘባበቡ:: ፉጂ እና ሂታቺ የተባሉት ድርጅቶች ተዋሕደው በታላቅነቱ በዓለም አንደኛ የሆነውን "ኒፖን ስቲል" የተባለ ሞኖፖል ድርጅት ፈጠሩ:: ቶዮታና ኒሳን የተባሉት ሁለቱ የተሽከርካሪ ፋብሪካዎች በብዙ ገበያዎች ላይ የጋራ ትብብር አላቸው:: ሚትሱቢሺ በኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ፣ በመርከብ ግንባታ፣ በተሽከርካሪና አይሮፕላን ሥራ ወዘተ... የተሰማራ ልዩ ልዩ ኢንዱስትሪያዎችን አሰባስቦ ራሱን የቻለ "ከመንግሥት ውስጥ ያለ መንግሥት" የሆነ ሞኖፖል ድርጅት ፈጠረ:: በኮምፒዩተር ዘርፍ ደግሞ /ጥቂቶችን ብቻ ለመጥቀስ/ "ኒፖን ኤሌክትሪክ" ቶሺባ "ፉጂትሱ ሂታቺ" ወዘተ... ታላላቅ ሞኖፖሎች ድርጅት ፈጥረው የእስያንና የብዙ አገሮችን ገበያዎች በቁጥጥራቸው ሥር አውለዋል:: ለነዚህን ድርጅቶች ሁሉ ከላይ ሆኖ ሥርዎታቸውንና ወረራቸውን የሚያቀናብርላቸው የፈናንስ ካፒታሉ መሪ "ባንክ ኦፍ ጃፓን" ነው:: ከዚህም በላይ ዋና ጽሕፈት ቤቱ በማኒላ ፊሊፒንስ ውስጥ የሆነውን የዓለም ባንክ ቅርንጫፍ የደቡባዊ እስያ ባንክን የሚመሩትና የሚበልጠውን ካፒታል የመደቡት የጃፓን ሞኖፖሎች ናቸው:: በዚሁ ባንክ በደቡባዊ እስያ ላይ ያላቸውን የሞኖፖል ገዢነት በበለጠ እንዲያጠናክሩ ረድቷቸዋል::

## 2.4 የሞኖፖሎች የገበያ ሽሚያ

ካፒታልን ወደ ውጭ በመላክ ያንዱ አገር ሞኖፖሊስቶች ባንዱ አገር ወይም ባንዱ አህጉር ፍፁም የበላይነት ኖሯቸው በብቸኛነት ለመበዝበዝ ይጥራሉ:: ይህንንም ዓላማ ተግባራዊ ለማድረግ የመንግሥታቸውን እርዳታ ይጠይቃሉ:: ከፍ ብለን እንደተመለከትነው የጃፓን መንግሥት በጦር ኃይልና በእርዳታ ስም ለደቡብ እስያ አገሮች ገንዘብ መስጠቱ ላገሩ ሞኖፖል ድርጅቶች ገበያ ለመክፈትና ሌሎች ተወዳዳሪዎችን አሸንፈው በብቸኛነት በእስያ ላይ እንዲነግሡ ለመርዳት ነበር::

መጀመሪያ ካፒታል፣ ቀጥሎ ሞኖፖል ድርጅቶችና ቀጥሎም መንግሥታት በግል አሰባሰብ ለየተሰማሩ ወረራቸውን ያፋጥማሉ፡፡ ሞኖፖል ድርጅቶች ገበያውን በብቸኛነት ይይዛሉ፡፡ መንግሥቱም የዚያን አገር የውስጥና የውጭ ፖለቲካ ከሞኖፖሎች ጥቅም አኳያ መቆጣጠር ይጀምራል፡፡ የለጀ አዘር ቀኝ አገዛዝ የሚባለው ከዚህ ብዙ የተለየ አይሆንም፡፡ በራሱ መንግሥት ጠባቂነት ሥር ሆነው በብቸኛነት የሚበዘበዙት የሞኖፖል ድርጅቶች የሌላ አገር ወይም የሌሎች አገሮች ሞኖፖሎች እንዳይገቡና ገበያውን እንዳይከፋፈሉ ይከላከላሉ፡፡ በልዩ ልዩ መንገድ ጥረትና ትግል ከተካሄደ በኋላ የጥቅም ድርድር ተደርጎ የሞኖፖሎች ስምምነት ይደረባል፡፡

አንድ ምሳሌ እንውሰድና ነገሩን በቅርብ ለማየት እንሞክር፣ ዩናይትድ ፍሩት የተባለው የፍራፍሬ መገቦችን በቆርቆሮ እያሸገ ለገበያ የሚያቀርብ አንድ የአሜሪካ ሞኖፖል ድርጅት አለ፡፡ ይህ ድርጅት በዚህ መስክ በታላቅነቱ በዓለም ተወዳዳሪ የሌለው ነው፡፡ በአሜሪካ የሚመረቱት አብዛኞቹ አሸግ ፍራፍሬ ምግቦችና መጠጦች የቡ ምርቶች ናቸው፡፡ ይህ ድርጅት ከአገሩ አልፎ በልዩ ልዩ አገሮች የሞኖፖል መረቡን ዘርግቷል፡፡ በተለይም በመካከለኛው አሜሪካ /ማለትም በኒካራጓ፣ ኤልሳልቫዶር፣ ጓቲማላ፣ ሆንዱራስ/ ይህ ድርጅት የፍራፍሬ እርሻዎችና የማሸጊያ ፋብሪካዎች በብዛት አሉት፡፡ በነዚህ አገሮች ያሉት የፍራፍሬ ተክሎች ሁሉ የዚሁ ድርጅት ንብረቶች ናቸው ለማለት ይቻላል፡፡ በአንዳፉም የዩናይትድ በቴትቦ ተጽእኖ በጣም ከፍ ያለ በመሆኑ የነዚህን አገሮች የብሔራዊ አርነት እንቅስቃሴዎች ሁሉ አፍኖ ይዟል፡፡ ለነዚህ አገሮች የዩናይትድ ፍሩት ክልል ግዛቶች በመሆናቸው ፍራፍሬን በማያስመለክት ረገድ የሌላ አገር ሞኖፖል ድርጅት ለመግባትና ለመነገድ አይችልም፡፡

በዚህ ዓይነት መንገድ ሞኖፖል ድርጅቶች የዓለምን ገበያ ተከፋፍለው ይይዙና አንዱ በሌላው ክልል ውስጥ እንዳይገባ ይከላከላሉ፣ ወይም በመካከላቸው ውለታ ይፈራረሙና አንዱ በሌላ ክልል ውስጥ እንዳይገባ ቃል ይገባል፡፡ ነገር ግን የአንዱ አገር የሞኖፖል ድርጅቶች በጣም ተጠናክረው

ተወዳዳሪ ገበያ በመፈለግ በሌላው ክልል ውስጥ ይገባሉ፣ በዚህ ጊዜ በካፒታሊስት አገሮች ውስጥ ያለው ቅራኔ ይከረራል፣ ወደ ግጭትም ሊያመራ ይችላል። በታሪክ ውስጥ አንደኛውና ሁለተኛው የዓለም ጦርነቶች በመባል የታወቁት የሞኖፖል ድርጅቶች ውድድር ያስከተላቸው ትግሎች ናቸው።

ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ ሞኖፖሎች ቅርጻቸውንና ይዘታቸውን እየለወጡ ልዩ መልክ ይዘው መምጣት ጀመሩ። እነዚህ አዳዲስ ሞኖፖሎች ትራንስናሽናልስ ይባላሉ። ትራንስናሽናልስ ከጥንቱ ዓይነት ሞኖፖሎች በስፋታቸው እጅግ የሚበልጡ ከመሆናቸውም በላይ የብዙ አገሮች ካፒታልም ያለባቸው ናቸው። ይህ ዓለም አቀፋዊ ባሕርያቸው ያላንዳች ገደብና ክልል በማናቸውም አገር እየገቡ የሞኖፖል መረባቸውን እንዲዘረጉ ይረዳቸዋል። ለምሳሌ ጄኔራል ሞተርስ የተባለውን የአሜሪካ የተሽከርካሪዎች አምራች ትራንስናሽናልን እንውሰድ። እርግጥ ይህ ድርጅት መሠረቱ በአሜሪካ ነው፣ ከካፒታሉም ይበልጡ የአሜሪካ ነው። ነገር ግን በእንግሊዝ፣ በጀርመን፣ በቤልጂግ፣ በስፓኝ፣ በአውስትራሊያ፣ በብራዚል፣ በጃፓንና በሌሎችም ብዙ አገሮች ፋብሪካዎች አቋቁሞ ተሽከርካሪዎችና ሌሎችም ዕቃዎች ያመርታል። በነዚህ አገሮች የተቋቋሙት ፋብሪካዎች በአሜሪካን ካፒታል ብቻ ሣይሆን ከአስተናጋጆቹ አገሮች ባንኮችና ግለሰቦችም ካፒታል ጭምር ነው፤ በዚህ ምክንያት ጄኔራል ሞተርስ እንደ ባዕድ ድርጅት ባይቆጠር በአስተናጋጅ አገሮች እንደፈለገው ሊነግድና ትርፉን እንዳሻው ወደ አሜሪካ ለማዛወር መብት አለው።

የትራንስናሽናልስ መከሰት በኢምፔሪያሊስት አገሮች መካከል የነበረው ውድድር ተቀንሶ በጋራ ዓለምን እንዲበዘብዙ ረድቷል። ትራንስናሽናሎች በካፒታሊስት አገሮች ውስጥ በከፍተኛ ደረጃ የሚደረገው የምርት መሰባሰብ ውጤት ናቸው። ይህ አዲስ ክስተት የሞኖፖል ድርጅቶች ብቻኛ ጥረት ሣይሆን የመንግሥቶቻቸውም ጭምር ነው። ትራንስናሽናሎች ከመንግሥቶቻቸው ተጽእኖ

ነፃ አይደሉም። የመንግሥታቸው ካፒታል አለባቸው፤ ለመንግሥታቸው ቀረጥ መክፈል አለባቸው፤ የመንግሥታቸውን ፖሊሲ መከተል አለባቸው፤ የመንግሥታቸውንም ጥበቃ ማግኘት አለባቸው። በዚህ ምክንያት ትራንስናሽናል ከመንግሥቶቻቸው ጋር የፈጠሩት ሞኖፖሊ <u>የመንግሥታት ሞኖፖሊ</u> ሊባል ይችላል። የሞኖፖሊ ድርጅቶቻቸውን ገበያ ለማስፋፋትና ድርጅቶቹንም ለማጠናከር ሲሉ መንግሥታት ካፒታላቸውን አሰባስበው ታላላቅ ድርጅቶችን ፈጠሩ፤ <u>የጋራ ገበያም</u> መሠረቱ። የአውሮፓ የጋራ ገበያ፤ የአውሮፓ የነፃ ንግድ ልውውጥ ክልል/ኤፍታ/ የተባሉት ክልሎች በመንግሥታት መካከል የተደረጉ የሞኖፖል ስምምነቶች ውጤቶች ናቸው።

## 2.5 <u>ኢምፔሪያሊስቶች ዓለምን ለመቀራመት የሚያደርጉት ትግል</u>

ከሞኖፖል ካፒታል ባሕርዮች አንዱ የካፒታሊስት አገሮች ዓለምን ተከፋፍለው በቁጥጥራቸው ሥር ለማድረግ የሚያደርጉት ጥረት ነው። የሞኖፖል ካፒታሊዝም እጅግ የተስፋፋባቸው አገሮች ማለትም እንግሊዝ፤ ፈረንሣይ፤ አሜሪካ፤ ጀርመንና ጃፓን እ.ኤ.አ. ከ1870 እስከ 1914 ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ ከ25 ሚሊዮን ኪሎ ሜትር ያላነሰ ስፋት ያላቸው አገሮች በመላው ዓለም በተለይም በእስያና በአፍሪካ በቅኝ ግዛት ያዙ። ሌሎችም ታናናሽ አገሮች ማለትም ቤልጅግ፤ ሆላንድ፤ ፖርቱጋልና እስፓኝም ይዘው ነበር። እስከ አንደኛው የዓለም ጦርነት ዋዜማ ማለት በ1914 ዓለም በዚህ ዓይነት በኮሉኒያሊስቶች ተቀራምታ ነበር።

በዚህ ወቅት ውስጥ በካፒታሊስት አገሮች መካከል የተፋፋመ ውድድር ተነስቶ ዓለምን እንደገና የመቀራመት ግፊት አስከተለ። የመጀመሪያው የዓለም ጦርነት የተከፈተው ዓለምን እንደገና ለመቀራመት የተደረገውን ግፊት ተግባራዊ ለማድረግ ነበር።

ከአንደኛው የዓለም ጦርነት በኋላ በካፒታሊስት አገሮች ውስጥ የፋሽዝም ኃይል እያቆጠቆጠ መጥቶ እንደገና ዓለምን ለመቀራመት የሚደረገው ግፊት ተጠናከሮ ተጀመረ። ፋሺዝም በጀርመን፣ በኢጣልያ፣ በጃፓን፣ በስፓኝ ወዘተ... ተነስቶ የመንግሥት ሥልጣን ወሰደ። ፋሺዝም አዲሱን የዓለም ቅርምት ተግባራዊ ለማድረግ በወሰደው እርምጃ መሠረት ፋሺስት ኢጣልያ ኢትዮጵያን ወረረች፣ ጃፓን ማንቹሪያን ያዘች፤ የጀርመን ፋሺዝም ኦስትሪያን፣ ቼኮዝሎቫኪያን ወዘተ... ያዘ። በዚሁ ሣቢያ ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ፈንድቶ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠር የሰው ሕይወት አለፈ፤ በብዙ ቢሊዮን ዶላር የሚገመት ንብረትም ወደመ።

ኢምፔሪያሊዝም ሁለተኛውን የዓለም ጦርነት በመቀስቀስ የታሪክን ሂደት ወደ ኋላ ለመመለስ ያደረገው ጥረት ባይሳካለት ቀርቷል። ይህንን ጥረት ያከሸፉት የሶቪየት ሕብረትና የዓለም ፀረ ፋሺስትና ፀረ ኢምፔሪያሊስት ኃይሎች ናቸው። በፀረ ፋሺስቱ ትግል ውስጥ የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል።

ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ የካፒታሊስት አገሮች በአፍሪካና በእስያ፣ በካሪቢያን አገሮችም የመሠረቷቸው ቅኝ አገሮች ነፃነታቸውን ተቀዳጁ። በአንፃሩም የካፒታሊዝም ኃይል እየተዳከመ የሶሻሊዝም ዕድገት እየተፋጠነ መጣ። የቅኝ ግዛት ሥርዓት ምን ማለት እንደሆነ ለካፒታሊስት አገሮችም ምን ጥቅም እንዳመጣላቸው ተገዢ ሕዝቦችም ምን ጉዳት እንደደረሰባቸው ግልጽ በመሆኑ እዚህ ላይ በሰፊ ያለ ትንታኔ ማቅረብ አስፈላጊ አይደለም። ይሁን እንጂ ከቅኝ አገዛዝ ነፃ የወጡ አገሮች ገዢዎቻቸው ዘርግተውባቸው የሄዱትን የኢኮኖሚና የፖለቲካ ሥርዓት ውርስ በሙሉ አፈራርሰው በምትኩ የሕዝባቸውን እውነተኛ ፍላጎት የሚያንፀባርቅ

አዲስ ሥርዓት በመዘርጋት ረገድ አሁንም ቢሆን ከፍተኛ ጥረት በማድረግ ላይ ናቸው። ብዙዎቹን አዲስ አገሮች የቀድሞ ገዢዎቻቸው የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ቀንበር ጫነውባቸው ባዲስ መልክ ሊያበዘብዙአቸው ነው።

ይሁን እንጂ አብዛኞቹ ብሔራዊ ነፃነታቸውን የተጎናፀፉ፣ የተፈጥሮ ሀብታቸው ባለቤት ለመሆን ያላቸውን መብት ለማስከበርና ከኢምፔሪያሊዝም የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ለመላቀቅ ከፍተኛ ትግል በማካሄድ ላይ ናቸው። ይህም ትግል ለኢምፔሪያሊዝም ወይም ለሞኖፖል ካፒታሊዝም መዳከም አስተዋጽኦ አድርጓል። ከዚህም ሌላ ለኢምፔሪያሊዝም መዳከም ዋነኛ ምክንያት የሆኑት ከዚህ በታች የተዘረዘሩት የውስጥና የውጭ ምክንያቶች ናቸው።

ሀ. <u>የውስጥ ምክንያቶች</u>

1. በሞኖፖል ሥርዓት ነፃ ውድድር ባለመኖሩ ሞኖፖሎች የዋጋ መወሰን ኃይል ስላላቸው የፍጆታ ዕቃዎች ወይም መሣሪያዎች ጥራታቸው አጥጋቢ ባይሆንም ሁልጊዜ ገዢ አላቸው። በመሆኑም ሞኖፖሎች ጥቅማቸው እስካልተጓደለባቸው ድረስ አዳዲስ ብልሃቶችንና ግኝቶችን የኢንዱስትሪን ቀልጥፍና ከፍ ለማድረግ ለሚጠቀሙ ዘዴዎች አምብዛም ጥረት አያደርጉም። በሌላ ሥፍራ እንደተገለጸው ይህ አድኃሪ ዝንባሌያቸውና ድርጊታቸው የሳይንስና የቴክኖሎጂን ዕድገት ያቆረቁዛል።

2. የገንዘብ ካፒታል ወደ ውጭ አገር ልኮ በሥራ ላይ ማዋል የኢምፔሪያሊዝም መስፋፋት በትራተኛ አንዱ ዘርፍ ነው። በየባንኮች ተቀማጭ ያላቸው የገንዘብ ባለቤቶች ወይም የኩባንያ ባለ አክሲዮኖች ግለሰቦች ናቸው። አክሲዮኖቹ በያመቱ ከፍተኛ

ትርፍ በለማያመጣላቸው ባይሠሩ ባይደክሙ "ተቀ/ጋቢ" ሆነው ይኖራሉ:: የተቀላቢነቱም ኑሮ ሌሎች በያችን በተውጣሪ ሊየባበ ይሄዳና ይህ ሁኔታ አገሪን ራሱን "ተቀላቢ" ያደርገዋል::

እነዚህ ሁኔታዎች በኢምፔሪያሊስት አገሮች ባንድ በኩል ተቀላቢዎች በየጊዜው እየበለጸጉ እንዲሄዱ፣ ቢያደርጉ በሌላ በኩል በሠርቶአደሩ ሕዝብ ዘንድ ደግሞ ሥራ አጥነትና አንፃራዊ ድኅነት እየበረከተ እንዲሄድ ምክንያት በለማሆኑ በኅብረተሰቡ ውስጥ የነበረውን የመደብ ቅራኔ በበለጠ እንዲፋፋም ያደርጉታል:: ኢምፔሪያሊዝም ቅራኔውን በመጠኑም ቢሆን ገብ ለማድረግ ከሠርቶአደሩ ወገኖች አንዳንዶቹ የጥቅሙ ተቋዳሾች እንዲሆኑ ጥረት ያደርጋል:: ለርግጥ ይህ በሠርቶአደሩ ዘንድ አድርባይነትን በማስፋፋት ለጊዜው ውጥረቱን ረገብ ያረገው በመስለም፣ የኋላ ኋላ ግን ሁኔታው እየተባባሰ ይሄዱና ፍንዳታ ደረጃ ላይ መድረሱ የማይቀር 'ሀ ታሪክ ጠቀ ነው::

ሀ. <u>የውጭ ምክንያቶች</u>

1. ለኢምፔሪያሊዝም መዳከምና ማቆልቆል የሶሻሊዝም ድል አድራጊነት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው:: ታላቁ የጥቅምት ሶሻሊስት አብዮት ድል በማድረጉ በዓለም ታሪክ የመጀመሪያው የሶሻሊስት ሥርዓት በሶቪዬት ሕብረት ተወለደ:: በጥቅምት አብዮት አነባሽ ኃይል አማካይነት ብዙ አገሮች የሶሻሊስት ሥርዓት ማኅበርን መከተል ጀመሩ:: በስልሣ ዓመት ጊዜ ውስጥ ከዓለም ሕዝብ ቢሶው የሶሻሊዝምነት ሥርዓት ተከታይ መሆኑ ለኢምፔሪያሊዝም መዳከም ዐቢይ ምክንያት ነው::

2. የብሔራዊ አርነት ኃይሎች በሶሻሊስት አገሮች ዐሪ ኢምፔሪያሊስት አጋርነት በመደገፍ የሚያደርጉት ትግል ለኢም

የነበሩ አንድነት [illegible]

በሕዝብ [illegible]

በኢምፔሪያሊስት አገሮች [illegible]

[illegible] ፀረ ኢምፔሪያሊስት [illegible]

[illegible] በሰው [illegible]

[illegible]



ፔሪያሊዝም መዳከም ለላው ተጨማሪ ምክንያት ሆኗል፡፡ ከብሔራዊ አርነት ነፃና ቹ ሀገሮች አንዳንዶቹም የሶሻሊስት የእድገት ፈርን በመከተል የሚያካሄዱት ፀረ የአሙ አዛዥ ቀኝ አገዛዝ ትግል ኢምፔሪያሊዝምን በማዳከሙ ረገድ ከፍተኛ ሚና በመጫወት ላይ ይገኛል፡፡

፫. የዓለም ወዛደሮች እንቅስቃሴና የዓለም የዲሞክራሲና የሰላም ኃይሎች ከፍ ብሎ ከተጠናከሩት ጋር የትግል አንድነታቸውን በማጠናከር በኢምፔሪያሊዝም ላይ ከፍ ያለ ግፊት እያደረጉ ነው፡፡ የኃያላቀ ካፒታሊስት አገሮች ወዛደሮች በየበኩላቸው የሚያደርሱባቸውን የሞኖፖል ካፒታሊዝምን ብዝበዛ ለመቋቋም ከሚያ ርጉት ትግል ባሻገር ከመደብ አጋሮቻቸው ከሆኑት ከሶሻሊስት አገሮችና ከሌሎች አገሮች ሠራተኞች ጋር ሆነው የጋራ ፀረ ኢምፔሪያሊስት ትግል እያካሄዱ ነው፡፡ በ1920ዎቹ በሶቪዬት ሕብረት በኢምፔሪያሊስት ከበባ ውስጥ በነበረችበት ወቅት "ከሶቪዬት ሕብረት ላይ እጃችሁን አንሱ" በሚለው መፈክር ዙሪያ በመሰባሰብ ከፍ ያለ ዓለም አቀፋዊ ትግል አካሂደዋል፡፡ የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም የቬትናምን ሰላማዊ ሕዝብ እየጨፈጨፈ ከፍተኛ ሕዝባዊ እልቂት ባስከተለበት ወቅት የዓለም ወዛደሮች የዲሞክራቲክና የሰላም ኃይሎች በአንድነት ሆነው፣ በአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ላይ ያደረጉት ከፍተኛ ግፊት ኢምፔሪያሊዝም ሽንፈት ደርሶበት ከቬትናም እንዲወጣ ካደረጉት ምክንያቶች አንዱ ነበር፡፡ የኢትዮጵያ አብዮትም በኢምፔሪያሊዝምና በአድኃሪት ኃይሎች ቀንጆት አደገኛ ግፊት በደረሰበት ወቅት የሰላምና የዲሞክራቲክ ኃይሎች ከኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ጋር ያላቸውን

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

proudly brought to you by

www.binyamhk.wordpress.com



## ጥ ያ ቄ ዎ ች

1. ሁለተኛውን የኢንዱስትሪ አብዮት ከአንደኛው ልዩ የሚያደርገው ምንድነው?
2. በሞኖፖል ካፒታሊዝምና በኢምፔሪያሊዝም መካከል ያለውን ግንኙነት ዝርዝር ባለ ሁኔታ አስረዳ ::
3. ፊናንስ ካፒታል ምን ማለት ነው? አመጣጡስ እንዴት ነው?
4. የሞኖፖል ካፒታልን ዋና ዋና ባሕርዮች ዝርዝር ::
5. የምርት መሰባሰብን ባሁኑ ወቅት እንዲጠናከር የሚያደርገው ምንድነው?
6. በግሬኝና በሲንዲኬት መካከል ያለውን ልዩነት አብራራ ::
7. ተቀሳቢ የተባለውን ጽንሰሃሳብ አብራራ ::
8. ለኢምፔሪያሊዝም መዳከም ምክንያት የሆኑት የውጭ ምክንያቶች ምንድን ናቸው?
9. ከኢንዱስትሪ ካፒታሊዝም በፊት በአፍሪካና በእስያ የነበሩትን "ቅኝ አገሮች" የንግድ ጣቢያዎች እንጂ በእርግጥ ቅኝ አገሮች ናቸው የማንልበት ለምንድነው?
10. የፊናንስ መሣፍንት ይህን መጠሪያ ለምን አገኙ? በሞኖፖል ካፒታሊዝም የሚጫወቱትን ሚና አስረዳ ::
11. ባንኮች በሞኖፖል ካፒታሊዝም ላይ የነበራቸውን ብቸኛ ሥልጣን የተጋሩዋቸውን አዳዲስ ክስተቶች ዝርዝር ::
12. በውጭ ንግድ ዘርፍ የብዝበዛ መጠን የሚለካበት ዘዴ ምን ይባላል? ባገራችን ምሳሌ አስረዳ ::
13. የጃፓን ሞኖፖል ካፒታል በደቡብ ምሥራቅ እስያ እንዴት ሊገባ እንደቻለ አስረዳ ::
14. በቀደመ አብዮት ኢትዮጵያ የነበሩትን የውጭ አገር ሞኖፖል ድርጅቶች ዝርዝር :: የተሰማሩትስ በየትኛው ዘርፎች ነበር?
15. በአፍሪካ አህጉር የተሰማሩት የሞኖፖል ድርጅቶች ከየትኛው ኢምፔሪያሊስት አገሮች ናቸው? ድርጊታቸውንና የተሰማሩበትን ዘርፍ ዝርዝር በማድረግ አስረዳ ::

## ቃ ላ ት

| | |
|---|---|
| 1. አክሲዮን | Share |
| 2. አቶሜሽን | Automation |
| 3. የባንክ የበላይነት | Bancocracy |
| 4. ኮምፒዩተር | Computer |
| 5. ኮንግሎሜሬት | Conglomerate |
| 6. ሳይበርኔቲክስ | Cybernetics |
| 7. ውስጠ ነደድ ሞተር | Internal Combustion Engine |
| 8. ናፍታ ጠጥ ሞተር | Diesel Engine |
| 9. የንግድ ወኪል | Factor |
| 10. የንግድ ጣቢያ | Factory |
| 11. ፋሺዝም | Fascism |
| 12. የፋይናንስ መሣፍንት | Financial Oligarchs |
| 13. የፋይናንስ መስፍንነት | Financial Oligarchy |
| 14. ሆልዲንግ | Holding |
| 15. ፓቴንት | Patent |
| 16. ተቀባቢ | Rentier |
| 17. የእንፋሎት ሞተር | Steam Engine |
| 18. ትራንስናሽናልስ | Transnationals |
| 19. ካርቴል | Cartel |
| 20. ሲንዲኬት | Syndicate |
| 21. ትረስት | Trust |
| 22. ግሩፕ | Group |
| 23. የካፒታል ልከት | Capital Export |
| 24. የአርነት ንቅናቄ | National Liberation Movement |

## ምዕራፍ 8

# በታሪክ የኢምፔሪያሊዝም ሥፍራ

## 1. ሦስቱ ጣምራ የኢምፔሪያሊዝም ልዩ ባሕርያት

ሌኒን የኢምፔሪያሊዝምን ሙሉና ቀጥተኛ ትርጓሜ ሲሰጥ "ኢምፔሪያሊዝም የካፒታሊዝም ከፍተኛውና የመጨረሻው የዕድገት ደረጃ ነው" ብሎታል። ካፒታሊዝም የተወሰነ ዕድገት ደረጃ ላይ ሲደርስ ኢምፔሪያሊዝም ይከሰታል። ኢምፔሪያሊዝም የካፒታሊዝም ልዩ ታሪካዊ የዕድገት ደረጃ ነው።

ኢምፔሪያሊዝም በራሱ የተለየ ስልተምርት ወይም ሥርዓተ ማኅበር ባይሆን የካፒታሊዝምን የተለየና ከፍተኛ የዕድገት ገጽታ የሚያንፀባርቅ ክስተት ነው። ከ1870 በፊት ካፒታሊዝም በነፃ ፉክክር ሕግ የሚሠራና የሚመራ በብዛት መጠነኛና መካከለኛ ካፒታሊስቶችን ያቀፈ ነበር። ከዚያ በኋላ ግን በነፃው ውድድር ሕግ ጥቂቶች ብዙኃኑን እየዋጡ ወደ ሞኖፖል ደረጃ አደገ። በዚህ ዓይነት በ19ኛው ምዕተ ዓመት መጨረሻና በ20ኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ ላይ ካፒታሊዝም ከነፃ ውድድር ወደ ሞኖፖል የሚያደርገውን ሽግግር በመጨረስ ወደኢምፔሪያሊዝም ደረጃ ደረሰ። ካፒታሊዝም አድጌ ኢምፔሪያሊዝም ደረጃ ሲደርስ ነፃ ውድድር ተዳክሞ የኢኮኖሚው መሠረት ሞኖፖል ሆነ። በኢምፔሪያሊስት አገሮች የብሔራዊ ሀብት አንቀሳ ቃሾች፣ ማኅበራዊ ምርትና የኅብረተሰብ ሀብት በጥቂት የሞኖፖል ካፒታሊስቶች ቁጥጥር ሥር ዋለ። ጥቂት ሞኖፖል ካፒታሊስቶች ኢኮኖሚውን በቁጥጥራቸው ሥር ማዋል ብቻ ሣይሆን የመንግሥትን የፖለቲካ ሥልጣንና ሌሎችንም የላዕላይ መዋቅር ዘርፎች ይቆጣጠሩ ጀመር። በዘመነ ኢምፔሪያሊዝም የወዝአደሩና የሰፊው ሠራተኛ ሕዝብ የኑሮ ሁኔታ እያቆለቆለ ሲመጣ በሞኖፖሊስቶችና /በዝባዦች/ በሠርቶአደሩ ሕዝብ /ተበዝባዦች/ መካከል ያለው ቅራኔ ይበልጥ እየተካረረ ሄደ። ይህም ለሶሺያሊስት አብዮት አመቺ ሁኔታ እየፈጠረ መጣ።

ኢምፔሪያሊዝም ልዩና የተወሰነ የካፒታሊዝም ዕድገት ደረጃ ነው በኋላ የሚኖሩትን ልዩ ባሕርያት መገንዘብ አስፈላጊ ይሆናል። ኢምፔሪያሊዝም ሦስት መሠረታዊ መለያ ባሕርያት አሉት። እነሱም፦ 1. ኢምፔሪያሊዝም ሞኖፖል ካፒታሊዝም መሆኑ፣ 2. ኢምፔሪያሊዝም የሸገተ ካፒታሊዝም መሆኑ፣ 3. ኢምፔሪያሊዝም ያረጀ ወይም የሚሞት ካፒታሊዝም መሆኑ ናቸው። እነዚህ ልዩና መሠረታዊ የኢምፔሪያሊዝም ባሕርያት ወደፊት ዝርዝር ብለው ይቀርባሉ።

ታላቁ የወዝአደሩ መሪ ሌኒን እንዳመለከተው ኢምፔሪያሊዝም በኢኮኖሚ ገጽታው ዐበይት የሆኑ የራሱ መለያዎች አሉት። እነዚህንም መለያዎችን በጥሩና ገምግሞ መረዳት የኢምፔሪያሊዝምን ታሪካዊ ሥፍራ ለማወቅ ያስችላል። እነዚህ አራት ዐበይት የኢምፔሪያሊዝም መለያዎች በአንዱ ካፒታሊስት አገር ቢታዩ ያ አገር ኢምፔሪያሊስት ደረጃ ደርሷል ለማለት ይቻላል።

## 2. በኢኮኖሚ ገጽታው የኢምፔሪያሊዝም አራት መሠረታዊ መለያዎች

1. ምርትና የካፒታል ክምችት ከመጠን በላይ ከማደጉ የተነሣ የማምረትና የማከፋፈል ተግባሮች በጥቂት ሞኖፖሊስቶች ቁጥጥር ሥር ይወድቃሉ።

2. የኢንዱስትሪ በሞኖፖሊስቶች ቁጥጥር ሥር መዋል የጥሬ ዕቃዎችንም በሞኖፖል መያዝን ያስከትላል። ለምርት ተግባር መሠረታዊ ናቸው የሚባሉት ማለትም ብረታ ብረት፣ የኃይል ምንጮች፣ የነዳጅ ማጣሪያዎች፣ የመገናኛ አውታሮች ወዘተ... በሞኖፖሊስቶች ቁጥጥር ሥር ቢውሉ በጥሬ ዕቃዎች ላይ የሞኖፖሊስቶች ይዞታ ቁጥጥር ሥር ቢውሉ... እየጠነከረ ይሄዳል።

3. በዘመነ ኢምፔሪያሊዝም የገንዘብና የባንክ ተቋሞች ተሰባስበውና ተማክለው በሞኖፖሊስቶች ቁጥጥር ሥር ቢውሉና የባንክና የኢንዱስትሪ ሞኖፖሊስቶች ኅብረት በመፈረትና በወባበቡ ኢኮኖሚውንና ፖለቲካውን የሚቆጣጠሩ የፋይናንስ ካፒታሊስቶች ብቅ ይላሉ::

4. ሞኖፖሊ፣ኢምፔሪያሊስት አገሮች ዓለምን በቀኝ አገዛዝ ሥር ለማዋል ከቀየሱት ፖሊሲ ጋር የተያያዘ ቢሆን፣ በዘመነ ኢምፔሪያሊዝም ዓለምን በቀኝ አገዛዝ ሥር ማዋልና በተለይም ዓለምን እንደገና ለመከፋፈል ወይም ለመቀራመት ከባድ ትግል ይካሄዳል።

ከዚህ በላይ በተመለከቱት ሁኔታዎች ሞኖፖሊ እያደገ ቢሄድ፣ ሞኖፖሊስቶች ይበልጥ በመንግሥት መዋቅር ይጠቀማሉ። በመንግሥታዊ መዋቅር ውስጥ ቁልፍና ወሣኝ ሥፍራዎችን በመያዝ የፖለቲካውንና የኢኮኖሚውን ለንቀበያቡ ይቆጣጠራሉ። በዚህም ጥቅማቸውን ይበልጥ ያዳብራሉ:: ሞኖፖሊስቶች በዚህን ወቅት በመንግሥታዊ መዋቅር ውስጥ ከፍተኛና ወሣኝ የሥልጣን ሥፍራዎችን በለሚይዙ ሞኖፖሊስቶችን ከመንግሥት ነጥሎ ለማየት ያስቸግራል። መንግሥቱ ማለት ሞኖፖሊስቶች፣ ሞኖፖሊስቶች ማለት መንግሥት ማለት ከሚሆንበት ደረጃ ላይ ይደረባል። ስለዚህ በዘመነ ኢምፔሪያሊዝም በካፒታሊስት አገሮች መንግሥትና ሞኖፖሊስቶች የአንድ ሣንቲም ሁለት ገጽታዎች ይሆናሉ። ሞኖፖሊስቶች ወዝአደሩን ለጥ በጥ አድርጎ ለመበዝበዝ የሚያስችሏቸው ልዩ ልዩ ሕጎች በመንግሥት አማካይነት ያወጣሉ፣ በሬውን ሠርቶአደር ሕዝብ ለችግር በመዳረግ ያለ ገደብ በሚያጋብቡት ትርፍ አነርቤ ግን የተንደላቀቀ ሕይወት ይኖራሉ።

ካፒታሊዝም ወደ ከፍተኛው ዕድገት ደረጃ ማለትም ወደ ኢምፔሪያሊዝም ሲሸ ጋገር ወቀባሳ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ሕጎች ይለወጣሉ ወይም መሠረታዊ ለውጥ ያስከትላሉ ማለት አይደለም። እንዲያውም ሞኖፖሊ ካፒታሊዝም በቀዳሙ ሞኖፖሊ ካፒታ ሊዝም ላይ የተገነባ /የነፃ ፉክክር/ ላዕላይ መዋቅር ነው ለማለት ይቻላል።

"ንፁህ ካፒታሊዝም" ሲኖር እንደአለመቻሉ ሁሉ "ንፁህ ኢምፔሪያሊዝም" ሊታሰብ አይችልም። ይበልጥ ለማብራራት እንሞክራለን። ሞኖፖሊ ካፒታሊዝም በጣም ተስፋፍቶ ብዙ የማምረቻና የንግድ ድርጅቶች በጥቂት ሞኖፖሊስቶች ይዞታ ሥር በወደቁበት ካፒታሊስት አገሮች ውስጥ ጥቃቅን የማምረቻ ድርጅቶች በግል ካፒታሊስቶች የተያዙ በብዛት ይገኛሉ። እነዚህ ጥቃቅንና መለስተኛ የማምረቻ ድርጅቶች ግዙፍ ከሆኑ በሞኖፖል ከተያዙ ድርጅቶች ጐን ለጐን ይገኛሉ። ይሁን እንጂ እነዚህ ጥቃቅን ድርጅቶች ከሞኖፖሊስቶች ጋር ለመወዳደር አቅም በለሚያንሳቸው በየጊዜው እየተዳከሙ በመምጣት ጥገኛ ይሆናሉ እንጂ ሞኖፖሊ መለስተኛ የማምረቻ ድርጅቶችን ሙሉ በሙሉ ሊያጠፋ አይችልም። ይህ ሁኔታ እንግዲህ የሚያስረዳን በቀደም ኢምፔሪያሊዝም የነበሩ መለስተኛ የማምረቻ ድርጅቶች በሞኖፖሊ ካፒታሊዝም ውስጥም ለመኖር መቻላቸው ኢምፔሪያሊዝም የካፒታሊዝምን መሠረቶች ሙሉ በሙሉ ሊያጠፋ አማይችል መሆኑን ያረጋግጣሉ።


ሌላው ማስረጃ ደግሞ ኢምፔሪያሊዝም ዕድገት ደረጃ በደረሱ ካፒታሊስት አገሮች ብዛታቸው በትንሹ የማይገመት በቀላል የሸቀጥ ምርት ላይ የተሰማሩ ገበሬዎች መኖራቸው ነው። ሞኖፖሊስቶች የኢንዱስትሪ፣ የፋይናንስ፣ የእርሻና እንዲሁም ሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎችን ለማጠቃለልና ወይም ለሙቆጥ የተቻላቸውን ያህል ጥረት ቢያደርጉም በእርሻው የኢኮኖሚ ዘርፍ በግል የሚያመርቱትን ገበሬዎች ሙሉ በሙሉ ለማፈናቀልና በእነሱ ቁጥጥር ሥር ለማዋል አልቻሉም። በከፍተኛ ደረጃ ሞኖፖሊስቶች ተጠናክረው በሚገኙባቸው ካፒታሊስት አገሮች ለምሳሌ በአሜሪካ፣ በእንግሊዝ፣ በፈረንሣይ፣ ወዘተ... ብዙ ገበሬዎች በቀላል የሸቀጥ ምርት ላይ ተሰማርተው የሚገኙ እንደመሆናቸው ፉክክር አለ ማለት ነው። ፉክክር ወይም ውድድር እስካለ ድረስ ደግሞ ሞኖፖሊ ካፒታሊዝም ከገበያ፣ ከውድድርና ከኢኮኖሚ ቀውስ ነፃ ሊሆን አይችልም። የካፒታሊዝም የኢኮኖሚ ሕጎች ለምሳሌ፣ የእሴትና የተረፈ እሴት ሕጎች፣ የውድድርና የሥርዓቱ አልባ አመራረት ሕጎች በሙሉ በዘመነ ኢምፔሪያሊዝም ይሠራሉ።

[illegible] የወዛአደሮችና የባቄተኛን
[illegible] ይደረግ ነበር። በበዘበዥና
[illegible] ለማሟላት ይቻላል።

[illegible] በከፍተኛ ደረጃ ማኅበራዊ [illegible]

[illegible] ሠራተኞችን በማጥቃትና በቁ
[illegible] በመጠን፤ የምርትን ብዛትና
[illegible] [illegible]፣ ፋርዱ፣
[illegible] የሚቶጠሩ ሠራተኞች
[illegible] ከኅብረተሰቡ አጠቃላይ ምርት
[illegible] የአብዮታዊና የፖለቲካ ኃይል
[illegible] የተጣሩትን ፀርጁቶችና ባይነቱ
[illegible] አዳዲስ ፋብሪካዎችንና የተሻሻሉ
[illegible] ድርጅቶች ብዙዎችን ብዛ
[illegible] በተቀናቃኞቹ ጋር ያወሳሉ።


[illegible] በመጨ የሰነዱ
[illegible] ከለላው የአብዮታዊ ዘርፍ
[illegible] የኅብረተሰቡ
[illegible] መግባት ወደ
[illegible] ጋር የሚገኙት የማምረቻ
[illegible] ይወጣል። የአመራረት
[illegible] ለማምረት በብዛ
[illegible] ይህ ሁኔታ
[illegible] የማምረት ተግባርን



የሞኖፖሊ ምርት ሁሉንም የምርት አካባቢ የሚያጠቃልል መሆኑን የሚያሳይ (ታዳጊ አገሮች ከማርክሳዊ ፖለቲካ ኢኮኖሚ አንፃር፣
በዩሪ ፖፖቭ)

proudly brought to you by

www.binyamhk.wordpress.com



ምርትም የበለጠ ማኅበራዊ እየሆነ ይመጣል። ይሁንና የማምረቱ ተግባር የበለጠ ማኅበራዊ ቢሆን፣ የምርት ውጤቱን ግን የሚወስዱት ጥቂት ሞኖፖሊስቶች ይሆናሉ።

በዚህ አንፃር ሞኖፖሊስቶች ከፍተኛ ትርፍ ለማጋበስ በአላቸው ጉጉት የሠራተኛው ሕዝብ የኑሮ ሁኔታ በየጊዜው እያቆለቆለ ይመጣል። ብዝበዛውም እየጨመረ ስለሚመጣ የሠራተኛው የኑሮ ሁኔታ ይበልጥ ይወድቃል፣ ይደቃል። ይህም ሁኔታ የካፒታሊዝም መሠረታዊ ቅራኔ ማለትም በማኅበራዊ አመራረትና ምርትን በግል ካፒታሊስቶች ወይም ሞኖፖሊስቶች መወሰዱ መካከል ያለው ቅራኔ በከፍተኛ ደረጃ እንዲካረር ያደርገዋል። ስለሆነም በማኅበር የሚከናወነው የምርት ሂደት የማምረቻ መሣሪያዎችን ማኅበራዊ መሆን ስለሚጠይቅ ቅራኔው የሚፈታው በዚህ መንገድ ብቻ ይሆናል። ካፒታሊዝም ወደ ኢምፔሪያሊዝም ዕድገት ደረጃ ቢደርስ በጣም አድኃሪና የኅብረተሰቡን ዕድገት ጎታች ይሆናል፡፡ የምርት ኃይሎች እንዳይዳብሩ በሞኖፖሊስቶች ይታፈናሉ። ይህም በምርት ኃይሎችና በምርት ግንኙነቶች የመጣጣም ሕግ መሠረት የካፒታሊስት የምርት ግንኙነቶች በአዲስ የሶሻሊስት የምርት ግንኙነቶች እንዲተኩ ይገደዳሉ። ይህም ሊከናወን የሚችለው ሠራተኛው ሕዝብ በዝባዥ መደቦችን ለመደምሰስ በሚያካሂደው ውስብስብና መራራ ትግል ይሆናል።

## 2.2 ኢምፔሪያሊዝም የሸገተ ካፒታሊዝም ነው

ካፒታሊዝም ከነፃ ውድድር ወደ ሞኖፖል ደረጃ እያደገ በመጣ ቁጥር በውስጡ ያሉት የተለያዩ ቅራኔዎች እየተካረሩ ይሄዳሉ። የመደብ ትግሉ ይበልጥ እየተፋፋመ ይመጣል። በተካረሩት ቅራኔዎች ምክንያት የሚጧጧፈው የመደብ ትግል የኢምፔሪያሊዝምን ሕልውና አደጋ ላይ ይጥለዋል። የመጨረሻውንም ጊዜ እያቀረበው ይመጣል። የኢምፔሪያሊዝም ትክክለኛው

ገጽታ ማለትም የሻገተ ካፒታሊዝም መሆኑ ይፋ ይወጣል። የሻገተ ካፒታሊዝም ወይም በሌላ አነጋገር ኢምፔሪያሊዝም የበሰበሰ አብዮት ዋዜማ መሆኑን የሚያሳዩ ጉልህ ሁኔታዎች ከዚህ በታች ተጠቅሰዋል።

### 2.2.1 የምርት ኃይሎች ዕድገት ይቀንሳል፡

የተረፈ እሴታቸው መጠን እስከአሻቀበ ድረስ ሞኖፖሎች የምርት ኃይሎችን ዕድገት የሚያራምዱ ቢሆንም በዘመነ ኢምፔሪያሊዝም የምርት ኃይሎች ዕድገት ግን እየቀነሰ ይመጣል፡፡ ይህም አንደኛው የኢምፔሪያሊዝም የመሻገት ጠባዩ ነው፡፡ ካፒታሊዝም ወደ ኢምፔሪያ ሊዝም እያደገ በመጣ ቁጥር ይበልጥ እየዘገና እየተጓከመ ይመጣል፡፡ ኢምፔሪያሊዝም የሻገተ ካፒታሊዝም ነው የሚባለውም ለዚህ ነው፡፡ የኢምፔሪያሊዝም የመሻገት ጠባይ የሚመነጨው የኢኮኖሚው መሠረት ከሆነው ከሞኖፖል ነው፡፡ የኢምፔሪያሊዝም መዘግና መሻገት የሚንፀ ባረቀው በሞኖፖል ድርጅት ባበያ የምርት ኃይሎችን ዕድገት በጽኑ ቢገታ ነው፡፡ ኢምፔሪያሊዝም ከፍተኛ ትርፍ እሚያስገኝ እስከሆነ ድረስ ለቴክኒክ ዕውቀት፣ ለምርት ኃይሎችና ለቴክኖሎጂ ዕድገት አስተዋጽኦ ያደርጋል። በቀዳሚ ሞኖፖሊ ካፒታል እያንዳንዱ ካፒታሊስት ከሌሎች ካፒታሊስቶች ተወዳድሮ ይበልጥ ትርፍ ለማጋበስ ሲል የማምረቻ መሣሪያዎችን ያሻሽላል፤ አዳዲስ ቴክኖሎጂም ለመጠቀም ያልተቆጠበ ጥረት ያደርጋል። አዳዲስ ቴክኖሎጂ መጠቀም ምርታማነትንና ትርፍንም ከፍ ስለሚያደርግ ካፒታሊስቶች የምርት ኃይሎችን በማሳደግ በኩል ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል። ሞኖፖል ካፒታሊዝም ሲዳብርና ሲስፋፋ ብዙ አምራች ክፍሎችን ሙሉ በሙሉ በቁጥጥሩ ሥር በማድረግ የሸቀጦችን ዋጋ እንዳሻው ስለሚወስንና የወዝአደሮችንና የጭቁን ሕዝቦችን የሥራ ኃይል በርካሽ ዋጋ በመግዛት ገበያውን ስለሚቆጣጠር ከፍተኛ የሞኖ ፖል ትርፍ ያጋብሳል፤ ስለሆነም የትርፉን መጠን በዚህ ዓይነት

መንገዱ ለማባደግ አስከቻለ ዱረስ ለምርት ኃይሎችና ለቴክኖሎጂ ዕድገትና መዳበር አምተዛዝም አይወነቀም:: በዚህም የተነሣ አንዳንዱ ወደር የሌላቸው ለዓለም ሕዝቦች ከፍተኛ ጠቀሜታ ወይም ግልጋሎት ሊሰጡ የሚችሉ የሳይንሳዊ ምርምር ውጤቶችና ቴክኒካዊ ፈጠራዎች ለብዙ ዓመታት እንዳይጠናቀቁና ተግባራዊ እንዳይሆኑ አድርገዋቸዋል። ለምሳሌ በአለፉት ሃያ ዓመታት ሳይንቲስቶች በሰው ሠራሽ ቤንዚን ለማግኘት ከፍተኛ ጥረት አድርገው አጥጋቢ ውጤት አግኝተው ነበር። በሰው ሠራሽ ቤንዚን በቀላል ወጪ በማምረት በመጠነኛ ዋጋ ሊሸጥ እንደሚችልም አረጋግጠው ነበር። ይሁን እንጂ ይህ ቴክኖሎጂ በሥራ ላይ እንዳይውል ታግዷል:: ይህም የሆነበት ምክንያት የቤንዚን ሞኖፖል ኩባንያዎችን የደለበ ጥቅም ሊቀንስ ብሎም ሙሉ በሙሉ ሊያበቀር በለሚችል ነው። የቤንዚን ሞኖፖል ኩባንያዎች ባላቸው የኢኮኖሚና የፖለቲካ ኃይል በመጠቀም አፍነውታል:: የዚህ ዓይነት አያሌ ምሳሌዎች መጥቀስ ይቻላል።

የሳይንሳዊ ምርምር ውጤቶች የሞኖፖል ቡርዧውን ጥቅም የሚፃረሩ ወይም የሞኖፖል አቋሙን የሚያናጉ መስለው የሚታዩ ከሆነ ምርምሩን ከአከናወነው ድርጅት ወይም ግለሰብ የምርምሩን ውጤት በተግባር የማዋሉን መብት በከፍተኛ ገንዘብ ሞኖፖሊስቶች ገዝተው በመውሰድ ለምርምሩ ውጤት ዋና ባለቤት ይሆናሉ:: ከዚያን በኋላ የምርምሩን ውጤት አፍነው ያስቀሩታል። ወይም ብዙ ትርፍ ሊያስገኝላቸው በሚችል ተግባር ላይ ያውሉታል። ለምሳሌ የአቶሚክ ኃይል መገኘት ትልቅ የሳይንስ ምርምር ውጤት ነው:: የአቶሚክ ኃይል ለሰላማዊ ተግባር ቢውል የዓለምን ሕዝብ አሁን ከሚገኝበት አሠቃቂ ሁኔታ በሚያስደንቅ ፍጥነት ሊያሻሽለው በቻለ ነበር። ይሁን እንጂ ሞኖፖሊስቶች የአቶሚክን ኃይል ምርምር ውጤት ተግባራዊ ያደረጉት ለዓለም ሕዝቦች መቅሰፍት የሆነውን የአቶሚክ

በምዓነ ለመሥራት ነው፡፡ ይህም ለጥቂቶቹ ሞኖፖሊስቶች ከፍተኛ ትርፍ አስገኝቶላቸዋል፡፡ ይህ ለንግዲህ የሚያሳየው የሥርዓቱን መሸገት ወይም መበስበስ ነው፡፡

በኢምፔሪያሊስት አገሮች የማይንበየ ምርምርና የቴክኖሎጂ ዕድገት ለየቀነበ ወይም ለየተዳከመ ይመጣል ሰንል ፍፁም ዕድገት የለም ማለት አይደለም፡፡ ዕድገት አንፃራዊ እንጂ ፍፁማዊ አይደለም፡፡ በጣም በዳበሩት የካፒታሊስት አገሮች ማለትም ሞኖፖሊስቶች የኢኮኖሚና የፖለቲካ የበላይነት ባላቸው አገሮች እንኳን እንደሚፈለገውና የምርት ኃይሎች እንደሚጠይቁት ያህል የቴክኖሎጂ ለዕድገት አይኑር እንጂ ባይንበየ ምርምሮች መደረጋቸው አዳዲስ የቴክኒክ ፈጠራዎች መከናወናቸው አልቀረም፡፡ በተለይም በአንዳንድ የካፒታሊስት አገሮች በተወሰኑ የካፒታሊስት ኢኮኖሚ ዘርፎች ውስጥ ዘለቄታ ባይኖረውም ፈጣን የቴክኖሎጂ ዕድገት ይታያል፡፡ ይህ የሚሆንበት ምክንያት በነፃ ውድድር ያደገው ሞኖፖል በምንም ዓይነት ውድድርን ለማጥፋት በለማይችል ነው፡፡ እንዲያውም ውድድርን የበለጠ እንዲጠናከር ያደርገዋል፡፡ ውድድሩ የሚካሄደው በአንድ አገር በሚገኙ የሞኖፖል ካፒታል ቡድኖች መካከል ብቻ ሣይሆን በተለያዩ አገሮች በሚገኙ ሞኖፖሊስቶች መካከልም ነው፡፡ አንዱ የሞኖፖል ቡድን ሌላውን የሞኖፖል ቡድን ለማጥፋት ወይም እርስ በርሳቸው ለመቋቋም አዳዲስ የቴክኒክ ሥራዎችን ስለሚጠ በተወሰነ ደረጃ ቴክኖሎጂ ሊያድግ ይችላል፡፡ ይሁን እንጂ በአሁኑ ጊዜ በጣም ለየተራቀቀ የመጣው ቴክኖሎጂ አዳዲስ ተግባሮች፣ አዳዲስ ምርምሮች ባለማቋረጥ እንዲከናወኑ ይጠይቃል፡፡ ሆኖም ተግባሮችን ለማከናወን የካፒታሊስቱ የምርት ግንኙነት ከፍተኛ እንቅፋት ሆኗል፡፡ በዚህ አኳኋን በሞኖፖል ደረጃ በኢምፔሪያሊስት አገሮች የምርትና የቴክኖሎጂ ዕድገት ባጠቃላይ ለየተዳከመ የመሄድ አዝማሚያ አለው፡፡

## 2.2.2 የኢምፔሪያሊዝም ለመበስበስ ወይም ለመሻገቱ መያሟት ይበልጥ ልንረዳ የምንችለው ለያደር በሚያሳየው የተባይነት /ደም መጣጭ/ ባሕርይው ነው።

በቀደመ ሞኖፖሊ ካፒታል ዘመን በግል ካፒታሊስቶች ተይዘው የነበሩት ድርጅቶች በመስከላቸው በሚካሄደው ነፃ ፉክክር ቀስ በቀስ እየተሰበሰቡ በጥቂት ሞኖፖሊስቶች ይዞታ ሥር ይወድቃሉ። ካፒታሊስቶች የግል ባለቤት መሆናቸው እየቀረ የሞኖፖል ድርጅቶች የአክሲዮን ድርሻ ይኖራቸዋል። ብዙ ድርጅቶች እየተጠቃለሉ በመጡ ቁጥር ብዙ ካፒታሊስቶች የሥራ አመራር ይዞታቸውን እየለቀቁ ባለአክሲዮን ይሆናሉ። በዚህ ሁኔታ የካፒታሊስቱ መደብ በየጊዜው ከምርት ሂደት ጋር የነበረው ግንኙነት እየተቋረጠ ይመጣል። የሞኖፖል ድርጅቶች ሥራ አመራር የሚከናወነው በቀጥር ሥራ አስኪያጆች ይሆናል። ቀደም የግል ድርጅታቸውን ሥራ ይመሩ የነበሩ ቡርዧዎች ፍፁም ተገልለው ያለ ሥራ ይቀመጣሉ፤ የመሬት ከበርቴዎች መሬታቸውን ለሞኖፖል ድርጅቶች ካከራዩ በኋላ ከሥራ በመገለል ቁጭ ብለው እንደሚቀለቡ ሁሉ እነዚህም ከአክሲዮናቸው በሚያገኙት የትርፍ ድርሻ ያለምንም ሥራ ተቀላቢ በመሆን ይኖራሉ። ይሄንን ነጥብ ቀረብ ብለን በምሳሌ እናስረዳ። በአንድ ካፒታሊስት አገር ትላልቅና መለስተኛ ካፒታል ያላቸው 20 የተለያዩ የጫማ ፋብሪካዎች አሉ እንበል። ከእነዚህ 20 ፋብሪካዎች አብዛኛውን ጫማ የሚያመርቱት ፉክክሩ ባያቆማቸው ቢቀር ሦስቱ በጣም ትልቅ ፋብሪካዎች ድርጅታቸውን ለማዋሃድ ስምምነት ያደርጋሉ። ሦስቱ ትላልቅ የጫማ ፋብሪካዎች ባለቤቶች ፋብሪካቸው ያወጣል በተባለው ግምት ልክ ድርሻ /አክሲዮን/ እንዲኖራቸው ተደርጎ ይዋሃዳሉ። ቀጥረኛ ሥራ አስኪያጅ ተቀጥሮ ወዲ ገበያውን እየተቆጣጠረ ሥራውን ያካሂዳል።

እንግዲህ አንድ ሞኖፖል ድርጅት ተፈጠረ ማለት ነው። በዚህ ጊዜ የቀድሞዎቹ ፋብሪካዎች ባለቤቶች ከሥራ ተቋረጡ ማለት ነው። ይህ አዲስ የተቋቋመው የሞኖፖል ድርጅት በልዩ ልዩ ዘዴዎች በመጠቀም ሌሎቹ መለስተኛ የጫማ ፋብሪካዎች ከሞኖፖል ድርጅቱ እንዲቀላቀሉ ተጽእኖ ያደርግባቸዋል። እነዚያም መለስተኛ በግል የተያዙ የጫማ ፋብሪካዎች ውድድሩን ለመቋቋም ስለማይችሉና ለሞኖፖሊስቶች ጥቅም በቆመው መንግሥት ተጽእኖ የፋብሪካቸውን ግምት በአክሲዮን መልክ እየወሰዱ የሞኖፖል ድርጅቱ አካል ይሆናሉ። በዚህ ሁኔታ የሃያ ጫማ ፋብሪካዎች ባለቤቶች ምንም ሳይሠሩ በየዓመቱ ከሞኖፖል ድርጅቱ በሚያገኙት ትርፍ ቁጭ ብለው ይቀለባሉ።

ይህ በሠባት የጫማ ፋብሪካዎች መዋሃድ የተጀመረው የሞኖፖል ድርጅት የተረፉትን ጫማ ፋብሪካዎች በመዋጥ ብቻ አይቆጠብም። ሌሎች ድርጅቶችም እንዲዋሃዱ ያደርጋል። ድርጅቱንም ለማስፋፋት የመሬት ከበርቴዎችንም ይበላል። እንዲህ እንዲህ እያለ ብዙ ድርጅቶችን በማዋሃድ ብዙ ካፒታሊስቶችን ከምርት ሂደት ያፈናቅላል። ቁጥራቸውም እየጨመረ ይመጣል። በዚህ አኳኋን ምንም ሳይሠሩ ቁጭ ብለው የሚቀለቡ የበዝባዦች መደብ አባላት ብዛት ይጨምራል። እንግዲህ ከዚህ ሁኔታ የምንረዳው በዘመነ ኢምፔሪያሊዝም ያለሥራ ቁጭ ብለው የሚቀለቡ ደም መጣጮች እየበረከቱ ሲሄዱ፣ የወዝአደሩ ኑሮ ግን እየቆረቆዘ መምጣቱ ነው።

የኢምፔሪያሊዝም የተባይነት /ደም መጣጭ/ ባሕርይው በጉልህ የሚታየው ከኋላ ቀር አገሮችና በቅኝ ግዛት ሥር ከወደቁ አገሮች ሕዝቦች በሚዘርፈው ከፍተኛ ሀብት ነው። ሞኖፖሊስቶች የአገራቸውን ሠራተኛ ሕዝብ በመበዝበዝ ያከበቱትን ካፒታል ወደ ሌሎች አገሮች በመላክ በርካሽ የሚያገኙትን ጥሬ ሀብትና የሥራ ኃይል በማቀናጀት ከፍተኛ

ትርፍ ያገኛሉ። ይህም የካፒታሊስት አገሮችን ብሔራዊ ሀብት እንዲጠራቀም ከማድረጉም በላይ የቡርዧውን መደብ ገቢ በጣም ከፍ ያደርገዋል። ብዙ የቡርዧው መደብ አባላት ወደ ውጭ በላኩት ካፒታል አማካይነት በሚያገኙት ትርፍ ያለ ሥራ ቁጭ ብለው በመቀለብ የተንደላቀቀ ኑሮ ይኖራሉ። በአገራቸው ያለውንም ሠራተኛ ሕዝብ ከቅኝ ግዛቶች ከበዘበዙት ሀብት ጥቂት ፍርፋሪ በመጣል ለጊዜውም ቢሆን ከመደብ ትግሉ ሊያዘናጉት ይሞክራሉ።

ታላላቅ የካፒታሊስት አገሮች ለድሃ አገሮች ከፍተኛ ብድር በመስጠት ተመጣጣኝ ያልሆነ ወለድ በማስከፈል ብዙ ትርፍ ለማጋበስ ከመቻላቸውም በላይ ለነዚህን አገሮች በኢኮኖሚና በፖለቲካ ተገዢ ያደርጓቸዋል። ይህም የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝን ያስከትላል። አሁን እንደምንመለከተው የዚህ ዓይነቱ አስከፊ ብዝበዛ የሚፈጸመው በአፍሪካ፣ በላቲን አሜሪካና በእስያ አገሮች ሕዝቦች ላይ ነው። ካፒታል በመዋዕለ ንዋይ መልክ ወይም በብድር ወደውጭ መላክ እያደገ በሄደ መጠን ጥቂት ሀብታም ሀገሮች ወለድ ተቀባይ በመሆን ላይ በማተኮር በኢኮኖሚ ዕድገት ወደኋላ በቀሩ የአፍሪካ፣ የላቲን አሜሪካና የእስያ አገሮች ላይ እንደ መዥገር ተጣብቀው የቅኝ ግዛቶችንና የጥገኛ ሀገሮችን ሕዝቦች ይበጠብጣሉ። ይህ እንግዲህ የሚያሳየን ኢምፔሪያሊዝም ካፒታልን ወደውጭ በመላክ ብዙ ብሔሮችን በመጨቆንና በመበዝበዝ ደም መጣጭ ለሆኑ ጥቂት የካፒታሊስት መደብ አባላት የትርፍ ክምር የሚያበረክትበት ዘዴው ነው። የካፒታሊስት አገሮች ቡርዧዎች ምንም የምርት ተግባር ሳያከናውኑ በጭቁኑ ሕዝቦች ጫንቃ ላይ ተለጥፈው ደማቸውን በመምጠጥ ቢኖሩ ካፒታሊዝም ምን ያህል እየጥገኛና እየበሰበሰ መምጣቱን ልንረዳ እንችላለን።

### 2.2.3 ሌላው የኢምፔሪያሊዝም የተባይነት /ደም መጣጭ/ ባሕርይ የሚገለጸው በየጊዜው እያደገ በሚመጣው ጦረኝነት ነው

ወደ ዕድገቱ መጨረሻ ላይ ሲቃረብ ኢምፔሪያሊዝም ኢኮኖሚውን የሚያራምደው በጦረኝነት ይሆናል። ኢምፔሪያሊዝም በሰፊው ሠርቶአደር ሕዝብ ላይ ከፍተኛ ግብር በመጣል የሚሰበስበውን የመንግሥት በጀት ለሞኖፖሊስቶች ጥቅም መዳበሪያ፣ ለከባድ የጦር መሣሪያ ማምረቻ ያውለዋል። የጦር መሣሪያ ኢንዱስትሪዎችን ያስፋፋል፣ ያጠናክራል።

ኢምፔሪያሊዝም ለጦር መሣሪያ ኢንዱስትሪዎች መስፋፋት ከፍተኛ ወጪ በመመደብ ጭቁን ሕዝቦች ለብሔራዊ ነፃነት የሚያካሂዱትን ትግል ያፍናል፣ በካፒታሊስት አገሮች የወዝአደሩን ትግል ያፍንበታል፣ ታዳጊውንና ለተበዘበዙ ሕዝቦች ሙሉ ነፃነትና በሰላም የሚያጎናጽፈውን ሶሻሊዝምን ለማዳከም ያውለዋል፣ በአጠቃላይ የሞኖፖሊስቶችን ጥቅም ለማስጠበቅና ለማዳበር ይገለገልበታል። በዛሬው ጊዜ ከኢምፔሪያሊስት አገሮች ብሔራዊ ሀብት ከፍተኛው ድርሻ ለጨግ በጣም ብዙ የሆነውን ወታደር ለመደገፍ፣ የጦር መሣሪያዎችን ለመሥራት፣ ከጦርነት ጋር የተያያዙ ጥናቶችን ለማካሄድና ወራሪ የኢምፔሪያሊስት ጦርነቶችን ለማካሄድ ይውላል። የኢምፔሪያሊስት አገሮች ለጦርነት የሚመድቡት ሀብት ከዓመት ወደ ዓመት እያሻቀበ በመገስገስ ላይ ነው። ለምሳሌ ጥቂት ኢምፔሪያሊስት አገሮች እ.ኤ.አ. ከ1975 - 1978 በአራት ዓመታት ውስጥ ለጦር የመደቡትን ገንዘብ እንመልከት፣

| | |
|---|---|
| እንግሊዝ | 47.5 ቢሊዮን ዶላር /98.3 ቢሊዮን ብር/ |
| ፈረንሣይ | 58.5 ቢሊዮን ዶላር /122 ቢሊዮን ብር/ |
| ምዕራብ ጀርመን | 70 ቢሊዮን ዶላር /145 ቢሊዮን ብር/ |
| አሜሪካ | 397 ቢሊዮን ዶላር /822 ቢሊዮን ብር/ |

ወጪ ቢደረግ በ1978/እ.ኤ.አ/ ብቻ 14 የሰሜን አትላንቲክ ቃል ኪዳን አገሮች/ኔቶ/ ለወታደራዊ ተግባር ወጪ ያደረጉት 188.4 ቢሊዩን ዶላር ቢሆን፣ በአራት ዓመታት ጊዜ ማለትም እ.ኤ.አ. ከ1975–1978 ውስጥ የአሥራ አራቱ የኔቶ ቃል ኪዳን አባል አገሮች ጠቅላላ ወታደራዊ ወጪ 654 ቢሊዩን ዶላር/1354 ቢሊዩን ብር/ ነው። በአሁኑም ጊዜ የሬጋን አስተዳደር ለኒውትሮን በምብና ለከባድ ተበፈንጣሪ የኒውክሊር መሣሪያዎች ማምረቻ ከፍተኛ በጀት በመመደብ ዓለምን ወደ አስከፊ ጦርነት ለመክተት እየተሯሯጠ ነው። እ.ኤ.አ. ለ1982 ብቻ የሬጋን አስተዳደር ለመከላከያ ወጪ የጠየቀው\በጀት 250 ቢሊዩን ዶላር መድረሱ የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ዓለምን ለአደገኛ ጥፋት ለመዳረግ የሚያደርገውን መቅበዝበዝ የሚያረጋግጥ ሐቅ ነው። ይህ ሁሉ ወጪ የጥቂት ሞኖፖሊስቶችን ትርፍ በጣም ከፍ ሲያደርገው የሠራተኛውን ሕዝብ ኑሮ ግን በኃይል ያቆረቁዘዋል። በብዙ ሚሊዩን የሚቆጠሩ ሠራተኞች በወታደራዊ ተግባር ላይ በመሠማራታቸው ማኅበራዊ ጠቀሜታ ካለው ተግባር ከመነጠላቸውም በላይ በሌላ ሥፍራ እንደተጠቀሰው የሥራ አጡ ሠራዊት ከዕለት ወደ ዕለት በማሻቀብ ላይ ነው። ይህ እንግዲህ ፡ኢምፔሪያሊዝም በመሸገትና በመበሰበሰ ላይ መሆኑን ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ነው።

ካፒታሊዝም ወደ ከፍተኛው ዕድገት ደረጃው ማለትም ወደ ኢምፔሪያሊዝም ቢደርስ ጥቂት ሞኖፖሊስቶች የማምረቻ ድርጅቶችን፣ የመገናኛ ተቋሞችን፣ ማዕድናችን፣ ባንኮችን ወዘተ... በቁጥጥራቸው ሥር በማዋል የሞኖፖል ገበያ ዋጋ በመተመን ከፍተኛ ትርፍ ይዝቃሉ። በየጊዜው ከማምረቻ ድርጅቶች የሚባረሩት ወዝአደሮች ከትምህርት ቤት የሚወጡ ወጣቶች፣ የሞኖፖሊስቶችን ውድድር መቋቋም ያቃታቸውና ከበረው ከብዝበዛው ዓለም የሚባረሩት ንዑስ ከበርቴዎች የሥራ አጡን ቁጥር እያበዙት ይመጣሉ። ሞኖፖሊስቶች ከሠራተኛው ሕዝብ ከሚሰበስቡት ገንዘብ የሥራ አጥነት መድኅኒያ እያሉ ለሕይወታቸው መጠበቂያ ያህል


ለሥራ አጦች ይወረውሯቸዋል። ይህም ከፍተኛ ብዛት ያለው ሥራ አጥ ምንም ሳይሠራ ጥቂትም ቢሆን ገንዘብ በሰማበው ይህም ሁኔታ የተቀሳቢውን ቁጥር ያበዛዋል። የሥራ አጡ ብዛት በየጊዜው በመጨመሩ ቁጥር የሠራተኛው ሕዝብ ሸክም ይበልጥ እየከበደ ይመጣል። ይህ ሁሉ ኢምፔሪያሊዝም በመሸገትና በመበስበስ ላይ ያለ ካፒታሊዝም መሆኑን የሚያንፀባርቅ ነው።

2.2.4 <u>የወዝአደር መሣፍንት/ባንዳ ወዝአደሮች/ መከሰት የኢምፔሪያሊዝም የመሸገት ገጽታ ነው።</u>

የኢምፔሪያሊዝምን መበስበስ በጥልቀት ልንመለከተው የምንችለው ሞኖፖል ቡርዧው የቀሟ ግዛቶችን፣ ኋላ ቀር ሀገሮችንና የራሱን አገር ወዝአደር መደብ በመበዝበዝ ካገኘው ትርፍ ለጥቂት የቡርዧው አፈቀላጤ ለሆኑ ሠራተኞች ማለትም "መሣፍንት ሠራተኞች" ከፍተኛ ደመወዝና ልዩ ልዩ ጥቅሞች በመስጠት የሠራተኛውን ትግል ለማኮላሸት የሚፈጽመውን ሤራ ገምግመን ለመረዳት ስንችል ነው።

የኢምፔሪያሊዝም ሸጋታ ገጽታ በሠራተኛው ንቅናቄ ውስጥም ይከሰታል። የወዝአደር መሣፍንትና የተበረዘ ርዕዮተዓለም በሠራተኛው ንቅናቄ ውስጥ መከሰት የኢምፔሪያሊዝም የቀባይነት ባሕርይ መከሰቻ ምልክት ነው።


ሞኖፖሊስቶች ባገራቸው ውስጥ የሚገኘው ሠርቶ አደር ሕዝብ እንዳያምጽ ካሳቸው ወይም ከሚያገኙት ትልቅ የሞኖፖል ትርፍ ከወዝአደሩ መደብ አፈንግጠው የወጡትን ጥቂት ከሐዲዎች በገንዘብ በመደለል የሞኖፖል




ኢምፔሪያሊዝም ካፒታሉ ምርትን ያለቅጥ ለጦር መሣሪያና ለጦርነት የሚያወጣው ከፍተኛ መሆኑን የሚያሳይ (ሶሊዳሪቲ መጽሔት)
ጥር 1982 ፣ [illegible]

proudly brought to you by

www.binyamhk.wordpress.com



ቡርዧው አፈቀላጤ ያደርጋቸዋል። እነዚህ ከሐዲያች ከፍተኛ ደሞዝ የሚያገኙ ከመሆናቸውም በላይ በየማምረቻ ድርጅቶች የአክሲዮን ድርሻ በስማስጧቸው አመለካከታቸውም ሆነ የሚከተሉት ርዕዮተዓለም የቡርዧው ነው፣ ስሠራተኛነት ስም ቡርዧውን ያገለግላሉ። ከወዝአደሩ ጋር ተቀላቅለው ብዙውን ጊዜ የሠራተኛውን የሙያ ማኅበራት አመራር በመያዝ የወዝአደሩን የመደብ ጥቅም ከመሸጣቸውም በላይ ንቅናቄውን ያኮላሻሉ። እነዚህ "የወዝአደር መሣፍንት" የሞኖፖል ቡርዧዎች ቡችሎችና አሽርባዬችም ናቸው። ኢምፔሪያሊዝም በተንሰራፋበትና የወዝአደር መሣፍንት ባቆጠቆጡበት ጊዜ በወዝአደሩ መደብ እንቅስቃሴ ውስጥ የኢምፔሪያሊዝምን አገዛዝ በመደገፍ ከላሽ ንድፈሃሣብና መሥመር ይከሰታል። አድርባዮች ካፒታሊዝም በጥገና ዘዴ እየተሻሻለና እየተለወጠ እንደሚመጣ፣ የሠራተኛው ኑሮ ከጊዜ ወደጊዜ እንደሚሻሻል፣ ለዚህም የቡርዧው መንግሥት የሚቀይባቸውን የውስጥና የውጭ ኢምፔሪያሊስት ፖሊሲዎችን ሠራተኛው መደገፍ እንዳለበት የሚሰብክ አዝማሚያ ይሠራጫል፣ ይህ ሁሉ የወዝአደሩን አዕምሮ ለማደንዘዝና ውዥንብር ውስጥ ለመክተት ሆን ብሎ የሚደረግ የቡርዧው የፕሮፖጋንዳ መርዝ ነው። አድርባዮች በመሠረቱ በሠራተኛው የትግል እንቅስቃሴ ውስጥ የቡርዧው አፈቀላጤ ሆነው ያገለግላሉ። የሠራተኛውን መደብ አንድነት በመበታተን ሠራተኛው በተባበረ ክንዱ በዝባዥ ካፒታሊስቶችን ከጫንቃው እንዳያስወግዳቸው ይከላከላሉ። ይህም ሁኔታ ለቡርዧው መደብ በሥልጣን ላይ መቆየት አስተዋጽኦ አድርጓል።

## 2.3 ኢምፔሪያሊዝም የበሰለበት አብዮት ዋዜማ ነው

ኢምፔሪያሊዝም ወደ ሞት የሚጓዝ፣ ለሞት የተቃረበ፣ በሞት አፋፍ ላይ የደረሰ ካፒታሊዝም ነው።

ካፒታሊዝም ወደ ሞኖፖል ማለትም ወደ ኢምፔሪያሊዝም ደረጃ በሚያድግበት ጊዜ መሠረታዊ የሆነው በቡርዧውና በወዝአደሩ መካከል ያለው ቅራኔ አይለወጥም።

እንዲያውም እየተካረረ ይመጣል። ይህ መሠረታዊ ቅራኔ ብቻ ሣይሆን የካፒታሊዝም ውስጣዊና ውጫዊ ቅራኔዎች ሁሉ ወደ ተከባበና የተካረረ ደረጃ ይደርሳሉ። ይህም የአብዮት መቀስቀስን ያስከትላል።

## 2.3.1 በወዝአደሩና በቡርዧው መካከል ያለው ቅራኔ እየተካረረ ይሄዳል

በካፒታሊስት አገሮች ሞኖፖሊስቶችና የፋይናንስ ካፒታሊስቶች የኢኮኖሚውንና የፖለቲካውን እንቅስቃሴ ይበልጥ በቁጥጥራቸው ሥር እያዋሉ በመጡ ቁጥር የሠራተኛው የኑሮ ሁኔታ እያቆለቆለና እየቀነሰ ይመጣል። ብዝበዛውም ከዕለት ዕለት እያየለና አስከፊ እየሆነ ይሄዳል። ቡርዧው በየጊዜው የሸቀጥ ምርትን ዋጋ በማናር የሠርቶአደሩን ሕዝብ ንፁህ ገቢና የመግዛት ችሎታ ይቀንሳል። ያቆረቁዛል። የኑሮ ውድነትን ያስከትላል። ሠርቶአደሩ ሕዝብ ይጎሳቆላል። ወዝአደሩ ያበገኘውን ተረፈ እሴት በቀጥታ በቡርዧው ከመነጠቁም በላይ ቡርዧው መንግሥትን ከለላ በማድረግ ሠርቶአደሩ ሕዝብ ከባድ ታክስ እንዲከፍል በማድረግ ገደብ የለሽ ብዝበዛ ያካሂዳል። ሞኖፖል ቡርዧው በወዝአደሩ ላይ የሚያደርሰው ይህ ነው የማይባል ብዝበዛና የፖለቲካ ጭቆና በወዝአደሩና በቡርዧው መካከል ያለውን ቅራኔ ያባብሰዋል። ጭቆናው እየከፋ በሄደ መጠን ጭቆናውን በመቃወም የሚያካሂደውም ትግል እያየለ ይሄዳል። በዚህ ወቅት ቀደም ወዝአደሮች ሲያካሂዷቸው የነበሩት የፖለቲካና የኢኮኖሚ የትግል ስልቶች በቂ ሆነው አይገኙም፤ ማለትም ከዚህ አስከፊ ሁኔታ ለመውጣት አያስችሉም። ሥራ አጥ ከቡርዧው ጋር ተደራድሮ መጠነኛ ጭማሪ ማግኘት የሥራ ሰዓት ማስቀነስ፤ የዕረፍት ጊዜን ማስጨመርና አንዳንድ የሥራ ሁኔታዎች እንዲሻሻሉ ማስደረግ በመሠረቱ ጠቃሚ ይሁኑ እንጂ በየጊዜው እየጨመረ የሚመጣውን ጭቆናና ብዝበዛ ሊያቆሙ አይችሉም። ስለዚህ ለየት ያለና መራራ ትግል ማካሄድ ይጠይቃል። ይህም ወዝአደሩን ለሶሻሊስት አብዮት ያዘጋጀዋል። የሠራተኛው

ሕዝብ ሙሉ ነፃነቱን የሚቀዳጀው፣ ከብዝበዛና ከጭቆና የሚላቀቀው፣ የጭቆናና ብዝበዛ መሠረት የሆነውን ሞኖፖሊ ካፒታሊዝምን በመደምሰስ በለሆነ በጠቀኛ የሠራተኛው መደብ ጋር ቱ ለየ ተመራ ለመሠረታዊ ለውጥ ይታገላል። የካፒታሊዝምም የወደፊት ዕድል እየመነመነ ይመጣል።

## 2.3.2 በኢምፔሪያሊስት ኃይሎች መካከል ያለው ቅራኔ ይባባሳል

የልዩ ልዩ ካፒታሊስት አገሮች ሞኖፖሊስቶች ከፍተኛ ትርፍ ለማጋበስ ባላቸው ጽኑ ፍላጎት ለሚያመርቱት ሸቀጥ ማራገፊያ የዓለም ገበያዎችን፣ የጥሬ ዕቃ ምንጮችንና ወደውጭ የሚልኩት ካፒታል በአብ ተማማኝ ሁኔታ ትርፍ ሊያስገኝላቸው የሚችልበትን አካባቢ ለመቆጣጠር በሚያደርጉት ትግል አርበ በርባቸው ይጋጫሉ። የሁሉም ካፒታሊስት አገሮች በፖለቲካም ሆነ በኢኮኖሚ ዕድገታቸው ያልተስተካከለ ወይም ያል ተመጣጠነ በለሆነ በኢኮኖሚ ዕድገቱ ባቀ ያለው ካፒታሊስት አገር ደከም ያሉትን ካፒታሊስት አገሮች ከዓለም ገበያ ለማስወጣትና በቁጥጥሩ ሥር ለማዋል ይጣጣራል። ደከም ያሉትም ካፒታሊስት አገሮች በይዞታቸው ሥር ካለው የዓለም ገበያ ለመውጣት ፈቃደኛ በለማይሆኑ በመካከላቸው ያለው ቅራኔ ይባባሳል። ይህም ቅራኔ እየተባባሰ ሲመጣ የኢምፔሪያሊስት ጦርነቶችን ይቀሰቀሳል።

የአንደኛውና የሁለተኛው የዓለም ጦርነቶች የተነሱትና አሠቃቂ አልቂት ያስከተሉት ኢምፔሪያሊስት አገሮች ዓለምን እንደገና ለመከፋፈልና ለመቀራመት ሲሉ በፈጠሩት ግብ ግብ ነው። በአንደኛው የዓለም ጦርነት 10 ሚሊዩን ሰዎች ሲገደሉ፣ 20 ሚሊዩን ሰዎች ቆስለዋል። በዚህም ጦርነት ሣቢያ ብዙ ሚሊዮን ሰዎች በተስቦ በሽታዎችና በረሃብ አልቀዋል። በወዝአደሩ የሥራ ኃይል የተገነቡ ሕንፃዎች፣ ፋብሪካዎች፣ ታሪካዊ


ሥራዎችና ንብረቶች ወድመዋል። በሁለተኛው የዓለም ጦርነትም ከወደመው ንብረትና ሀብት ሌላ 50 ሚሊዮን ሕዝብ አልቋል። ኢምፔሪያሊስት አገሮች የሞኖፖሊስቶችን ጥቅም ለማስጠበቅ ሲሉ ከሚያስነሱት ጦርነቶች ሞኖፖሊስቶች ከፍተኛ ትርፍ ለመዛቅ ቢያስችላቸው የጦርነቶችን መቅሰፍት ግን የሚሸከመው ሠርቶአደሩ ሕዝብ ነው። በጦርነቶቹ ምክንያት ሠርቶ አደሩ ሕዝብ ከፍተኛ ጉዳት ስለሚደርስበት ሥርዓቱን ይጠላል፣ ብሎም ለመደምሰስ ይነሣል። ሙሉ ነፃነትና ሰላም ለሚያጎናጽፈው ለሶሻሊዝም ድል አድራጊነት ይታገላል።

### 2.3.3 በቅኝ አገዛዝና በእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ሥር ወድቀው በሚመዘበሩት ሕዝቦችና በኢምፔሪያሊስት ኃይሎች መካከል ያለው ቅራኔ ይፋፋማል

ኢምፔሪያሊስት ኃይሎች የአፍሪካን፣ የላቲን አሜሪካንና የእስያን ሕዝቦች በጠመንጃ ኃይል እ.ኤ.አ. 1875–1941 ተከፋፍለው በቁጥጥራቸው ሥር አዋሉ። ከዚያ በፊትም ካፒታሊዝም በአውሮፓ አገሮች ማቆጥቆጥ እንደጀመረ ብዙ አገሮች የቅኝ ግዛት ሆነው ነበር። ኢምፔሪያሊስቶች በቅኝ ግዛትነት በያዟቸው አገሮች በመጀመሪያ ወደቦችን በመክፈት፣ የቀረጥና የውጭ ንግዱን በመቆጣጠር ሸቀጣቸውን አምጥተው በማራገፍ ማዕድናትን በኃይል በመያዝ፣ ለንግዱ እንቅስቃሴ አመቺ እንዲሆን የመገናኛ አውታሮችን በመዘርጋት፣ ባዕድ በመፈንገል ሙሉ የኢኮኖሚ ቁጥጥራቸውን አስፈኑ፣ በየአገሩ የሕዝባቸውን ጥቅም አሳልፈው ለኢምፔሪያሊስቶች የሸጡትን ባላባቶችና ፊውዳሊስቶች ከጎናቸው በማሰለፍ ፖለቲካውንም መቆጣጠር ቻሉ። በኃይል የያዙትን አገር ይበልጥ ለመጠቀምና ለመመዝበር እንዲያስችላቸው በየአገሩ የጦር ሠፈር በመሥራት ወታደራዊ



ኢትዮጵያ ቅኝ ገዥነትንና የእድ አዘር ቅኝ አገዛዝን የተዋጋች አገር ናት (የ20ኛው ምዕተ ዓመት ታሪክ ከሚለው መጽሐፍ የተገኘ)


Proudly brought to you by
www.binyamhk.wordpress.com

ኃይል አሠፈረ። በጥቂት ወጪ ወይም ያለምንም ወጪ የቀኝ ግዛት ሕዝ
በችን የሥራ ኃይልና ጥሬ ዕቃዎች፣ ወዘተ... እየመዘበሩ የሞኖፖል
ኃይላቸውን አጠናከሩ። የቀኝ ግዛቶችና የከፊል ቀኝ ግዛቶች ብሔራዊ
የኢኮኖሚ ዕድገት ታፈነ:: የኢንዱስትሪ እንቅስቃሴ በተለይም የከባድ
ኢንዱስትሪ ዕድገት ተገታ:: ለዳበሩ የካፒታሊስት አገሮች የጥሬ
ዕቃዎች ብቻ አቅራቢ እንዲሆኑ ተገደዱ:: በዚህም የተነሣ በኢምፔ
ሪያሊዝም ሥር የወደቁ አገሮች ኢኮኖሚ የኢምፔሪያሊዝም ጥገኛና ተቀጥያ
ሆኑ::

ይህ ከዚህ በላይ የጠቀስነው በኢትዮጵያም ተፈጽሟል።
ኢትዮጵያን በቀጥታ የቀኝ ግዛት ለማድረግ የኢምፔሪያሊስት አገሮች
ለምሳሌ ጣሊያን፣ እንግሊዝ፣ ፈረንሣይ የተቻላቸውን ያህል ጥረት
አድርገው ነበር። ግን በኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ትግል ይህ ሊሳካላቸው
ባለመቻሉ በተዘዋዋሪ መንገድ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ተቀጥያ አደረ
ጉት:: ኢምፔሪያሊስት አገሮች በተለይም የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም
ከአቡንጓሊቱ የፊውዳል መንግሥት ጋር በመተባበር ኢትዮጵያን ለኢምፔሪያሊስት
አገሮች ጥሬ ዕቃዎች አቅራቢ እንድትሆን በማድረግ የኢንዱስትሪ
ዕድገት እንዳይስፋፋ ጀገደ:: የሠራተኛውንም የሥራ ኃይል አራክሰው
ከፍተኛ ብዝበዛ ፈጸሙበት:: ለረሃብ፣ ለድንቁርና ለበሽታ፣
አጋለጡት። የጦር ሠፈርም በመመሥረት ቁጥጥራቸውን አጠናከሩ፣ የፖለ
ቲካውን አመራር ለእነሱ እንደሚያመች አድርገው ቀየሱት:: ይህ
ሁኔታ ግን ሊቀጥል አልቻለም። ስለሆነም ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ
በ1966 በኢምፔሪያሊዝምና በቡችሎቹ ላይ የተባበረ ክንዱን አነሣ::
እንግዲህ እንደኢትዮጵያ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ በኢምፔሪ
ያሊዝም ብዝበዛ ሥር የወደቁ የዓለም ሕዝቦች ትግላቸውን በማፋፋም
ድልን በድል እየተጎናፀፉ ፍትሕና እኩልነት ላይ የተመሠረተ


ሶሺሊስት ኅብረተሰብ መገንባት ቢችሉ፣ የኢምፔሪያሊዝም መቃብር እውን እየሆነ ይሄዳል።

እነዚህ ከዚህ በላይ በአጭሩ ለማሳየት የሞከርናቸው መሠረታዊ ቅራኔዎች በትክክል የሚያበረዱን ኢምፔሪያሊዝም ወደሞቱ በመጓዝ ላይ ያለ ካፒታሊዝም መሆኑን ነው።


ኢምፔሪያሊዝም ወደ መቃብሩ በመጓዝ ላይ ያለ ካፒታሊዝም ነው ሲባል ጭቁን ሕዝቦች እጃቸውን አጣጥፈው በመቀመጥ ኢምፔሪያሊዝም በራሱ ይሞታል ወይም ይጠፋል ማለት አይደለም። ይህ ዓይነቱ አስተሳሰብ የቡርዧዋ አፈቀላጤዎች የሚያሰራጩት አደናጋሪ ፕሮፓጋንዳ ነው፡፡ "ኢምፔሪያሊዝም የሚሞት ካፒታሊዝም ከሆነ ለምን እስኪሞት አንጠብቅም፣ ይህን ያህልስ መስዋዕትነት ለምን እንከፍላለን" በማለት ሰፊውን ሕዝብ ከትግል በማዘናጋት የኢምፔሪያሊዝምን ዕድሜ ለማራዘም ይፍጨረጨራሉ። ኢምፔሪያሊዝምን በጸም በጸሎት ልንደመስሰው ከቶ አንችልም። ኢምፔሪያሊዝምን ልንደመስስ የምንችለው የነቃ፣ የተደራጀና የታጠቀ ኃይል መራራ ትግል ቢያካሂድ ነው። ሰፊው ወዛደር ሕዝብ በሚያካሂደው ወስብስብና መራራ ትግል ነባራዊና ሕሊናዊ ሁኔታዎች በለሟሉ ኢምፔሪያሊዝምን መደምሰስ ይችላል። ታላቁ ሌኒን "ኢምፔሪያሊዝም የሶሺሊስት አብዮት ዋዜማ ነው" እንዳለው በኢምፔሪያሊዝም መቃብር ላይ በሶሺሊዝም መገንባት የሚቻለው ወዛደሩና ጭቁን የኅብረተሰቡ ክፍሎች በኢምፔሪያሊዝም አስከሬ ብዝበዛ ላይ የተገበረ ክንዳቸውን ቢያነሱ ብቻ ነው።

## 3. <u>መንግሥታዊ ሞኖፖሊ ካፒታሊዝም</u>

በዘመነ ኢምፔሪያሊዝም የፋይናንስ ካፒታል ሞኖፖሊ አብዛኛውን የኅብረተሰቡን ሀብት በቁጥጥር ሥር ካዋለ በኋላ በኅብረተሰቡ ሕይወት ውስጥ በተለያዩ አቅጣጫዎች



ሞኖፖሊ ካፒታሊዝም ወደመንግሥታዊ ሞኖፖሊ ካፒታሊዝም መለወጡን የሚያሳይ (ለታዳጊ አገሮች ከማርክሳዊ ፖለቲካ ኢኮኖሚ
አንግር በዩሪ ፖፖቭ)


Proudly brought to you by
www.binyamhk.wordpress.com

ሠርጎ በመግባት የወሣኝነት ሚና ይጫወታል። ሠርቶአደሩን ሕዝብ ያለገደብ በመጨቆንና በመበዝበዝ ከፍተኛ የሞኖፖል ትርፍ ለማጋበስ ባለው ጽኑ ፍላጐት የመንግሥቱን የኢኮኖሚ የደም ሥር ከመቆጣጠር አልፎ የመንግሥቱን የፖለቲካ ሥልጣን ከመቆጣጠር ደረጃ ላይ ይደርሳል። በሞኖፖሊስቶች ቁጥጥር ሥር የዋለው የቡርዧው መንግሥት የፋይናንስ መሣፍንትን ጥቅም ለማስጠበቅ ዋነኛ መሣሪያ ይሆናል። በተለይ በካፒታሊዝም ውስጥ ያሉት የተለያዩ ቅራኔዎች እየተካረሩ ሲመጡ ሞኖፖሊስቶች በመንግሥት ላይ ያላቸውን ቁጥጥር ይበልጥ ያጠናክራሉ። በየጊዜው በመንግሥት አመራር ላይ ያሉ ባለሥልጣኖች ከካፒታሊስቶች ጋር ያላቸው ግንኙነት እየጠበቀ በመጣ ቁጥር ሞኖፖሊ ካፒታሊዝም ወደ መንግሥታዊ ካፒታሊዝም እየተለወጠ ይመጣል። የፋይናንስ ካፒታል ሞኖፖሊስቶች ከፍተኛ ባለሥልጣኖችንና የመንግሥት ሕግ አውጪዎችን በገንዘብ ኃይላቸው በመግዛት አፈ ቀላጤዎቻቸው እንዲሆኑ ያደርጓቸዋል። አብዛኛውን ጊዜም ሞኖፖሊስቶች የእነርሱን ቀጥረኞች በመንግሥት መዋቅር ውስጥ ወሣኝ ሹመፊነትቦታዎችን ያስይዛሉ። በሥልጣን ላይ የሚቀመጡም የሞኖፖሊስቶች ጥቅም አስጠባቂ ቡድን ካፒታሊስቶች በፕሮፖጋንዳቸው እንደሚያናፉት በሕዝብ ምርጫ ሣይሆን በሞኖፖሊስቶች ምርጫ ነው። ለምሳሌ ማንኛውም የአሜሪካን ፕሬዚደንትና የምክር ቤት አባሎች በሙሉ የሞኖፖሊስቶችን ድጋፍ ካላገኙ በስተቀር ሥልጣን አይዙም። ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ አይዘንሐወር የአሜሪካን ፕሬዚዳንት በመሆን ሥልጣን ሲይዝ የቻለው በሮክፌለርና በሞርጋን ሞኖፖሊስቶች ድጋፍ ነው። በ1955/እ.ኤ.አ./ በአይዘንሐወር አስተዳደር ውስጥ ከተገኙት 272 ከፍተኛ ባለሥልጣኖች መካከል 150 የሚሆኑት ትላልቅ ቡርዧዎች፣ 30 የሚሆኑት የትላልቅ ኮርፖሬሽኖች የሕግ አማካሪዎች ነበሩ። ከመካከላቸው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የነበረው ፎስተር ዳላስ የሮክፌለር ድርጅት ባለአደራ፣ የመከላከያ ሚኒስትር የነበረው ዊልሰን የጄኔራል ሞተርስ ኩባንያ ዋና አስተዳዳሪ፣ እንደነበሩ የታወቀ ነው። እንዲሁም እ.ኤ.አ. በ1961 በፕሬዚደንት ኬነዲ አስተዳደር ብዙ ወሣኝ የሆኑ መንግሥታዊ ቦታዎች ተይዘው የነበረው በትላልቅ ካፒታሊስቶች ነበር። ማክናማራ የፎርድ ሞኖፖሊ ድርጅት ፕሬዚዳንት የነበረ የመከላከያ ሚኒስቴር፣ ዳግላስ ዲሉን የዲሉንና የሪድ ኩባንያ መሪ የነበረ የገንዘብ ሚኒስትር ወዘተ... ጆን ኤፍ ኬነዲ የአሜሪካን ፕሬዚዳንት ሆኖ የተመረጠው የናጠጠ ሚሊየነር ነበር። የኬነዲ ቤተሰብ ሀብት 400 ሚሊዮንዶላር እንደነበር

የአደባባይ ምስጢር ነው። በሌሎችም ካፒታሊስት አገሮች አብዛኛዎቹ ባለሥልጣኖች እራሳቸው የሞኖፖል ድርጅቶች ባለከፍተኛ ድርሻ ወይም አስተዳዳሪዎች ናቸው፡፡

ይህ የፋይናንስ ካፒታል ሞኖፖሊ የመንግሥቱን ሥልጣን ብቻ ሳይሆን ሌሎች የላዕላይ መዋቅር አካሎችን ይቆጣጠራል። ጋዜጦች፣ ማተሚያ ቤቶች፣ ዜና ማሠራጫዎች፣ የቴሌቪዥንና የሲኒማ ኢንዱስትሪዎች፣ ሙዚየሞች፣ ሆስፒታሎች "የበጎ አድራጎት" ድርጅቶች ወዘተ... በሞኖፖሊስቶች ቁጥጥር ሥር ወድቀዋል። በእነዚህ መሣሪያዎች በመጠቀም የኅብረተሰቡን አስተሳሰብና አመለካከት እንደሚፈልጉትና እንደሚያመቻቸው ጠፍጥፈው ቀርጸውታል፡፡ ሀብታምና ድሃ ከጥንት ጀምሮ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣና ክርስቶስም ያስተማረን ይሄንኑ በለሆነ መቀበል አለብን ብለው ብዙውን ሕዝብ ሊያሳምኑት ይጣጣራሉ፡፡ ከዚህም ሌላ የካፒታሊስት ሥርዓት የመጨረሻውና ፍፁም ዲሞክራሲ የሰፈነበት ሀብትን የሚያትረፈርፍ ሥርዐት ነው፣ ይሉታል፡፡ በዚህ መርዛኛ ኘሮፓጋንዳቸው ዕድሜአቸውን ለማራዘም እየተጣጣሩ ናቸው።

መንግሥታዊ ሞኖፖል ካፒታሊዝም የቡርዧው መንግሥት ሙሉ በሙሉ ለሞኖፖሊስቶች ተገዥና አገልጋይ ነው በኋል እንዴት ነው ገልጋሎቱን የሚሰጠው?

1. በጀትና የብሔራዊ ሀብትን በሕግ በመደልደል ሞኖፖሊስቶች ከፍተኛ ጥቅም ሊያገኙ የሚችሉበትን ሁኔታበማመቻቸት፣
2. ሞኖፖል ቡርዧዊ ካፒታል እንዲሰበሰብና እንዲማከል ብሎም መሰበተኛና አነስተኛ የግል አምራች ድርጅቶችን እንዲውጥ አመቺ ሁኔታዎችን በማዘጋጀት፣
3. የኃይል ማመንጫዎችን፣ የመገናኛና የመጓጓዣ ወዘተ... ተቋሞችን በመንግሥት ቁጥጥር ሥር በማዋል ከሠራተኛው ሕዝብ በሚሰበሰበው ታክስ በመደጎም ለሞኖፖል ቡርዧው በቅናሽ ዋጋ በመሸጥ ወይም በማከራየት ከፍተኛ ትርፍ እንዲያገኝ በመርዳት፣

4. የሞኖፖል ቡርዧው የሚያመርታቸው ሸቀጦች በዓለም ገበያም ሆነ በአገር ውስጥ ገበያ ተቀባይነት ቢያጡ ቡርዧው ኪሳራ እንዳይደርስበት መንግሥት በጅምላ ገዝቶ በማቃጠል ወይም ባሕር ውስጥ በመወርወር ወይም በእርዳታና በብድር ስም ለኋላቀር አገሮች በማቀረብ ሞኖፖሊስቶችን ከኪሳራ በማዳን፣

5. የሞኖፖል ቡርዧው እንዳይከስር ከመንግሥት ቀረጥና ግብር ልዩ ልዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ነፃ በማድረግ፣

6. የሞኖፖል ቡርዧውን ይበልጥ ለማጠናከር መንግሥት ሊገለገልባቸው አማይችል ወይም ማኅበራዊ ጠቀሜታ የሌላቸው ሸቀጦች በከፍተኛ ወጪ እንዲመረቱ በማድረግ ወዘተ... ነው::

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ነጥቦች የቡርዧው መንግሥት ለሞኖፖሊስቶች የሚያበረክታቸው ገልጋሎቶች ይሁኑ እንጂ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገዱ ሞኖፖሊስቶች የሚጠቅሙት መንግሥት ኢኮኖሚውን ወደጦር ኢኮኖሚነት ቢለውጠው ነው:: ኢኮኖሚው ወደጦር ኢኮኖሚነት ቢለወጥ በተለያዩ የኢኮኖሚ ዘርፎች ብዙ ኢንዱስትሪዎች የግል ይዞታነታቸው ሳይለወጥ በአስተዳደር በኩል በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ይወድቃሉ። ይህም የሚሆነው ለሞኖፖሊስቶች በቂ የሥራ ኃይል ለማስገኘት፣ የጥሬ ዕቃዎች እጥረት ላለባቸው ኢንዱስትሪዎች ያለችግር ለማቀረብ እንዲቻል፣ ምርትን በቀላሉ ለማከፋፈል፣ የጦር መሣሪያ የሚያመርቱ ፋብሪካዎች በብዛት እንዲቋቋሙ ለማድረግ ወዘተ... ቢሆን የማምረቻ መሣሪያዎች ግን በግል ይዞታ ሥር እንደተጠበቁ ይቆያሉ::

በኢምፔሪያሊስት አገሮች የመንግሥት ይዞታ በጉልህ የሚታየው የጦር መሣሪያ ፋብሪካዎችን፣ የባቡር ሐዲዶችን፣ የማዕድን ድርጅቶችን፣ የኃይል ማመንጫዎችን፣ ወዘተ... በመንግሥት ወጪ በመገንባት ወይም ከፍተኛ ካሣ በመክፈል የተወሰኑ የግል

ድርጅቶችን ከቡርዣው በመረከብና በመንግሥት ቁጥጥር ሥር በማዋል ነው። ይህን በማስመልከት ሶሻል ዲሞክራቶች አንዳንድ የማምረቻና የአገልግሎት ድርጅቶች ቀስ በቀስ በቡርዣው መንግሥት ይዞታ ሥር እየዋሉ መምጣት "ካፒታሊዝም ቀስ በቀስ ወደ ሶሻሊዝም ያድጋል" ማለት ነው እያሉ ለማሳመን ይጥራሉ። ይሁን እንጂ በሞኖፖል ካፒታሊዝም ደረጃ አንዳንድ ድርጅቶች በመንግሥት ይዞታ መጠቃለላቸው ከሶሻሊዝም ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት የለውም። እናስረዳ፤ በመጀመሪያ ደረጃ በካፒታሊስት አገሮች የመንግሥት ይዞታ እንደኛው የካፒታሊስት ይዞታ ገጽታ ነው። ልዩነቱ የግል ካፒታሊስቶች ይዞታ ሣይሆን ሁሉም ካፒታሊስቶች በጋራ ሊጠቀሙበት ወይም ሊገለገሉበት መቻላቸው ነው እንጂ ለሠራተኛው ሕዝብ ምንም ልዩነት የለውም። ሠራተኛውን ይበልጥ ለሞኖፖሊስቶች ብዝበዛ ያጋልጠዋል።

ሞኖፖል የመንግሥትን ኃይል በመጠቀም ካፒታል በጥቂቶች እጅ እንዲሰበሰብና እንዲማከል በማድረግ ብቃታቸውና ጥንካሬያቸው ከፍ እንዲል ያደርጋል። ከሞኖፖሊ ነፃ የሆኑ የማምረቻ ድርጅቶች ለሞኖፖሊስቶች ተገዥ እንዲሆኑ መንግሥት በልዩ ልዩ መንገድ ያስገድዳቸዋል። በተለይ በጦርነት ጊዜ የቡርዣው መንግሥት እያዘዘው ምርት በሞኖፖል ድርጅቶች እንዲመረት በሰሚፈልግ አነስተኛና መለስተኛ አምራች ድርጅቶች እንዲዘጉ ያስገድዳቸዋል።

ሞኖፖሊስቶችን ጥቅም ለማስጠበቅ የቡርዣው መንግሥት ወደ አገር ውስጥ በሚገቡት ሸቀጦች ላይ ከፍተኛ ቀረጥ እንዲጣል ሲደነግግ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ሞኖፖሊስቶች ዕቃዎች በመሸጥ የውጭ ገበያ ሊንሰራፋ ያደርጋል። ይህም የሚሆንበት ምክንያት በዓለም አቀፍ ደረጃ ሸቀጦችን ማራገፊያ የሚሆኑ አዳዲስ ገበያዎችን በመቆጣጠር የጭቁን ሕዝቦችን ሀብት ለመበዝበዝ እንዲችል ነው። ሞኖፖሊስቶች መንግሥት ሠራተኛው ላይ ከፍተኛ ቀረጥ /ግብር/ እንዲጥልና በበጀት ከፍተኛ ትርፍ የሚያስገኙቸው ውል እንዲሰጧቸው ያደርጋሉ።

"የንግዱን እንቅስቃሴ ለማበረታታት" በሚል ሰበብ የቡርዧው መንግሥት ለትላልቅ ሞኖፖሊስቶች መጠን የለሽ ድጎማ ይሰጣል። በአጋጣሚ ሞኖፖሊስቶች ኪሣራ ቢገጥማቸው ከመንግሥት የኪሣራ ማካካሻ ይሰጣቸዋል። ያለባቸውም የመንግሥት ግብር ሙሉ በሙሉ ይሠረዝላቸዋል።

በሌላ በኩል መንግሥታዊ ሞኖፖሊ ካፒታሊዝም የሀብት ማለትም የምርት መገልገያዎች በከፍተኛ የዳበሩበትና ማኅበራዊ አመራረት የላቀ የዕድገት ደረጃ ላይ የደረሰበት ነው። ይህም ካፒታሊዝምን በሶሻሊዝም ለመተካት ቁሳዊ መሠረትን ያረጋግጣል። ሌኒን እንዳለው መንግሥታዊ ሞኖፖሊ ካፒታሊዝም በሚገባ ለሶሻሊዝም ቁሳዊ ዝግጅት የሚጠናቀቅበት ወቅት ነው።

በሁለተኛ ደረጃ መንግሥታዊ ሞኖፖሊ ካፒታሊዝም የወዝአደሩ አንጻራዊና ፍጹማዊ የኑሮ ሁኔታ ቁርቁዝ/ድኅነት/ እየወረደ እንዲሄድ ያደርጋል። ሞኖፖሊስቶች በመንግሥት ኃይል በመጠቀም በወዝአደሩና በገበሬው መደቦች ላይ የሚፈጽሙት ጭቆናና ብዝበዛ እየተባባሰ ሲሄድ በበዝባዦችና በተበዝባዦች መደቦች መካከል ያለው ቅራኔ ክረት ወደ ከፍተኛ ደረጃ ይሸጋገራል። ይህም ለሶሻሊስት አብዮት ሕሊናዊ ዝግጅት መሠረትን ይጥላል።

የቡርዧ ኢኮኖሚስቶች መንግሥት ለሞኖፖሊስቶች አገልጋይና ታዛዥ መሆኑን በመሸፈን መንግሥት የካፒታሊስት አገሮችን ብሔራዊ ኢኮኖሚ በዕቅድ ለመምራት ወሣኝ ሚና የሚጫወት ኃይል ነው ብለው ይሰብካሉ። እንደእውነቱ ከሆነ ግን የቡርዧው መንግሥት ኢኮኖሚውን በተቀነባበረ ዕቅድ ሊመራ የሚያስችል ምንም ዓይነት አመቺ ሁኔታ የለውም። ምክንያቱም አብዛኛው የኢኮኖሚው እንቅስቃሴ በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ሳይሆን በጥቂት ሞኖፖሊስቶች ይዞታ ሥር በመሆኑ ነው። ሞኖፖሊስቶች የሚመሩት በትርፍ እንጂ በማዕበላዊ ችሳን አይደለም። ይህ የሞኖፖሊ የናውና መሠረታዊ ባሕርይ ነው።

ሌላው የቡርዧ ኢኮኖሚስቶች ሊያሳምኑን የሚሹት "መንግሥት ኢኮኖሚውን ከውድቀት የሚጠብቅ ኃይል" መሆኑን ነው። ይህም እንኳን ቢባል የሞኖፖሊስቶችን ጥቅም ከማስጠበቅ አንፃር እንጂ የካፒታሊስት ስልተምርት ባሕርይ የሆኑትን የሥርዓተ አልባ አመራረት ዘዴንና የኢኮኖሚ ቀውስ ለመቆጣጠር ወይም ለማስተካከል አይችልም። ስለሆነም በካፒታሊስት ሥርዓት ውስጥ ያሉትን ቅራኔዎች ይበልጥ እንዲከረሩ ያደርጋል።

## 4. በዘመነ ኢምፔሪያሊዝም በካፒታሊስት አገሮች ያልተስተካከለ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ዕድገት ሕግና በአንድ አገር ሶሻሊዝም በድል አድራጊነት ሊወጣ ስለመቻሉ

በዘመነ ኢምፔሪያሊዝም የካፒታሊስት አገሮች ያልተስተካከለ /እኩ ያልሆነ/ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ዕድገት የናው መለያ ሆኖ ይቀርባል።

በኢምፔሪያሊስት አገሮች መሐል የነበረው የኢኮኖሚ ኃይል ልዩነት ቀደም ታይቶ በማይታወቅ ፍጥነት እየተለዋወጠ መጥቶአል። ይህም በአንፃሩ የኢምፔሪያሊስት አገሮችን የወታደራዊ ኃይል ሚዛን ለውጦታል። የኢኮኖሚና የወታደራዊ ኃይል ሚዛን እየተለዋወጠ መምጣት ከቀድሞ የቅኝ ግዛት ይዞታ ጋር ሊጣጣም አልቻለም። ስለሆነም ተከፋፍሎ የነበረውን ዓለም እንደገና መከፋፈል አስፈላጊነት እየጎላ መጣ። ዓለምን እንደገና ለመከፋፈል የተካሄደውም ትግል አስከፊ ጦርነቶችን አስከተለ። በዚህም ካፒታሊስት አገሮች ወታደራዊና ኢኮኖሚያዊ ኃይላቸውን አባዩ። በዓለም ያላቸው ሥፍራ እየተለዋወጠ መጣ።

እ.ኤ.አ. በ1860 እንግሊዝ በአንደኛ ደረጃ የዓለም የኢንዱስትሪ ውጤት አምራች ስትሆን ፈረንሣይ በሁለተኛ ደረጃ ትገኝ ነበር። በዚህ ወቅት አሜሪካና ጀርመን በኢንዱስትሪ ምርት ውጤት በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ነበሩ። ከአሥር ዓመታት በኋላ አሜሪካ ፈጣን የካፒታሊስት ዕድገት በማሳየቱ በፈረንሣይ አገር

ተተክታ ሁለተኛውን ደረጃ በትይዝ ፈረንሣይ ወደ ሦስተኛ ደረጃ አቆለቆለች፡፡ በሚ
ቀጥሉት አሥር ዓመታት የአሜሪካ ዕድገት ይበልጥ እየተፋጠነ መጥቶ በዓለም
የኢንዱስትሪ ውጤት በማምረት የአንደኛነቱን ወይም የመሪነቱን ቦታ ከእንግሊዝ ተረክባ
ስትወስድ፣ እንግሊዝ በሁለተኛ ደረጃ፣ ጀርመን በሦስተኛ ደረጃ ሲከተሉ፣ ፈረንሣይ
ወደ አራተኛ ደረጃ መውረድ ግድ ሆነባት፡፡ በሃያኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ ላይ
ጀርመን እንግሊዝን በመተካት ከአሜሪካ ቀጥሎ የሁለተኛውን ደረጃ ያዘች፡፡

በካፒታሊስት አገሮች እንዲህ እየተለዋወጠ የመጣው የኃይል ሚዛን የካፒታ
ሊስት አገሮችን በሁለት ተፎካካሪ ጎራዎች በመከፈል አሠቃቂ የዓለም ጦርነቶችን
አስከትሏል፡፡ በካፒታሊስት አገሮች ያልተስተካከለና ያልተመጣጠነ የኢኮኖሚና የፖለቲካ
ዕድገት ከሥርዓቱ ጋር የተቆራኘ በመሆኑ አሁንም የጦርነት ክብሪት ሊጫር ይችላል፡፡

በሌላ አንጻር በዘመነ ኢምፔሪያሊዝም ያልተስተካከለ የኢኮኖሚ ዕድገት ያልተ
መጣጠነ የፖለቲካ ዕድገት በማስከተሉ በተለያዩ ጊዜያትና አገሮች ለወዝአደሩ አብዮት
ፖለቲካዊ ሁኔታዎች እየተመቻቹ ሊመጡ ችለዋል፡፡ ከእነዚህም ፖለቲካዊ ሁኔታዎች ዋና
ዋናዎቹ በበዝባዦችና በተበዝባዦች መደቦች መሐል ያሉት ቅራኔዎች የበለጠ መክረርና
የመደብ ትግሉ መፋፋም፣ የሠራተኛው ሕዝብ የንቃተሕሊና ደረጃ የበለጠ ከፍ ማለት፣
ወዝአደሩ ፖለቲካዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ የበለጠ ትኩረት ማድረጉና መደራጀቱ፣ በአብዮታዊ
እንቅስቃሴዎች ውስጥ ንቁ ተሳትፎ ለማድረግ ዝግጁ መሆኑ፣ የሠራተኛው መደብ ሰፊውን
አርሶ አደር ከጎኑ ለማሰለፍ መቻሉና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

ሌኒን በዘመነ ኢምፔሪያሊዝም ያልተስተካከለ የካፒታሊስት አገሮች የኢኮኖሚና
የፖለቲካ ዕድገት ሳቢያ በጥቂት አገሮች ወይም በአንድ አገር ብቻ ሶሻሊዝም ድል
አድራጊ ሊሆን ይችላል፣ እንዳለው ሁሉ ያልተስተካከለ የካፒታሊስት አገሮች የኢኮ
ኖሚና የፖለቲካ ዕድገት ሕግ ለሶሻሊዝም ድል ማድረግ አንደኛው መነሻ ነጥብ ሊሆን
ችሏል፡፡

ማርክስና ኤንግልስ በ19ኛው ምዕተ ዓመት አጋማሽ ላይ ቀደም ሞኖፖሊ ካፒታሊዝምን ሲያጠኑ በአብዛኛው በሠለጠኑ/በዳበሩ/ ካፒታሊስት አገሮች የሶሻሊስት አብዮት በአንድ ጊዜ ወይም በተያያዘ አኳኋን ሊካሄድ እንደሚችል ቢጠቁም የካፒታሊዝም ወደ ኢምፔሪያሊዝም የዕድገት ደረጃ መሸጋገር ሁኔታውን ለወጠታል። በሃያኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ ላይ በተለይም በአንደኛው የዓለም ጦርነት ወቅት ሁኔታዎች በፍጥነት በመለዋወጣቸው ሞኖፖሊ ካፒታሊዝም የካፒታሊዝም ዋና ገጽታ ለመሆን በቃ። እያደገ የመጣው ካፒታሊዝም እያቆለቆለና እየሞተ ወደሚሄድ ካፒታሊዝም ማለትም ኢምፔሪያሊዝም ተሸጋገረ። የአንደኛው ዓለም ጦርነት ቁራሽ ሊጠገን የማይችለውን የኢምፔሪያሊስት ደካማ ጎኖችን ጉልቶ አደርጎ አሳየ:: ያልተስተካከለ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ዕድገት በተለያዩ ካፒታሊስት አገሮች የወዝአደሩን ትግል በሚመለከት የተለያዩ ሁኔታዎችን እንደሚያስከትል ታየ። ለወዝአደሩ ትግል መቃናት ሁኔታዎች በሁሉም አገሮች ተሟልተው ሊገኙ አለመቻላቸው ግልጽ እየሆነ መጣ:: ሌኒን ይሄንን አዲስ ሁኔታ ከማርክሲዝም ጋር በማገናዘብ የሶሻሊስት አብዮት የኢምፔሪያሊዝም የብዝበዛ ሰንሰለት እጅግ በጣም ልል በሆነ በአንድ ወይም በርከት ባሉ አገሮች ሊካሄድ እንደሚችል በባይንቧ ትንታኔ አሳየ::

ይህ አዲስና መሠረታዊ የሶሻሊስት አብዮት ንድፈ ሃሣብ የተፈጠረው በሌኒን ሲሆን፣ ንድፈ ሃሣቡ ማርክሲዝምን ከማዳበሩም በላይ በተለያዩ አገሮች ለሚገኙ ወዝአደሮች የብሩህ ተስፋ በር ከፈተላቸው:: የያገሩ ወዝአደሮች በቀዳሚያ የራሳቸውን የቡርዧ መደብ መታገልና መደምሰስ እንደሚገባቸው ግልጽ ሆነ:: የወዝአደሩም አብዮት የኢምፔሪያሊዝም ቀለበት በላላበት ቱራ በቱራ በዱል አይራጊነት እንደሚወጣ ብዙ ባይቆይ በሩሲያ አብዮት ሊረጋገጥ ቻለ::

በአወቃላይ ዛሬ ለሶሻሊስት አብዮት በዓለም ካፒታሊስት የኢኮኖሚ ሥርዓት ውስጥ ነባራዊ ሁኔታዎች ተሟልተው ይገኛሉ። የሶሻሊስት አብዮት በዱል አይራጊነት እንዲወጣ የተደራጀ አንድነቱ የጠነከረ በአብዮታዊ ፓርቲ የሚመራ የወዝአደር መደብ፣

እንዲሁም የወዝአደሩ ጠንካራ አጋርና ተከታይ ሆኖ ከኢምፔሪያሊዝም ጋር ቆራጥ ትግል ሊያካሂድ የሚችል የገበሬ ክፍል ሊኖር ይገባል።

በዘመኑ ኢምፔሪያሊዝም በካፒታሊስት አገሮች ያሉ ወዝአደሮች፣ በብዝበዛ ሥርዓት ላይ ያላቸው ጥላቻ እያደገ ሲመጣ አብዮታዊ ወኔውም እየጨመረ ይሄዳል።

በቅኝ ግዛትና በእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ሥር ወድቀው የሚመዘበሩት ሕዝቦች በኢምፔሪያሊዝም ላይ የሚያካሂዱት የብሔራዊ ነፃነት ትግል እየዳበረ ይሄዳል።

ዓለምን እንደገና ለመቀራመት ወይም ለመከፋፈል ኢምፔሪያሊስቶች የሚያካሂዷቸው የኢምፔሪያሊስት ጦርነቶች የኢምፔሪያሊዝምን ሥርዓት ቢያዳክሙ የወዝአደሩን አብዮት ይበልጥ እያቃረቡት ይመጣሉ።

በአንድ አገር በድል አድራጊነት የወጣው ሶሻሊስት አብዮት ለዓለም ሶሻሊስት አብዮት የመጀመሪያውና አለኝታው ነው። ሌኒን ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ እንዳመለከተው ሶሻሊስት አገሮች በሚሰጡት ድጋፍና በሚያካሂዱት መራራና ውስብስብ ትግል በኢምፔሪያሊስት አገሮች የሚገኙት ወዝአደሮች ድልን ይቀዳጃሉ። እንዲሁም በሶሻሊስት አገሮችና በካፒታሊስት አገሮች የሚገኙ ወዝአደሮችና ተራማጅ ኃይሎች በሚያደርጓቸው እርዳታና በትግላቸው በኋላ ቀርና በቅኝ ግዛት አገሮች የሚገኙት ሠርቶአደሮች የኢምፔሪያሊዝምን የጭቆናና የብዝበዛ ቀንበር አንኮታኩተው ሰው በሰው የማይበዘበዝበት አዲስ ሶሻሊስት ኅብረተሰብ የመገንባት ትግላቸውን ይያያዙታል። ይህ ሁሉ ዛሬ በተግባር እየታየ መሆኑን ከአካባቢያችንና ከራሳችንም ሁኔታ የምንገነዘበው ነው።

## 5. የካፒታሊዝም አጠቃላይ ቀውስ

የሰው ልጆች ለነጻነት፣ ለእኩልነትና ለፍትሕ የሚያደርጉት ትግል፣ ጭቆናና ብዝበዛ እስከአለ ድረስ የማያቆም መሆኑን ቀደም ባሉት ምዕራፎች ተረድተናል። አሁንም ትግሎቻቸውን በበዝባዦችና በጨቋኞች ላይ እያካሄዱ አዲሱን ሶሻሊስት ኅብረተሰብ እውን ለማድረግ ያላሰለሰ ትንንቅ በማካሄድ ላይ ናቸው። ብዙ አገሮችም ወደዚሁ አዲስ ኅብረተሰብ እያመሩ ነው። ይህ ከካፒታሊዝም ወደሶሻሊዝም የሚደረገው ጉዞ ራሱን የቻለ ታሪካዊ ወቅት ነው። ያለንበት ወቅት በሶሻሊዝምና በካፒታሊዝም መካከል ያለው ቅራኔ እጅግ በጣም የከረረበትና፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ ሶሻሊስትና ብሔራዊ የአርነት አብዮቶች ኃይልን በኃይል እየተቋቋሙ ወደፊት የሚገሰግሱበትና ወሳኝ የትግል ምዕራፍ ላይ የደረሰበት ዘመን ነው።

የወዛደሩ አብዮት ድል ባደረገባቸው አገሮች ውስጥ የሶሻሊዝም ግንባታ ከከፍተኛ ደረጃ ደርሷል። ካፒታሊዝም ባንሰራፋባቸው አገሮችም የወዛደሮች ትግል እየተፋፋመና እየተጠናከረ ቢሄድ፣ በአንጻሩ ካፒታሊዝም ቀውስ ውስጥ እያዘቀጠ ነው። በመሆኑም ካፒታሊዝም በኢኮኖሚ፣ በፖለቲካና በርዕዮተዓለም መስኮች ውድቀትና ሽንፈት እየደረሰበት ነው።

በለዚህ፣ የካፒታሊዝም አጠቃላይ ቀውስ ማለት የካፒታሊስት ሥልተ ምርት የእድገትና የመስፋፋት ዘመን ወርዶ ወደግብአተ መሬቱ እያሽቆለቆለ መሄዱና በአብዮታዊ ትግል በሶሻሊዝም እየተተካ መምጣቱን የሚያሳይ ታሪካዊ ሂደት ነው። ይህ ቀውስ የተለያዩ ገጽታዎች እና የእድገት ደረጃዎች ያሉት ቢሆንም፣ ጠቀለል ባለ ሁኔታ በሚከተለው መልክ በመመደብ ሂደቱን ለማየት ይቻላል።

የዓለም ምዝበሮና ጭቁን ሕዝቦች ካፒታሊዝምን በመዋጋት ረጅም ዘመናት አሳልፈዋል። ሆኖም የተጣሉበት ዓላማና ስልት ቀስ በቀስ ከጭፍንነት፣ ከገር ጻፊነትና ከሥልት አልባነት ወደሳይንሳዊነትና ጥራት ወዳለው ዓላማና ሥልት እያደገ የመጣው በሳይንሳዊው ርዕዮተዓለም መከሰት ነው። በጭቁኖችና በምዝበሮች የትግል ታሪክ ውስጥ ከፍተኛውን ቦታ ይዞ የሚገኘው የዓላማቸውና የትግባራቸው አንድነት የሚረጋገጥበት የማርክሲስት ሌኒኒስት ፓርቲ መፍጠራቸው ቢሆን፣ ይህም ሰዉል አዉራጎነታቸው ጽኑ መሠረትነቱን በተግባር ያረጋገጠ ነው። በዚህ ፓርቲ መሪነት ካፒታሊዝምን ተቃውመውና ድል አድርገው የዓለም አንዱ ክፍል በሆነችው በሶቪዬት ኅብረት ውስጥ ሶሺሊዝምን ለመጀመሪያ ጊዜ ለመሠረት ችለዋል። ብዝበዛና ጭቆናም ዘላለማዊነታቸው ቀርቶ አላፊና ጠፊ መሆናቸው ታየ።

እስቲ የዚህን አመጣጥና ያስከተለውንም ሁኔታ ጠቅለል አድርገን ለመመልከት እንሞክር። በመሠረቱ ይህ የካፒታሊዝም አጠቃላይ ቀውስ በየጊዜው በተደጋጋሚ እንደሚደርሰው የካፒታሊስት ኤኮኖሚ ቀውስ አይደለም። አጠቃላይ ቀውሱ ከኤኮኖሚ ቀውሱ የሚለይበት ዓይነተኛው ነገር ዙሪያ ገብ የሆነ የኤኮኖሚ፣ የፖለቲካና የርዕዮተዓለም ቀውስ በማውረስ ለካፒታሊስት ሥርዓት የደረጃ በደረጃ አርጅናን በማስከተሉ በአዲሱ የሶሺሊስት ሥርዓት መተካቱ እንደማይቀር የሚያሳይ መሆኑ ነው። ይህ አጠቃላይ ቀውስ በድንገት ወይም አንዳንድ የኢምፔሪያሊስት አገር መሪዎች በሚፈጥሩት ስሕተት የመጣ ሳይሆን በሥርዓቱ ውስጣዊ ጥንካሬ መዳከም ማለትም በሥርዓቱ ባሕሪ ምክንያት የውስጡ ቅራኔ በመባባሱ የሚፈጠር ነው። ቀውሱ የሚያቋርጥ ሳይሆን ደረጃ በደረጃ የሚያድግና የጎላ የሶሺሊዝምን መመሥረት የሚጠይቅ ነው። ለዚህም ነው የካፒታሊዝም አጠቃላይ ቀውስ ካፒታሊዝም ተገርስሶ የሚወገድበትና ሶሺሊዝም የሚመሠረትበት ዘመን፣ ሶሺሊስት አብዮቶችና ብሔራዊ የአርነት እንቅስቃሴዎች በኢምፔሪያሊዝም ላይ የሚነሱበት

ወቅት ነው የሚባለው። በኢምፔሪያሊዝም ላይ ለነዚህ ኃይሎች መነሣታቸው የግድ ነው። ምክንያቱም ኢምፔሪያሊዝም የሥርዓተ ማኅበሩ ማእተሚያ፣ የእርጅናው መገለጫ በለሆነ አዲስ ሥርዓት እንዲፈጠር የሚጠይቅ ነውና። በለሆነም ኢምፔሪያሊዝም በራሱ ቅራኔ ተወጥሮ በተዳከመበት ሩሲያ ውስጥ የሶሺሊስት አብዮት ፈንድቶ ሶሺሊዝም እንዲመሠረት አስችሏል። ይህም ብቻ አይደለም። ካፒታሊዝም ወደ ኢምፔሪያሊዝም አደገ ወይም ወደዚህ ደረጃ ገባ ማለት የካፒታሊዝም አጠቃላይ ቀውስ ተጀመረ ማለት ነው። ይህም አጠቃላይ ቀውስ ከአንደኛው የዓለም ጦርነት ጀምሮ እየታየና እየዳበረ፣ ለአዲስ ሥርዓት መከሰት አመቺ ሁኔታን እየፈጠረ በመምጣቱ ዓለም በሁለት ኃይሎች በሶሺሊዝምና በኢምፔሪያሊዝም መካከል እንድትከፈልና ኢምፔሪያሊዝም የዓለም ብቸኛ ኃይል መሆኑ ቀርቶ ተቀናቃኝ ሥርዓት እንዲፈጠር ማድረጉ ተረጋግጧል።

በኢምፔሪያሊዝም /ሞኖፖሊ ካፒታሊዝም/ ምክንያት የተፈጠረው የአንደኛው ዓለም ጦርነት ሞኖፖል ካፒታሊዝም ወደ መንግሥታዊ ሞኖፖል ካፒታሊዝም እንዲሸጋገርና ሶሺሊስት አብዮትም እንዲነሳ አመቺ ሁኔታን ፈጠረ። በዚህም የተነሣ በታላቁ የጥቅምት አብዮት የሩሲያ ከካፒታሊስት ኅብረተሰብ መገንጠል፣ በተለያዩ ቅኝ አገሮች የብሔራዊ ነፃነት ትግል መነሳሳት፣ በኢምፔሪያሊስት አገሮች የሚገኙ ወዛደሮች የኑሮ ሁኔታ በሞኖፖሊስቶች ርኅራኄ የለሽ ብዝበዛ ምክንያት ማሽቆልቆል፣ የገበያውን ስፋት እያጠበበው መምጣቱ ለገበያ እሽቅድድም የሚደረገውን ውድድር ይበልጥ እያባባሰው ስለሄደ በኢምፔሪያሊዝም ላይ ከፍተኛ የኢኮኖሚ ችግር ፈጠረ። በለሆነም ኢምፔሪያሊዝም ተቀናቃኙን በሩሲያ የተጣለውን የሶሺሊዝም መሠረት ለማስወገድና ብቸኛ ኃይል ለመሆን፣ እንዲሁም ከደረሰበት አጠቃላይ ቀውስ ለመውጣት በግብታዊነት የሚይዝ የሚወጥነውን በማጣት በነፃይቱ ሩሲያ ላይ ወረራውን ቀጠለ። ግን ሽንፈትን ተከናንቦ የሶሺሊዝምን መኖር የግድ እንዲቀበል የተደረገበት ወቅት ሆነ እንጂ መፍትሔ አድርጎ ያቀረበው ወረራ

ባለፉት ምዕራፎች በዝርዝር እንደተመለከትነው የዕቃዎች ለውጥ የሚካሄደው በእሴታቸው ላይ በመመሥረት እንደመሆኑ ካፒታሊስቱ አንዱን ሸቀጥ ለማምረት የሚያስፈልጉትን ነገሮች ማለት የሥራ ኃይል፣ ጥሬ ዕቃና የማምረቻ መሣሪያዎች የሚገዛው በእሴታቸው ነው። በተመሳሳይ መልክ የሚያመርታቸውንም ሸቀጦች ሊሸጥና ሊለውጥ የሚችለው በእሴታቸው ወይም ሸቀጦችን ለማምረት በወሰደበት አስፈላጊ ማኅበራዊ የሥራ ጊዜ መጠን ነው። ስለዚህ ምንም እንኳን እሴት የሚገለጸው በለውጥ ሂደት ውስጥ ቢሆንም የማናቸውም ሸቀጥ እሴት የሚመነጨው በምርት ሂደት ውስጥ ያንን ሸቀጥ ለማምረት በፈሰሰው አስፈላጊ ማኅበራዊ የሥራ ጊዜ መጠን እንደመሆኑ በለውጥ አማካይነት ተጨማሪ እሴት ሊፈጠር አይችልም። በሌላ አነጋገር ለውጥ በዕቃ መልክ ያለን እሴት በገንዘብ መልክ የሚቀይርበት ሂደት እንደመሆኑ በዚህ ሂደት ውስጥ የእሴቱ መልክ እንጂ መጠኑ ሊለወጥ አይችልም። ባጭሩ ለውጥ እኩሌታ እሴት ባላቸው ሸቀጦች መካከል የሚካሄድ እንደመሆኑ ትርፍ እሴት ወይም አጠቃላይ ትርፍ በርካሾች እንደሚሉት አንዱን ሸቀጥ በርካሽ ዋጋ ከመግዛትና በውድ ከመሸጥ ወይም በገበያ ውስጥ ከሚታየው የዋጋ፣ ውጣ ውረድ የሚመነጭ አይደለም።

እርግጥ በሸቀጦች የአቅርቦትና የፍላጎት መጠን አለመጣጣም የተነሣ በገበያ ውስጥ የሸቀጦች ዋጋ ከእሴታቸውም በላይ ሆነ በታች ከፍና ዝቅ ሊል ይችላል። ይህ የዋጋዎች ከእሴታቸው በላይና በታች መዋዠቅ አንዱ ካፒታሊስት በሌላው ካፒታሊስት ኪሣራ የሚከብርበትን ሁኔታ የሚያሳይ እንጂ የሌቤት ጭማሪን የሚያመለክት አይደለም። ይህንን በይበልጥ ለመገንዘብ የሚከተለውን ምሳሌ እንመልከት።

ለምሳሌ ያህል በአንድ ወቅት በአንድ ኅብረተሰብ ውስጥ የተመረቱ ብር ዋጋ ያላቸው 100 ናቸው እንበል። የአንዱ ብር ዋጋን እሴት በዋጋ ቢገለጥ

ማኪያቬ የሌለት ተግባራቸው አደረጉት። ይህ በሊበናሚና በፖለቲካ ረገድ የተፈጠረው አጠቃላይ ቀውስ በርዕዩተዓለሙም ላይ ተንፀባረቀ። የቡርዧው ርዕዩተዓለም ከዚህ የሊበናሚና የፖለቲካ ከስረት የሚያወጣ፣ ወርቶ አደራን ሕዝብ ከድህነት ማጥ ውስጥ የሚከትና ከማርክሲዝም ሌኒኒዝም አንፃር በአቻነት ሊቆም የማይችል መሆኑ በርዧው በርዕዩተዓለሙም በኩል ቀውስ እንዲደርስበት ሆኗል።

ባጠቃላይ የእነዚህ ሁኔታዎች ተጧልቶ መገኘት የሞኖፖል ካፒታሊዝም ወደ መንግሥታዊ ሞኖፖል ካፒታሊዝም መሸጋገርንና በዚህም የፋሽስት መንግሥታት ተፈጥረው ካገር ውስጥ ባሻገር በዓለም አቀፍ ደረጃ ለሁለተኛው የዓለም ጦርነት መነሻት ምክንያት መሆናቸውን አረጋግጧል። ከአንደኛው የዓለም ጦርነት እስከ ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ይደረስ ባለው ወቀትም የካፒታሊዝም አጠቃላይ ቀውስ የመጀመሪያው ደረጃ መጠና ቀቆን ቢያባይ፣ ለዚህ መለያ የሆኔት ቀደም ሲል የጠቀስናቸው የቦሻሊዝም በቦቭዬት ኅብረት መመሥረት፣ የብሔራዊ አርነት ለንቅስቃሴ መጀመርና በተለዩ ካፒታሊስት አገሮች ወዘደርኛ በሞኖፖሊያች ላይ የቀሰቀሴት አብዬት /ምንም በፋሽስት መንግሥታት ለጊዜው ቢመታም/ ታይተዋል፡ ፡

ሞኖፖሊያች ባስነሷቸው ሁለት የዓለም ጦርነቶች ወርደትን ከመከናነባቸውም በላይ ከእነቡ አንፃር በዓለም ላይ ሌላ አዲስ ኃይል ሕልውና አግኝቶ የሚገታቸው መሆኑን ተረድተዋል። ሕልውናውን ባይወዱ በግድ በደረሰባቸው ሽንፈት ተቀብለዋል። ኢምፔሪያሊዝም አየደቀቀ ቦሻሊዝም ኃያል ሆኗል። በእነዚህ ሁለት ጦርነቶች ወቀት ከፍተኛ የንብረትና የሰው ሕይወት ጠፍቷል። በዚህ በመጀመሪያው ቀውስ ውስጥ የደረሰውን ይህን ጥፋት ከሚከተለው ሠንጠረዥ መመልከት ይቻላል:—

| ጦርነት | የጠፋ የሰው ሕይወት | በገንዘብ ቢተመን |
|---|---|---|
| አንደኛው የዓለም ጦርነት | 10 ሚሊዮን በቆች ሞቶ፣ 20 ሚሊዮን አካል በንኳሳን ሆኑ | ከ260 እስከ 360 ቢሊዮን ዶላር |
| ሁለተኛው የዓለም ጦርነት | ከ50 ሚሊዮን በላይ ሞቶ፣ 90 ሚሊዮን አካለ ጉደሉ ሆኑ፣ | ከ3,300 እስከ 4,000 ቢሊዮን ዶላር |

ከላይ የጠቀስነው ሁለተኛው የዓለም ጦርነት አንዳንዱ ኢምፔሪያሊስት አገሮች እንደ አሜሪካ ያሉት ትርፍ ያገኙበት፤ ሌሎቹ ደግሞ ድል የተጎናፀፉበት ቢሆንም ለብዙዎቹ በኢኮኖሚ የደቀቁበት፤ በወታደራዊና ፖለቲካ ረገድ ሽንፈት የተከናነቡበት ወቅት ነበር ፡፡ በጦርነቱ ሳቢያ እንደ አሜሪካ ያሉት የጦር መሣሪያ በማምረት ጦርነት በሚካሄድባቸው አገሮች ውስጥ በመሸጥ እጅግ ከፍተኛ ትርፍ እንዲያጋብሱና ባጋጣሚው እንዲጠቀሙ አመቺ ሁኔታ ተፈጥሮላቸው ነበር ፡፡ ሌሎች የአውሮፓ ኃያላን መንግሥታት ደግሞ የጦርነት ሞገዱ ባገራቸው ውስጥ በመነሳቱ ከፍተኛ የንብረትና የሕይወት ጥፋት ደርሶባቸው ሊወጡት በማይችሉት ማጥ ውስጥ ገብተው እጅግ ተዳክመው ነበር ፡፡

በመሆኑም፤ በዚህ ጦርነት ወቅትና ጦርነቱም እንዳለቀ ኢምፔሪያሊስት አገሮች በከፍተኛ የውስጥ ቅራኔ ተወጥረው የነበር በመሆኑ በአብዛኛች አገሮች በተለይም በምሥራቅ አውሮፓ የተነሣውን የወዛደሩን አብዮታዊ ማዕበል ሊገቱ በሚችሉበት ሁኔታ ላይ አልነበሩም፡፡ እነዚህ የምሥራቅ አውሮፓ አገሮች መንግሥታት በፋሺስት ወረራ ምክንያት የጀርመን፤ የጣሊያንና የጃፓን ፋሺስት መንግሥታት ተቀጥላዎች ሆነው ያገለግሉ ስለነበር ጦርነቱ ከምሥራቅም ከምዕራብም በኩል ያደቀቃቸው በመሆኑ ከሁሉም የከፋ ሁኔታ ላይ ነበሩ፡፡ ስለሆነም ሠራተኛው መደብና የኮምዩኒስት ፓርቲዎች ከሶቪዬት ሕብረት ባገኙት ርዳታ በቀላሉ የሠራተኛውን መደብ የበላይነት በማረጋገጥ ወደ ሶሻሊዝም ማምራት ቻሉ፡፡ የምሥራቅ አውሮፓ ከኢምፔሪያሊዝም ከምኝ መውጣትና ብቸኛ ወደ ነበረችው የሶሻሊስት መሠረት አገር መቀላቀል የዓለም ሶሻሊስት ሥርዓት እንዲጠናከር ስላደረገ የዓለምን የኃይል ሚዛን አናጋው፡፡ የምሥራቅ አውሮፓ አገሮች ብቻ ሣይሆን ከሩቅ ምሥራቅም ከፊል ቅኝ ግዛት የነበረችው ቻይና በረጅም ጊዜ ትግል ከዚያ ሥርዓት በድል በመውጣት ወደ ሶሻሊዝም ጎዳና በማምራቷ ሌላ ተጨማሪ ኃይል ሆነች፡፡

በሌላ በኩል በመጀመሪያው የካፒታሊዝም አጠቃላይ የቀውስ ደረጃ ማለትም ከአንደኛው የዓለምጦርነት እስከ ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ባለው ጊዜ ተቀስቅሰው የነበሩት የብሔራዊ አርነት እንቅስቃሴ ትግሎች ተጠናክረው በጦርነቱ ማግሥት ከፍተኛ

ደረጃ ላይ ደርሰው ነበር። ስለዚህም፣ ቀኝ ገዢዎች በጦርነቱ ክፉኛ በመመታታቸው ኃይላቸው ከመዳከሙም በላይ ቀኝ ገዛቶች ከሶሻሊስት አገሮች ያላቸው ድጋፍና ርዳታም ይበልጥ ስላበረታታቸው ኢምፔሪያሊዝምን በየአቅጣጫው እየመቱ የፖለቲካ ነፃነት እየተቀዳጁ ሄዱ። ብዙ የእስያ አገሮች ከኢምፔሪያሊዝም ቀኝ ተገዥነት ወጡ። ይህም ከምንጊዜውም የበለጠ የኢምፔሪያሊስቱ ካምፕ እየጠበበ መምጣቱን አረጋገጠ። አጠቃላይ ቀውሱም ሥርዓቱን ካላጠፋ በስተቀር የማያቆም መሆኑ ታየ። በየጊዜው የኢምፔሪያሊዝምን የጭቆና ቀንበር እየሰበሩ የሚሄዱት አገሮች እንደመብዛታቸው የጥሬ ሀብት ምንጩንና የገበያ ክልሉን እያጠበቡት መምጣታቸው ገሀድ ሆነ።

በዚህ ወቅት በኢኮኖሚው መስክም የተለያዩ ሁኔታዎች ተከሰተዋል። የሶሻሊስቱ ሥርዓት እየተጠናከረ በመምጣት ከካፒታሊዝም ይልቅ ከፍተኛ የኢኮኖሚ የዕድገት ደረጃ በማሳየቱ የሶሻሊዝም የበላይነት ተረጋገጠ። ለምሳሌ፣ እ.ኤ.አ. በ1937 በኢንዱስትሪ ምርት አካባቢ የሶሻሊስት አገሮች ድርሻ 10 በመቶ የነበረው እ.ኤ.አ. በ1955 27 በመቶ ማደጉ ይህንኑ ነው የሚያሳየው።

በሌላ በኩል፣ ኢምፔሪያሊስት አገሮች ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት በኋላ በሣይንስና ቴክኖሎጂ አብዮት፣ እንዲሁም በአንዳንድ ሁኔታዎች የተነሣ ኢኮኖሚያዊ ዕድገታቸው የተፋጠነ መስሉ ቢታይም የኢንዱስትሪያዎች አስተዳደግ በደረሰባቸው ጥፋት የተነሳ /ጀርመን፣ ጃፓን፣ ጣልያን፣ እንግሊዝና ፈረንሣይ/ የተስተካከለ ባለመሆኑ በሁሉም አካባቢና አገር በእኩልነት ላይ ተመርኩዞ ያደገ አልነበረም። ስለዚህ በመካከላቸው በተፈጠረው ውድድር በበለጸጉትና /አሜሪካ/ በደከሙት /ምዕራብ አውሮፓ/ አገሮች መካከል የገበያ ሽሚያ በመድራቱ አንዱ አንዱን መዋጡ የግድ ነው። ይህ ከመሆኑም የተነሣ ባገር ውስጥም ከአንዱ የኢኮኖሚ ተቋም ካፒታልን ወደ ሌላው በማዟዟር፣ የቀድሞውን በመዝጋትና ካፒታሉን ወደ

ለዱቤ ተቋም በማዞሩ በሚፈጠረዉ የማይፈለግ ምርት መመረት ምክንያት ገበያ ማጣት ሊሲዉ እየተባባሰ የሄደ ችግር ነበር። ካፒታልም በጥቂት ሞኖፖሊያች እጅ እየተጠቃለለ መምጣቱ የማይቀር ሆነ። ይህ ደግሞ የካፒታሊዝምን አርጅና ወይም ጊዜዉ እያለፈበት በመሄዱ ላይ ያለ ሥርዓተ ማኅበር መሆኑንና ቀራኔዉ ይበልጥ እየበሰ መምጣቱን ነዉ የሚያሳየዉ። በዚህ የተነሣ በካፒታልና በሥራ/በጉልበት/ መካከል ቅራኔዉ አደገ። ምክንያቱም የቴክኖሎጂ መዳበር ባንዱ በኩል ማለትም የምርት ኃይሎችን ማሻሻል እንደመሆኑ፣ በግል ባለቤትነት ዉስጥ የማምረቻ መሣሪያዎች መሻሻል ደግሞ የብዙ ወዛደሮችን ከሥራ መባረር አስከትሏል። በሌላ በኩል፣በሥራ ላይ የተሠማሩት ወዛደሮች ከማሽኖች መሻሻል የተነሣ አንዱ ወዝአደር ለራሱ ሕልዉና፣የሚበቃዉን ምርት የሚያመርትበትን አስፈላጊ የሥራ ጊዜ ቀንሶ ትርፍ የሥራ ጊዜዉን /ለካፒታሊስቱ የሚያመርትበትን/ ስለሚያበዛዉ ብዝበዛዉ ከምንጊዜዉም የከፋ ይሆናል። በመሆኑም ዋና የኢምፔሪያሊስት ቁጠራ በሚባሉት አገሮች ዉስጥ መንግሥታዊ ሞኖፖል ካፒታሊዝም እየገበገበ ሄደ። ይህ ደግሞ የሚያመራዉ ወደ ፋሺዝም በመሆኑ ፋሽስታዊ ፍላጎቱን ለማርካትና ኢምፔሪያሊዝም ለዘላለም ነዋሪ እንዲሆን ለማድረግ ቢል /ሊሆን አይችልም፣ ምክንያቱም ታሪክ በተደጋጋሚ እንዳሳየን ከሆነ የመጨረሻ የዉድቀት ደረጃዉ ነዉና/ ብዙ የኢኮኖሚ ተቋሞችን እና አብዛኛዉን የአገሪቱን በጀት ለጦር መሣሪያ ምርትና ለጦር ኃይል እንዲዉል አድርጓል። በዚህም የጦር መሣሪያ እሽቅድምድም ተፈጠረ። ይህም ጠብ አጫሪነትን አስከተለ። ይህ ከሁለተኛዉ የዓለም ጦርነት እ.ኤ.አ. እስከ 1955 ድረስ ባለዉ አካባቢ የተፈጠረዉ አጠቃላይ ቀዉስ ሁለተኛዉ ደረጃ መሆኑ ነዉ።

እ.ኤ.አ. 1955 አካባቢ ጀምሮ በሶሻሊዝም አማካኝነት በዓለም የኃይል ሚዛን ላይ የተፈጠረዉ ለዉጥ የካፒታሊዝም አጠቃላይ ቀዉስ ሦስተኛዉ ደረጃ ዉስጥ መግባቱን አመለከተ። ቀደም ያሉት አጠቃላይ ቀዉሶች ከአንደኛዉና ከሁለተኛዉ የዓለም ጦርነት ጋር ተያይዘዉ የመጡ ነበሩ። ይህኛዉ ግን ዓለም አቀፍ በሆነ

ምርነት አማካኝነት የመጣ አይደለም። ሆኖም በዚህ ደረጃ የታዩት ቀውሶች ከሙሳ ጉደል በአንደኛውና በሁለተኛው ደረጃ ቀውሶች ታይተው የነበረት ተባብሰውና አፅግው በመሸጋገር የመጡ ናቸው። እንዲህ በለ ተባለም በዚህ ደረጃ መሠረታዊና አዳዲስ የሆኑ ክስተቶች አልታዩም ማለት አይደለም።

በዚህ ወቅት ሶሺሊዝም ከካፒታሊዝም ጋር በሚያደርገው ታሪካዊ ውድድር በሊክናሚ፣ በባይንስና በቴክኖሎጂ ከፍተኛ ዕድገት ከማሳየቱም በላይ የመከላከያ ኃይሉን በማጠናከር ረገድ የበላይነቱን መያዙ አንዱ መሠረታዊ አዲስ ክስተት ነው። ከዚህ በተጨማሪም የኢምፔሪያሊዝም የና የማይነጥፉ ጥገኞች ሆነው ያገለግሉ የነበሩ የቀኝ ግዛት አገሮች ከምንዝሐውም በበለጠ ትግላቸውን አጠናክረው ከመዳፉ ያፈተለኩበት ወቅት ነው። በሌላ አቅጣጫ ደግሞ ኢምፔሪያሊስቶች ጥቂት ነፃ ያልወጡና ጥገኛ አገሮችን እንደገና ለገበያ ክፍፍል ለመቃረጥና የበላይነታቸውን ጋር ዝኛ የ በሆነ የቀኝ ገዢነት መልክ ለማረጋገጥ የሚያደርጉት ትግል ቀጠለ። ይህንንም ደከም ያሉ ቀኝ ገዢያች በሚጠቁበት ቦታ አሜሪካ በዕርዳታ ስም በመግባት የቀኝ ግዛት ሥርዓትን ለማቆየት በተለያዩ ቦታዎች በመፈጸም አባይታለች። ሌላው ባሕርይ የቀጥታ ቀኝ ገዢነት ጣክተም እየተረጋገጠ በመምጣቱ በምትኩ የመበዝበዣ መንገዱ የአዲ አዘር ቀኝ አገዛዝን ተግባር ላይ ማዋላቸው ነው። ኢምፔሪያሊስቶች ባበነቤት ሁለተኛው የዓለምጦርነት ብዙ የምዕራብ አውሮፓ ሞኖፖሊስቶች ተዳክመው በነበሩበት ጊዜ አሜሪካ ጠንካራ እንደነበረች ቀደም ሲል ገልጸን ነበር። ባሁኑ ወቅት ግን ተዳክመው የነበሩት በማገገም ከአሜሪካም ጋር ነፃ ውድድር መግጠማቸው በመካከላቸው ያለውን የኢምፔሪያሊዝም ውስጣዊ ቅራኔ አባባሰው። ክፉኛ ተመታ የነበረችው ጃፓን እንደገና በማንሠራራት ከፍተኛ የቴክኖሎጂ ዕድገት ላይ ደርሳ የብዙ አገሮችን ገበያ አጧበ በቻቸው። ምዕራብ ጀርመንም በከፍተኛ ደረጃ ያንሠራራችበት ወቅት ነበር። እስቲ ሁሉንም HCHC አፅርገን ለመመልከት እንሞክር፡፡

በዚህ ደረጃ የሶሻሊዝም የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የርዕዮተዓለም ትግል ልዩ ባሕርይ የሆነው በሰላም አብሮ የመኖር መርህ በሁለቱ ሥርዓተ ማኅበሮች መካከል ተግባር ላይ መዋል ጀመረ። ኢምፔሪያሊስቶች በሰላም አብሮ የመኖርን መርህ ለምን ተቀበሉ? ሶሻሊዝም ዓለም አቀፋዊ ሥርዓት ለየሆነ በመምጣቱና የዓለም የኃይል ሚዛን በመለወጡ ካፒታሊስቶች የሶሻሊስቱን ዓለም ከሚቷቸውት ወዲና እንደ ልባቸው ተነስተው ለመውረር በማያስችላቸው ደረጃ መሆኑ ነው። በሌላ በኩል በየትም አገር ያሉ ሠርቶአደር ሕዝቦች ሰላምን ከካፒታሊስቶች ይልቅ በለሚፈልጉት በሠርቶ አደር ሕዝቦች መካከል ሰላም እንዲሰፍን በተለያዩ ድርጅቶቻቸው አማካይነት ኢምፔሪያሊስቶችን ለዚህ እንዲንበረከኩ ተጽእኖ በለሚያሳድሩባቸው ነው። ሌላው ምክንያት በመርሁ ውስጥ ያሉት የማንኛውንም አገር ኢኮኖሚያዊ ሥርዓትን፣ ፖለቲካን፣ ርዕዮተዓለምን፣ ብሔራዊ ክብርና ዳንበርን፣ ባንዱ አገር ውስጥ ጣልቃ አለመግባትን፣ ወዘተ... የሚያወሱት ነጥቦች በአብዛኛው የሁሉም የጋራ ፍላጎት በለሚገልጹና የንግዱ ልውውጥን በለሚፈቅዱ ነው። እንዲህ ስለተባለም ሶሻሊስት አገሮች በካፒታሊስት አገሮች ውስጥ አብዮታዊ እንቅስቃሴ የሚያካሂዱ ወዝአደሮችን ትግል በሞራል፣ በማቴሪያልና በማስተማር ረገድ ዓለም አቀፋዊ ተልእኳቸውን አይወጡም ማለት አይደለም። እርዳታቸውንበሚችለው መንገድ ሁሉ ይሰጣሉ።

0 የሦስተኛው ደረጃ የካፒታሊዝም አጠቃላይ ቀውስ ዋና መለያ የዓለም ሶሻሊስት ሥርዓት በስፋት ተፈጥሮ ለኅብረተሰብ ዕድገት በጣም አስፈላጊ ሆኖ መገኘቱ ነው። በተለያዩ አገሮችም በየወቅቱ ይህን የሶሻሊዝምን ፈለግ ተከትለው ትግላቸውን ያካሄዱ አገሮች ድል እያደረጉ መምጣት የሶሻሊዝምን ድል አይቀሬነትና እያደገ መሄዱ የሚያረጋግጡ ሆኑ። ከዚህ ባሻገርም፣ አብዛኞቹ ሶሻሊስት አገሮች በመካከላቸው የጠበቀ ግንኙነት መፍጠራቸውና አዲስ አባል አገሮችም እያገኙ መምጣታቸው የሶሻሊዝምን መጠናከር ያበስራል። ከአሜሪካ አህጉር ሶሻሊዝምን በቆራጥነት የምታራምደዋ ኩባ ወደሶሻሊዝም

ጉዳና ያመራችው በዚህ ደረጃ ውስጥ ነው። ይህ ለአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም ታላቅ ሽንፈት ነበር። ባሁኑ ወቅት ደግሞ፣ ከእስያ ካምቦዲያ፣ ላኦስ፣አፍጋኒስታን፣ ከአፍሪካ ኢትዮጵያ፣አንጎላ፣ ሞዛምቢክ፣ ከላቲን አሜሪካ እነ ኒካራጓዋ እና ሌሎችም በትግል ጉዳና ላይ ያሉ ሁሉ እስካሁን ድረስ ከሚታየው ትግል ለመረዳት እንደሚቻለው የሶሻሊስት ኅብረተሰብ አባል የመሆን አዝማሚያ ነው የሚታይባቸው። አገሮቹ ወደሶሻሊዝም መምጣታቸውና ዓለም አቀፋዊ ሥርዓትነቱን ማበሩታቸው ብቻ ሣይሆን በተያያዙት የብልጽግና ጉዳና ከዓለም የኢንዱስትሪ ጠቅላላ ውጤት እ.ኤ.አ. በ1970ዎቹ መጀመሪያ 39 በመቶውን ምርት ማምረታቸው ከጊዜ ወደጊዜ የኢምፔሪያሊስቱ ካምኘ ድርሻ አያዘቀዘቀ እንዲሄድ አድርገዋል።

ሌላው የካፒታሊዝም ሦስተኛው አጠቃላይ ቀውስ መለያ ደግሞ ኋላ ቀር ናቸው በሚባሉት በአፍሪካና በላቲን አሜሪካ አህጉሮች ውስጥ የሚገኙ ሕዝቦች የኢምፔሪያሊዝም ቀኝ ግዛታዊ ሥርዓት አያሽቀለቀለ ብሔራዊ ነፃነታቸውን እየተ ጎናፀፉ መምጣታቸው ነው። ለምባለ በአፍሪካ ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በፊት ነፃ የነበሩ አገሮች ከሁለት ወይም ከሦስት የማይበልጡ ነበሩ። ባሁኑ ወቅት አልፎ አልፎ ካንዳንዱ ደሴቶችና በዘረኞች ከተያዙት አገሮች በቀር በይበልጥ እ.ኤ.አ ከ1960ዎቹ አካባቢ ጀምሮ በተደረገው የአርነት እንቅስቃሴ ሁሉም ብሔራዊ ነፃነ ታቸውን አግኝተው ብሔራዊ ሕልውናቸው ተረጋገጠላቸዋል። በሁሉም አህጉር የቅኝ ግዛት አገሮቹ ነፃ መውጣት በቅኝ ገዢነታቸው ታዋቂ የነበሩ እንደ እንግሊዝ ያሉ አገሮቹ ባዶ እጃቸውን እንዲቀሩ አድርጓል። በእንግሊዝ ግዛት ፀሐይ አትጠልቅም የሚለው አባባል አክትሞ ማጣፊያው አጥሮት በኢኮኖሚ ቀውስ እየዳሸቀ ነው።

በዚህ ደረጃ ላይ የኢምፔሪያሊዝም መንግሥታዊ ሞኖፖል ካፒታሊዝም ባሕርይው እያደገ በመሄዱ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቅራኔዎችም አብረው አደጉ። መንግሥታዊ ሞኖፖሊዎች በበለጸጉ ካፒታሊስት አገሮች ውስጥ የካፒታሊስትን ኅብረተሰብ ቅራኔዎች ለማባሳት ቢፈልጉም ኢኮኖሚውን ለማመጣጠን፣ የበለጠ የምርትን ቀውስ ለማቆም ወይም ደግሞ ዓለም አቀፍ የካፒታሊስት ኢኮኖሚያዊ ቀውስን ለመግታት አልቻሉም።

እንዲያውም ብዝበዛና ጭቆናቸውን በወዛደሩና ሞኖፖል ባልሆኑ ክፍሎች ላይ ከምንጊዜውም ይበልጥ እያባቡት በመምጣታቸው ማኅበራዊ ቅራኔያቸን አክርረው መደብ ትግሉ እንዲፋፋፍ ነው ያደረጉት። በሌላ በኩል ደግሞ፣ ቡርዧው ይበልጥ እያሿቆጠ ቢሄድ የዚያኑ ያህል ከሌላው መደብ ጋር ያለው ልዩነት እየሰፋ መሄዱ፣ ፍጹም አውራ የሆኑ ኢምፔሪያሊስት ኃይሎች አለምር ቧበ መሆንና በዲታነት ላይ ያላቸው ግትር አመለካከት፣ የቡርዧዎች ፖለቲካና ርዕዮተዓለም ከምንጊዜውም ይበልጥ እያሽቆለቆለ መሄዱን ያሳዩናል።

ከዚህ በላይ የጠቀስናቸው ነገሮች የሚያጃጡ አይደሉም። እንዲያውም ይበልጥ እየተባባሱ በመሄድ ላይ ናቸው።

ካፒታሊዝም የዘመኑ አብዮታዊ ሁኔታዎች በኢምፔሪያሊዝም ላይ የሚፈጥሯቸውን ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ርዕዮተዓለማዊ ቀውሶች እየተሻገራቸው በመሆኑ በራሱ ሥርዓት ውስጥ መፍትሔ ይፈልግላቸዋል፣ ወይም እየፈለገላቸው ነው የሚሉ ብዙ የዋህ ሰዎች አሉ። ይህ በመሆኑም ካፒታሊዝም እንደነበረ የሚኖር፣ የተደላደለ የሥርዓተ ማኅበር መረጋጋት የሚፈጥር አድርገው ይመለከታሉ። እ.አ.አ. ከ1970ዎቹ ጀምሮ የተፈጠሩትን ሁኔታዎች በትክክል ካጤናቸው ግን በካፒታሊዝም አጠቃላይ ቀውስ ውስጥ የዓይነት ለውጥ እየታየ መሆኑንና ቀውሱም እንደሚቀጥል መገንዘብ/መረዳት/ እንችላለን።

እ.አ.አ. ከ1970 ጀምሮ ብዙ አገሮች ከኢምፔሪያሊስት ካምፕ እየወጡ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ርዕዮተዓለማዊ ነፃነትን በመሻት፣ ፀረ ኢምፔሪያሊስት ትግል በማካሄድ ለዲሞክራሲና ለሶሻሊዝም እየታገሉ በሁለት ካምፕ በተከፈለችው ዓለም ውስጥ የኃይል ሚዛኑን እያዛቡ ናቸው። ኢምፔሪያሊዝምን ዐብቆ አጥቂ ወደሶሻሊዝም ካምፕ በመገባታቸው ኢምፔሪያሊዝም ክልሉ እየጠበበ፣ ሶሻሊዝም እየጎላ መሄዱ በኢምፔሪያሊዝም የኃይል ሚዛን ላይ አዲስ ቀውስ እየተፈጠረ መሄዱን የሚያሳይ ነው።

ከ1970 ወዲህ የቬትናም ከአሜሪካ የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ በአሸናፊነት መውጣትና የለየላት የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም ተቀጥላ ሆና የነበረችው ኢትዮጵያ ፊውዳሊዝምንና ኢምፔሪያሊዝምን በመምታት ትክክለኛውን የሶሻሊስት ፈር በመከተል በብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ አብዮት ወደፊት ማምራቷ፣ አንጎላ፣ ሞዛምቢክ፣ ካምፑቺያ፣ ላኦስ፣ አፍጋኒስታን፣ ኒካራጓ፣ የመሳሰሉት ከኢምፔሪያሊዝም ጋር የሞት የሽረት ትግል እያካሄዱ ከሶሻሊስት አገሮች ጋር መሰለፍ፣ ከላይ የጠቀስነውን የካፒታሊዝም አጠቃላይ ቀውስ እየተባባሰ መሄዱ የሚያረጋግጥ ነው። በየቦታው ዘረኝነትና ኢምፔሪያሊዝምን በመቃወም የሚካሄደው ትግል መጠናከር ሌላው ማረጋገጫ ነው። ይህ በኃይል ሚዛን ብቻ ሳይሆን ኢምፔሪያሊዝም እንደልቡ የሚመዘብራቸውን አገሮች በማጣቱ ከፍተኛ የኢኮኖሚ ቀውስም አስከትሎበታል።

በሌላ በኩል ደግሞ ሶሻሊስት አገሮች በዓለም ኢኮኖሚ ውስጥ ከፍተኛ ሚና በመጫወት ላይ ናቸው። ዓለም አቀፍ ሶሻሊዝም ከምንጊዜም በበለጠ ሁኔታ በመጠናከሩ ሶቪዬት ሕብረት የኮምዩኒዝምን ቁሳዊና ቴክኒካዊ መሠረት በመጣል ላይ ስትሆን ሌሎች ብዙ ሶሻሊስት አገሮች ደግሞ በሁሉም መልክ የዳበረ ሶሻሊስት ኅብረተሰብን የመገንባት ሥራ ተያይዘውታል። ሶሻሊስት አገሮች በተለይም ደግሞ ሶቪዬት ሕብረት የደረሱበት ወታደራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ኢምፔሪያሊስቶች የጠብ አጫሪነታቸውን እንዳይገፉበት የሚገታ ኃይል ሆኗል። ሶሻሊስት አገሮች በመካከላቸው ያለው መረዳዳትና ሕብረት ይበልጥ ወዳጅነታቸውን ማጠናከሩ ሌላው ለኃይል ሚዛናቸው ክብደት የሚሰጥ ነገር ነው።

የኃይል ሚዛን ይበልጥ በመለወጡ የተነሣ በኢምፔሪያሊዝምና በሶሻሊዝም መካከል የጦርነትን ሥጋት ለመቀነስ ቢቻል በሶሻሊስት አገሮች የቀረበውን የዴታንት ፖሊሲና በሰላም አብሮ የመኖር መርህን ተግባራዊ ለማድረግ ኢምፔሪያሊስቶች ምንም እንኳ የጠብ አጫሪ ባሕርያቸው ሊያቅበጠብጣቸው ቢሆንም ቀስ በቀስ ለመቀበል እያዘነበሉ ነው። የጦር መሣሪያ ቅነሳም ጉዳይ እንዲሁ ድርድሩ እየቀጠለ ነው።

በካፒታሊስትና በሶሻሊስት አገሮች መካከል በንግዱ፣ በኢኮኖሚክስ፣ በሳይንስና በቴክኖሎጂ፣ በባሕልና በሌሎችም መስኮች ሁሉ ትብብሩ በአስተማማኝ ሁኔታ እያደገ ነው። በየትኛውም አቅጣጫ የሶሻሊስቱ አገሮች፣ ኮምዩኒስት እና የሠራተኛ ፓርቲዎች፣ የተለያዩ ዲሞክራሲያዊ፣ ፖለቲካዊና ሕዝባዊ ድርጅቶች በዓለም አቀፍ ደረጃ ለሰላም በመታገል ሰላምን እያስከበሩ ናቸው።

ሌላው የካፒታሊዝም አጠቃላይ ቀውስ እየቀጠለ መሆኑን የሚያሳየን ካፒታሊዝም ከ1974–76* ባሉት ጊዜያት የደረሰበት ኢኮኖሚያዊ ቀውስ ነው። የዚህ ቀውስ ዋናው ገጽታ በበለጠ ምርት የተነሣ የሚደርሰው ቀውስ ከነዳጅ ሰጥረት፣ አካባቢ መበከልና ከገንዘብ ቀውስ፣ መንግሥታዊ ሞኖፖሊያት ቀውስን ለመግታት ካለመቻላቸው፣ በከተማ ከደረሰው ቀውስና ታይቶ ተሰምቶ በማይታወቅ መጠን እያደገ ከሄደው የዋጋ ንረት ጋር ተገጣጥሞ መምጣቱ ነው።

ቀውሱ እንዲሁ የመጣ ሣይሆን በመጀመሪያዎቹ ዓመታት የበለጠ ምርት ቁጥሩ ከገበያው ፍላጎት ውጭ በመሆኑ በሚቀጥሉት ዓመታት አቀርቦትን ለመቀነስ በተወሰደው እርምጃ የተፈጠረ ኢኮኖሚያዊ ቀውስ ነው።

ወዛደሩ ሥራ በማጣቱ ምክንያት የተፈጠረውን ቀውስ ብንመለከተው ደግሞ የካፒታሊዝም አጠቃላይ ቀውስ ባሁኑ ወቀት እየቀጠለ የሚሄድ መሆኑን የሚያሳይ ሌላ መረጃ ነው። እ.ኤ.አ. በ1969 በኢምፔሪያሊስት አገሮች 10 ሚሊዮን ሠራተኞች ሥራ አጥ ነበሩ። እ.ኤ.አ. ከ1975–1976 ባሉት የበጋ ወራት የሥራ አጡ ቁጥር ባሻቀበበት ወቀት ለሥራ አጥነት በይፋ የተመዘገቡት ወደ 17 ሚሊዮን ይጠጋ ነበር። በዚህም የቀውሱ እድገት በምን ያህል እንዳደገ መገንዘቡ አዳጋች አይደለም። በአሁኑ ወቀት ማለትም እ.ኤ.አ. 1981 የሥራ አጡ ቁጥር ከ23 ሚሊዮን በላይ መሆኑ የካፒታሊስት አገሮች አጠቃላይ ቀውስ እየተባባሰ መሄዱን መረዳት ይቻላል።

---
*እ.ኤ.አ.

ቀደም ባሉ ሥራ አጥነት በምን ምክንያት እንደሚፈጠር የተነገረ ቢሆንም ባጠቃላይ በሁለት ምክንያቶች እንደሚመጣ መጠቆሙ አስፈላጊ ይሆናል። እነዚህም፣

1/ በኢምፔሪያሊስት አገሮቹ ውስጥ በኢንዱስትሪ አካባቢ የሚካሄዱ ሥራ በዝባ መልክና ትርፍ ለማግኘት ቢባል በውድድር ላይ በለሚመሠረት፣ አዲስ የሚሠሩት ማሽኖቹም ከፊልና ሙሉ አውቶማቲክ በለሚሆኑ፣ የሠራተኛውን ቦታ በብዛት በመተካት ያገለግላሉ። በለሆነም፣ አዲስ ማሽኖች በመሠራታቸው በሠራተኛው ላይ የሚያደርሱት ችግር ቀደም ብሉ በማዕከላዊነት በለማይታሰብበት ባልተጠበቀ ጊዜ ሠራተኛውን ከምርት ሥራ ውጭ ያደርጉታል።

2/ ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ ባለው የረጅም ጊዜ የኢንዱስትሪ መስፋፋት በኢንዱስትሪው አካባቢ ተጠባባቂ ሠራተኛ እንደገና እንዲኖር ለማድረግ ቢል ካፒታል ብዙ ባለትዳር ቢቶችን፣ ወጣቶችንና ወይም ተሳሳፊሠራተኞችን ኋላ ቀር ከሆኑ አገሮች ቀደም ቀጥሮ ያሠራቸው በነበሩት ሠራተኞች ላይ በተደራቢ እያመጣ በየሰበቡ ነባሮችን እያባረረ ይተካል። ይህ ደግሞ እስከሁንምእየተባባሰየሄደ ችግር ነው። በሥራ በተሰማሩት ወይም ሥራት ብቃቱ ባላቸው የምንዳዕ ቀጥረኞች ላይ እነዚህ ኋላ የመጡት ክፍሎች ባጠቃላይ ዝቅተኛ ክፍያ የሚከፈላቸው፣ የሥራ ልምዱን በማይጠይቀ ወይም ጤናማ ባልሆነ ሥራ ላይ የሚሰማሩ ቢሆኑ፣ የሚቀጠሩትም በገዜያዊነት ነው። በለዚህ እንደ ነገር/ቀውስ/ በተፈጠረ ጊዜ በቀላሉ ለማባረር አመቺ ናቸው። ባጠቃላይ ይህ ነገር ማኅበራዊ ችግርን እያባባሰው በመሄድ ላይ ይገኛል።

በተለይ እ.ኤ.አ. ከ1970 አካባቢ ጀምሮ የተፈጠረው የነዳጅና የጥሬ ዕቃዎች እጥረት ቀውስ በካፒታሊስቱ ኢኮኖሚ ውስጥ ከፍተኛ ችግር ፈጥሮ እንደነበር የታወቀ ነው። የነዚህም ነገሮች የጋ ማየል በካፒታሊስት አገሮች ውስጥ የተፈጠረውን ቀራኒ ይበልጥ እያባባሰው ሄደ።

ለሳው ካፒታሊስት አገሮችን እ.ኤ.አ. በ1970ዎቹ አካባቢ የገጠማቸው ችግርና እንደተፈለገ የተፈጥሮ ሀብትን መዝረፍና መውሰድ በማይችሉበት ደረጃ ያስጨጣቸው

የአካባቢ ሁኔታ በኢንዱስትሪና በሌሎችም ከሚካል መበረዝ ነው። ይህም ከራሱ ከካፒታሊዝም ጥንቃቄ የለሽ የምርት ሂደት የሚመጣ በመሆኑ ሊወጣው የሚችል አይደለም። የአካባቢ ውቅያኖሶች በፋብሪካ ቆሻሻ መበከል ከውቅያኖስ የሚገኙ የተለያዩ ጥሬ ሀብቶችን አሳጣ። ይህም በቴክኖሎጂ መዳበር የተነሣ ሳይሆን በቡርዧው ማኅበራዊ አወቃቀር የሚመጣ ነው። ለአካባቢው መበከል ዋና ምክንያት ለትርፍ ማጋበስ ብቻ የቆመ ሥርዓት ማኅበር መኖር ነው። እንደነዚህ ያሉት ክስተቶች በየጊዜው የየወሰ ገጽታ እየበዛ የሚሄዱ መሆኑን ያሳያሉ።

በሌላ በኩል ሶ.ኅ.ሶ. በ1970ዎቹ ዓመታት ከፍተኛ የማኅበራዊ ችግር ተፈጥሯል። በሰሆነም ማኅበራዊ ችግሩ በወንጀለኞች መብዛት፣ በከፍተኛ የሞራል ውድቀት፣ በሥልጣን መባለግና በመባበሱት ታይቷል።

የመንግሥታዊ ሞኖፖሊ ካፒታሊዝም ሰላው ባሕርይ በሁለተኛው ቀውስ ደረጃ ጀምሮት የነበረውን ጠረኛነት፣ በከፍተኛ ደረጃ እያባደገ መምጣቱ ነው።

አሜሪካ ባሁኑ ወቅት ሶ.ኅ.ሶ. 1982 ካሳት ከ2 ሚሊዮን የጦር ኃይል ወስጥ በአውሮፓ 331.700፣ በፓሲፊክ ውቅያኖስና በሩቅ ምሥራቅ 124,080፣ በላቲን አሜሪካ 14,900፣ በሌሎች አገሮች 31,600 ወታደሮች ለጦርነት ዝግጁ አድርጋ አስቀምጣለች። ለዚህም ኃይል የመደበችው በጀት በዚሁ ዓመት 250 ቢሊዮን ዶላር የሚደርስ ነው። በአጠቃላይ አሜሪካና ሌሎችም የኔቶ ቃል ኪዳን አገሮች ለጦር ኃይል የሚመድቡት ወጪ ከዓመት ወደ ዓመት በከፍተኛ ደረጃ እየናረ መጥቷል።

ለጦር መሣሪያና ለጦር ኃይል የሚወጣውን ገንዘብ ለተለያዩ የልማት ሥራዎች እንዲውል ቢደረግ ምን ያህል ጥቅም እንደሚሰጥ ለማየት ለመጀመሪያው 30 ዓመት ለኔቶ የወጣውን በግምት 2,625 ቢሊዮን ዶላር እንመልከት። የ30 ቢሊዮን

ቶን ዘይት የጋ /ባሁኑ ወቅት/ ያህል፣ ወይም የላቲን አሜሪካ አገሮችን ጠቅላላ የዓመት ብሔራዊ ገቢ በሙሉ፣ ወይም የአፍሪካን አገሮች ጠቅላላ የዓመት ብሔራዊ ገቢ 13 ጊዜ፣ ወይም በታዳጊ አገሮች ውስጥ ባሉ ሥራ አጦች በሙሉ ቢከፋፈል ለእያንዳንዳቸው 150,000 ዶላር ሲደርስ፣ አሜሪካ ጤናን ለመንከባከብ በዓመት የምታወጣውን 45 ጊዜ ወይም ለትምህርት በዓመት የምታወጣውን 180 ጊዜ ይሆናል። በዚህ ዓይነት ብዙ ምሳሌ ማቅረብ ይቻላል።

እነዚህ የጦር መሣሪያ ክምችትና የጠብ አጫሪነት ፖሊሲዎች በሚፈጥሩት ሁኔታ የተነሣ ከ1945 ወዲህ በግምት 150 ያህል ጦርነቶች ሲካሄዱ ከ10 ሚሊዮን በላይ ሰዎች ሞተዋል፣ በእነዚህ ጦርነቶች በግምት 7,500 ሚሊዮን ዶላር ወጥቷል።

ካፒታሊዝም ወዴት ያመራል?

ሌኒን በኢምፔሪያሊዝም የሰጠው የንድፈ ሃሣብ ትንተና ቀደም ሲል ማርክስ በለካፒታሊስት ክምችት ታሪካዊ አቀጣጫና ካፒታሊዝም በአብዮታዊ ሂደት መገርሰሱ የማይቀር መሆኑን በማበገንዘብ ካቀረበው ንድፈ ሃሣብ ላይ በመነሳት የቀረበ ነው።

ታላቁ የጥቅምት ሶሺሊስት አብዮትና የሌሎች አገሮች ሶሺሊስት አብዮቶች፣ ዓለም አቀፍ የሶሺሊስት ሥርዓት መመሥረት፣ በመላው ዓለም የብሔራዊ አርነትና የሠራተኛው መደብ እንቅስቃሴ ማደግ በማርክስና በሌኒን የተተነተኑትን የማርክሲዝም ሌኒኒዝም ትምህርቶች እውነትነት የሚያረጋግጡ ናቸው።

ባሁኑ ወቅት የዓለም አብዮታዊ ሂደት አካል የሆኑት ሦስቱ ኃይሎች ማለትም ሶሻሊስት አገሮች፣ በበለጸጉ ካፒታሊስት አገሮች ውስጥ የሚታገለው ሠራተኛው መደብና በማደግ ላይ ያሉ አገሮች የሚያካሂዱት ብሔራዊ የአርነት ትግል መኖር የኢምፔሪያሊዝም ጠላቶች በዓይነትና በስፋት እየጨመሩ መሄዳቸውን ያሳያሉ።

ዓለም አቀፍ የሶሻሊስት ሥርዓት መመሥረት ባንዱ በኩል ለመላው ሠርቶአደር ሕዝብ ከፍተኛ ድል ቢሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ የሶሻሊስት አገሮች አንድነታቸውንና ኅብረታቸውን እያጠናከሩ ለነፃነታቸው ለሚታገሉ ሕዝቦች ሁሉ አለኝታ ከመሆናቸው ባሻገር የሰላም አቀንቃኞች በመሆን የዲሞክራሲና የሶሻሊዝም ትግል ይበልጥ እየተጠናከረ፣ የኢምፔሪያሊዝም የጠብ አጫሪነት ፖሊሲን የተጸለና ክልል ውስን እየሆነ እንዲሄድ ይረዳል። ለዚህም ነው ባሁኑ ወቅት የተለያዩ ሥርዓተ ማኅበር ባላቸው አገሮች መካከል በሰላም አብሮ የመኖር ሌኒኒስታዊ መርህ ተግባራዊ እየሆነ ለመሄድ የቻለው።

የሶሻሊስት ሥርዓት በፈጣን ምጥቀት እያገኘ በመሄዱ በየትም አገር ያሉ፣ በተለይ በካፒታሊስት አገሮች ውስጥ የሚገኙ ወዝአደሮች በለኑሮአቸው መሻሻል፣ የተሻለ ደመወዝ ስለማግኘት፣ ስለነፃ የፖለቲካ ድርጅት መፈቀዱ ጥያቄ፣ ወዘተ... ከፍተኛ ትግል እንዲያካሂዱ ረድቷቸዋል። ይህም ዕለት ከዕለት የወዛደሩን ኃይል፣ ድርጅታዊ ጥንካሬና የፖለቲካ ብስለት እየጨመረለት በመሆኑ መላው ሠራተኛ መደብ ሞኖፖልን በከፍተኛ ደረጃ እንዲቃወም አብቅቶታል።

በዚህ ሁኔታ ካፒታሊዝም መውደቂያው እየተቃረበ ቦታውን ለሶሻሊዝም እየተወ መሄዱ የማይቀር መሆኑ በገሀድ እየታየ ነው። በካፒታሊዝም ሥር ያለው ወዛደር በሶሻሊስቱ ካምፕ ውስጥ የሚገኘውን ሠራተኛ መደብ ኑሮ በመመልከትና ከእርሱም ትምህርት በማግኘት ይህን የሶሻሊስት ሥርዓት ለመገንባት ወይም ለመመሥረት የሚያደርገውን ትግል ይበልጥ እያፋፋመው በመሆኑ ካፒታሊዝም ከዚህ በፊት ሲያታልልና ጭቁን ሕዝቦችን ሊመዘብር በሚችልበት ደረጃ አይደለም። በለሆነም የዘመኑ ካፒታሊዝም ታሪካዊ አቅጣጫ ለሶሻሊዝም ቦታ ሊለቀቅ ሕልውናውን ማጣት እንጂ በዘላለማዊነት ሊኖር የሚችል ኃይል መሆኑ አክትሟል። በለሆነም ጊዜው የሶሻሊዝም ነው። ዓለምም የወዛደሮች ትሆናለች።

# ጥ ያ ቄ ዎ ች

1. የኢምፔሪያሊዝምን ታሪካዊ አመጣጥ ዝርዝር አድርገህ ግለጽ።
2. የኢምፔሪያሊዝም ባሕርያት ምን ምን ናቸው?
3. አንድ አገር ኢምፔሪያሊስት የሚባለው ምን ምን ምልክቶችን ሲያሳይ ወይም ምን ምን ድርጊቶችን ሲፈጽም ነው? በምሳሌ አብራራ።
4. የኢምፔሪያሊዝም ብዝበዛ በኢትዮጵያ እንዴት ነበር? ምን ምን ገጽታዎች ወይም መልኮች ነበሩት? ዋና ዋናዎቹን ጥቀሳቸው።
5. በኢትዮጵያ የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም እንዴት ነበር ስር የሰደደው? ዝርዝር አድርገህ ግለጽ።
6. ኢትዮጵያን ለመቀራመት አሰፍስፈው የነበሩት ኢምፔሪያሊስት አገሮች የትኞቹ ነበሩ? ሴራቸውስ እንዴት ሊከሽፍ ቻለ? አብራራ።
7. ኢምፔሪያሊዝም የሸገተ ካፒታሊዝም መሆኑን ዝርዝር አድርገህ ግለጽ።
8. ኢምፔሪያሊዝም ሊሞት የተቃረበ ካፒታሊዝም ነው ሲባል ምን ማለት እንደሆነ ዋና ዋናዎቹን ምክንያቶች ዝርዝር።
9. በዘመነ ኢምፔሪያሊዝም የወዝአደሩን አብዮት በማስመልከት ሌኒን የቀየሰው ንድፈ ሃሳብ ምንድነው? አብራራ።
10. ኢምፔሪያሊዝም የሶሻሊስት አብዮት ዋዜማ ነው ሲባል ምን ማለት ነው? ዝርዝር አድርገህ ግለጽ።
11. ኢምፔሪያሊዝም በኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮት ላይ ምን ደባ ሠርቷል፣ እየሠራስ ነው? አብራራ።
12. ኢምፔሪያሊዝም የዓለምን ሰላም አስጊ ሁኔታ ላይ የሚጥለው ለምንድነው? ከወቅቱ ሁኔታ ጋር በማገናዘብ አብራራ።
13. ዋና ዋናዎቹን የኢምፔሪያሊዝም ቀውሶች መከሰቻዎች አመልክት፣ በተጨባጭ ምሳሌ አብራራ።

14. የኢምፔሪያሊዝምን ሦስቱን የአጠቃላይ ቀውስ ደረጃዎች ዘርዘር በማድረግ አስረዳ።

15. ከ1970ዎቹ ወዲህ አጠቃላይ ቀውሱ የዓይነት ለውጥ ያሳየባቸውን መስኮች አመልክተህ አብራራ።

16. ሶሺያሊዝም የበላይነቱን ያሳየባቸውን መስኮች ዘርዘር አድርገህ አብራራ።

17. የካፒታሊዝም የኢኮኖሚ ቀውሶች ዐበይት ምክንያቶች ምን ምን እንደሆኑ በተጨባጭ ምሳሌ ጭምር አብራራ።

18. ኢምፔሪያሊዝም ከታዳጊ አገሮች የሚያጋብሰው የትርፍ ምንጭና መጠን እንዴትና እስከምን ድረስ እንደሆነ ዘርዘር አድርገህ ግለጽ።

19. በቅድመ አብዮት ኢትዮጵያ የኢምፔሪያሊዝም ብዝበዛ እንዴት ነበር? ዘርዘር አድርገህ በተጨባጭ ምሳሌ አስረዳ።

20. ዛሬ አፍሪካ ውስጥ በኢምፔሪያሊዝም የእጅ አዙር ቅኝ ግዛት ሥር ያሉትንና ከዚህ በመላቀቅ የሶሺያሊስት የዕድገት ፈለግ በመከተል ላይ ያሉትን አገሮች ለይተህ ካስቀመጥህ በኋላ ዓይነተኛውንና የሚለያቸውን ባሕርይ ወይም ሁኔታ አመልክት።


## ቃ ላ ት

| | | |
|---|---|---|
| 1. | ሞኖፖል — ሞኖፖሊ | *Monopoly* |
| 2. | ኢምፔሪያሊዝም | *Imperialism* |
| 3. | የፊናንስ ካፒታል | *Finance Capital* |
| 4. | የባንክ ካፒታል | *Banking Capital* |
| 5. | ደም መጣጭ | *Parasitic* |
| 6. | የሻገተ | *Decaying* |
| 7. | ጦረኛነት | *Militarism* |
| 8. | የወዝአደር መሣፍንት | *Labour Aristocrat* |
| 9. | ሟች — ወደ ሞት የተቃረበ | *Moribund* |
| 10. | ያልተመጣጠነ ዕድገት | *Uneven development* |
| 11. | የላላ ቀለበት | *The Weakest Link* |
| 12. | የጦር አጫሪነት | *Aggressiveness* |
| 13. | መንግሥታዊ ሞኖፖሊ ካፒታሊዝም | *State Monopoly Capitalism* |
| 14. | የኃይል ሚዛን | *Balance of Forces* |
| 15. | በሰላም አብሮ መኖር | *Peaceful Co-existence* |
| 16. | ዴታንት | *Detente* |
| 17. | ውጥረት | *Tension* |

## የሚነበቡ መጻሕፍት*


1. Karl Marx - Capital Vol. I /በቅርብ ጊዜ በአማርኛ የሚወጣ/
2. " " Contribution to the Critique of Political Economy
3. " " Wages, Price and Profit /የአማርኛ ትርጉም አለው/
4. F. Engels - Anti Duhring
5. V.I. Lenin - Imperialism, the Highest and Last Stage of Capitalism /የአማርኛ ትርጉም አለው/
6. G.A. Koslov - Political Economy - Capitalism
7. P. Nikitin - Fundamentals of Political Economy /የአማርኛ ትርጉም አለው/
8. L. Leontyev - Political Economy - A Beginner's Course
9. L. Leontyev - Political Economy - A Condensed Course
10. M.N. Ryndina - Fundamentals of Political Economy
11. ካርል ማርክስ — የመጀመሪያ ደረጃ የካፒታል ክምችት



*እነዚህ ከዚህ በላይ የተመለከቱት መጻሕፍት በዚህ ጥራዝ ለቀረበው የካፒታሊስት ስልተምርት ትምህርት ስፋትና ጥልቀት ያለው ዕውቀት ይሰጣሉ ተብለው የቀረቡ እንጂ ሁሉም ሰው በግዴታ እንዲያነባቸው የታቀዱ አለመሆኑ እንዲታወቅ ያስፈልጋል።




ዛሬ ሥራ፣ ነገ ሥራአጥ በወዛደሩና በቤተሰቡ ኑሮ ውስጥ የሰቀቀንና የሀዘን ስሜትን ይፈጥራል



ሁለት መልክ ፣ ሁለት ገፅታ ። ጧት ለወዛደሩ ፣ ማታ ለቡርዧው ። ለዘብተኝነት የወዛደር መሳፍንትንት ፣ አድርባይነት ፣ ወዘተ ………



የኢምፔሪያሊዝም አስከፊ ገፅታ በላቲን አሜሪካ ውስጥ



ሞኖፖሊዎችና የሥልጣን ወኪሎቻቸው የመጨረሻ እጣ

ካፒታሊዝም ይወድማል ሶሻሊዝም ይለመልማል ፣

proudly brought to you by
www.binyamhk.wordpress.com



ማርክሲዝም ሌኒኒዝም መጠናት ያለበት ሳይንስ ነው ፡


proudly brought to you by

www.binyamhk.wordpress.com